YAHOO! MAIL Classic

[FETEHE MUSLIM YOUTH] 1ለ5 ለሁሉም በሁሉም Sunday, March 25, 2012 2:00 PM

From: "Zulkerneyn Zul" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

To: "FETEHE MUSLIM YOUTH" <277933545612995@groups.facebook.com>

Zulkerneyn Zul posted in FETEHE MUSLIM YOUTH.




Zulkerneyn Zul 9:00pm Mar 25


1ለ5 ለሁሉም በሁሉም

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡
አሰላሙ አለይኩም ወረህመቱላሂ ወበረካቱ ያ አህለል ሙዕሚኒን፡፡

መንግሰት ድህነትን ኋላቀርነትና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለማባረር 1 ለ 5 መደራጀት የሚባል መርሃ ግብር ቀርጸ ለተግባራዊነቱ እየተንቀሳቀሰ ነው ፡፡ እኛም አህባሽን ከመጅሊሳችን፣ ከመሰጊዳችን ፣ብሎም ካገራችን ለማባረር የአህባሽን ስንኩልና ከዲን የወጣ የግል አስተሳሰብ እንዲሁም በማህበራዊ፣አኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፉ እጅግ የዘቀጠና ለተለያዩ ግጭቶችና ጣኦት አምልኮን የሚፈቅድ ከሌሎች የእምነት ተከታዮች ጋር የሚያጋጭ ባጠቃላይ በትክክል ላየው ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር የማያስፈልግ ተራና ውዳቂ አስተሳሰብ መሆኑን ተጨባጭ መረጃ በማቀረብ 1 ሰው ለ 5 ሰወች ማስተማርና ማብቃት አለብን በተለይ ኢንፎረሜሽን የማይደርሳቸውን ለምሳሌ በእድሜ ትልልቅ ሰወች በ አህባሽ አስተሳሰብ እንዳይሰረቁ ማድረግ አለብን እላለሁ፡፡ 1ለ5 ዛረውኑ እንጀምር ዛረውኑ እንጀምር ዛረውኑ እንጀምር ዛረውኑ እንጀምር !!!!



View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.



137



ከሳሚ ኢሳመል ኢሰመጣ ሸፋቻለሁ
SAMI 25/12/04

2. ሳለ ኢሳመል የተገኘ መረጃ ወሳኝ ነው

25/12/04

FOLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

[YeMuslimoch Dimts የሙስሊሞች ድምጽ] መንግስት እውነት ሙስሊሙ እምነቱ ላይ እንዲጠናከር አስቦ ነው አሕባሽ ያስመጣው...

Tuesday, July 3, 2012 5:18 AM

From: "Ibn Nuru" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
To: "YeMuslimoch Dimts የሙስሊሞች ድምጽ" <458458377517344@groups.facebook.com>

Ibn Nuru posted in YeMuslimoch Dimts የሙስሊሞች ድምጽ

Ibn Nuru 12:17pm Jul 3

መንግስት እውነት ሙስሊሙ እምነቱ ላይ እንዲጠናከር አስቦ ነው አሕባሽ ያስመጣው ብለን የምናስብ ከሆነ ተሳስተናል ከመች ጀምሮ ነው ራሱን ሴኩላሪዝም ነኝ የሚል መንግስት ብዙ እምነቶች ባሉበት ሐገር አንዱን እምነት ተከታይ ለማጠናከር በጀት መድቦ የሚንቀሳቀሰው? ምንስ ታይቶት ነው ሀይማኖታዊ ሰባኪዎችን ከሌላ ሀገር የሚያስመጣው? ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የሱፍይም ሆነ ሌላ ዐሊሞች ለኛ አይደለም ለአለም የሚተርፉ ናችw ሐጅ መሐመድ ሳኒን የመሳሰሉ ዐሊሞች ያሉኖብትና አሁንም ታላላቅ አሊሞች ያሉበት ሐገር ከውጭ የመጣ አስተማሪ አያስፈልገውም የመጡት አስተማሪዎች ሐቅን ይዘው ከመጡ መደበቃቸው ለምን አስፈለገ? ለምን በመሳሪያ እተጠበቁ yንቀሳቀሱሉ ? ሐቅን ይዘው ከመጡ መስጂድ ገብተው ለምን አያስተምሩም? እነዚሕ ሠዎች ከላይ የጠቀስኩአቸውን አንዱንም አያደርጉም ምክንያቱም ውሸትን ይዘው ስለመጡ ይፈራሉ ሐቅን ስለማያውቁት ይጨነቃሉ በጣም የሚገርመው ከአመታት በፊት ከፓኪስታን የሚመጡ ዑለሞች ነበሩ እነዚሕ ሠዎች መንደርና ገጠር ውስጥ እየገቡ ዳዕዋ ሲያደርጉ በመሳሪያ አይደለም ዱላ በያዘ ፖሊስ አልተጠበቁም ምክንያቱም ሐቅን ነበር የሚሠብኩት እውነተኛውን ኢስላም ነበር የሚያስተምሩት ሐቅን የያዘ አይፈራም ! አይደበቅም! በመሳሪያ አይጠበቅም ! መንግስት እንደ መንግስትነቱ ሀገራዊ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል ሀይማኖታዊ መመሪያ ሊያወጣልን ግን አይችልም ለሐገራዊ እድገት የመረጠውን አካሔድ ሊሔድ ይችላል ሐይማኖት ግን ሊመርጥልን አይችልም ብልጥ እንሁን አሕባሽ ኢሲላምን ለማጥፋት የመጣ አንጃ ነው

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

1 of 1

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

[FEZEKIR CENTER] ትላንት ጋዳፊ በህዝቦቹ ላይ የሚሰራውን አኬልዳማ ዛሬ የኛ መሪዎችም... Monday, July 16, 2012 9:44 AM

From: "Abu Nurjenna Shemse" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

To: "FEZEKIR CENTER" <fezekircenter@groups.facebook.com>

Abu Nurjenna Shemse posted in FEZEKIR CENTER

Abu Nurjenna Shemse 4:44pm Jul 16

ትላንት ጋዳፊ በህዝቦቹ ላይ የሚሰራውን አኬልዳማ ዛሬ የኛ መሪዎችም በኮሚቴዎቻችንና በሙስሊሙ ላይ ሊሰሩ እየተዘጋጁ ነው ነገሩ እንዲህ ነው ሙአመር ጋዳፊ እሱን የሚቃወሙትን እንዲ ነበር የሚያደርጋቸው ህዝብ በተሰበሰበበት የተቃወመውን አካል ያቀርባል ከዚያም እንዲገደል ያደርጋል ከዚያም የሟች ቤተሰቦች በድርጊቱ የደስታመግለጫ በቴሌቭሽን እንዲሰጡ ያስገድዳል ዛሬም የኛ መንግስት እራሱ ደብድቦ እራሱ የሰው ህይወት አጥፍቶየራሱን ጥፋት በኮሚቴዎቻችንን ላይ ሊያላክክ መሆኑን ተደርሶበታል ይህን በተመለከተ በቅርቡ አኬልዳማ 3 በቅርቡ ውሸትን በስፋትና በጥራት በመላ ሀገሪቱ በሚያሰራጨው ኢቲቪ ለማሳየት ዝግጅታቸውን ጨርሰዋል በኢቲቪ ውሸት ስለተነገረ እውነት አይሆንም

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECLN

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፍትህ ሚኒስቴር የመመርመሪያ ዘዴ ጽ/ቤት ቁጥር 3
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution Process 3

ከሳሽ፡ ፖሊስ
ተከሳሽ፡ አህመድ ሽፋ
ጉዳዩ፡ ክስ መስማት
25/12/04

ከሳሽ፡ ፖሊስ
ተከሳሽ፡ አህመድ ሽፋ
ጉዳዩ፡ ክስ መስማት
ቀጠሮ፡ ለ25/12/04 ቀን
ከጠዋቱ 3 ሰዓት

25/12/04

35

http://ethcriminalawnetwork.com/

ተዋህዶና ጴንጤ ግን አንዳቸው ስለአንዳቸው ምንም ትንፍሽ አላሉም

8-ጅማ ላይ ስለተከሰተው የቤተክርስቲያን መቃጠል በሰፊው ሲወሳ በጉራጌ ዞን ስለተቃጠሉ 9 መስጂዶች ግን አንድም አልተወሳም

9- ኒቃብ ለውጭ ሙስሊሞች የሃብት መገለጫ ተደርጎ ሲቀርብ ለሃገራችን ሙስሊሞች ግን የአክራሪነት መገለጫ ተደርጎ ቀርቧል መጅሊስን እወክላለሁ ባለ ግለሰብ (እጅግ በጣም የሚያሳፍር አገላለጽና ከማን ጋር ምን ማውራት እንኳ እንዳለበት በማያውቅ ሰው ሙስሊሙ እስልምናን የዘረጠጠበት)

10-ሙስሊሞች በብዛት በሌሉበት አካባቢ መስጊድ መስራት አክራሪነትን የሚጠቁም ፍንጭ እንደሆነ በዲያቆኖች ሲዘመር በተመሳሳይ ሁኔታ ቤተክርስቲያን ስለመስራት ግን ምንም አልተባለም

እነዚህና ሌሎች ነጥቦች ሁሉ ዙርያ ጥምጥም በመሄድና በቀጥታ ሙስሊሙን አክራሪና አሸባሪ ለማስመሰል ከዚህ ቀደምም ለሃገር ደህንነት ስጋት እንደነበርና አሁንም ይህ ስጋት ብቅ ብቅ እያለ ስለመሆኑ ለማሳየት ETV በሰራው ፕሮግራም ውስጥ የተንጸባረቁ ናቸው:: ይህ ፕሮግራም የቅጥፈትና የደባ ሙስሊሙን ያለወንጀሉ የሚከስ እንጂ መቻቻልና በሰላም ተከባብሮ መኖርን የሚሰብክ አይደለም! ::

ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያውን ሙስሊሞች ተችለው ሳይሆን የደረሰባቸውን ግፍና መከራን ችለው ኖረዋል: ይህንን እየተገፉና እየተጨቆኑ የመኖርን ታሪክ እንድንደግምላቸው ፈልገው ከሆነ በድሮ በሬ አይታረስም ታሪክና ዘመን ዳግም ላይመለሱ ሄደዋል ሙስሊሞችም የሚፈለግባቸውን ያህል ባይሆንም ተለውጠዋል በመሆኑም ህገመንግስቱ የሰጠንን መብት ያለመሸራረፍ በጋራ እንጠቀምበት የሚል ይሆናል መልሳችን! ውሸት በመናገር እውነትን መደበቅ ፈጽሞ አይቻልም!!!!!

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

FDRE

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

[Comparative Religion(የሃይማኖት ንጽጽር)] ውሸት በመናገር እውነትን መደበቅ ፈጽሞ አይቻልም!!!!! Tuesday, July 3, 2012 5:32 AM

From: "Abdurehman Nasser" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

To: "Comparative Religion(የሃይማኖት ንጽጽር)" <comparativereligion1432@groups.facebook.com>

5911

Abdurehman Nasser posted in Comparative Religion(የሃይማኖት ንጽጽር)

Abdurehman Nasser 12:31pm Jul 3

ውሸት በመናገር እውነትን መደበቅ ፈጽሞ አይቻልም!!!!!

****

ትላንት ምሽት በETV የቀረበው ፕሮግራም መቻቻል ለማምጣትና የነበረውን ጥሩ ባህል ጠብቆ ለማቆየት ሳይሆን ሙስሊሙን አሸባሪ እና አክራሪ አስመስሎ ለማቅረብ ሙስሊሙን ለማኮሰስ የተሰራ ፕሮግራም ነው: ከድሮው ከአጼዎቹ ስርዓት ጀምሮ ያለውን የክርስቲያኑ ድርጊት የፖለቲካ የሙስሊሙ ግን ሃይማኖታዊና ከማክረር ጋር አያይዘው አቅርበውታል: በፕሮግራሙ ላይ ጎልተው እንዲወጡ የተፈለጉት የሚቀጥሉት ነጥቦች ናቸው:-

1-ከአህመድ ግራኝ ጀምሮ የነበሩ ሙስሊሞች ክርስቲያኑን ሆን ብለው ለማጥቃት እንደተነሱ ማሳየት

2- በሙስሊምና በክርስቲያን መሪዎች መሃል ስለነበረው የጦርነት ታሪክ ሲነሳ ሙስሊሙ ቤተክርስቲያንና ገዳማትን እንዳቃጠለ ሲነገር ክርስቲያኑ ስላቃጠላቸው መስጊዶችና የእምነት መጽሃፍቶች አልተነገረም: ይህም የሆነው ሙስሊም ለሃገር የስጋት ምንጭ እንደሆነ ለማሳየት ነው

3- አራት ኪሎ ላይ የአንገት መሃተብ ክር መበጠሱንና የቤተክርስቲያን የግድግዳ ስእል መቃጠሉ ሲነገር በየዩንቨርስቲው የሙስሊሞች መመሪያ የሆነው ቁርዓን ተቀዳዶ የሽንት ቤት መጥረጊያ ስለመደረጉ ግን የተወራ ነገር የለም

4-አንድ ሰው ከእስልምና ወደ ክርስትና ሲገባ እንደሚገደል ሲገለጽ (ፍጹም ውሸት ሆኖ ሳለ) በፕሮቴስታንት ሚሽነሪዎች በተወረሩ አካባቢዎች የሚኖሩ ሙስሊሞች እየሱስን ተቀበል አለያም አካባቢውን ለቀህ ውጣ እየተባለ መከራውን ስለሚያየው ሙስሊም ግን ምንም ትንፍሽ አላሉም

5-የፕሮግራሙ ተራኪ ስለ አሸባሪነትና ስለ አክራሪነት ባወራ ቁጥር የሙስሊሞች ምስል በተደጋጋሚ ሲታይ የክርስቲያኑ ግን አንድም አልታየም በመቻቻልና በፍቅር ምሳሌ ካልሆነ በቀር

6-ሙስሊሞች በማስረጃ ለክርስቲያኑ ወገን ጥሪ ለማድረግ የጻፏቸው መጽሃፍትና የሰሩዋቸው ሲዲዎች በጉልህ በተደጋጋሚ በአሉታዊ ገጽታ እንዲታዩ ሲደረግ ማህበረ ቅዱሳንም ሆነ ሌሎች በሃሰት አስልምናን ለማጠልሸት የጻፏቸው መጻህፍትና የሰሩዋቸው ሲዲዎች ግን አልታዩም

7- ሙስሊሙ እርስ በራሱ እንደሚገዳደልና እንደሚተቻች በሙስሊሙ በራሱ አንደበት እንዲነገር ሲደረግ ጎራ ለይተው በተለያየ ቤተክርስቲያን ውስጥ ቁጭ ብለው ስለሚናጩትና ስለሚፋጁት

26

1 of 2

8/21/2012 12:5

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

[LIVE FOR TRUTH] ቅጥፈትን ስራየ ብሎ የተያያዘው ኢቲቪ በትላንተናው የዜና እወጃው ምናልባትም... Tuesday, July 17, 2012 12:38 AM

From: "Marie Maru" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>

To: "LIVE FOR TRUTH" <livefortruth@groups.facebook.com>

Marie Maru posted in LIVE FOR TRUTH

7:37am Jul 17

Marie Maru

ቅጥፈትን ስራየ ብሎ የተያያዘው ኢቲቪ በትላንተናው የዜና እወጃው ምናልባትም ዛሬ ይደግመው ይሆናል የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አስተያየት አስመስሎ ያቀረበውና ሙስሊሙን ሲወነጅሉ የነበሩት ግለሰቦች እንዳለው የአዲስ አበባ ኗሪዎች ሳይሆኑ ኮምቦልቻን የሚያምሱ አህባሾች ናቸው፡፡ አረንጓዴ ጠምጥሞ ቀልጠፍ ያለ አስተያየት ሲሰጥ የነበረው ሼህ ዑመር የተባለውና በአማራ ክልል ቁጥር አንዱ አህባሽ ሲሆን ወጣቶቹ ደግሞ የርሱ ተከታዮች ናቸው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ በዚህ መደናበር የለበትም፡፡

ሌላው ልብ ሊባል የሚገባው መሰረታዊ ጉዳይ ሙስሊሙን አክራሪ፣ አሸባሪ ወዘተ እያሉ የሚከፋፍሉት ለማጥቃት ይመቻቸው ዘንድ እንጂ ይህ ጉዳይ በትክክል አሳስቧቸው እንዳልሆነ ማስተዋል አለብን፡፡ አያት ቅድመ አያቶቻችን አንገታቸው የተቀነጠሰው፣ እጆቻቸው ተቆርጦ በገደል የተወረወሩትና ሌላም ሌላም ዘግናኝ ድርጊቶች የተፈጸሙባቸው አክራሪና አሸባሪ ስለነበሩ ነው እንዴ? በፍጹም አይደለም፡፡ ሙስሊም ስለሆኑ ብቻና ብቻ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን እየተሰራ ያለው ከዚያ የተለየ አይደለም፡፡ ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ጅግራ እንደሚያደርጓት ሆኖ ነው እንጂ በትክክል የሀገር ስጋት ሆነን አይደለም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሙስሊሙ ሊጠነቀቅ የሚገባው ጉዳይ በየትኛውም የኢስላም ታሪክ ውስጥ በኢስላምና በሙስሊሞች ላይ ከፍተኛውን ጉዳት ያደረሱትና ወደፊትም የሚያደርሱት ሙናፊቆች ናቸው፡፡ ከሙናፊቆች ተንኮል ራሳችንንም ዲናችንንም መጠበቅ ይገባናል፡፡ አሏህ ቀልባችንን ከኒፋቅ ይጠብቅልን! አሚን!!!

Qitfetin sirayr bilo yteyayazaw etv Betinantinaw yezena ewejaw minalibatim zare yidegimaw yihonal ye addis ababa newariwoch aseteyayet asimesilo yaqerebewuna muslimun siwenejilu yeneberut gileseboch endetebalew ye addis ababa newariwoch sayhonu kombolchan yemiyamisu ahbashoch nachew. Xrenguadie temitimo ermija endiwesedibin siwetewut yeneberew sheh umer yetebalewuna be amara kilil qutir and ahbash sihon wetatoch degimo yersu teketayoch nachew. Hizibe muslimu bezih medenaber yelebetim. Lelaw lib libal yemigebaw meseretawi guday muslimun akrari, ashebari eyalu yemikefaflut lematiqat endimechachew enji yih guday betikikil asasbowachew aydelem. Ayat qidme ayatochachin angetachew yeteqenetesew, ejochachew eyeteqorete begedel yetewerewerut lelam zegnagn dirgitoch yetefetsemubachew akrarina ashebari sileneberu naw endie? Befitsum aydelem. Muslim silehonu bichana bicha new. Ahunim bihon eyetesera yalew kezih yeteleye aydelem. Libeluwat yasebuwatin awora jigra endemiyaderguwat hono naw enji betikikil yehager sigat honen ayidelem. Kezih gar teyayizo muslimu liteneqeq yemigebaw guday beyetignawum ye islam tarik wust be islam ina bemuslimoch lay keftegnawun gudat yaderesutina wedefitm yemiyadersut munafiqoch nachew. Kemunafiqoch tenkol rasachininim dinachininim metebeq yigebanal. Allah qelbachinin kenifaq yitebiqilin! Amin!!!

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

[UNITY ISLAMIC GROUP] ማሳሰቢያ! ይነበብ! ይነበብ! ይነበብ! እንደሚታወቀው ሰላማዊ የድምፃችን... Tuesday, July 17, 2012 3:25 AM

From: "Ibn Aby Murejah" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
To: "UNITY ISLAMIC GROUP" <ibnusultan@groups.facebook.com>

Ibn Aby Murejah posted in UNITY ISLAMIC GROUP

Ibn Aby Murejah 10:25am Jul 17

ማሳሰቢያ! ይነበብ! ይነበብ! ይነበብ! እንደሚታወቀው ሰላማዊ የድምፃችን ይሰማና መብታችን ይከበር ጥያቄያችን ከጀመርን አነሆ አንድ አመት ሊደፍን ተቃርቦል:: ምንም አንካ ፍትህን ከማስፈን ይልቅ ሰላማዊ ትግላችንን ለመቀልበስ ብሎም የተለያዩ የውሸት እና የማስፈራሪያ ፕሮፓጋንዳ እየነዙ ሙስሊሙ ተስፋ እንዲቆርጥ ለማድረግ ያልፈነነቀሉት ድንጋይ የለም:: ታዲያ በታላቁ አላህ(s.w) አገዛ ያሰቡት ሳይሳካ ቀርታል:: በዚህ በጀመርነው ትግል ታዲያ በተለይ መረጃዎችን ከማድረስ አንፃር ጉልህ ሚና FACEBOOK የፌስቡክ እንደሆነ እርግጥ ነው:: ማሳሰብ የምንፈልገው ነገር ከረመዳን መቃረብ ጋር ተያይዞ ወደ ዒባዳ ለማተኮር በሚል ሀሳብ እራሳችንን ከፌስቡክ FACEBOOK ለማረቅ ያሰብን እንኖራለን! በመሆኑም በአግባቡ ከተጠቀምንበት ለጀመርነው ሰላማዊ ትግል ቀላል እማይባል ሚና ነበረው:: ይኖረዋልም ኢንሻአላህ:: ለዚህ አላማ ብለን ፌስቡክን FACEBOOK ከተጠቀምን እና ኒያ ካከልንበት እንዲሁም ላልሰሙ ወገኖች ካሰተላለፍነው ይህ በራሱ ዒባዳ እንደሆነ ልንረዳ ይገባል:: ለዚህ ለተነሳንለት አላማ ብለን ከተጠቀምንበት አንገብጋቢ እና አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ወሳኝ ዒባዳ ይሆንልናል ኢንሻአላህ:: ስለዚህ እራሳችንን ከፌስቡክ FACEBOOK ለማራቅ ያሰብን ይህን ከግምት ውስጥ ልናስገባ የገባል ማለት ነው:: ድል ለኢስላምና ለሙስሊሞች ይሁን! አሚን! አላሁ አክበር! አላሁ አክበር! አላሁ አክበር!

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

1166

52

http://ethcriminalawnetwork.com/

መስጂድን በነጃላ ጫማ መርገጥ (እንኳን ጫማቸው እነርሱም ነጃሳ ናቸው) በአጼው ነው በደርግ ይህ የተሰራው? ... አጼውና ደርጉ ይህን ቢሰሩ ላያስገርም ይችላል፡፡ አንዱዉኑ አምባገነንታቸውን አምነው ተቀብለዋል፡፡ ይህ ተልካሻ ተግባር ግን ዲሞክራት ነኝ፣ ለህዝቦች ነጻነትና እኩልነት ታግያለሁ፣ እያለ ቀን ከሌት ከሚያደነቁር አካል ሲሆን ግን ያሳፍራል፡፡ ያ ሁሉ ትግልና መስዋዕትነት ለህዝብ ነጻነትና እኩልነት ሳይሆን ለራስ ጥቅምና ስግብግብነት እንደሆነ ነው የሚገባን፡፡ ከዚህ ሁሉ የመብት ጥሰትና ግድያ በኋላ እንኳ አሸባሪ፣ አመጸኛ፣ ወዘተርፈ የሚሉ ውንጀላዎች ማዥጎድጎድ ምን ይሉታል? ጅራፍ ራሱ ገርፎ አሉ...! ለነገሩ የሰባት ዓመት ጨቅላን በጥይት አረር ካነደደ በኋላ ባንክ ቤት ሊዘርፍ ነበር ያለ አካል አሁን ይህን ቢል አያስገርም ይሆናል፡፡ ሀገሪቱና ይህ ምስኪን ህዝብ ግን በጣም ያሳዝናሉ፡፡ አሏህ መልካሙን ይምረጥልን! አሚን!!!

View Post on Facebook · Edit Email Settings · Reply to this email to add a comment.

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

YAHOO! MAIL Classic

[International Muslim Facebook Group] ዛሬ ከማለዳው 3:30 ገደማ በታላቁ አንዋር መስጂድ የተዘጋጀውን የአንድነትና...

Sunday, July 15, 2012 4:33 PM

From: "Marwolela Mekonnen" <notification+zj4oy94fo446@facebookmail.com>
To: "International Muslim Facebook Group" <369004106472442@groups.facebook.com>

Marwolela Mekonnen posted in International Muslim Facebook Group

Marwolela Mekonnen 11:32pm Jul 15

ዛሬ ከማለዳው 3:30 ገደማ በታላቁ አንዋር መስጂድ የተዘጋጀውን የአንድነትና የሰደቃ ፕሮግራም ለማስኬድ ወደ መስጂዱ በመጓዝ ላይ በነበሩት የኮሚቴ አባላት ግለትም በሰብሳቢው ኡስታዝ አቡበክር አህመድ፣ በዳዒ ካሚል ሸምሱ፣ በአህመዲን ጀበልና በአህመድ ሙስጠፋ ላይ ያልታወቁ የደህንነት ሰዎች ያደረጉት የመጥለፍ ሙከራ ሳይሳካ ቀረ።
በተጠቀሰው ሰዓት ከሀብተጊዩርጊስ ድልድይ በኩል በአሜሪካን ግቢ አድርገው ወደ ታላቁ አንዋር መስጂድ በማምራት ላይ የነበሩት ኮሚቴዎች ከኋላቸው አንድ መኪና በተደጋጋሚ የመኪናውን ጥሩምባ በማስጮህ ስለረበሻቸው መኪናቸውን ዳር በማስያዝ ለማሳለፍ ይሞክራሉ። ይሁን እንጂ መኪናው በማለፍ ፋንታ የነሱን መኪና መንገድ ዘግቶ ይቆማል። ከዚያም ከመኪናው ውስጥ በፍጥነት የወረዱት ግለሰቦች አጸያፊ ስድብን በማስቀደም "እያንዳንድህ እንዳትንቀሳቀስ! ስልክም እንዳትደውል! እደውላለሁ ትልና ግንባርህን ነው የምንልህ! ቀጥ ብለህ ይህን መኪና ተከተል!" የሚል ንቁት የታከለበት ትዕዛዝ ሲያስተላልፉ አህመዲን ጀበል "እናንተ ማናችሁ? መታወቂያችሁን አሳዩን" በማለት ጥያቄ ያቀርብላቸዋል። አሁንም ጸያፍ ስድብ ከተሳደቡ በኋላ በተለይ አንደኛው አህመዲንን በቦክስ ይመታዋል። በዚህን ጊዜ ኮሚቴዎቹ ሊወስዷቸው ወደሚፈልጉበት ቦታ እንዲወስዷቸው ፈቃደኛ መሆናቸውን በመግለጽ መኪናዋን ተከትለው ጉዞ ይጀምራሉ።
ከአሜሪካን ግቢ በሱማሌ ተራ አድርገው ወደ ኑር መስጂድ በመጓዝ ላይ እንዳሉ ከኋላቸው ከአራት ያላነሱ መኪኖች እየተከተሉዋቸው መሆኑን ያረጋግጣሉ። የነበረውን ግርግር የተመለከቱ በቦታው የነበሩ የጸጥታ አስከባሪዎች መኪኖቹን በማስቆም ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም የደህንነት ሰዎች መሆናቸውን ከገለጹላቸው በኋላ ለቀዋቸዋል።
በጉዟቸው መሀል "እኛ እነዚህን ሰዎች መከተል ያለብን አይመስለንም፣ መታወቂያ አላሳዩንም፣ የምንሄድበትንም አልነገሩንም፣ ቢያንስ እንኳ የት እንደሚወስዱን እንጠይቃቸው" በማለት በጎንና በጎን ካጀቧቸው መኪናዎች አንዱን በመስኮት በኩል ሲጠይቁ የሰጧቸው መልስ ከአንድ የሀገርን ደህንነት እጠብቃለሁ ከሚል አካል የማይጠበቅ ሆኖ ያገኙታል። ጸያፍ ስድቦችን በእጆቻቸው ጣቶች ሳይቀር አወረዱባቸው። በዚህ ጊዜ "እነዚህ አካላት ሌላ ተልዕኮ ያላቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ ብንመለስ ይሻላል" ብለው ኑር መስጂድ አጠገብ ያለውን አደባባይ ዞረው ከአሳዳጆቻቸው በተቃራኒ አቅጣጫ በመጋለብ አንዋር መድረስ ችለዋል። አልሐምዱሊላህ።


. . . . . .

በውነቱ እዚህች ሀገር ላይ ምን እየተደረገ ነው ያለው? ማንስ ነው ሀገራቱን የሚመራት? ከጉሮሮዋችን እየነጠቁ በሚወስዱት ግብር ወሮበላ ነው እንዴ የሚቀልቡበት? ከዚህ በላይ አፈና፣ ከዚህ በላይ ጭቆና፣ ከዚህ በላይ አምባገነንነት ከየት ሊመጣ ነው? መስጂዳችን የተደፈረው እኮ አሁንና አሁን ነው። የመስጂድ መስኮትና በር ሰብሮ በእብሪት ሰላማዊ ዜጋን መደብደብ ለዚያውም መስጂድ ውስጥ ... በአጼው ነው በደርግ ይህ የተፈጸመው? መስጂድ ውስጥ አስለቃሽ ጭስ መተኮስ፣

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 ዓ.ም ከሰዓት ከ ጎንደር ፎቶ ግራፍ ያነሳሁ ኃይሉ

ፊርማ ስም ሁለገብ



ታህሳስ ማሕሉዳር ኃይሉ
08/01/2005

ታህሳስ ሚያዝያ ግንባታ

08/01/2005

ECLN

አጠቃላይ 53 ገጽ (105 slids) ላይ ፈርሜ
ያለሁ

ፊርማ ስም ሁለገብ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

169

http://ethcriminalawnetwork.com/

01/2005 ክሊኒክ ከሳ ተከተ የተገኘ ነው

ለጅጉ ሀሰብ



ታዛቢ መሐመድን ጀበል
08/01/2005

ታማኙ ሀገሰዉ ገመቹ
08/01/2005



ፈርማ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 አንቺ ሴት ተናችን ተገኝ ይሁን

ለደሬ ሀሴን



ታላቁ መሐመድ ጀማ ታላቁ ሊንፃሮ ገመሬ

08/01/2005 08/01/2005

ECLN

አስቸኳይ! አስቸኳይ!

መንግስት በአዳማ ሰልፍ ጠራ

ከሳምንት በፊት አመራሮቻቸው የተጨፈጨፉት ንፁህ መንፈሳዊ ኃይል የመንግስት ድራማ ይሐም

ከዋናው ፈርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 አዲስ ኩፍ ተፃፈና የተገኘ ነው

ለጅሩ ሁሴን

ያ ጀመአ የኡማዉ ብርሃኖችን በሀሰተኛ ዉንጀላ በአሸር ቤት አጉሮ ሊጨርሳቸዉ ነዉ

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል, ሼህ መኩተ ሞሄ, ሼህ ሱልጣን እና ኡስታዝ ጀማል ያሲን እንዲሁም የቁራ ሰላም መስጂድ ምክትል ኢማም ኡስታዝ ሰኢድ አሊ, ኡስታዝ ኑሩ ቱርኪ የሙስሊሞች ጉዳይ መፅኤት ዎና አዘጋጁ ዩሱፍ ጌታቸዉ በሽብርተኝነት ፍርድ ቤት ተከሰሱ!!

ኧረ በዱአ ተበራቱ!!

ታዛቢ መሓመድ ኢብራ 08/01/2005

ታዛቢ: ሊናያም: ገብረ 08/01/2005

ከመንግስት አካላት ጋር በመጣመር ሙስሊሙን ለማስጠቃትና ለማዳከም የምትጥሩ ሙስሊሞች (አህባሽ ወይም ሌላ) አላህን ፈርታቹህ: ነገ አላህ ፊት መጠየቅ እንዳለ አስታውሳቹህ: ታሪክ በቅሌት መዝገብ እንደሚመዘግባቹህ ተረድታቹህ: ነገ እናንተም መሰል የመብት ጥያቄ ብታነሱ አክራሪ ጽንፈኛ መባል እጣ ፈንታቹህ ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛ ሆናቹህ: ከሙስሊሙ ጋር ያላቸሁን ልዩነት ወደ ጎን ብላ በመተው መንግስት በልዩነታችን ተጠቅሞ ሙስሊሙን ለማዳከም የጠነሰሰውን ሴራ እንዲትቃወሙ ወንድማዊ ምክሬን አለግሳለሁ!

ከሞናው ጋር ተመ

ፊርማ

ECTN

http://ethcriminalawnetwork.com/

1/2005 ...ከኔ ከ... ...ተከታ ...ተከ ...

...ለደረ ...



...ከሳሪ መሰከሪያ ...ሰጠ ...ከሳሪ: ...ግንቦ

08/01/2005 ...

08/01/2005

ECLN



http://ethcriminalawnetwork.com/

01/2005 ...

...



ታህሳስ ሚኒሶታ ደብተ- 08/01/2005

ታህሳስ ፲፭፻፹፯ ዓ/ም 08/01/2005



ከዋናው ጋር የተመሳከረ ፎርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

01/2005 ሃገሬ ከሳ ተናቶና ፣ተገኝ ነፋሬ

በደሩ ሀሰን

አስቸኳይ
መንግስት በአሁኑ ሰዓት የከፈተብንን የስነ ልቦና ጦርነት (በተለይ በኢቲቪ ላይ የሚቀርቡት ዶክመንተሪ ፊልሞች) ለመመከት የሙስሊሙን በደል የሚያሳዩ ዶክመንተሪ ፊልሞችን መስራት የምትችሉ ሰዎች እባካችሁ በተቻለ አቅም እንድትሰሩ እና ለህዝብ እንድታደርሱ::
አንድ ኮፒ ከተገኘ ሁሉም ኮፒ እያደረገ ላልደረሰው ማድረስ ይችላል::
በተለያየ ግዜ ፀሞባይል እና በካሜራ የተቀረጸ ምስልም ይሁን ቪዲዮ ያላችሁ ሰዎች ደግሞ ወደ ዩቱብ አፕሎድ አድርጋችሁ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ አድርጉ:::

ታላቅ ጣሊኮን እቴት
08/01/2005

ታዛቢ: ለገሰ: ገመቹ
08/01/2005

ያ ጀመአ የኢማዉ ብርሃኖችን በሀሰተኛ ዉንጀላ በእስር ቤት አጉሮ ሊጨርሳቸዉ ነዉ

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል, ሼህ መኪተ ሞሄ, ሼህ ሱልጣን እና ኡስታዝ ጀማል ያሲን እንዲሁም የቁራ ሰላም መስጂድ ምክትል ኢማም ኡስታዝ ሰኢድ አሊ, ኡስታዝ ኑሩ ቱርኪ የመ·ስሊሞች ጉዳይ መፅኤት ዎና አዘጋጁ ዩሱፍ ጌታቸዉ በሽብርተኝነት ፍርድ ቤት ተከሰሱ!!

ሼሪ በዴአ ተበራቱ!!

ፈርማ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Investigation

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 ዓ.ም ከቀኑ ከ[illegible] ገደማ
ተጋጥ ሄሩ ።

[illegible] ቦሩሩ ሆኑ

መስጂዳችን ተደፈረ!

ባሁኑ ሰዓት አወሊያ የሚገኘውን የሙስሊሙን
ንበረት ሁሉ በመንግስት ጸጥታ ሃይሎች
እየተዘረፈ ይገኛል!

ፓሊስ መኪኖችን እየተ[illegible]
08/01/2005

ታዛቢ: ሲራጅ ገመቹ
08/01/2005

ECLN

በአሁኑ ሰዓት ወንድሞቻችን
በአወሊ እየተደበደቡ ነው
ሁኔታውን በመረጃ ለመያዝ
ካሜራ ይዛችሁ ድረሱላችው!

ፍጠኑ!!!!

ከዋናው ጋር ተመሳክሯ
ፌርማ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Investigation [illegible]

178

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 አንድ ሉህ ተጋቶ የተገኘ ነው

ለደንበኛ ሁሉን

Status Photos Check In

አደራ ሰጭው መብሌሙ በመጫ!!
የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ልጆች በዚሁት ወቅት የሚመጣው
ዕለታዊ የመኖሪያ ችግሬ ወደ ሌላ ምዕራፍ እያቀፍኩለሁ ይህንኳ
በከተማችሁ ከሚያስቡት ወገኖቻችሁ በሙሉ ማከበርያ
ሽምጋዮች፣ ሃገ መሰሪዎች አደባባዮች፣ ወረቃቆችም፣
ፈላጭቆሪም ሠፈሩ አለህ ብሎ ጫቤ በመሆንም የሚመርጣችሁን
ሰላማዊ ትግል እያካሄዳ አለሁ ደረጃ ሊደርስ ሚችል
አገዛዝችን ጭራም በሚገባ በመሆኑ ነው:: አሁንም በአንድነ
የሚሳካልበት ኮሚቴዎቻችን በመሆኑ በታሰሩ አሊሆኑትን
ማሊቃቸውን አሊቀሩትን በመሆኑ ቢታሰሩ ይበል በሚሉም ወገና
ፈርተውማል ሃገ ምክሯ መታሰሯ ብቻ መሆን እንዳለበት
ብተማመኑ አሳስበውናቸዋል ይህ አደራ ሚሚፈጽማችሁን ሰለሆነ
አስቸኳይ ማሰሪያ ሚሰጣቸው ብቻ መሆኑም
አንዳችሁን አሳስባችኋል:: ዓመጣዉ ፈተና አደራውም ማጽደቁንም
አኛ አንስቸመጥን ብለሆል":: ህዝበ መብሌሙ በምንም
አኳኋኑ መጫኑ አንሁ አንተጋል ጀመሩ አንሻፈል አንችም
ብለሆል:: በዕለቱም አንደምመጣን አስከመጨረሻዉ በወኖች
በዕለታዊ መኖሪያ መኖሪያ አገዛዛችን አሳስበናል:: ከሚቴዉ
ቢታሰርም ቢገደልም አስተምን ማህደም ሆን መኖሪያ
ስለማይኖሩ ከሚቴዉ ሳይ ምንደርገዉ ግር ሰሞኑ ስጠቀምንን
ቢያጨማልቃ በመታገል ከደብኝ ከብቸኝነት አደባችን
አንደንከብት አሳስበናል:: ደግሞ የኢሰላም ነዉ!! አደራ አማርኛ
ሰሞኑን አደራ መብሌሙ በመጫሉ አሳስበናል አንጨመዉ

ታዛቢ ማጊሌቶን ፈርሞ
08/01/2005

ታዛቢ: ባጋዥ: ግዛው
08/01/2005




ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/


01/2005 ሂደቱ ሉዋ ገፃቶኝ የተገኘ ነው

ስልክ ለጀነራ ሀሰን




ታዛቢ ማዜሆን ፈርሜ
08/01/2005

ታዛቢ: ሪጓናልዶ: ገጠሌ
08/01/2005





ከዋናው ጋር ገ
ፊርማ



ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

01/2005 ጊዜ ሊያ ተፃፉ የተገኘ ጽሁፍ

ለዶሩ ሁለን



ታክሰ መሐከሩ ጀምቶ
08/01/2005

ታክሰ: ጸንፀ: ገስሰ
08/01/2005



1/2005 ከአቤ ከሳ ፣፻፩፫ የተሰኘ ጉዳይ

ለደረሳ ሁሉ





ታዛቢ ማሔሌሙሪ እሸቱ
08/01/2005

ታዛቢ፡ ሪያዓ፡ ገመቹ
08/01/2005



ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

1820

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

01/2005 ሳጂን ኩባንያቸው የተገኘ ሰው

ስለሆነ ሁለን



ታክሲ መኪኖችን ይዘው

08/01/2005

ታሁሉ: ሲንቄም: ገንዘብ

08/01/2005

ECLN

በመስጅድ ያላችሁ ጀምዓዎች
ከመስጅድ እንዳትወጡ ፣እዚያው
ተቃውሚችሁን አሰሙ ተብሏል!
ስልክ በመደወልና ሜሴጅ
በመላክ እናስተላልፍ

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል

ፊርማ

http://ethcriminalawnetwork.com/

[redacted]/01/2005 ሃሳቤ ከዚህ ገንዘቦች የተገኘ

ሀሳቤ ከዚህ ሁለት

ሁላችንም ዛሬ አዳራችንን አወሊያ
በማድረግ የሙስሊሙ ንብረት
ከመወረስ እንታደግ!!!
ኑ ወደ አወሊያ!!!!

ታዘቢ መሐመድን እዘት
08/01/2005

ታዘቢ: ሚያዝያ: 7ለሊ
08/01/2005

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 ሀሳቤን ሐ. ተናቶ ; ቦታ ገነ ናሁ

ከመደረ ሁሉን


ኮሚቴዎቻችንን በሀሰት በሽብርተኝነት አስረው ሊጨርሷቸው ነው! ወገን ስማ! ዛሬ በአንዋር ተቃውሞ እናሰማለን!!!

ታዛቢ ማዘጋጃ ቤት

08/01/2005


ታዛቢ: ሪንጎ ገብሬ

08/01/2005





የዝምታውን ተቃውሞ እንዴት ነው የምናካሂደው?		
1ኛ	አፋችንን በያዝነው ነገር በመሸፈን ሳን ለሳን እጅ ለእጅ እንያያዝለን	ለ7 ደቂቃ
2ኛ	የያዝነውን መፈክር ወደላይ ከፍ አድርገን እናሳያለን	ለ6 ደቂቃ
3ኛ	እጃችንን ወደላይ ከፍ በማድረግ እጅ ለእጅ ተያይዘን እንቆያለን	ለ3 ደቂቃ



ፈርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 ዓ/ዓ ከሰዓት ከሥ ተጀምሮ የታተመ/የወጣ
ጉዳይ፡

ከጀርባ ሁለን

ሰበር ዜና!!!

የህዝበ ሙስሊሙ መጭትሄ አይለሳለሴ
ኮሚቴው አባል የሆኑት አስታግዘ ያሲን
ኡጉ ሲኤምሲ አካባቢ በፖሊስ ታሰሩ!!

ረመዳን 3/1433

ታዛቢ፡ ሀናን ፡ ገመሰ
08/01/2005

ታዛቢ መሐመድ እድሪስ
08/01/2005

ያ ኡመተል ኢስላም ጉዞ ወደ አወሊያ ! የቾግር ግዜ አዛን እየተደረገ ነው! የተኙትን እየደወላችሁ ቀስቅሷቸው!!!

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Justice Investigation and Prosecution

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 ዓ.ም ተፈቶ ፕላን) ሮ
በፊት ሀሳብ

መቃወሚ ሲደለበት

የደምን ግዴታነት
አምነውና ተቀብለው
በውዴታ ይፀሙ
ግንዳውንም ከአላህ
ብቻ ይጠብቁ




ታዛቢ ማረሚያቤት ጌታቸ
08/01/2005



ታዛቢ: ረ/ኢ/ል ንጋሪ
08/01/2005







ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005

አዴ ዩሃንስ ሙስሊሞችን ሲያሰቃዩ አላህ ተቆጣባቸው
መጨረሻ አድላቸውም አንገታቸውን መቆረጥ ሆነ !!!!
አዴ ሃይለሥላሴ ሙስሊሞችን ጨቆኑ
መጨረሻቸው ሽንት ቤት መቀበር ሆነ!!!!
ሻሮን ፍልስጥኤማውያንን ጨፈጨፈ መጨረሻው ከአሰት በታች
ከሞቱት በላይ በመሆን በጣረሞት እየተሰቃየ ይገኛል!!!
የኢሃ አዲግ መንግስት ሰላማዊ ሙስሊሞችን በማሰቃየት እና በ
እምነታቸው ጣልቃ በመግባት አሁን ደግሞ በጅምላ እየጨፈጨፈ
ይገኛል
አላህ ሆይ የ ፊር አውንን እና የሃማንን የቃሩንን አይነት ቅጣት በኢህ
አዲግ አረመኔዎች እና ተባባሪዎቻቸው ላይ እንድታወርድባቸው
እንማጸንሃለንና ድሉን ለተበደሉት ሁሉ ቅርብ አድርገውና አሚን በሉ

ታዛቢ መሐመድ ጌቶ
08/01/2005


ታዛቢ: ሀጊ ገመሌ
08/01/2005

ዛሬ ሙስሊሙ ሊደርስበት
ከሚችለው አደጋ አላህ
እንዲጠብቀው ኢስቲግፋርና ዱዓ
እናብዛ! ሰላማዊነታችንን
በያለንበት እንስበክ! ለመበጥበጥ
የቲዘጋጁ ሃይሎችን በዝምታ
እናስቁማቸው!

ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፊርማ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/



ታዛቢ መርማሪ ኃ/እ/ት
08/01/2005
ታዛቢ: ረ/ሳጅን ገብረ
08/01/2005

በአሁኑ ሰዓት ወንድሞቻችን በአወሊ እየተደበደቡ ነው ሁኔታውን በመረጃ ለመያዝ ካሜራ ይዛችሁ ድረሱላችው!
ፍጠኑ!!!!

ከዋናው ጋር ተመሳክሮ ፎርማ

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

08/01/2005 ዓ.ም አንድ ኪሎ ብቻ ተይዞ የተገኘ
ሰው ስለሌለ ሁላችን




ታዛቢ ማረጋገጫ ሰጠን
08/01/2005







ከዋናው ጋር ተመሳክሯል
ፈርማ



ታዛቢ ሪፖርተር ገብረ
08/01/2005

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የመ.ቁ 124754

14/5/05 ዓ.ም

ዳኞች:- ብስራት ተልዕፅ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሣሽ:- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድሣገኝ ቴዎድሮስ ባህሩ ዘረሰናይ ምስግና እንደዚሁም ቴዎድሮስ ጊታቸው ቀርቧል

ተከሣሾች:- አነ አበብከር አህመድ 31 ሰዎች 2 ድርጅቶችን ጀምሮ ቀርቧል

ከቀረቡት ተከሣሾች የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አቶ ሀሚድ ጀማል ቀርቧል የሌሎቹ ተከሣሾች ጠበቆች ባህሩ መካንጋ ተማም አባቡልጉ ሀሰን ሁሴን ተካ ዳባ ሀሊማ ሰይድ ዳዊት ነጋሽ ንጉሱ ጌታሁን ሞላልኝ መለሰ መሐመድ አብደላ እና አዲሰ መሐመድ ቀርበዋል

- ፍ/ቤቱ ስለችሎቱ በእዚህ በዝግ በክፍት ይታይ እንደዚሁም ስለምስክሮቹ ማንነት ከግራ ቀኝ የቀረበው ክርክር ላይ ብይን ከሰጠ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ምስክሩን ይቀጥል ብሏል ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ የሚያስመዘግበውን ጭብጥ እንቀጥላለን ከተጠቀሱ ጠበቆች ያልቀረበ አለ ስለዚህ ሳይመሰጠን ማስመዝገብ እንቀጥል
- እሺ. የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን ጭብጣችንን ከሳችነው ነገር ግን በስነ ስርዓት ሕግ 136/1 መሠረት እንደሚከተለው ክሳችንን እንከፍታለን ይኸውም በአጠቃላይ 31 ተከሣሾች ላይ

1179

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

29 የተፈጥሮ ሰዎች እና የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ሰዎች ላይ ክስ አቅርበናል ይኸውም ነኛ ክሰ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1 ሀ ለ እና 38/1 እና የፀረ ሽብርተኛ አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 3 1/2/4/6 የተመለከተውን ተላልፏል ተብሎ ክስ ቀርቧል 2ኛው ክስ ፍ/ቤቱ በብይን ውድቅ ያደረገው ነው ስለዚህ 3ኛ እና 4ኛ ክስ በተመለከተ በ 30ኛ እና በ 31ኛ ተከሣሾች ላይ የሽብር ተግባርን መደገፍ በሚል የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ 652/2001 አንቀፅ 5/1 መ ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል በማለት በ 30ኛ እና በ31ኛ ተከሣሾች ላይ ክስ አቅርበናል ክሱ የክሱ ጭብጥ የክሳችን ክሳችን በአጭሩ እና የማስረጃው ባህሪውን በተመለከተ እንደሚከተለው አቀርባለሁ ተከሣሾች ክስ የቀረበባቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት እና የአድማ ስምምነት በማድረግ ኃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ ከ 2001 ዓ.ም ጀምሮ /ግልፅ ያልሆነ / ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ ከቆዩ በኋላ የተለያዩ ሕዝበ ሙስሊሙ ጥያቄዎች ምላሽ እናፈላልጋለን በማለት ለራሳቸውም ስያሜ በመስጠት በተለያየ ግብ እና አቅጣጫ አስቀምጠው ሲንቀሳቀሱ በመቆየት 17 ኮሚቴዎችን አቋቁሟል እነዚህ 17 ኮሚቴዎች በመጀመሪያ ደረጃ የተቋቋሙት እና ሂድን የሆነው ወይም ድብቅ የተባለውን አላማ የሚያራምዱ የተወሰኑ ሰዎች ናቸው የነበሩት በእዚህ 17 ኮሚቴ 17ቱ ኮሚቴ እንደኮሚቴ መጨረሻ ላይ ፎርም የተደረጉት ይሄንን ኮሚቴ /ግልፅ ያልሆነ/ ለመስጠት የተለያዩ ሽማግሌዎ እና ሙህሮችን በማካተት መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ በማለት እራሳቸውን በመሰየም ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል ይኸው ኮሚቴ ከ 2001 ጀምሮ ፎርም ያደረጉ ሰዎች አሉ በኋላ ላይ 17 ኮሚቴ 17 ሰዎች መፍትሔ አፈላላጊ በማለት መጨረሻ ላይ ሰይሞ ሲንቀሳቀሱ ነበር እነዚህ ኮሚቴ ሲጀምር የአወለያ ት/ቤት እንደማንኛውም የት/ቤት የሀይማኖት ት/ቤትም ቢሆን የመማር ማስተማር ግጭቶች ያለውን የመማር ማስተማር አለመግባባት የአወሊያ ት/ቤት የሕዝበ ሙስሊሙ ጥያቄ ነው በሚል እንደአንድ ጥያቄ በማቅረብ 2ኛ የራሳቸው ድብቅ የሆነውን ዓላማ ወይም ደግሞ ከእኛ ኃይማኖት ወይም ከእኛ አስተምሮ ውጪ ሌላ አስተምሮ በእዚህ ሀገር ሊኖር አይገባም የሚለውን ከሕገ መንግስቱ ውጪ የሆነውን አስተሳሰብ ለማራመድ ሀበሻ የሚባል አስተምሮ ወይም ደግሞ ሴፍት በእኛ ሀገር መንግስት በግድ እየጫኑብን ነው በሚል እንዲሁም መጅሊስ አልወከለንም የሚሉ 3 ጥያቄዎችን እንደኮሚቴ በማንሳት እነዚህን የራሳቸው ሂድን የሆኑ ወይም ድብቅ አላማቸውን ለማራመድ የ[illegible] አድርገዋል እንደሚያሳየው በማያዝ ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል እነዚህ በዋነኛነት በመጀመሪያ ክሱ ክሱ እንደሚያሳየው

1190

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

በሽብርም ያስባለው ሞቲቫቸው ከእኛ አስተምሮ ውጪ ወይም ደግሞ እኛ ከምንፈልገው የኃይማኖት ሴት ውጪ ሌላ ኃይማኖት በእዚህ ሀገር ሊራመድ አይገባም ወይም ደግሞ ከውጪም ከየትኛውም አለም ሊገባ አይገባም በማለት ይሄንን ሂድን የሆነውን ወይም የተደበቀ ዓላማውን ዓላማቸውን ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ ጥያቄዎችን በማንሳት በመሸፈን በእዚሁ የሌላውን የኃይማኖት ነፃነት እና መብት ሲጋፉ ቆይተዋል ይሄንን አልፎ ከማራመድ ውጪም ወደ ሀይል ተግባር በመግባት በክሳችን ላይ በተገለፀው በሰው እና በንብረት ላይ ጉዳት እንዲደርስ አድርገዋል በአጭሩ የክሱ ጭብጥ ተከሣሾቹ ፖለቲካዊ እና ሀይማኖታዊ ዓላማን ለማራመድ ፖለቲካው እየተባለ ያለው መጀመሪያው በማስረጃ ወደ ፊት የሚታይ ሆኖ ወደ ፊት የአጭር እና የረጅም ጊዜ በማለት በራሳቸው መስራቾቹ ማለት ነው የእዚህ የረጅም እና የአጭር እቅዳቸው ጠንሳሾቹ የሆኑ ሰዎች ያስቀመጡት የፖለቲካ አላማ አለ ያንን የፖለቲካ አላማ እየተባለ ያለው የኃይማኖት አሁን የገለፅኩት ከእኛ አስተሳሰብ ወይም ደግሞ የኃይማኖት አስተምሮ ውጪ ሌላ ኃይማኖት አይኖርም የሚለው በድብቅ ሲራመድ የነበረው በመጨረሻ ላይ ለንብረት እና ለአካል ጉዳት መድረስ ውጤት ምክንያት የሆነው ማለት ነው መጀመሪያው ይኸው ነው ሞቲቫቸው ወይም ደግሞ ዓላማቸው ይኸው ነው የፖለቲካዊ እና ሀይማኖታዊ ነው ይሄንን ዓላማ እና መብታቸውን ማራመድ ሕገ መንግስታዊ መብታቸው ነው እንደኃሳብ ማለት ነው አስተሳሰቡ በራሱ ወንጀል አይደለም ነገር ግን ይሄንን አስተሳሰብ በሕገ ወጥ መንገድ በኃይል በሌላው ላይ መጫን ወይም ደግሞ የሌላውን ኃይማኖት መጋፋት ሕገ ወጥ ተግባር ነው ኃሳቡ ብቻውን ሳይሆን ይሄንን ሞቲቩ ነው የክሱ መነሻ ነው 2ኛው የሕገ ወጥ ተግባሩ በክሱ ላይ የተገለፀው ነው የክሱ ጭብጥ በአጭሩ ይኸው ነው ወደ ማስረጃው ባህሪ እና ዓይነት ስንመጣ የሰው ማስረጃ እና የሰነድ ማስረጃ የሰው የሰነድ የድምፅ ከምስል እንዲሁም ኤግዚቢት ማስረጃዎችን አቅርበናል የሰው ማስረጃዎቹ በተለያዩ ጭብጦች በክሳችን ላይ ያለውን ጭቦጦች የተለያዩ የሰው አካል የንብረት ላይ እንዲሁም ሕገ ወጥ የሆኑ ቅስቀሳዎችን የሚያስረዱ ምስክሮች ናቸው በ2ኛው ያሉ ምስክሮች ታዛቢዎች ናቸው እነዚሁም በ 32 በስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 32 ንዑስ ቁጥር 3 ላይ በተከሣሾች ቤት ንብረት ላይ በተደረገ ብርበራ በታዛቢነት ተገኝተው በተያዙት ፖሊስ በብርበራ የያዛቸው ሰነዶች ላይ የፈረሙ ምስክሮች ናቸው ስለዚህ የመጀመሪያዎቹ ምስክሮች በክሱ ጭብጥ ላይ የተገለፀውን ተግባር ለመጥቃም በተዘዋዋሪም የሚያውቁትን ምስክርነት የሚያስረዱ ናቸው 2ኛዎቹ የሰው ምስክር ዓይነቶች አሁን

1191

http://ethcriminalawnetwork.com/

የገለፅኳቸው በታዛቢነት ቀርበው በብርበራ የተያዙ ሰነዶችን እና የብርበራ አካሄዱን በተመለከተ ሰነ ስርዓታዊ አካሄዱን የሚያስረዱልን ናቸው ወደ ሰነድ ማስረጃው ሲኬድ በአብዛኛው የቀረበው ሰነድ ከተከሣሾች በብርበራ የተገኘ የእጅ ፁሑፍ የግል ማስታወሻዎች እንዲሁም ከኤሌትሮኒክ ግንኙነታቸው ወይም ደግሞ የኢሜል ግንኙነታቸው ላይ ከላፕቶፓቸው እና ከኮምፒዩተራቸው ላይ በራሳቸው ፍቃደኝነት እንዲወጡ ተደርገው በሰነድ ማስረጃነት ለፍ/ቤቱ እንዲሁም ለተከሣሾች እንዲርሱ የተደረጉ ናቸው ሌላው በእዚህ በሰነድ ማስረጃነት ተከሣሾች በስልክ ያደርጓቸው የነበሩ ግንኙነቶች በኢንተርሰፕሽን ማለት ነው ቴሌፎን ኤንተርሴፕሽኖቹ በፁሑፍ ተቀይረው በሰነድ ማስረጃነት ቀርበዋል ሌላው በሰነድ ማስረጃነት የቀረቡ ተከሣሾች በብርበራ የተያዙባቸው በእጅ ፁሑፍ የተፃፉ በርካታ እጅ ፁሑፍ ሰነዶች አሉ እነዚህ እጅ ፁሑፎች የተከሣሾች እራሳቸው መሆናቸውን በፎረንሲክ ምርመራ ተመርምሮ የተረጋገጠበት ሰነድ በማስረጃነት አቅርበናል ሌላው እነሱ በእዚህ በወንጀል ተግባር ለመቀስቀስ ይጠቀሙባቸው የነበሩ ቅድምም የገለፅነው ድምፃችን ይሰማ የሚል በተለያዩ አጋጣሚ ሲበተኑ የነበሩ ወረቀቶች በማስረጃነት እንዲሁ አቅርበናል በ3ኛ ደረጃ ያቀረብነው የድምፅ ከምስል ማስረጃ ነው የድምፅ ከምስል ማስረጃው ክሱን ይኸውም በአብዛኛው በብርበራ ከራሳቸው ከተከሣሾች ቤት የተገኘ ነው ይኸው የድምፅ ከምስል ማስረጃ የሚያስረዳው ተከሣሾቹ ቅድም የገለፅነውን ኃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ግባቸውን ለማራመድ ያደርጓቸው የነበሩ እንቅስቃሴዎችን የሚያሳይ ቅስቀሳዎችን ሕገ ወጥ ቅስቀሳዎችን የሚያስረዳ ማስረጃ ነው በ4ኛ ደረጃ ያቀረብነው ኤግዚቢቶች ናቸው እነዚህ ኤግዚቢቶች የተለያዩ መሣሪዎች ናቸው ከላፕቶፕ እስከ ሲልክ እንዲሁም በክሱ ላይ የተገለፀው የሰደቃ እና የአንድነት ፕሮግራም ሊዘጋጁባቸው ወይም ደግሞ ሊሰናዳባቸው የተዘጋጁ ቁሳቁሶችንም እንዲሁ በማስረጃነት አቅርበናል በዛሬው ዕለት ምስክሩ ፍ/ቤቱ ቀጠሮ ለ 10 ቀን ይዟል ምስክሮችን ለመስማት ከምስክሮቹ ብዛት በዛሬው ዕለት በአጠቃላይ 10 ምስክር ይዘን ቀርበናል ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሮቻችን ማሰማት እንድንችል እንዲፈቅድልን ነው የምናመለክተው

- እሺ /ግልፅ ያልሆነ/
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ደንበኞቻችን የተከሰሱት የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ 652/2001 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 1/2/4/6 ን በመተላለፍ የሽብርተኝነት ድርጊት ፈፅመዋል ነው የተከበረው ፍ/ቤት በክስ ማሻሻያ ብይኑ የተቀበለው እሱ ነው እንድንከላከል የወሰነበትንም

1192

http://ethcriminalawnetwork.com/

በእዚህ አንቀፅ መሠረት የቀረበውን ክስ ነው ዐቃቤ ሕግ አሁን ያስያዘው ጭብጥ የተከሣሾቹን የወንጀል ሞቲቭ በሚል ያስቀመጠው አለ የወንጀል ዓላማ እና ኃሳብ ነገር ግን ይሄንን ዓላማ እና ኃሳብ ያሳኩበታል ያለው ፈፀሙት የተባለው የሽብርተኝነት ድርጊቱ የታለ ማን ምን ፈፀመ ስለወንጀል ጉዳይ ነው የወንጀል ክስ ነው እያንዳንዱ ተከሣሽ የፈፀመው የተላለፈውን የተጠቀሰበትን የሕግ ድንጋጌ በመተላለፍ የፈፀመውን የወንጀል ድርጊት በግልፅ ማወቅ አለብን ያንን ስናውቅ ነው ለመከላከል የምንችለው ዐቃቤ ሕግም በእዚህ መልኩ ጭብጡን ካስያዘ በኋላ ነው በማስረጃ ሊያስረዳ ሊፈቀድለት የሚገባው አሁን የክስ መክፈቻ ንግግሩ በአንቀፅ 3 የተከበረው ፍ/ቤት በተቀበለው አንቀፅ መሠረት መቅረብ ካለበት መቅረብ ያለበት ምንድን ነው በእነኚህ 4ቱም ውስጥ አንቀፆች ስር የተፈፀሙ ድርጊቶች መኖር አለባቸው እነኚህን ድርጊቶች ደንበኞቻችን መፈፀማቸውን ማሳየት አለበት በእዚህም መሠረት የክስ ጭብጡን አስይዞ ከእዚያ የሚያስማቸውን ማስረጃዎች ዓይነትም ማስመዝገብ አለበት የማስረጃዎቹ ባህሪ ዓይነት እንደሰማነው ለቅስቀሳ እና ለማነሳሳት /ግልፅ ያልሆነ/ ንግግሮች ፀሐፎች ናቸው በእዚህ ዓይነት ማስረጃ የሽብርተኝነት ድርጊትን ማስረዳት አይቻልም የተከበረው ፍ/ቤት ስለዚህ አልገባንም ክስ ጭብጡ ምንድን ነው ይሄንንስ የክስ ጭብጥ ሊያስረዳ የሚያቀርበው ማስረጃ ምንድን ነው ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት ቀደም ሲል በሰጠው ብይን መሠረት በአንቀፅ 3 ስር የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ካለ በግልፅ ይንገረን ነኛ ተከሣሽ አቡበከር መሐመድ አህመድ ምን ፈፀመ የትኛው 2ኛ ተከሣሽ እያለ የእያንዳንዱ ተከሣሽ ድርሻ ካልተገለፀልን መከላከል አልንችልም ዐቃቤ ሕግም ክሱን በእዚህ ሁኔታ እንዲያስረዳ እና ማስረጃም እንዲያሰማ ሊፈቀድለት አይገባም ስለዚህ ግልፅ እንዲሆንልን ነው በእኔ በኩል ያለው ይሄ ነው

- ድጋሚ ነው ወይስ የተለየ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ አጠቃላዩ ነው የተከበረው ፍ/ቤት አጠቃላዩ ሆኖ አሁን ከቀረቡ ነገሮች ውስጥ ነገሮች ጭብጥ ሲያዝ ነገሮች እዚህ ፊት ለፊት ወጥቶ ግልፅ ሆነው እንዲታዩ ነው እንጂ በድፍን የሚታለፍ ነገር አይኖርም የማስረጃውን ዓይነት ይገልፃል ሲል ፍ/ቤቱ ሕጉን ያወጡት ሰዎችም የሕጉም ዓላማ ምንድን ነው
- አሁን የተነሳውን ሳይደግሙ
- አልደግምም የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ አሁን እኔ ጥያቄዬ መብራራት አለባቸው በምለው ጭብጦች ላይ ነው የማተኩረው እና አሁን ዐቃቤ ሕጉ ሲያቀርቡ ሂደል የተባለ ኮማቱ አሳስቶ

1193

http://ethcriminalawnetwork.com/

የተባለውን ኮሚቴ አቋቋሙ የትኛው ኮሚቴ ነው እሱ መገለፅ አለበት አንድ 2 ነገር ነው የጠቀሱት 2ኛ እንደኮሚቴ ጥያቄ በማንሳት ብለዋል ጥያቄ የራሳቸው ነው ወይ ነው ይሄ መብራራት አለበት ነው ኃይማኖት ሊገባ ወደ ሀገር ሊገባ አይገባም ሲሉ ኃይማኖት መንግስት ማስገባት ይችላል ወይ ነው የሚለውን /ግልፅ ያልሆነ/ አለባቸው ሌላ 3ኛው ሌላ ኃይማኖት አይኖርም ሲሉ ሁሉም ኃይማኖትን ነው ለማለት ፈልገው ነው ክርስትናን ጨምሮ ማለት ነው አልሀባሽ የሚባለውን /ግልፅ ያልሆነ/ አልሀባሽ የሚባል ስልት የለም ነው ወይ ነው እነዚህ ጥያቄዎች መብራራት አለባቸው ነው አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት

- እዚህ ላይ ዐቃቤ ሕግ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል አያስፈልግም የሚለውን ያው ፍ/ቤቱ እራሱ ማየት ይችላል ዐቃቤ ሕግ ሲያስመዘግብ ያው የተተነተነው አለ ነገር ግን ጭበጠ ክሴ ነው የሚል ነገር አለ ክሱን በተመለከተ ግን ከእዚህ በፊት የተወሰነው ክስ ወጥቶ የተወሰነው ክስ ቀርቷል አሁን ዛሬ መከላከልም ጥያቄ መጠየቅም አንቀፅ 3 አዋጁ እና ሌሎች ሌጋል አርጋናይዜሽኖቹ 5 አር 9 አንቀፆቹ ላይ ብቻ ነው የሚጠቀየው እና እሱ ግልፅ ነው እዚህ ጋር የታለፈም ደግሞ ዛሬ የተነሳ ስላለ ማለት ነው አረዲ በብይን የታለፈም ዛሬ የተነሳ አለ ያ ብይኑን ድጋሚ ዛሬ ማየት ስላለብን አስፈላጊ ስላልሆነ ነው ዐቃቤ ሕግ እዚህ ላይ ግልፅ አድርግ ማለት ያልፈለግነው ማለት ነው ለምን አረዲ በብይን የታለፈ አለ እስከእዚህ ድረስ ግልፅ ነው ይሄ ይሄ አያስፈልግም ተብሎ አረዲ ታልፏል ከእዚህ በኋላ አፕል እስቴጅ ነው ሊኖር የሚችለው በእዚህ እስቴጅ ግን አንቀፅ ስሪ ስር የቀረበው ክስ ግልፅ ነው እና ሌሎችም 2 ድርጅቶች ላይ የቀረበው ክስ ግልፅ ነው ተብሎ ታልፏል እሱ ነው ዛሬ ማረጋገጥ የምችለው ማለት ነው የተዘረዘረው እሱ ውስጥ አለ የለም እሱ ማስረጃ ሲመስክር ተጣርቶ ወዴት ይሄዳል የሚለው በኋላ የሚወሰን ነው ሌላው ነኛ ተከሣሽ ምን መፈፀመ 2ኛ ምን ፈፀመ የሚለው ነኛ አድሚል ተስማምቷል ውጤቱንም ተቀብሏል የሚል ዝርዝር አለ የአድማ ፅንሰ ኃሳብ ደግሞ ግልፅ ይመስለኛል ያ ግልፅ ከሆነ እገሌ ምን ፈፀመ ምን ፈፀመ የሚለው ክስ ላይ እንዳለ ሆኖ ብዙም አከራካሪ ሊሆን የሚችል አይደለም ሌሎቹም ከእዚህ ጋር የተያዙ ስለሆኑ ዐቃቤ ሕግ እዚህ ላይ መልስ መስጠት አስፈላጊ አይደለም አረዲ በብይን የታለፈውን ነገር ድጋሚ የተነሳ ስለሆነ ማለት ነው ስለዚህ በእዚህ መሠረት ምስክሮቹ ቀርበው ቃለ መሀላ እንዲፈፅሙ ትዕዛዝ ሰጥተናል

- ምስክር ቀርቧል እስቲ ወደ እዚህ ዞር ብለው ምስክር ኖት አያደርጉ ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ነኝ
- ቃለ መሀላ ፈፅመዋል ቅድም ለምስክር ደህንነት ተብሎ ብይን ተሰጥቷል ስለዚህ ምስክሮቹ እንዲገልፁ ተብሎ ብይን የተሰጠው የራሳቸውን ስም ብቻ ነው ስለዚህ የአባታቸውን ስም እንዲገልፁ አንጠይቅም አይጠበቅም አድራሻቸውንም ከእዚህ ውጪ ያለውን አንጠይቅም የራሳቸውን ስም ብቻ ነው የምንጠይቀው ከእዚህ በኋላ ማን ላይ ሊመሰክሩ እንመጡ እና ሌላው ሂደቶች ይቀጥላሉ ስለዚህ ምናልባት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ዝርዝር ላይ ስንተኛ ላይ እንደተጠቀሱ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- አላውቅም
- አያውቁትም በክሱ ቻርጅ ላይ 62ኛ ላይ የተጠቀሰ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ነው የራስህን ስም ትነግረናለህ የራስህን ስም ብቻ ?
- ቢስሚላሂ ራማን ኢረሂም ተስፋዬ እባላለሁ
- ተስፋዬ ?
- ሀጂ ተስፋዬ እባላለሁ
- ሀጂ ተስፋዬ ?
- አዎ
- ዛሬ ለምስክርነት ነው የመጡት ?
- አዎ
- እነ ማን በተከሰሱበት ጉዳይ ነው ?
- እነ አቡበከር አህመድ በተከሰሱበት
- ከእነሱ ውስጥ ማን ማን ላይ ለመመስከር ?
- ቢስሚላሂ ራህማን ረሂም እንግዲህ እኔ ከሰኔ 2003
- አሁን አጠር አድርገው ከእነ አቡበከር ላይ 30 ሰዎች አካባቢ ናቸው እና ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- እኔ ነኛ ሙባረክ አደም
- ሙባረክ አደም ላይ ነው የምመሰክረው አንዱ ብለዋል
- ሙባረክ አደም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ 20ኛ ላይ ተጠቅሷል ተብሏል
- ሙባረክ አደም
- ሌላ ?
- አመዲን ጀባል
- አመዲን ?
- ጀባል
- ስንተኛ ነው 2ኛ ተከሣሽ እሺ ?
- አቡበከር አህመድ
- እሺ 1ኛ ተከሣሽ ?
- ጀማል ያሲን
- 19ኛ ተከሣሽ እሺ ሌላ ?
- ያሲን ኑሩ
- እና 3ኛ ተከሣሽ እሺ ሌላ ?
- በእነዚህ ሰዎች ላይ እመሰክራለሁ ብሏል ያውቁታል እንዴ ሰዎቹን ?
- አውቃቸዋለሁ
- ዐቃቤ ሕግ ጥያቄ ይቀጥሉ
- እሺ ሀጂ ተስፋዬ አሁን በዘረዘሯቸው እና ምናልባት የሚያስታውሷቸው ካለ በእያንዳንዳቸው ላይ ማለት ነው ማን ምን ሲያደርግ እንደነበረ እና ጊዜውን ቦታውን አጠቃላይ ያሎትን እውቀት እነኚህን በሚመለከት በዝርዝር እንዲገልፁልን ነው የምንጠይቀው በመጀመሪያ ከአቡበከር አህመድ በሚመለከት መጀመር ይችላሉ እና ምን ሲያደርግ እንደነበረ ጊዜው መቼ እንደነበረ ቦታው የት እንደነበረ የሚያውቁትን ለተከበረው ፍ/ቤት በዝርዝር እንዲገልፁ እጠይቃለሁ በመቀጠል ያው እንደዚያ ይገልፁታል ማለት ነው ?
- አቡበከር አህመድን ያው
- ተስፋዬ ወደ እዚህ ፊትዎን ወደ ፍ/ቤቱ እያዩ የሚያውቁትን ይቀጥሉ
- አቡበከር አህመድን ቀደም ብዬም ነው የማውቀው በአጋጣሚ እኔ ቀድም ስጀምር ለመነሳሳ እንደሞከርኩት ከሰኔ 2003 ጀምሮ ይሄ ተቋም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር

1196

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ቤት እንዲረከብ ተደርጎ ከተረከበ ጀምሮ በምክትል ስራ አስኪያጅነት ተመድቤ እዚያ እየሰራሁ ነበር እና ቀኑን አላስታውስም በታህሳስ ወር ውስጥ ከጠቅላይ ምክር ቤቱ በተፃፈልን ደብዳቤ በተወሰደው መምራኖች እና

- /ግልፅ ያልሆነ/
- 2004 በተወሰደው እርምጃ ተማሪዎች ተቃውሞ አንስተው ከግቢ ውስጥ አንድ ሁለት ሶስት ሣምንት ሄደው ነበር እንቅስቃሴው እና
- የት ተማሪዎች ?
- የአወሊያ ተቋም ተማሪዎች
- ቀጥሉ ?
- እና ይሄንን በተመለከተ ቀኑን የማላስታውሰው አንድ ቀን ከአንድ ጓደኛው ጋር ይመጣ እና ግቢ ሳይገባ ውጪ ቆሞ ነበር በአጋጣሚ እኔ ሻይ ልጠጣ ወጣሁ ተገናኘን ሰላም ተባባልን ሀጂ ተስፋዬ አለኝ አቤት አልኩት አንተ እንኳን ጥሩ ሰው ነበርክ ሀጂ እና ኡምራ በምትሰራበት ጊዜ አሁን እዚህ ሆነህ የእናንተ ሰዎች የሚወስዱትን እርምጃ ምን አለ ተው ብትላቸው ብሎ በግል ጠየቀኝ አይ እኔ ምን አቅም አለኝ ታዛኝ ነኝ ይሄን ተው ለማለት የታዘዝኩትን መፈፀም ነው ብዬ ያው በሰላማዊ ንግግር ተለያየን ከእዚያ በኋላ ይሄ እንቅስቃሴ የተማሪዎቹ ተቃውሞ እንቅስቃሴ እየቀጠለ ሄዶ ያው ጁማ ጁማ ቀን ማለት አርብ ቀን ማለት ነው በየሣምንቱ እዚያ ውስጥ ብዙ ሰው ከየክፍለ ከተማው ከሌላውም ቦታ እየመጣ ስግደት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ተቃውሞ ለማሰማት አንድ ቀን አንወጣም ብለው እዚያ ውስጥ ማደር ተጀመረ ከእዚህ አንቅስቃሴ በኋላ ነው አቡበከርም አመዲንም ያሲንም እንግዲህ እዚያ ውስጥ አይደሉም ስራቸውም ኑሯቸውም ውጪ ነው ግን ያው በሙስሊምነታቸው እኔ ሳስብ ይሄንን እቅስቃሴ ለመምራት ይመስለኛል አርብ አርብ እየመጡ መድረክ መምራት የጀመሩት በእዚህ መልኩ ነው አቡበከርን የማውቀው እና ይሄንን መድረክ ከሚመሩት ሰዎች የመጀመሪያው ሰው አቡበከር ነው 2ኛው አመዲን ነው 3ኛው ያሲን ኑሩ እና
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እዚህ ጋር አቡበከር አህመድ አሁን እንዳሉት የግልፅነት እንዳለ ሆኖ ነገር አንወጣም በማለት ማደር ጀምረው ነበረ በሣምንቱ ይሄንኑ [illegible] ለመፈፀም ይመጡ እና

1197

http://ethcriminalawnetwork.com/

መድረክ ይመሩ ነበር ብለዋል ስለዚህ እስቲ አቡበከር ላይ ምንድን ነው ከእዚህ በኋላ ምን ነበር የነበረው ሁኔታ አጠቃላይ ሂደቱ ምን ይመስል ነበር ?

- እነ አቡበከር ከእዚህ ግቢ አንወጣም ብለዋል አላለም ምስክሩ ስለዚህ ዐቃቤ ሕጉ እራሳቸው እየተናገሩ ነው ያሉት እና ምስክሩ ያላለውን ነው እያሉ ያሉት የተከበረው ፍ/ቤት ይሰረዝልን ጥያቄውም ይሰረዝልን እንዳይመዘገብብን የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከበረው ፍ/ቤት ለእዚህ የምሰጠው መልስ አለ ምንድን ነው አሁን በዝርዝር ሲገልፁዋቸው ማለት ነው እውቀታቸው እና ግንታቸው መቼ እንደነበረ ከገለፁ በኋላ ይሄንን መድረክ ለመምራት በጁማ ቀን አርብ አርብ ተቃውሞ ለማሰማት ከእዚያም እንደገና አንወጣም ብለው ማደር ሲጀምሩ እያሉ ነው በዝርዝር የገለፁት አሁን የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም እንደተገለፀው እያስጨረስን ለመሄድ ሲባል የ ነኛ ተከሣሽ ድርሻ እዚህ ውስጥ ያላቸው አካሄዳቸው የሁሉም አንድ ሆኖ ግን የነኛ ተከሣሽ ድርሻ በሚመለከት ምን ነበር ፓርስፔሽኑ አንድ እንዲህ እያልን ለመምጣት ነው ስለዚህ ሲጠቃለል ግን ገልፀውታል ማለት ነው እንጂ የተለየ የሚሰረዝበት ምንም ዓይነት የሕግ መሠረት የለውም
- ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል ምስክሩ ሲመሰክር ተማሪዎቹ ያው ቀኑን ጠቅሰዋል በ 2004 ዓ.ም በአወሊያ መስኪድ ረብሻ ያነሱ ነበር ይሄ ረብሻ አርብ አርብ ይቀጥላል አቡበከር አህመድ እና ያሲን ይመጡ ጀመሩ ከእዚያ በኋላ ይሄንን ሊያስተባብሉ ይመስለኛል አንወጣም አሉ የሚለው ነገር አለ ነገር ግን አንወጣም የተባለው ተማሪዎች ይሁኑ እነ አቡበከር ግልፅ አይደለም እዚህ ፖይንት ላይ ስለዚህ ዐቃቤ ሕጉ ይሄንን ጭብጥ ይዞ ያው ረብሻ ተጀምሯል አቡበከር አህመድ እና ያሲን መጥቷል ይሄንን ሊያስተባብሩ ይመስለኛል ብለዋል እና በእዚህ ድርጊት ውስጥ የአቡበከር ድርሻ ምን ነበር ብለው ጠይቀው መቀጠል ይችላል ነገር ግን አንወጣም ያለው ክለ.ር አይደለም
- የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ ከእዚሁ የአሁን ምስክር አቶ ሀጂ ተሰፋዬ ከእዚሁ በመነሳት የአቡበከር ድርሻ እና አንወጣም ያሉበትን ይሄንን አጠቃላይ ይዘት በሚያውቁት ያው አንዲገልፁልን እንጠይቃለን ?
- እንግዲህ እኔ ስገልፅ ቅድምም አንወጣም ያሉት ያው ተማሪዎቹ እዚያው ግቢ ውስጥ ነበሩ ተማሪዎች ስንል ከኪጂ እስከ 12ኛ ክፍል ነው ፕላስ ኮሌጅም አሉ የተወሰኑ ተማሪዎች የተወሰኑ በቁጥር 36 የሚሆኑ የአረብኛ ተማሪዎች አሉ መጀመሪያ 36 የአረብኛ ቋንቋ ተማሪዎች እዚያ

1197

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እያደሩ ማለት ይሄንን ነገር የተጀመረው በእነዚህ ነው በእነዚህ ተማሪዎች ነው መጀመሪያ እነዚህን ተማሪዎች የሚመሩት የተማሪዎቹ ካውንስሎች ናቸው የእነዚህ ተማሪዎች ካውንስል ደግሞ ቅድም እንዳልኩት ተማሪ ሙባረክ አደም ነው ሌሎችም አሉ በእነሱ ነው የተጀመረው አንወጣም ተብሎ ለስግደት የመጣው ምዕመናን ሰጋጁ ከእነሱ ጋር ሆኖ አንወጣም ያለው ምዕመናኑ ነው እነሱን አላየሁም አንወጣም ሲሉ እነ አቡበከርን ግን ይሄንን ነገር ለማስተባበል የጀመሩት ከእዚያ በኋላ ነው ነው ለማስተባበል በየሚዲያው ይመጣሉ መድረኩን ይይዛሉ እዚያ ላይ

- /ግልፅ ያልሆነ/ ቀኑን ያስታውሳሉ እነ አቡበከር መጥተው ማስተባበል ጀመሩ ብለዋል እና የጀመሩበትን ቀን ካስታወሱ ወሩን ?
- ጥር ውስጥ ነው
- ጥር ወር ?
- አዎ
- ዓ.ም ?
- 2004
- ምን ምን ብለው እንዳስተባበሩ ?
- እንግዲህ የተነሱ 3 መሠረታዊ ጥያቄዎች ነበሩ በወቅቱ 3 መሠረታዊ ጥያቄዎች 1ኛ መጅሊስ ከአወሊያ ላይ እጁን ያንሳ የመጅሊስ ሠራተኞች ከእዚህ በአወሊያ ግቢ እንዲወጡልን የሚል ነው 1ኛው 2ኛው ያልመረጥነው መጅሊስ አይመራንም ይልቀቅልን ለፍርድ ይቅረብልን የሚል ነው 3ኛው አባሽ የሚባል አዲስ እምነት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አባሽ
- አባሽ ?
- አዎ የሚባል አዲስ እምነት መጅሊሱ አምጥቶብናል ይሄንን እንዳመጣ ወደአመጣበት ይመለስ የሚል እነዚህ 3 መሠረታዊ ጥያቄዎች ናቸው እነሱ የነበሩት እና እነሱም መድረክ ይዘው ማስተባበል ሲጀምሩ ይሄንኑ 3 መሠረታዊ ጥያቄ በማጠናከር ነው
- እነሱ ማለት
- እነ አህመድ እነ አቡበከር አህመድ መድረክ

1199

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- እነ አቡበከር እየጠቀሰ ነው ጅምር በቀጠሉት እነ አቡበከር አህመድ ብለዋል ?
- አዎ
- ሌላ ማን ነው ?
- አቡበከር አህመድ ያሲን ኑሩ አህመዲን ጀባል የተማሪዎቹን እንቅስቃሴ ከእዚያ በፊት መድረክ ይዞ ይመራ የነበረው ቅድም ተናግሬአለሁ ሙባረክ ነው ሙባረክ አደም ይሄንን መድረክ በማመቻቸትም ያው ፋሲሊቴት የሚያደርገው ሙባረክ ነው በተማሪዎቹ እነሱ ደግሞ ይሄ መድረክ ሲይዙ ይሄንኑ አሁን ያልኳቸውን መሠረታዊ ጥያቄዎች በማጠናከር ነው ምዕመናኑን የሚቀሰቅሱት የነበረው ከእዚያ በኋላ እየቀጠለ ሲመጣ እነዚህ ያልመረጥናቸው መጅሊሶች ሊመሩን ስለማይችሉ ይሄ የተሰበሰበው ሙስሊም ሕዝብ የሚመራውን መምረጥ አለበት ብለው የፒቲሽን ፊርማም እንዲፈረም እንዲሰባሰብም በእዚያው መድረክ ላይ የተጀመረው ይሄንን ነው እያጠናከሩ የመጡት ነው እነዚህ መድረክ ይመራሉ ያልኳቸው 3 ሰዎች ከእዚያ ውስጥ አንዳንድ ነገሮች በግል ያሉትን መጥቀስ እችላለሁ ለምሳሌ ያሲን ኑሩ አንድ ጁማ ቀን የአክሱም ሀውልት በድርድር ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ ያልመረጥነው መጅሊስም ወደ ትውልቅ ቀዬው መመለስ አለበት እንግዲህ መድረኩን በሚመሩበት ወቅት አንዳንድ ከማስታውሳቸው ነገሮች ማለት ነው በግል እንደዚህ ዓይነት ፖቴሽን አስቀምጧል አንድ ቀን ያው ተራ በተራ ነው መድረኩን የሚመሩት
- እዚህ ጋር በማያያዝ አሁን የእያንዳንዳቸው ተሳትፎ ተገልፀዋል እስቲ ስለጀማል ያሲን ምን ነበር የሚያደርገው የሚያስታውሱትን አጠቃላይ በዝርዝር እና ይሄ ደግሞ የተጀመረው ከጥር ጅምሮ አጠቃላይ የነበረው ሂደት ቀጣይነት ነበረው ብለዋል እና እስከ መቼ ድረስ እንደነበረ ምን እንደነበረ በእዚያ ሂደት ውስጥ ሲደረግ የነበረውን ያው እሱን እንዲገልፀው ነው የምጠይቀው ?
- ጀማል ያሲን እኔ ምክትል ሰራ አስኪያጅ ሆኜ ወደ እዚያ ስመደብ ቀደም ሲል የለቀቀው የተቋሙ ሰራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ኃላፊ ነበር እዚያው ነው ያገኘሁት ከእዚያ በኋላ እኔ ስሄድ ያው በነበረው ስነ ምግባር እና ባለው ሙያ ከእዚያ ከጽ/ቤት ኃላፊነት አንሰቼ የቁራን ማዕከል የሚባል አለ ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ስላለው የእዚያ የቁራን ማዕከል ኃላፊ አድርጌ መድቤው ነበር ምክንያቱም የተቋሙ ሠራተኛ ነው እና እንደዚያ ሆኖ እያለ በእዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ አንዳንዳ

1200

http://ethcriminalawnetwork.com/

ቀን አርብ ሰላት በምንሰግድበት ቀን ማለት ነው ሰላቱ ከመድረሱ በፊት ያው ዳዋ የምንለው ትምህርት የምንለው ነገር አለ እየተነሳ ያው ትምህርት ይሰጣል ትምህርት ይሰጣል ይሄንን ትምህርት እየሰጠ ይሄ እንቅስቃሴ ሲጀመር ከእነዚህ ጋር መሆኑን ስላወኩኝ በግል አማከርኩት ጀማል ለምን ይሄንን አትተውም ይሄንን እንቅስቃሴ አንተ አንደኛ የእዚህ ተቋም ሠራተኛ ነህ ለምን አተውም ብዬ እዚያው ግቢ ውስጥ ቢሮ በር ላይ ቆመን ሳማክረው አይ አልተውም ይሄ የሕዝብ አማና ነው የሕዝበ ሙስሊሙ አማና ነው እንዴት እንደዚህ ትለኛለህ ብሎኛል ይሄንን ካለ በኋላም እምነት ቃልኪዳን እንደማለት ይሆናል ወይም ኃላፊነት መስጠት ብሎኝ ከእዚህ በኋላ እነሱ ቅድም እንዳልኩት ከእዚህ ከተሰበሰበው ሕዝበ ሙስሊም መሀከል ሙስሊሙን የሚመራ መመረጥ አለበት ብለው ይሄንን ተግባር ሲፈፅሙ ከተመረጡት 17ዎቹ አንዱ ሆነው ያው ተመርጠዋል ስለዚህ ይሄንን እንቅስቃሴ ያው ከእነሱ ጋር አባሪ ሆኖ ጉቡዩበል ማለት ነው በእዚያ መልኩ ነው ጀማል ያሲንን የማውቀው ሌላው ከቡር ዐቃቤ ሕግ የጠየቀኝ ጥያቄ እስከ መቼ ነው የገፋው ይሄ እንቅስቃሴ የሚለው ይሄ እንቅስቃሴ እስከ መጨረሻው ነሐሴ ወር መሰለኝ እኔ በአጋጣሚ በዕለቱ የመጨረሻው ሰደቃ ፕሮግራም ተብሎ እዚያ ውስጥ ሙስሊሙ ሲሰባሰብ ሁከት ሲፈጠር ለስራ ጉዳይ ወደ መቀሌ ሄጄ ስለነበረ ነሐሴ 6 ጁማ ቀን ይመስለኛል እስከ እዚያ ድረስ ነው እንቅስቃሴው /ግልፅ ያልሆነ/ የማውቀው

- ዓ.ም ?
- 2004 ነሐሴ በወቅቱ አልነበርኩም ግን እስከእዚያ ድረስ እንቅስቃሴው እንዳለ ያው እዚያው ስለነበርኩኝ አውቃለሁ
- እሺ ምስክር ቅድም በዋና ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ ሲጠይቅህ 36ቱ የአረብኛ ቋንቋ ተማሪዎች አወሊያ የጀመሩት የተፈጠረ አለመግባባት ነበረ ያንን አለመግባባት ተከሳሾች በመሪነት ቀጥለዋል የሚል ነገር ስትናገር ነበር ያ አለመግባባት የተፈጠረው ለምንድን ነው በተማሪዎቹ እና በአወሊያ መካከል ?
- በተማሪዎቹ እና በአወሊያ መካከል ያለመግባባት የተፈጠረው ቅድም እንዳልኩት ጠቅላይ ምክር ቤቱ እራሱ የወሰደው እርምጃ ነበረ ይሄ የወሰደው እርምጃ ምንድን ነው እነዚህ ተማሪዎች የሚማሩት ትክክለኛ የአረቢኛ ቋንቋ አይደለም ሌላም ተጨማሪ ትምህርት አላቸው
- ምንድን ነው ያ ተጨማሪ ትምህርት ?

5



13

1201

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ አቂዳ የሚባል ትምህርት ነው እንግዲህ ደብዳቤው ላይ ደብዳቤው ሲደርሰኝ ደብዳቤው ላይ የሚለው የአረብኛ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን እንትን ብለን ከደረስንበት ካሪኩለማቸው ላይ የዋቢያ አቂዳ ነው የሚማሩት ስለዚህ ይሄ ካሪኩለም በትክክል ተጠንቶ ትክክለኛ የአረቢኛ ቋንቋ መሆኑ ታውቆ
- ዋቢያ ምንድን ነው ?
- እኔ አላውቅም /ግልፅ ያልሆነ/
- የዋቢያን ትምህርትም አብረው ይማሩ ነበረ ?
- አዎ
- ከአረብኛ ቋንቋው በተጨማሪ ብለዋል ?
- አዎ
- ታዲያ ምንድን ነው ችግሩ ከእናንተ አስተዳደር ጋር ያላግባባችሁ ምን ችግር ስላለው ነው ወይስ ምንድን ነው ያወቃችሁት ነገር አለ ?
- እኛ በደረሰን ደብዳቤ መሠረት ተማሪዎቹ ለ ፣ ወር ትምህርታቸውን አቁመው ወደ ቤታቸው ይሂዱ የሚል ነው ይሄንኑ ትዕዛዝ ተፈፃሚ ለማድረግ
- እሱ እናንተ ምክር ቤቱ የወሰነው ይሄ ?
- አዎ
- ለምን ወሰነ ይሄንን ?
- አላውቅም እኔ ለምን እንደወሰነ
- ሰላም ስለነበረ ነው ይሄንን የወሰነው ?
- ሰላም ስለነበረ ሳይሆን እኔ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር ከታህሳስ ወር 2004 ጀምሮ ይሄ እንቅስቃሴ መጀመሩን ገልፀህል አይደለም ?
- አዎ
- እነዚህ ተማሪዎች በወቅቱ ያደርጓቸው የነበሩ ሕገ ወጥ ተግባራት አሉ ?
- መቼ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ምስክር የጠቅላይ ምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ጋር በተያያዘ የሚያውቁትን ያስረዱ ?
- ጠቅላይ ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ ጋር የተያያዘ የማውቀው ነገር አለኝ
- ምንድን ነው ?
- ምንድን ነው ይሄ ነገር ቅድም እንዳልኩት ተማሪዎቹ እንትኑን እየጨመሩ ሄደው
- ምኑን ?
- ሁከቱን ማለት ነው እዚያ ግቢ ውስጥ ስራ አስኪያጅ እንደመሆኔ መጠን በወቅቱ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም ያልኳቸው 3 ጥያቄዎች አላህ ከበር እየተባለ እየተጮኸ ግቢውን እና ቢሮውን ሲያጨናንቁ እንግዲህ ከአቅሜ በላይ ነው እኔ ይሄንን እርምጃ የወሰደው ጠቅላይ ምክር ቤት መጥቶ እንዲያስረዳቸው ጥሪ አቀረቡ
- ከእዚያስ ?
- በእዚህ መሠረት ዋና ፀሐፊው በአቶዝ መኪና መጣ
- ማን ናቸው ?
- ሀጂ አሊ መሐመድ ሲራጅ ይባላል መጣ ያው ቢሮ እኔ ቢሮ በላይ ነው ተሰብስበው የነበሩት ተማሪዎቹ ያለውን ሁኔታ እንዲያስረዳቸው ጋበዝኩት የተወሰነ ነገር አስረድቶ ያው ተማሪዎቹ ሊያስጨርሱት አልቻሉም መሳደብም ነበረ
- ማን ነው የሚሳደበው ?
- እገሌ እገሌ ብዬ መጥቀስ
- ጥሩ ተማሪዎቹ ናቸው ወይስ ?
- ተማሪዎቹ ናቸው
- ተማሪዎቹ ?
- አዎ
- ከእዚያስ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ውጣልን አንፈልግህም ኧንግዲህ ያንን ያው ኧሱ ሲናገር እንደዚሁ በሳቅ ይረበሽ ነበረ በወቅቱ ለምን ትስቁብኛላችሁ የሚል መልስ መልሷል እሱ ከእዚሁ ጋር ተያይዞ ውጣልን በተለይ ሴት ተማሪዎች ከውጪም የመጡ ሴቶች ነበሩ በጣም ይሳደቡ የነበሩት ሴቶች ናቸው ተማሪ ያልሆኑ የአረቢኛ ተማሪዎች ከውጪ እየተመላለሱ የሚማሩ የአረብኛ ተማሪዎች
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ኖ ኖ ከግቢ ውጪ ከግቢ ውጪ እና ይሳደቡ ነበረ ከእዚህ ጋር ተያይዞ በቃ በኋላ ነገሩ እሱንም ንግግሩን ሊያስጨርሱት ባለመቻላቸው ፖሊስ እሱን ይዞ ሲወጣ ይዟት የመጣው መኪና እዚህ ሆስፒታል ጤና ጣቢያ በር ላይ ቆማ ነበረ እሷንም 4ቷንም ጎማ እንትን አድርገው አተንፍሰው ከኋላ ታርጋዋንም እንትን አድርገው
- ምን አደርገው ?
- ገነጣጠሏት እሱን ፖሊስ ነው ይዞ የሄደው መኪና እዚያ እንደቆመች ነው 4ቱም ጎማ ተንፍሶ ታርጋ ተገነጣጥሎ ተበጫጭራ እዚያው እንደቆመች ከሣምንት በኋላ ነው የተነሳችው ጎማ ሁሉም ነገር ተቀይሮላት
- ይሄንን ያደርጉ የነበሩት በወቅቱ ተማሪዎቹ ናቸው ?
- ተማሪዎች ናቸው
- ይሄንን በአወሊያ ት/ቤት ውስጥ የነበረውን የመጀመሪያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የሚመራ የነበረው ማን ነው ?
- ሙባረክ አደም
- 20ኛ ተከሣሽ ?
- በመድረክ አዎ
- ቅድም ስለጀማል ያሲን ሲናገሩ ተው ብዬው ነበር አንተ ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ ብዬ ተው ብዬው ነበረ ብለዋል ?
- አዎ
- እሱ የሰጡት መልስ አለ ?
- አዎ
- እኛ የምንፈልገው ካልሆነ ምን እናደርጋለን አለ ?
- አይ አላለኝም ቅድም ያስቀመጥኳትን ነው ያለኝ የሕዝብ አ[illegible] ነው

1204

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆይ ተቃውሞ ምንድን ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ተቃውሞ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት የተጠየቁት ጥያቄ በመሠረቱ ተመልሷል አሁን መጨረሻ ላይ እራሱ ምስክሩ ቅድም ያልኩትን ነው ያልኩት እያሉ ነው ያሉት
- ያላሉትን ነው እያሉ ያሉት አሁን ቅድም እሳቸው ቅድም ያልኩትን ነው ያልኩት ያሉበት ምክንያት የተከበረው ፍ/ቤት አሁን 2ኛ ጊዜ መደገሙ ነው ፍ/ቤቱን እንዳናሰለች የተከበረው ፍ/ቤት ነኛ እየመሩ ነው የሚጠይቁት 2ኛ እኛ ብዙ ስለሆንን በተደጋጋሚ እየተነሳን ፍ/ቤቱንም ላለማሰልቸት ዐቃቤ ሕጎች አሁን ያላሉትን ጥያቄ መልሰዋል አሁን ይሄ ጥያቄ ሊሰረዝልን ይገባል ነው የምንለው
- የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት ግን በእዚህ ሁኔታ ልንቀጥል ከሆነ እኛ መልስ እንስጥ እና እንቀጥል ከእዚያ መሪ ጥያቄ የሚባለው ምስክሩን ነው አይደለም የሚል መልስ የሚያሰጥ ጥያቄ ነው በሕጉ መሠረት /ግልፅ ያልሆነ/ እኛ ይሄንን ምስክር እየጠየቅን ያለነው ጥያቄ አሁን ነው ወይም አይደለም የሚል መልስ የሚያስመልስ ነው አይደለም ይሄ ነው መመዘን መሪ ጥያቄ ማለት ይሄ ነው እኛ ደገምነው ምክንያት ስላለን ነው ደግመን የጠየቅንበት ምክንያት መምራት ስለማንችል ነው በዋና ጥያቄ ይሄንን የሚቃወሙበት ሕጋዊ መሠረት የላቸውም ጠበቆች ጠበቆች መቃወም የሚችሉት ልክ በስነ ስርዓት ሕጉ 146 በተቀመጠው መልኩ ነው መሪ ጥያቄ ስንጠይቅ ነው አሁን እኛ የጠየቅነው ጥያቄ ይሄ ምስክር ቅድም ጀማልን ተው ስለው ምን አለኝ አለ አማና የሙስሊሙ አማና ስለሆነ ነው አለኝ አለ ባይሆንስ ባይሆንላችሁስ እንደምትሉት ባይሆንላችሁስ ምን ታደርጋላችሁ አለ ነው ያልነው ካወቀ አኬ ይሄንን አውቃለሁ እንዲህ እንዲህ ብሏል ብሎ ይመሰክራል አዎ ወይ አይደለም የሚል መልስ የሚያሰጥ ጥያቄ እስካልሰጠ ድረስ በየጣልቃው እነሱን የሚጎዳ ነገር በተነሳ ቁጥር ጣልቃ እየገቡ ካቋረጡ ችግር ነው
- ግልፅ ነው በተነሳው ጉዳይ ላይ ብይን ሰጥተናል ምስክሩ በፊት የተናገሩት ነገር አለ አሁን የተጠየቀው አሁን መጨረሻ ላይ ዐቃቤ ሕግ የተናገሩት ነው እነሱ የሚፈልጉት ካልሆነ ምን ሊያደርጉ ነው የሚል ነገር ተጠይቆ የቆመው በእዚያ በኩል የተነሳው 2 ነገር አለ ነኛው ምስክሩ ያላሉትን እየጠየቁ ስለሆነ ነው እኔ ያልኩት ብለው ምስክሩ አስተካክለ የሚል አለ 2ኛ ስለዚህ ይሄ ይሰረዝልን የሚል ነገር ነው በእዚያ በኩል የተነሳው ይሄ እኛ አንድ በአንድ እየመዘገብን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ነው የምንሄደው ክርክሩን ለመምራትም ለማስተናገድም ለፋይሉ የሚሆነው እየተመዘገበ ነው በሪከርድ ማሽን ነገር ግን እኛ ለእኛ ኮንስፕሽን እየመዘገብን ነው አሁን የተነሳው ጉዳይ ላይ ምስክሩ ያላሉትን አልተጠየቁም ያው መልሰዋል ተጠይቆ ከእዚያ በኋላ ወዴት ሊኬድ እንደተፈለገ ከእዚያ በኋላ የፈለጉት ነገር ካልሆነስ ምን ይሆናል የሚለው ተቃውሞአችሁ ግልፅ አይደለም መሪ ነው የሚል ነው ደግሚል ስለዚህ አንድ መሪ አይደለም ይሄ ያላሉት ካልተፈፀመ ምን ይሆናል ዚስ አፕን መሪ የሚባለው እኮ አንድ እና ሁለት ተደምሮ የሚቀመጥ አይደለም ነገር ግን መልሱን ሳጀስት የሚያደርግ ጥያቄ ነው መሪ የሚባለው /ግልፅ ያልሆነ/ እዚህ ላይ የለም እሱ እሱ በፊት ምስክሩ የተናገሩት ነው የመስሊሙ አማና ነው እና አልተውም ብሎኛል አለ ያ ካልሆነስ ምን ይሆናል የሚለው ነገር ሰፊ ስለሆነ መልሱን የሚያመላክት አይደለም እና መሪ አይደለም በእዚያ መሠረት ግልፅ የሆነ ነገር ወጣ ያለ ነገር ካልታየ እያንዳንዱ ከሰንድ ላይ ጣልቃ ባትገቡ ቀጥል

- እሺ ምስክር ይቀጥሉ አሁን በጠቀሱት መልኩ ጀማል ያሲንን 19ኛ ተከሣሽን ለምን ይሄንን እንቅስቃሴ አታቆምም ለምን አተውም ሲሉት የመስሊሙ አማና ነው አልተውም አለኝ ብለዋል ጥያቄአቸውን ደግሞ ቅድም በዋና ጥያቄ ገልፀዋል እርሶ መጅሊስ ይወገድልን አባሽ ይወገድልን እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አሁን እኛ የምንፈለገው ካልሆነ ምን እናደርጋለን አለ ?
- እንግዲህ ይሄንን ሳማክረው አይ ይሄ የሙስሊሙ አማና ነው እንዴት አድርጌ እተዋለሁ ነው ያለኝ ከእዚያ በኋላ ካልተውክ ምን ታደርጋለህ ብዬ አልጠየኩትም ነገር ግን አልተውም ሲል ፍፃሜው ምን እንደሆነ እና እስከ ምን እንደሆነ ይታወቃል ይሄ ምንድን ነው እነዚህ 3 ጥያቄዎች ካልተመለሱልን እንቀጥልበታለን ነው .
- እንዴት በምን መልኩ ?
- በተያዘው መልኩ
- በምን እኮ የያዘው ምንድን ነው ይበሉት ይግለፁት እኛ ስለምንፈልገው ነው እርሶ አሁን ያውቁታል ለእዚያ ነው ?
- ኖ አይደለም
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መጨረሻው መጅሊስ ይውረድልን ከአወሊያም ይውጣልን አባሽ የተባለውም ከሀገራችን ይውጣልን ነው ጥያቄው ይሄ 3ቱ ጥያቄ ተፈፃሚ እስከሚሆን ድረስ ጨኸቱንም በየሳምንቱ

1206

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የተያዘውን ፕሮግራም እንቀጥላለን ነው እንግዲህ እኔ ስረዳው ግን እንደዚህ በሉ ዘርዝሮ የሰጠኝ ነገር የለም አልተውም ስል ግን ያንን የጠየቁትን ጥያቄ እስከሚፈፀም ድረስ የያዙትን ነገር ተግባራዊ እያደረጉ እንደሚቀጥሉ ነው በእኔ ስሜት የተረዳሁት

- ግምት ማለት ነው ?
- የራሴ አረዳድ
- ምስክር ቅድም 17 ኮሚቴ እያሉ ደጋግመው ሲጠቅሱት የነበረው ነገር አለ ከእዚህ ውስጥ 17 ኮሚቴ አባል የሆኑ ሰዎችን እስቲ በስም ይንገሩን ?
- 17 የሆኑ ሰዎችን
- አሁን እዚህ ውስጥ ካሉ የ 17 ኮሚቴ አባላት
- የማስታውሰውን በቃሌ ልናገር ምንም ችግር የለውም
- እስቲ ከእዚያ በፊት ኮሚቴው ያሉት እንዴት ለምን እንደተቋቋመ አጠር አድርገው እሷን ስለ ኮሚቴ አባላት ከመናገርዎ በፊት ይሄ 17 ኮሚቴ ለምን ተመሰረተ እሷን ?
- በወቅቱ የደሰኝ የያዝኩት የእነሱ ወረቀት የመስሊሙ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ነው የመስሊሙ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ
- ቀጥሉ
- ነኛ አቡበከር አህመድ ነው ያሲን ኑሩ አመዲን ጀባል መከተ ሙሄ ካሚል ሸምሱ ጀማል ያሲን ኑሪ ከማል
- የእዚህ ኮሚቴ አላማዎች ምንድን ነበሩ ?
- እንዴት
- ምንን ለማስፈፀም ነው ይሄ ኮሚቴ የተዋቀረው ?
- በቃ መጀመሪያ የተነሱትን ጥያቄዎች ተግባራዊ ለማድረግ እና ያው ያለው የነበረው መጅሊስ በሕዝበ ሙስሊሙ ያልተመረጠ ስለሆነ በያዙት እንትን ይሄ ፒቲሽንም በማስፈረም በያዙትም መድረክ አካሄድ ሙስሊሙን የሚመራ ኮሚቴ ለመምረጥ እነዚህን ጥያቄዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ
- በማን እውቅና ነው የተቋቋመው ይሄ ኮሚቴ ?
- እሱን ምንም አላውቅም
- እርሶ የጠቅላይ ምክር ቤቱ መዋቅር ውስጥ ያሉ ሰው ኖት አይደለም ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ጠቅላይ ምክር ቤቱ ፍቃድ ሰጥቷል ?
- አልሰጠም
- ሌላው ተማሪዎች እዚያ ውስጥ ይቆዩ ነበር ያድሩ ነበር ብለዋል ሌሎችም ሰዎች ይመጡ ነበር በየጁማ ብለዋል ምግብ ከየት ነው የሚያመጡት ?
- እንግዲህ ከውጪ ሰል ያው ከእዚያ ከአወሊያ ተቋም
- ምግብ እና ተያይዘው ያሉ ወጪዎችን ?
- ከግቢ ውጪ ነው ከእዚያም አልፎ ከክልልም በፈሰ ቡክ በሞባይል ኤስኤምኤስ በበራሪ ወረቀቶችም ይጠራል ለእኛም ይደርሳል ለእኔም ይደርሰኛል በየጊዜው
- ምን የሚል ነው ?
- የሚቀጥለው ጁማ ጥያቄአችን ለማስፈፀም ጁማ ሰላት አወሊያ እንድትገኙ ይላል በእዚህ መልኩ ነው ሰው እየተሰባሰበ ቁጥሩ እየበዛ የመጣው ምግብ ያገኙ የነበሩት
- ሰው ይመጣል ገንዘቡን ከየት ያገኛሉ ታዲያ ሰው መጣ ማለት ገንዘብ ነው እንዴ ?
- ወደ እዚያ እየሄድኩ ነው ምግብ ያገኙ የነበሩት በወቅቱ እዚያ ውስጥ ያድሩ በነበረ ጊዜ የገንዘብ መዋጮ ተደርጓል እዚያው ገንዘብ ማሰባሰብ ስራ አካሂደው ከ ነዐዐ ሺህ ብር በላይ ሰብስበዋል
- ማን ሰበሰበ ?
- ከምዕመናኑ ያው ኮሚቴው
- ኮሚቴው ነው የሰበሰበው ?
- አዎ ኮሚቴው ነው የሰበሰበው ገንዘቡ የነበረው ተማሪዎች ካውንስል እጅ ነው እነ ሙባረክ ጋር ማለት ነው
- በአንድ ቀን ነው ነዐዐ ሺህ ብር የተሰበሰበው ?
- አዎ በአንድ ቀን ነው የተሰበሰበው
- አወሊያ ዘበኞች አሉት አይደለ ?
- አዎ
- እነዚህ ዘበኞች ላይ የደረሰ ነገር የሚያውቁት ነገር አለ ?
- የተደበደበ ዘበኛ አለ ሆስፒታል አስተኝተን አሳክመን ያወጣነው ዘበኛ አለ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለምንድን ነው እንዴት ነው እስቲ ዝርዝር ሁኔታውን ይንገሩን ?
- እኔ እሱ ላይ ለምን እንደተደበደበ አላውቅም መደብደቡን እና ከተጎዳ በኋላ ሆስፒታል
- ማን ነው ደብዳቢው ዱርዬ ነው ?
- ተማሪዎች
- ተማሪዎች ?
- አዎ
- ስለዚህ እንደዚያ እያሉ ይንገሩን አሁን እርሶ ስለሚያውቁት ሲናገሩ ይገባናል ግን ፍ/ቤት ስለሆነ ዝርዝር ነገሩን ይንገሩን ?
- ተማሪዎች ናቸው የደበደቡት
- ለምንድን ነው ?
- ልቀቁት ግቢውን እኛ እንጠብቃለን
- ግቢውን ልቀቁ ብለው ነው ?
- አዎ
- ጥሩ ይሄ እንቅስቃሴ እርሶ በገለፁት ከግምት ከታህሳስ 2004 ጀምሮ ቀጥሎ እስከ ሐምሌ ቅድም እንዳሉት እስከ ሐምሌ 2004 ቀጥሏል እስቲ ሐምሌ ላይ የተፈፀመ ነገር አለ ?
- ሐምሌ 8 እዚህ እያለሁ ማለት ነው ቢሮ ስራ ላይ እያለሁ
- /ግልፅ ያልሆነ/ እስከ ነሐሴ ቀጥሏል ነው ያሉት ምስክሩ ያላሉት ቀጥሏል ማለት እኮ መንገር ነው የተከበረው ይሄማ አሁን ግልፅ ወጣ ማለት ነው የተከበረው ፍ/ቤት እና እስከ ነሐሴ ቀጥሏል ቀጥሏል ና ነሐሴ የሆነውን ንገሩን ሊሉ አይችሉም የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ፊት ለፊት በሕጉ በተቀመጠው መሪ ጥያቄ ነው እስከ ነሐሴ ቀጥሏል ብለው አልመሰከሩም ምስክሩ
- የተከበረው ፍ/ቤት ሐምሌ ላይ የተፈፀመውን ነገር ንገሩን ማለት መሪ ጥያቄ ከሆነ መሪ ጥያቄ ምናልባት ለተከበሩ የጠበቆች ፍጆታም ከዋለ ምናልባት ምሳሌ ሊሆን የሚችለው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ብናደርግ ይሄ መቃወሚያ አይመጣም የተከበረው ፍ/ቤት ለእዚያ እኮ ነው ጥሩ እኛ እንግዲህ መሪ ጥያቄ ማለት ምናልባት እኔ አሁን ምስክሩን ሙባረክ እንዲህ እንዲህ አድርጓል አይደለም ብዬ ብጠይቅ መሪ ጥያቄ ነው አዎ አይደለም ነው መልሱ ሙባረክ ቁይ ልብስ ለብሶ ነበር በዕለቱ አይደለም ብዬ ብጠይቅ ይሄ አዎ ወይ አይደለም ነው ይሄ ነው መሪ ጥያቄ ማለት

1209

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሐምሌ ላይ የተፈፀመ ሐምሌ እለ ምስክሩ ከጥር ጀምሮ እስከ ሐምሌ ቀጥሏል አለ ሐምሌ ላይ የተፈፀመው እስቲ አሁን ጥር ላይ እና ቀጥሎ ያሉትን ነገረን መጣን ሐምሌ ደግሞ እስቲ የተፈፀመውን ንገረን ማለት ምስክሩ ቀደም ብሎ የተናገረው ነገር ነው እና ምኑ ነው ችግሩ እኔ አልገባኝም

- ብይን ተሰጥቷል አሁንም ምስክሩ ቅድም ሲመሰክሩ እኔ መቀሌ እያለሁ እስከ ነሐሴ 6 ወይም 9 ቀጥሏል ድርጅቱ እዚያ ሆነው እስከ ነሐሴ 6 ወይም 9/2004 ድርጊቱ ቀጥሏል ሲል ነበር በፊት ገና ሲጀምሩ እራሱ ሲመሰክሩ እና ከእዚህ ሁሉ ጋፕ የሐምሌ የተፈፀመውን ድርጊት ንገረን ማለት መሪ አይደለም ስለዚህ ጥያቄው ይቀጥል ተብሏል
- ምስክር ይቀጥሉ ሐምሌ 2004 ዓ.ም ተፈፀመ የሚሉትን ነገር እስቲ በዝርዝር ያስረዱን ?
- እንግዲህ ቅድምም ተናግሬ ነበር እኔ በወቅቱ ከመሄዴ በፊት ቢሮ ስራ ላይ እያለሁ የተበተኑ ወረቀቶች ነበሩ
- ምን የሚሉ ?
- በእጄ የገቡ
- ምን የሚሉ ?
- እነዚህ ወረቀቶች ምን ይላሉ ሐምሌ 8 ቀን በአወሊያ ቅጥር ግቢ አጠቃላይ የሰደቃ ፕሮግራም ስለምናደርግ በእዚያ ፕሮግራም ላይ እንድትገኙ የሚል ይኤስኤምኤስም በበራሪ ወረቀትም ደርሶኛል ቢሮ ላይ እያለሁ ማለት ነው አጋጣሚ ሆኖ እኔ ሐምሌ 6 የለሁም ነበር ሐምሌ 4 ነው ከአዲስ አበባ የወጣሁት መቀሌ ለስራ ጉዳይ ሄጄአለሁ መቀሌ ሆኜ ሐምሌ 6 ቀን ያን የ 8ቱን የሐምሌ 8ቱን ፕሮግራም ለማስፈፀም ጁማ ሰላት ጀምሮ ከእዚያው ጋር በተያያዘ ለዱንካን መጣያ እንጨት ሲገባ ሌሎች ሌሎች ነገሮች ሲገቡ ዝግጅቱን ሲጀምሩ በተከሰተው ነገር ላይ እዚያ ሆኜ የሰማሁት ድርጊቱን ነው የለሁም በቦታው
- ምን ሰሙ ምን ተፈጠረ ተባለ ?
- አወሊያ ላይ ድንኳን እየተተከለ ስጋ በሬ እየገባ ችግር ተፈጥሮ ይኸው አወሊያ ሰዎች መስኪድ ላይ ተያዙ የሚል ከቢሮም ተደውሎልኛል ከጓደኞቼም ተደውሎልኛል የሰሁት ይሄንን ነው ከእዚያ በኋላ ከ 4 ነው 5 ቀን በኋላ ነው እኔ ተመልሼ ወደ አዲስ አበባ የገባሁት ስራዬን ጨርሼ የሄድኩበትን ወደ አዲስ አበባ ገብቼ ለስራዬ ወደ ቢሮ ስገባ ያገኘሁት ግቢው ተለውጦ ነው ተለውጦ ሲባል ሜዳ አለ ከመስኪዱ ፊት ለፊት ያ ሁሉ ባህርዛፍ ለዱንካን መጣያ ባህር

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ዛፍ ቆሞ ማገር ተማግሮ ሞልቶ ነው ያገኘሁት ሌላ መስኪድ በር ላይ ቀበሮ ሳሚማ ተከማችቶ ነው ያገኘሁት ሁኔታውን ያው እንግዲህ ይመለከተኛል ለመረዳት በምሞክርበት ጊዜ ያው ሰዎች ከመስኪድ ከግቢ ውስጥም ተይዘው እንደታሰሩ የሰማሁት በመስማት ነው ይሄንን አሁን በምላቸው ነገሮች ጠይቄ በመረዳት ነው እንጂ ድርጊቱ ሲፈፀም አልነበርኩም ብዬ ቅድምም ገልጬአለሁ ይሄ ሐምሌ ወር ነው ከእዚያም በኋላ ያው ድርጊቱ መስኪዱ ተዘግቷል ከእዚያ በኋላ አሁን ቅርብ ጊዜ ነው የተከፈተው የማውቀው እስከእዚህ ድረስ ነው

- ቅድም ጥሪዎች ይደርሱኝ ነበረ የሰደቃ ፕሮግራም ላይ እንድትገኙ የሚል ቀን እየጠቀሱ ሐምሌ 8 ፕሮግራም አለ እንዲህ እያሉ መስክረዋል የእነዚህ የሰደቃ ፕሮግራሞች ዓላማ ምን ነበር ለምንድን ነው የኮሚቴው አባሎች የሚፈልጓቸው ይሄንን የሰደቃ ፕሮግራሙን ?
- እንግዲህ ይሄንን እነሱ የሚፈልጉት ያው ለያዙት ዓላማ ማጠቃለያ ሲተገብሩ የነበረውን ማጠቃለያ አድርገው እዚያ ላይ ውሣኔ ሊወስኑ ይመስለኛል የመጨረሻ ውሣኔ እኔ ስረዳው እንጂ እዚያ ላይ እንደዚህ ነው ብሎ አይጠቅስም ለምሳሌ የደረሰኝ በራሪ ወረቀት ላይ
- ጥሩ አዎ አይጠቅስም ልክ ነው
- አይጠቅስም አሁን የሚሉትን
- ማጠቃለያ ይላል ግን
- እርሶ የሚሉትን ውሣኔ ሰደቃ ሳይጠሩስ መወሰን አይችሉም ለምን ፈለጉት ሰደቃውን ?
- ሕዝቡ እንዲሰባሰብ
- ዋና ጥያቄ አበቃን
- የተከበረው ፍ/ቤት ዋና ጥያቄአችን እንቀጥላለን ሀጂ ተሰፋዬ ከታህሳስ ወር ጀምሮ በየሣምንቱ አርብ የሚደረግ እንቅስቃሴ አለ ብለዋል ይሄ እንቅስቃሴ በምን መልኩ ነበር ሲካሄድ የነበረው ወይም በእዚህ እንቅስቃሴ ምን ምን ድርጊቶች ይካሄዱ ነበር ?
- ዝርዝር ነገሩ ያው የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች በተነሱት 3 መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ይሄ እዚህ የሚሰባሰበው ሙስሊም ተጠናክሮ ይሄንን ማስፈፀም መቻል አለበት የሚል ነው ወደ /ግለፅ ያልሆነ/ ምርጫ እንዴት እንደሚሄዱ የመግለፅ ነው የነበረው እንቅስቃሴ
- በየሣምንቱ እርሶ ይከታተሉ ነበር ?
- እኔ በየሣምንቱ እከታተላለሁ የማልከታተልበት ቀንም አለ
- ቢሮዎት እዚያ ነው አይደል ?

ECLN

http://ethiopianlawnetwork.com/

- ቢሮዬ እዚያው ነው መስኪዱ አጠገብ
- እነዚህ እንቅስቃሴዎችን አሁን ማጠቃለያ ወይም የእርሶን ግምት ሳይሆን የሚነግሩን በተከሣሾች ሲፈፀሙ የነበሩት ነገሮችን ለፍ/ቤቱ እንዲናገሩ ነው የምንፈልገው ለምሳሌ በስም የጠቀሷቸው ተከሣሾች አሉ ሙባረክ አደም ምን ምን ሲል ነበር ያስተባብር ነበር ብለዋል ቅድም ተማሪዎችን ያሰባስብ ነበር ካውንስልም ነበር ይመራ ነበር ብለዋል ምን ምን ቃል ነበር የሚናገረው እንዴት ነበር ይመራ የነበረው እንደዚሁም የሌሎቹን እያንዳንዱ ተከሣሽ ምን ያደርግ ነበር ይሄንን በወቅቱ የተናገሩትን ወይም ያደረጉትን /ግልፅ ያልሆነ/
- እንግዲህ ሙባረክ አደም ያው ነኛ የተማሪ ካውንስል ነው 2ኛ ይሄንን መድረክ ሲመራ በመፈክር ተማሪውን ይቀሰቅሳል
- ምን ምን ነበረ መፈክሮቹ ?
- መፈክሮቹ ያው ቅድም የጠቀስኳቸው መጅሊስ ላይ ያነጣጠረ ነው
- እሰቲ
- አወሊያ ነፃ ትሁን የታገዱ ሰዎች ማለት የታገዱ ተማሪዎቻችን ወደ ትምህርታቸው ይመለሱ የታገዱ ሰዎች ነበሩ በወቅቱ ጠቅላይ ምክር ቤቱ የወሰደው እርምጃ የታገዱ ከኮሌጅ የታገዱ ሰዎች ነበሩ ከግቢውም መመህራኖችም ነበሩ ይሄ ነገር የተነሳበት መንስኤ አንዱ የአረቢኛ ተማሪዎችን
- እሱን ገልፀውታል አሁን መፈክሮቹ ምን ምን ይሉ ነበር ለምሳሌ ከአረብኛ ትምህርት ጋር ተያይዞ ምን ሆነ ነው የሚሉት አረብኛ ትምህርት ምን ተደረገ ነበር የሚሉት የነበረው ?
- የአረብኛ ትምህርት እንዲህ ተደረገ የሚል ሳይሆን ተማሪዎቹ ያቆሙ ተማሪዎች
- እናልፈዋለን ይሄንን ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤት
- ሀጂ ተስፋዬ መጀመሪያ ላይ ወደ እርሶ ቀርበው ጥያቄ እንዳቀረቡ ገልፀዋል አይደል ?
- አዎ
- ምን አደረጉ ያኔ ?
- ማን
- እርሶ ምን አደረጉ ወይም ከተማሪዎች ጋር የተደረገ ይሄንን ጥያቄ ሲያቀርብሎት እርሶ ምን አሉ በምን ሂደት ነበር የቀጠላችሁት ችግሩን ለመፍታት ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ቅድም ፍ/ቤቱ ጭብጡን ለይቶ በክሱ ላይ የተገለፀዉ ነገሮች መሆናቸውን አስቀምጧል ዐቃቤ ሕግም በእዚያ መልክ እንዲያስመሰክር ነው የተባለው ተማሪዎቹ ስላነሱት ተቃውሞ እና በት/ቤት ውስጥ ስለተሰጣቸው መልስ የክስ ምክንያት አያደለም የክርክር ምክንያት አይደለም አልተከሰሱም በእዚህ ጉዳይ አሁን እሳቸው እንደተምህርት ቤቱ ሰራ አስኪያጅነታቸው ለተማሪዎቹ ጥያቄ ምንም ምላሽ ሰጡ የሚለው ነገር የክስ ምክንያት ስላልሆነ እሳቸው ሊመሰክሩ አይገባም ጭብጥም አይደለም የእሳቸው 20ኛ ተከሣሽ ናቸው ስለ መባረክ ነው እየተጠየቀ ያለው የ 20ኛ ተከሣሽ ድርጊት ተበሎ በዐቃቤ ሕግ የተገለፀው ነገር ከእዚህ ጋር ምንም አይገናኝም ስለዚህ ከጭብጡ ውጪ ስለሆነ ጥያቄው እራሱ ሊቆም ይገባል
- በተጨማሪ የተከበረው ፍ/ቤት ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙ ወገኖች ማሳሰቢያ በሰጠበት ጊዜ ምስክርን ልናከብር ይገባል ከመሰከረው ውጪ ልናስጨንቀውም አይገባም ነው እኔ እንደተረዳሁት ከሚመሰክረው ውጪ የማስጨነቅ ስራ በዐቃቤ ሕግ እየተሰራ ነው እና የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን በእርምት እንዲቆም እንዲደረግልን እናመለክታለን
- መልስ እንሰጣለን የተከበረው ፍ/ቤት አሁን ያቀረብነው ጥያቄ ከክሱ ወይም ከጭብጡ ውጪ ነው የሚል ነው በክሳችንም እንደገለፅነው ወይም ኮሚቴ ወይም ተከሣሾች ይሄንን የተማሪዎች ጥያቄ እንደሸፋን ተጠቅመዋል የሚል ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የሚል ነው ስለሆነም ይሄንኑ በክሳችን ላይ ገልፀናል ከጭብጡ ውጪ የሆነ ጥያቄ አላነሳንም እንደዚሁም ከተማሪዎቹ ተማሪ የነበረ በእንደዚሁም በእዚሁ እንቅስቃሴ ተሳታፊ የሆነ ተከሣሽ አለን በእሱ ላይ ነው እያስመሰክርን ያለነው ሌላው ምስክርን ማስጨነቅ የተባለው ነገር የተከበረው ፍ/ቤት በእኛ በኩል ምስክሩ ተጨነኩ ብሎ አላመለከተም ለችሎቱ የሚያውቀውን ነገር የተዘነጋ ነገር ለማስታወስ ነው የሰጠውን ቃል ለችሎቱ ለፖሊስ የሰጠውን ቃል ለፍ/ቤት እንዲገልፅ ነው እኛ እያደረግን ያለነው ስለሆነም ተቃውሞ ያለአግባብ ነው ጥያቄውም በጭብጡ መሠረት ነው
- ብይን ተሰጥቷል አሁን በተነሳው መቃወሚያ ላይ የቀረበው ጥያቄ እርሶ እንደ ጉዳዩን እንደሚመለከተው ግለሰብ ለተማሪዎቹ ጥያቄ ምን ምላሽ ሰጡ የሚል ነው ጥያቄው በእዚህ ላይ የተነሳው ተቃውሞ ይሄ ለተማሪዎች የተሰጠው ምላሽ ከክሱ ጭብጥ ጋር አይገናኝም የሚል ነው ሌላው ምስክር አስጨንቋል የሚል ነገር ነው የተነሳው ከክሱ ጭብጥ ጋር ዐቃቤ

1213

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሕግ በሰጠው ምላሽ ተከሣሽ እዚህ ውስጥ አለ ጉዳዩን የሚመለከተው ከክሱ ጭብጥ ጋር ይያያዛል ብሏል ምስክርንም አላስጨነቅንም ብሏል ምስክር ማስጨነቅ አለማስጨነቁን በተመለከተ ያው አሁን ፍ/ቤቱ በሚረዳው ምስክሩ የሚያውቀውን ነው የሚጠየቀው የሚያውቀውን ሲጠየቅ አላወቅም ማለት መብቱ ነው የሚያውቀውን እንዲመሰክርም አይፈለግም እውነቱን ብቻ ነው እንዲመሰክር የሚፈለገው እና ስለዚህ በእዚህ አንፃር አስጨንቋል የሚለውን ነገር ፍ/ቤቱ አልታየውም ማስጨነቁ ምስክሩን ማለት ነው ስለዚህ እሱን በእዚህ እናልፋለን ከጭብጥ ጋር ይያያዛል አይያያዝም የሚለውን በተመለከተ ስናይ ግን አሁን የተነሳው 20ኛ ተከሣሽ የተማሪዎች ተወካይ ነው የእዚያ ጥያቄ ካልተመለሰ እንቀጥላለን የሚል በዝርዝር የተመሰከረው ነገር አለ በምስክር መመስከር ያለበት ያው በሕጉ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው ከጭብጡ ጋር የሚያያዝ ሆኖ ነገር ግን ምስክሩ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ስለሚያውቀው ነገር ነው የሚጠየቀው አሁን የተባለው ነገር ምስክሩ በቀጥታ ሊያውቀው ይችላል አኬ ይሄ አንድ ነገር ነው ነገር ግን ከክሱ ጋር ይያያዛል አይያያዝም የሚለውን ስናይ የክሱ መነሻ ሆኖ የተደረገው የተማሪዎች ጥያቄ ነው ወደ እዚህ ያመራው የሚል ነገር አለ በአጠቃላይ አሁን ከምስክሩ የምንረዳው ማለት ነው ካልተመለሰ እንቀጥላለን ጥያቄው ነው የሚል ነገር ስላለ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በክሱ ጋር የሚገናኝ ጥያቄ ስለሆነ ጥያቄው ይቀጥል ተብሏል

- ቀጥሉ
- እኔ የመ/ባረክን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው ክቡር ዐቃቤ ሕግ የጠየቀኝ
- ይቀጥሉ ?
- የመ/ባረክ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመድረክ ቅድም እንዳልኩት በመድረክ ተማሪውን መቀስቀስ ነው ይሄ በመድረክ መቀስቀስ በመፈክር መቀስቀስ ማለት ያው መጅሊስ ይውጣልን እጁን ያንሳልን አወሊያ ነፃ ትሁን የተባረሩ መምህሮቻችንን ወደ ስራ ይመለሱ ያው በጨቨት ይሄንን ያሰማል ባነሮችንም ያዘጋጃል ከሚያዘጋጃቸው ባነሮች መካከል ያው የሚለጠፉ ግርግዳ ላይ የሚለጠፉ ባነሮች ናቸው እነዚህም ያው ይሄንን መልዕክት የሚሰጡ መፈክሮች ናቸው የሚለጠፉት ሌላው አንድ ጁማ ቀን የ 13 ሰዎችን ፎቶ ግራፎ በባነር እንትን ላይ ተለጥፏል ይሄም ያው በተማሪነቱ ሌሎችም አሉ ይሄንን እንቅስቃሴ ተግባራዊ አድርጎ የሚያመቻቸው ያው የመጅሊሶች የመጅሊስ አመራሮች ናቸው እነዚህ ፎቶ ግራፎቸው በባነር የተለጠፈው

1214

http://ethcriminalawnetwork.com/

መጅሊሱን ይልቀቁልን ለፍርድ ይቅረቡልን ይላል እንትኑ እና ፎቶ ግራፋቸው በባነር ተለጥፏል በፌስ ቡክም ተበትኗል ይሄ ስራ እንቅስቃሴ እዚያ ግቢ ውስጥ እንትን የሚያደርገው ያው ሙባረክ ነው ሙባረክ በመሪነት ማለት ነው ሌሎችም ጓደኞቹ አሉ እና ይሄ ማለት ያመቻቻል ማለት ነው መድረክ ያመቻቻል ተማሪዎችን ይቀሰቅሳል በተግባር ያው ቅድም የተናገርኩ የተሰበሰበውንም ገንዘብ እንትን የሚያደርገው በወቅቱ እዚያ ካሉት እኔ ለራሴ መረጃ እንትን እንዳደረኩት ይሄንንም የሚመራው እሱ ነው ከእዚያም ባሻገር ይሄ አወሊያ ውስጥ የሚካሄደው የነበረውን እንቅስቃሴም በመሪነት ሲመሩ የነበሩትን ግቢ ውስጥ ባለው የ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አዳራሽ ውስጥ እኛ በሌለንበት ከእኛ ስራ ቀን ውጪ ማለት ነው ፕሮግራም አዘጋጅተው የሽልማት መሸለም ተግባር ፈፅመዋል ይሄም የተከናወነው ያው በእነሱ በእነ ሙባረክ የተማሪዎቹ ካውንስል ነው እና ይሄ ማለት እንግዲህ ይሄንን እንቅስቃሴ የሚመራው በእዚህ ዓይነት መልኩ ነው ነው ከእዚያ ውጪ ሌላ ነገር /ግልፅ ያልሆነ/

- ቅድም ሲገልፁ ከተከሣሾቹ ውስጥ አህመዲን አውቀዋለሁ ወይም እሱ ላይ እመሰክራለሁ ያሉት ነገር ነበር ከምን ጋር በተያያዘ ነው ምን ሲያደርግ ነው የሚያውቁት ከመቼ ጀምሮ ነው የሚያውቁት አህመዲንን ከእዚያም በፊት አውቀዋለሁ
- ከእዚህ ድርጊት ጋር በተያያዘ ?
- ከእዚህ ድርጊት ጋር በተያያዘ ቅድም እንዳልኩት የተማሪዎቹ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላ ና እዚያ ውስጥ ማደር ከተጀመረ በኋላ ለተወሰነ ቀን አድረው ዲል ተደርጎ ደግሞ ከለቀቁ በኋላ ያው በየሣምንቱ ለመድረክ እንደሚመጣ ነው የማውቀው ሲመጣ ነው የማውቀው አመዲን ጀባል ማንነቱን ከእዚያም በፊት አውቀዋለሁ ግን በእዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ የማውቀው ከእዚህ ከተማሪዎቹ እንቅስቃሴ በኋላ ይሄንን ቅድም የተባለውን ነገሮችን ለመምራት እና ለማመቻቸት ባለመድረክ ሆኖ እንደሚመጣ ነው
- እነዚያን ቅድም የጠቀሷቸውን ጥያቄዎች ለመምራት እና ለማመቻቸት መድረክ እንደሚይዝ ነግረውናል ይሄንን መድረክ ይዞ ወይ የተናገረው ነገር ወይ የቀሰቀሰው ነገር የሚያውቁት ነገር አለ ?
- የማውቀው ያው የሚናገረው የመጅሊስን ተቃውሞ ነው የአባሽን ተቃውሞ ነው ይሄ አንዳንድ ቦታ ላይ ምዕመናን ኢማሞቻችን ከመስኪድ እየተባረሩ ነው ያለአግባብ ነው መጅሊስ ያልተመረጠ መጅሊስ ነው እየመራን ያለ ይሄንን ለማስተካከል እኛ መንቀሳቀስ አለብን የሚል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ንግግር ነው ያው መድረኩን ሲይዝ እንትን የሚለው እና እንደገና ያው ለእዚህ ለተመረጠ ኮሚቴ እንቅስቃሴም የጋራ አንድነትን እንዲመጣ የመቀስቀስ ስራ ነው የሚናገሩ የነበሩ

- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ሀጂ ተስፋዬ አወሊያ ምንድን ነው እርሶ አሁን በስራ አስኪያጅነት እመራዋለሁ እዚያ ት/ቤት ሠራተኛ ነኝ ብለዋል ምንድን ነው አወሊያ ?
- አወሊያ ማለት እንግዲህ እኔ /ግልፅ ያልሆነ/ ማለት በኃላፊነት እዚያ እስከተመደብኩ እስከ ነሐሴ 2003 ጀምሮ ብዬአለሁ ቅድም ከእዚያ ጀምሮ የጠቅላይ ምክር ቤቱ አንድ ተቋም መሆኑን ነው
- ምንድን ነው ተግባሩ ?
- ይሄ ተቋም አወሊያ ማለት በውስጡ 7 የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የያዘ ከአዲስ አበባም ውጪ ሌሎች ፕሮጀክቶችን ያለው እነዚህ 7 ጤናን ትምህርትን ቁርአንን አረብኛ ትምህርትን ወላጅ አልባ ሕፃናት የማሳደግን ጤና ጣቢያን እነዚህን የመሳሰሉ ፕሮጀክቶችን በውስጡ የያዘ አንድ ተቋም ነው
- አንድ ተቋም ነው ?
- እስከተረዳሁት ድረስ ማለት በኃላፊነት እስከተመደብኩት እና እስከረከብኩት ድረስ በኋላ ማለት ነው ከእዚያ በፊት እንደዚህ ሆኖ የመጣ ተቋም ነው
- ቅድም ሲገልፁልን አንዱ አሁን ከዘረዘሯቸው ውስጥ የትምህርት ጉዳይ ተማሪዎቹ ረብሻ አንስተው እንደነበር ገልፀውልናል አይደል ?
- አዎ
- እናም ሲገልፁ ካውንስል የት/ቤቱ የካውንስል የተማሪዎች ካውንስሎች አሉ ያንን በተመለከተ እነ ሙባረክ የሚመሩት አለ በሌላ በኩል ደግሞ አቡበከርን ውጪ አገኘሁት ይሄንን እንቅስቃሴ ሊመራ ብለዋል ምን ግንኙነት አላቸው እነዚህ ቅድም ጠቅለል አድርገው ኮሚቴ ያሏቸው ሰዎች ከእዚህ ት/ቤት ጋር ምን ግንኙነት ኖሯቸው ነው እንቅስቃሴውን የሚመሩት በመዋቅር የሚያገናኛቸው ነገር አለ ወይ ከእናንተ ጋር ?
- እዚህ ላይ የተጠየኩት ጥያቄ ማስተካከያ ምንድን ነው አቡበከር ይሄንን ይመራል አላልኩም ውጪ ሳገኘው
- እንቅስቃሴውን

1246

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- እኔ አቡበከርን በሙስሊምነቱ በወንድምነቱ ነው ውጪ የማውቀው በፊት ከእዚያም በፊት የእዚያን ቀን ውጪ ስንገናኝ ነቢል ከሚባል ጓደኞችን 2 ሆነው ቆመው ነበር ያገኘዋቸው ሰላም ተባባልን ቅድም ያልኩትን ነገር ነው የጠየቀኝ
- አሁን የምጠይቆትን ይሽውሎት ሀጂ ተስፋዬ
- ወደ እዚያ ልመጣ ነው
- ይሽውሎት ተረጋግተው ምንም ሳይረበሹ የምጠይቆትን ብቻ ይንገሩኝ ት/ቤት ነው ነው ብለውናል ት/ቤት ውስጥ የተነሳ ረብሻ ወይም የተማዎችም አመፅ ካለ የሚፈታው እዚያ ት/ቤት ነው አሁን በግልፅ የጠየኮት ኮሚቴው ያሉት ወይም ደግሞ እነ አቡበከር ከእዚህ ት/ቤት ጋር ምንድን ነው ያገናኛቸው ?
- ግንኙነት የላቸውም ብዬ ቅድም እኮ አስቀምጬአለሁ ውጪ ናቸው እዚያ ውስጥ አይደሉም ሠራተኞች አይደሉም ከእዚያ በኋላ ግን ይሄንን ነገር ለመምራት ከውጪ ይመጣሉ ብዬ ቅድም
- የተማሪዎች ጥያቄ ምንድን ነው የነበረው በአጭሩ ?
- መልሼአለሁ
- ተመልሷል
- እኔ አሁን እየጠየኮት ነው በስነ ስርዓት ይመልሱ ሀጂ የተማሪዎቹ አጭር ጥያቄ ምንድን ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ክቡር ፍ/ቤት አስተካክላለሁ እኔ ጥያቄውን ስለመሰለስኩት ነው እንጂ /ግልፅ ያልሆነ/ አይደለም ወይም ወደ ሌላ ክቡር ዐቃቤ ሕግ ያቀረቡት ነገር ውስጥ ገብቼ አይደለም ነፃ ነኝ ግን ተማሪዎቹ እንቅስቃሴአቸው ምን ነበረ ሲሉኝ እነዚያ 3 ጥያቄዎች ናቸው ብዬ ቅድም ስለገለፅኩ ነው መልሼአለሁ ያልኩት እንጂ አንቲጌደስት አልሆንኩም ክቡር ፍ/ቤት
- በተደጋጋሚ ያው ምስክሩ እንቅስቃሴ መኖሩን ይገልፃሉ ይሄንን ደግሞ እኛ እንዲመሰክሩልን የምንፈልገው እንቅስቃሴ ሳይሆን በእንቅስቃሴው ምን ምን ድርጊቶችን እንደነበሩ እንዲገልፁልን ነው ከእዚህ አንፃር ምናልባት ፍ/ቤቱ በማጣሪያ ጥያቄም ወይም እንዲህ ሆኖ ብለን መመሪያ መስጠት ስለማንችል ነው እና ፍ/ቤቱ እንትን እንዲልልን ነው የምንፈልገው ለምሳሌ ሀጂ ተስፋዬ ጀማል ያሲንን አግቼው ይሄንን ጥያቄ ይሄንን እንቅስቃሴ ተው ብዬዋለሁ ብለዋል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ስለሆነ ነው ይሄንን ጥያቄ ተው ያሉት እርሶ ጥያቄው ምን ስለሆነ ነው ከእዚህ ነገር ውስጥ ውጣ ይቅርብህ ብዬአለሁ ያሉት ምን ስለሆነ ነው ይሄ ጥያቄ ?
- ጥያቄው በወቅቱ ያው እኔ ቅድም እናንተም እንደገለፃችሁት የተቋመ አንድ አካል ነኝ ማለትም አንድ ሠራተኛ ነኝ በእዚያ ውስጥ አንድ መዋቅር የአወለያ ተቋም ምክትል ስራ አስኪያጅ ነኝ እዚያ እየተካሄደ ያለው እንቅስቃሴ ደግሞ የተቋመ ተቃራኒ ነው ማለት ጠቅላይ ምክር ቤቱ ነው የመደበኝ ይሄ እየተካሄደ ያለው የሁከት ወይም የጥሪ እንቅስቃሴ ወደ ተቃራኒነት የሚያመራ መሆኑን ስለተገነዘብኩ ነው አንድ እሱ ነው 2ኛ እሱ እራሱ የተቋመ ሠራተኛ ስለሆነ ሌሎች ከውጪ እየመጡ ነው እኔ እሱን በግል ለማናገር ያስቻለኝ ሌሎች ከውጪ እየመጡ ነው አላማዬ ብለው እንግዲህ የሚፈልጉት ነገር አለ ያንን ለማስፈፀም ነው እነዚያም የተነሱ ጥያቄዎች ናቸው እሱ ደግሞ የግል የተቋመ ሠራተኛ ነው አንድ ዲፓርትመንት ኃላፊ ነው እሱን የሚመራው እኔ ነኝ ስለዚህ ከመግባባት ጋርም እግባባው ስለነበረ
- በእዚህ መነሻ ነው ?
- በእዚህ መነሻ ለምን አንተ ከእነዚህ ጋር እንቅስቃሴውን አታቆምም ብዬ ጠይቄዋለሁ
- አሁን ከገለፁት 2 መነሻዎች ነኛ እንቅስቃሴው ከእዚህ የሁከት እና የጥሪ እንቅስቃሴ እንትኑን /ግልፅ ያልሆነ/ በማለት ገልፀዋል የመጅሊሱን እንትን የሚቃወም
- የተከበረው ፍ/ቤት እንደዚህ ከሆነ እኮ በቃ ይሄ ምስክርነትም አያልቅም ለሁላችንም መጨረሻህ ነው አሁን ምስክሩ ያልመሰከሩትን ያላሉትን ነገር የነውጥ እና ምናምን እንቅስቃሴ ብለው ተርጉመው አስተካክለው በዐቃቤ ሕግ መናገሮ ተገቢ አይደለም ተገቢ የክርክር አመራርም አይደለም እና ነኛ ምስክሩ /ግልፅ ያልሆነ/ እንዲሰረዝልን እንጠይቃለን 2ኛ ጥያቄውም ሊቀጥል አይገባም ከእዚያ በላይ እንዲህ ዓይነቱ ነገር እንዳይቀጥልም ይነገርልን አላሉም ምስክሩ
- የተከበረው ፍ/ቤት ዐቃቤ ሕግ ምስክር ነው ማስመስከር ያለበት እንጂ ወስኖ መወሰን የለበትም እኮ ፍ/ቤት መወሰን ያለበት የሁከት እና የምናምን ተግባር ነው ይሄ ምናምን ብለው እኮ ማለት ለምስክሩ ቅድም ዝም ብለናል የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ፊት ኃሳብ ያቀርባሉ እኛ እንዲህ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ልናስመሰክር የፈልገግነው ይሄ እኮ ማለት ምስክሩን ይሄንን መስክርልን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ማለት ነው እኛ ፍ/ቤቱን ላለማሰልቸት ነው ዝም ያልነው የተከበረው ፍ/ቤት ያው ግምት ይወስዳል ይታዘባቸዋል በሚል ጭምርም ኖርማሊ

- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ቃላት 2 ምክንያቶች ገልፀዋል 1ኛው የሁከት እና ጥሪ ብለዋል 2ኛ ሌሎች የማያገባቸው የውጪ ሰዎች ናቸው እሳቸው ደግሞ ሠራተኛ ናቸው ብለዋል ይሄንን ምናልባት ፍ/ቤቱ እየሰማቸው ነው ምናልባት ካላሉ ተነስተን ከሆነ ፍ/ቤቱ ብይን ይስጥበት እኛ ግን ምስክሩ ይሄንን ቃል ካሉት ተነስተን ነው እየጠየቅን ያለነው ስለሆነም የቀረበው መቃወሚያ ያለአግባብ ነው
- ብይን ሰጥተናል /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክሩ ቀደም ብለው ብጥብጥ ተነስቷል የሚል ተናግረው ነበረ በእዚያ ብጥብጥ ምክንያት ምን ተፈጠረ የሚል ነው በእዚህ ምናልባት ቃሉ ነው የተቀየረው እንጂ ብጥብጥ የሚለው ምልክቱ ያው ስለሆነ ዐቃቤ ሕግ ይቀጥሉ ብለናል ግን ዐቃቤ ሕግ ጥያቄአችሁን አጠር አጠር አድርጋችሁ በቃ ይመሰክሩልናል ብላችሁ የምታስቡትን ጠይቁ ምስክሩ አልመልስም ብለው ካለፉ እሱን ምንም ማድረግ አንችልም /ግልፅ ያልሆነ/
- እስቲ 2ቱን ምክንያቶች ለፍ/ቤቱ ይድገሚችው በምን ምክንያት ነው እርሶ ሀጂ ጀማል ያሲንን ከእዚህ እንቅስቃሴ ተቆጠብ ወይም ይሄንን ከእዚህ እንትን ውስጥ ተው ብዬዋለሁ ብለዋል ምን ስለሆነ ነው ይሄ እንቅስቃሴ ተው ያሉት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ይበቃናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዋና ጥያቄ ተጠናቋል የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ ?
- አቶ ሀጂ ተስፋዬ እርሶ የመጂሊስ ኃላፊ ኖት አይደለም መጅሊስ ማለት ኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ማለት ነው ነው አይደለም ?
- አዎ
- የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ነው የሚተዳደረው ?
- አዎ
- ኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በየ 5 ዓመቱ አንቀፅ 22 ላይ በየ 5 ዓመቱ ምርጫ ማድረግ አለበት ለመጨረሻ ጊዜ ምርጫ ያደረገው በ 1992 ዓ.ም ነው ከ 1992 በኋላ ምርጫ አላደረገም ይህ ማለት ሕገ ደንቡን ጥሷል ማለት ነው ነው አይደለም ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- እርሶ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ለመጨረሻ ጊዜ ምርጫ ያደረገው መቼ ነው በ 92 ዓ.ም ነው ከእዚያ በኋላ ምርጫ አላደረገም አይደለም ?
- ይሄንን መልሰዋል
- ስለዚህ የነበረው መጅሊስ በሕዝብ የተመረጠ መጅሊስ አይደለም ማለት ነው ?
- ቅድም ቀደም ሲል ምስክሩ አጠቅላይ የመሰከሩት ምስክር በእያንዳንዶቹ ተከሣሾች እና አጠቃላይ በዝርዝር ያው የገለፁዋቸው 3 መሠረታዊ ጉዳዮች እና እንዲሁም አጠቃላይ የሰጡት የምስክርነት ቃል አለ ከእዚህ ጋር በተያያዘ አሁን እሳቸው የተከላካይ ጠበቃ እያቀረቡት ያለው በ /ግልፅ ያልሆነ/ ዓ.ም መቼ መቼ ተቋቋመ እስከ መቼ /ግልፅ ያልሆነ/ ምን ነበር የሚል በክስ ጭብጣችን መሠረት አድርገን እኛ ይሄንን /ግልፅ ያልሆነ/ ሁኔታ ከዋና ጥያቄ ካልጠየቅነው መሠረት በማፈንገጥ እየጠየቁ ነው እና የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ ውድቅ እንዲያደርግልን ነው በአክብሮት ያምጠይቀው
- መምራት ማለት አፍኮርስ መምራት ይችላሉ ይሄ መስቀለኛ ጥያቄ ነው መምራት ማለት ግን መልሱን መመለስ ማለት አይደለም ቀድሞ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መልስ እንሰጥበታለን የተከበረው ፍ/ቤት ዋናው ክርክር ጥያቄው ተነሳ ተብሎ ደንበኞቻችን እየተከሰሱ ያሉበት ነገር መጅሊሱ ቀጥሎ የምንመጣበት ጥያቄ ለምሳሌ መጅሊሱ ፍቃድ የመስጠት ስልጣን አለው የሚል አለ /ግልፅ ያልሆነ/ ውጪ ነው የሚል አለ መጅሊሱ እራሱ ሕጋዊ ነው የሚለው ነገር ዋናው ጭብጥ ነው የተከበረው ፍ/ቤት የእዚህ ሁሉ መነሻም የመጅሊሱ ሕጋዊ አለመሆን ነው ስለዚህ ከእዚያ ተነስቶ ዐቃቤ ሕግ ክሱን መሠረት ያደረገው መጅሊሱ ስለሆነ በእዚያ ላይ ሰውዬው መመስከራቸው እኛ ይሄን ጥያቄ ማንሳታችንም ሬለቫንት ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መምራት አለመምራት ከሚለው አንፃር ከሊትሬቸሩም [illegible]
- /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መልስ ሰጥቶ ሙሉ መልስ ሰጥቶ አዎ ወይም አይደለም ማስባል መምራት ማለት ነው ይፈቀዳል አይከለከልም ይሄንን ልንገደብ አይገባም አጠቃላይ እኔንም ወደ ፊት ስለሚመለከተኝ ነው ይሄንን ታሳብ የምሰጠው
- ትክክል ነው እሱን ፍ/ቤቱም አልከለከለም ዋናው ነገር ግን ጥያቄውን መርታችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ ግን ምስክሩ ከመመስከሩ በፊት ሌላ እንትን እየጨመሩ ያንን ነገር ማለት ነው እራሳችሁ መደምደሚያ እየሰጣችሁ የምትሄዱ ከሆነ እሱን ነው የምናስቆመው ጥያቄውን መርታችሁ ጠይቁ የሚደመድመው እሱ ነው ግልፅ ነው ጥያቄው ሲጠየቅ እሱ ነው የሚደመድመው ጠበቃው አይደለም የሚደመድመው ጠበቃው የሚደመድመው ከሆነ የምስክሩ አባባል እየመሰለ ይሄዳል መጨረሻ ላይ ይሄንን መሠረት አድርጋችሁ ጠይቁ ነው የምንለው
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ
- ሌላው ተቃውሞ ምንድን ነው ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የለውም የሚል ነው እሱ ምናልባት ጉዳዩ ተያያዥነት ያለው ነው ተያዥነት ያለው ማለት ምንድን ነው መነሻው መነሻው ምንድን ነው የሚለውን ነው እናንተ መነሻው ምንድን ነው ወደ የሚለው /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት መጅሊስ እራሱ ምንድን ነው ሀጂ ተስፋዬ መልሰዋል እሺ ኮሚቴው ምንድን ነው እርሶ መቼ እስከ መቼ ነው አዲስ አበባ ያልነበሩት አዲስ አበባ ጥር ላይ ወደ መቀሌ የሄዱት መቼ ነው መቼ ነው የተመለሱት ?
- ጥር አይደለም /ግልፅ ያልሆነ/
- መቼ ነው የሄዱት ?
- እኔ ከሐምሌ 4 እስከ ሐምሌ 12 አዲስ አበባ /ግልፅ ያልሆነ/
- መቼ ነው የሄዱት መቼ ተመለሱ ?
- እየተናገርኩ ነው ሐምሌ 4 ወጣሁ ከአዲስ አበባ ሐምሌ 12 አዲስ ተመለስኩ
- የእዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ መነሻ የነበረው ጉዳይ ቅድም እዚያ ስለሙባረክ ሲመሰክሩ የእዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ የነበረው ጉዳይ ምንድን ነው የነበረው ምንድን ነው የሆነው እነ ሙባረክ የተማሪዎች ካውንስል አባል ነው ምንድን ነው ስልጣኑ እዚያ ላይ ወሳኝ የሚባል የወላጅ ተማሪዎችና የመምህራን ኮሚቴ የሚባል ነበረ አልነበረም ?
- ነበረ

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወተማ ውስጥ ነበረ ሙባረክ አይደለም ነበረ አልነበረም ሀጂ ተስፋዬ ?
- ነበረ
- ወተማ የተቋቋመው በአወሊያ ት/ቤት ውስጥ የተደረጉትን ነገሮችን ቅድም እርሶ የዘረዘሯቸውን ሊመረቁ 6 ወር የቀራቸውን ተማሪዎችን ጭምር ወደ ኋላ አስቀርቶ ካሪኩለም እንለውጣለን ኮሊጅ ሊመረቁ 6 ወር የቀራቸውን ተማሪዎች ጨምሮ ካሪኩለም እንለውጣለን ሲል ተማሪ ተቃውሞ አነሳ ነው አይደለም ?
- ነው ብዬ መልሼአለሁ
- ነው ብለው መልሰዋል እነዚህ ተማሪዎች ሊሎቹ መምህራኖቻቸው ከት/ቤቱ እንዲባረሩ ስለተደረጉ 50 የሚያክሉ ተማሪዎች አስተማሪዎቻቸው እንዲባረሩ ስለተደረጉ ተቃውሞ አቀረቡ ነው አይደለም ?
- 50 ሳይሆኑ 23
- 23 የአረብኛ ቋንቋ መምህራን ቀጥሎ ይሄ በደረጃ በደረጃ ወደ ታች እንዲሄድ ተደረገ ማለት ነው ነው አይደለም ?
- አቶ ተማም እስቲ አንዴ ቆዩ እሺ ጥያቄውን አጠር አጠር አድርገው ከቆመበት ይቀጥሉ
- ሀጂ ተስፋዬ ተማሪዎቹ ሀጂ ተስፋዬ የታገዱ ሰዎች ይመለሱ ሲሉ ግቢ ውስጥ ሆነው ነው ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበሩት አይደለም ?
- አዎ ተማሪዎቹ ከግቢ አልወጡም ነገር ግን ተማሪዎቹ ብቻ አይደለም ቅድም እንደገለፅኩት ብዙ ሰው በቁጥርም መጥቀስ የማልችለው ሰው ብዙ ሰው ይመጣል
- ብዙ ቅድም ወደ እሱ እመለሳለሁ በሞባይል በሲኤም ኤስ /ግልፅ ያልሆነ/ መልዕክት ይላካል ብለዋል እነዚህን እነዚህን ተማሪዎች ልከው ወላጆቻቸውን ጠርተው አይደለም እነዚህ ልጆች ወላጆች ከውጪ የመጡት ማለት ተማሪዎች ጥያቄዎቻቸውን አቀረቡ ጥያቄዎቻቸው መመለስ ሲገባቸው ሳይመለስ ሲቀር ይባስ ብሎ እርምጃ ሲወሰድባቸው ከውጪ ወላጆቻቸውን ጠርተው ወላጆቻቸው መጥተው አይደለም በመጀመሪያ ቀን 900 የሚሆኑ ሰዎች ግቢ ውስጥ ያደሩት ?
- ገልጬአለሁ
- ገልፀዋል ነው አይደለም ይበሉ ?
- እኔ ወላጅ ሳይሆን ወላጅ የሚለውን ነገር አላውቅም ለይቼ ነገር ግን
- /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ኣይ እሱን ነው እሱን ነው እኮ አሁን እያልኩ ያለሁት እኔ ከውጪ ወላጅ ሲባል እንግዲህ አወሊያ የማስተምረው የሚያስተምረው ተማሪ እዚያ አካባቢ እዚያው ሰርክ ላይ ያሉትን ተማሪዎች ነው ወላጅም ከተባለ እዚያው ሰርክ ላይ ያሉ የተማሪዎቹ ወላጆች ናቸው የሚመጡት ነገር ግን ይመጡ የነበሩ ሰዎች ከጅማ ከአማራ ክልል ከኣቃቂ ከጉለሌ ከአስሩም ክፍለ ከተማ ነው የሚመጡ የነበሩት
- አወሊያ ምንድን ነው የሚሰራው ቅድም ሲያስተምሩ አወሊያ አባት እናት የሞተባቸውን ተማሪዎች ያስተምራል ብለዋል ከአዲስ አበባ ብቻ ነው እንዴ የሚቀበለው አወሊያ?
- አላልኩም
- ታዲያ ምን እያሉ ነው ያሉት አሁን
- ተማሪዎች አባት እናት የሌላቸው ተማሪዎች ሌላ እዚያ የሚያድጉ ናቸው እነሱ ሌሎች ናቸው እዚያው የሚማሩ ናቸው እዚያው ግቢ ውስጥ ያድጋሉ እዚያው የሚማሩ ናቸው
- ቅድም ወደ
- እያልን ያለነው ወላጅ ግን ከ ነኛ እስከ 12ኛ እዚያ የሚማሩ ተማሪዎች ወላጅ ነው ወላጅ የምንለው እነሱ ደግሞ እዚያው አካባቢ ለት/ቤቱ ቅርብ ሆኖ እዚያ የተመዘገቡ ልጆች ወላጆች ናቸው እኔ እያልኩ ያለሁት ከእነሱ ውጪ ከክልልም ከአዲስ አበባ አስሩም ክፍለ ከተማ የሚመጡ ሰዎች አሉ ቅድም በተጠቀሰው ጥሪ እና በሚበተነው ፓምፕሌት ወረቀት ነው እያልኩ ያለሁት
- ቅድም ሀጂ ሰዎች ሰደቃ ሰደቃ እራሱ ምንድን ነው ሰደቃ ምንድን ነው ትርጉሙ ?
- ሰደቃ ሳውቅ
- ትርጉሙ ?
- ትርጉሙ የተቸገሩ ሰዎችን ማብላት ነው
- በትክክል
- ቅድም ጠቅላይ ምክር ቤቱ ዐቃቤ ሕግ ሲጠይቆት እርሶ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ታህሳስ 9/1996 ያወጣው አዋጅ አለ ጠቅላይ ምክር ቤት በሕገ ደንብ የተቋቋመ የተመዘገበ ኤንጅአ ነው አይደለም በማህበራት ደንብ መሠረት በ1952 በወጣው ደንብ መሠረት የተመዘገበ ማህበር ነው አይደለም ነው ወይስ አይደለም ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይደለም ማህበር አይደለም ጠቅላይ ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝበ ሙስሊም ተቋም መሆኑን ነው
- ተቋም ነው
- የሚተዳደረው ግን በመተዳደሪያ ደንብ ነው ?
- አዎ
- በመተዳደሪያ ደንብ ነው በማህበራት ምዝግባ የተመዘገበ ነው እራሱ ነው በአዋጅ ነው የተቋቋመው ?
- በአዋጅ ነው የተቋቋመው
- በየትኛው አዋጅ ?
- አላስታውስም
- አያስታውሱትም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መተዳደሪያ ደንብ ግን አለው የለውም ?
- አለው
- መተዳደሪያ ደንብ ካለው ታዲያ እንዴት በአዋጅ ይቋቋማል መተዳደሪያ ደንብ የሚቋቋም አካ ማህበር ነው
- እዚህ ላይ
- ስለዚህ ለሌላ ማህበር ፍቃድ የመስጠት ችሎታ አለው ወይ ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም ስለ ሀጂ ጀማል ያሲን ሲያወሩ የሙስሊም አማና ነው ማለት የሙስሊም አደራ ነው ብለዋል ይህ ማለት ሕዝቡ የሙስሊሙ አደራ ሰጥቶኛል ማለት ነው አይደለም ?
- አዎ እንግዲህ ይሄ ነኛ በኮሚቴም ውስጥ አለ 2ኛ እኔም እንደኃላፊው እንደጓደኛውም ይሄንን ነገር ተው ብዬ ስጠይቅ ሕዝብ የሰጠን ኃላፊነት ነው ነው ሌላ ምንም
- ስለዚህ ሕዝብ የሰጠን ኃላፊነት ነው ማለት ተመርጨአለሁ በሕዝብ ማለት ነው አይደለም ?
- እኔ እሱን ዝርዝር እንትኑን ተጨባጭ መረጃ የለኝም ግን እሱ ያለኝ ይሄ የሕዝብ አማና ነው መተው አልችልም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አለ በጣም ጥሩ ቅድም አንድ ቦታ ላይ በእዚህ በጩኸቱ በምናምን ብለዋል እንቀጥላለን ብለዋል አልጠየኩትም ብለዋል ስለዚህ የተናገሩት ግምቶትን ነው ማለት ነው
- እንዴት
- ግምቴን ነው ብለዋል በጣም ጥሩ ስላልሰማሁ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ሌላ ሀባሽ የሚባል አዲስ እምነት መጅሊሱ አምጥቶብናል ብለው የአወሊያ ተማሪዎች ጥያቄም ጭምር 3ቱን ጥያቄዎች አነሱ እነዚህን ጥያቄዎች በማጠናከር ነው የቀጠሉት የሚል ነገር ፅፌአለሁ እነሱ አላነሱትም ማለት ነው አይደለም እነ አቡበከር አላነሱትም ማለት ነው ቅድም ቃል በቃል የፃፍኩት ነው ሪከርድ ውስጥ አለ እሺ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ለጓደኞቼ ላሳልፍ የተከበረው ፍ/ቤት
- ሀጂ ተስፋዬ ቅድም ያሲን ኑሩ የአክሱም ሀውልት በድርድር ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ ያልመረጥነው መጅሊስ ወደ ቀዬው ይመለሳል በድርድር ይመለሳል ሲል ሰምቼዋለሁ ብለዋል ትክክል ነኝ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄንን ሲል እርሶ የት ቦታ ሆኖ ነው ያለው ይሄንን ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የት ቦታው የት ጋር ነው ?
- ግቢ ውስጥ
- ግቢ ውስጥ ነው ?
- ማንኛውም ሙስሊም የሚሰግድበት ቦታ ግቢ መስኪድ ብቻ ሳይሆን ግቢው ሁሉ ይሰገዳል /ግልፅ ያልሆነ/
- ግቢ ውስጥ ነው ያለው ?
- መስኪድ ውስጥ ነው ያለው
- መስኪድ ውስጥ ነው ያለው ?
- መድረክ ላይ
- እርሶ መስኪድ ውስጥ ነበሩ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መስኪድ ውስጥ አልነበርኩም ቢሮ በር ላይ
- ከመስኪድ ውጪ ነበሩ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቀኑን አያውቁትም ?
- ቀኑን አላስታውስም
- ወሩንም አያስታውሱም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ከግቢው ውጪ ከሆነ እንዴት ሰሙት እርሶ እሱ መስኪድ ውስጥ ነው ?
- ትልቅ ማይክራፎን አለ /ግልፅ ያልሆነ/
- ገባኝ መድረክ ላይ ነው ብለዋል መድረክ ላይ መሆኑን ካላዩት በምን አወቁ ?
- መጀመሪያ ገብቶ መድረክ ይዞ የለ እንዴ
- ማለት እርሶ እኮ ውጪ ኖት ? መገመት ይችላሉ በማይክራፎን ስለሰሙ ነው ?
- በማይክራፎን ሰማሁ ያው መድረክ ላይ ናቸው እነሱ ሲገቡ መጀመሪያ እኔ በሬ ላይ ነው የነበርኩት ግን ይሄንን በማይክራፎን የሰማሁት /ግልፅ ያልሆነ/
- በማይክራፎን የተሰማውን ሰምተው ነው የሚነግሩን ጥሩ በማይክራፎን በዕለቱ ያሲን ኑሩ ይናገር አይናገር ወይም እሱ የተናገረው ተቀርፆ በመድረክ ይተላለፍ በምን ያውቃሉ እርሶ አላዩም በአይንዎ ለምሳሌ ያሲን ኑሩ በሌላ ቀን የተናገረው በመድረክ ላይ በቴፕ ተቀርፆ ከሆነስ?
- በሰዓቱ ነው እኮ በወቅቱ ሌሎች መልዕክቶችን ሲተላለፍ እንዴት ነው በእዚያ መሀከል /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ የግምትዎ ነው ጥሩ
- ቅድም ሲነግሩን ተማሪዎች የሚሰጠው የአረብኛ ቋንቋ የወሀቢያ አቂዳም ስላለበት በሚል ነው እንዲቆም የተደረገው ብለዋል ይሄ ትክክል ነው እስኪጣራ ድረስ ?
- የደረሰኝ መረጃ የደረሰኝ ደብዳቤ እንደዚያ ነው ትክክል ነው
- እንደዚያ ነው የሚለው ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነዚህ የአረቢኛ ተማሪዎች የክፍለ ሀገር ተማሪዎች ናቸው አይደል ከክፍለ ሀገር የመጡ ?
- የክፍለ ሀገርም አሉ የአዲስ አበባም አሉ
- ጥሩ ስለዚህ ቋንቋው እንዲቋረጥ ሲደረግ በቋንቋ ብቻ ሳይሆን አቂዳ ማለት እምነት ማለት ነው አይደል የእምነት ክፍል ማለት ነው ትክክል ነኝ ?
- አዎ
- ስለዚህ እገዳው አንድን ወሀቢያ የሚባል የእምነት ክፍል እምነትን ለማገድም ጭምር ነው አይደል ምክንያቱም የወሀቢያ ነው የሚል ነገር ተብሏል
- እኔ እምነትን ለማገድ ነው የሚል እንትን ተገልጾዋል
- ከወሀቢያ ጋር የተያያዘ የወሀቢያ አቂዳም ጭምር ስላለበት በአረብኛው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ደብዳቤ በወቅቱ ደብዳቤ ብቻ አይደለም 36ቱ ተማሪዎች ጋርም ጠቅላይ ምክር ቤቱ በወቅቱ የነበሩ የመጅሊስ ፕሬዘዳንት ጋር 4 ሰዓት ሙሉ ውይይት የተደረገበት ነው እነሱም የራሳቸውን ትምህርት እንትናቸውን አቅርበው ታይቶ ይሄ የአረብኛ ካሪኩለም ብቻ አይደለም በሚል ተማምነው ከመተማመን ውጪ ደብዳቤም በእዚህ መልኩ ደርሶኝ ለ ፣ ወር ይሄ በትክክል ተጠንቶ ተስተካክሎ ትምህርቱ እስኪቀጥል ድረስ ወደየቤታችሁ ሄዳችሁ ለ ፣ ወር እረፉ ተብሎ የሚል ተወስኖ በእዚያ መልኩ ደብዳቤ ደረሰኝ
- ስለዚህ ከእዚህ ጋር ተያይዞ ነው እርምጃው የተወሰደው አይደል ?
- አዎ ቅድም ገልጬአለሁ ከእዚህ ጋር ነው የእነሱ የተማሪዎቹ ትምህርት ማቆም እና የመምህራኖቹ ከስራ መታገድ
- ሙባረክ ቅድም አንድ ሙቶ ሺህ ብር አሰባስበዋል ብለዋል ይሄንን በምን አወቁ እርሶ ?
- ይሄንን ያወቁት 100 ሺህ ብር ቆጥሬ እኔ ትክክለኛ አይደለሁም 100 ሺህ ብሩ ከእዚያም በላይ ነው የሚል ነው በወቅቱ በወሰድኩት መረጃ ገንዘቡ ወጪ የሚሆነው ከእነሱ ከተማሪዎች
- የለም ስለመጠኑ ነው የጠየኮት መጠኑ
- አልቆጠርኩም ከእዚያ በላይ ነው በነበረ በደረሰኝ ከእዚያ በወቅቱ ሲሰባሰብ ከ 100 ሺህ ብር በላይ የሚሆን ገንዘብ በዕለቱ ተሰብስቧል ነው ይሄንን አልቆጠርኩም በግምት ነው
- በምን አወቁ ታዲያ በግምት ግምት ለመገመት ከምን ተነሱ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በተነገረኝ በተነገረኝ እና እራሴ ላገኝ በፈለኩት መረጃ ነው
- ስለዚህ በተነገሮት መሠረት ነው ?
- አዎ
- ጥሩ ስለዚህ በወቅቱ አልነበሩም እርሶ አይደል ?
- ነበርኩ
- እዚያ ብሩ ሲሰበሰብ ?
- አዎ
- ብሩ የት ነው የተሰበሰበው ?
- እዚያ ጁማ ሰላት የሚሰግዱ ምዕመናን
- ግቢ ውስጥ ነው መስኪድ ?
- ግቢ ውስጥም መስኪድ ውስጥም
- ለምን ተብሎ ነው የተሰበሰበው ?
- አላውቅም አላማውን ለምን እንደተሰበሰበ
- አያውቁም ለምን እንደዋለም አያውቁም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም 17 ኮሚቴዎችን ስም ጠቅሰዋል መቼ እንደተመረጡ ያውቃሉ ?
- አላስታውስም ቀኑን አላስታውስም
- ቢያንስ ከተማሪዎች እንቅስቃሴ በኋላ ነው አይደል ?
- በኋላ ነው
- እነዚህ ኮሚቴዎች ሲመረጡ ነበሩ እርሶ እዚያ መስኪድ ?
- አልነበርኩም
- አልነበሩም ?
- ወረቀቱ ግን ደርሶኛል ስም ዝርዝራቸው አለ አሁን /ግልፅ ያልሆነ/
- የመረጣቸው ማን ነው ?
- እገሌ ነው ለማለት ያስቸግረኛል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት በዕለቱ የነበረው ሕዝብ አይደለም እንዴ እዚያ ተሰብስቦ የነበረው ?
- ነው ሕዝብ ነው ነገር ግን አወሊያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው
- አወሊያ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተሰበሰበው ሕዝብ ነው የመረጣቸው ይሄንን ነው የሰሙት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ፒቲሽን ያሰባስቡ እንደነበረም ተናግረዋል ?
- በየክልሉ
- የፒቲሽኑን ይዘት ያውቁታል እርሶ አንብበውታል ?
- 17ቱ ሰዎች ከላይ ስም ዝርዝራቸው ተፅፏል ከእዚያ በታች ፊርማ እንዲፈረም
- በሚፈረምበት ቀን ነበሩ እርሶ የመጀመሪያው ቀን ?
- አልነበርኩም
- አልነበሩም
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ሀጂ ተስፋዬ ቅድም ተከሣሽ ሙባረክን በተመለከተ ሲመልሱ ከነበረው ውስጥ መጅሊስ ከአወሊያ ይውጣልን የተባረሩ መምህራን ይመለሱ እና ከእዚያም በተጨማሪ 3 መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ይዘው ነው የተነሱት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚያ ውጪ ግን መንግስትን ወይም ሕዝብን የሚያጥላላ ወይም መንግስትን የሚሳደብ ዓይነት ንግግር የተናገረው ነገር የለም ?
- የመንግስት ጣልቃ ገብነት ይነሳ የሚል አለ
- ከእዚያ ውጪ ግን አሁን ለፍ/ቤቱ ግልፅ እንዳደረጉት 3ቱ ጥያቄዎች ነኛ መጅሊስ ከአወሊያ ይውጣልን የሀባሽ አስተምሮ በግድ አይጫንብን 3ኛው ያልተመረጡ የመጅሊስ አስተዳደሮች አይወክሉንም እያሉ ተማሪዎቹ መፈክርም ሲያሰሙ ነበረ አይደል ያሉት ይሄ ጥያቄ የተማሪዎቹ ብቻ ነው ወይስ የሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ የሌላውን ሰው ሊሆን የሚችል ነው ?
- እኔ በወቅቱ ሲጀመር የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ነው ከእዚያ በኋላ የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ከውጪ የሳባቸውም ሰዎች ይሄንን አጎልብተው ቀጠሉበት ነው
- አመሰግናለሁ የተማሪዎቹ የጀመሩት እንቅስቃሴ ነው ሌሎችም ከውጪ ያሉ ሰዎች ይመለከተናል ብለው ስለመጡ ነው ነው ይሄ ጉዳይ የሳባቸው ሌሎች ሰዎችም መጡ ነው መልሶት ይሄ ነው አይደለም ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ሌላ ግቢው ላይ ተፈጠረ ካሉት ነገር ውስጥ የመፈክሮች መጅሊስ አይወክለንም መጅሊስ ይውረድ የመሳሰሉ ንግግሮች ነበሩ ከእዚያ የመጅሊሱ ፀሐፊ አሊ መሐመድ ሲራጅ ጎማ ተነፈሰ ነው ያሉት ከእዚህ ውጪ የደረሰ ምንም ነገር የለም በወቅቱ ማለት ነው ተማሪዎቹ ሲጀምሩ ይሄንን ጥያቄ የመጅሊሱ ፀሐፊ ጎማ ከመተንፈሱ ውጪ ሌላ የደረሰ ምንም ዓይነት ነገር የለም አይደል ?
- ማለት
- የመጅሊሱ ፀሐፊ መኪና አቶዝ መኪና ይዞ መጥቶ ግቢ ውስጥ ጎማቸው ተነፈሰ ነው አይደለም ያሉት ?
- አዎ
- ጎማቸው ከእዚህ ውጪ ሌላ ምንም የደረሰ ጉዳት የለም ?
- የለም
- ይሄንን መኪና መቧረክ ሲያተነፍስ አላዩም ?
- አላየሁም
- ከእዚህ ውጪ ሌላ ምንም ዓይነት የኃይል ተግባር ሲፈፅመም አላዩም መቧረክ ምንም ዓይነት በግቢ ውስጥ የኃይል ተግባር ምንም ዓይነት ነገር ሲፈፅም አላዩም?
- አላየሁም ግን
- አመሰግናለሁ መልሰውታል የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄዬን መልሰውልኛል
- የኃይል እርምጃ ሲወስድ አላየሁም ግን መድረኩን በኃላፊነት እየመራ ነበር ባነሮችን ያዘጋጅ ነበር ቅድም ያልኳቸውን ነገሮች በግንባር ቀደምነት ተማሪውን ይመራ የነበረው በመድረሱ እሱ መቧረክ ነው
- አመሰግናለሁ ሌላ ተከሣሽ ሼህ ጀማል ያሲንን በተመለከተ ከጁማ ሰላት በፊት ዳዋ ወይም ኃይማኖታዊ ጥሪ ሲያደርግ ነበረ የሚል ነገር ተናግረዋል ምን እያለ ነበረ ኃይማኖታዊ ጥሪ ሲያደርግ የነበረው ?
- በእምነታችን ላይ እንጠናከር

1250

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ካለ ለፍ/ቤቱ ቢያብራሩልን በእምነታችን ላይ እንጠናከር ከሚል ውጪ ሌላ መንግስትን ወይም ሕዝብን የተመለከተ ነገር ሲናገር አልነበረም ?
- መንግስትን ሲነካ የሰማሁት ነገር የለም ያው እንጠናከር ሲል በተለይ በተጀመረው እንቅስቃሴ የመበርታት እንትን ይሰጣል የእሱ እንትኖች ቅስቀሳው ማለት ነው ከጁማ በፊት ምክንያቱም እንግዲህ ከእምነት ጋር ተያይዞ ነው ከተጠየቀው ጥያቄ ጋር ተያይዞ
- ይሄ ግምት እንጂ አላለም አይደለም ግምት እንጂ ይሄ የእርሶ ግምት ነው አይደለም ?
- አዎ
- ሌላ ከመጅሊሱ ወደ አወሊያ ከመግባቱ በፊት በማን ነበር የሚተዳደረው?
- ምኑ
- ከአወሊያ መጅሊስ ወደ አወሊያ ከመግባቱ በፊት ማን ነበር የሚያስተዳድረው አወሊያን ?
- አሪቦ የሚባል ድርጅት ነበረ በእሱ ይተዳደራል የተወሰነ ጊዜ እሱ ለቆ ከሄደ ደግሞ የተወሰነ ጊዜ በራሱ ነው የቆየው ማን ያስተዳድረው በእዚያ ጋፕ አላውቅም እኔ
- ቅድም መባረክን በተመለከተ ጥያቄ ጠይቄዎታለሁ አሁን ደግሞ ሌላ እነ ሼህ ጀማል ያሲን እነ አቡበከር እና ሌሎችም በድርጅት ውስጥ ወይም በአወሊያ ቅድም ተስበው መጡ ኃይማኖት ጥያቄዎች ስለተነሱ ተስበው መጡ ሕዝቡም በፒቲሽን መረጣቸው ብለዋል እስቲ ሲናገሩት ከነበረው ነገር የሚያስታውሱት ነገር አለ ለምሳሌ ለሕዝቡ ሰላማዊነትን በተመለከተ ጥያቄው በሰላም ለመንግስት መቅረብ ያለበት መሆኑን በተመለከተ ሲናገሩ ከነበረው ነገር የሚያስታውሱት ካለ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ጥያቄው ምንድን ነው እያሉ ነበር ለሕዝብ ሲናገሩ የነበሩት ወይም ጥያቄው በምን መልኩ ነው ለመንግስት መድረስ አለበት ሲሉ የነበረው ?
- ቅድም ገልጬአለሁ
- ያ ፕሮግራም እየተጠራ ነበረ ?
- ሐምሌ 8

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሐምሌ 8 ይቅርታ የሰደቃ ፕሮግራም እየተጠራ ነበረ መሴጆችም ደርሰውኛል በራሪ ፁሑፎችም አንብቤአለሁ ብለዋል እነዚህ በራሪ ፁሑፎች ወይም መሴጆች ይዘታቸው ምን ነበር ከሚያስታውሱት ውስጥ ምን ምን ፕሮግራም ይኖራል ይላሉ ?
- ይዘታቸውን አይደለም ይሄንን ፕሮግራም ስለምናካሄድ ፕሮግራሙ የሕዝበ ሙስሊሙ ስለሆነ እንትገኙ ይላል
- የሕዝበ ሙስሊሙ ፕሮግራም ነው እንድትገኙ ይላል ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አመሰግናለሁ
- አመሰግናለሁ ማለት ኮሚቴዎች ተመርጠዋል ብለዋል ምን ያህል ሰው እንደመረጠው ያውቃል ወይ ምን ያህል ሰው በየጁማው ይሰበሰብ ነበር ብለዋል እስቲ በግምት ይንገሩን ምን ምን ያህል ሰው ይሰበሰብ እንደነበረ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መገመት አይችሉም
- ምን ያህል ሰው እንደሆነ ላውቅ አልችልም ግን የሚሰበሰበው ሰው በዕለቱ ብዙ ሰው ነው ቁጥሩን ይሄ ነው ብዬ መወሰን አልችልም
- በግምት ቁጥሩን ማስቀመጥ አይችሉም ?
- አልችልም
- ግቢው ይሞላ ነበር መስኪዱ ብቻ ነው የሚሞላው እንዴት ነበር እስቲ ከግቢ ውጪስ ሕዝበ የሚሰግድ ሰው ነበር እንዴት ነበር አስረዱን እስቲ ?
- እኔ መስኪድ እና ግቢ ውስጥ ሞልቶ ሲሰግድ ያየሁበት ቀን አለ ግቢ ውጪ ሲሰገድ ግን አላየሁም
- አወሊያ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሙስሊም እዚያ ልጆቹ ማስተማር ሁሉም ሰው ሄዶ መማር መስገድ ይችላል ሁሉም ሙስሊም ?
- እንግዲህ መስጊድ አለው ግቢ ውስጥ መስጊድ ደግሞ ማንኛውም ሙስሊም መስገድ ይችላል ግን መስገድ ይችላል ሲባል ሆን ተብሎ ከአየር ጤና ወይም ከአቃቂ መጥቶ እዚያ ለመስገድ ይመጣል ማለት አይደለም በእዚህ መሀከል ብዙ መስኪዶች አሉ የተለየ ተልኮ ካልሆነ በስተቀር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ አወሊያ የሙስሊም ተቋም ነው ብለዋል ቅድም ሲመሰክሩ እና ሁሉም ሰው መጥቶ መስገድ ይችላል ወይ ነው እያልኩ ያለሁት ማንም ሙስሊም የሆነ ሰው ?
- ብዬአለሁ ኧረ እኔ አላውቅም
- አያውቁም ሀባሽ የሚባል እምነት ?
- አዎ
- ጥያቄውን ሲያነሱ 3 ጥያቄዎች ነው ይዘው የተነሱት ኮሚቴዎቹ ብለዋል ከእዚህ ውስጥ ነኛው ሀባሽ በግድ አይጫንብን ነው ብለዋል አላሀባሽ የሚባል ብለዋል አያውቁም አላሀባሽ የሚባል እምነት እንዳለ አያውቁም ?
- ኧረ አላውቅም እኔ አንድ እምነት አንዳለ /ግልፅ ያልሆነ/
- ስልጠና ሲሰጥ ያውቃሉ አያውቁም በእናንተ በምክር ቤቱ የሰጠ ስልጠና ነበር ያውቃሉ አያውቁም ይሄንን በተመለከተ ?
- የምን ስልጠና
- ሀባሽን በተመለከተ የተሰጠ ስልጠና ያውቃሉ አያውቁም ?
- ኧረ እኔ አላውቅም አልሰለጠንኩም አላውቅም
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት የአሁኑ ጥያቄ የመጨረሻው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም ሲመሰክሩ ሀጂ አቡበከርን አግኝቼው ነበር እና ያገኘሁትም ከነቢል ከተባለ ሰው ጋር ነው ብለዋል ቅድም አቡበከርን ነቢል ከተባለው ሰውጋር አግኝቼው ነበር ብለዋል መጀመሪያ ላይ በእዚያን ቀን የእናንተ ሰዎች የሚሰሩትን ስራ ተው አትልም ወይ ብሎ ያሎት ነቢል የተባለው ሰው ነው አይደለም መጀመሪያ ላይ ከአቡበከር ከተባለ ከነኛ ተከሣሽ ጋር ነቢል ከተባለ ሰው ጋር አንድ ላይ ሆኖ ተገናኝተን ነበር ብለዋል ?
- ነቢል ሳይሆን ነብዩ አስፋው
- ነብዩ አስፋው እሺ ነብዩ አስፋው ከተባለው ሰው ጋር አግኝቼዋለሁ ብለዋል በእዚያን ዕለት የእናንተ ሰዎች የሚሰሩትን ተው አትልም ወይ ያሎት ነብዩ አስፋው አይደለም ወይ ነው
- አቡበከር

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቡበከር ከተማሪዎቹ ት/ቤት ውስጥ እየተደረገ ነበር ያሉት እንቅስቃሴ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም አይደል ?
- የለም
- ቅድም ይሄ የእናንተ ሰዎች የሚሰሩትን ስራ ተው አትልም ወይ ብሎ ሲጠይቅት እኔ ምን አቅም አለኝ የሚል መልስ ነው የሰጠሁት ነው ያሉት እኔ ምን አቅም አለኝ ማለት እርሱ የመጅሊሱ አባል እንደሆኑ ገልፀዋል እኔ ምን አቅም አለኝ ያሉት ሌላ ቦታ ላይ ያለው ከእርሶ በላይ አቅም በላይ ስለሆነ ነው ወይስ ምንድን ነው ምክንያቱ እኔ ምን አቅም አለኝ ማለት ምን ማለት ነው ?
- እኔ አቅም የለኝም ማለት በመሰረቱ እኔ ባለሙያ ነኝ ተቀጣሪ ሠራተኛ ነኝ እንጂ የመጅሊስ ተመራጭ አይደለሁም መጀመሪያ በባለሙያነቴ ሲመደብ የመደበኝ ጠቅላይ ምክር ቤቱ ነው ስልጣን ያለው ኃላፊነት ያለው እሱ ያወረደውን መመሪያ ለማስፈፀም ነው እዚያ የተመደብኩት ከእዚያ አንፃር ይሄንን ቻሌንጅ ማድረግ እኔ አቅም አይደለም ነው
- እነሱ የእናንተ ሰዎች የሚሰሩትን ተው አትልም ወይ ሲሉ ምንድን ነበር የእናንተ ሰዎች ይሰራሉ የተባለው ?
- እንግዲህ አቡበከር እንደዚያ ሲለኝ የተረዳሁት እኔ ያው በደረሰው ደብዳቤ መሠረት ተማሪዎቹ ይሄንን ተቃውሞ ስላነሱ ነው ያንን አስመልክቶ እንዳለኝ ነው እኔ ግምት ወስጄ
- ለተማሪዎቹ ተቃውሞ መነሳት ምክንያት የሆነውን ተግባር ተው አትልም ወይ ነው ?
- እንደሱ ነው
- የአርብ የአርብ መድረኩን የሚመሩት ከ 1ኛ እስከ 3ኛ ያሉት ተከሣሾች ናቸው ብለው ቅድም ስማቸውን ዘርዝረዋል ይሄ መድረክ ሀይማኖታዊ ትምህርት የሚሰጥበት መድረክ ነው አይደል ለየአርብ የአርብ መድረክን የሚመሩት ብለው ቅድም አቡበከር አመዲን ብለው ገልፀዋል ?
- ሀይማኖታዊ መድረክ ነው
- ሀይማኖታዊ መድረክ ነው አይደል ?
- አዎ
- በእዚህ አሁን በአወሊያ መስኪድ በአርብ በአርብ ቀን በሚደረገው የሀይማኖታዊ ትምህርት ላይ ከተማሪዎቹ ውጪ የሆኑ ሌሎች ሙስሊም ማህበረሰቦችም ይገኙ ነበር አይደል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ይሄ አስቀድሞም የነበረ ነገር ነው አይደል ?
- እንዴት
- ከተማሪዎቹ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የተጀመረ ሳይሆን አስቀድሞም የነበረ ነገር ነው ?
- የአካባቢው ሰው እዚያ ቅርብ ያለው ሰው በፊትም ገብቶ ይሰግዳል የነበረ ነው፡ ነገር ግን የተለየ የሚያደርገው ከእዚህ እንቅስቃሴ በኋላ ከተለያየ አካባቢም እየመጡ ግቢም ሞልተው የሚሰግዱ ሰዎች ናቸው ለውጡ እንጂ የአካባቢ ሰው ሁል ጊዜ /ግልፅ ያልሆነ/ ሰላት ይሰግዳል
- በእዚያን ጊዜ ከስግደት በፊትም ትምህርቱም ይሰጥ ነበር ?
- ይሰጣል አዎ
- በተማሪዎቹ ተቃውሞ መነሻው ምክንያት ከአረብኛ ትምህርት በተጨማሪ የዋቢያ ትምህርት እንዲማሩ መደረጋቸው ነው ተብሎ ደብዳቤ ደርሶኛል ብለዋል ይሄ ከአረብኛ ትምህርት በተጨማሪ የዋቢያ ትምህርትም ለተማሪዎቹ ይሰጣል ብሎ ደብዳቤ የፃፈው ማን ነው ?
- ጠቅላይ ምክር ቤት
- በማን የተፈረመ ነው ደብዳቤውን ያስታውሱታል ?
- በጀማል መሐመድ ሳላህ የመጀመሪያው ደብዳቤው የተፈረመው በእሱ ነው
- ሌላስ ደብዳቤ አለ ከእዚያ በኋላ ሌላም ደብዳቤ አለ የመጀመሪያው ደብዳቤ ሲሉ ?
- ከእዚያም በኋላ አለ ሌሎች ደብዳቤዎች ይሄንኑ በተመለከተ በተደጋጋሚ የተፃፉ ግን የመጀመሪያው መነሻ የመምህራኖቹ እና የተማሪው ደብዳቤ የተፈረመው አሁን በጠቀስከት ግለሰብ ፊርማ ነው
- እርሶ የት/ቤቱ አመራር ኖት ይሄ ደብዳቤ እስከሚደርሶት ድረስ ከት/ቤቱ መርአዊ ግቡር ውጪ ትምህርት ይሰጥ የነበረ ስለነበረ የሚያውቁት ነገር የለም አይደል ?
- የለም
- ይሄ ደብዳቤ ከመፃፉ በፊትም አሁን ያሏቸው ሰው ስለእዚህ ጉዳይ እርሶን አላነጋገሮትም አይደል ?
- አላነጋገረኝም



1235

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእዚህ ምክንያት የተማሪዎች ተቃውሞ ተነሳ ብለዋል ይሄ የተማሪዎቹ ተቃውሞ የሁሉም ተማሪዎች ድጋፍ የነበረው ተቃውሞ ነበር አይደል ?
- አዎ እንግዲህ በወቅቱ ያሉት ተማሪዎች ይወጡ ነበር ከእዚያ ውስጥ ያልወጡትን ለይቼ ለማወቅ ያስቸግረኛል ግን የተማሪዎቹ እንቅስቃሴ መሆኑን እርግጠኛ ነኝ
- የሁሉም ድጋፍ ነበረው ?
- አዎ
- አይደል ?
- መለስኩ
- ትምህርቱ እንዲቋረጥ የወሰነው ማን ነው አሁን መጅሊስ ከመጅሊስ ነው የተገፈው ትምህርቱ እንዲቋረጥ ለአንድ ወር ተብሎ ስምምነት ነበረው ወይ የተማሪዎቹ ስምምነት ነበረው ወይ ትምህርቱ እንዲቋረጥ ሲደረግ የተማሪዎቹ ስምምነት ነበረው ተማሪዎች ናቸው ?
- በውይይት ነበር ደብዳቤው ከመጣ በኋላ ነው ያፈረሱት 4 ሰዓት በተደረገ ውይይት ላይ ስምምነት አድርገው ነው የተለያየነው እኔም ነበርኩኝ የጠቅላይ ምክር ቤቱ አመራሮችም ነበሩ ተማሪዎቹም ነበሩ ከእዚያ ውስጥ የተቃወሙት 2 ተማሪዎች ናቸው መጨረሻ በንግግር ተቃውሞ የገለፁት 2 ተማሪዎች ናቸው 34ቱ ግን አምነው ነው በቃል ተለይተን የነበረው በነጋታው ደብዳቤ ሲፃፍ ነው ተቃውሞ እንትናቸውን የለወጡት
- መምህራንም ከእዚህ ውስጥ ከእዚህ ጋር በተያያዘ ከትምህርት ቤት እንዲታገዱ ተደርጓል በትምህርቱ መቋረጥ ላይ ለ ፣ ወር በትምህርቱ መቋረጥ ላይ የመምህራኖች ስምምነት ነበረው ?
- እንዴት
- መምህራንም ታግደዋል አይደለም ?
- ታግደዋል 23 መምህራን ታግዷል /ግልፅ ያልሆነ/
- የታገዱት ከትምህርቱ መቋረጥ በኋላ ነው አይደለም ?
- አዎ
- ግን ከትምህርቱ መቋረጥ
- እነሱ ታግደው ነው ትምህርቱ የተቋረጠው
- እነሱም ታግደው ነው ?

ECLN
1236
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ስለዚህ /ግለፅ ያልሆነ/
- የሚቀድሙት አረብኛ ተማሪዎች ናቸው አሁን ይለያያሉ እንዴት ነው ኮሌጅ ውስጥ የሚማሩ 36 ተማሪዎች ናቸው ለብቻ ደግሞ ከ፱ኛ ደረጃ እስከ 12ኛ አረብኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራኖች ደግሞ አሉ
- 23 ?
- እነሱም ከተማሪዎቹ በኋላ ነው ከእነዚህ ከ 36ዎቹ ተማሪዎች ማቆም በኋላ 23 መምህራኖችም እንዲታገዱ ደብዳቤ የደረሰው
- ይሄ የአረብኛው ትምህርት በኮሌጅ ደረጃ የሚሰጥ ትምህርት ነው አይደለም ?
- አዎ በኮሌጅ የሚሰጥ ነው
- ታዲያ ትምህርቱ እንዲቋረጥ ይሄንን በኮሌጅ የሚሰጠውን ትምህርት እንዲቋረጥ መጅሊስ መወሰን ይችላል እንዴ ?
- እሱን አላውቅም እኔ በደብዳቤ ነው የተገለፀው ይችላል አይችልም የእኔ ውሣኔ አይደለም
- አያውቁም ትንሽ ጥያቄዎች አሉኝ ከተማሪዎች ጋር የተፈጠረውን ያለመግባባት ለመፍታት ከመጅሊስ የመጡት ሰው መኪና በተማሪዎች ጉዳት ደርሶበታል ብለዋል በተማሪዎች ጉዳት የደረሰበት መሆኑ እርሶ አይተዋል ?
- እንግዲህ እዚያ ተማሪዎች መሀል ነው ቆመው የነበው በወቅቱ ተማሪዎች ናቸው የነበሩት ሌላ ማንም
- እርሶ አይተዋል ወይ ነው ያልኮት ጉዳት ያደረሰው ተማሪ አይተዋል ?
- ሲያተኩሱ አላየሁም ግን ተንፍሶ አይቼአለሁ 4ቱም ጎማ እገሌ ነው ብዬ መለየት አልችልም ማን እንዳተነፈሰው
- ማን እንዳተነፈሰው አያውቁም ቅድም ስለኮሚቴው ሲጠየቁ ኮሚቴውን እንዲቋቋም ማለት የሙስሊሙ ሕብረተሰብ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ እንዲቋቋም ከመጅሊስ ፍቃድ ተሰጥቷል ወይ ተብለው ሲጠየቅ አልተሰጠም ብለዋል አለመሰጠቱን እርሶ በምንድን ነው የሚያውቁት
- መጅሊስ እንዳይደርስ እየተባለ እንዴት ነው መጅሊስ ፍቃድ መሰጠቱን መጅሊስ ያለው የመጅሊስ ሠራተኛ ይውጣልን እየተባለ ነው እኮ ያኛው መጅሊስ [illegible] ቀርቶ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ስለዚህ ከመጅሊስ እንግዲህ በወቅቱ ያለው መጅሊስ ጋር ነው ተቃውሞ ስለዚህ እንዴት ነው ፍቃድ የሚሰጠው መጅሊሱ

- ስለዚህ
- አልሰጠም ለማለት የቻልኩት ነኛ የመጅሊሱ ሠራተኛ ነኝ እየተመራሁ ያለሁት በመጅሊሱ ነው ቢሰጠው እኔን ይደርሰኝ ነበር ከእዚያ አንፃር መጅሊሱ አልሰጠውም
- ተቃውሞውን በመጅሊሱ ላይ ነው የነበረው ?
- አዎ
- ፍቃድ መጠየቅ ያስፈልጋቸዋል ይሄንን በእዚህ ላይ ተቃውሞ ያነሱት ሰዎች ከመጅሊስ ፍቃድ መጠየቅ ያስፈልጋቸዋል እንዴ የመጅሊሱ አባል ነኝ ስላለ በመጅሊሱ አባልነትዎ እንዲመሰክሩልኝ ነው ፍቃድስ መጠየቅ ያስፈልጋቸዋል እንዴ ?
- በወቅቱ ተቃውሞ በመጅሊሱ ይተዳደር ስለነበረ የበላይ ኃላፊው መጅሊስ ነው እና መጅሊስ ያወቀ ያላወቀው እንቅስቃሴ ከመጅሊስ ፍቃድ ውጪ ነው ያስብላል በእኔ አስተዳደር
- እርሶ እንግዲህ ሙሉዳደሪያ ደንቡን አያለሁ መተዳደሪያ ደንቡንም አወቀዋለሁ ብለዋል በሙሉዳደሪያ ደንቡ ላይ ልታወምህ ነው እና ፍቃድ ስጠኝ ተብሎ እንዲጠየቅ የሚያደርግ ደንብ አለ ወይ ነው ?
- እኔ አሁን ስለእዚህ መልስ መስጠት አልችልም
- በዘበኞች ላይ ጉዳት ደርሷል ብለዋል ነበዘበኞች ላይ ተማሪዎች ጉዳት ሲያደርሱ እርሶ አይተዋል?
- እኔ አላየሁም ግን ዘበኛው እኔ ጋር ቀርቦ ሲያመለክት በተማሪዎች ተደብድቤ ነው ብሎ አመልክቷል በእዚያ መሠረት አሳክመናል
- መቼ ነው ይሄ የደረሰው መቼ ነው ይሄ የተባለው ?
- አላስታውስም ቀኑን
- ጉዳት መድረሱን እርሶም አላዩም እርሶም አላዩም በተማሪዎች ጉዳት ይድረስ አይድረስ አላዩም?
- በተማሪዎች ለይቼ ተማሪዎች ናቸው የሚለውን አላየሁም ግን ጉዳት እንደደረሰበት አረጋግጬአለሁ አሳክሜዋለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ገባኝ ዘበኛው መጥተው በተማሪዎች ጉዳት ደረሰብኝ ማለታቸውን እንጂ በተማሪ ይድረስ አይድረስ እርሶ አላዩም እርሶን ነው ?
- እየለፅኩ ነው አላየሁም
- አሁን ቅድም ለኮሚቴ ለሙስሊም ሕብረተሰብ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ተቋቁሟል ብለዋል የት መቼ እንደተቋቋመ እርሶ ያውቃሉ ?
- አቤት
- መቼ እንደተቋቋመ ይሄ ኮሚቴ ያውቃሉ መቼ እንደተመረጠ ?
- አሁን አላስታውስም ግን አለኝ መረጃ ቢሮዬ አለ ስም ዝርዝሩም ቀኑም
- ካላስታወሱት ግድ የለም ይሄ ኮሚቴ የተቋቋመው ተማሪዎች ተቋውሞአቸው በት/ቤቱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ካነሱ በኋላ ነው አይደል ?
- ቅድም አዎ ብዬአለሁ
- ተማሪዎች ተቃውሞ ባነሱበት ጊዜ እና ኮሚቴው በተመረጠበት ጊዜ ላይ የምን ያህል ጊዜ ልዩነት ነበረው እርሶ የሚያስታውሱት ?
- አላስታውስም
- ለተማሪዎቹ ደግሞ በት/ቤቱ ላይ አንወጣም ብለው እዚያው በመቀመጣቸው እና ትምህርት በመቋረጡ ለተፈጠረው አለመግባባት አለመግባባት ተፈጥሮ በነበረ ጊዜ ገንዘብ ተሰብስቦ ነበር ብለዋል ለተማሪዎቹ ?
- ተጠይቄአለሁ
- እንዲመልሱልኝ ገንዘቡ ይሄ ኮሚቴ መቋቋሙን እና የገንዘቡን መሰብሰብ አሁን ቅድም ስለገንዘቡ ተጠይቀዋል ትክክል ነው አሁን የገንዘቡ መጠን ሳይሆን ይሄ ገንዘብ የተሰበሰበው የሙስሊሙ ሕብረተሰብ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት አይደለም ወይ የሚለውን ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም የሰደቃ ፕሮግራሙ ጥሪ የተደረገው እና የሰደቃ ፕሮግራሙ የተፈለገው የሙስሊሙ ሕብረተሰብ እንዲሰባሰብ ለማድረግ ነው ብለዋል ሰደቃ ማለት ምን ማለት ነው መጀመሪያ ?
- መልሼአለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሀጂ ተስፋዬ ቅድም ከመቀሌ ከሐምሌ 4 እስከ 12 ነበርኩ ብለዋል
- ድጋሚ ጥያቄ እስቲ ዐቃቤ ሕግ
- ሀጂ ተስፋዬ ቅድም ከሐምሌ 4 እስከ 12 መቀሌ ነበርኩ ብለዋል ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ በንብረቱ ላይ ከመኪናዋ ቅድም ከጠቀሷቸው ግለሰብ መኪና ውጪ እና ከዘበኞች በዘበኛው ላይ ከደረሰ ጉዳት ሌላ የደረሰ ጉዳት የማውቀው ነገር የለም ብለዋል በእዚህ ጊዜ ውስጥ ጉዳት ይድረስ አይድረስ የሚያውቁት ነገር አለ ባልነበሩባቸው ሰደቃ በተደረገባቸው ?
- ያየሁት /ግልፅ ያልሆነ/ በኋላ ማን እንዳደረገው አላውቅም ያው የመስኪዱ ሙሉ መስታወት ተሰባብሯል ብዙ አዳራሽም የሴቶች መስኪድም የሕፃናት ማለት የቁራን ማዕከል መስታወቶቻቸው ተሰባብረው አይቼአለሁ ግን በማን እንደተሰበረ በወቅቱ ስላልነበርኩ /ግልፅ ያልሆነ/
- እኮ በምን ምክንያት ነው ይሄ ጉዳት የደረሰው ተባለ ?
- እንግዲህ በዕለቱ ሐምሌ 6 በተደረገው አቁመው አታቁመው በሚለው ይመስለኛል በዕለቱ ነው
- ሌላ የምጠይቆት እና ግልፅ የሚያደርጉልን ተማሪዎቹ ከእኛ ጋር ተወያይተው ደብዳቤ ከመጣ በኋላ ነው ተቃውሞ የመጣው ብለዋል አይደል ?
- አዎ
- ከ 36ቱ 2ቱ ብቻ እንጂ ሌሎቹ የተቃወሙ የሉም ብለዋል ?
- አዎ
- በእዚያ ጊዜ ውስጥ የሀባሽ ጉዳይ እና የመጅሊስ ይውረድ ጉዳይ በተማሪዎች ጥያቄ ነበር ወይ የተማሪዎች ጥያቄ ነው ወይ እርሶ እዚያ ት/ቤት ውስጥ ሠራተኛ ኖት አይደል ?
- በ 36
- ልጨርስ ቆይ ሀጂ እዚያ አስተማሪ እያሉ የተማሪዎቹ ጥያቄ ነው ወይ የሀባሽ ጉዳይ የመጅሊስ ይውረድ ጉዳይ የተማሪዎች ጥያቄ ነው ወይ የተማሪዎች ካውንስል የፕሬዘንታቲቭ ይሁኑ ተማሪዎቹ እናንተ ስታናግሯቸው የነበሩ ተማሪዎች ጥያቄ ነው ወይ ይሄ ?
- ሲጀመር አዎ
- ይሄ ጥያቄ እነሱ ከእናንተ ጋር አንስተውታል ይሄንን ጥያቄ ?
- መጅሊስ ይውጣልን እነዚህ 3ቱንም አንስተዋል ተማሪዎቹ /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተማሪዎቹ መቼ ነው ይሄ የተነሳው ?
- ቀኑን ቅድም መጀመሪያ ላይ እኮ ገልጬአለሁ
- ያስታውሱታል ?
- ቀኑን አላስታውስም ታህሳስ ወር 2004 ብዬ መጀመሪያ ገልጬአለሁ
- ኮሚቴው ከተቋቋመ በኋላ ነው ከእዚያ በፊት ነው ?
- ከእዚያ በፊት
- ሀጂ ተስፋዬ ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ወተማ ስለሚባል ነገር አንስተው ነበር አይደል?
- ይሄ ወተማ ማለት የወላጆች እና የተማሪዎች ኮሚቴ ነው ?
- የወላጆች የተማሪዎች የመምህራኖች አንድ ላይ የተዋቀረ ኮሚቴ
- ይሄ ኮሚቴ ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ የተማሪዎችን ትምህርት መቋረጥ እና ከመምህራን መባረር ጋር ተያይዞ ለመፍታት ያደረገው ጥረት አልነበረም መጀመሪያ ላይ ?
- ብዙ ጥረት ነበር እኔም /ግልፅ ያልሆነ/
- ምንድን ነበር ይሄ ጥረት መጨረሻ ላይ የደረሰው ?
- ምንም አልደረሰም
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አሁን ይሄ አዲስ ጥያቄ ነው አዲስ ማብራሪያ ነው እየተጠየቀ ያለው ይሄ የቅድመ ጥያቄ አይደለም በዋና ጥያቄዎቹ ላይ አይደለም የወላጅ ተማሪዎች ወተማ ላይ የተነሳው ነገር ተጠይቆ ተመልሶ አልቷል አሁን በእዚህ እንትን ይደረግ የነበረው ጥረት ምንድን ነው ብሎ ጥያቄ መጠየቅ አዲስ ጥያቄ ነው አዲስ ማብራሪያ ነው በዋና ጥያቄ ጋር ያልነበረ የማይገናኝ ነገር ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቅ ከውጪ የሚመጡት ሰዎች በእዚህ ከማህበሩ ጋር የተያያዘ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች ናቸው ወላጆች ናቸው የሚባል ነገር ተነስቷል እና ከእዚህ ጋር በተያያዘ ምስክሩ የሚያውቁትን እንዲያብራሩ ነው እኛ እየጠየቅን ያለነው እና ከመለሱት መልስ በመነሳት ስለሆነ ምንም አዲስ ነገር ሳይሆን መጀመሪያ ላይ የሰጡትን ነገር እንዲያብራሩ ነው እየጠየቅን ያለው
- ብይን ሰጥተናል መጀመሪያ ይሄ የተማሪዎች መምህራን እና ወላጆች ኮሚቴ የሚል ነገር ተነስቷል ነገር ግን ኮሚቴው ምን ጠየቀ ምን ምላሽ ተሰጠ የሚለው አልተነሳም ስለዚህ በእዚህ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ላይ ተንተርሶ ምን ጥያቄ አንስተዋል የሚለው ነገር በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ያልተነሳ ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ያልተነሳውን በድጋሚ ጥያቄ ማንሳት ስለማይቻል ሌላ ጥያቄ

- በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ የተማሪዎቹ ጥያቄ ከመጅሊስ ጋር እንዲሁም ከሀባሻ እንደዚሁም መምህራን ይመለሱ የሚል ጥያቄዎች እንዳሉ ገልፀዋል መጀመሪያ ላይ የተማሪዎቹ ጥያቄ ይሄንን አለመግባባት ላይ የደረሰው ደብዳቤዎች 2 ደብዳቤዎች በጀማል በተባሉ ሰው የተፈረመ ደብዳቤ እንዳለ ገልፀዋል እዚህ ደብዳቤ ላይ ስለሀባሻ ወይም ስለመጅሊስ የሚያወራው ነገር አለ ?
- የለም
- ምንም የሚያወራው ነገር የለም ?
- የለም
- ሌላው ይሄ ከ 100 ሺህ ብር በላይ ተሰብስቧል በዋና ጥያቄ ቅድም ስንጠይቆት የሚመገቡትም እንደዚሁም ሌሎች ወጪዎች የሚሸፈነው በእዚህ ነው ሲሉ መልሰዋል በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ይሄ ገንዘብ ለምን እንደዋለ አላውቅም ብለዋል የትኛውን እንውሰድ ?
- እንግዲህ እኔ መስቀለኛ ጥያቄው ለእዚህ ዋለ ብዬ ለመናገር ያስቸግረኛል ነገር ግን ከእዚያ በኋላ ያው ምግብ ይቀርብላቸው ነበረ ኮርድኔት የሚያደርጉት የተማሪዎቹ ካውንስሎች እና ሌሎችም የወጪም ሰዎች ዳቦም ምግብም ስጋም ይቀርብ ነበር እና ከእዚያ አንፃር ነው ቅድም የገለፅኩት ከእዚህ የቀረበልኝ መስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ ገንዘቡ ለምን እንደዋለ ስል እኔ ይሄ ነው ብዬ ያላየሁትን ነገር ለእዚህ ውሏል ብዬ መንገሩ ከእንትኔ ውጪ ስለሆነ ነው እንደዚያ ያልኩት እንጂ ምግብ ያገኙ እንደነበረ ያው ቅድም አስረድቼአለሁ
- እስቲ ስለዚህ አሁን የትኛውን ነጥብ ነው እንትን የምንለው ማለት በዝርዝር ለምን ለምን ምን እንደተገዛበት ሙሉ ገንዘቡ አላውቅም ነው ወይስ ከእዚህ ገንዘብ ?
- አዎ
- እንጂ ተማሪዎቹ ሌላ ጥቅም አላገኙም ኦር ሌሎች ተማሪዎች አገልግሎቶች በእዚህ ገንዘብ አልተሸፈኑም?
- ገልጬአለሁ

54

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ሌላው ጥያቄአችን ሌሎች ሰዎች ከተለያየ መስኪዶች በተለምዶ አወሊያ መስኪድ ውስጥ የሚሰግዱት በአካባቢ ያሉ ሰዎች ናቸው ብለዋል ሌሎች የተለያየ ተልኮ ያላቸው ከክፍለ ሀገርም እንደዚሁም ከተለያየ ሰፈር
- ቆይ ቆይ አንዴ እስቲ ተልኮ የምትለው የምስክሩ አይደለም እና እሷን ተውት እና
- የተከበረዉ ፍ/ቤት ሪከርድ የተደረገው ምናልባት የሚታይ ከሆነ ለእኛ ይጠቅመናል በተደጋጋሚ ምስክሩ ያሉት ቃል
- ቆዩ እና እኛ የተረዳውን እንግለፅ እኛ የተረዳነው በፊት ከአካባቢው ብቻ ያሉ ሰዎች ይመጡ ነበር ነገር ግን ከእዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከክፍለ ሀገርም ከየትም ከየትም ይሄ ጉዳይ ከተጀመረ በኋላ ከክፍለ ሀገርም ከየትም ከየትም ይመጣሉ ከእዚህ ጋር የተያያዘ ይመስለኛል ነው ተልኮ የምትለውን ነገር አልተናገረም ተናግረሀል ተልኮ የምትለው ነገር ?
- አላስታውስም
- አልተነሳም ተልኮ የሚለው ነገር
- ምናልባት የያዝነው ማስታወሻ ስንይዝ ተሳስተን ይሆናል
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌላ ዓላማ ያላቸው ወይም ሌላ አላማ ለማሳካት የመጡ ሰዎች ነበሩ ብለዋል ምን ዓይነት አላማ ሊያሳኩ ነው የመጡት ?
- ማለት እንግዲህ እኔ ቅድም ገልጬአለሁ እኮ ተማሪዎቹ እዚያ ውስጥ ናቸው ይሄንን ዓላማ ለማሳካት የተማሪዎቹ አካል ያልሆኑ ወይም የእዚያ መስኪድ ሰጋጆች አካባቢ ሰጋጆች ያልሆኑ ሰዎች ለእዚህ ለተጀመረው ዓላማ ለማስፈፀም ይመጣሉ ብዬ ገልጬአለሁ ቅድም አሁንም እንደዚያ ነው አገላለፄ ተልኮም ብል ይሻው ነው ሌላ አማርኛ አይደለም ለእኔ በእኔ አነጋገር
- ምስክር አንድ ሁለት ጥያቄ ልጠይቆት ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲመልሱ ከተከበሩ የተከሣሽ ጠበቆች ሲጠየቁ ያሲን ኑሩ በማይክራፎን እንደአክሱም ሀውልት መጅሊስ ወደ የሚመለስበት ይመለሳል ሲል ሰምቼአለሁ ብለዋል በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ደግሞ በአይኔ አላየሁትም እንደዚህ ሲል ብለዋል ታዲያ ያሲን ኑሩ መሆኑን እንዴት አወቁ ?
- መስማት እና በአይን ማየት ይለያያል
- የያሲን ኑሩን ድምፅ ያውቃሉ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ድምፁን ሰማሁ በማይክራፎን እዚያው አጠገብ ነው እኮ ብዬአለሁ
- ችግር የለም ይንገሩኝ አሁን ያውቁታል የያሲን ኑሩን ድምፅ ?
- አዎ
- በጣም ጥሩ 2ኛ እዚህ አወሊያ ውስጥ ጎማ ሲተነፍስ መስታወስ ሲሰበር በሙሉ የጠቀሷቸው ውድመቶች ደርሰዋል እነዚህን ውድመቶች ተማሪዎቹ በቀጥታ ይፈፅሟቸው አይፈፅሟቸው አላውቅም ብለዋል በመስቀለኛ ጥያቄ በድጋሚም ጠበቃው ሲጠይቅት መባረክ ይሄንን ድርጊት ሲፈፅም በአይኔ አላየሁም ብለዋል አይደለም ?
- አዎ
- ይሄንን የተማሪዎች እንቅስቃሴ ግን የሚመራው ማን ነው ?
- እንደገለፅኩት መባረክ ነው
- መባረክ ነው በቃ ጥሩ እንዲህ እኮ ነው ሌላ አልፈለግንም የመጨረሻ ጥያቄ ልጠይቆት በየሣምንቱ አርብ ኃይማኖታዊ ይሄ የሚመዘገብ ነገር ስለሆነ ነው እንዲናገሩት የምንፈልገው ሳናውቅ ቀርተን አይደለም እንደዚያ ይረዱ ምስክር በየአርብ መድረኮቹ ኃይማኖታዊ ሰበካዎች ይደረጋሉ ጥሪዎችም ይደረጋሉ ብለዋል የተከሣሽ ጠበቃ በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቆት አዎ ጥሪ ብቻ ነው የሚደረገው ሌላ ምንም ችግር የለውም ብለዋል ግን ይሄ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት ሰው በወረቀት እየተበተነ እየተጠራ ነው እንዴ የሚመጣው አወሊያ ?
- ኧረ እኔ ቅድምም አላልኩም ይሄ ጥሪ ከተጀመረ በኋላ በጥሪ ይመጣሉ ከእዚያ በፊት የአካባቢው ሰዎች ብቻ ናቸው የሚገኙት ነው ያልኩት
- አበቃን የተከበረው ፍ/ቤት
- /ግልፅ ያልሆነ/ የፍ/ቤት ጥያቄ
- አንድ ከመጀመሪያ 3 ዓላማዎች አንግበው እየሄዱ ነበር ብለው የጠቃቀሷቸው ሰዎች እና ተማሪዎች አሉ እና ይሄ መጨረሻ ላይ ሰደቃ ተብሎ መጨረሻ ላይ የተደረገው ስብሰባ የመጨረሻ ስብሰባ ነው የተባለው ምንድን ነው የመጨረሻው ስብሰባ የሚሆነው ምን ለማድረግ ነው ?

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እግዲህ መጨረሻ ሲል መልዕክቱ ላይ በየአካባቢው በየመስኪዱ ሰደቃ ይወጣ ነበር ከእዚያ በፊት በየክፍለ ከተማው በየመስኪዱ ማለት ነው በራሪ ወረቀቱ ላይ የሚለው የመጨረሻ የማጠቃለያ ሰደቃ ፕሮግራም ነው የሚለው
- እኮ ከእዚያ በኋላ የት ለመሄድ ነው የመጨረሻ ተብሎ ምን ለማድረግ ነው ?
- እኔ ማጠቃለያ ሲል ያው የተጀመረውን ነገር የመጨረሻ ውሣኔ እዚያ ላይ ሕዝቡ ተሰብስቦ በሚሰበሰበው ሕዝብ
- እኮ የሚያውቁት ከሆነ እሱ ውሣኔ ምንድን ነው የመጨረሻው ውሣኔ ?
- ያው የተባሉትን ለማስፈፀም ነው ፤ኛ መጅሊሱን ለማውረድ ነው
- እኮ ማለት የት ሄደው ነው የሚያወርዱት ወዴት ሄደው ነው ?
- እንግዲህ እሱን እነሱ ናቸው የሚያውቁት ክቡር ፍ/ቤት
- የሚያውቁትን ከሆነ ነው የሚያውቁትን ነው ?
- መጅሊሱ
- ምክንያቱም ምንድን ነው ወደ መጨረሻ መጨረሻ ሰደቃ ተደርጓል የያዙት ዓላማ አለ መጅሊሱ ይውረድ የሚሉ እና ቅድም የተጠቃቀሱ 2 /3 ነገሮች አሉ ?
- አዎ
- እና ይሄ ነገር የመጨረሻ ነው ተብሎ የመጨረሻ ውሣኔ ምን ለማድረግ ነው ?
- አሁን ያው 2 ነገሮች ይኖራሉ ማድረግ አለማድረግ ወይም ደግሞ አንድን ዓላማ ለማስፈፀም ከግብ ለማድረስ እና ማቆም
- ግብ የሚያደርሷት ነገር ምንድን ናት እሷን ነው ?
- ማለት እነሱ ናቸው የሚያውቁት እንግዲህ እኔ ማጠቃለያ ይላል እንትኑ ላይ ግን እዚያ ላይ የሚወሰነው ውሣኔ በትንቢት ላውቀው አልችልም ነገር ግን የማጠቃለያ የመጨረሻ ፕሮግራማችን ይላል ከእዚያ በኋላ ፕሮግራሙ ውሣኔው ወዴት እንደሆነ በምን ላውቅ እችላለሁ
- ይሄ ነገር ተሰበሰቡ መጨረሻ ላይ ? በእዚህ ምክንያት ስብሰባ ተደረገ ?
- 2 ቀን ሲቀረው ተቋረጠ
- ተቋረጠ ?

1245

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሐምሌ 8 ነበረ ፕሮግራሙ ሐምሌ 6 ሲጀምሩ ጅማሬው ላይ ተቋረጠ
- አንድ ጥያቄዎች አሉኝ እና ማጠቃለያው መጅሊሱን ለማውረድ የሚለው ነገር አለ እና ይሄ ነገር እንዴት ነው የተረዱት ነገር ነው ወይስ የእርሶ ግምት ነው እሷን ብቻ ግልፅ ያድርጉ ?
- ማለት ያው የተነሱ ጭብጥ ሆነው የተነሱ ጥያቄዎች አሉ እንግዲህ ለእዚያ ጥያቄዎች ነው እንቅስቃሴው መጨረሻ ላይ ያው የተነሱለትን ዓላማ ለማሳካት ይመስለኛል እኔ 3ቱ መጨረሻ ፕሮግራም ያሉት
- ቅድም አንድ መንግስት ጣልቃ ገባብን የሚል ጥያቄም አንሰተዋል ነው ያሉት ?
- ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ግርግዳ ላይ ተለጥፎ
- እኮ እሱን ነው የተለጠፈው ነገር ምን ብሎ ነው ጣልቃ የገባው እሱን ምን ብለው ነው የሚቃወሙት ?
- የመንግስት ጣልቃ ገብነት ይነሳልን የሚል በቃልም ሰምቼአለሁ በግርግዳ በቢሮዬ እራሱ በቢሮዬ ላይ በማርከርም ተፅፏል በወረቀትም ተለጥፏል እንግዲህ ያ ጣልቃገብነት እነሱ ናቸው የሚያውቁት እኔ ይሄ ነው ብዬ ለመግለፅ ያስቸግረኛል ግን ቃሉ ይሄ ነው
- እናመሰግናለን ጨርሰዋል እንግዲህ የዛሬውን በእዚሁ ብናበቃ ነው የሚሻለው ዛሬ ያው እንግዲህ የዛሬው ብዙ ስራዎችን ሰርተናል ጊዜውን ደግሞ ሸኝተናል ምናልባት በሚቀጥሉት በእዚህ መንገድ እስከመጨረሻው እስከማታ ድረስ አንሄድም ምክንያቱም እዚህ ሩቅ የሚሄዱ ሰዎችም አሉ ማረሚያ ቤትም ይመሽበታል ምናልባት ዐቃቤ ሕግ ምስክሮቻቸውን በእዚህ ግምት ውስጥ የሆነ ሰዓት ሊጨርሱ የምትችሉትን እያመጣጠናችሁ በእዚያ መንገድ እንጨርሻለን ስለዚህ ቅድም ያልነው ማሳሰቢያ ነገም ይውላል በእዚሁ እንዳይረሳብን ነገ 3 ሰዓት ተኩል አር

ECHN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- /የማይሰማ/
- ጌታቸው ቀርበዋል
- ተከሣሾች እነ አቡበከር አህመድ መሐመድ 31 ሰዎች መካከል 30ኛ እና 31ኛ ተከሣሾች የሕግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ሲሆኑ ሌሎቹ ተከሣሾች ከማረሚያ በአጃቢ ሆነው ቀርበዋል ጠበቆቻቸው ተማም አባቡሉ ፣ሀሰን ሁሴን፣ ተካ ዳባ ፣ አሊማ ሰይድ ፣ ዳዊት ነጋሽ፣ንጋቱ ጌታሁን ፣ሞላልኝ መለስ፣ መሐመድ አብደላ፣ አዲስ መሐመድ ቀርበዋል
- መዝገቡ በአዳሪ የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አህመድ ጀማል ቀርበዋል መዝገቡ በአዳሪ ተቀጥሮ የነበረው በትላንትናው ዕለት ቀጥሎ የነበረውን የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች መቅረብ ጠብቆ ለመስማት ተብሎ ነበረ በእዚህም መሠረት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች መስማት ሂደቱን ፍ/ቤቱ ቀጥሏል ምስክሮች ይቅረቡ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የመጡት ለምንድን ነው ?
- ለምስክርነት
- ተከሣሾችን ያውቋቸዋል ?
- አውቃቸዋለሁ
- እነ ማንን ነው እስቲ የሚያውቁት ያስመዝግቡ ?
- አቶ ያሲን ኑሩ ፣ አቶ አቡበከር አህመድ
- ቀጥሎ እስቲ ማንን ማንን ነው የሚያውቁት አንድ በአንድ ?
- 1ኛ አቶ አቡበከር አህመድ 2ኛ አቶ ያሲን ኑሩ 3ኛ አቶ ካሚል ሸምሱ 4ኛ መሐመድ አባተ
- መሐመድ አባተ ?
- መሐመድ አባተ አዎ
- መሐመድ አባተ እሺ 8ኛ ተከሣሽ ?
- ግብረአበራቸው ያው ሳዲቅ ኃይሉ
- ሳዲቅ ?
- ኃይሉ
- ይሄንን ነው የሚያውቁት 4 ሰዎች ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ከሣሽ ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ አቅርቡ
- አቶ ሰይድ የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለዋል እስቲ አሁን በጠቀሷቸው ሰዎች ላይ ምን ምንድን ነው የሚያውቁት ከመቼ ጀምሮ ነው የሚያቋቸው ?
- የማውቃቸው በሰኔ 14 ቀን ላይ ጀምሮ ማለት ነው
- ስንት ዓ.ም ነው ?
- 2004 መሐመድ አባተ በአንዋር መስኪድ ላይ መውሊድ ማን ነው የአንድነት እና የሰደቃ ፕሮግራም በማለት በፈትህ ፈትህ አባቦራ /ግልፅ ያልሆነ/ መንግስት በሀይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል በማለት ንግግሮችን እያደረገ እያለ
- ንግግሮቹን ሁሉንም ይጥቀሱ እስቲ ምን ምን ነበር ሲሉ የነበረው ?
- መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል
- ለማን ነው ይሄንን ይል የነበረው ?
- ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ መስኪድ ውስጥ ላሉት ማለት ነው
- ለምን ስንት ሰዓት አካባቢ ነው ?
- 2 ሰዓት ተኩል ጀምሮ
- ማታ ነው ?
- ጠዋት ጠዋት
- ለምን ነበር ሰው የተሰበሰበው ?
- ለአድማ
- ማን ነበር የጠራውን ሰውን እዚያ ?
- ጥሪ ያደረጉ በማይክራፎን ነው የሙስሊሙ መብት ኃይማኖቱ ተነክቷል ና ቶሎ ተንቀሳቀስ ለዲንህ ለዲናችን ስንል እንሰብሰብ በማለት ማታ ዕለት ነበር መጀመሪያ ጥሪውን ያደረጉ
- ምን ማለት ነው እስቲ ለዲናችን የሚለው ቃል አረብኛ ቃል ነው አይደል ?
- አረብኛ ነው
- ምን ማለት ነው ?
- ኃይማኖታዊ ማለት ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለምንናችን ሰል እንሰብሰብ ማለቱ ነው ?
- ለኃይማኖታችን ስንል እንሰብሰብ በእዚያ ተባለ ከእዚያ ልክ ጠዋት መንግስት በሀይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ምርጫችን በመስኪዳችን የሚሉትን ቃላቶች ከተናገረ በኋላ ሰኔ 21 ላይ
- በእዚያው ዓ.ም ማለት ነው ?
- አዎ በእዚያው ነው ሰኔ 21 ላይ መንግስት ኮሚቴዎቻችን ይዞብናል ታሰሩብን ቄራ መስኪድ ላይ ብሎ መግለጫ ሰጠ ከእዚያ በኋላ ሐምሌ 7 ቅዳሜ ቀን አንዋር መስኪድ ላይ ጠዋት ይሄ ነኛው ግብረአበር ብዬ ያልኩት ሳዲቅ ኃይሩ እና መሐመድ አባተ
- አብሯቸው ነበር እንዴ ሳዲቅ ኃይሩ ?
- አዎ አብሯቸው ነበረ ኮንቴነሯ ላይ ከእዚያም በኋላ
- የት የሚገኝ ኮንቲነር ነው ?
- አንዋር መስኪድ ውስጥ
- መስኪድ ግቢ ውስጥ ነው ?
- ግቢ ውስጥ አዎ
- ምን ይል ነበር ኮንቴነሩ ጋር አካባቢ ሆኖ ?
- አላህምዲሊላህ አባሽ እንኳን ደስ ያለህ የኢትዮጵያ መንግስት እንኳን ደስ ያለህ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ አለቀልህ ከእዚያ እኛ የባሰ የጠና ነገር ካለ ጀሀድ መውጣት አለብን ገጀራችንን ይዘን መታገል አለብን ብሎ ሲል ሳዲቅ ኃይሩ ከእዚያ ከተቀበለ በኋላ መሐመድ አባተም በተመሳሳይ እኛ ለዲናችን ነው ዲናችን እስከሆነ ድረስ ትግላችን ይቀጥላል መታገል አለብን ብሎ መሐመድ አባተ መግለጫ እዚያው ላይ ሰጠ የእዚያን ሰዓት ማለት ነው
- እንዴት ነው መታገል አለብን ሲል ምን ምን ቃላት እየጠቀሰ ነው ሲል የነበረው ?
- በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ላይ አዲስ ኃይማኖት አመጣብን መንግስት 2ኛ ሀባሽ የሚባል አስተሳሰብ የኢትዮጵያ መንግስት አዲስ እምነት የለኝም ብሎ ይል ነበር ዛሬ እምነት አዲስ እምነት አምጥቶ ለሕዝበ ሙስሊሙ ትምህርት እያስተማረ ነው ብሎ መግለጫ ሲሰጥ ነበር እዚያ ላይ
- ማን ነው ይሄንን መግለጫ የሰጠው ?
- መሐመድ አባተ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ ሳዲቅ ኃይሩ ከተናገረ በኋላ መሐመድ አባተም በተመሳሳይ በማለት ገልፆዋል ሳዲቅ ኃይሩ ያለውን ቃል ደገመው እያሉን ነው ?
- አዎ
- ምን ብሎ ነው የደገመው እስቲ ?
- ደማችን ለዲናችን
- ደማችን ለምናችን ማለት ነው ?
- ደማችን ለዲናችን ማለት ትግላችን ለኃይማኖታችን ነው ትግላችን በኃይማኖታችን መጋደል አለብን ማለት ነው በአማርኛ አነጋገር
- አሁን እንትኑን ተርጉመውልን ነው ደማችን ለዲናችን ማለት ደማችን ለኃይማኖታችን /ግልፅ ያልሆነ/ ማለት ነው እንዴት ነው ?
- የተከበረው ፍ/ቤት እንቃወማለን ይሄንን ጥያቄ /ግልፅ ያልሆነ/ ዐቃቤ ሕግ የሚፈልጉትን ነገር የማረጋገጥ መሪ ጥያቄ እና ትርጉም
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ የሙያ ምስክር ሳይሆኑ በአይን ያዩትን ነው እና ትርጉሙ ምን ማለት ነው የሚለው ነገር እሳቸው እንዲተረጉሙ ማድረጉ አግባብ አይደለም ወይም መጀመሪያ የሙያ ምስክር ስለመሆናቸው ይረጋገጥ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ይስጡበት
- አሸ. የተከበረው ፍ/ቤት ምስክራችን ያዩትን ነው እየመሰከሩ ያሉት ድርጊቱም የተፈፀመው መስኪድ ውስጥ ነው ኃይማኖታዊ ቋንቋ ተጠቅመዋል በኃይማኖት ሽፋን ተጠቅመው የሽብር ወንጀል ፈፅመዋል እኛም ክሳችን ስለሆነም የኃማኖቱ ተከታይ እንደመሆናቸው በኃይማኖታቸው ምን ማለት እንደሆነ ነው እየገለፁልን ያሉት እንጂ የሆነ እንትን ቃል ሰጠን ይሄንን ተንትኑልን እያልን አይደለም ስለሆነም ተቃውሞ ያለአግባብ የቀረበ ነው ውድቅ ሊሆን ይገባል
- ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን እና ምላሹን /ግልፅ ያልሆነ/ ትዕዛዝ ሰጥቷል ምስክሩ እየሰጡ ካሉት ቃላት ውስጥ ኃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ንግግሮችንም እያካተቱ ለመሆኑ ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል ይሄንንም መሠረት አድርጎ ዐቃቤ ሕግ ምን ለማለት እንደሆነ ማብራሪያ ነው እየጠየቀ ያለው ወይም ትርጉሙ እንዲገለፅ ግልፅ እንዲሆን ጥያቄ እያቀረበ ያለው ምናልባት ምስክሩ ይሄንን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለመግለፅ የማይችሉ እንደሆነ መግለፅ የሚገደዱበት ሁኔታ ባይኖር እንጂ እነዚህ የቀረቡትን ኃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ቃላትም ምን ለማለት ነው ብሎ መጠየቁ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥም የሚጠቅም እና ትክክለኛ ጥያቄ ነው ብሏል ፍ/ቤቱ ስለዚህ ጥያቄው ይቀጥል

- እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት እስቲ እንዴት ነበር ሲሉ የነበረው ?
- ዲናችን ለደማችን በሙስሊሙ ሕብረተሰብ መንግስት አዲስ ኃይማኖት አምጥቶ እያጠመቀን ነው ያለው ለእዚህም ሀባሽ እንኳን ደስ ያለህ መንግስት እንኳን ደስ ያለህ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ አለቀልህ
- እንዴት ነው አለቀልህ ማለት ምን ነበር ?
- ተጨፈጨፈላችሁ ማለት ነው
- ማን ነው ጨፈጨፉችሁ የሚሉት ?
- እነ መሐመድ አባተ እና ሳዲቅ ኃይሩ
- በማን ተጨፈጨፉ ነው የሚሉት ?
- እነሱ የሚሉት በሀባሽ ማለት በእምነት ተከታዩ ማለት ነው ትክክለኛ የቀደምቱ ኃይማኖት ተከታዩ ማለት ነው እና መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ጀሀድ ልንነሳሳ ይገባል ሰላማዊ እኛ በአሁን ሰዓት ሰላማዊ ትግል ነበር እያደረግን ያለነው አሁን ግን እየተደረገብን ያለው መንግስት እያመጣብን ያለው በኃይማኖታችን ነፃነታችን እንዳይከበር አዲስ ኃይማኖት አምጥቶ እያጠመቀብን ባለበት ሰዓት እኛ ለዲናችን ደግሞ ልንቆም ይገባል በማለት ቅስቀሳዎችን እዚያ ጋር ሲደረግ ነበረ ከእዚያም በኋላ አቶ ያሲን ኑሩ ሐምሌ 8 ቀን ላይ ጠዋት አንዋር መስኪድ ላይ አላህምዲሊላህ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሆይ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል የቀድምቶች መንግስታቶች በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብተው የማያውቁት የአሁኑ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ሀባሽ የተባለ አስተሳሰብ እያስተማረብን ነው እየጠመቀብን ነው እሱን አቁምልን ነው ብለን እየጠየቅን ያለነው ስለዚህ መንግስት ጣልቃ ገብቷል ሲል ያሉት የነበሩት ጩኸት ነው ሲሰማ የነበረው
- እንዲህ ሲል ማን ነበር መስኪድ ውስጥ ?
- ያው ምዕመናን ነበረ
- ተከታዮች ማለት ነው ?

12 51

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተከታዮቹ የእነሱ ጥቂት ተከታዮች ከእዚያን ማይክራፎኑን እንደገና ቀጠለ እና ለአቡበከር ተሰጠው አቡበከር ከተሰጠው በኋላ
- አቡበከር ማን ?
- አቡበከር አህመድ ከተሰጠው በኋላ እኛ እስካሁን ድረስ የፌዴራል ፖሊስ መግለጫ ያወጣውን እንቃወመዋለን ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ለፀጥታ ስነ ስርዓት ተብሎ መግለጫ ወጥቶ ነበር ፌዴራል ፖሊስ በፀጥታ ዙሪያ ማለት ነው እንቃወመዋለን አሁን ማንንም አንፈራም መታገል እንችላለን ጀሀድ መውጣት እንችላለን ጀሀድ መነሳት እንችላለን ጀሀድም መነሳት አለብን ብሎ ሲል በስነ ስርዓት አዳምጬዋለሁ ሰምቼዋለሁ
- ምንድን ነው ጀሀድ ማለት ?
- ጀሀድ ማለት ጦርነት ማለት ነው እልቂት ማለት ነው በቃ የኃማኖታዊ ሰበብ ተደርጎ ሽፋን ተደርጎ /ግልፅ ያልሆነ/ ማለት ነው ኦልሞስት በሸሪያችን የሌለ ሕግ ማለት ነው
- ማን ላይ ነው ጀሀድ እናደርጋለን የሚሉት ?
- በመንግስት ላይ
- ይቀጥሉ ሌላስ ?
- ከእዚያን አቶ ካሚል ሸምሱ መድረኩን ከተረከበ በኋላ የኢትዮጵያ ላይ ያሉት ኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ ከ 100 65 ፐርሰንት ነው እስላማዊ መንግስትን መመስረት ሊመሰርቱ ነው ብለው እንዳሉን መመስረት እኮ እንችላለን አሁንም እስላማዊ መንግስት መመስረት እንችላለን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቆጣሪ አካል የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን በምንም ታምር አላወቀውም ስለዚህ ከ 100 65 ፐርሰንቱ ሙስሊም ሕብረተሰብ ነው መንግስታትን መመስረት እንችላለን እስላማዊ መንግስት ሲል በስነ ስርዓት እዚያው ላይ አዳምጬዋለሁ ሰምቼዋለሁ
- ሌላስ ይቀጥሉ
- ከእዚያን በኃይማኖታችን ጣልቃ የገባብን መንግስት ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ልንታገለው ይገባል መንግስት በኃይማኖታችን እስከገባ ድረስ ትግላችን ይቀጥላል ከብቶታችንን ቢታረዱም እኛም ደግሞም እስከ መጨሻው ድረስ ደማችንን ለመስጠት የተነሳሳን መሆኑን እናረጋግጣለን እያለ ባሉት ላይ ያንቀሳቅስ ነበር
- ከእዚያ በኋላስ ምን ዓይነት እንቅስቃሴ ነበረ እዚያ አካባቢ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አካባቢው ላይ ከእዚያ በኋላ ያለው አካባቢው ላይ ነዋሪው በተለይ አንድ የታዘበው ነገር አለ ኢትዮጵያ መንግስት ለኃይማኖታችን እስካሁን ድረስ ቀደምት ባልነበሩት መንግስታት የተሰጠን ነፃነት ያለን ሀገሮች ነን የተከፋ ያለው ሕብረተሰቡ እዚያ አካባቢ ላይ ልማትን እንጂ ጦርነትን ያልፈለገ አካል ነው በነበረው ሕዝብም ላይም እራሱ ግን የተነሳሳው ሕዝብ ግን በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ሽፋን ኃይማኖታዊ ይዘት ተደርጎ ፖለቲካዊ ነበር ሲሰጥ የነበረው ፣ አፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰሳ አለ ተብሎ እየተባለ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትንም ቢሆን የመቃወሙ መብት አለን
- ማን ነበር ሲቃወም የነበረው ?
- ያሲን ኑሩ መብት አለን መታገል እንችላለን
- እንዴት ነበር እንቅስቃሴአቸው በቡድን ነው ወይስ በግለሰብ ነው እንዴት ነበር ሲያደርጉ የነበሩ ?
- በቡድን ነበር
- ማን ነበር የሚመራው እንቅስቃሴውን ?
- መድረክ መሪው ኦልሞስት ማን እንደሆነ ስሙን አላውቀውም
- አጠቃላይ እንቅስቃሴው በምን ነበር የሚመራው ?
- በቡድን ነበረ
- ምን ነበር የሚባለው ቡድኑ ስሙ ?
- ቡድናቸው ኦልሞስት ኮሚቴዎቻችን ነው የሚሉ የግል ኮሚቴዎቻቸው ናቸው እንጂ የሕዝብ ኮሚቴነት የላቸውም
- ስንት ናቸው ኮሚቴዎቹ እስቲ ማን ማን ናቸው የኮሚቴው አባላት የሚያውቁት ካለ ?
- አቶ አየነው መሐመድ ፣ ያሲን ኑሩ ፣ አቡበከር አህመድ ፣ አህመዲን ጀባል ፣ ኑሪ ቱርኪ
- ይቀጥሉ ?
- ያሲን ኑሩ እነ አህመዲን ጀባል በቃ እነሱን እነሱን የማውቃቸው
- እሺ ስላለፉት መንግስታትም ያነሱ ነበር ብለዋል ምን እያሉ ነበር የሚያነሱት ስላለፉት መንግስታትም ስላለፉት ነገስታትም ያነሱ ነበር ብለዋል ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን እያሉ ነበር የሚያነሱት ?
- የሚያነሱት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ሲዋቀር በእነ ሀጂ መሐመድ ሳሊ ሀቢብ በትዕግስት እና በትዕግስት ነበር ሲመሰርቱ የነበረ ከእዚያ በፊት ግን እስልምና ኢትዮጵያ ውስጥ ላይ ባልነበረችበት ሰዓት ለእዚህ ያበቁልን እነ ሀጂ መሐመድ ሳኒ ሀቢብ ትክክለኛውን እስልምና ሲያስፋፉልን የቆዩ ነበሩ እና በእዚያ ሰዓት እንኳን ባልነበሩት ጊዜ ኢትዮጵያ ሙስሊም ላይ ተቻችለን እና ተከባብራ ነበረች የኖረችው አሁን ግን መንግስት አዲስ ኃይማኖት አምጥቶብናል እና ያንን እንታገላለን ብለው ሲሉ እንደእኔ አስተሳሰብ የተከበረው ፍ/ቤት ልትገነዘቡልኝ የሚባ እኛ ሙስሊሞች ተቻችለን የኖርን ነን
- /ግልፅ ያልሆነ/
- በስም የጠሩት ካለፉት መንግስታት ወይ ነገስታት አለ በስም የተጠራ ንጉስ ወይም ባለፉት ነገስታት ወይ መሪዎች በስም የተጠራ መሪ አለ ?
- አዎ
- ማንን ነበር ሲጠሩ የነበሩት?
- አፄ ኃይለስላሴ እና ደርግን
- እንዴት ነበር እንቅስቃሴአቸው አሉ የእነሱ ተከታዮች ግቢ ውስጥ ነበሩ ብለዋል ?
- አዎ
- ምን እያሉ ነበር የሚቀሰቅሷቸው የሰውስ መልስ እንዴት ነበረ ?
- አላህ ክበር /ግልፅ ያልሆነ/ አላህ ዋክበር
- ሁሉም ሰው ነው የሚለው እንደዚያ ?
- የእነሱ እንትኖች አባሎቻቸው አዎ
- ማን ነበር መስኪድ ውስጥ የነበረውን እንቅስቃሴስ የሚቆጣጠረው ማን ነው ?
- ማንም የለም አስተዳደሩም የለም ፀጥታዎች አካሎችም የሉም
- በማን ተተክተዋል ማን ነው ፀጥታ ለምሳሌ ጥበቃን ስራ የሚያከናውነው ማን ነው ?
- ፖሊስ ነበር በዳር በዳር ውጪ ላይ ፖሊስ ነበረ
- ውስጥስ ?
- ውስጥ ማንም የለም

ECLN
1254
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስትገባ እንዴት ነበር የገባኸው ወደ መስኪድ ?
- እኔ ጠዋት ሱቢን ሰላት ሰገድኩኝ በእዚያው እዚያው እንደተቀመጥኩኝ ያው አዳዕመጥኩ አንድ ላይ የጋራ ሆኜ ማለት ነው
- ባልደረባዬ ይቀጥል
- ሰይድ ሐምሌ 2003 ዓ.ም የተፈፀመ ነገር /ግልፅ ያልሆነ/
- ማታ ማለት ነው
- ሐምሌ 2003 ላይ የተፈፀመ ነገር ካለ ንገረን ?
- መቃወሚያ
- አስመዝግቡ
- ዐቃቤ ሕግ እየመሩ ነው ምስክሩ ሐምሌ 2 የተፈፀመ ድርጊት አልገለፁም ስለዚህ ሐምሌ 2 እያሉ እየመሯቸው ነው በትክክል ስለዚህ ይሄ ጥያቄ ሊመዘገብብን ስለማይገባ መቃወሚያውን /ግልፅ ያልሆነ/
- የተከበረው ፍ/ቤት እኔ ሐምሌ 2 አላልኩም ሐምሌ 2 የተፈፀመ ነገር የለም ምስክሩ ከ 2003 ዓ.ም ጀምሮ ስላሉ ሐምሌ 2003 ላይ የሆነ ነገር አለ ወይ ነው ያልኩት የሚያስታውሱት ነገር ካለ ይናገሩሉ መሪ ጥያቄ ትላንትና ተደጋግሞ ፍ/ቤቱ ብይን የሰጠበት ጉዳይ ነው ምስክሩን አሎ ወይ አይደለም የሚል መልስ የሚያሰጥ ነው መሪ ጥያቄ የሚባለው ስለዚህ ብይኑን ሊያከብሩ ይገባል የተከሣሽ ጠበቆቹ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ ነው ስነ ስርዓቱ መቃወሚያ ቀርቧል መልስ ሰጥተዋል
- /ግልፅ ያልሆነ/ ትላንትና ደግሞ የተሰጠ ብይንም የለም በእዚህ ጉዳይ ላይ
- የተከበረው ፍ/ቤት ስነ ስርዓታዊ አይደለም የጠቢቃው ንግግር
- ቆይ አልጨረስንም እኛ ከእዚያ በኋላ
- ስነ ስርዓታዊ አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አይችሉም የተከበረው ፍ/ቤት መልስ ሰጥተናል ብይን የሚሰጠው
- /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል እንግዲህ በዋነኛነት በጠበቃ የተነሳው ጥያቄ ሐምሌ 2 ቀን ስለተፈፀመ ነገር ምስክሩ የመለሰው ነገር የለም ስለዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ዐቃቤ ሕግ እያለ ያለው ምስክሩ በአጠቃላይ እስከምን ያህል ጊዜ ስለጉዳዩ እንደሚያውቅ አስረድቷል አጠቃላይ እርዝመቱን ከእነዚህ ጊዜአቶች ውስጥ በእዚህ ጊዜ ስለተፈፀመው ነገር የምታውቀው ነገር አለ ብለን ነው የጠየቅነው የሚል ነው ፍ/ቤቱም ጥያቄውን እንደተመለከተው ምስክሩ አጠቃላይ ጊዜዎቹን እርዝመቱን አመልክቷል ከእዚህ ውስጥ ምናልባት ተለይቶ የተጠቀሰው ቀን በጥያቄው ውስጥ መካተቱ ቀርቶ በወራት በወራት ውስጥ ስለተፈፀመ ነገሮች ጥያቄው መቅረቡ መሪ ጥያቄ /ግልፅ ያልሆነ/
- /ግልፅ ያልሆነ/ ሌላም እንደዚህ ከመጀመሩ በፊት ምናልባት ፕሮሲጅሩ የማይፈቅደውን ነገር እያየን ከግራ ቀኙ ከዐቃቤ ሕግም ከእዚያም እና አንዴ ጠይቋል ዐቃቤ ሕግ መሪ ነው ተብሏል ምላሽ ተሰጥቷል እሱ አለቀ ከእዚያ 2ኛ ያለው ከእዚያ በኋላ ከእዚያም ከእዚህም የሚቀርበው ስነ ስርዓቱ የሚፈቅደው አይደለም ከእዚህ በኋላ አንታገሰውም እንደዚህ ዓይነት ነገር አንፈልግም ፕሮሲጀሩ የማይፈቅድ ነገር ስለሆነ ከእሱ አንድትታቀቡ ነው ግራ ቀኙ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን ሰይድ እንቀጥላን ካቆምንበት በ 2003 ዓ.ም ሐምሌ ወር ላይ የተፈፀመ ነገር ካለ የምታስታውሰው ነገር ንገረን ?
- ትደግምልኝ
- 2003 ዓ.ም ሐምሌ ወር ላይ የተፈፀመ የተደረገ ነገር ካለ ?
- በሐምሌ ወር ውስጥ ላይ የማስታውሳቸው ማታ 5 ሰዓት ላይ ማለት ነው
- ጥሩ ምስክር ወደ ሌላ ጥያቄ እንግዲህ ስልጠናዎች ይሰጡ ነበር ይሄ እንቅስቃሴ የመጀመሪያው አካባቢ አንተ ቅድም ስትመሰክር የነበርከው እንቅስቃሴ ሲጀመር አካባቢ ስልጠናዎች ይሰጡ ነበር ብለህል እና ምንድን ነው ስልጠናው ?
- እሱ ላይ መስከረም 4 ዓ.ም ላይ 2004 ላይ ማለት ነው በእዚያን ሰዓት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በቀደምት የነበሩት መሻይኮቻችን እና አላማዎቻችን ተንተርሶ ትምህርቶች ሲሰጥ ነበረ ያንን ሲሰጥ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ለመንግስት አዳራሽ ፀጥታ ጠይቋል በደብዳቤ ከጠየቀ በኋላ ለአንድ ቀን ለመንግስት ስለሕገ መንግስቱ ትምህርት እንዲያስተምርለት መድረኩን /ግልፅ ያልሆነ/ ያስተማረውም መንግስት ስለ ኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አወያይቷል ካወያየ በኋላ በነጋታው የቀደምት የነበሩት መሻይኮቻችን

1256

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

አልሸህ አብደላ ያልሀረሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ላይ ተወልደው ሲያድጉም በነበሩት በአፄዎች ጊዜ ነበሩ እሳቸው በእዚያን ሰዓት ኢትዮጵያ የምትመራ የነበረው በክርስትና ሕግ ነበረ በእዚያን ሰዓት አልሸህ አብደላ ያልሀረሪ ለምንድን ነው እኔ አንድ ሙስሊም አካል ነኝ መንግስት እና ኃይማኖት ለምን አይለያይም ብለው አፄዎችን ጠይቀው ነበር በአፄ ኃይለስላሴ ጊዜ ማለት ነው ከእዚያን ይደበደቡ ነበር ይገረፉ ነበር ያዝንን ሁሉ ፈተና ካሳለፉ በኋላ ወደ ውጪ ሀገር ሄዶ

- በመንግስት ይሰጥ የነበረው ማን ነው በመጅሊሱ ጥያቄ የሕገ መንግስት ስልጠና ተሰጥቶ ነበር /ግልፅ ያልሆነ/ የምታውቀው ?
- አዎ
- ከእዚህ ስልጠና ጋር በተያያዘ አሁን የጠቀስካቸው የኮሚቴ አባላቶች የሚሉት ነገር ነበር?
- አዎ ሀባሽ የሚባል አስተሳሰብ እየሰጠ እያስተማረብን ነው አዲስ ኃይማኖት እየሰበከ ነው የሚል መንፈስ ነበር ይሰጡ የነበረ
- ሌላስ ?
- ሌላ ያው ቅስቀሳቸው በእሱ ላይ ተንተርሰው ቀጥታ ወደ አወሊያ የማድላት ዘመቻ ነው እነሱም የሄዱት ተሰባስበው ማለት ነው
- ቅድም ሀምሌ ወር 2004 ዓ.ም ላይ ስለተፈፀሙ ነገሮች ስትነግረን ነበር አንተ የት መስኪድ ነው የት መስኪድ አባል ነህ ?
- አንዋር
- በእዚያን ወቅት በመስኪዶች አካባቢ የነበረ እንቅስቃሴ ነበር ?
- በሐምሌ ወሮች ውስጥ ላይ
- አዎ ?
- ያው ቅዳሜ ሐምሌ 7 እና ሐምሌ 8 ቀን ነው
- ምን ነበር ?
- ሐምሌ 7 ጠዋት ላይ ያው እነ መሐመድ አባተ እና የሳዲቅ ኃይሩ ያልኳቸው እነሱ ጠዋት ላይ ጁማ ማታ ላይ ከተረበሸ በኋላ ማለት ነው ማታ ጁማ ማታ ላይ
- ጁማ ስንት ነበር ቀኑ ?
- የእዚያን ሰዓት ምሽት 5 ሰዓት

237

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀኑ ስንት ነበር ?
- ቀኑ በ 6 መስለኝ
- ሐምሌ 6 ማለት ነው ?
- አዎ
- የት የት ተረበሸ ሐምሌ 6 ?
- ሐምሌ 6 በባይሼ መስኪድ በፈትህ አባቦራ መስኪድ በሳላሀዲን መስኪድ እነዚህን አጎራባቾች ናቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- እንዴት ነበር ረብሻው በምን መልኩ ነበር ?
- ሀዛን ነው የተባለው በቃ ጥሪ
- እንዴት ይባል ነበር አዛን ማለት እንዴት ?
- በአላህ ክበር አላህ ዋክበር የሚል ነው ጥሪው /ግልፅ ያልሆነ/
- 5 ሰዓት ላይ ?
- 5 ሰዓት ላይ
- 5 ሰዓት ላይ ይደረጋል እንዴ ?
- በእስልምናችን ተደርጎም አይታወቅምም አይደረግምም
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ምሽት 5 ሰዓት
- ይሄ የአዛን ጥሪ በምን በምንድን ነው የሚደረገው በእስልምናችሁ ሕግ ?
- በእስልምና ሸሪያችን ሕግ የጦርነት መቀስቀሻ ነው
- አይደለም ?
- የጀሀድ ማወጃ ማለት ነው ማነሳሻ ነው ሕዝቡ እንዲነሳሳ
- ጥሩ ወደ እዚያ እንመጣለን ጥሩ ሰይድ ወደ እዚያ እንመጣለን ወደ እዚያ ከመሄዳችን በፊት በመደበኛ ሁኔታ አዛን የሚባለው ስንት ስንት ላይ ነው ?
- ዙር 10 ሰዓት ላይ ማን ነው 6 ሰዓት ወደ 7 አካባቢ ማለት ነው
- ቀን ማለት ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀን ሀሱር 10 ሰዓት ላይ መቅሪብ 12 ተኩል ላይ ኢሻ 2 ሰዓት ላይ ሱቢሂ ንጋት 12 ሰዓት
- ስለዚህ ከለሊቱ 5 ሰዓት ላይ ምንም ዓይነት አዛን የሚያስብል ምክንያት አልነበረም ለምን ነበረ ታዲያ ይሄ አዛን ሲደረግ የነበረው ?
- ያው ለቅስቀሳ ማለት ለጦርነት ነው
- ማን ነው ጦርነት ምን እንዲሆን ?
- ጦርነት ተነሳስቶ እንድንረባበሽ ማለት ነው
- ማን እንዲነሳሳ ለጦርነት ?
- ሙስሊሙ ሕብረተሰብ
- ሙስሊሙ እንዲነሳሳ ?
- ሙስሊሙ እንዲነሳሳ
- አሁን አንተ በጠቀስካቸው እነ ባዩሽ ሳላሀዲን አቡበከር የተባሉ መስኪዶች እነዚህ እንቅስቃሴዎች በለሊት ሲደረጉ የነበሩት በማን ነው ?
- ሲመሩት የነበረ አቡበከር ነው በመሴጅ የላከለት
- ለማን ?
- ለሳዲቅ ኃይሩ ባዩሽ መስኪድ ላይ ማለት ነው የመጀመሪያው ባዩሼ ላይ ነው
- አቡበከር ማን ?
- አቡበከር አህመድ
- ነኛ ተከሣሽን ነው የሚሉ የተከበረው ፍ/ቤት እሺ
- እሱ ቀጥታ ለእሱ ነገረው እሱ ከነገረው በኋላ አወልያ ላይ ተረበሸ ገደለ ተጨፈጨፉ
- ምን ብሎ ነው የተናገረው አቡበከር አህመድ ?
- ከብቶችም እንስሳቶችም እዚያ አስተናጋጆችም መንግስት ጨፈጨፋቸው ስለዚህ አዛን በሉ ብሎ ለእሱ ነገረው እሱ ደግሞ ቀጥታ እዚያ ጋር አዛን ሲል ያው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ሳዲቅ ኃይሩ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነዚህ በለሊት አላህ ዋክበር እያሉ የወጡ ሰዎች የኮሚቴው አባሎተ ነጥው ሠራዊ ምንድን ናቸው ?
- ግብረአበሮቻቸው ናቸው
- ግብረአበሮቻቸው ናቸው ?
- አዎ
- ምንድን ነው ያደረጉት ከወጡ በኋላ በለሊት ?
- ከእዚያን እሁድ ማን ነው ቅዳሜ እንትን አለ ቅዳሜ ላይ
- ለሊት ወጥተው አላህ ክበር ካሉ በኋላ ምንድን ነው ያደረጉት ?
- ማለት በቃ አላህ ዋክበር አላህ ዋክበር ደማችንን ለዲናችን እንታገላለን አላህ ዋክበር በቃ እየተባለ ያው ድንጋይ ውርወራ ሁሉ ነበረ ድንጋይ ውርወራ /ግልፅ ያልሆነ/ በእዚያን ሰዓት እኔም የተወሰነ ሰዓት ወጥቼ ነበረ ድንጋይ ውርወራ ወደ ፖሊሶች ነበረ በቀጥታ ሲወረወር የነበረው ከእዚያም እኔም ቀጥታ ወደ ቤቴ ምሽት ስለሆነ ገባሁ
- በእዚህ አለቀ የእዚያን ቀን ?
- አዎ
- በማግስቱስ ?
- በማግስቱ ቅዳሜ አላህምዲሊላህ የኢትዮጵያ መንግስት እና ህባሾች እንኳን ደስ ያላችሁ ሙስሊሞች እኮ አለቁላችሁ የሚል ቃል
- ማን ነው ይሄንን ?
- በሳዲቅ እና በመሐመድ አባተ አማካይነት ቅድም የተናገርኩት ማለት ነው
- መሐመድ አባተ የት ሆኖ ነው ይሄንን የሚናገረው ?
- አንዋር መስኪድ ላይ
- ምን ቦታ ላይ ሆኖ ?
- ኮንቴነሯ የሆነች ኮንቴነር አለች እሷ እላዋ ላይ ማለት ነው
- ኮንቴነር ላይ ወጥቶ ነው ?
- አዎ
- ለምንድን ነው ኮንቴነር ላይ የወጣው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እላይ ሆኖ እንዲታይ ማለት ነው ከላይ እንዲሆን
- እንደመድረክ መሆኑ ነው ?
- አዎ እንደመድረክ
- ምን አድርጎ ነበር መሐመድ አባተ ?
- እንትን ይዟል ማናገሪያ ድምፅ እንትን
- ማይክራፎን ይዟል ?
- ይሄ ገጠር እንትን የሚሉበት ማለት ነው እሱን ነበር የያዘው
- ጥሩ ምን አድርጎ ነበር ?
- የለበሰው በእዚያን ሰዓት ኮፍያ አድርጓል ጀለቢያ አድርጓል
- ቅድም ያሲን ኑሩ አቡበከር አህመድ እንዲሁም 8ኛ ተከሣሽን እያነሳህ ስትመሰክር ነበር የአህመዲንን ጀባልንም ስም በቅድሚያ አንስተሀል አህመዲን ጀባል ምን ሲያደረግ ነው የምታውቀው ?
- አህመዲን ጀባል አብሯቸው ገብቶ ነበር ውስጥ እሱም የተናገረው ንግግሮች አለ
- ይቀጥሙ እሌ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ በመጀመሪያ ስለ አህመዲን ጀባል ያወራው ነገር የለም መጀመሪያ የሰጡትን ቃል ፍ/ቤቱ ማየት ይችላል አህመዲን ጀባል ብሎ አልተናገረም አህመዲን ጀባል ስለተናገረው ነገር የገለፀው ነገር የለም ስለዚህ ዐቃቤ ሕጉ
- የተከበረው ፍ/ቤት መልስ እንስጥ
- አልጨርስኩም ፍ/ቤቱ ያስቆማል እያልኩ ነው እንጂ ከመጀመሪያው ጀምሮ ዐቃቤ ሕጉ አሁንም በተደጋጋሚ እያነሱ ነው ምስክሩ ያልጠየቀውን ነገር እየጠየቁ ነው እኛ እንዳንጠይቅ ምናልባት ፍ/ቤትም መሰልቸት ይሆናል ወይ ፍ/ቤቱ ይቆጣጠርልን ምስክሩ ያላነሱትን ነገር ነው ያነሱ አሁንም ስለአህመዲን ጀባል በግልፅ ፍ/ቤቱ ማየት ይችላል ከመጀመሪያ ጀምሮ አልተናገሩም ስለዚህ ይሄ ነገር ይስተካከል
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ሪከርዲንግ ማሽን ወደ ኋላ መልሶ ማጫወት ይቻላል ምናልባት ከአሁን በኋላ ተደጋግሞ እንዳይነሳ ምስክሩንም ደግሞ መጠየቅ ይችላል ቅድም ማን ማን ላይ ነው የምትመሰክረው ተብሎ የ 5 ሰዎችን ዝርዝር አውጥቶ ጠቅሷል የአህመዲንን ጀባል ስም

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ጠቅሷል አንድ የሌላ ሰው ስም ጨምሮ ጠቅሷል እነዚያ 4ቱ ሰዎች ላይ እንዲህ አደረጉ እንዲህ አደረጉ ብሎ ሲናገር ነበር አህመዲን ጀባል ላይስ ምንድን ነው ያደረገው ቅድም ስሙን ጠቅሰህል ምን ሲያደርግ ታውቃለህ ብሎ መጠየቅ የቱ ጋር ነው የስነ ስርዓት እና ግድፈቱ ምንም ሊታየን አልቻለም

- ወደ ኋላ ሪከርዱ /ግልፅ ያልሆነ/ የተከበረው ፍ/ቤት
- ጨረስን እኮ
- ምስክሩ ያው የሰዎችን ስም ዝርዝር ሲጠቅስ ነበር በእዚህ ላይ ኮሚቴዎች ነበሩ የኮሚቴ አባላት ነበሩ እነ ማን ናቸው አባላት የምታውቀው ሲባል ያው የጠቀሰ ብዙ ሰዎች አሉ ከእዚያ ውስጥ አህመዲን ጀባል ጠቅሷል ብዙ ሰዎችን ከጠቀሰው ውስጥ ማለት ነው ወደ 5 ወይ 6 ሰዎችን ጠቅሷል ከ6ቱ አንዱ አህመዲን ጀባልን ጠቅሷል እዚህ ውስጥ ሌላም በኩል ያው በግልፅ ምላሽ እንትን ላይ ያልደረስነው ነገር አለ አከራካሪ ሊሆን የሚችለው እና /ግልፅ ያልሆነ/ ተከሣሽ ነው ስለተከሣሽ ምን ታውቃለህ የሚለው ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ነገር እንደታሳብ አለ ነገር ግን አሁን ለያዝነው ጉዳይ ግን ያው የተጠቀሰ ስለሆነ መቀጠል ይችላሉ ተብሏል
- የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን ምስክር ካቆሙበት ይቀጥላሉ ቅድም ከኮሚቴ አባሎች መካከል አህመዲን ጀባል አንዱ ነው ብለዋል አህመዲን ጀባል ምን እንዳደረገ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- አህመዲን ጀባል አወሊያ ላይ እንቅስቃሴ ሲያደረግ እዚያ ንግግር ሲያደርግ
- መቼ ነበር እስቱ ከጊዜው ይጀምሩ እና ? ያስታውሳሉ ?
- ቀኑን ብዙም አላስታውሰውም በተደጋጋሚ መድረኮችን አዘጋጅቷል 2004 ዓ.ም ውስጥ ነው
- 2004 ዓ.ም ውስጥ?
- አዎ
- ተደጋጋሚ መድረኮችን ሲያዘጋጅ ምን ሲል ነበር ?
- እዘ.የ ውስጥ ላይ የምርጫ ማን ናች ይቺ ፎርም
- ወሩ መቼ ነው ?
- ወሩ የመጀመሪያ ወደ ጥቅምት አካባቢ ወደ ሕዳር አካባቢ ላይ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አዎ ፎርም አዘጋጁ እና ስም ዝርዝሩን አዘጋጁ እና የእዚያን ሰዓት አርብ ሰዓት ነው ዕለቱ አርብ ቀን ነው

1262

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ወረቀቶችን ይዘው ኮሜቴዎች እነዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ እነ አህመዲን ጀባል እነ አቡበከር አህመድ እነ ያሲን ኑሩ እነ ኢየነው ሙሐመድ እነ ካሚል ሸምሱ የሚሉትን ገፃቱን ዝርዝር አድርገው ወረቀቶች መበተን ተጀመሩ

- ማን ነው ያዘጋጀው ይሄንን ዝርዝር ?
- አህመዲን ጀባል ካዘጋጀው በኋላ ይሄንን በየሰፈራችሁ በያላችሁበት ቦታ እየሄዳችሁ አስፈርማችሁ አምጡልን ኮሚቴዎች እኛ ነን ብሎ ወረቀቶቹን የእዚያን ሰዓት አስበትኗቸዋል
- ከእዚያ በኋላስ በነበሩ ተደጋጋሚ መድረኮች ?
- ከእዚያ ከተደጋጋሚ መድረኮች ላይ ጥቂት የእምነት ሰበካ ተደረገ እና /ግልፅ ያልሆነ/ ያሉት ግን መንግስት እና ሙስሊሙ ላይ የተንተራሱ ከጠመቃዎች እያሉ የሚሏቸው ለምሳሌ ሀባሽ የመጣው ሱሪ /ግልፅ ያልሆነ/ ልታሰግድ ነው ሰላት 2 ወቅት ሰላት ነው ተባለ 2 ቀን ብቻ 2 ጊዜ ብቻ ዘካ ተከልክሏል መብላት ይቻላል ይፈቀዳል ተብሏል የሚሉ ሁሉ ቃላቶችን መንግስት አዲስ ኃይማኖቱ ላይ ካመጣቸው እነዚህ ናቸው ሕዝበ ሙስሊሙን የሚያደናግሩ ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌላስ ምን ሲል ሰምተውታል አቶ አህመዲን ጀባል ?
- ሌላ ከማስታውሳቸው ብዙ ቀናቶች ስለሆኑ
- 2003 ላይ በእስልምና ምክር ቤት የተደረገ ስብሰባ ነበር እንዴ ?
- 2003 ስልጠናው ከማውቀው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አቶ ሰይድ የእዚህ አሁን ሁላ የገለፁት እንቅስቃሴ አላማው ምንድን ነው ?
- ዓላማው በአጭሩ የሽብርተኝነት እንጂ /ግልፅ ያልሆነ/ የእምነታችን ጉዳይ አይደለም
- በምን ማለት ምንድን ነው እንቅስቃሴው ?
- እንቅስቃሴውን ማለት ያው ግልፅ እንዲሆን በኃይማኖታችን የሌለ እምነቱ በአጠቃላይ የማያዝ ከቁራአን እና ከሀዲስ ውጪ የወጣ ይዘት እንቅስቃሴ ነው
- ቅድም እነዚህ አሁን ሀበሽ እንደዚህ ሊያደርግብን ነው እንዲህ ሊያደርግብን ነው ብለው የገለፁዋቸው አስተምሮ የሚመስሉ ነገሮች አሉ አሉ ማለት ከእዚህ የተለየ አስተምሮ ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚከተሉት ምንድን ነው አሁን የእነሱ በአስተምሮ ደረጃ እናንተ የምትለዩት ወይም የሚያውቁት ነገር አለ ?

- እነሱ እና እኛ የእኛ እና የእነሱ የሚለያይበት ዋናው እነሱ የሚከተሉት በፈረንጆች ነው በአረቦች ማለት ነው በቁራን እና በሀዲስ አያምኑም በቁራን እና በሀዲስ አለማመናቸው ደግሞ አንዱ የአላህን ቃል ማክበር ብቻ ትክክለኛ ሙስሊም ነው ብለን እናምናለን
- አዎ እነሱ አሁን የእነሱ ዓላማ ምንድን ነው ማለት ምንድን ነው የሚፈልጉት ?
- ስልጣን ነው በቃ በሽብርተኝነት ስልጣን ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እነ አህመዲን ጀባል እነ አቡበከር አህመድ ለስልጣን ስልጣኑ ምንድን ነው እስላማዊ መንግስትን ለመመስረት ነው
- ይሄንን በምንድን ነው የተረዱት ?
- ይሄንን የተረዳነው ነኛ በእኔ አንድ ሰው የፈለኩትኝን ማምለክ እችላለሁ ማንም አይከለክለኝም የእኔን እራሴን የአንተ እምነት ትክክል አይደለም ብዬ መስበክ አልችልም ወንጀል ነው የእኛን አምነት ካልተከተላችሁ
- የእነሱ እምነት ምንድን ነው እሷን ነው የፈለኩት በአጭሩ የእነሱ ምንድን ነው የእኛን እምነት ካልተከተላችሁ ማለት የትኛው ?
- የወሀብያ
- የወሀብያ ?
- የወሀብያ
- ቅድም ሲገልፁ ጀሀድ እንወጣለን ብለዋል እንዴት ነው ጀሀድ እንወጣለን ማለት ምን ማለት ነው ?
- ገጀራ ይዞ ጦርነት መውጣት ማለት ነው
- ገጀራ ይዞ ?
- መውጣት /ግልፅ ያልሆነ/ መቆራረጥ ማለት ነው
- እርሶ የት ነው የሚሰሩት ?
- እሱ የሚሰራው /ግልፅ ያልሆነ/

1764

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ እርሶ ?
- እኔ የምሰራው አንዋር አካባቢ ነው
- አንዋር አካባቢ ?
- አዎ
- አንዋር አካባቢ የደረሰ ነገር የሚያውቁት ነገር አለ ?
- በእዚያን ሰዓት የደረሰ ያው አንዋር ግቢ ውስጥ ላይ መስታወት መሰበሩን አስታውሳለሁ
- መስታወት ማለት የትኛው ?
- የቢሮው የአንዋር መስኪድ
- ማለት መስታወት መሰበር ማለት በማን ምን ጊዜ ቀኑን ወሩን ዓ.ም ?
- ቀኑን እና ወሩን አላስታውሰውም ግን የእነሱ ግብረአበሮች የእስልምና ጉዳይ ምክር ቤቱ ፀሐፊ በተቀመጠበት በድንጋይ ና በጫማ ደብድበውታል
- በምን ምክንያት በምን መነሻ ?
- ምክንያቱ የወረቀት የእነሱ አካል ወረቀት ይበትናል ወረቀት ሲበትን ያ ወረቀት ነኛ ከመጅሊሱ እውቅና የሌለው ነው 2ኛ ለፀረ ሽብርተኝነት የሚያስኬድ እንትን ነው ለምሳሌ መንግስት እና መጅሊስ ጋብቻቸው የሚል ወረቀት ነበረ እና የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ያው አንዳንድ ሚኒስትሮችን እየገለፀ አዲስ ኃይማኖት የሚያስተምሩልን አካሎች ናቸው የሚል ሕዝበ ሙስሊሙ ንቃ የሚል ወረቀት ነበር በእዚያን ሰዓት ያለው ያንን ወረቀት ይዞ የሚሄደውን አካል ለምንድን ነው ብለው ሲይዙት የእዚያን /ግልፅ ያልሆነ/ ማለት ነው
- ዋና ጥያቄ አብቅተናል
- ዋና ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የተከሣሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- ጥያቄአቸውን መግፍ እችላለሁ ለሚጠይቁት ጥያቄ ማስታወሻ መያዝ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ጥያቄዉ አንድ በአንድ ነው
- እሺ ምስክር ከጥቅሉ ልጅምር እርሶ ወህብያ ማለት ቁራን እና ሀዲስ የማይከተል ከእስልምና የወጣ ብለዋል ?
- ትክክል
- /ግልፅ ያልሆነ/

1265

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለጀሀድም ትርጉም ሰጥተዋል ኃይማኖቱ አሁን የምጠይቆት እርሶ ስለ እስልምና ዲግሪ አሎት በእስልምና በዩኒቨርስቲ የገቡት ዲፕሎም ዲግሪ ወይም ዶክትሬት አሎት ?
- እሱ እዚህ የሚቀርብ እሱ የሚቀርቡ አይመስለኝም ክቡር ፍ/ቤት
- ጥያቄውን ይመልሱ አሎት የሎትም ?
- እሱ ቢኖረኝ ባይኖረኝ ለእራሴ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- መቃወሚያ ምንድን ነው ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያችን ይህ ምስክር ቀደም ብለን ባስያዝነው ጭብጥ መሠረት የአይን ምስክር ነው የሙያ ምስክር ነው ብለን አላቀረብንም ኤክስፐርት /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ የተከበረው የተከሣሽ ጠበቃ ያነሱት ጥያቄ ምስክሩን /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ አግባብነት የለውም የሚል ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት በእዚህ ላይ ምንድን ነው በሀይማኖት ጉዳዮች ጀሀድ ማለት እንደዚህ ነው ወሀብያ ማለት እንደዚህ ነው ከቁራን ከሀዲስ የወጣ ነው እያሉ በአይን ያዩትን ሳይሆን ሙያዊ ማብራሪያ እሶ ነው እየሰጡ ያሉት በኃይማኖቱ ጉዳይ የጅሀድን ትርጉም ሰጡ ስለዚህ በኃይማኖት ጉዳይ በሰጡት ላይ ኤክስፐርት ናቸው ወይም ባለሙያ መሆን አለመሆናቸውን ፍ/ቤቱ ማወቅ አለበት
- ግልፅ ነው ግልፅ ነው
- ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ትዕዛዝ ሰጥቷል ምስክሩ የምስክርነት ቃሉን ሰጥቷል በዋና ጥያቄ ላይ ያንን መሠረት አድርጎ አሁን የቀረበው ጥያቄ ከየትኛው ት/ቤት ተምረሀል ወይም በእዚህ ኃይማኖት ምን ዓይነት ኳሊፊኬሽን ወይም የትምህርት ደረጃ አለህ እየተባለ ነው ጥያቄ የቀረበው ነገር ግን ከየትኛው ት/ቤት ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ አለህ የሚለው ቀርቶ በእዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን የእውቀት ደረጃ ወይም ያለውን ግንዛቤ መሠረት አድርጎ ጥያቄው ተስተካክሎ ይቅረብ
- ምስክር በኃይማኖቱ በእዚህ በእስልምና ጉዳይ ያለህ እውቀት እስከ ምን ድረስ ነው ?
- የኃይማኖቴ እውቀት እስከ 4ቱም መዛሀቦችን ፊቅህ ኡመራ [illegible] እውቀቶች አሉኝ በትልቅ መሻይኮች የተማርኳቸው ማለት ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄንን የተማሩት ገጠር ውስጥ ነው ?
- አዎ በመሻይኮች ናቸው
- በተወለዱበት መንደር ማለት ነው ?
- እንደመሰረቱ ትምህርት ኢትዮጵያ
- ለተጠየቁት ብቻ ይመልሱ መስቀለኛ ጥያቄ ስለሆነ
- እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ላይ ያጋጠማኖታዊ ተቋም /ግልፅ ያልሆነ/
- መቃወሚያ አለን
- መቃወሚያ ካለ ያው የግድ መቀበል ነው ምክንያቱም መቃወሚያ ይቀድማል ከእዚያ በኋላ ብይን እንሰጣለን ቀጥሉ መቃወሚያችሁን ?
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን መቃወሚያ አቅርበን ታልፏል በብይን ይታለፍ ጥያቄው ተስተካክሎ የኳሊፊኬሽን ጥያቄው ይቅር እና የእውቀት ደረጃቸው ይጠየቁ ተብለው የእውቀት ደረጃቸውን ጠይቀዋቸዋል አሁን በድጋሚ ያንኑ ጥያቄ በብይን የታለፈውን ትምህርት ቢታቸውን ተመሳሳይ ነው ኳሊፊኬሽን አሁን አሁንም የኳሊፊኬሽን ጉዳይ ነው የትኛው ቢታ ነው የተማርከው ባህላዊ ነው ኃይማኖታዊ ነው ተብሎ ነው እየተባለ ነው እየተጠየቁ ያሉት እና አግባብ አይደለም በብይን ታልፏል እንትናቸውን ተናግረዋል የኃይማኖት እውቀታቸው ምን ያህል እንደሆነ
- የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም በብይን የተሰጠው እና አሁን እየጠየኩ ያለሁት ዞሮ ዞሮ ቅድም ይሄ በተጨባጭ ዲግሪ ዲፕሎማ የሚለው ተስተካክሎ ይቅረብ ነው እንጂ የተባለው ይቅር አልተባለም በእዚያው መሠረት ኃይማኖታዊ ጉዳይ በሰጡበት ጉዳይ ምን ያህል እውቀት አላቸው የሚለውን ነው እኛን ፍ/ቤቱን ሁሉም ማወቅ ስላለበት ያንኑ በሚገልፅ ነው አሁን የእውቀት ደረጃቸውን ገለፁ ይሄ በእርግጥ ያሉት ነገር እውነት ነው እውነት አይደለም የሚለው ነገር ለማረጋገጥ ነው ቀጥሎ የመጣው ጥያቄ ስለዚህ መቃወሚያው አግባብ ስላልሆነ ጥያቄውን እንድንቀጥል ይፈቀድልኝ
- ምንድን ነው ጥያቄው ነገሪ ነው ጥን ጥያቄው ነገሪ ነው ሲባል ምን ማለት ነው ምስክሩ ከሚያውቀው በላይ እንዲመለስ ባይገደድ ጥሩ ነው የሆነ መልሰዋል ከእዚያ ውጪ ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ ነው እንጂ ቅድም ስለኃይማኖታዊ የሆነ ነገር የዘረዘሩት ምን ማለት ነው የሚሉት ከሚያውቁት እየዘረዘሩ ነበር እሱን ምናልባት እሱ ላይ ጥርጣሬ ካላችሁ የማያውቁት መሆኑን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እና የሚያውቁት መሆኑን ማረጋገጥ ትችላላችሁ ምስክሩ ከመሰሰ በኋላ ጥያቄ መሄድ ነው አሁን ምስክሩ የሆነ የሚያውቃቸው ነገሮች ጠቅሷል ከእዚያ በኋላ የግድ ይሄንን መጫሰስ አይጠልም ምስክር እስከሚያውቀው ብቻ ድረስ ነው የሚመልሰው የሚያውቀውን ብቻ ተጠይቆ የሚያውቀውን ይመልሳል ይሄንንም ቀደም ሲል ዐቃቤ ሕግ መጀመሪያ አንስቶት ስለነበረ ኃይማኖታዊ ቃሎች ይናገር ስለነበረ ከራሱ የሚወጡትን ደግሞ ማብራራት ስለነበረበት ያንን አብራርቷል እሱን መሠረት አድርጋችሁ ነው የምትጠይቁት ስለዚህ አሁን የሆነ መልስ መልሷል ከእዚያ የቀረ አለ የምትሉት ካለ ብቻ ነው እንትን የምትሉት

- የተከበረው ፍ/ቤት በማሳሰቢያ መልክ ነው ምናልባት እንትኑ እንዳያስቸግር ምስክሩ በፍ/ቤት ጥያቄ ይቁም እስካልተባለ ጊዜ ድረስ የተጠየቁትን ጥያቄ የመመለስ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ እንዲነገራቸው ነው ይሄንን አልገልፅም ግዴታ የለብኝም ይሉ ስለነበር እንዲህ ዓይነቱ ነገር ከቀጠለ ችግር /ግልፅ ያልሆነ/
- አላሉም ምስክሩ አላሉም ይሄንን አልገልፅም ይሄ ግዴታ የለብኝም አላሉም አልሰማናቸውም እኛ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እኮ እሱን ማለት መመስከር ያለባቸው የሚያውቁትን ብቻ ነው የግድ ይሄንን አልመለሳችሁም ተብሎ ሌላ ጥያቄ /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ጥሩ አንድ ጥያቄ ብቻ ከእዚህ ጋር በተያያዘ ልጠይቆት እና አሁን ይሄንን ይሄንን አውቃለሁ ብለው ዘርዝረዋል ለእዚህ የሚያውቁ ለመሆኑ ማስረጃ አሎት እዚህ ሊያሳዩ የሚችሉት ይቺን ብቻ አለኝ የለኝም ብቻ ይበሉ እና አሎት የሎትም ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- አሁን ይሄ እንትን አይደለም
- ጨርሰናል እሺ ወደ የሚቀጥለው እንሂድ
- ይሽውላችሁ አሁንም ግልፅ ሁኑ ትታችሁታል ጥያቄውን ?
- አዎ
- ምክንያቱም ማስረጃ የማስባሰብ ግዴታ ስለሌለባቸው እራሳቸው የሚያውቁትን ብቻ ነው

1262

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ስለ ሀምሌ 2003 መጅሊስ መንግስትን ጋብዞ በሕገ መንግስት ዙሪያ ስልጠና እንደሰጠ ተናግረዋል ትክክል ነኝ ?
- ስልጠና ሰጥቷል አዎ
- በእዚያ ስልጠና እርሶ በመጅሊስ መንግስት መጋበዙን በምን አወቁ የመጅሊስ ተወካይ ኖት እንዴ ?
- ተሳታፊ ነኝ
- እዚያው ስብሰባ ነበሩ ?
- ነበርኩኝ
- መንግስት መጋበዙን ታዲያ በምን አወቁ ?
- ነበርኩ የእዚያን
- እራሱ ይምጣ ወይም ይጋበዝ በምን አወቁ ?
- አስተባባሪነት ሆኜ እዚያው ላይ ነበርኩኝ እኔ እራሴ
- እርሶ ስብሰባው ከመሳተፍ መንግስት የሚጋበዘው እንዴት ነው ማለት ተጋበዘ ሲሉ መንግስት የሚጋበዝበት አግባብ አለ እርሶ እዚያ ስብሰባውን ከማስተባበር ውጪ ከመንግስት አካላት ጋር ሄደው አልተገናኙም መንግስት እዚያ የመንግስት ተወካይ ሲመጣ ከማየት በስተቀር ይጋበዝ አይጋበዝ በምን ያውቃሉ ?
- ትምህርቱ ሲሰጥ የነበረው ስለ ሕገ መንግስቱ ሲያስተምሩ የነበሩ የመንግስት አካላቶች ናቸው
- ስለዚህ በቦታው ተገኝተው ሲያስተምሩ በማየትዎ ከእዚህ ተነስተው ነው አይደል ተጋብዘዋል ያሉት ?
- ሕገ መንግስቱን ሲያስተምሩ
- ነው አይደለም ከእዚህ በመነሳት ነው አይደል ያሉት ለጥያቄው ብቻ አሁን መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ስለሆኑ ማብራራት የሚፈልጉትን በኋላ ለዐቃቤ ሕግ ያብራራሉ ሲጠይቆት
- ጥያቄዋ ምንድን ነች ?
- ጥያቄው እዚያ በቦታው የስብሰባ አስተባባሪ ነበሩ ከእዚያ መንግስት የመንግስት ተወካይ መጥቶ እዚያ ንግግር ሲያደርግ ከማየቱ ውጪ የመንግስት ተወካይ በመጅሊስ ይጋበዝ ወይም በራሱ ይምጣ በምን ሊያረጋግጡ ይችላሉ ?

1269

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ይቺን ብቻ መልሱ ?

በመጅሊስ ተጋብዘ ነው የመጡ

በደብዳቤ ነው በቃል ይሄንን ማወቅ ይችላሉ ካላወቁ እኮ አላውቅም ማለት መብትዎ ነው ?

ለምን አውቀዋለሁ በእዚያን ሰዓት አዳራሽ ፀጥታ እና ስለሕገ መንግስቱ እንዲያስተምር የሚል ደብዳቤውን ነኛ በአዲስ አበባ ደረጃ ይዤው ወደ ፍትህ ጽ/ቤቱ የወሰድኩት እኔ ነኝ ስለዚህ አውቃለሁ

የመጣው ከየት ነው ባለስልጣኑን ያውቁታል ከየት ነው የመጣው?

የመጣው ከፍትህ ጽ/ቤት ሕግ እና ፍትህ ስለ ሕገ መንግስቱ ያስተማሩት አካሎች

የትኛው መስሪያ ቤት ?

- አዲስ አበባ
- ከአዲስ አበባ ?
- አዎ
- ሳልጠናው የት ነው የተካሄደው ?
- ስልጠናው የተካሄደ በኮተቤ እና በሲኤምሲ አዳራሽ
- ሌላ ቅድም ስለ አዛን ማብራሪያ ሲሰጡ ነበረ አዛን በቀን የሰላት ወቅቶችን ጠቅሰው 5 ጊዜ እንደሚደረግ ገልፀዋል ትክክል ነኝ ?
- ትክክል
- ከእዚያ ውጪ አይደረግም ነው ያሉት ?
- 6ኛ አይደረግም የለም አይደረግም
- ይሄ የሚሉት አይደረግም የሚሉት በአጠቃላይ በእስልምና ውስጥ ነው የሚሉት ?
- በእስልምና ውስጥ የተከለከለ ነው አጠቃላይ
- ከ5ቱ ውጪ ?
- ከ5ቱ ውጪ
- የለሊት ወይም የመጨረሻው ለንጋት አካባቢ የሚደረገው ሰላት ላይ 2 አዛን የተደረገበት የለም በእስልምና ታሪክ ውስጥ 2 አዛን እንዲደረግ ወይም የተደረገበት ጊዜ የለም ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሱቢሂ አንድ አዛን እንጂ 2 እዚህ አዛን የለም
- 2ኛ አዛን የለም ?
- ኢትዮጵያ ውስጥ ላይ አይተንም ሰምተንም አናውቅም ትምህርቱንም ከተማርኩት ቀናት ጀምሮ አላውቅም
- የለም የጠየኮት አሁን ስለኃይማኖት ጉዳይ ስለሆነ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ በጁማ 2 ጊዜ አዛን አይደረግም ?
- ጁማ ላይ ሁጥባ ከመጀመሩ በፊት
- ይደረጋል አይደረግም ?
- የጁማ ዙር ላይ 6 ሰዓት ቀን 6 ሰዓት ይደረጋል
- የተከበረው ፍ/ቤት ማብራሪያ አሁን እዚህ ጋር
- ቆዩ ምስክርን ጠይቀዋል አይደል ጠይቀዋል እየመለሰ ነው አያቋርጡ ምስክርን
- ማለት መስቀለኛ ጥያቄ ስለሆነ እኔ አዎ ወይም አይደለም ብዬ ከጠየኩ
- መስቀለኛ ጥያቄ አኮ ይታወቃል ፍሎሶፊው /ግልፅ ያልሆነ/ የሚነሳ አይደለም አዎ አይደለም ብቻ አይደለም መስቀኛ ጥያቄ
- ማለት እኔ የጠየኩት
- አንዱ ፓርት ነው እሱ እና ጠይቀዋል እርሶ ምስክሩን አፉ ላይ አያቋርጡ ይጨርስ እና የፈለጉትን መጠየቅ እኮ ይችላሉ ይሄ መብትዎ ነው ግን አያቋርጡት
- ስለዚህ በጁማ ቀን 2 አይደረግም ?
- ጁማ ቀን 6 ሰዓት ከቀኑ 6 ሰዓት የመጀመሪያ ጥሪ ይደረጋል 2ኛ ፎጥባ ወይም ትምህርቱን ሳምንታዊ ዘገባውን የሚያስተላልፈው አካል ሰላምታን ያቀርባል ከእዚያ በኋላ አዛን ይደረጋል ያ የሚደረገው ጁማ ቀን ላይ ነው የሚሆነው ማታ አይደለም
- ሕፃን ልጅ ሲወለድ አዛን አይደረግም ?
- እሱ ተደርጎ አይታወቅም
- አይደረግም ?
- ተደርጎ አይታወቅም እንደውም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሳሳቢ ሁኔታ ሲገጥም አዛን አይደረግም ?
- ተደርጎ የማይታወቅ ነገር ነው ይሄ
- ቅድም 4 መስኪዶች ላይ በእዚያን ለሌት አዛን ሲደረግ ሰምቼአለሁ ብለዋል እነዚህ መስኪዶች ርቀታቸው አንዱ ከአንዱ ምን ያህል ይሆናል ?
- ቅርበታቸው በጣም
- በኪሎ ሜትር ባያስቀምጡም በግምት ?
- በእስፒከር ስፋት ስለሆነ ባዩሼ ከፈትህ አባቦራ ጋር በደንብ ይሰማል ሰላሀዲን መስኪድም በተመሳሳይ ለባዩሼ ይሰማል ቅርብ ነው እስፒከሩ ከፍተኛ ስለሆነ የሚሰሙ የአክራሪዎች መስኪዶች ስለሆኑ ማለት ነው
- ጥሩ እርሶ የትኛው መስኪድ ውስጥ ነበሩ ?
- እኔ በታላቁ አንዋር መስኪድ
- አንዋር መስኪድ ምኑ ላይ ሆነው ነው ?
- አንዋር መስኪድ በስተጀርባው በኩል ላይ ማለት ነው እዚያው ነው መኖሪያ ቤቴ
- ከመስኪዱ በስተጀርባ ?
- አዎ
- እዚያ ሆነው ነው እነዚህ ከ 4 መስኪዶች የሚወጣውን ጥሪ የሰሙት ?
- ትክክል
- የትኛው ከየትኛው እንደሆነ በምን አወቁ ?
- አውቀዋለሁ ያሉትን አካሎችን አውቃለሁ
- በምን ?
- በድምፃቸው አውቃለሁ
- የምኑን ድምፅ ?
- የጩኸቱን ያሰማው አካል ድምፆችን አውቃቸዋለሁ
- ማን ነው ያደረገው እንግዲህ ድምፁን ይለያሉ ማን ያደረገውን ሰው ያውቃሉ ?
- ድምፃቸውን አውቃቸዋለሁ የት መስኪድ እንደሆነ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስፒከሮቹ ውፍረት እና ቅጥነት የትኞቹ መስኪድ የትኞቹ እንደሆኑ በደንብ ይታወቃሉ
- በእስፒከሩ ከሚወጣው ውፍረት እና ቅጥነት ?
- ትክክል
- አዛን ያደረገው ማን እንደሆነ ግን አያውቁም ?
- ሰውዬውን ማን እንደሆነ በወቅቱ አላውቅም
- እርሶ አንዋር መስኪድ ቁጭ ብለው ከእስፒከሩ
- አንወር መስኪድ በስተጀርባ በኩል
- በስተጀርባ ቁጭ ብለው ?
- አዎ
- ከእስፒከሩ እንጂ አዛን ያደረገው ማን እንደሆነ አያውቁም ?
- ማን እንደሆነ አዛን ያደረገው አካል ማን እንደሆነ አላውቅም ሲጮህ ግን አዛኑን ጩኸት ሲያደረግ ግን ሰምቼአለሁ
- ከእዚያ በኋላ ስለሆነው ሁኔታ ነግረዋል እርሶ እንግዲህ አሁን አንዋር መስኪድ ጀርባ ነው የተቀመጡት በአዚያ ከእነዚህ ከ 4 መሰረቂድ አካባቢ ሰው ወጥቶ አንዴት አንዳለ ምን አንዳለ አዛን ተክቢራ እንዳለ ፖሊሶች ላይ ድንጋይ እንደወረወረ ሁሉ ተናግሯል ትክክል ነኝ ?
- ትክክል
- ስለዚህ ያዩትም ይሄንን ሁሉ ያዩት አንዋር መስኪድ ጀርባ ሆነው ነው አይደል መኖሪያ ቤትዎ ሆነው ?
- አዎ
- ይሄንን ሁሉ ያዩት ሌላ ቅድም ያሲን ኑሩ ሲናገር እርሶ እንደሰሙትም ነግረውናል የት ሆኖ ነበር ይናገር የነበረው ?
- ያሲን ኑሩ አንዋር መስኪድ ውስጥ
- አንዋር መስኪድ ውስጥ ?
- አዎ
- ምን ዓይነት ልብስ ነበር በዕለቱ የለበሰው ?
- የእዚያን ሰዓት የለበሰው ልብሶችን ጀለቢያ መልበሱን የማውቀው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ዓይነት ጀለቢያ ?
- ነጭ ጀለቢያ
- እሺ ሌላስ ?
- ለ,ላውን አላስታውሰውም
- ቆሞ ነበር ቁጭ ብሎ ነበር የሚናገረው ?
- ቆሞ ነው የተናገረው
- እሱ ሲናገር ሌሎች የእሱን ንግግር የሚቀርፁ ሰዎች ምን አይተዋል ታዝበዋል የእሱን ድምፅ ይቀርፁ የነበሩ በተለያየ ነገር ይሄንን ነገር ታዝበዋል ?
- የሚቀርፅ ሰው የለም ነበር በወቅቱ አላየሁም
- ማንም አልቀረፀም ?
- ትክክል
- እርሶ ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ነው ያዩት ?
- ከ 2 ሰዓት ተኩል እስከ 6 ሰዓት
- እስከ 6 ሰዓት ?
- አዎ
- ጥሩ በእዚያን ቀን ተናጋሪ እሱ ብቻ ነበር እንዴ ?
- ሌሎችም የእሱ ጓዶች አሉ
- እስቲ እንደው ስለ ሂደቱ ቢነግሩን መጀመሪያ ማን ቀጥሎ ማን ማለት ያሲን መጀመሪያ ነው የተናገረው መሀል ላይ ነው ከኋላ ነው ?
- መጀመሪያ ያሲን ቀጥሎ አህመዲን ጀባል ቀጥሎ አቡበከር አህመድ ቀጥሎ ካሚል ሸምሱ
- ከእዚያ ውጪ ሌላ ተናጋሪ ነበር ?
- ሌሎችም ያደረጉ አሉ
- ጥሩ አሁን ያሲን ኑሩ ወይም እነዚህ አሁን ያሏቸው ተናጋሪዎች ሲናገሩ ሕዝቡ ቁጭ ብሎ ነበር የሚያዳምጣቸው ?
- ትክክል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቁጭ ብሎ ?
- ቁጭ ብሎ
- አላህ ዋክበር ይል ነበር እንጂ ከእዚያ ውጪ ሌላ የሚያደርገው ነገር አልነበረም ?
- ድምፃችን ደማችን ለድምፃችን ሲሉማ እነዚኛው ሲሉ ሌላውም አካልም አብሮ ይላል
- ደማችን ?
- ለዲናችን
- ለዲናችን ሲል ይሄንን ያሉት ቀን መቼ ነበር ሐምሌ ?
- ሐምሌ 8
- የትኛው ዓመት ?
- 2004
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ለመሆኑ የሚመሰክሩባቸውን ሰዎች የት ነው የሚያውቋቸው?
- በወቅቱ በግርግር እዚያው እንትን ሲሉ ነው የማውቃቸው
- ከእዚያ በፊት ያውቋቸዋል ?
- ከእዚህ በፊት አላውቃቸውም
- አያውቋቸውም ?
- አዎ
- ከእዚያ በፊት አያውቋቸውም ?
- አላውቃቸውም
- ስለዚህ ታዲያ እንዴት ማን ምን እንደተናገረ እንዴት ሊለዩ ይችላሉ ?
- ስም ዝርዝራቸውን እዚያ ይነገር ነበረ
- ማን ነው ሲናገር የነበረው ?
- መድረክ የሚመራው አካል
- መድረክ የሚመራው አካል ምን እያለ ይናገር ነበረ ?
- ንግግር እንዲያደርጉ እየጋበዛቸው ነበር ስማቸውን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም እኮ መድረክ የሚመራው አካል የለም ነበር አይደል ያሉት ?
- አለው
- መድረክ የሚመራው አካል ማን ነው ?
- እሱን አላውቀውም ስሙን እያልኩ ነው
- እርሶ የት ሆነው ነበረ ሲሰሙ የነበሩት ?
- አንዋር መስኪድ ውስጥ ነበርኩ
- ውስጥ ?
- አዎ
- ቅድም ከጀርባ አላሉንም ?
- መኖሪያ ቤቴ ነው
- እኮ መኖሪያ ቤትዎ ?
- ማታ ለሊት ምሽት 5 ሰዓት ላይ ማለት አንዋር መስኪድ በስተጀርባ ላይ በነበረው መኖሪያ ቤቴ ጩኸቱ ሲሰማ እየሰማሁ ነበር ከሰማሁ በኋላ ወጥቼአለሁ ነው ያልኩኝ
- ወጥተው ወዴተ ሄዱ ?
- ጠዋት ግን
- በቃ ማብራሪያው ይበቃናል አጭር አጭር መልስ ከሰጡን ይበቃናል ጩኸቱ ሲሰማ ወዴት ሄዱ ?
- ጩኸቱ ሲሰማ ወጥቼ አዳመጥኩ
- የት ሆነው አዳመጡ ?
- በባዩሽ አካባቢ
- እኮ አይ የነበሩበት ቦታ ነው እንጂ ጩኸቱ ከየት ይመጣል ብዬ አይደለም የጠየኩት የት አካባቢ ሆነው ሲሰሙ የነበሩት ?
- አንዋር ጀርባ ላይ ሆኜ መኖሪያ ቤቴ /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚያ ውጪ ወደ መስኪዶቹ ምናምን አልሄዱም ?
- እሁድ ዕለት ነበርኩኝ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእሁዱን ሳይሆን የቅዳሜውን ለሁነ የለርብ ግታ የተደረገውን ነገር ነው ለፍ/ቤት እያስረዱ ያሉት መኖሪያ ቤቴ ሆኜ ነው የሰማሁት ብለዋል ?
- አዎ
- ከመስኪዱ ጀርባ ነው የነበርኩት ብለዋል ?
- ትክክል
- ከእዚያ ውጪ ሌላ ቦታ ሄደዋል እዚያው መስኪዱ አካባቢ ?
- ምሽት ላይ እቤቴ እንጂ መስኪድ አይገባም
- የትም ሊሄዱ አይችሉም በጣም ጥሩ ታዲያ ድንጋይ ሲወረወር እንደነበር በምን ?
- ወጣሁኝ ወጥቼ ዞርኩኝ እና አየሁኝ
- ኧሀ ምሽት ላይ የትም አይሄድም አላሉም እንዴ ?
- እኮ መስኪድ ተብሎ አይሄድም ስራ ተብሎ አይወጣም ምሽት ከሆነ ወደቤት ነው የሚገባ ችግር በተፈጠረ ደግሞ ወጥቶ ደግሞ ችግሩ ያለበትን ቦታ ደግሞ መቃኘት ደግሞ
- ስለዚህ ባዩሼ ወይም ሌላ ቦታ ድንጋይ ተወረወረ የተባለበት ቦታ አልሄዱም ?
- ሄጀአለሁ /ግልፅ ያልሆነ/
- አሁን እኮ ምሽት ነው ተብሎ የትም አይኬድም አሉ ?
- አይደለም ሰላት ላይ ሰላት ተብሎ ምሽት 5 ሰዓት አይገባም ምሽት ነው መሸቷል ረብሻ እና ግርግር እና ጫጫታ ካለ ግን እስከሚመለከተው ድረስ መሄድ እስከሚነጋ ድረስ መሄድ ሕገ መንግስቱ ፈቅዶልኛል ብዬ አምናለሁ
- ሕገ መንግስቱ ፈቅዶሎታል ትክክል ነው ግን ለደህንነትዎ አይሰጉም እንዴት ነው ዝም ብሎ ረብሻ ጫጫታ ወይም ቅድም ድንጋይ ሲወረወር ነበር ብለዋል ዝም ብለው እንዳገኙ ይሄዳሉ ወይስ ለደህንትዎ ጥንቃቄ እያደረጉ ነው የሚሄዱት ?
- ኧረ እኔ
- ለማንኛውም አሁን የምፈልገው ጥያቄ ምንድን ነው እርሶ ከመኖሪያ ቤትዎ ወጥተው የት ሄዱ ?
- በባዩሼ አካባቢ በፈታህ አካባቢ ላይ በአውቶቢስ ተራ ዞሬ
- ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ሰዓት ?
- እስከ 6 ሰዓት ድረስ ውጪ ነበርኩኝ ከ 5 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ነ ሰዓት /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከ 5 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ?

አዎ

ረብሻ ያሉት ነገር አልቆ ነው የተመለሱት ወይስ ሳያልቅ ነው ?

ያው እያለቀ አካባቢ ላይ ልበል እዚያ አካባቢ ላይ

እያለቀ ሰዓት ላይ አለቀ ተጠናቀቀ ?

አዎ

ከእዚያ እርሶ ወደ ቤትዎ ተመለሱ ?

አዎ በሰፈራችን አካባቢ ማለት ነው ሌላ ቦታ ላይ አላወኩም

የእርሶ ሰፈር አንዋር መስኪድ ነው ባዩሼ ነው ?

አዎ እዚያው አንድ ሰፈር ነው እዚያው

እስቲ ምን ያህል ለፍ/ቤቱ ግንዛቤ እንዲረዳ ከአንዋር መስኪድ ባዬሼ ቅድም የጠቀሷቸው 4መስኪዶች ርቀታቸው ምን ያህል ይሆናል

በኪሎ ሜትር የማውቀው ነገር የለም

በግምት ለፍ/ቤቱ እንዲረዳ አሁን ከመጡበት በጢያሳ እዚህ ድረስ ነው ወይስ በግምት ማለት ነው ርቀቱ ?

ቅርበት ነው እዚያው ነው እዚያው በእዚያው ነው

እዚያው በእዚያው ?

ቅርበት አለው አዎ

እዚያው በእዚያው ሲባል ማለት እንዴት ነው እዚያው ወጥቶ መስኪድ ፊት ለፊት ?

አይራራቅም ይሰማል

ምስክር ጥያቄው ምንድን ነው እዚያው በእዚያው ማለት እንደዚህ እንደኛ አቀማመጥ ማለት አሁን ርቀታቸው ምን ያህል ይሆናል 3 መስኪዶች ነው የጠቀሱት ምናልባት በኪሎ ሜትር ምናምን ላይጠቅሱ ይችላሉ ግን እዚህ ሆነው እስከ በሩ ሊጠቅሱ ይችላሉ ወይ ከበሩ በኋላ ገምተው ሊጠቅሱ ይችላሉ ?

ማለት ሰፈሩ እዚያ ያለሁበትን ቦታ ስለማላውቀው በእንደዚህ ተምሳሌት ብዬ ማድረጉ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚህም ተነስተው ለእኛ ግምት ሊነግሩን ይችላሉ እዚህም ተነስተው ግምት ሊነግሩን ይቻላሉ ለምሳሌ በኪሎ ሜትር ፣ ኪሎ ሜትር 2 ኪሎ ሜትር ኪሎ ሜትር መቁጠር ይችላሉ እስቲ ምን ያህል ይሆናል ነው እነሱ እየጠየቁ ያሉት ?
- ማለት ግምቱ እኔ እንጃ ሰፈሩ እዚህ ያለሁበት ቦታውን አላውቀውም አሁን ለምሳሌ ከእዚህ እስከእንደዚህ ድረስ ብሎ ለማለት ማለት ነው ካለሁበት ቦታ አኳያ ስለዚህ ግን ክፍለ ከተማውም አንድ ነው ወረዳዎችም እዚያው አጠገብ ለአጠገብ ስለሆኑ በ 2 ወረዳዎች መካከል ያለ ስለሆነ
- እንግዲህ የምታውቋቸው ከሆነ መርታችሁ ጠይቁ ?
- እናመሰግናለን የኑር መስኪድ ወይም ቤኒን መስኪድን ያውቁታል ?
- አቤት
- ቤኒ መስኪድ ወይም ኑር መስኪድን ያውቁታል ?
- አውቀዋለሁ
- ርቀቱ ከእሱ ያልፋል ወይስ ከእሱ ይቀርባል ?
- ከኑር መስኪድ
- በአንዋር መስኪድ እና በኑር መስኪድ ያህል ያለው ርቀት ያክላል ወይስ ከእዚያ በላይ ይሆናል?
- እሱ ወደ እዚህ ትንሽ ቀረብ ይላል
- ከእሱ ምን ያህል ?
- ቀረብ
- ቀረብ ይላል ትንሽ ?
- ወደ ማን ነው የሚቀርበው ወደ አንዋር ነው ?
- ወደ አንዋር
- ወደ አንዋር መስኪድ ?
- አዎ
- ስለዚህ በአንድ ጊዜ ይሄንን ያህል ርቀት ባላቸው መስኪዶች ውስጥ ከ 6 ሰዓት ድርጊቱ ወይም አዛን ሲባል የነበረው 5 ሰዓት ነው ብለዋል እንዴት ይሄንን ያህል ሊዞሩ እና ሊሸከረከሩ ይችላሉ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ርቀቱ አልታወቀም አሁን ያው ያወዳደሩት ነበረ እና /ግልፅ ያልሆነ/ ግልፅ ሊሆን ይችላል ለእናንተ መዝገብ ላይ ለማስፈር ግን
- ቅድም በመሴጅ አላህ ዋክበር እንዲል የጨራው አቡበከር ለሳዲቅ ነው አሉ ?
- አዎ
- ይሄንን እንዴት እርሶ ሊያውቁ ይችላሉ ቅድም አላውቃቸውም ብለዋል በአካል አላውቃቸውም ብለዋል እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ ተነግሮት ?
- እሱን ለሳዲቅ ሀይሩ ሲደውልለት የሳዲቅ ሀይሩ ወንድም በቀጥታ ለእኔ ነው መጥቶ የደወለልኝ እንደገና ወደ እኔ
- የሳዲቅ ሀይሩ ወንድም ስንት ሰዓት ደወለለት ?
- 4 ሰዓት ከ 20 አካባቢ ማለት ነው
- ለእርሶ ስንት ሰዓት ደወለሎት ?
- 4 ሰዓት ከ 20 አካባቢ
- ከሳዲቅ ጋር እርሶ ትውውቅ አሎት ?
- ከሳዲቅ ጋር አንተዋወቅም
- የሳዲቅ ወንድም ጋር በምንድን ነው የምትተዋወቁት ?
- ከወንድሙ ጋር እንተዋወቃለን
- አቡበከርን አላውቀውም ብለዋል ?
- አዎ
- የሳዲቅ ወንድም አቡበከርን ይሁን ወይም ሌላ ሰው ይሁን ያሉት በምን ያውቃሉ ?
- አቡበከር አህመድ ነው ብሎኛል እሱ እራሲ
- እኮ እርሶ በምን ያረጋግጣሉ ስለተባሉ ብቻ ማለት ነው ?
- አቡበከር አህመድ ብሎ ስላለኝ በእሱ ነው ያረጋገጥኩት
- ሰምተው እንጂ እርሶ ያዩት ወይም እንትን ያሉት ያረጋገጡት ነገር የለም ?
- አልሰማሁኝም ግን እሱ መላኩን ግን የነገሩኝ
- ማን ነው ስሙ የሳዲቅ ወንድም የሳዲቅ ወንድም ማን ነው ስሙ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መሐመድ የሚባል
- መሐመድ ?
- መሐመድ ማን ?
- መሐመድ ሀይሩ
- መሐመድ ሀይሩ የት ነው የሚሰራው ?
- ስራውን አላውቀውም
- በምንድን ነው ትውውቃችሁ ከእሱ ጋር ?
- የምንተዋወቀው በመስኪድ አካባቢ
- በመስኪድ አካባቢ ?
- አዎ
- ስልኩን ይነግሩናል ?
- ስልኩን መስጠት አልችልም
- ስራዎት ምንድን ነው እርሶ ?
- ስራዬ እኔ አንዋር አካባቢ ላይ ንግድ
- አንዋር አካባቢ ነጋዴ ኖት ?
- አዎ
- ቅድም የመጅሊስን ደብዳቤ ለፍትህ ቢሮ ድረስ ያደረስኩት እኔ ነኝ ብለዋል ?
- አዎ
- ስራዎስ ነጋዴ ነው ?
- አዎ
- እንዴት ሆነው ይሄንን ሊሰሩ የሚችሉት ?
- በአሁኑ ወደ ንግድ አለም ውስጥ ነው የገባሁት ቀደምት ግን የመጅሊስ ስራ አስፈፃሚ ነበርኩኝ
- በምን ያህል ጊዜ ርቀት መቼ ነው የመጅሊስ ስራ አስፈፃሚ መሆኖት የቀረው ?
- ስራ አስፈፃሚ ነበርኩኝ ማለት በአሁኑ ዓ.ም ማለት ነው
- መቼ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልፃሕት በ 27 ጅምሮ
- 27 ምን ወር ?
- ምርጫ ካለቀ በኋላ /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ወር ላይ ?
- ወሩን አልሞስት አላስታውስም
- 27 ምን ዓ.ም ምን ወር ?
- 2005 ውስጥ ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ደብዳቤውን መቼ ነው ያደረሱት ?
- ደብዳቤው በመስከረም 2 ላይ ነው
- ነጋዴ በነበሩ ጊዜ ነው ወይስ ?
- ንግድ አለም ውስጥ የገባሁ ከመጅሊስ ኃላፊነቴን ሳስረክብ ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የተከበረው ፍ/ቤት ከመጅሊስ ጋር የተያያዘውን ነገር ነው
- አሁን ከመጅሊስ ጋር የተያያዘ የሚሰራውን ስራ መጠየቅ ይችላሉ አሁን ምን ስራ ላይ አለ የተባለውን ነገር አይፈቀድም በብይን የታለፈ ስለሆነ
- ቅድም ስጠይቆት ሳዲቅን ወይም ሌላውን ሰዎች አላውቃቸውም ብለዋል አይደለም በአካል አላውቃቸውም ብለዋል ?
- አላውቃቸውም የሚል ቃል አላልኩኝም
- አላውቃቸውም
- ሳዲቅን አላውቀውም አላልኩም
- ያውቁታል ?
- ሳዲቅን አውቀዋለሁ
- መሐመድ አባተን ያውቁታል ?
- አውቀዋለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተነስተው ለፍ/ቤቱ ያሳዩልን የትኛው እንደሆነ የተከበረው ፍ/ቤት ይነሱ እና ይሄኛው ነው መሐመድ አባተ ብለው ያሳዩልን ይለዩልን ሳዲቅን እና መሐመድ አባተን የትኞቹ እንደሆኑ ይለዩልን ?
- ሳዲቅ ሀይሩ ከእዚህ ውስጥ ላይ የለም
- የተከበረው ፍ/ቤት መሐመድ አባተን ይለዩልን መሐመድ አባተስ አለ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእዚህ ውስጥ
- ተነስተው እንዲታያቸው
- ተነስተው /ግልፅ ያልሆነ/ ወይ ሄደው /ግልፅ ያልሆነ/ ሄደው መሀል መለየት ይችላሉ ተረጋግተው አይተው ማን እንደሆነ ጠጋ ብለው ይለዩዋ
- የትኛው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የትኛው እኮ አስረዱ ?
- በትክክል ሳትጠቆሙ እጃችሁን አታውጡ
- ቆመው እርሶ ያሳዩልን /ግልፅ ያልሆነ/
- እሱ ነው ?
- እሱ ነው ተነስ
- /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን የተነሳው ስምህ ማን ነው ?
- አብዱራዛቅ
- ስንተኛ ተከሣሽ 23ኛ ተከሣሽ
- ማን ነው ያሉት ስሙን መሐመድ አባተ ነው ያሉት አይደል ?
- አዎ መሐመድ አባተ
- እሱን የሚመስል ነው ያሉት ?
- የሚመስለው አዎ
- የተከበረው ፍ/ቤት አውቀዋለሁ ብለዋል ለይተው አሳይተዋል
- የሚመስል /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእዚያን ሰዓት ነው ያየሁት እና ያየሁት በእዚያን ሰዓት እሱን ነው የሚመስለው
- የተከበረው ፍ/ቤት ግን በስነ ስርዓቱ መሠረት መሆን ያለበት ተከሣሾች ብዙ ስለሆኑ ቁጭ ብለው እንዲከራከሩ እየተደረገ ያለው አንድ ምስክር መጥቶ በእነዚህ በእነዚህ ሰዎች ላይ ነው የመመሰክረው ሲል እነዚያ ስማቸው የተጠራ ሰዎች መነሳት አለባቸው ቆመው ነው
- እንቃወማለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄ ነው 128 የሚያዘው ይሄንን ነው እና የተለየ ፕሮሲጀር /ግልፅ ያልሆነ/
- ምናልባት አንድ ተከሣሽ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ፍ/ቤቱ ያውቀዋል ምን እንደሚደረግ
- ለእናንተም እኮ አልተፈቀደም ለእናንተም አልተፈቀደም ዐቃቤ ሕግም እንዲያቆሙ ተደርጓል ስለዚህ ምስክርነት ቃሉ በሚሰጥበት ሰዓት አንድ መሐመድ አባተ መሐመድ አባተ ነው የተባለው እንዲለዩ ተብሏል የሚያውቁ ወይም የሚያስተውሉ ከሆነ እስቲ አሳዩን ብለናል ማን ነው አቡበከር አብዱራዛቅን ይመስላሉ እሳቸውን ይመስሉኛል ብለዋል እንግዲህ በኋላ ላይ ፍ/ቤቱ ሲመዝን የሚመለከተው ነገር ነው የሚሆነው ከእዚያ ውጪ ግን ስለ ማን ሊመስክሩ ምስክሩ እንደመጡ ያስመዘገቡት ነገር አለ ዝርዝር ጥያቄዎቹ ቀርበው በግራ ቀኞቹ የተመዘገበ ነው የሚል ነገር ስላለ በእዚህ ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ ጨርሳችዋል መስቀለኛ አለ ?
- አዎ አመሰግናለሁ ሰይድ ከእዚህ በፊት በተመሳሳይ /ግልፅ ያልሆነ/ ጉዳዮች አሉ ስንት ናቸው በተመሳሳይ ጉዳይ የመሰከርክባቸው ስንት ናቸው ?
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ተቃውሞአችሁ ምንድን ነው
- ከእዚህ ጉዳይ ጋር የተያያዘ አይደለም እኛ የምስክሩን የምስክርነት ታሪክ አይደለም ያስመሰከርነው ምስክሩ የአይን ምስክር ናቸው ያዩትን እና የሰሙትን በቀጥታ አስረድተዋል ከእዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዥነት እውነት አይደለም የሚለውን ኢምፒች ማድረግ ነው የሚችሉት ስለዚህ ከእዚህ በፊት የነበራቸው የምስክርነት ታሪክ መጠየቅ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነትም የለውም አግባብነትም ያለው ጥያቄ አይደለም
- የተከበረው ፍ/ቤት ታአማኒነቱ መመዘን እንዲያስችለው ነው ለፍ/ቤቱ ባለቤት የሚጠይቀውም ነገር ካለ መጠየቅ እንዲያችል ነው ያነሳሁት በማን በማን ጉዳይ ላይ መስክረሀል አይደለም

http://ethcriminalawnetwork.com/

ለስንት ጊዜ እና በእዚህ በተመሳሳይ ጭብጥ ላይ ስንት ጊዜ ምስክርነት ቀርበሀል ይሄንን ብቻ ነው የጠየኩት

- ይሽው ሌላ ክርክር ሳንገባ ግልፅ ነው እኛ የምናውቀው እዚህ ነው አሁን ምንድን ነው እዚህ ነው የመሰከሩት አሁን ሌላ ምስክር ከእዚህ በፊት አልጠራንም እኛ እንግዲህ ተነስታችሁ የምትጠይቁት ጥያቄ ካለ ከእዚህ በፊት እዚህ መጥተው መስክረዋል ?
- አይ በተመሳሳይ ጉዳዮች ምስክርነት ቀርበው ሲመሰክሩ
- ጥያቄው ግልፅ ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ጥያቄውን ብቻ ይጠይቁ መስቀለኛ ጥያቄ
- እሺ 2003 እና 2004 ስልጠና ተሰጥቷል ብለዋል ማለት የአብደላ ሀረሪ ቀደም ያሉ መሻሂ ነበሩ የእሳቸውን እንትን በተመለከተ ስልጠና ተሰጥቷል ብለዋል ለምን ያህል ጊዜ የት ነበር የተሰጠው የ2003 ለምን ያህል ጊዜ ነበር የት ነበር ስልጠናው የተሰጠው ?
- የተሰጠው ቦታ በአዲስ አበባ ደረጃ በማውቀው በሲኤምሲ እና በኮተቤ
- ለስንት ጊዜ ለስንት ለአንድ ወር ለ 5 ቀን ለ 10 ለስንት ጊዜ ?
- የእዚያኔ የተሰጠን ለ 15 ቀን
- ለ 15 ቀን የተሰጠው ?
- አዎ
- ያኔ እርሶ የት ነበር የሚሰሩት ?
- የእዚያኔ እስልምና ጉዳይ
- እስልምና ጉዳይ ነበር የሚሰሩት ለሳዲቅ መሴጂድ ልኮለት ነው ብለዋል መሴጅ መላኩን ነግሮት ነው ?
- አዎ ወንድሙ ደውሎ ነገረኝ
- መሴጅ ላከለት ብሎ ስንት ሰዓት ላይ ነው ? ሰዓቱ ?
- 4 ሰዓት ከ 20
- እዚያ ስልጠናው ላይ ነበሩ እርሶ አስተባባሪ ነበርኩ ብለዋል ?
- አዎ
- ምንን በተመለከተ ነበር ሲሰጥ የነበረው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለቀደምት መሻይኮቻችን እና ስለ አሎማሦታችን
- ሀረሪ ያራምዱት የነበረውን-እንትን ነው ሲሰጥ የነበረው ቀደም ሲል እሳቸው ሲያስተምሩት የነበረውን ትምህርት ነው ሲሰጥ የነበረው በእዚያ ስልጠና ?
- 4ቱም የፊቂህ መፅሐፎችን የቀደምት መሻይኮቻችን አሎማዎቻችን የነበሩበትን እና ያሳለፉትን ብሎም ኢትዮጵያ ውስጥ ላይ እንዴት እንደገቡ የሚያስተነትን ትምህርት
- ማን ነበር ስልጠናውን ሲሰጥ የነበረው ?
- ሲሰጡን የነበሩት አሎማዎቻችን ናቸው
- አለማዎች ማለት ከውጪ ሀገር የመጡ ናቸው ሀገር ውስጥ የነበሩ ናቸው እነ ማን ነበሩ ?
- ኢትዮጵያዊያኖችም አሉ
- ስንት ነበሩ የውጪ ሀገር ሰዎች ?
- ብዛታቸውን አላውቀውም
- ከየት ሀገር ነበር የመጡት ?
- ቦታቸው ሉብላን ነው
- ሉብላን ማለት ሊባኖስ ማለት ነው ?
- ሉብላን /ግልፅ ያልሆነ/
- በአረብኛ ስለሆነ የጠሩት ብዬ ነው ?
- አዎ
- በተደጋጋሚ አወሊያም እዚያም ይሰበሰቡ ነበር ብለዋል ለመሰብሰብ መነሻ የሆነው ነገር ምንድን ነበረ ?
- መነሻ የነበረው
- ይሄንን ስብሰብ እየተሰበሰቡ ስለመጅሊስም እየተናገሩ ነበር እነዚህ ኮሚቴዎችም ነበሩ ብለሀል ምንድን ነበር ይሄንን ስብሰብ የፈጠረው ምንድን ነበር ?
- ቅስቀሳ ነው
- ምን ዓይነት ቅስቀሳ ነበር ምንድን ነበረ ሲያነሱ የነበሩት ሲነሱ የነበሩት ጥያቄዎች ምን ምን ነበሩ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእምነታዊ የዘለለ የፖለቲካዊ ንግግሮች ነበሩ መንግስታዊ ጉዳዮች
- የጠየኮት እሱን አይደለም ቃል በቃል ሲነሱ የነበሩ ጥያቄዎች ነበሩ ብለዋል አይደለም ቅድም ብለዋል እየተሰበሰቡ ነበር ኮሚቴ ነበረ ብለዋል ያ ኮሚቴ የሚያነሳ የነበረው ጥያቄ ምንድን ነበር ይሄንን ነው ለፍ/ቤት ግልፅ እንዲያርጉ የፈለኩት ?
- ኮሚቴነት በእዚያን ሰዓት የለም ነበር ኮሚቴ የለም ግለሰቦች ናቸው
- እሺ ግለሰቦቹ
- እውቅና የሚሰጠው ነው ብዬ ነው ኮሚቴ ነው ብዬ የማስበው ሕዝብ አልሰጠው በመንግስት አልፀደቀ በሀገር አልታወቀ
- እንዴት አወቁ እርሶ ይሄ ?
- በግለሰብ ነው በግለሰብ በቃ የእዚያኔ እየተነሱ ሲናገሩም የነበረው እንጂ የኮሚቴነት እውቅና የላቸውም
- አህመዲን ወረቀት አዘጋጅቶ ነበር ብለዋል መቼ የት እንዴት ነበር ያዘጋጀው ?
- ፎርም የስም ዝርዝር ያለበት ፎርም እና ሰው እንዲፈርምለት የተዘጋጀ ኮሚቴ እንድንሆንላቸው የሚል ፎርም ነበር
- በምን የተፃፈ ነበረ ?
- በኮምፒዩተር
- በኮምፒዩተር የተፃፈ ማን ነው ያዘጋጀው አሉ ?
- አይደለም ፕሪንት የተደረገ ብዛት ነው
- እኮ ማን
- ለእያንዳንዱ ነው የደረሰው
- እኮ እንዴት አወቁ አህመዲን ሲያዘጋጀው ?
- ከእሱ እጅ የወጣ ከእሱ እጅ ሲወጣ ለሌሎቹ
- የት ነበረ ቦታው ?
- አወሊያ
- አወሊያ ነበሩ እርሶ ?
- ነበርኩኝ አዎ

1287

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

መቼ ነበር ጊዜው ?

ቀኑን አላስታውሰውም ጁማ ቀኑ አርብ ቀን መሆኑን አስታውሳለሁ

ምን ያህል ወረቀት እንደነበር ያስታውሳሉ?

ድምሩን አላውቀውም

ቅድም መጀመሪያ ላይ ስትመሰክር 5 ሰዎችን ዝርዝር አሸቀምጠህ ነበር የማውቃቸው በእዚህ ጉዳይ ነው ያሉን አቡበከር ካሚል መሐመድ አባተ ሳዲቅ ሃይሩ እና አህመዲን /ግልፅ ያልሆነ/እስቲ እነሱን በየስማቸው እየለየህ አሳየን እስቲ ?

አህመዲን ጀባል አቡበከር አህመድ

አዎ እንደቅድሙ ስህተት እንዳይፈጠር እዚህ ጋር ና እና እያየሀቸው ስማቸውን እንዲናገሩ ይደረጋል ና እዚህ ጋር እና እየለየሀቸው ?

- /ግልፅ ያልሆነ/
- የትኛው
- የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ያቀረብነው መቃወሚያ ነበር እዚያ መቃወሚያ ላይ ብይን አልተሰጠም ተከሣሽ በ 128 መሠረት ስነ ስርዓቱ የሚያዘው ቆሞ እንዲከራከር ነው እነዚህ ተከሣሾች 29 ስለሆኑ ነው ቁጭ ያሉት ሁሉም እንዳይቆሙ ስለዚህ ስማቸው ሲጠራ በምስክር ቆመው ነው መከራከር ምስክሩ አስቸጋሪ የዛሬ ስንት ወር ያያቸውን በሰውኛም አስተሳሰብ የማይሆን ነው ስለዚህ መቆም አለባቸው
- ቆይ ቆይ እንትኑ ትክክል ነው አሁን ሌላ ክርክር ሳይነሳ ቆመው ነው መከራከር ያለባቸው ግን ምንድን ነው ብዙ ስለሆኑ ቁጭ በሉ አልናቸው አሁን ለመለየት ግን ለማስቸገር ሁላችሁም ትነሳላችሁ
- 2ኛ ተከሣሽን አሳይቷል እሺ ሌላ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክሩ 1ኛ ተከሣሽን ለይተው አሳይተዋል
- ምስክሩ አመዲን ጀባል ብሎ ያው 2ኛ ተከሣሽን አሳይቷል የተፃፈውም ያው አመዲን ጀባል ነው እንደዚሁም አቡበከር ያሉት የትኛውን ነው እሱ በእዚህ መጨረሻ 2ኛ አቡበከር ነው የእሱ ስም እሺ እንደዚሁም 1ኛ ተከሣሽን አሳይቷል ሌላ አለ
- ሌላ የምትፈልጉት አለ ?

1287

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጨርሰናል
- ጨርሰዋል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
- ለጥያቄ እኮ ነው ከጨረሱ
- ካሚልን ካሚል ነው ቅድም ተርቶታል ካሚልን
- /ግልፅ ያልሆነ/ መጨረሻ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ እዚህ ውጡ ወደ ጫፉ ጋር በእዚህ በኩል ምስክር በእዚህ በኩል ይምጡ /ግልፅ ያልሆነ/ እሱ ነው አይ የተጠራጠርከው ሰው ይውጣ ንገረን ቀና በሉ አንገታችሁን አትድፉ አንገታችሁን አትድፉ ቀና ብላችሁ ተመልከቱ ወደ ውስጥ ገብተህ ማየት ትችላለህ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አልተናገረም ወደ ውስጥ ግባ
- እስቲ ቆዩ ሰውዬው አሁን እኮ ሰውዬው እየፈለገ ነው አላወቀም እኮ ገና
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቁጭ በሉ እናንተ ለክ ነው ለመለየት እንዲያመች
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቆይ ቆይ እናንተ እጃችሁን ሰብሰብ አድርጉ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ሰማን እኮ ቁጭ ብሉ 2ታችሁም ቁጭ በሉ ከእዚያ እሱ ብቻ /ግልፅ ያልሆነ/
- የተከበረው ፍ/ቤት
- ቁጭ በሉ አሁን እኮ በቃ ትዕዛዝ ሰጠን ቁጭ በሉ ቁጭ አይሉም እንዴ
- ተቀመጡ 2ታችሁ ተባለ ምስክሩ ይፈልግ ተባለ ሌላ ነገር እያወራ ነው እና ባይደገም እንደዚህ ዓይነት
- ጥያቄው ይቀጥል
- የተከበረው ፍ/ቤት ካሚልን ሸምሱን አለያለሁ ብሎ ጀምሮ ነበር የተመለሱት ይቀመጡ ተብሎ ለይተው ቅድም ያሳዩት ሰው በፍ/ቤቱ ተመዝግቦ ከሆነ የእሳቸው ስም ተመዝግቦ ይለፍ
- ማን ነው ያሉ ?

1289

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ካሚል ሸምሱ
- ካሚል ?
- አዎ ካሚል
- /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን መለየት አይችሉም እያንዳንዱ እየተነሱ መለየት ትችላለህ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ቅድም ስትመሰክር በፈትህ አባቦራ መስኪድ መንግስት ጣልቃ ገብቷል ሲሉ ተናግረዋል ብለህ ነበር ይሄንን በትክክል የተናገረው ማን ነው መንግስት ጣልቃ ገብቷል በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ብሎ የተናገረው ማን ነው ?
- ያሲን ኑሩ
- መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ሲል መንግስት በመጅሊሱ ምርጫ ጣልቃ ገብቶብናል እያለ ነው የነበረው ?
- አይደለም
- ምንድን ነበር ?
- መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ነው ያሉ
- ምን ማለት ነው የተረዳኸው በምንድን ነው መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል አሉ ስትል በምን ጉዳይ ጣልቃ ገባ ነው ያሉት ?
- አዲስ ኃይማኖት አመጣብን
- ስለዚህ መንግስት በእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮ ጉዳይ ጣልቃ ገባብን ነው እያሉ የነበረው?
- አዲስ አስተምሮት የሆነውን ሀባሽ አመጣብን መንግስት
- ይሄንን አስተምሮ በማምጣት ነው ጣልቃ ገባብን ያሉት ?
- አዎ
- መንግስት በመጅሊስ ምርጫ ላይ ምርጫ ተካሂዷል አይደለም ?
- አዎ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መንግስት በመጅሊስ ምርጫ ሒደት ውስጥ የሚታይ ተሳትፎ አልነበረውም መንግስት ተሳትፎ አልነበረውም ?
- ተሳትፎ አይደለም ፀጥታን በተመለከተ ነው ሲያስተባብር የነበረ ምርጫውን ሲያካሄድ የነበረ ሕዝበ ሙስሊሙ ነው
- የት ነበር ምርጫው የተካሄደው ?
- በሁሉም ቦታ
- ቦታው የት የት ነው ?
- በሁሉም ወረዳዎች የመወይም በድሮ ቀበሌ ድንኳን ተጥሎ ውጪ
- ቀበሌ ?
- ከቀበሌ ውጪ ማለት ነው
- በቀበሌዎቹ ውስጥ በቀበሌዎች አካባቢ ድንኳን ተጥሎ ነበረ ?
- ማህበረሰብ ማሰባሰቢያ ማለት ነው
- እዚያ ነው የተደረገው ?
- አዎ
- ይሄ ምርጫ የተደረገው መቼ ነው ?
- የተደረገው
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለ የተከበሩ የተከሣሽ ጠበቃ ያቆማሉ ብለን ነበር /ግልፅ ያልሆነ/ ላለማቋረጥ እኛ ስለምርጫ ያወራነው ነገር የለም 2ኛ ምስክሩ የመጨረሻ የመሰከረበት የጊዜ /ግልፅ ያልሆነ/ ነሐሴ 2004 ምርጫው የተደረገው በእዚህ ዓመት ነው በእዚህ ዓመት /ግልፅ ያልሆነ/ እኛ በዋና ጥያቄ አላነሳንም እና ጠበቃው እኛም ካስመሰከርነው ከተያዘው ጭብጥ ውጪ ነው እየሄዱ ያሉት እና እንዲያስቆሙልን
- መልስ
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን እኮ ዐቃቤ ሕግ ምርጫው መቼ እንደተደረገ እሳቸው መልሰው ነው እየተቃወሙ ያሉት ይሄ አካሄድ ከሆነ ልክ አይሆንም ሲጀመር አሁን እሳቸው ምርጫው የተደረገው በእዚህ ዓመት ነው አሉ በቃ ምስክሩ በእዚህ ዓመት ነው ብሎ ይመልሳል ማለት ነው እኔ የጠየኩት ምርጫው የተደረገው መቼ ነው እሳቸው መልሰዋል ስለዚህ ምስክር መሆን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የነበረባቸው እሳቸው ሊሆኑ ነው ይሄ አካሄዱ እራሱ ልክ ስለማይሆን ለዐቃቤ ሕግም ተገቢ አይደለም /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ አሁን ጥያቄማ አልጠይቃቸውም

አልተነሳም በዋና ጥያቄ

አይ ምርጫው የተደረገው መቼ ነው አልኩ አልተነሳም የሚለው ተቃውሞ ቢሆን እኔም መልሴን አስረዳለሁ እሳቸው ግን ምርጫው የተደረገው በእዚያ ዓመት ነው አሉ አሁን ምስክሩ ፍ/ቤት ፈቅዶ ቢጠይቀው ምርጫው በእዚህ ዓመት ነው የተደረገው ይላል አለቀ ማለት ነው እንደዚህ ዓይነቱ አካሄድ እራሱ ልክ ስለማይሆን እኔም ጥያቄውን እተዋለሁ ግን እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ ትክክል አይደለም ለዐቃቤ ሕግም ለእኛም እንደሚሰጠን ማሳሰቢያ ትክክል አይደለም መልሰውታል ምስክር ነው የሆኑት

አለፋችሁት ጥያቄውን ?

ከእዚያ በኋላ /ግልፅ ያልሆነ/ ግን ሌሎች ጥያቄ ልቀጥል ምርጫችን በመስኪዳችን ብሎ ተናግሯል ብለሀል ቅድም ይሄንን በትክክል የተናገረው ማን ነው ?

ምርጫችን በመስኪዳችን ብሎ ያሉት በእነ አቡበክር አህመድ በመሐመድ አባተ አማካይነት ምርጫችን በመስኪዳችን ብሎ አለ እሱ ባለው አልተሳካም

ቆይ ቆይ

አሎማዎች ባሉት ግን ተሳክቷል

አሁን እኮ እየጠየኩ ያለሁት ማን ነው ያለው ነው ምርጫው የት እንደተደረገ ነግረውኛል በኃይማኖቱ ሕግ መሠረት በእስልምና ሕግ መሠረት የመጅሊስ ምርጫ መደረግ ያለበት የት ነው እውቀት አለኝ ብለዋል ?

ከመስኪድ ውጪ

የት ቦታ ?

በማንኛውም ቦታዎች ላይ ሜዳ ላይ መደረግ ይችላል መስኪድ የመምረጫ የማስመረጫ የስልጣን መሸዋሸሚያ የገንዘብ መመካከሪያ ንብረት አይደለም የአላህ ቤት ነው የኢባዳ ቦታ ነው የፀሎት ቦታ ነው ከፈጣሪ ጋር ብቻ እና ብቻ የምንገናኝበት ቦታ ነው የፍርኃትም ቤትም አይደለም ሲጀመር

ስለዚህ ምርጫ በመስኪድ ውስጥ እንዳይደረግ ?

1292

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከልክል ነው
- የኃማኖቱ ሕግ ይከለክላል ነው የሚሉ ?
- በጣም ኃይማኖቱም ይከለክላል
- በትክክል ከመፀሐፉ ላይ ቁጥር ተይተው ሊነግሩኝ ይችላሉ የሚችሉ ከሆነ ይሄ ምርጫ በመስኪድ ውስጥ አይደረግም የሚለውን የኃይማኖት ?
- በቁራን ሀያትም ካስቀመጡት ትክክለኛው
- ይኸውሎት አሁን
- አላህ ሱባህ /ግልፅ ያልሆነ/ ይህ የእኔ ቤት ነው
- አቶ ሰይድ ይኸሎት አሁን እኔ እየጠየኩ ነው ለምጠይቀው ነገር ብቻ ነው የሚመልሱልኝ የምጠይቆትን ብቻ አሁን የምጠይቆትን በደንብ ስሙ
- ክቡር ጠበቃ የጠየቁኝ ነው እየመለሱ ያለው ይመስለኛል
- ቆይ አይደለም ይኸሎት በቃ ይሄ እዚህ ድረስ ነው እኔ የማውቀው ማለት ይችላሉ የሚያውቁትን ብቻ ነው ከእዚያ ውጪ ካላወቁ እኔ የማውቀው ይሄንን ነው ማለት ይችላሉ
- አሁን የእኔ ጥያቄ እንደገና ስሙኝ ከኃይማኖቱ መፅሐፎች ሕጉ ከተፃፈባቸው መፅሐፎች ውስጥ ምርጫ በመስኪድ ውስጥ እንዳይደረግ የሚከለክለው ትክክለኛው ቁጥር ለይተው ሊነግሩን ይችላሉ ወይ ነው ?
- ቁጥር አልተቀመጠለትም
- ቦታውስ /ግልፅ ያልሆነ/ ?
- ቦታም አልተቀመጠለትም ቦታ የተቀመጠለት መስኪድ አላህ የእኔ ቤት ነው
- ቆይ ይኸውሎት ትንታኔ አይደለም
- ቆይ ዐቃቤ ሕግ
- ትንታኔ ሳይሆን የእኔ ጥያቄ ከመፅሐፉ እሳቸው እኮ ወደ ትንታኔ
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ተቃውሞ እንዳለን እየገለፅን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ ምንድን ነው አሁን ችግሩ ጠይቁት እና ምስክሩ ይመልሱ ምስክሩ ከመለሰ በኋላ ጥያቄአችሁን ቀጥሉ አሁን የሆነ መናገር አንዱን ቃል ሳይጨርስ ሌላ የምትደግሙት ከሆነ ወደ ትክክለኛው ነገር ለማምጣትም አይመችም ስለዚህ የጠየቃችሁትን ጥያቄ በትክክል ያዳምጥ እሱን እስከሚመልስ ጠብቁ እና
- እሺ
- የቀረበውን ጥያቄ /ግልፅ ያልሆነ/ ማብራራውን ነው የማትፈልጉት
- ማብራራውን ያልፈለኩት እኔ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ለእሳቸው
- መፅሐፉ አሁን ቁጥር ከሌለው በመፅሐፉ የትኛው ክፍል ላይ ይገኛል ነው በመፅሐፍ ውስጥ
- እንዴት እንደሆነ እሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ያስረዱ እሺ ያስረዱ
- መስኪድ የአላህ ቤት ነው የፀሎት ቦታ ነው የእኔ ቤት ነው በምትመጡ ሰዓትም ስለ ፀሎታችሁ እንጂ ስለ ነበራችሁበት ስለዋላችሁበት ውሎ መናገር አትችሉም ድምፅ ማሰማት እራሱ አይቻልም ስለዚህ ስልጣን መሻሻሚያ ስለገንዘብ መነጋገሪያ ስለጩኸት መጫጫያ ቦታ አይደለም ይሄንን የምታደርጉት ከሆነ ደግሞ የእኔን /ግልፅ ያልሆነ/ ተከታዮች አይደለም ብሎ ነው በግልፅ ያስቀመጠ እና ምርጫ በመስኪድ አይደለም የሚለው
- ምስክር እሱን ብለዋል ምንድን ነው መሠረቱ ነው የእነሱ ጥያቄ የሚያውቁት ካለ እሱን ይጥቀሱ የማያውቁት ከሆነ
- ይሄ ቁራን ሀያት ላይ አንቀፅ አልተቀመጠም እያልኩ ያለሁት በአሎማዎቻችን እና በመሻይኮቻችንን የተቀመጠልን
- በምን የመጣ ነው ወይ በኃይማኖታችሁ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው ?
- አዎ በአሎማዎቻችን በማሻይኮቻችን የመጣ ነው ሲወረድ ሲዋረድ የመጣ
- በቃ ሌላ ጥያቄ ካላችሁ
- ቅድም ሰ መስክሩ አስቀድሞ የነበረው እና የኢትዮጵየ ነባሩ አስተምሮ ሀባሽ ትክክለኛው እምነት ነው ብለው ተናግረዋል ትክክል ነኝ ?
- ሀባሽ የሚባል እምነት የለም ሀበሻ መሆናችንን እናውቃለን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አስተምሮ ነው ያልኩት ቅድም ሰ ናገሩ
- ሀባሽ የሚባል አስተምሮም የለም ነው እያልኩ ያለሁት
- ስለዚህ
- በቃ የለም ካሉ በቂ ነው
- ሀባሽ የሚባል አስተምሮ የለም
- /ግልፅ ያልሆነ/ ማለት አሁን ጥያቄው እያቀረባችሁ ነው አይደል
- አሁን ጥያቄውን ቀጥሉ
- ቅድም ሲመሰከሩ ጅሀድ ማለት ጦርነት ማለት ነው በቁራንም በሀዲስም የሌለ ሕግ ነው ብለዋል ለእዚህስ መነሻው ምንድን ነው ?
- ጂሀድ ማለት በቁራን ከተቀመጡት ከድህነት ጋር ሰውዬው ድህነትን ለመዋጋት ቢሄድ ወደ እድገት አለም ውስጥ ቢገባ በእስልምና ታይማኖቱ ትግል በማድረጉ ይሄ የጅሀድ ይባላል ይሄኛው ግን ጅሀድ ብሎ የተባለው ግን ጦርነት መቀስቀስ ወይም በተራረድ በሰይፍ መቆራረጥ ማለት ነው እሱም መልዕክቱን ያንፀባርቅ የነበረ በእሱ ጉዳይ ነው
- አሁን እኔ ጥያቄው ጥያቄዬ ጅሀድ የሚል አስተሳሰብ እንደተረዳሁት ጅሀድ የሚባል ነገር በቁራንም በሀዲስም የሌለ ሕግ ነው ነው ያሉ ይሄንን ከሆነ የማሉን
- መቃወሚያ አለ የተከበረው ፍ/ቤት
- መቃወሚያው ምንድን ነው
- ምስክሩ ጅሀድ የለም አላሉም ጅሀድ አለ 2 ዓይነት ነው አንደኛው ለድህነት ሲሆን አንደኛው ለጦርነት ነው ብለው እዚሁ አሁን የተከበሩ ጠበቃ በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቋቸው መልሰዋል ጅሀድ የሚባል ነገር የለም ብሎ እንደገና የተሳሳተ 3ኛ ጠበቃው የሚፈልጉትን ድምዳሜ ነግረው እንዲህ ካላልክ ብለው ምስክርን ማሳመን አይረዳም
- ምንድን ነው ?
- የተከበረው ፍ/ቤት 1ኛ አሁን የጠየኩትን ሲመልሱ መጀመሪያ ጠይቄአቸው አልተቃወሙም አሁን ሲመልሱ ያሉትን ነገር እንዲያስተካክሉልኝ ነው የጠየኳቸው እንዲያብራሩልኝ ግን እዚህ ጋር እንደገና እንትን ሲል ዐቃቤ ሕግ ተንትነው የሚያስረዳ ከሆነ እኔ የዐቃቤ ሕግ ትንተና ነው ያልፈለኩት ቅድምም የተቃወምኩት እኛ መተንተን የለብንም ቅድም ተነግሮናል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እስማማለሁ አሳቸውም መተንተን የለባቸውም የምስክሩ ቃል ይጠቅ ውስጥ አይግቡ ነው ማሳሰቢያው ግን ይሰጥልን የተከበረው ፍ/ቤት

- ትንተና አይደለም አሁን የሰጡት አሁን ምናልባት እዚህ ጋር የተሰጠው ነገር መልሱንም እኛ ሰምተናል
- አዎ
- ጅሀድ በ 2 ከፍለው ነው ያስረዱት ዐቃቤ ሕግም የደግሙት ይሄ ነው ሌላ ትንታኔ ስለዚህ ይሄ ተመልሷል ነው የሚሉት ዐቃቤ ሕግ ግልፅ ነው ተመልሷል ይሄ ከተመለሰ ምንድን ነው የሚፈልጉት ነው ያሉት ስለዚህ ከእዚህ ተነስታችሁ ነው አሁን ምላሻችሁን የምትሰጡን
- ጥያቄዬን ሳልጨርስ ስለሆነ ነው እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ጅሀድ የሚለው አስተሳሰብ በቁራን እና በሀዲስ የሚታወቅ አስተሳሰብ ነው ?
- ጅሀድ ቃላቱ ለብጥብጥ እና ለአመፅ የሚሄድ ቃላት እና ለልማታዊ ቃላት የሚሄደው በ 2 ቅድም እንዳስቀመጥኩት ማለት ነው የእነዚኞች ግን ጅሀዳቸው
- አሁን እኮ ስለ እነዚኞቹ አልጠየኩም አሁን ስለ ጅሀድ ብቻ ነው የጠየኩት
- የእነሱ የነበረው በእዚያን ሰዓት ጅሀድ ብሎ የሰየመው የጦርነት ጅሀድ ነው
- አቶ ሰይድ ይሸውሎት ሰዓታችንን እየገደልን ነው እኔ የምጠይቆትን እየሰሙኝ ለምጠይቆት ነገር ብቻ ይመልሱልኝ ስለዚህ ጅሀድ ለጦርነት ጅሀድ ለልማት ተብሎ በቁራአን ይታወቃል ?
- ትክክል
- ጅሀድ ስለዚህ ጅሀድ ማለት በራሱ ጦርነት ማለት አይደለም ትክክል ነኝ አይደል ?
- አቤት
- ጅሀድ ማለት በራሱ ጦርነት ማለት ?
- ጦርነት ማለት ነው ያው
- ጦርነት ማለት ነው ?
- ትክክል
- ስለዚህ ለሰላም ብሎ ጦርነት ?

1296

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሰላም ማለት የድህነት ጦርነት ከድህነት ጋር ከታገልኩኝ እኔ ትግል ነው ያደረኩኝ ትግል ማለት ደግሞ ጅህድ ማለት ነው ከድህነት ጋር ለአመፅ እና ለረብሻ ከሆነ ደግሞ ጦርነት ወይም ደግሞ መገዳደል ወይም ገጀራ ይዞ ወጥቶ ሕይወት ማሳጣት ጂህድ ይባላል
- አሁን በትምህርት ደረጃ ነው እንጂ እንትኑ ላይ ቁጥር የተሰጠው ትርጉም አይደለም ይሄ ?
- አሁን እሱ ላይ ትርጉሙ ላይ አይደለም የቃላት አንቀፅ ቁጥር ላይ አይደለም የገባሁት
- ፍ/ቤቱ ይመዝነዋል እኛ እየመለሱ ያለው በራሳቸው እውቀት ነው ከእዚያ በኋላ ሌላ የሚያስፈልግ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቱ እናንተም /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም ሲመሰክሩ በአንዋር መስኪድ ውስጥ ተግቢራ እያደረጉ ይቀሰቅሱ ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- ተግቢራ ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው ?
- ተግቢራ አንድም ለመልካም አንድም ለመጥፎ ማለት ነው
- አሁን የጠየኮት ተግቢራ ማለት ምን ማለት ነው ነው ያልኮት ?
- እኛ የምናውቀው ተግቢራ የፈጣሪ አንድነት መገለጫ ነው ተግቢራ በ 2 መስመር ስለሚጠቀም ማለት ነው እነሱ የተጠቀሙት ግን የአመፅ
- ልጠይቆት እኮ ነው አቶ ሰይድ ልጠይቆት እኔ /ግልፅ ያልሆነ/ በእዚያ በመስኪድ ውስጥ ሲደረግ የነበረው ተግቢራ ቃል በቃል ምን የሚል ነበር ?
- መስኪድ ውስጥ የነበረው ተግቢራ የአመፅ ተግቢራ ነበር
- አይደለም ቃሉን ነው የጠየኮት አሁን ቃሉ ምንድን ነበር የሚል የነበረው ?
- አላህ ዋክበር ድምፃችን ይሰማ ዲናችን ለደማችን የሚሉ ቃላቶች ነበሩ
- አላህ ዋክበር ማለት አረብኛ ነው ?
- አረብኛ ነው
- ወደ አማርኛ ሲተረጎም ምን ማለት ነው ?
- ወደ አማርኛ ሲተረጎም አላህ የተከበረ ነው አልተከበረም የሚል ቃላት አልተቀመጠም
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ጥያቄውን ብቻ ይመልሱ ጥያቄውን ብቻ አዳምጠው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

በመስከረም ወር 2004 ዓ.ም ስልጠና ይሰጥ ነበር ብለው ነበር ቅድም ከአስተምሮት አንፃር ስለኃይማኖ ይሰጥ የነበው ስልጠና ምን ዓይነት አስተምሮት ነበር ?

አስተምሮት ሲሰጥ የነበረ የቀደምት አሎማዎቻችን እና የመሻይኮቻችን ታሪክ እንዲሁም የነብያችሁ ሰሎላሪ ሰለም አመጣጥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ እስልምናን እንዴት እንደተቀበለች የሚገልፅ ነበር ትምህርት ሲሰጥ የነበረው

- የእዚህ አስተምሮት መጠሪያ አለው አስተምሮቱ መጠሪያ አለው የሚለይበት ?
- እስልምና
- ከሌሎች እስልምና
- እስልምና ነው ወሀብያ አይደለም እስልምና ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ወሀብያ ማለት ምን ማለት ነው ቅድም አንስተውት ስለነበረ ?
- አቶ አብዱሉሀብ የሚባል የውጪ ዜጋ የእሱ ፈለግ የሚከተል ማለት ነው
- የእሱ ፈለግ የሚከተል ?
- አዎ ወይም የእሱን አስተሳሰብ የሚመራ ማለት ነው ከእምነቱ ውጪ የወጣ ግለሰብ አንድ ግለሰብ ማለት ነው የሞተ ግለሰብ
- በእኛ ሀገርስ አሁን ቅድም ሲሉት የነበረው የማን አስተምሮ የሚከተል የነበረው ?
- ኢትዮጵያ ላይ የምንከተለው የእነ ኢማሙ ሻፊ ኢማሙ ማልኪ ኢማሙ አምበሊ የ4ቱን መዛሀቦች ነው የምንከተል የነበረው ሙስሊም
- ቅድም ስትመሰክር የአንዋር መስኪድ አባልኝ ብለህ ነበር ?
- ኖ አባል ነኝ አላልኩም አንዋር መስኪድ
- የት መስኪድ አባል ነህ ?
- አንዋር መስኪድ አካባቢ ነኝ ነው እያልኩ ያለሁት
- አባል ነኝ አላልክም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ መስገጂያ ቦታዬ በማንኛዎቹም ቦታ የመስኪድ መብት ስላለኝ አትገድቡኝ ክቡር ጠበቃ
- ይኸሎት ምስክር አሁን ምንድን ነው እርሶ ምስክር ኖት ?
- ትክክል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ዐቃቤ ሕግም ቢጠይቅ ጠበቃም ቢጠይቅ መልሷን ብቻ መልሰው የሚያውቁ ከሆነ አውቃለሁ የማያውቁ ከሆነ አላውቅም ይሄ ነው
- ገብቶኛል
- ምክንያቱም ግልፅ ካልሆነ አንዳንድ ጊዜ
- ክቡር ዳኛ ገብቶኛል
- ያዳምጡ እኛ አንዳንድ ጊዜ ሲደገም እናውቃለን ግን ምንድን ነው ያ ሰው ግልፅ ካልሆነ ምናልባት እንዲብራራለት ስለምንፈልግ እና ይቺን ነው እንጂ ወደ ዐቃቤ ሕግ ወደ እንትን አያስገድድም ምናልን እሱን እኛ እንጠብቃለን
- ገብቶኛል
- /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ጥያቄ ሲጠየቁ እሷን አዳምጠው ጥያቄዋን ብቻ ነው የሚመልሱት
- ሀምሌ 6 ቀን 2004 ላይ ከምሽቱ 5 ሰዓት ላይ በአንዋር መስኪድ ያልተለመደ አዛን ተደርጓል ብለህ ነበር ?
- ምሽት 5 ሰዓት ላይ አዛን አልተደረገም አንዋር ላይ
- የት ነው የተደረገው ?
- በሌሎች መስኪዶች ነው
- እሱን እዚያው አንዋር መስኪድ አካባቢ ባለው መኖሪያ ቤትህ ሆነው የሰማኸው ?
- አዎ
- ምን የሚል ነበር ቃል በቃል የአዛኑ ቃል በቃል ምን የሚል ነበር ?
- አላህ ዋክበር አላህ ዋክበር
- ምን ማለት ነው እሱ ?
- አላህ የተከበረ ነው ማለት ነው
- አላህ ክበር 3 ጊዜ ተጠይቆ 3 ጊዜ ምላሽ ተሰጥቷል
- እሺ አይ
- ሌሎችም አሉ በመሀል በመሀል ስለዚህ እሱን ካለው ጊዜ አንፃር
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት በእዚህ ጥሪ ምክንያት ወደ መስኪዶቹ የሄደ ሰው ነበር ?
- በእዚህ ጩኸቱ ወደ ውጪ ነው እንጂ የወጣው ወደ መስኪድ አልተሄደም

ECLN
1219
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም አህመዲን የኮሚቴ አባላት ዝርዝርን በትኖ የኮሚቴ አባላት ማለት እነዚህ ናቸው አስፈርሙ እያለ ወረቀት እንዲሰጥ አድርጓል ብለሀል ?
- አዎ
- ይሄ የተደረገው በትክክል መቼ ነበር ?
- ቀኑን አላስታውሰውም
- ወሩስ ?
- ወሩንም አላስታውሰውም ቦታው አወሊያ መሆኑን እና አርብ ዕለት መሆኑን አስታውሳለሁ
- ዓ.ም ?
- ያው 2004 ውስጥ
- አሁን ቅድም የጠየኩህ ጥያቄ አለ በመስኪዶቹ ከምሽቱ 5 ሰዓት የተደረገ ጥሪ የተባለ ከእዚያ ቀን ይሄን ከሰማህበት ቀን ወደ ፊት ነው ወደ ኋላ ነው ?
- በፊት
- ምን ያህል ጊዜ ?
- ምን የህል ጊዜ ጊዜውን አላስታውስም
- በግምት የሚያውቁትን ?
- ግምትም ለመገመት ማለት ያው 2004 ውስጥ ላይ ነው የመጀመሪያ ጊዜ የአመፁ መቀስቀሻ 2ኛ ማግስት አካባቢ ላይ ማለት ነው
- ስለዚህ እንደው የትኛው አመፅ የሐምሌ 8
- 2004 ዓ.ም ውስጥ
- እኮ ሐምሌ 8 ያለው አመፅ ላይ ?
- 2004 ዓ.ም ውስጥ ላይ ነው ወራቱን እና ቀኑን አላስታውሰውም ዕለቱ አርብ ቀን ነው
- 2004 መጀመሪያ አካባቢ ይሆናል ?
- እሱን አላስታውሰውም
- ይሄንን ወረቀት አህመዲን ማዘጋጁ አንተ በምንድን ነው ያወከው ?
- ከእሱ እጅ አይቼዋለሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከአህመዲን እጅ ?
- አዎ ሲያከፋፍል እይቼዋለሁ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ አህመዲንን መለየት አለመቻላቸውንም እዚህ ላይ ግንዛቤ እንዲይዝልን
- አዐተያየታችሁን
- ይቅርታ ቅድም ያለየሁ ሰው መስሎኝ ነው የእኔ ስህተት ነው
- ሌላ ጥያቄ ከጨረሱ
- አህመዲን ወረቀቱን በእጁ ይዞ ስላየህ ነው እሱ ያዘጋጀው መሆኑን ያመንከው ?
- እዚያው አወሊያ ላይ ሲያከፋፍል ሲሰጥ
- እኮ ያዘጋጀው ነው ያልኩህ እኮ እኔ አሁን ያዘጋጀው ነው ያልኩህ ?
- ይዞት ያለ /ግልፅ ያልሆነ/ በእሱ እጅ ላይ አህመዲን ጀባል እጅ ላይ ነው
- ሌላ ሰው እጅ ላይ ማንም ሰው አልነበረም ?
- ከእሱ በኋላ ወደ ሌላ ሰው አሳልፎ /ግልፅ ያልሆነ/
- ለእሱ አስቀድሞ ይሰጠው ወይም እሱ /ግልፅ ያልሆነ/
- እሱ እራሱ እጅ ላይ ያየሁት
- መጀመሪያ ይዞ የመጣው እሱ ነው ?
- እሱ እጅ ላይ ነው
- በዝርዝሩ ላይ የራሱ የህመዲን ስም አለበት ?
- ትክክል
- አንተ ደርሰህ አይተኸዋል ?
- አይቼዋለሁ
- ምኑ ጋር ነው የተፃፈው ዝርዝሩ ላይ ?
- በዝርዝር ላይ ነው ጥያቄዎቻችን 3 ጥያቄ የሚሉ አሉ የእራሳቸው ጥያቄ ማለት ነው
- ጥያቄዎቹ ምን ምን የሚሉ ነበሩ ?
- እነሱን አላውቃቸውም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጅህድ ማለት ቅድም ሲመሰክሩ ለጦርነት ከሆነ ገጀራ ይዞ መጥቶ መቆራረጥ መከታከት ነው ብለዋል በገጀራ ምክንያት ተከትክቶ ጉዳት የደረሰበት ሰው አለ ?
- ጉዳት ደረሰበት ያልኩት ነገር የለኝም ግን
- አለ ወይ ነው የጠየኮት አቶ ሰይድ
- እነሳሱ
- አለ ወይስ የለም ነው ያልኮት ?
- እነሳሱ
- አቶ ሰይድ የምጠይኮትን ይመልሱልኛ ?
- አላልኩም እያሉ ነው ቀጥሉ የደረሰ ጉዳት አላልኩም እያሉ ነው ቀጥሉ ?
- አቶ ሰይድ ቅድም ወሀብያ ከቁርአን ከሀዲስ የወጣ ነው ይሄ ማለት ሙስሊም አይደለም ማለት ነው ?
- ከቁራአን እና ከሀዲስ የማይከተል በአብዱሉህ በአስተሳሰብ ብቻ የሚመራ ነው ብዬአለሁ
- ሙስሊም ነው ሙስሊም አይደለም ?
- ሙስሊም እና ሙስሊም አይሆን እምነቱን እኔ አላጡቀውም
- አያዉቁም ?
- አዎ
- ኢትዮጵያ ውስጥ አለ እንዴ ወሀብያ ?
- አዎ አሁን መጥቷል
- ማን ነው ?
- ይዘውት የመጡት እነ አህመዲን ጀባል እነ አቡበከር አህመድ ይዘውት መጥተዋል
- እነዚህ ይዘውት ነው የመጡት ?
- ይዘውት ነው ተምረተውት ከእዚያው
- ተከታይ አለው ኢትዮጵያ ውስጥ ?
- እሱን አላውቅም
- አወሊያ የወጣው ሕዝብ ምን አሁን አወሊያ የተሰበሰበው ሕዝብ ምን ምን ዓይነት ሕዝብ ነው?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አወሊያ ላይ የወጣ ሕዝብ የለም የአባኮራን በፈር እና የአሜሪካን ግቢ ዱሪዬ በስተቀር አንዲ እዚያ አካባቢ ላይ በወቅቱ ሕዝብ አልወጣም
- ፒቲሽን የፈረመም ሰው የለም እንዴ ?
- በየቤትህ ይዘህ ሂድ እና አስፈርም ብሎ መልዕክቱ የመጣ በእነሱ አማካይነት ነው
- ፒቲሽን መፈረሙን ያውቃሉ አያውቁም ?
- ፒቲሽን አልተፈረመም
- አልተፈረመም ?
- የለም
- አቡበከር ሰጠ እንጂ ?
- ወረቀት በተነ እንጂ እኔ /ግልፅ ያልሆነ/ ኮሚቴ ብሎ በተነ እንጂ ተፈርሞ ሲሰጥ አላየሁኝም
- ምንም አላዩም ?
- የለም
- አልሰሙም መፈረሙን በየቤቱ ተበተነ ብለዋል ?
- ተበተነ እንጂ አስፈርማችሁ አምጡ ተባለ እንጂ የተፈረመ ነገር የለም
- ያልተደገመ ጥያቄ
- አቶ ሰይድ ቅድም አቶ ሰይድ በተከበሩ ዐቃቤ ሕግ ሲጠየቁ ሰኔ /ግልፅ ያልሆነ/ ቀን 2004 ዓ.ም እርግጠኛ ከሆንኩ ካልሆንኩ ይመልሱኛል መሐመድ አባተ እና ሳዲቅ ብለው ነበረ በእዚህ ሰዓት የ 2ቱን ሰዎች ድርጊት ሳዲቅ ምን አደረገ መሐመድ አባተ ምን አደረገ ?
- መሐመድ አባተ ሰኔ 14 ቀን ከመጀመሪያው ስመጣ
- በእዚች ቀን ምናልባት ቅድም ስለተናገሩ ?
- 21 ላይ
- 21 ላይ አዎ ስለ 21 ነው ?
- ድምፃችን ይሰማ ዲናችን ለደማችን አላህ ዋክበር የሚሉ ቃላቶችን ሲያስተላልፉ ነበር
- ሃገ ፡
- መሐመድ አባተ እና ሳዲቅ ሀይሩ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምናልባት ጠበቃ ይሄ ጥያቄ ቅድም ተመልሷል ጥያቄው ተጠይቆ በዋና ጥያቄ ማለት ነው ስለዚህ እናንተ እዚህ ጋር የምታነሱት የመስቀለኛ ጥያቄ ካለ መስቀለኛ ጥያቄ አንሱ ዋና ጥያቄ ተጠይቆ ተመልሷል ቅድም እንዲህ ዓይነት መልሶች ተመልሷል እንዳያደጋግም ስለዚህ እሱ ጋር የምታነሱት መስቀለኛ ጥያቄ ብቻ ጠይቁ
- 2ቱንም አንድ ላይ ስላነሱ 2ቱን ምንድን ነው ያሉት እኔ አሁን ጥያቄዬ መሐመድ አባተ በተለይ ምን ተናገረ ሳዲቅ በተለይ ምን ተናገረ ነው 2ቱን አንድ ላይ አድርጓቸው 2 ሰዎች ስለሆኑ እያንዳንዳቸው የተናገሩትን ያስረዱ ቅድም በዐቃቤ ሕግም ጥያቄ እንደዚሁ ስላለፈ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ተመሳሳይ ቃላቶችን ነበር የተናገሩት
- 2ቱም ምን እያሉ ነበር ?
- ዲናችን ለደማችን ድምፃችን ይሰማ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል የሚለውን በተመሳሳይ ቃላቶች
- 2ቱንም ዞር ዞር ብለው እያዩ ነበር ?
- እዚያው አካባቢ አንድ ቦታ ነበርኩ
- ስንት ሰዓት ላይ ነው ይሄ ?
- ወደ 4 አካባቢ
- 4 ማለት ?
- 4 ሰዓት ከቀኑ
- ይሄ ዕለት ሰኔ 21 የሚሉት ምን ቀን ነው ዕለቱ ?
- ዕለቱን አላስታውሰውም
- የት ቦታ ነው ይሄንን ያሉት ?
- አንዋር
- አንዋር መስኪድ ቅድም በሐምሌ 8 ቀን የተለያዩ ሰዎች ንግግር አድርገዋል ብለው ነበር እኔም ከሱቢን ሰላት ጀምሮ እዚያው ነበርኩ ብለው ነበር እና ማን ምን እንዳለስ የሚያስታውሱት ነገር አለ አጠር አድርገው ? ወይም ለማሳጠር ያህል ከእዚህ ሰዓት ጀምሮ ጠዋት ከገቡ ወዲህ አልወጡም እርሶ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቤት
- ጠዋት እዚያው መስኪድ አንዋር ገብተው ብለዋል በሱቢ አልወጡም ?
- እዚያው ነበርኩኝ
- እስከ ስንት ሰዓት ?
- እስከ 6 ሰዓት እዚያው ነበርኩኝ ሰላት አብሬአቸው አልሰገድኩኝም ተነስቼ ነው የወጣሁ ሌላ መስኪድ ነው ሄጀ የሰገድኩ ለምን ከዋቢያ ጋር መስገድ ቢዳሀ ነዋ በጣም ይከለከላል እምነታቸው ስለማይታወቅ ለምን እምነታቸው በግልፅ ስለማይታወቅ
- ይኸውሎት ምስክር በቃ የሚጠይቁትን ከመለሱ ሌላ ካላችሁ ?
- እሺ 6 ሰዓት ወጡ ?
- አዎ
- ይሄ ሁሉ ንግግር ቅድም የተናገሯቸው ሰዎች ዘርዝረዋል ከእነሱም ሌሎች ሌሎች ሰዎች እንደተናገሩ ገልፀዋል በእዚያች ሰዓት ውስጥ ነው ይሄ ሁሉ ሰው የተናገረው ወይስ ከእዚያ በኋላ ነበር ?
- ከ 2 ሰዓት ተኩል ጀምሮ የእነሱ ፕሮግራም እስከ 6 ሰዓት
- እስከ 6 ሰዓት ?
- አዎ
- እነሱ ነበር የሚናገሩት ?
- አዎ
- እሺ በወቅቱ የሚያስታውሱት ነገር አለ መብራት ነበረ ?
- መብራት ነበር አዎ
- ነበረ ?
- አዎ
- አልሄደም ?
- መብራት ነበረ አንዳንዴም ስሄድ ያው ብቻ እኔ መብራት መኖሩ ድምፅ መኖሩን አውቃለሁ እስፒከሮቹ እንደሚሰሩ ነበር የእዚያን ሰዓት
- ስለዚህ አልሄደም ሙሉ ለሙሉ መብራት ነበር ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄ ሐምሌ ወር ነው እና ዝናብ ነበር ደረቅ ነበር የሚያስታውሱት ነገር አለ ?
- ዝናብ ምናምን እኔ እሱን አላስታውስም
- ዝናብ መኖሩን አያስታውሱም ?
- ዝናብ የለም
- አልነበረም ?
- ዝናብ አልነበረም የእዚያን ሰዓት /ግልፅ ያልሆነ/
- አሁን ከእርሶ ጋር ከመጡት ምስክሮች ውስጥ በእዚህ ዕለት የነበሩት የሚያስታውሱት አለ እዚህ የቀረቡ ከእርሶ ሌላ አሁን ለምስክርነት ከመጡት ውስጥ የሚያስታውሱት ሰው አለ በወቅቱ ከእርሶ ጋር የነበረ ?
- እነ ማን እነ ማን እንደመጡ እኔ በምስክርነት አላየዋቸውም ስለ እራሴ ለምስክርነት ቃል
- እሱ ብቻ ሳይሆን ስለምስክሮች እዚህ የመጣ ምስክር ባለፈው /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
- ሌላ ጥያቄ
- ቅድም በኮተቤ እና በሲኤምሲ መስኪድ ስልጠና ሲሰጥ ነበር ብለዋል ?
- በሲኤምሲ መስኪድ አላልኩም
- ያስተካክሉ የት ነበር ያሉት /ግልፅ ያልሆነ/ ?
- ሲኤምሲ መስኪድ አላልኩም ሲኤምሲ የስብሰባ ማዕከል ላይ እና ኮተቤ ስብሰባ ማዕከል
- ስብሰባ ማዕከል
- አዳራሽ ላይ
- አዳራሽ ላይ ስልጠና ሲሰጥ ነበር ?
- አዎ
- /ግልፅ ያልሆነ/ እና በመንግስትም በመጅሊስም ሲሰጥ ነበር ብለዋል ልክ ነኝ ?
- እሱ እንደሱ አይደለም ያልኩት
- እንዴት ነው ?

1306

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያልኩኝ መንግስት ስለሕገ መንግስቱ ለአንድ ቀን ስልጠና ሰጥቶናል
- እሱን ነው ያልኩት እኮ
- ስለ ሕገ መንግስቱ ከእዚያ በኋላ ስለ እስልምና ተሰጥቶናል በኡሎማዎቻችን አማካይነት
- ስለ እስልምና ?
- ስለ እስልምና ኃይማኖት ስለኡሎማዎቻችን ስለ መሻይኮቻችን አመጣጥ ስለእሱ ጉዳይ
- ስለዋህብያ ተነገራችሁ ?
- ወህብያ እንደውም ጭራሽ ስሙ ሲነሳ እራሱ እኔ አልወደውም እንኳን አይደለም እዚያ ትምህርት ሊሰጥ ይቅር እና
- ስለማን ተሰጠ ታዲያ እዚያ ላይ ?
- ስለመሻይኮቻችን ስለ ኡሎማዎቻችን ስለናንይ ስለነዳንይ ስለአብረትይ ስለቀትበርይ ስለነሹንኪ
- እንግዲህ ቅድም እርሶ በተከበሩ ዐቃቤ ሕግ በተደጋጋሚ ሲጠየቁ ካለፉት ስርዓቶች ከእነ ሀጂ ሀቢብ /ግልፅ ያልሆነ/ ጀምሮ እንደሚያውቁ ገልፀውልናል በእነዚህ ጊዜአት ውስጥ ሁሉ ለኃይማኖቱ ቅርብ ኖት ቅድም 4ቱንም መዛብ ጥጥት አድርጌአለሁ ብለዋል ስለዚህ በእነዚህ ገዢአቶች ውስጥ ሁሉ መንግስት በኃይማኖት እንደዚህ ዓይነት ሕገ መንግስት ሰ የስተምር አይተው ያውቃሉ አጭር ጥያቄ ያውቃሉ አያውቁም ማብራሪያ አልፈለኩም ያውቃሉ አያውቁም ካወቁ አውቃለሁ ካላወቁ አላውቅም ?
- በእሱ ሰዓት አንተ እና እኔም አልደረስንም እርግጠኛ ነኝ ዕድሜ አልደረስንም ይኑር አይኑር የማውቀው ነገር የለም
- ይበቃል በቃ ይበቃል አልደረስኩም ብለዋል
- አያውቁትም እሺ ቅድም ሰይድ ቅድም አጠቃላይ እንቅስቃሴው ፖለቲካዊ ነው ብለው ነበር ?
- ትክክል ነው
- ፖለቲካዊ እንደሆነ ያውቃሉ እንዴ እርሶ ?
- ንግግሩ ከእምነቱ ውጪ መሆኑን ከእምነቱ ውጪ የኢትዮጵያ እስታስቲክስ ከ 165 ፐርሰንት ነው የኢትዮጵያ ሙስሊም ብዙ ማለት ኃይማኖታዊ ትምህርት ሰጭ መሆኑ ግልፅ ነው ትምህርት የሚሰጠው ስለእምነቱ እንጂ ስለፖለቲካ /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄ ፖለቲካዊ ንግግር ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትክክል ነው
- ፖለቲካዊ ነው ይሄ ?
- ፖለቲካዊ ነው
- ጥያቄዬ ፖለቲካ
- ይበቃል እኮ አሁን መለሱ እኮ በቃ እኔ በማውቀው ይሄ ማለት ፖለቲካዊ ነው ብዬ ወስጀአለሁ አሉ
- ፖለቲካ ነው ብለው ተረጎሙ እሺ ቅድም ሀባሽ የሚባል አዲስ እምነት መጣ ብለው ነበር ?
- አልመጣም አላልኩም አዲስ እምነት ሀባሽ የሚባል አልመጣም እኔ ሀበሻ መሆኔን እንጂ እምነት ሀባሽ የሚባል የለም ወሀብይ የሚባል ግን አዲስ እምነት መጥቷል
- ግልፅ ነው ግልፅ ነው በቃ ይሄም ቅድም ተመልሷል ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- በእነዚህ ቅድም ባሏቸው ለሊቶች በተለይ አዛን ተደረገ ካሉበት ሰዓት በኋላ 5 ሰዓት ነው ያሉት ቅድም ?
- ጩኸት የተጮኸው አዎ
- ጩኸት አዛን ?
- ያው ለጩኸት ለአመፅ የሚያነሳሳ ነው ለሰላት አይደለም ለፀሎት አይደለም ለሰላም አይደለም ለብጥብጥ ነው በእዚያን ወቅት
- ይበቃል
- በእዚህ ሰዓት መሐመድ አባተን አይተውታል እርሶ ?
- ምሽት ላይ አላየሁትኝም
- አላዩትም አቡበክርን አይተውታል ?
- ምሽት ላይ አላየዋቸውም
- ተከሣሾችን ሁሉ አላዩም ?
- ኦልሞስት ምሽት ላይ እነሱን አየሁኝ አላልኩም መጀመሪያውኑ ነበሩም ብዬም አላልኩም ስለዚህ ጩኸቱ ምሽት 5 ሰዓት ላይ የተካሄደ ዕለት ጩኸት ተደርጓል ከእምነቱ ውጪ የወጣ ለአመፅ የሚሆን ነው ያልኩት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ወሀብያ ማለት በፈረንጆች የሚመራ ነው ብለዋል ?
- ትክክል ነው
- በፈረንጆች ነው የሚመራው ?
- ፈረንጅ ማለት አስተሳሰቡ ግለሰቡ አብዱሉሀብ የሚባለው ግለሰብ የእሱ እምነት የሚከተሉ ማለት ነው አብዱሉሀብ ማለት ደግሞ የውጪ ዜጋዊ ነው የእኛ ዜጋ ኢትጵያዊ አይደለም
- ምናልባት ስለግለሰቡ ነው እየጠየቁ ያሉት ?
- አይ ወሀብይ እሳቸው
- ምናልባት ቅድም ተመልሳል የሆኑ ከውጪ ያሉ ሰው በእዚሁ ተከትሎ እዚያ የመጣ ነው ብለዋል ሌላ የምትጠይቁት ካለ ምክንያቱም ድግግሞሽ ነው የሚሆነው
- ስለ እስላማዊ መንግስት ምንነት ያውቃሉ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ነው ብለዋል ስለዚህ ምንነት ያውቃሉ ስለ እስላማዊ መንግስት እስላማዊ መንግስት ማለት ምን ማለት ነው ?
- የእስላማዊ መንግስት ማለት ክርስቲያኑን ገድሎ ሙስሊም ለመሆን ማለት ነው ኃሳባቸው
- የተከበረው ፍ/ቤት
- መቃወሚያ ነው ?
- ያው መለሱት ግን ምንድን ነው አሁን እኛ እስላማዊ መንግስት ምንድን ነው ብለን እኚህን ሰውዬ የሙያ ምስክርነት አላሰጠንም ሰዎቹ ሲናገሩ ሰማሁ እከሌ እስላማዊ መንግስት እንመሰርታለን አለ እያሉ ነው የመሰከሩት ብሏል አላለም የሚለውን /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ አግባብ አይደለም
- እንደተባለው ተመልሳል ነገር ግን ወደ እናንተም ሳንመጣ ቅድም እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ነው የሚል ስላለ እሱን ለማጣራት ስለሆነ የሚያውቁ ከሆነ ይመልሱ የማያውቁ ከሆነ ይተውት
- አቶ ሰይድ አቤት ስለ እስላማዊ መንግስት የሚያውቁት ነገር አለ ወይ ነው እስላማዊ መንግስት ማለት ምንድን ነው የሚመራው ከቁርአን እና ከሀዲስ ውጪ ይመራል ብለው ያስባሉ እስላማዊ መንግስት ?

ECLN
1309
http://ethciminalawnetwork.com/

እስላማዊ መንግስት ማለት ባለው ግለሰብ አባባል

በማን ?

በአቡበከር አህመድ

- እሱ ሲናገር እርሶ ተርጉመው የተረዱት ማለት ነው ?
- አንድ በአብዱሉሀብ ኪታብ አካሄድ ነው እነሱ የሄዱት እንጂ በቁራአን እና በሀዲስ አይደለም ሽፋን ነው ሽፋኑ እስላማዊ መንግስት ነው
- ይቅርታ ሼህ ሰይድ ይቅርታ እኔ የጠየኮት ስለእነ አቡበከር ወይም ስለ ዋሀብይ አይደለም እስላማዊ መንግስት ቅድም ለመመስረት የፈለጉት እስላማዊ መንግስት ነው አሉ እርሶ በግልፅ እራሱ ?
- አዎ
- እነሱ አሉ አላሉም ?
- እነሱ ናቸው ያሉት
- እነሱ አሉም ብለዋል እንደገናም መጨረሻ ላይ እርሶ ደግሞ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ነው ፖለቲካዊ ነው ጥያቄአቸው አሉ ?
- ፖለቲካዊ ነው ትክክል ነው ፖለቲካዊ ሲሆን ደግሞ እና እስላማዊ ብዬ ያልኩበት ልዩነት አለው
- ቆይ ይሽውሎት ምስክር አሁን ግልፅ አድርገው የሚያውቁ ከሆነ /ግልፅ ያልሆነ/ የማያውቁ ከሆነ ግን ሰዎች ያሉትን ነው አዳምጠናል ቅድም ብለዋል ሰዎች እንዲህ እንዲህ ብለዋል ይሄንን ሊመሰርቱ ነው ብለው አስረድተውናል ስለ እስላማዊ መንግስት እርሶ የሚያውቁት ነገር ካለ ይቀጥሉ እውቀት ከሌሎት ደግሞ አይ ብዙም የለኝም ወይም የለኝም ብለው ማለፍ ይችላሉ
- እሺ በእኔ አግባብ እስላማዊ መንግስት እስከ ዛሬም አይቼም ሰምቼም ስለማላውቅም አላውቅም
- ሌላ ጥያቄ
- ስለዚህ እስላማዊ መንግስት ነው ሊመሰርቱት ነው ያሉት ኃሳብ ስህተት ነው ማለት ነው ?
- ትክክል ናቸው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ኧረ ይኸውላችሁ መልስ ተመልሷል እኮ ተመልሶ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ እያልን አሁን እርሶ ምንድን ነው የሚጠይቁት አሁን እኮ ተመለሰ በቃ አላውቅም አሉ ስለ /ግልፅ ያልሆነ/ እስላማዊ መንግስት የሚባለው /ግልፅ ያልሆነ/
- ለፍ/ቤቱ ልተወው እሺ /ግልፅ ያልሆነ/
- አቶ ሰይድ አንዋር መስኪድ ግርግር ተፈጠረ ነቦርኩ ከጠዋት እስከ ማታ ብለዋል አንዋር ምን ያህል ሕዝብ እንደሚይዝ ያውቃሉ ?
- አቤት
- አንዋር መስኪድ ውስጡ ውጪው ምን ያህል ሰው እንደሚይዝ ያውቃሉ ?
- ብዛቱን ቶታሊ አላውቀውም
- መገመትስ አይቻልም ?
- በግምትም በመቼ ወር ላይ በምን ቀን ?
- የእዚያን ቀን ለምሳሌ ያህል ሐምሌ 8 ባሉን ቀን ምን ያህል ሕዝብ ነበረ ?
- ጥቂት ያው የአባኮራን ሰፈር እና የአሜሪካን ግቢ ዱሪዬዎች ናቸው በብዛት ጥቂት ናቸው
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን ማለት ከብዛት ጋር ተያይዞ ምንም ከገዳይ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም ስለሆነም አላግባብ እየተነሳ ያለ ጥያቄ ነው ምን ያህል ይይዛል ምንያህል ሰው ይዞ ነበር የእዚያን ቀን ምንም የሚፈይድ የለም ስለሆነም /ግልፅ ያልሆነ/
- /ግልፅ ያልሆነ/ ምናልባት ለዐቃቤ ሕግ አይጠቅም ይሆናል
- ጥያቄው ቀርቦ መልስም ከእናንተ በኩል እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ ዋናው ነጥቡ ላይ አተኩራችሁ /ግልፅ ያልሆነ/ እሳቸው አላውቅም ብለዋል
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ይሄ ጥያቄ የጥቂቶች ነው ብለዋል ቅድም የሕዝብ አይደለም ብለዋል /ግልፅ ያልሆነ/ ቆጠራ ቆጥረዋል እርሶ ስንት ሰው እንደተቃወመ ስንት ሰው እንደደገፈ ቆጠራ ሰጣሂደዋል በግልዎ ጥያቄዬ ግልፅ ነው አደርገዋል አላደረጉም ?
- ቆጠራ ስንት እንደሆነ አላወኩትም ስለ ቁጥሩ አላወቅኩም
- /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥቂት መሆናቸውን ግን በአይኔ ግምት ስገምታቸው ጥቂቶች ናቸው
- እሱ እኮ ብይን ተሰጥቷል መሰለኝ ቁጥሩን ያው መልሰዋል ቁጥሩን ያው ጥቂት ከምን ሰፈር የተሰበሰቡ ነበሩ ብሎዋል ቁጥሩን አላውቅም ያን ያህል ብዙ ብለዋል አሁንም ወደ ቁጥሩ ተመለሱ /ግልፅ ያልሆነ/ በብይን የታሰረ ስለሆነ ሌላ ጥያቄ ካሎት ይቀጥሉ ስለ ቁጥሩ ግን ጨርሰናል
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም እላቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- በብይን ታልፏል ስለቁጥሩ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት
- ብይኑን የማይቀበሉ ከሆነ /ግልፅ ያልሆነ/ በፕሮሲጀሩ ከእዚያ ውጪ ግን ቁጥሩ ላይ ብይን ተሰጥቷል ለምን ተመለሱ
- ቅድም ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ.ም ኮሚቴዎቻችን ታሰሩ ብለው እንደመሐመድ አባተ ተናግረው ነበር ብለዋል በእዚህ ወቅት ኮሚቴዎቹ ታስረው ነበር እርግጠኛ ኖት ?
- እኔ አላየዋቸውም አላውቅም የእዚያን ሰዓት
- መታሰራቸውን አያውቁም ?
- አላውቅም
- በእኔ በኩል ጨርሻለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ
- ጨረሳችሁ
- ተደጋጋሚ ጥያቄ
- አይ ተደጋጋሚ አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ሰይድ የውጪ ዜጋ የሞተ ሰው ነው መሐመድ ማን ነው መሐመድ አብዱሉሀብ ብለዋል ሰለሉላዊ አሉሰለም ነብዩ መሐመድም ሞተዋል ስለሞት ቁርአን ሁሉም ነብስ ሞትን ትቀምሳለች ብለዋል ትክክል ነው አይደለም ?
- ሞትም ሁሉም አይቀርም
- ሁሉም ይሞታል /ግልፅ ያልሆነ/
- መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወጡ በቃ አሁን እኮ እኛ ያስያዝነውን ጭብጥ ሁሉም ተረሳ አሁን ምስክሩ የተናገራቸው እያንዳንዷን ነገር እየወሰዱ የአንድ ሰው ስም እዚያ ላይ ማንንም አይጠቅምም ተከሣሾቹንም የእኛንም የፍ/ቤቱን ጊዜ ነው
- ተመልሷል
- /ግልፅ ያልሆነ/ አስገዳጅ ብይን ይሰጥልን የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆይ ቆይ እሺ አሁን ጥያቄው የተመለሰ ስለሆነ ጊዜ መጨረስ ነው የሚሆነው ሌላ ከደገሙ እሱ ላይ
- የተከበረው ፍ/ቤት አስገዳጅ ብይን ሊሰጥ አይችልም እሳቸው መስክረዋል
- ቆይ እርሶስ መቼ ተሰጡት ይሄ እኮ ነው ችግሩ አሁን እኛ ተነጋግረን ሳንጨርስ እናንተ የምትይዙት ከሆነ ወይ እኛ እጃችን አጣጥፈን እንቀመጥ ስለዚህ አሁን ምንድን ነው አትደጋግሙ ተብሏል ስለዚህ አሁን ያለው ድግግሞሽ ነው እንደገና ደግሞ ማብራሪያ አታብዙ ማብራሪያው በሚበዛ ጊዜ ጥያቄውም ይጠፋል ምስክሩ የሚመልሰው ነገር የለም አንዳንዷን ጥያቄ /ግልፅ ያልሆነ/ መስቀለኛ ጥያቄው ላይ እያነሳችሁ ሂዱ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እርሶ ስልጠና የተሰጠው ስለመሻይኮቻችን ነው ብለዋል ?
- ትክክል
- እስልምናን ያመጡት እኛ መሻይኮች ናቸው እንዴ ?
- እስልምናን ያመጡት በኢትዮጵያ የሰጡን ለእዚህ እኔን ያዳረሱኝ እምነቱን መሻይኮቻችን ሕዝቦችንም ሙስሊሞችን ሕዝቦችን
- ለእርሶ ያዳረሱት አይደለም የጠየኮት ይስሙኝ ለእርሶ ያደረሱትን ሳይሆን
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁንም እንደተባለው ያው ማብራሪያ ነው የያዙት ይሄ ነገር ችሎቱ አስገዳጅ ብይን ካልሰጠ እንደዚሁ ነው የሚቀጥለው ማለት ጠቅላላ የኃይማኖት ክርክር ነው እየሆነ ያለው ስለዚህ ይሄንን ሊያስቆምልን ይገባል ከጭብጣችን ውጪ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት መልስ እንሰጥ እዚህ ላይ መልስ የምንሰጠው እኛ ሙግቱ ነገሩን ለማቅረብ ፈልገን አይደለም ያ የእኛ ፍላጎትም አይደለም እስካሁን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይኸሎት እርሶ አይቸኩሉ ብዙ ጊዜ ስለሚቸኩሉ ነው 1ኛ እኛ ተነጋግረን ምን ምላሽ መስጠት እንዳለበት ስንሰጦት ነው መመለስ ያለቦት ጥያቄው ይግባን የዐቃቤ ሕግ ጥያቄ ይግባን አይግባን ምንድን ነው ያሉት ልንል እንችላለን ስለዚህ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ በቃ ክኃይማኖት ልውጣ የተከበረው ፍ/ቤት እሺ አቶ ሰይድ እርሶ የመጅሊስ አባል ነበርኩ ብለዋል ከመቼ እስከ መቼ ?
- የገባሁበትን ነው
- የገቡበትን የወጡበትን
- የወጣሁበት እና የገባሁበትን ዓ.ም አላውቀውም
- የገቡበትን እንዴት አያውቁም ?
- ሙስሊም ከሆንክ ጀምሬ ወደ እስልምና ነው
- የመጅሊስ አባል ማለት ?
- መጅሊስ ማለት የእስልምና ኃይማኖት ጉዳዮች ምክር ቤቶች ናቸው ኃይማኖት ጉዳይ ስለሆነ መታወቂያውን ከወሰድኩ ጀምሬ አባል ነኝ
- ቆይ ምስክር ቆዩ እንዴ ይኸው ጠበቃ አሁን አላውቀሃም ባሉ አንዴት አያውቁም ተብሎ አላውቅም ካሉ በቂ ነው ምላሻቸውን ነው ስለዚህ እንዴት አያውቁም የሚል መልሱ /ግልፅ ያልሆነ/
- አኬ እርሶ የመጅሊስ እንግዲህ ከልጅነትዎ ጀምሮ የመጅሊስ አባል ከሆኑ መጅሊስ መተዳደሪያ ደንብ አለው አይደለም ?
- ልጅም ጀምሬ አላልኩም እዚህ ጋር
- መተዳደሪያ ደንቡን አያውቁትም ?
- ሕፃን ልጅ /ግልፅ ያልሆነ/ ጀምሬ እስልምና ጉዳይ ምክር ቤት አባል ነኝ አይደለም እያልኩ ያለሁት የገባሁበት ቀን እና
- አንድ አሁን ክኃይማኖቱ ልውጣ ብለው ወጥተዋል አሁንም ወደ መጅሊስ ተመልሰው ገቡ
- መተዳደሪያ ደንቡ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ስለመተዳደሪያ ደንቡ አልመሰከረም ምስክር

1314

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ መጅሊስ አባል ነኝ ብሏል መተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ አለው ብሏል የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄንን ይለፉት እና ሌላ ጥያቄ ካሎት ?
- እሺ ቅድም ምርጫችን በመስኪዳችን ብለዋል የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 2/6 ምርጫ የሚደረገው በመጅሊስ ነው ይላል ያጨቀቱል አያውቁትም ይሄንን ?
- ጠበቃ ደገሙት እኮ እሱን ስለመጅሊሱ ስለ አንቀፁ ተውት ተብሎ ብይን ተሰጠ እሱን ደገሙት አሁን አንቀፁ ይሄ ይላል ምርጫ እዚህ ነው የሚለውን ነገር ከእዚያ ውጡ እና ሌላ ጥያቄ ካሎት
- ቅድም እነ አቡበክር ሲመረጡ የተፈረመ ነገር የለም ብለዋል የሆነ ፁሑፍ እና የእነሱ ስም ያለበትም አለ ብለዋል አላማቸውም ሰውን ማረድ ነው ብለዋል አሁን እኔ እርሶን አስተሳሰብ አይደለም የምፈልገው ግምትዎን አይደለም የምፈልገው የሚያውቁትን ነገር አላማቸውን እንዴት አወቁ
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን
- ተቃውሞአችሁ ምንድን ነው
- ማለት በተደጋጋሚ ምስክራችን ሀራስ እየተደረገ ነው እንደዚሁም ካሉት ያላሉትን ነገር /ግልፅ ያልሆነ/ እየተደረገ ዓላማቸው ሰው ማረድ ነው ብለዋል እንደዚህ ዓይነት ወረቀት እንዲህ ብለዋል ማለት ምስክሩን ሀራስ የሚያደርግ እና ክብራቸውን የሚነካ ነው ስለሆነም ተገቢ ያልሆነ አጠያየቅ ነው ችሎትን የማይመጥን ቃል ነው ስለሆነም ውድቅ ሊሆን ይገባል ጥያቄአቸውን እንዲያስተካክሉ
- መልስ ልስጥ የተከበረው ፍ/ቤት መልሴ የትኛው ክብራቸውን እንደሚነካም አላወኩም እኔ ግን ዋናው ነገር እዚህ ጋር እኔ ያልኩት የትኛው ንግግሬ የትኛው ክብራቸውን እንደነካ መገለፅ ነበረበት እኔ ያልኩት አላማቸውን ኖርማሊ እዚያ ውስጥ ያለው ዝርዝሩ ነገር አላውቅም ሲሉ ነው የከረሙት አላማቸው ግን እንደዚህ መደራረግ ነው ብለዋል ዓላማቸውን እንዴት አወቁ ማለት በፁሑፍ አዩት ወይ ሲምፕሊ አላማ ማለት አንድ ፓርቲ አላማ አለው ወይም ሳምበዲ እንዲህ አለው ያ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የተገለፀበት መልኩ ማወቅ ፈልጌ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ያንን እንዲገልፁልኝ ነው የጠየኩት

- እሺ ብይን ሰጥተናል ምስክሩ ቅድም ሲመልሱ ያሉት ሰዎች ዓላማቸው ሰው ማረድ ነው አላሉም ያሉት ምንድን ነው ጅሀድ ምን ማለት ነው ሲባል ጅሀድን ነው ያብራሩ ጅሀድ ማለት በ 2 ከፍለው ቅድም ሲሰማ የነበረውን ነው ያብራሩት እንጂ ሰዎቹ ከመነሻቸው ጀምሮ ሰው ለማረድ እየተንቀሳቀሱ ነው ዓላማቸው ይሄ ነው ብለው ያስቀመጡት ነገር ስለሌለ ይሄንን ጥያቄ እለፉት እና ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- አቶ ሰይድ እርሶ የመጅሊስ አባል በነበሩበት ጊዜ መስከረም 2004 ወይም እዚያ አካባቢ ከተሰጡ ስልጠናዎች በፊት ስልጠና ተሰጥቶ ያውቃል ከተሰጠ የት በማን መቼ ?
- ከመስከረም 4 ወዲያ ነው ወይስ ወዲህ ?
- ቅድም ከተናገሯቸው 2 ስልጠናዎች በፊት ስልጠና ?
- 2 ስልጠና ተሰጥቷል የሚል ቃል አላቀረብኩም ይቅርታ ስልጠና ቦታዎች
- /ግልፅ ያልሆነ/ አልገለፁም 2 ስልጠናዎች
- ስልጠና ቦታዎች 2 ቦታ ናቸው
- ከእነሱ በፊት እርሶ አባል በነበሩበት ጊዜ ስልጠና ተሰጥቶ ያውቃል ወይ ?
- ለእኔ የተሰጠኝ ስልጠና የለም
- በጣም ጥሩ
- ሀባሽ አንዳንድ የእስልምና ነገሮችን ይከለክላል ዘካ ይከለክላል እንደማይከለክል እርሶ የአባሽ አባል ኖት እንዴት ያውቃሉ ?
- ሀባሽ የሚባል እኔ ሀበሻ ነኝ እያልኩ ያለሁት
- ቆይ ቆይ
- ይኸሎት አላሉም አባሽ ነኝ አላሉም አባሽ የሚባል አላውቅም ነው
- ካልሆኑ እንዴት አወቁ /ግልፅ ያልሆነ/
- እንዴት አወቁ ብሎ መጠየቅ ነው እንጂ አባሽ ነኝ ብለዋል ብለው አላሉም በጀመሪያ ጀምሮ ሲጠየቁ ሀባሽ የሚባል እኔ አላውቅም እኔ ሀበሻ መሆኔን ነው የማውቀው ብለዋል ስለዚህ ጊዜ /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሀባሽን ፕሪንሲፕል ያውቃሉ ምን እንደሚል ምን እንደማይል ?
- ሀባሽ የሚባል ነገር እምነት የለም ሀበሻ መሆኔን ግን ግልፅ ነው-- አባሽ የሚባል እምነት የለም
- እንዴት አወቁ እንደሌለ ?
- እንደሌለ ሀባሽ ተብሎ የሚባለው አካል ኣለ መጥቷል የሚባለው አካል አይተነም ሰምተንም አናውቅም አልሰማነውም
- ወደ እምነት ኮምፕሊትሊ የገባው ይሄ ክርክር በሙሉ ከእዚህ በኋላ ፋክት ተዘርዝሯል የተዘረዘረው ይመዘናል ያለው በቃን ከእምነት ጋር የተያያዘ ከተከሰሰው ጉዳይ ጋር ከእዚያ ውጪ የወጣ ፋክት ጥያቄ ካላችሁ አቅርቡ
- ስልጠና ተሰጥቷል ብለዋል ስልጠና ስለተሰጠው ስለ ኢትዮጵያዊያን መሻይኮች ነው ብለዋል ከእነዚያ ኢትዮጵያዊያን መሻይኮች አንዱ ደግሞ አብደላ ሀረሪ ናቸው ?
- ትክክል ነው
- ስለእሳቸው ስልጠና ተሰጥቷል ማለት ነው
- ስለ እሳቸው አይደለም የተሰጠው
- ስለመሻይኮች ?
- ስለመሻይኮቻችንን እስልምናውን ያመጡትን ስለ እስልምና አመጣጣቸው እነሱ ይከተሉት የነበረ በእዚህን አካሄድ ለእዚህ እያለ እያለ
- ስለዚህ
- የተወራረስነውን ውርስታችን ነው
- በትክክል የተወራረስነው ውርስ አንዱ
- ስለእሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለአብደላ አለሀረሪ ተሰጥቷል
- የግል እምነት የእሳቸው የሆነ የተነጠለ እንደአብዱሉሀብ የላቸውም ሙስሊሞች ሙስሊም ናቸው
- እርሶ አብዱሉሀብ የተነጠለ መሆኑን እንዴት አወቁ ?
- የተነጠለ መሆኑን 1ኛ

ECLN
1317
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆይ /ግልፅ ያልሆነ/ በማንኛውም እምነት ውስጥ ከሚያገናኘው ፓርት ውጡ እና ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ አለ በፊት የተነገረው ይመዘናል ተባለ ብዬን ተሰጠ ስለዚህ ከእዚህ በኋላ በእዚህ ምስክር ላይ ማለት ነው ሌላ ምስክር /ግልፅ ያልሆነ/ ሊቀርብ ይችላል በእዚህ ምስክር ላይ ስለእምነቱ በቃን
- አሁን የተከበረው ፍ/ቤት ስለእምነቱ አልጠይቀውም እኔ ስለስብሰው
- ዞሮ ዞሮ ስለገባን እሱን በቃን ነው
- ጨርሻለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሰናል መስቀለኛ ጥያቄ
- አቶ ሰይድ /ግልፅ ያልሆነ/
- 28ኛ ተከሣሽ ጥያቄ የለንም ብለዋል መስቀለኛ ጥያቄ በቀረቡት /ግልፅ ያልሆነ/ ዳግመኛ ጥያቄ አቅርብ ተብሏል እዚሁ ጋር ቅድም የተሰጡት /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚህ የተያያዙ ጥያቄዎችን /ግልፅ ያልሆነ/
- አቶ ሰይድ ቅድም ለዩ ሲባሉ ተከሣሾችን ለመለየት ሞክረዋል የቻሉትን ያህል ምን ያህል ጊዜ ነው ያዩዋቸው መሐመድ አባተን መቼ ምን ያህል ቀን ነው ያዩዋቸው ለምን ያህል ጊዜ ነው ትውውቃችሁ ?
- አሁን ዓመት በአንድ ቀን ነው አንድ ቀን ነው ያየዋቸው ግን ዓመት ሆኖናል
- ካዩዋቸው
- እነሱን ካየዋቸው ከዓመት በፊት ነው ያየዋቸው
- ከዓመት በፊት ነው ያዩዋቸው ?
- አዎ
- አቶ ሰይድ ለሊት ላይ አዛን ተብሏል ወይም ጥሪ ተደርጓል ብለዋል ምን ምን ነበር ሲባል የነበረው ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ አላህ ዋክበር ብቻ ነው የተባለው ብለዋል ሌላ የተባለ ነገር አለ ?
- አላህ ዋክበር ነው ብለው ያሉት
- ውጪ ሲወጡ ሰዎችን አይቼአለሁ ብለዋል ምን ይዘው ነበር እነዚያ ያዩዋቸው ሰዎች ?
- ድንጋይ ነበረ ስለትም የያዙም ነበረ እና በድንጋይ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት

1372

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተቃውሞ ምንድን ነው
- የማጣሪያ ጥያቄ እኮ እንደገና አዲስ ጥያቄ መጠየቂያ አይደለም የመስቀለኛ ጥያቄ ላይ የተያዘውን ለማስረዳት እንጂ እኛ ጠይቀናቸው መውጣታቸውን መስክረዋል እሳቸውም መስክረዋል ምን ይዘው ነበር ምን አልያዙም ነበር የሚል ነገር በዋና ጥያቄም አልተነሳም እኛም አልጠየቅንም አሁን እሳቸው እንደገና አዲስ /ግልፅ ያልሆነ/ ጥያቄ አዲስ ፋክት ነው እየጠየቁ ያሉት ስለመውጣታቸው ተመስክሯል በቃ እዚያ ጋር ነው የሚቆመው
- ዐቃቤ ሕግ ምላሽ
- የተከበረው ፍ/ቤት በተደጋጋሚ ከቦታቸው አንፃር የተለያየ ቦታ ነበር የነበሩት እንደዚሁም በርቀት እንዴት አዩ እና ማየታቸውን ለማስተባበል የተጠየቁ ጥያቄዎች ነበሩ ያንን በቦታው እንደነበሩ ኮንፈርም ለማድረግ እና ተያያዥነት ያለው ጥያቄ ነው ስለሆነም በእኛ እምነት በመስቀለኛ ጥያቄ ለማስተባበል የተሞከሩ ፍሬ ነገሮችን ነው ለማስተካከል እየጠየቅን ያለነው ስለሆነም ከእዚህ ውጪ ያልሆነ ከእዚህ ውጪ የሆነ ጥያቄ አልጠየቅንም ተቃውሞ ያለ አግባብ ነው
- ብይን ተሰጥቷል ምስክሩ በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ቅድም የተጠየቁት ነገር ነበር ጥሪ ተደርጎ ነበር /ግልፅ ያልሆነ/ በእዚያ ጥሪ መሠረት የወጡ ሰዎች ነበሩ ረብሻ ነበር እስከ 6 ሰዓት ውጪ ቆየሁ ከእዚያ በኋላ ተመለስኩ ብለዋል ረብሻው አሁን ዐቃቤ ሕግ በእዚያ በኩል የተነሳው ምንድን ነው የያዙት የሚል ጥያቄ ተነስቷል በተከሣሽ በጠበቃ በኩል የቀረበው መቃወሚያ ይሄ በመስቀለኛ ጥያቄ አልተነሳም አዲስ ነገር /ግልፅ ያልሆነ/ በመስቀለኛ ጥያቄ የሚጠየቀው ያው ግልፅ ነው በድጋሚ ጥያቄ ይቅርታ በድጋሚ ጥያቄ የሚጠየቀው ግልፅ ነው በመስቀለኛ ጥያቄ የተነሳ ነገር መሆን አለበት ጥያቄው ተነስቷል አልተነሳም የሚባለው ያው በተዘዋዋሪም በቀጥታም ጥያቄ ሊነሳ ይችላል አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ የተጠየቀው ረብሻ ነበር በእዚያ ጥሪ መሠረት 1 ሰዓት ውጪ ቆይቼ ተመለስኩ ብለዋል እና ረብሻው በምን ተፈፀመ ተብሎ መጠየቅ አዲስ ፋክት መፍጠር አይደለም ስለዚህ ጥያቄው በእዚህ መልኩ ተስተካክሎ ይቀጥል ተብሏል

1319

http://ethcriminalawnetwork.com/

እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ሰይድ አሁን ፍ/ቤቱ እንደገለፀው ረብሻው በምንድን ነበር የእዚያን ቀን የተፈፀመው ወይንም ሲወጡ ያዩዋቸው ሰዎች እንዲሁ ነበር ረብሻውን ሲፈፅሙ የነበረው ?

ያው ድንጋይ በመወርወር

ሌላስ ?

ደማችን ለዲናችን ብሎ በመጮህ ድንጋይ በፖሊሶች በመወርወር እና የተለያዩ ስለታስለቶችን ይዞ በመውጣት

የተለያዩ ምኖች ይዘው ነበር ?

አዎ

ምን ነበር ይዘው የነበሩት ስለታ ስለት ማለት ?

እንደገጀራ ነገር ማለት ነው

ገጀራ ?

አዎ

ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ 2 ዓይነት ጅሀድ አለ አንዱ ለልማት አንዱ ለጦርነት ብለዋል?

ትክክል

ይሄንን በእዚህ ለሊት የተጠራው ጅሀድ ምን ዓይነት ጅሀድ ነው ?

ይሄኛው ጅሀድ ለሽብርተኝነት ነው

ለምን ድርጊት ነበር የተጠራው ?

ግልፅ ነው ዐቃቤ ሕግ እሱ ላይ የተመለሰው ግልፅ ነው ሌላ እንትን ካላላችሁ በእሳቸው እውቀት ልክ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ ፍ/ቤቱ ይመዝነዋል

እሺ የተከበረው ፍ/ቤት

ምስክር አንድ ሁለት ጥያቄዎች ልጠይቆት የምጠይቆትን ብቻ ይመልሳሉ /ግልፅ ያልሆነ/ መዝለፍ ውስጥ ምናምን አይግቡ እነ ወሀብያ ምናምን ይሄንን እንዲዘልፉ አይደለም የጠራኖት ምስክርነት እንዲሰጡ ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- 15 ቀን የተሰጠ ስልጠና አለ ብለዋል ቅድም በተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ የሕገ መንግስት ስልጠና ነበር ብለዋል 15ቱንም ቀን በሙሉ የሕገ መንግስት ስልጠና ነበር እንዴ ?
- አይደለም አንድ ቀን ነው
- ስንት ቀን ነው ?
- አንድ ቀን
- አንድ ቀን ብቻ ?
- አዎ
- ቅድም እንደገና በተከሣሽ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ሕፃናት ሲወለዱ እና በአካባቢው ሁኔታ የአካባቢው ሁኔታ አሳሳቢ ሲሆን ነው ጅሀድ የሚጠራው ተብለው ሲጠየቁ የመለሱት አለ
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለ ምስክሩ ያላሉትን ነው ዐቃቤ ሕግ እያሉ አስመስለው እየጠየቁ ያሉት የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ እንግዲህ ሁላችንም ሰምተነዋል አዛን የሚደረገው ተብሎ ነው እንጂ የተጠየቀው ጅሀድ የሚደረገው እንግዲህ በአነጋገር ስህተት ከሆነ እሱን ያስተካክሉ አለበለዚያ እንዲህ ብሎ አልተናገሩም አልጠየቁም ጠበቆችም የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ ጥያቄአቸውን እንዲያስተካክሉ ይደረግ
- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ከፍ ያሉት ጠበቃ ናቸው የጠየቁት አዛን የሚደረገው ሕፃናት ሲወለዱ ወይም አሳሳቢ ሁኔታ ሲኖር ነው ያሉት ምናልባት ጅሀድ ብዬ ከሆነ ከአነጋገር /ግልፅ ያልሆነ/ በእዚያ መልኩ እንዳስተካክለው ይፈቀድልኝ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አመሰግናለሁ ምስክር ቅድም አዛን የሚደረገው ሕፃናት ሲደወለዱ ወይም ደግሞ አሳሳቢ ሁኔታ ሲያጋጥም ነው በሚል በጠበቃው ተጠይቀው መልሰዋል የእዚያ አሁን እርሶ በጠቀሷቸው ሐምሌ ወር ውስጥ የተደረጉ በምሽት የተደረገው አዛን ምን ነበር ዓላማው ?
- ማለት
- ምን እንዲሆን ነው ?
- ለረብሻ ማለት ነው ለአመፅ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዛን ሳይደረግ ረብሻ ማድረግ አይቻልም
- እንዲወጣ ማለት ነው እንዲወጡ ሰው እንዲወጣ ወደ ውጪ እንዲወጣ ማለት ነው ጥሪ ነው
- ድጋሚ ጥያቄ አበቃን
- በፍ/ቤቱ የተነሳ ማጣሪያ ጥያቄ የለም ምስክር እናመሰማናለን መሄድ ይችላሉ አሁን 6 ተኩል ሆኗል ከእዚህ በኋላ ሌላ ምስክር መስማት አንችልም ስለዚህ 8 ሰዓት ትደርሳላችሁ ማረሚያ እስቲ አሁን ምንድን ነው እናንተም እኛም እንደምናውቀው ትላንት ሁሉም ከመሸ ነው የደረሰው ስለዚህ 8 ሰዓት ጀምረን በኋላ ሰዓቱን አጠር ብናደርገው ነው የሚሻለው ስለዚህ ሁላችሁም 8 ሰዓት እንገናኛለን እዚህ ከሰዓት በኋላ የጠዋት ችሎት በእዚሁ አብቅቷል።

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከምስክር በፊት አቤቱታ አላችሁ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ የተከበረው ፍ/ቤት ኬዙ ስፋት ፍ/ቤቱ የሚያውቀው ነው በመጀመሪያ ግን አሁን አሁን የተሰጡን ማሰሳቢያዎች በሙሉ አስተካክለን ለመስራት እንሞክራለን ሁሉንም አስተያየቶችን የምንቀበላቸው ናቸው እኛም ጋር የታዘብናቸው ነገሮች ነበሩ እናስተካክላለን /ግልፅ ያልሆነ/ ሌላው ከኬዙ ስፋት አንፃር እንደገና ተከሣሾችም ብዛት አንፃር ጉዳዩን ለመምራት እንዲያስችለን በእዚሁ ደግሞ መስቀለኛ ጥያቄ እዚሁ /ግልፅ ያልሆነ/ ለእዚህም መረጃ ለመለዋወጥ እንዲመቸን በማሰብ የተከሣሾችን አቀማመጥ እኛ በሚመቸን መልኩ አድርገነው ነበር ለምስክርቱ/ግልፅ ያልሆነ/ ምስክሩ በሚመሰክርበት ነጥብ ላይ የተሻለ መረጃ ሊሰጠን የሚችለውን ተከሣሽ ወደ አጠገባችን አድርገን ሌሎቹ እንደሚመቻቸው እንዲቀመጡ አድርገን ነበር ጠዋት ግን ማንነቱን መለየት ጋር /ግልፅ ያልሆነ/ ይመስለናል አሁን ክሱ ላይ በተግፈው ተራ ቁጥር ነው እንዲቀመጡ የተደረገው ቁጥራቸው እየተጠየቀ ነው የተቀመጡት ይሄ ደግሞ እኛ አሁን ኬዙን ለመምራት ያስቸግረናል የተሻለ መረጃ ልናገኝበት የምንችለው ተከሣሽ አለ ያንን ተከሣሽ አጠገባችን ማድረጋችን ለመስቀለኛ ጥያቄው ይጠቅመናል የተሻለ መረጃ እንዲሰጠን የሚያግዘንን ሰው /ግልፅ ያልሆነ/ ይሄ ከተከለከለ ግን መስቀለኛውን ጥያቄ ለመጠየቅ እንደገና ተነስተን እዚያ ጋር ልንጠይቅ ነው እዚያ ጋር እየሄድኩ ልጠይቅ ነው የፍ/ቤቱን ጊዜ እናጠፋለን እራሳችንም እንቸገራለን ኦርጋናይዜሽኑም ይጠፋብናል እና ተከሣሾቹ ለእኛ ለምስክርነቱ በሚመቸን መንገድ እንዲቀመጡልን ቢደረጉ ይሄ በቁጥር እንዲቀመጡ መደረጋቸው /ግልፅ ያልሆነ/ እና እሱ እንዲስተካከልልን ነው
- ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶታል ይሄንን ጥያቄ በተመለከተ ከዐቃቤ ሕግ ምላሽ መቀበል አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም እንግዲህ ተከሣሾቹ በቁጥራቸው በተከሣሽነት ቁጥራቸው ሊሆን ይችላል ኦረ በሌላ መንገድ ተቀምጠዋል አቀማመጣቸውም ዘሆን ፍ/ቤቱ ችግር ያለበት ሆኖ አላገኘውም ምናልባት ልታነጋግሯቸው የምትፈልጓቸው ምስክሮች ራቅ ብለው ተከሣሾች ራቅ ብለው ያሉ ከሆነ በኋላ ላይ ቀረብ ብለዋችሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እንዲያነጋግሯችሁ ማድረግም ይቻላል ካገር ግን አሁን ምስክርነት ሂደቱ ከመሰማቱ በፊት ተሰይቶ ወደ አንድ ቦታ እንዲዛመዛ ማድረግ የሚለው ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ግን የምትፈልጓቸው ተከሣሾች ያሉ እንደሆነ ገልፃችሁ ቀረብ ብለው ወደ እናንተ አካባቢ እንዲያነጋግሯችሁ ዕድሉን መስጠት ስለሚቻል የምስክርነት መስማት ሂደት ተከናውኗ በኋላ ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክር ይግባ እስቲ ቀጥሎ ያለው ምስክር

- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ይቀመጡ ምስክር ምናልባት ምስክሩ ቅድም የተፈጠረው ችግር እንዳይደገም ተከሣሾች በግን ላይ እንደሚመሰክሩ እስኪለዩ ድረስ እንድትነሱለት ትጠየቃላችሁ እንድትነሱ
- ስምዎት ማን ይባላል የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ?
- ፎአድ
- በማስረጃ ዝርዝር ስንተኛ
- የመጡት ለምንድን ነው ?
- ለምስክር
- ተከሣሾች ውስጥ የሚያውቋቸው አሉ ?
- መጀመሪያ በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- ያሲን ኑሩ
- ያሲን ኑሩ
- አህመዲን ጀባል አቡበከር አህመድ ካሚል ሸምሱ
- ሌላስ ?
- በቃ
- በ 4ቱ ላይ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እስቲ እነዚህ ሰዎች ይለዩዋቸዋል በአካል ?
- ያሲን ኑሩ
- ያሲን ኑሩ የትኛው ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- የትኛው ነው ይሄ ነው እጁን ያወጣው ነው ?
- አዎ
- 8ኛ ተከሣሽ ማን ነው ስምህ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሱማ ይችላሉ እኮ እሱን ይችላሉ
- አሁን ምስክሩ ይሸውሎት ምስክር ወደ እዚህ ዙር አሁን ምንድን ነው የሚያውቋቸው ከሆነ ነው የማያውቋቸው ከሆነ ደግሞ ለምን እንደሚመሰክሩ በኋላ ይዘረዝራሉ ለምን እንደማያውቋቸው ለምን እንደሚያቋቸው የሚያውቋቸው ከሆነ ነው ስለዚህ ጠጋ ብለው መለየት ይችላሉ ቁጭ በሉ እናንተ /ግልፅ ያልሆነ/
- በልብሱ ምን የለበሱ እሱ ነው መጨረሻ ላይ ያለ ነው እሱን ነውያሉት ስምህ ማን ነው?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌላ እስቲ ምንአልባት እነ ቅድም ከተናገሩት እንጠይቆት እና አቡበክር አህመድ ብለዋል ቅድም አቡበክር አህመድ ላይ እመሰክራለሁ ብለዋል እና አቡበክርን መለየት ይችላሉ አቡበክር አህመድ ምን የለበሰ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የትኛው እሱ ነው ፊት ለፊት ያለው እስቲ አንተ ነህ ስምህ ማን ነው እሱን ነው ስምህ ማን ነው እሱን ነው ያሉኝ አሁን ምስክር እሱን ነው ያሉት ወይስ ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ ይመለሱ በቃ ይመለሱ እና ቁጭ በሉ
- እነዚህን ሰዎች የት ነው የሚያውቋቸው ቅድም በስም የጠሯቸውን ሰዎች እንዴት ሊያውቋቸው ቻሉ ?
- እንዴት
- የወቋቸው አጋጣሚ ምንድን ነው ?
- አንዴ ሁለቴ ነው ያየዋቸው
- ዝምድና ወይም ፀብ የሎትም ?
- የለኝም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቅረብ ተብሏል
- አቶ ፎአድ ቅድም ለችሎቱ ሲገልፁ የመጣሁት ለምስክርነት ነው በማለት የጠሯቸው ስሞች አሉ እነዚህ ሰዎች የት ነው የሚያውቋቸው የት ነው የሚያውቋቸው ?
- አንዋር መስኪድ አካባቢ ኢንዴ ሁለቴ አይቼአቸዋለሁ
- መቼ ነው ቀኑ ?
- ቀኑ አላውቀውም
- በስንት ዓ.ም ነው አምና ነው ዘንድሮ ነው ?
- ያው ሕዳር ላይ
- ሕዳር ላይ ?
- አዎ
- የትኛው ሕዳር የአሁኑ የትኛው ነው ?
- ሕዳር የአሁኑ ቀን 8
- ስንት ዓ.ም ነው ?
- 11ኛ ወር
- አይ ይረጋጉ እና አሁን ሕዳር እያሉን ነው 11ኛ ወር እያሉን ነው ምን ያህል ጊዜ ይሆነዋል ካዩዋቸው ምን ያህል ጊዜ ይሆነዋል ከምን ያህል ጊዜ በፊት ነው ያዩዋቸው ?
- ቆይቷል ከዓመት ምናምን
- ከዓመት በፊት ?
- አዎ
- ስለዚህ አሁን ምን ወር ላይ ነው ያለነው ?
- አሁን ጥር ላይ ነው
- ጥር ላይ ነው ያለነው ?
- አዎ
- አምና ነው ያዩዋቸው ማለት ነው ?
- አዎ
- ምን ወር ላይ አምና ምን ወር ላይ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወሩን አላውቀውም
- ወሩን አያውቁትም ?
- አዎ
- በግምት የወሩ መጀመሪያ ነው አጋማሽ መጨረሻ የወሩ መግቢያ ነው ወይስ እንዴት ነው የዓመቱ ?
- ዓመት ብቻ መሆኑን ነው የማውቀው
- በግምት 1 ዓመት ይሆነዋል ?
- አዎ
- ምን ሲያደርጉ ነው የሚያውቋቸው ?
- ያው አንዋር መስኪድ ላይ ያው ሲያስተምሩ ነዋ
- ሲያተምሩ ?
- አዎ
- ምን እያሉ ነበር የሚያስተምሩት ?
- አሁን ያለው መንግስት ያው አያዘንም ነው አልሀባሽ የሚባል ኃይማኖት መጥቷል አንቀበልም እና ደግሞ ያው የራሳችን መንግስት እናቆማለን
- ምን ዓይነት መንግስት ነው እናቋቁማለን ያሉት ?
- ምን ዓይነት መንግስት ያው የእነሱ ፍላጎት የሚያሟላ ነዋ
- የእርሶን እምነት ሳይሆን ይዜንን ነገር ሲናገሩ ነው የሰሟቸው ?
- አዎ
- ማይክራፎን ነው የሰሙት ወይስ በአካል አጠገባቸው ነበሩ ሲያወሩ ?
- ማይክራፎን ላይ
- በማይክራፎን ነው የሚያወሩት ?
- አዎ
- ስማቸውን እንዴት ሰሙ ?
- ስማቸው እዚያ ሲያስተዋውቁ ነዋ
- ማን ነው የሚያስተዋውቃቸው ?
- እዚያው ያው ለሕዝቡ ሲያስተዋውቁት ነዋ

1327

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እራሳቸው ስማቸውን እያስተዋወቁ ነው የሚናገሩት ?
- አዎ
- እስቲ ማን ማን በማለት አስተዋወቁ ማን ስሙን አስተዋውቆ ምን ተናገረ ?
- ያሲን ኑሩ ያው ስሙ አስታዋውቋል
- እሺ ምን አለ ?
- ስሙ አስተዋውቆ ያው ከጠዋት 2 ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ 7 ሰዓት ያው
- ምን ያደርግ ነበር በእዚህ አሁን ባሉት ሰዓት ?
- እኛ ያው መንግስት አያዘንም
- የትኛው መንግስት ነው አያዘንም የሚሉት ?
- አሁን ያለው መንግስት እና አልሀባሽ የሚባል ኃይማኖት መጥቷል አንቀበልም
- ለማን ነው ይሄንን የሚሉት ?
- ለሕዝቡ
- ምን እንዲያደርግ ነው ሕዝቡን እንደዚህ የሚሉት ?
- ሕዝቡ እንግዲህ አመፅ እንዲፈጥር ነዋ
- ይሄንን በምን ተረዱ አመፅ እንዲፈጥር መሆኑን እርሶ ?
- አመፅ ደግሞ መፍጠር መነሳት ደግሞ ያው ለሀገርም ሆነ
- አይ እሱ ሳይሆን አመፅ እንዲፈጥሩ የቀሰቀሱ መሆኑን ከምን ተረዱ ከሚናገሩት ቃል ከምን ተረዱ እርሶ ?
- ከሚናገሩት ነዋ ያው ለሕዝብ ላይ ከሚያስተላልፉት ንግግር ነዋ
- እስቲ ለሕዝብ ከሚያስተላልፉት ከሚሉት ቃላት ወይ ንግግሮች ውስጥ የሚያስታውሱትን ለችሎቱ ይግለፁ ተረጋግተው ?
- እንግዲህ ያው የመንግስት ጥላቻ ነው
- እስቲ ጥላቻ የሚሉት በምን ተገለፀ ?
- በምን ተገለፀ እንግዲህ በተለያየ ነገር ነዋ
- ይሄ የተለያየ ነገርን አሁን ለችሎቱ ምስክርነት እየሰጡ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የእርሶን ቃል ይፈልጋል እና ተረጋግተው እስቲ ምን ይሉ ነበር ምን ይሉ ነበር የሚለውን ነገር እስቲ አስረዱ ያሲን ኑሩ ከ 2 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ነበር ብለዋል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ቀኑ ምን እንደሆነ ያስታውሳሉ የሣምንቱ ?
- ቀኑ ያው 3 ጁማ ነበር ጁማ ቅዳሜ ያው እሁድ ነዋ 3 ቀን
- 3 ቀን አርብ ቅዳሜ እሁድ ?
- አዎ
- ምን ወር ላይ ነው ?
- ሐምሌ
- ሐምሌ ላይ ?
- አዎ
- ሐምሌ ስንት እንደሆነ ?
- ቀኑ ቀን 8 ነዋ
- ሐምሌ 8 ?
- አዎ
- የትኛው ነው ሐምሌ 8 የጀመረበት ነው ወይስ የመጨረሻው ቀን ነው ?
- የጀመረበት ነዋ
- የጀመረበት ?
- አዎ
- እስቲ ሐምሌ 8 ከጀመረ መቼ ምን ተደረገ ማን የትኛው ተከሣሽ ምን አለ እስቲ ለፍ/ቤቱ ተረጋግተው ?
- አሁን ያሲን ኑሩ አበቃ
- ምን አለ ያሲን ኑሩ ?
- ያሲን ኑሩ ያው ያለው መንግስት አሁን ያለው መንግስት አያዘንም
- ምን አደረገ ነው የሚለው መንግስት ?
- በኃይማኖት ላይ /ግልፅ ያልሆነ/ ገብቷል
- ምን አደረገብን አለ ?
- ሙስሊም ለሙስሊሙ ያው ከፋፍሎታል ነዋ
- ሌላስ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እና አልአባሽ የሚባል ኃይማኖት ደግሞ ያው ከመጅሊስ ጋር ሆኖ ከሊባኖስ ስላስገባ ያው ይሄንን ደግሞ በየመስኪዳችን ያው ያስተምር ስለሆነ ያው አንማርም አንቀበልም እያሉ ነው
- ምን እናደርጋለን ነበር አንቅበልም ምን እናደርጋለን ነበር ሲሉ የነበረው ?
- ያው እንግዲህ ሕዝቡ እንግዲህ ያው በመሴጅም ሆነ በፌስ ቡክ ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ያው ያስተላልፋሉ
- ምን ነበር የሚለው መልዕክታቸው ?
- ያው እዚያ ቦታ /ግልፅ ያልሆነ/ እዚያ ቦታ ተገናኝተን ያው ተክቢራ /ግልፅ ያልሆነ/ የሆነ የራሳቸው መለያ ለእይታ ነገር ያው ቢጫ ወረቀትም ሆነ ነጭም ወረቀት ሆነ ያው እና ያው ሰውን ደግሞ ሰግዶ ሲወጣ ደግሞ ያው እጅ ለእጅ ተያይዘው ደግሞ እዚያ ቦታ ላይ ያው ማንም ሰው እንዳይንቀሳቀስ ያው የማድረግ ነበር ሲሰራ የነበረው
- እሺ እስቲ አሁን ቅዳሜ እና እሁድ በአንዋር መስኪድ ተሰብስበዋል ነው የሚሉት ?
- አዎ
- ምን ስለተፈጠረ ነው እዚያ የተገናኙት ምን ተፈጥሮ ነው እዚያ የተገናኙት ወይስ እዚያ ምን አሉ የእዚያን ቀን እንደተገናኙ ?
- እዚያ የተሰበሰቡት እንግዲህ ያው በየመስኪዱ ያው ሰደቃ ይደረግ ነበር
- የምን ሰደቃ ነበር ይደረግ የነበረው ?
- መውሊድ ያው የሙስሊሙ አንድነት ትላንት ያው መውሊድ አይቻልም ሲል የነበረው ዛሬ ያው የሰደቃ እንትን ብሎ በየቦታው በየመስኪዱ ያው ይሄን ነበር ያው እስፖንሰር ሲደረግ የነበረው በእዚያ ምክንያት ያው ሲከለከሉ ያው አወሊያ ላይ ሰደቃ ማድረግ ተጀመረ ከእዚያ በኋላ ደግሞ ያው እንግዲህ
- ስለ ስለ አወሊያው ሰደቃ ምን ሆነ ?
- ምን ሆነ እንግዲህ ያው መንግስት ያው ኢንፎርሜሽን ደርሶት ያው ምን እንደሚያደርጉ ደርሶት ያው ለሚያደርጉት ነገር ያው እንዲቆም አደረጉ
- እንዲቆም ከተደረገ በኋላ ከእዚያ ምን አደረጉ እነሱ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ በኋላ በየመስኪዱ ያው ተክቢራ እንዲደረግ ያው እንግዲህ በስልክም ደውሎ በየቦታው ያው መስኪድ አላህ ዋክበር እንዲባል ይሄንን ያው አስተላልፈዋል
- ምንድን ነው ተክቢራ እንዲደረግ ማን ነበር እዚያ እንዲሰበሰብ የተጠራው ለምንድን ነው የተጠራው የተጠራው ሕዝብስ ምንድን ነው የተነገረው መንግስት ምን አደረገን ነው የተባለው የእዚያን ቃን ?
- ያው ኃይማኖት በኃይማኖት ገብተዋል ነው በኃይማኖት ገብተዋል ስለዚህ ያው እኛ የራሳችን ያው የራሳችን ያው መንግስት እናቆማለን ያው እራሳችን ተገንጥለን ያው ማለት ነው
- ማን ማን ነው ምን ዓይነት መንግስት ምንን ያካተተ መንግስት ነው እናቋቁማለን ያሉት ?
- እንግዲህ መጀመሪያ
- ስንት ሆነው ነው መንግስት እናቋቁማለን ያሉት ?
- ያው ይሄ አንዋር መስኪድ ነው ያው ሲያስተላልፉት የነበር ያው 4ቱ ናቸው ያው ያው በየተራ እየተቀያየሩ በማይክራፎን ያው
- ሚገኘ የሚወክል መንግስት ነው እናቋቁማለን ያሉት ?
- ያው የእስላም መንግስት ነዋ
- አይ ነዋ ሳይሆን ያሉትን ነው ምን ዓይነት መንግስት እናቋቁማለን አሉ ?
- እንግዲህ ያው ይሄንን መንግስት ያው ይሄንን መንግስት ያው ለሙስሊሙ ስላልተስማማ ያው ሙስሊም የሚስማማ መንግስት ያው እናቆማለን ነዋ
- እንዴት ነው ሙስሊም ብቻውን መንግስት ያቆማል ነው ያሉ አሁን ብቻውን ስለሆነ ሲሉ ?
- አዎ
- ምንድን ነው ተቃውሞ ?
- በተደጋጋሚ የመምራት ጥያቄዎች እየጠየቁ ነው አሁን ግን የሙስሊሙን ብቻ መንግስተ ነው ወይ እናቋቁማለን ያሉተ ብለው ነው የጠየቁተ ይሄ ቀጥታ መልሰውት ነው የጠየቁት ይሄ ጥያቄ 3/4 ጊዜ /ግልፅ ያልሆነ/ ምክንያ ያልመለሱት ጥያቄ ነው የነበረው አሁን በቀጥታ መመስከር ያለበት ግን ነገሮችን ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የጠየቁት ጥያቄውም እንዲሰረዝልን ሊመለስም አይገባም የዐቃቤ ሕግ ጥያቄም እራሱ መሰረዝ አለበት የሙስሊም መንግስት ብቻ ነው ወይ እናቋቁማለን ያሉት ብለው የጠየቁት

- ዐቃቤ ሕግ መልስ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄአችን ፊፅሞ እየመራን አይደለም አሁን ያነሳነው ጥያቄም ተከሣሹ በተደጋጋሚ እንድምታ ሲያስቀምጡ እኛ ደግሞ በወቅቱ የሰሙትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያወቁትን ጉዳይ ነው ለፍ/ቤቱ እንዲናገሩ እየፈለግን ያለነው እንድምታው ቅድምም ወደ ረጅም እንትን እየወሰደ ስለሆነ ከእዚያ አንፃር ነው እያብራራን ያለነው እሳቸው ከሰጡት ቃል ተነስተን ነው የእሳቸውን ቃል ተውሰን ነው እንጂ ፊፅሞ አዲስ እኛ የምንናገረውን ቃል እንዲመሰክሩልን አንፈልግም ስለሆነም አልመራንም ጥያቄውም የሚሰረዝበት አግባብ የለም ተቃውሞው ውድቅ ይሁንልን ነው
- ፍ/ቤቱ ጉዳይን መርምሮ ትዕዛዝ ሰጥቷል ምስክሩ ምን እየመሰከሩ እንዳሉ በእዚህ ፍ/ቤትም በማስታወሻዎች እየተያዙ ነው ሪከርድ እየተደረገ ነው ያለው ከእዚህ በፊት በሰጡት ቃል አሁን ዐቃቤ ሕግ ጠይቆ መልስ የሰጡበትን ጉዳይ ተመዝግቦ ነው ያለው እኛም መዝግበነዋል ምስክሩም ቃላቸውን ሰጥተዋል ስለዚህ ተመዝግቦ ባለ ነገር ላይም ነው ድጋሚ ጥያቄ አሁን ተደግሞ ጥያቄ የቀረበው እና ወደ ሌላ ጥያቄ
- ያሲን ኑሩ ይሄንን ተናገረ ብለዋል እስቲ ሌሎቹስ ?
- ያው ሌሎቹም ያው
- ስም እየጠሩ እገሌ ይሄንን ተናገረ
- አህመዲን ጀባልም ያው
- ምን አለ አቶ አህመዲን ጀባል ?
- እሱም ያው ይሄ አሁን ያለው መንግስት ያው አይገዛንም አልአባሽ የሚባል ኃይማኖት አንቀበልም እና ደግሞ የራሳችን መንግስት እናቆማለን
- ሌላስ ?
- በቃ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለማን ነበር ይሄንን ይሉ የነበረው ?
- ለተሰበሰበው ሕዝብ
- ሕዝቡ ምን ይል ነበር በወቅቱ ?
- ሕዝቡ እንግዲህ ያው እያለቀሰ ነው ያው እየሰማ ነው ማለት ያው ሙስሊሙ ላይ ማለት በደል ደርሷል እንግዲህ ያው ማለት ነፃነት እንዳጣ ምናምን ነገር እንደተጨቆነ ምናምን ነገር ያው ሌላም ያው
- እስቲ አብራሩት አሁን ያሉትን ነገር ሙስሊሙ እንደተጨቆነ እንደተበደለ ነፃነት እንዳጣ ያሉትን ነገር እስቲ ያብራሩ እና ሌላም ያሉት ምን ምን ማን ነው ይሄንን የሚነግረው ለሕዝበ ሙስሊሙ ?
- አህመዲን ጀባል
- ምን ምን እያለ ነው የሚነግረው ?
- ያው ይሄ አሁን ያለው መንግስት አያዘንም
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያ ?
- ምስክሩ ያልመሰከሩትን ሕዝቡ እንዴት ነው ጥያቄው ሕዝቡ ምን አለ ነበር ቀጥሎ ግን ዐቃቤ ሕግ ይሄንን ማን ነበር ለሕዝቡ የሚነግረው ምክንያቱም መጀመሪያ ሕዝቡ ምን ዓይነት ስሜት ነበረው ሆኖ እያለ ቀጥሎ ግን ይሄንን ለሕዝቡ ማን ነው የነገረው የሚል ነው ምስክሩም የመሰከሩት የሕዝቡ ስሜት ሕዝቡ የተጨቆነ ዓይነት ስሜት ነበረው ነው ያሉት እንጂ
- አሁን የቱ ጋር ነው ?
- ቀጥሎ የመጣው ጥያቄ
- መሪ ጥያቄ ነው ነው ወይስ ?
- ምስክሩ ያላሉትን መጀመሪያ ምስክሩ ያሉት ሕዝቡ ምን ዓይነት ስሜት ነበረው እነዚህ ሰዎች ሲናገሩ ተብሎ ተጠየቀ የመጨቆን ስሜት ነበረው ካለ በኋላ ይሄንን ማን ነው የነገራችሁ የሚል ነው የተከተለው ስለዚህ የሕዝቡን ስሜት ገልፀው ከእዚያ በኋላ ይሄንን ነገር ማን ነው የነገራቸው የሚባል ነገር አብሮ የማይሄድ ነው ጥያቄው እራሱ አግባብ አይደለም ምስክሩ መልሰውታል የሕዝቡን ስሜት ገልፀዋል

1333

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከአዚያ ይሄ የሕዝቡ ሶሜት ማን ነው የነገራችው የሚባለው አግባብ አይደለም ይሰረዝልን

- ዐቃቤ ሕግ
- የተከበረው ፍ/ቤት ሕዝቡ ምን ይል ነበር ብለን ስንጠይቅ ምስክሩ ሕዝቡ ያለቅስ ነበር ኃይማኖቱ እንደተበደለ እንደተጨቆነ የተነገረው ስለሆነ ነው ያሉት ይሄንኑ እንዲያብራሩ ነው ማን ነው ይሄንን ያለው ነው ስለዚህ ምስክሩም እዚህ ስላሉ እንትን የሚሉት ነው ምናልባት ተመዝግቧል ፍ/ቤቱም ሪከርድ የተደረገው እንትን ሊል ይችላል በተደጋጋሚ ጥያቄዎች ሪፍሬም እየተደረጉብን ነው እና ፍ/ቤቱ እዚህ ላይ ቴንሽን ይስጥልን ነው የምንለው በእኛ በኩል ጥያቄው አግባብ ነው ውድቅ የሚሆንበት የለውም

እንግዲህ አሁን በግልፅ ግራ ቀኞችሁም እንዳነሳችሁት በእናንተ በኩል የቀረበ መቃወሚያ ተመልክቶ ዐቃቤ ሕግ ምላሽ ሰጥተውበታል ሕዝቡ የነበረውን ስሜት ምስክሩ ገልፆዋል ከእዚያ ቀጥሎ ማን ምን አለ የሚለው ተያያዥነት ያለው ነው ሆኖ ፍ/ቤት ያገኘው እና ይቀጥል ተብሏል

ሕዝቡ ለምን ነበር ያለቅስ የነበረው ?

ካዝቡ እንግዲህ ያው በሙስሊሙ ሙስሊም ያው ምንም እራሱን እንደፈለገ ይሁን ንጂ ሌላ የመንግስት አባል መንግስት ለምን ይገባል መንግስት በኃይማኖት እገባም ይላል ግን ገብቷል አዎ ስለዚህ አሁንም ይሄ ሙስሊሙን በሙስሊሙ ግስደብደብ የተደረገው ነው እንጂ ማለት መንግስት ጥሩም ነገር ለሙስሊም ኖሮት ደለም ከእዚህ በፊትም ኖሮት አይደለም አሁንም ቢሆን ያው ሙስሊሙ አንድ ያው እንግዲህ አንድነት ኖሮት እንዳይኖር ነው ይሄን የተደረገው ንን ማን ነው ያለው ?

ዐዲን ጀባል

ይድገሙት ዝርዝር አድርገው ?

ያው ሕዝቡን ያው ሕዝቡን የሚያለቅስበት ምክንያት ያው ሙስሊሙን ያው እንዳይሆን

ው አንድ እንዳይሆን ያደርጋል የሚሉ ?

1334

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መንግስት ያው ገብቲል በሙስሊሙ ገብቶበታል ስለገባ ያው የገባ ምክንያት ምንድን ነው ያው አልአባሽ የሚባል ኃይማኖት ስለመጣ ያው ይሄንን አስተምሮት ያው በሚል ነውያው
- ይሄ አልአባሽ የሚባለው ማን አመጣባችሁ ነው የሚለው ?
- ያው መንግስት ከመጅሊስ ጋር ተያይዞ
- ማን ነው የሚለው ይሄንን ?
- አህመዲን ጀባል
- ቅድም ስለ ጭቆና ስለበደል አውርተዋል ይሄንንስ ማን ነው ያለው ?
- ያው ይሄንን አህመዲን ጀባል ነው
- ምንድን ነው ያለው ?
- ያው መአት ሙስሊሙ ያው /ግልፅ ያልሆነ/ አንድ እንዳይሆን ያው ያደረገው ያው መንግስት ነው
- ሌላስ በወቅቱ የነበረ ሰው ነበር እንዴ ?
- አካባቢው ላይ
- አይ ተከሣሾች ውስጥ አሁን ያሲን ኑሩ ብለዋል አህመዲን ጀባል ብለዋል ሌላ ሰው ነበረ ?
- አቡበክር አህመድም ነበረ
- ምንን ነበር /ግልፅ ያልሆነ/
- ስሙን ሲያስተዋውቅ የነበረ ነው
- ስሙን አስተዋውቆ ምን አለ ?
- ያው አሁን ያለው መንግስት አያዘንም
- አይገዛንም አያዘንም ?
- አያዘንም አልሀባሽ የሚባለው ያው ኃይማኖት መጥቷል አንቀበልም ደግሞ ያው የራሳችን መንግስት እናቆማለን የእስላም መንግስት እናቆማለን
- እስቲ የራሳችንን የምን መንግስት ነው እናቆማለን ያሉት ?
- የእስላም መንግስት
- ሌላስ በወቅቱ ሌላ ተከሣሽ ነበር ?

1335

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ካሚል ሸምሱ ነበረ
- ምን ይል ነበር አቶ ካሚል ?
- ካሚል ሸምሱም ያው አሁን ያለው መንግስት አያዘንም አልሀባሽ የሚባል ኃይማኖት መጥቷል አንቀበልም የራሳችን ደግሞ የእስላም መንግስት እናቆማለን
- የት ቦታ ነው ይሄንን የሚሉት ?
- አንዋር መስኪድ ላይ
- የት ነው የሚገኘው አንዋር መስኪድ ?
- ወረዳ 4ኛ ላይ
- ይሄንን ያሉት እነዚህ 4ቱ ተከሣሾች በተለያየ ቀን ነው ወይስ በአንድ ቀን ነው ?
- ያው 3ቱም ቀን ሆኖ ያው 3ቱም ቀን ያው የተለያዩ በ 3 ቀን 3 ቀን ውስጥ ነው የተካሄደው ያው
- ምኑ ጋር ሆነው ነበር ይሄንን ሲሉ የነበሩት ?
- እዚያ መንበሩ ጋር /ግልፅ ያልሆነ/
- ስንት ቀን ነው ያዩዋቸው እኚህን ተከሣሾች ?
- እኔ አንድ ቀን ብቻ 2 ቀን ብቻ ነው ያየዋቸው አንድ ቀን ሁለት ቀን
- በእዚህ ግርግር ነው እንጂ ከእዚያ የቆየ እውቅና አላችሁ ?
- የለንም
- የቆየ እውቅና የላችሁም ?
- አዎ
- እሺ ሌላስ ምን ተፈጠረ በአካባቢው ከእዚህ ጋር ተያይዞ ?
- በአካባቢው ያው ሴቶች ኩሊስ ምናምን ውኃ ይዘው እየመጡ ነበር ያኔ ሴቶች ያው ፖሊሶችም እንግዲህ ያው ወደ 4ኛ ይዘዋቸው ሄደዋል እና እነኚህም ሴቶች ይፈቱልን ያው ብሎ ያው ጠይቋል
- ማን ነው ይፈቱልን የሚለው ?
- ያው ያሲን ኑሩ ነው
- እሺ ሌላስ ?
- ሌላ ደግሞ ያው ሌላ በቃ ያው 2 ሰዓት ተኩል ጀመሩ ያው 7 ሰዓት ነው ያበቃው

1336

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በእዚያን ቀን ?
- አዎ
- እንዴት ነበር ይሄ እነዚህ ይሄ ጥያቄ እዚያ መድረክ ላይ ብቻ ነው ሲቀርብ የነበረው?
- ያው በጣም ይጮሀላ እስፒከሩ በጣም ይጮሀል በጣም ስለሚጮህ ያው ለሁሉም ሰው አይደለም ለመስኪድ ሰው አይደለም ለውጪም ሰው ይሰማል
- መቼ ነበር የጀመረው ይሄ ጥያቄ ?
- ጁማ ነዋ
- በየትኛ ጁማ ማለት ?
- ያው ሐምሌ ላይ ነዋ ሐምሌ ያው ቀኑ ሐምሌ 8 ነዋ
- አንድ ጥያቄ ፎአድ ?
- አቤት
- እነዚህ አንዋር መስኪድ አንተ ባየህባቸው /ግልፅ ያልሆነ/ የሚሰበሰቡ ሰዎች ከአዲስ አበባ ብቻ ነው እንዴ የሚመጡት ?
- ከተለያየ ሀገር ነው
- ከተለያየ ሀገር ማለት ከውጪ ሀገር ነው ?
- ከውጪ ሳይሆን ጅማ ሻሸመኔ ሌላም ሀገሮች ያው እንዲመጡ አድርጎ ነበር ማን ያው
- ጅማ ሻሸመኔ እነዚህን ሰዎች የሚጠራው ማን ነው ?
- ማን ነው ያው ይሄንን የሚያንቀሳቅስ ኃይል ነዋ
- እኮ እነ ማን ናቸው ?
- እነ ያሲን ኑሩ
- ስም አላቸው ምንድን ነው ስም አላቸው ?
- ያሲን ኑሩ
- አይደለም የግለሰብ ስም ሳይሆን
- የመጡ ሰዎች እሱ ስማቸው የለኝም
- አይደለም የመጡት ሰዎች አይደለም የሚያንቀሳቅስ ኃይል አሰይብለሀል ቅድም ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የሚያንቀሳቅስ
- ኃይል አለ ብለሀል ?
- ተቃውሞ አለኝ
- ተቃውሞ ምንድን ነው ?
- ሰም አለው የለውም እነ ማን ናቸው በምንድን ናቸው እያሉ ያለ አግባብ ነው እየተጠየቁ ያለው ሰው ይመጣል ወይ ብለዋል ይሄም መርተው ከየትኛው ሀገር ከክፍለ ሀገር ብለው ነው ገልፀው የጠየቁት እሱ አለፍነው እሱን አሁንም ደግሞ ምንድን ናቸው እነዚህ ማለት እንትኑን ነው ያለ አግባብ ነው መርተው እየጠየቁ ያሉት ዐቃቤ ሕግ ስለዚህ ይሄ ጥያቄ ሊታለፍ ይገባዋል
- ዐቃቤ ሕግ ላቀረበው መቃወሚያ ምላሽ
- የተከበረው ፍ/ቤት አልመራንም የመራነው ነገር ስላልተነገረን በተከበሩ ጠበቃ ምን ብለን እንመልስ
- አሁን በተነሳው ላይ
- አልመራንም ያው ምስክሩ
- የቀረበ ታሳብ አለ ?
- የጠየቅናቸው ሰው ከየት ከየት ሀገር ይመጣሉ ከጅማ ከሆሳና ምናምን አሉ እንግዲህ ሌላ የመራነው ነገር የለም የተከበረው ፍ/ቤት
- ብይን ተሰጥቶበታል ትዕዛዝ ተሰጥቷል ለመቃወሚያው መነሻ የሆነው ነጥብ እንግዲህ ምስክሩ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ ቆይተው አንዋር መስኪድ ያሉት ሰዎች ከየት ከየት ቦታ ወይም አካባቢ የተሰባሰቡ ናቸው የሚል ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥቷል ከእዚያ በኋላ ነው እንግዲህ መሠረት አድርጎ ሰዎቹስ እነ ማን ነበሩ የሚልም ጥያቄ ቦታዎቹንም ጭምር ዐቃቤ ሕግ እየጠየቁ ያለው ስለዚህ ይሄንን መሠረት አድርገው መልስ ስጡ በሚባልበት ሰዓት የትኛውን ጥያቄ እንደመራን አልተነገረንም ያሉትም በእዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል እና አንዋር መስኪደ ያሉ ሰዎች ከተለያዩ ቦታዎች ናቸው የተሰባሰቡት ስንሰማው ጥያቄ በኋላ ከየት ከየት ነው የተሰባሰቡት የሚለው መልስ ነው እነ ማን ናቸው እንደተሰባሰቡት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚታወቅ ከሆነ /ግልፅ ያልሆነ/ የቀረበው ጥያቄ የመምራት ጥያቄ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ አልወሰደውም ስለዚህ ከእዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥያቄዎች ካሉ ይቀጥሉ

- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር አሁን እርሶ ከጠቀሷቸው ክፍለ ሀገሮች እና ከአዲስ አበባም ጭምር ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር ብለዋል አንዋር መስኪድ አይደለም ?
- አዎ
- እነዚህ ሰዎች ከተለያየ ቦታ የሚጠራው ማን ነው ?
- ያው እነኚህ 4ቱም ያው ከ 17ቱ ሰዎች ያው እነኚህ 4ቱ ሰዎች
- ምንድን ናቸው 17ቱ ሰዎች ?
- እንግዲህ የሙስሊሙ ሕብረሰቡን ያው ያለውን ነገር ያው ማስጨረስ ማለት ነው
- እኮ ምንድን ናቸው ምንድን ነን ይላሉ ?
- ያው ተወክለናል ነዋ
- ተወክለናል ?
- ላለው ነገር ሁሉ ያው ከመንግስት ጋር መነጋገር ማለት ነው
- ዋና ጥያቄ አበቃሁ የተከበረው ፍ/ቤት
- ዋኔ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቡ ?
- ምስክር በአንዋር መስኪድ የተሰበሰቡት ሰዎች ከተለያየ ክፍለ ሀገር እንደመጡ ተናግረዋል ?
- አዎ
- ይዜንን በምን አወቁ ?
- በምን አወቁ
- ሕዝቡ ነው እዚያ የሚመጣው ?
- ሰው የተሰባሰበው ሰው ከተለያየ ክፍለ ሀገር መሆኑን እርሶ በምን አወቁ ?
- በምን አወቁ ያው እንግዲህ እዚያው ላለው ሙስሊሙ ያው ይነጋገራል የሕዝቡ ጭማሪ እንዴት ፈሰመረ አዳዲስ ሰዎችም ያው ለዚያ ቦታ ላይ ይገኛሉ አንግዲህ ያው ከየት መጣ ወዴት ነው እንዴት ነው ያው ተብሎ ሲባል ያው ከእዚህ ከእዚህ ለእዚህ ጉዳይ ነው የመጣሁት ብሎ ያው ሲናገር ነው የሰማሁት

1359

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያ የነበረው ሰው በሙሉ እንደዚህ ሁሉም ዞረው አይተዋል ?
- የተወሰነ እዚያ የተወሰነ /ግልፅ ያልሆነ/ አካባቢ ያው ጠይቄአለሁ እኛ ከእንደዚህ ነው ከእንደዚህ ነው ብሎ ያው ነገሩን
- አውቶቢስ ተራ ሄደህ አላየህም ?
- አልሄድኩም እዚያው አንዋር ነው
- እርሶ አንዋር በእዚያን አሁን ሲናገሩ ሰማሁ ተከሣሾቹ ባሉበት ጊዜ የት ጋር ነበር የነበሩት?
- እኔ እዚያ አስተዳደሩ ቢሮ ጋር
- ቢሮ ውስጥ ነው ?
- አይ በር ላይ በር
- በር ላይ ?
- አዎ
- ተከሣሾቹ የት ሆነው ነበር የሚናገሩት ?
- ውስጥ
- የት ውስጥ ?
- አንዋር መስኪድ ውስጥ
- መስኪድ ውስጥ ?
- መስኪድ ውስጥ
- ስለዚህ ሲናገሩ ሰሙ እንጂ አላዩዋቸውም አይደል ?
- አላየዋቸውም
- ጥሩ የተከሣሾች ንግግር መሆኑን በምንድን ነውያወቁት እርሶ ሲናገሩ አላዩም ሰሙ እንጂ ?
- አዎ
- ተከሣሾች
- ስሙን እያስተዋወቀ ነዋ
- ስሙን ስላስተዋወቀ ነው ?
- አዎ እያስተዋወቀ በእዚያ ንግግር ይቀጥላል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስሙን እያስተዋወቀ ስለተናገረ ተናጋሪው ስሙን የተናገረው ነው በሚል ነው አይደል እርሶ የሚያውቁት ?
- በሚል ሳይሆን ያው እከሌ የሚባል ሰውዬ እንግዲህ ያሲን ኑሩ ይሸው እኔ ጨርሻለሁ ለአህመዲን ጀባል ያው ሰጠሁት ብሎ ያው እንደዚያ እያለ ለአቡበከር አህመድ ከእዚያ ያው እያለ
- እንደዚያ ብሎ ሲናገር እራሱ ከአስፒከሩ ላይ የሚሰሙት ድምፅ ያሲን ኑሩ ጨርሻለሁ አህመድ ጀባል ሲል ከእዚያ ተነስተው ነው አህመዲን ጀባል ነው ያሲን ኑሩ ያሉን አይደል ?
- አዎ
- ጥሩ እርሶ እነ አህመዲንን እነዚህ ተከሣሾችን አንድ ቀን ብቻ ነው ያዩዋቸው ?
- አዎ
- አይደል ?
- አዎ
- ከእዚያ በፊት አይተዋቸው አያውቁም ?
- አላውቃቸውም
- ጥሩ በእዚያን ዕለት እርሶ በሰሙበት ቀን አንዋር መስኪድ ሕዝብ ብዙ ነበር ወይስ ትንሽ ነበር እንዴት ነው ?
- እስከ ውጪ ድረስ ነው
- ሞልቷል ?
- አዎ እኛ ስለዚህ እንደውም ምን ብለው አስተላልፈዋል እኛ እኮ የምናስተላልፈው አሉ መሣሪያም አይደለም ምንም የአላህ ንግግር ነው እና እንደውም ፍተሻ ባይኖር እና መንገዱን ብትለቁልን ምናምን ብሎ ያው እያሉ ነበር /ግልፅ ያልሆነ/ ማለት ከውስጥ ከውጪ ያው ይመጡ ና ውጪ እንደዚህ ፖሊስ መንገድ ተዘግቷል መኪና ተዘጋግቷል ብለው /ግልፅ ያልሆነ/ ገብተው ያው ተናጋሪዎች ሲናገሩ እሱ ደግሞ ወደ ውጪ ሆኖ ያው
- ስለዚህ መስኪዱ ሞልቶ ግቢው ሞልቶ ወደ ውጪ ፊሶ ነበር ሞልቶ ነበር ?
- አዎ

1341

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ያዩዋቸው አንድ ቀን ነው የሰሙትም ድምፅ ነው ተከሣሾቹ በዕለቱ ቀርበው ይነጋገሩ ወይም የእነሱ ድምፅ ተቁርፆ ብማይክራፎን ይገለፅ ይሄንን እንዴት እርግጠኛ መሆን ይችላሉ ?
- ማን ነው የሚቀርፀው
- እዚያ የሚያስተላለፈው መድረኩ ላይ የማያስተላልፉ ሰዎች በያሉን ኑሩ ወይም በሌሎች የተነገረውን መድረክ ላይ ሊያስተላልፍ አይችሉም እንዴ እነሱ በሌላ ቀን የተናገሩት በእዚያን ቀን እስሌ እየተናገረ ነው ለምሳሌ ቡቲፕ የተቀረፀ በሲዲ የተቀረፀ መድረክ ላይ ሊተላለፍ አይችልም እንዴ ?
- አይችልም እሱ እራሱ የቻለው ነዋ ይሄ መድረክ ነዋ እነዚህ የተመረጡ ሰዎች አሉ ያ የተመረጡ ሰዎች ተቀባብለው ማይክራፎን ተቀባብለው ያላቸውን መልዕክት ማስተላለፍ እንጂ በሲዲ ተቀዳ /ግልፅ ያልሆነ/ ተቀዳ በምናምን በሚሞሪ ተጭኖ ይሄ አይሆንም
- ጥሩ 4ቱም ተከሣሾች ተመሳሳይ ነገር እንደተናገሩ ነው የመሰከሩት አይደል?
- አዎ
- 4ቱም ተከሣሾች በቅደም ተከተል ነው የኮነጉት ?
- አዎ
- ማን ነው መጀመሪያ የተናገረው ?
- ያሲን ኑሩ
- ቀጥሎ ?
- አህመዲ ጀባል
- ቀጥሎ ?
- አቡበክር አህመድ
- ቀጥሎ ?
- ካሚል ሸምሱ
- በቃ አሁን የተባሉትን ነገሮች ብቻ ተናግረው ነው የተቀመጡት ?
- እንግዲህ አሁን እናውራ ካልን ያው ብዙ አለ
- ሌላ ነገር ተናግረዋል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ሰዓት ካለ
- ለምሳሌ ሕዝቡ ሰላማዊ እንዳይረብሽ ማስጠንቀቂያ የሰጡበት የለም-በንግግራቸው መሀል ብዙ ነገር ተናግረዋል ብለዋል ?
- አዎ
- ከእዚያ ውስጥ ሕዝቡ እንዳይረብሽ ረጋ እንዲል በሰላማዊ መንገድ እንዲጠይቅ አልተናገሩም ?
- አልተናገሩም እዚያ ጋር ምን እንዴት አድርጎ ሰላማዊ ነው ተሰብስበው ለሰላም አይደለማ
- አልተናገሩም ?
- አዎ
- ጥሩ እነሱ ሲናገሩ እዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ በሞባይሉ በሌላ ነገር አይቀርፅም ነበር እንዴ አይቀርፅም ነበር የሚናገሩት ?
- እሱን እኔ አላየሁም
- አላዩም ?
- አዎ
- ከውጪ ሆነው አስተዳደር ቢሮ ቁጭ ብለው እያዳመጡ ነበር ?
- አዎ
- ሲቀረፅ ድምፅ ሲቀረፅ አላዩም ?
- አዎ አላየሁም
- ቅድም በተባለው መሠረት የተለዩ የተለዩ እንትኖች ላይ ብቻ ቅድም ተደጋግሞ በመቅረቡ ምክንያት ነው ማሳሰቢያ የተሰጠው እና ያልተነሱ ነጥቦች ላይ
- አቶ ፎአድ ?
- አቤት
- እነዚህን
- ሰዎች የማውቃቸው አንዋር ሲያስተምሩ ነው ብለው ነበር ?
- አዎ
- አሁን ደግሞ ሲናገሩ አየዋቸው ብለዋል ያየዋቸው አንድ ጊዜ ነው ብለዋል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አም
- ስለዚህ እንዴት ነው ይሄንን ነገር የሚያደርጉት ያስተማሩትም የተናገሩትም በአንድ ቀን ነው ?
- የተናገሩትም አም በቃ በእዚያ በሕዝብ መሀል
- ምን እያሉ ነበር የሚያስተምሩት ሲያስተምሩ ኣውቃቸዋለሁ ብለዋል ቅዮም መግቢያው ላይ ስለዚህ ምን እያሉ ነበር የኃይማኖት ትምህርት የሚያስተምሩት?
- የኃይማኖት
- ትምህርት የሚያተምሩት ?
- የኃይማኖት ትምህርት እኮ አይደለም እዚህ ጋር የሚያስተምሩት የኃይማኖት እኮ ይሄ አሁን ያለው መንግስት እኮ አያዘንም ማለት እኮ ኃይማኖት እኮ አይደለም
- ቅድም ያሉት ይሄን የተናገሩት ሐምሌ 8 ነው ከእዚያ በኋላ ብለው ነበር መጀመሪያ ግን የማውቃቸው እነዚህን ሰዎች ሲያስተምሩ ነው ብለዋል ስለዚህ ምን እያሉ ነበር ከእዚህ ቀን በፊት የሚያስተምሩት ነው ምን እያሉ ነበር የሚያስተምሩት ከእዚህ ቀን በፊት ?
- ማለት ከእዚህ ከፕሮግራሙ ውጪ ሌላ ?
- እንግዲህ ከሕብረተሰቡ ጋር ያው አንድ ሆኖ ያው ተቻችሎ አለመኖር
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የተከበረው ፍ/ቤት ገና ችሎቱ ሲጀምር የት አወቃችሁ ተብሎ ከችሎት ሲጠየቅ የማውቃቸው አስተማሪዎች ናቸው ሲያስተምሩ አውቃለሁ ብለው ነበር እና ይሄንን ነገር እንዲያብራሩልኝ ነበር የፈለኩት ያ ተናገሩ ያሉት ቀን ሌላ ሆኖ ማለት ነው
- ምናልባት /ግልፅ ያልሆነ/ የሆነ አንድ ቀን ሲያስተምሩ የእዚያን ቀን አይቼአለሁ /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚያ በፊት /ግልፅ ያልሆነ/ ጥያቄው እየገባን /ግልፅ ያልሆነ/
- ሌላ ጥያቄ ልቀጥል ሰደቃ ተደረገ ብለው ነበር ሰደቃውን ማን እንዳደረገ ያውቃሉ ?
- የትኛው ሰደቃ
- ሰደቃ ተደረገ አሉ ብለዋል ?
- አድርገዋል አም
- ማን ነው ያደረገው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ከ 17 ሰዎች ማን እንደሆነ እኔ አላውቅም
- 17 ሰዎች መሆናቸውን በምን አወቁ ?
- እኔ አይደለም ማንም ሕዝብ ያውቃቸው /ግልፅ ያልሆነ/ ሰ
- አይ እርሶ በምን አወቁ ?
- እኔ አይደለም እኮ ሕዝብም ያውቃቸዋል እኮ
- እኔ የጠየኩት ሕዝብ ማወቅ አለማወቁን ሳይሆን 17ቱ ሰዎች ይሄንን ሰደቃ ስለማድረጋቸው እርሶ በምን አወቁ ?
- እንግዲህ ያው ከሕዝብም ያው ሕዝብም ያው በሕዝብ አውቋቸዋል እኔም ያው በስም ዝርዝር በምናምን አውቄአለሁ
- ስለዚህ ከሰው ሰምተው እንጂ በራስዎ ሰደቃ ሲያደርጉ ያዩት ነገር የለም ሰደቃ ሲያደርጉ ያዩት ነገር የለም ከሰው ሰምተው ነው ?
- እንዴት ሰደቃ ሁሉም ተካፍዬአለሁ ግን /ግልፅ ያልሆነ/ ሰደቃውን ተካፍዬአለሁ
- የት ነበር ሰደቃው የተደረገው ?
- ቂራ መስኪድ
- ማን አደረገ ሰደቃውን ?
- ማን አደረገ ያው ይሄኛው ኃይል ነዋ
- በምን አወቁ ?
- እንዴት በምን አወቁ ያው ሙስሊሙ እኛ ተወክለናል ብሎ ያው ይሄንን ጉዳይ
- ይኸውሎት ምስክር አሁን ምንድን ነው የሚያደርጉት በእርግጥ ፍ/ቤት ቀርበው ላያውቁ ይችላሉ እና /ግልፅ ያልሆነ/ የሚለውን ይተው እና የተጠየቀችውን መልስ ብቻ ተካፍለው ከሆነ አዎ ተካፍዬአለሁ ያደረገው ማን ነው የሚያውቁት ከሆነ እኮሌ የማያውቁት ከሆነ ደግሞ /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም ሕዝቡ ያለቅስ ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- በእዚህ ቀን ሁሉም ሕዝብ ነበር የሚያለቅሰው በምን ምክንያት ነበር የሚያለቅሰው ?
- የሚያለቅሰው እንደተጨቆነ ነዋ ያው
- ስለተጨቆነ ነው ያለቀሰው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ቅድም በተከበረው ዐቃቤ ሕግ ሲጠየቁ በእዚህ ፕሮግራም ከተሰያየ ክፍለ ሀገር ከጅማ ከሻሸመኔ ሰዎች መጥተው ነበር የጠራው ይሄ የተከሣሾች ናቸው ብለው ነበር ይሄንንስ በምን አወቁ ተከሣሾች ስለመጥራታቸው ተከሣሾች ይሄንን ስለመጥራታቸው በምን አወቁ ?
- በምን አወቁ እንግዲህ ያንን ሰውዬ እንግዲህ ይሄንን ፕሮግራም ያዘጋጀውስ ማን ነው የጠራው ማን ነው
- እነ ማን ናቸው እንዴት አወቁ ?
- እዚያው ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ሰዎች ናቸዋ እንግዲህ እዚያ ቦታ ላይ የሚያስተላልፉ የነበሩት ሰዎች
- ሰምተው ነው ወይስ ተናግረው ነው እንዴት አወቁ አሁን እየተጠየቁ ያሉት እንዴት አወቁ ይሄ መሆኑን ?
- ይሄንን ፕሮግራም ተጋብዘን ነው በስልክ ተጠርተን በመሴጅም በፊስ ቡክም ተጠርተን ነው የመጣነው ይሄንን ፕሮግራም ልንካፈል
- ለእርሰም ደርሶት ነው ለእርሶ ጭምር ነው ?
- እዚያው ሕዝብ እኔ እዚያው
- ስለዚህ ከሰው ነው የሰሙት ?
- አዎ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ፎአድ ሕዝብ ሲያለቅስ እርሶም አልቅሰው ነበር እንዴ አብረው ሕዝቡ ሲያለቅስ እርሶም አብረው አልቅሰው ነበር ?
- ምን ሆኜ የማለቅሰው
- መቃወሚያ አለ የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ መቃወሚያ አቅርቡ
- ይሄ በጣም ፐርሰናል ጥያቄ ነው በፍፁም ሊጠየቅ የሚገባ አይደለም ስለምስክሩ ሚልቀስ ጠበቃውም የሚተውት ይመስለኛል ጥያቄውን እንግዲህ እኛ ተቃውሞ ይሄ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄ ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም

1346

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልፈነዋል
- አስተካክላችሁ ጠይቁ
- ሕዝብ ሲያለቅስ ነበር ብለዋል አቶ ፎአድ ስሜቱ ተነክቶ ነበር ሲያለቅስ የነበረው?
- ያው ስሜቱ እንደተነካ ነገር ነው
- በምንድን ነው ስሜቱ ተነክቶ የነበረው ?
- ስሜቱ እንግዲህ ያው የተለያየ ዓይነት ብሶት ያለበት /ግልፅ ያልሆነ/
- እስቲ ምን ምን ብሶት እስቲ ፍ/ቤቱ እንዲረዳ ምን ምን ብሶት አለበት ?
- እንግዲህ ያው
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ እንቃወማለን ከእዚህ በፊት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እናመሰግናለን ተቃውሞአችን ለምንድን ሕዝቡ ለምንድን ነው የሚያለቅሰው የሚለው ጥያቄ ተጠይቆ መልስ ሰጥተውበታል ስለዚህ ተደጋግሞ መጠየቁ ያለአግባብ ነው ስለሆነም ጥያቄው ሌላ ጥያቄ እንዲያቀርቡ
- መልስ ስጡበት
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ያው ፍ/ቤቱም ሁላችን እንደምንረዳው ከእዚህ ጥያቄ ነጥሮ የሚወጣ ጉዳይ ነው እና ያንን የተከበረው ፍ/ቤት እንዲረዳልን ነው ይሄንን ጥያቄ የምንጠይቀው እኛ እንድናስረዳ አታብራሩ ተብለናል ስለዚህ ምስክሩ እንዲያብራራ ነው እየጠየቅን ያለነው ከእኔ በፊት በጠየቁ ባልደረቦቼ ቢጠየቅም ነጥሮ አልወጣም ፍ/ቤቱ ይረዳል ለፍትህ ሲባል መጠየቅ አለበት ነው
- ከእርሶ በፊት ቀደም ብለው የነበሩ ባለሙያ ይሄንን ጥያቄ አቅርበው ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል በምን ምክንያት ነበር ሕዝቡ ሲያለቅስ የነበረው ተብሎ በዝርዝር ምስክሩ መልስ ሰጥቷል ስለዚህ እሱን ነው አሁን ደግሞ ጥያቄው እየቀረበ ያለው በምን ምክንያት ነው ሰው ስሜቱ ተነክቶ ነው ብለዋል እሳቸው በዝርዝር ቅድም አስረድተዋል ስለዚህ እሱን ደግሞ መጠየቁ አግባብ ሆኖ አልተገኘም ምናልባት ከእዚያ ጋር አያይዛችሁ መጠየቅ የምትፈልጉት ጥያቄ ካለ ጥያቄው /ግልፅ ያልሆነ/
- ሕዝቡ ቅር የተሰኘበት ነገር ነበር አቶ ፎአድ ?
- ማለት

1347

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሕዝቡ ቅር የተሰኘበት ነገር ነበር እዚያ አንዋር መሸኪድ እንዲሰበሰብ ያደረገው ቅር የተሰኘበት ነገር ነበር ?
- ያው ለመሰብሰቡ እኮ የፈለገም አለ ያው ያልፈለገም አለ
- አይ ቅር የተሰኘበት ነገር ነበር ሕዝቡ በእርሶ እይታ አንዳንድ ሰዎችንም አናግራአለሁ ከክፍለ ሀገር የመጡትን ስላሉ እዚያ እንዲሰበሰብ ያደረገው ቅር የተሰኘበት ነገር የሆነ ስሜቱን የነካ ነገር ነበር ?
- ያው ግማሹ ያው መሰብሰቡ አላስፈላጊ ያው መሆኑን የተረዳ ሰው አለ
- አይ አሁን አስፈላጊነቱ ላይ ሳይሆን
- እየመለሱ እኮ ነው እየመለሱ ስለሆነ ይጨርሱ /ግልፅ ያልሆነ/
- እዚያ ቦታ ላይ መሰብሰብ ያው የማይፈልግም ሰው አለ ምክንያቱም እዚያ ቦታ ላይ ያው ጥሩ ነገር ያው ማለት አለ የሚል ሰው /ግልፅ ያልሆነ/ ግን እዚያ ቦታ ላይ ምን ጥሩ ነገር አለ /ግልፅ ያልሆነ/ ሰው የለም ምክንያቱም የሀገርም ሰላም የሕዝብም ሰላም አይደለም እዚያ ቦታ ላይ መሰብሰቡ ግን ያው እዚያ ቦታ ላይ መሰብሰቡ ያው በአጠቃላይ ያው ሰው ያው የተገነዘበውም አለ ያልተገነዘበውም አለ በቃ
- አቶ ፎአድ ሕዝቡ እዚያ ቦታ ላይ በፍላጎት ነው አይደል የተሰበሰበው ያስገደደው የለም ?
- በፍላጎት ያው እንግዲህ ዲን ተነክቶብኛል ብሎ ነውያው
- ዲኑን ማን ነካው ?
- ማን ነካው አልሀባሽ የሚባል መጥቷል
- አይ አሁን ዲኑ ተነካብኝ ብሎ ነው እዚያ የተሰበሰበው ብለዋል ከእዚያ በፊት ዲኑን የነካው ወይም ዲኑ ላይ ችግር የፈጠረ ነበር እንዴ ?
- አዎ
- ማን ነው ዲኑ ላይ ችግር ፈጠረ የሚሉት ?
- እንግዲህ ያው ዲባ ይቻላል ወለድ ይቻላል ዚና ይቻላል እና ሴት ልጅ ሱሪ አድርጋ /ግልፅ ያልሆነ/ ትችላለች ይሄንን ሁሉ ለሕዝቡ ተላልፎለታል ከእዚያ በኋላ ደግሞ ሕዝቡ ደግሞ ዲን ተነክቷል ብሎ ዲን መቼም አይነካም ግን ዲን ተነክቶብኛል ብሎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ኃይማኖት /ግልፅ ያልሆነ/ ብሎ ነው ለእዚያ ነገር ያው ወደ አንድ አቅጣጫ ለማስተካከል የተሰበሰቡ ግን ያው መሰብሰቡ ያው ማንም ማንም ሆነ ጥሩ ነገር እንዳልሆነ ማንም ያውቀዋል ከጀርባው ችግር ስላለ ያው

- 2 ቀን ብቻ ነበረ የነበሩት ?
- 2 ቀን
- 2 ቀን ነው ፕሮግራሙን የተሳተፉት አይደል ?
- ጁማም ቅዳሜም እሁድም
- ቅድም 2 ቀን ነበር የነበሩት ?
- ጁማአም ቅዳሜም እሁድም
- 3 ቀን ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- አዎ
- እነሱ የመጀመሪያው ቀን ላይ ነው የተናገሩት አሁን የተከሰሱት ሰዎች 4ቱ የጠቀሷቸው ሰዎች የመጀመሪያው ቀን ላይ ነው የተናገሩት ?
- 3ቱም ቀን /ግልፅ ያልሆነ/
- አንዋር መስኪድ ግብጦ ነበረ የሚል ነገር ተናግረዋል ግብጦ ነበር እንዴ ?
- ያው ግለሰቡን ያው ኩሊስ ውኃ ምናምን ይዘው እየገባ ነበር
- እንጂ ከእዚህ ውጪ ሌላ ምንም ዓይነት እንትን አልነበረም ?
- እሱ እንዳይደረግም መንግስትም ከልክሏል
- በምን ምክንያት ነው መንግስት የከለከለው ቅድም ሰደቃውን መንግስት አስቆመው አሉ ?
- ትላንት ሰደቃ አይቻልም ስለሚባል ነዋ ሰደቃ አይቻልም ሰደቃ የሚባል ነገር የለም ቢዳአ ነው ብሎ ያው የረጅም ዓመት ያው ተላልፎ ነበር ስለሆነም እዚያ ላይ ደግሞ አዲስ ሰደቃ ትላንት የለም ሲል ነበር ዛሬ ደግሞ ምን ማለት ነው የሙስሊም አንድነት ድሮም አንድ ነው አዎ
- ስለዚህ መንግስት ትላንት ያልነበረ ሰደቃ አሁን ልታመጣው አይገባም ትላንት ያልነበረ ሰደቃ ዛሬ
- ሰደቃ ትላትም ነበረ ምን ጊዜም ነበረ ሰደቃ ምን ጊዜም ያለ ነው ሰደቃ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አይ አሁን ከተናገሩት ነገር አንፃር
ምን ተናግሬአለሁ ምንድን ነው በየመስኪዱ
እያደመጡ ጥያቄውን /ግልፅ ያልሆነ/
በየመስኪዱ ያው እንግዲህ በየመስኪድ እንግዲህ መስኪድ በተባለው ቦታ ሰደቃ /ግልፅ ያልሆነ/ የለም ይሄ ምንድን ነው ያው ስንፀ ኃሳቡ ያው የሙስሊሙን ያው ልብ ለመያዝ ነው ያው እንግደህ ያው ኃይል ያው ኃይል ለመፍጠር ነው እንግዲህ እነኚህ ሰዎች ጥሩ ናቸው እንግዲህ እነኚህ ሰዎች እንደዚህ ጥሩ ነገር እየሰሩ እንዴት ለመሆኑ መጥፎ ነው ብለው መንግስት እንደዚህ ነፃነት ብሎ ሊል ይችላል ሰደቃ መቼም ሰደቃ መቼም /ግልፅ ያልሆነ/

- የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ለጠበቆችም ለዐቃቤ ሕጎችም ሲያስረዳን እንደነበረው ምስክርን ምን እንዲመልሱልን እንደምንፈልግ እንዲጠየቅልን ለፍ/ቤቱ /ግልፅ ያልሆነ/ መስቀለኛ ጥያቄ አጭር መልስ ነው የሚፈልገው እና የጠየቅናቸው ማብራሪያ አይደለም ለጥያቄአችን አጭር መልስ እንዲሰጡልን ፍ/ቤቱ ቢነግርልን እኛ ምስክሩን ከምንናገር ፍ/ቤቱ ስላለን ማለት ነው
- ዘገዩ እንጂ ከመመለሱ በፊት /ግልፅ ያልሆነ/ እኛ የእናንተን መልስ እየመለሱ መስሎን ነው አሁንም ቢሆን ችግር የለውም እናንተም አጭር ጥያቄ ጠይቁ እሳቸውም አጭር መልስ ይመልሳሉ ምስክር አሁን ቅድም እንደነገርኖት የሚጠየቅ አንድ ጥያቄ ነው እሱን ጥያቄ ብቻ መልሰው ሌላውን ማብራሪያ ቅድምም የተደገመ ስለሆነ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሷ ነች የተጠየቀችዋን በደንብ ያዳምጡ እና እሷን ይመልሳሉ
- እሺ
- አሁንም አጭር መልስ ነው የምፈልገው ቅድም ዐቃቤ ሕግ በጠየቆት ጥያቄ ላይ ሲመልሱ ሙስሊሙ እንደፈለገ ይሁን እንጂ ለምን በሙስሊሙ ጉዳይ መንግስት ጣልቃ ይገባል የሚል ከሕዝቡ በኩል ቅሬታ ነበር የሚል ነገር ነበረ ስለዚህ ሕዝቡ በእዚህ ነው ቅር የተሰኘው ማለት ነው ?
- አይደለም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ መቃወሚያ
- ተቃውሞ አለን
- ቀጥሉ
- ያው በተደጋጋሚ እንደተነገረው ይመስለኛል ጥያቄ በዋና ጥያቄ የተነሳ ነው ከቅድም ጀምሮ ብይን ሲሰጥበት የነበረው በዋና ጥያቄ ምስክሩ እንደዚህ የሚል ምላሽ አልሰጡም እና የተከበሩ ጠበቃ የራሳቸውን ድምዳሜ
- ምን የሚል ምላሽ ነው የሰጡት ?
- እንዲህ የሚባል እንዲህ የሚባል ድምዳሜም አልሰጡም ምስክሩ ሕዝቡ አኩሩፏል ሕዝቡ ተከፍቷል አሁን ጠበቃው በጠቀሱት ምክንያት ብሎ አልመሰከሩ ምስክሩ በዋና ጥያቄም አሁንም ኢቭን በመስቀለኛ ጥያቄም
- ስለዚህ በዋና ጥያቄ አልተነሳም ነው ?
- አልተነሳም አዎ አልተነሳም ምስክሩም አላሉም ጭራሽ አላሉም
- ለመመለስ ያህል ከሪከርዱ መስማት እንችላለን ሁላችንም እዚሁ ነው ያለነው እኔም ከፃፍኩለት ላይ ነው
- አመጣጡንም መሠረት አድርጋችሁ ?
- አዎ እኮ ከየትም ያመጣሁት አይደለም የፃፍኩትን ነው
- ይሄ ሊኖር ቢችልም ከምን አንፃር እንዳሉ
- አዎ የፃፍኩት ነው
- እሱንም ግንዛቤ ውስጥ ከታችሁ
- አዎ የፃፍኩትን ነው የተከበረው ፍ/ቤት የጠየኩት የሰማሁትን ነው ያም ሆኖ ዐቃቤ ሕግን ቅር የሚያሰኝ ከሆነ ትተነዋል ጥያቄውን አሁንም ቢሆን ማለት ነው ከእዚያ ውጪ ቄራ መስኪድ ሰደቃ
- የተዋችሁት እንደሆነ ሌላ
- አዎ ወደ ሌላ ጥያቄ እየሄድን ነው የተከበረው ፍ/ቤት ቄራ መስኪድ ሰደቃ ነበር ብለዋል ቄራ መስኪድ ነው አንዋር መስኪድ ነው ሰደቃ የነበረው ?
- ቄራ መስኪድ
- አንዋር አልነበረም ማለት ነው እርሶ ነበሩ ቄራ መስኪድ ?

1251

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ነበርኩኝ አዎ
- መቼ ነው የተደረገው ?
- ቀኑን አላውቀውም
- ምን ቀን ነው ከሰኞ እስከ አርብ ካሉት የትኛው ቀን ?
- ቀኑን አላውቀውም
- ወሩን ያስታውሱታል ?
- አላስታውስም
- ስለዚህ አልተደረገም አልነበረም ማለት ነው አልነበረም ቁራ መስኪድ ማለት ነው ?
- እንዴት እኔ ፕሮግራሙ ለመካፈል ነው እንጂ ቀኑ ሣምንቱ ወሩ /ግልፅ ያልሆነ/ ሰደቃውን ለመካፈል ነው የሄድኩት
- ቁራ መስኪድ ማን ማን ነበር ?
- ማን ነበረ ማን እንደነበረ ያው መልዕክቱ የሚያስተላልፈው ማን እንደሆነ እኔ አላውቀውም ያው እየተቀያየረ ያስተላልፋል /ግልፅ ያልሆነ/
- አመሰግናለሁ
- አቶ ፎአድ ተከሣሾች አልሀባሽን አንቀበልም ሲሉ ሰምቼአለሁ ብለዋል አልሀባሽ የሚባል ነገር አለ ታውቃለህ ?
- የለም አልሀባሽ ማለት የሀበሻ ስም
- አለ ያውቃሉ አያውቁም አልሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አለ የለም ?
- የለም
- ስለዚህ ታዲያ ምኑን ነው አንቀበልም ያሉት ታዲያ አንቀበልም ያሉት ምኑን ነው እርሶ የተረዱት /ግልፅ ያልሆነ/ አልሀባሽ የሚባል እምነት ከሌለ ወይም አስተምሮት ከሌለ እነሱ አንቀበልም ያሉት ታዲያ ምኑን ነው እርሶ የተረዱት ምንድን ነው ?
- እኔ የተረዳሁት እንግዲህ ምርጫ መስኪድ ላይ እንጂ አይሆንም አሉ ምርጫው መስኪድ ላይ እንጂ አይሆንም አሉ ቀበሌ ጨው እና ስኳር ማከፋፈያ ነው እንጂ
- አሁን ጥያቄው ይሄ ከሌለ እንዴት እንዲያ ሊሉ ቻሉ ነው እንዴት አልሀባሽ የሚባል ከሌለ እንዲህ ዓይነት ኃይማኖት ከሌለ እነሱ የሚሉት ይሄ ኃይማኖት እንዲህ መሆን አለበት መግባት የለበትም ምናምን እያሉ ነው አይደል ?

1352

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ስለዚህ ይሄንን ከሌለ ምኑን ነው እንደዚያ እያሉት ያሉት ነው ተከሣሾች ?
- ይሄ አሁን በኃይማኖት ላይ
- ልክ ነው ?
- አዎ ትክክል ነው
- ምንድን ነው ይሄ ምክንያቱም ይሄ ኃይማኖት ከሌለ የሌለን ኃይማኖት ለምንድን ነው ተከሣሾች እንዲህ የሚሉት አልሀባሽ ይጥፋ የሚሉት ወይም ሌላ ነገር የሚሉት ነገር ምን ለማለት ነው ?
- ይሄ አሁን ሌላ ኃይማኖት መጥቶ ሳይሆን ኃይማኖቱ ሽፋን አድርጎ /ግልፅ ያልሆነ/ አልሀባሽ ሌላ ዲን የመጣ ነገር ሌላ ኃይማኖት የመጣ ነገር የለም
- ስለዚህ ፈጥረው ነው ነው ?
- መነገጃ ነው አዎ
- በአንዋር መስኪድ የተካሄደው ፕሮግራም ሐምሌ 8 መሆኑን ገልፀሀል አሁን የቄራው ሰደቃ ፕሮግራም ያማም መቹ ነው ስትባል ቀኑን አላውቀውም የሂድኩት ለእዚያ ነው ብለሀል ስለዚህ ስለሆነ እኔ ቀኑን መጠየቅም ማወቅም አያስፈልገኝም ብለሀል የአንዋር መስኪዱ ሐምሌ 8 መሆኑን በምን ምክንያት ነው አንተ አስታውሰህ የያዝከው የቄራውን ማወቅ ካላስፈለገህ ሰደቃ ስትሄድ የአንዋር መስኪድን ሐምሌ 8 መሆኑን በምንድን ነው ያስታወስከው ?
- ዋና የነገሮች ምንጭ ያው አንዋር መስኪድ ስለሆነ ነዋ
- እኮ አንተ ሐምሌ 8 መሆኑን በምን አስታውሰህ ያዝክ ነው ወይም ማን ነው የነገረህ ወይም አንተ እንዴት ነው ያስታወስከው ?
- እኔ ይገፍዋለሁ
- በምንድን ነው የያዝከው በማስታወሻ ይዘኸው ነበር ?
- እራሴ ይገፍዋለሁ
- በቃልህ ነው የያዝከው ?
- አዎ
- ሐምሌ 8 አርብ ቀን ነው የነበረው ?

ECLN
1353
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ሐምሌ 8 ተጀምሮ እስከ እሁድ ድረስ ቀጥሏል ብለሀል የሐምሌ 8ቱ ፕሮግራም ስንት ሰዓት ላይ አለቀ ?
- 7 ተኩል
- ከእዚያ ሰው ሁሉ ወደ የቤቱ ሄደ ?
- አዎ
- በእዚያ ዕለት ሰው ተሰብስቦ የነበረው ለኃይማኖት ትምህርት እና ለስግድት ነበር አይደል?
- እንዴት
- ጁማ ስለነበር ለበዓል ቀኑ ነው አይደል ምክንያት ነው አይደለም መስኪድ ውስጥ የተገኘው ?
- ጠዋት 2 ሰዓት ተኩል ምን እንትን አለ ምን ሰላት አለ ጠዋት 2 ሰዓት ተኩል
- አንተ ታዲያ እዚያ በእዚያን ሰዓት ጠዋት 2 ሰዓት ተኩል የሄድከው በምን ምክንያት ነው ?
- እኔ መርካቶ ስሄድ ያው ሕዝቡ ያው ተሰብስቦ አይቼ ገብቼአለሁ
- ስራህን ትተህ ገብተህ አይተል ?
- አዎ
- ከጠዋት 2 ተኩል ጀምረህ ?
- እስከ 7 ሰዓት
- እስከ 7 ተኩል ?
- አዎ
- 7 ተኩል ላይ ግን ሲያልቅ ተለያያችሁ ?
- አዎ
- ሁሉም ወደየቤቱ ነው የሄደው ?
- በቃ እኔ ወደ ጉዳዬ ሄጃለሁ
- በነገታው ቅዳሜ ስንት ሰዓት ተጀመረ ?
- 2 ተኩል

1354

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በነጋታው ቅዳሜ ኑ የሚል ጥሪ አልነበረም አይደል በነጋታው ቅዳሜ ጠዋት 2 ሰዓት ተኩል ኑ የሚል ጥሪ አልነበረም አይደል ?
- ለምን የለም
- ነበረ ?
- ሳይኖር ዝም ብሎ ሰው ይመጣል እንዴ
- አይደለም መልሱን ካለ ?
- አለ ነበረ
- ማን ነበር ይሄንን ጥሪ ያደረገው ?
- አላወኩትም
- አንተም በነጋታው የተገኘኸው በእዚሁ ምክንያት ነው አንተም ይሄንን ጥሪ ተከትለህ ነው በነጋታው የተገኘኸው ?
- አዎ
- በነጋታው የነበረው ፕሮግራም ስንት ሰዓት አለ የቅዳሜው ?
- 2 ተኩል 7 ሰዓት
- አሁንም ሰው ወደየቤቱ ሄደ ?
- አዎ
- እሁድም ተመሳሳይ ነው የነበረው ?
- አዎ
- በእነዚህ በ3ቱም ቀን ምንም ረብሻ አልነበረም አይደል 3ቱም ቀኖች አርብ ቅዳሜ እሁድ ?
- እዚያ ቦታ እራሱ እኮ ረብሻ ድንጋይ መወርወር /ግልፅ ያልሆነ/ እራሱ መሰብሰቡ አንድ ረብሻ ነው
- አሁን የጠየኩት ሌላ
- ረብሻ ነበር አልነበረም በእነዚህ ቀኖች ረብሻ ያውቃሉ አይደል ረብሻ ነበር አልነበረም በእነዚህ 3 ቀኖች አሁን በተጠየቁት ?
- ረብሻ ሰው እኮ እንደፈለገ እኮ መንገድም እኮ መሄድ ካላገኘ እኮ ያው እንደረብሻ ነው ሰው መሄድ ሲሄድ ነፃነትን አግኝቶ ካልሄደ ያው ረብሻ እንደረብሻ ነው እኮ

ECLN
1255
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ምንድን ነው ረብሻ የሚሉት ነገር ምንድን ነው ረብሻ ያሉት ነገር ምንድን ነው?
- ረብሻ ያው እዚያ ጋር እዚይ በር ላይ መፈተሽ መስኪድ ላይ በእርግጥ ላይ አይፈተሽም ማንም ገባ ማንም አይፈተሽም ያ ቀን እስክሪቢቶ እንዳይዝ ደብተር እንዳይዝ አሞ ምንም ዓይነት ነገር ቦቃ ያው እዚያ በር ላይ ግማሹ አይኑ ሸፍኗል ምን ብሏል
- ስለዚህ ረብሻ የሚሉት ይሄንን ነው ?
- አሞ
- ቀጥሉ
- ቅድም በእነዚህ ቀኖች መንገዱ ላይ ሰው በጣም በዝቶ ስለነበረ የምንናገረው የአላህ ቃል ነው የሚገባው ሰው ይግባ አትዝጉ ብሎ ተናግሯል ብለሀል ማን ነው ይሄንን የተናገረው በእነዚህ ቀኖች ብዙ ሰው ስለነበረ የምንናገረው የአላህ ቃል ነው ሁሉም ሰው ይግባ አትዝጉ ብሎ ተናገረ ብለሀል ይሄንን ያለው ማን ነው ?
- እዚያው መድረኩ ላይ የሚያስተላልፍ ነዋ
- ማን ነኝ አሁን ቅድም ስማቸውን እየተናገሩ ስለሚናገሩ ሰምቼአለሁ ብለሀል ስሙን ተናግሮ የምንናገረው የአላህ ቃል ነው ያለው ማን ነው ?
- ያሲን ኑሩ
- ሕዝቡ ተሰብስቦ ሲያለቅስ የነበረው ብሶት ስለነበረበት ነው ብለሀል ብሶቱ ምንድን ነው ?
- ብሶት ይሄ መሰብሰብ ሳይሆን ከእዚህ ውጪ ነው
- እኮ ምንድን ነው ብሶቱ አንተ ብሶት ብለህ የተረዳኸው ምንድን ነው ብሶት ብለህ የተረዳኸው ነገር ምንድን ነው ?
- እንግዲህ መንግስት ያው ቤት ያፈርስብናል ቫት አምጥቷል ኪራይ ጨምሯል ይሄ ይሄንን ብሶት
- ሕዝቡ ተክቢራ ተደርጎ ተጠራ ብለህ ነበር ቅድም ተክቢራ ማለት ምን ማለት ነው ?
- ተክቢራ ማለት እኮ ሰላት ደርሷል ተነሱ ማለት ነው
- ማለት ነው ?
- አሞ ሰላት ደርሷል ተነሱ ተብሎ ነው ጥሪ የተደረገለት ለሰው ማለት ነው ?

1756

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ 6 ሰዓት ሰላት አለ እንዴ 6 ሰዓት
- እኮ እንደዚያ ተብሎ ነው ጥሪ የተደረገው ?
- አዎ
- ሰደቃ ሲደረግ ይሄ ተመልሷል ሴቶቹ ኩሊስ ምናምን ይዘው ነበር እና እነሱን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዷቸው ሴቶቹ ይፈቱልን እያለ ሰው ይናገር ነበር ብለሀል መቼ ቀን ነው ይሄንን የተናገረው መቼ ቀን ነው ?
- ቅዳሜ ጠዋት
- ቅዳሜ ጠዋት ሴቶቹ ማን ነው የወሰዳቸው እና ያሰራቸው ሴቶቹን ያሰራቸው ማን ነው ?
- ማን ነው ያሰራቸው መንግስት ነዋ
- እና ታዲያ ተፈቱ ሴቶቹ ይፈቱልን ተብሎ ስለተጠየቀ ተፈቱ ሴቶቹ ?
- ተፈተዋል አዎ
- ቅድም በመልዕክት በኤስአምኤስ ይተላለፍ ነበር ብለሀል በኤስኤምኤስ መልዕክት ይተላለፍ ነበር ብለሀል ኤስኤምኤስ አላልክም ?
- መሴጅ ነው
- መሴጅ ማለት ምን ማለት ነው ?
- መሴጅ ማለት እንደደብዳቤ ነዋ
- እኮ በምን ላይ የሚላክ ነው ?
- በምን ላይ በሞባይል ነዋ
- ሞባይል ላይ ?
- አዎ
- ለአንተ የላከልህ ማን ነው ደርሶሀል አንተ መልዕክት ?
- ደርሶኛል
- ማን ነው የላከልህ ?
- ስም የለውም
- ማን እንደሆነ አይታወቅም ?
- መቼም ስሙ አይገለፅም

ECLN

1357

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የላከልህን ሰው አታውቀውም ?
- አዎ
- ቁጥሩን አይተህ አታውቀውም ?
- አዎ
- ፌስ ቡክ ብለህል ፌስ ቡክ ትጠቀማለህ እንዴ አንተ ?
- አልጠቀምም
- ታዲያ በፌስ ቡክ መተላለፉን በምን አወክ ?
- ሰዎች ይጠቀማሉ ይሄ አይተን ይሄ አይተናል
- እኮ ሰዎች ሲናገሩ ነው የሰማኸው ?
- አይቼአለሁ እኔ እራሴም አይቼአለሁ አሳይተውኛል እኔ ባላውቀውም አሳይተውኛል
- እስቲ ፌስ ቡክ እንዴት ነው እስቲ አስረዳን እስቲ እስቲ ፌስ ቡክ እንዴት ነው አስረዳን እስቲ ምንድን ነውያየኸው ?
- እንዴት
- ፌስ ቡክ ማለት ምንድን ነው እስቲ ያየኸው ምንድን ነው አስረዳን ?
- ፌስ ቡክ ማን ሲጠቀም ነው ያዩት አይቼአለሁ ብለዋል ፌስ ቡክ ማን ሲጠቀም አዩ?
- ጓደኛዬ
- ጓደኛዎ ሲጠቀም ነው ያዩት ?
- አዎ
- ከጓደኛዬ አየሁ ነው የሚሉት
- ፌክ ቡክ ማለት ምንድን ነው እስቲ በትክክል ማየቱን ለማወቅ ?
- መልዕክት ማስተላለፊያ ነው
- እኮ ያየኸውን እዚያ ጓደኛህ ሲጠቀም ያየኸውን ነገር እስቲ አስረዳን ምንድን ነበር ያየኸው ?
- በቃ ሊያስተምረኝ ሞክሮ ነበር መማር አልቻልኩም በቃ አላወኩትም
- እስቲ ይሄ ጥያቄ አሁን እንግዲህ ፌስ ቡክ ሰውዬው ባለው አውቀት መሠረት ጓደኛዬ ሲጠቀም አይቼአለሁ እኔም ተመልክቼአለሁ ብሎ ከመለሰ በኋላ አሁን ፌስ

ECLN
1258
http://ethcriminalawnetwork.com/

ቡክ የሚሰው አጠቃላይ ሳይንሳዊ እንተኑን ተንታኔውን አሁን እሱ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚቻል ስላልሆነ ይሄ ጥያቄ /ግልፅ ያልሆነ/

- ምን ላይ ነው ያየኸው ፌስ ቡክን በሞባይል ላይ ነው ያየኸው ወይስ በምንድን ነው ያየኸው ፌስ ቡክ ያልከውን በሞባይል ላይ ነው ያየኸው በምን ላይ ነው ያየኸው ?
- ሞባይል ላይ
- ጨርሻለሁ
- ጨርሳችዋል መስቀለኛ ጥያቄ
- አቶ ፎአድ 3 ቀን ሙሉ ነበርኩኝ አንዋር ብለዋል እርሶ አንዋር ነው እንዴ የሚሰሩት የስራ ቦታዎት እዚያ ነው ?
- አዎ
- አንዋር ነው የሚሰሩት ምንድን ነው የስራ ድርሻዎት ?
- አንዋር ሳይሆን ከአንዋር ውጪ መርካቶ
- ሌላ ጥያቄ
- እስቲ አንድ ጊዜ አትድገሙ የሚለው ማሳሰቢያ ስንገባ ችሎት ተሰጥቷል አሁንም 2ኛ ነው 3ኛ ላይ የጠየቁት ጠቦታ አብዝኛው የተደገመ አለ የተለያየ ነገርኛም ቢኖሩ የ 3 ቀን ውሎም በእዚያ /ግልፅ ያልሆነ/
- አይ 3
- /ግልፅ ያልሆነ/ ማንኛውንም ድግግሞሽ ባትጨምሪ
- 3ቱም ቀን እራስዎ ነው የሄዱት ወደ አንዋር 3ቱንም ቀን እርሶ ነው የሄዱት እራስዎት ?
- አዎ
- በራስዎት ፍላጎት ?
- ያው ያለውን ነገር ለማየት
- ምን ትምህርቱን ለመከታተል ነው ?
- ሥዲያ
- ለእዚህ ነበር የሄዱት ?
- አዎ

1359

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጨርሻለሁ
- የተከበረው ፍ/ቤት አንድ የመጨረሻ ጥያቄ አለችን ያልተጠየቀ
- ጠይቀው ተቀምጠው ነበር እኮ
- ጠይቀናል እንጂ እኮ እኔ እስከምዘጋጅ ለሌሎች ነው የሰጧቸው እንጂ አልጨረስንም አጠቃላይ /ግልፅ ያልሆነ/ አልጨረስንም
- አንድ ጥያቄ ብለዋል እሺ ያንሱ
- ቅድም 3ቱም ተናጋሪዎች ምስክር ይሰሙኛል እየሰሙኝ ነው 3ቱም ተናጋሪዎች የራሳችንን መንግስት እናቋቁማለን ብለዋል ብለው ነግረውናል ትክክል ነኝ ?
- ማን እኔ
- ተከሣሾቹ እንደዚህ አላሉም እንዴ ?
- ብለዋል
- ከእዚህ ውጪ የት እንደሚያቋቁሙ መቼ እንዲያቋቁሙ እንዴት እንደሚያቋቁሙ አልተናገሩም አይደል ይሄንን ብቻ ነው የተናገሩት ?
- አዎ
- ይቺን ነው ጨርሻለሁ
- እስቲ አዎ ብለዋል እና እርሶ ጨርሰዋል መቀመጥ ይችላሉ እና የተጠየቀውን አዎ ብለዋል ግልፅ ከሆነሎት አዎ ያሉት ምንድን ነው እስቲ እሷን ግልፅ አድርጉልን ?
- አሁን የራሳችን መንግስት እናቆማለን
- ጥያቄው መቼ የት እና እንዴት እንደሚያቋቁሙ የተነጋገሩት ነገር አለ ወይ ነው እና አዎ ብለሀል ?
- እንግዲህ አሁን ይሄ በየሣምንቱ ተክቢራ የሚደረገው ለስሙ ይሁን ለምን ይሁን እኔ አላወኩም
- መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የከሣሽ ዐቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ካለ ይቅረብ ተብሏል
- አቶ ፎአድ እርሶ ከአርብ እስከ እሁድ አንዋር ነበሩ አንዋር ብዙ ሰው ይሰበሰብ ነበር?
- አዎ
- ፖሊስ ነበር ?

1360

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ነበር አዎ ዙሪያውን
- ተሰብሳቢው እና ፖሊሱ መሀል ምን ነበር ?
- ያው እኔ ውስጥ ስለነበርኩ ያው ፖሊስ ነበር ውጪ ነበር
- ተቃውሞ አለ በዋና ጥያቄ ላይ ያልተነሳ የተከበረው ፍ/ቤት በዋና ጥያቄ ላይ ያልተነሳ መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ያልተነሳ አሁን እንደ አዲስ በድጋሚ ጥያቄ ላይ እየተነሳ ነው ስለፖሊስ ስለሕዝብ ያለው በተመለከተ እና ይሄ በግልፅ ሊጠየቅ የማይገባ የዋና ጥያቄ ባህሪ የማያሟላ ስለሆነ ውድቅ እንዲደረግ
- ዐቃቤ ሕግ መልስ ስጡ
- ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ምስክሩ ሲጠየቁ ምን ነበር ሕዝቡ ከመሰብሰብ ውጪ ሌላ ምን ያደርግ ነበር ተብለው ሲጠየቁ በተከሣሽ ጠበቆች እየተመሩ ምንም አላደርግም ተሰብስበው ነበረ ዝም ብሎ ብለዋል እና ያንን መሠረት አድርገን ነው ይሄንን ጥያቄ መጠየቅ ያስፈለገን የተከበረው ፍ/ቤት
- ፍ/ቤቱ /ግልፅ ያልሆነ/ ትዕዛዝ ሰጥቷል ዳግመኛ ጥያቄ ላይ የቀረበውን ጥያቄ መሠረት አድርጎ የቀረበ ጥያቄ አይደለም የሚል ነው መቃወሚያው በዐቃቤ ሕግ በኩል ከእዚህ ተነስተን ነው ጥያቄውን ያቀረብነው /ግልፅ ያልሆነ/ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደተመለከተው በእዚህ በተባለው ጊዜ በግልፅ ችግር ለመኖር በእዚሁ መሀከል ችግሮች /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር በወቅቱ የደረሰ ጉዳት ነበር ?
- አልነበረም
- ምንም ጉዳት አልደረሰም ?
- አዎ
- ቅድም በተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ሰደቃ ሊደረግ ሲል ከእዚህ በፊት የማይደረግ ሰደቃ ዛሬ ምን ተገኘ ተብሎ ቆመ የሚል መልስ ሰጥተው ነበር ሰደቃ ከእዚህ በፊት አይደረግም እንዴ ?
- ይደረጋል
- ታዲያ እርሶ አሁን ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ተከለከለ ያሉት ሰደቃ ለምንድን ነው የተከለከለው ?

1361

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሕዝቡን መቀስቀሻ ስለሆነ ነዋ
- ሕዝቡን መቀስቀሻ ስለሆነ ነው ?
- አዎ
- ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ በተከሣሽ ጠበቆች ሲጠየቁ በድጋሚ መሴጅ ደርሶኛል ብለዋል ሞባይሎት ላይ ነው?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ይላል ?
- ያው እዚህ ቦታ ላይ ያው ስብሰባ መሰብሰብ እንዳለበት ነው
- የት ?
- አንዋር መስኪድ
- አንዋር መስኪድ ?
- አዎ
- አንዋር መስኪድ ስብሰባ መሰብሰብ አለብን ?
- አዎ
- አሁንም በድጋሚ ቅድም መጠቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ሰዒት 6 ሰዓት ሰላት አለ ወይ ብለው መልሰው ነበር ?
- አዎ
- ለምንድን ነው እንደዚያ ያሉት ?
- እኔ አይ አላህ ዋክበር ማለት ለምንድን ነው ሲሉኝ ሰላት ሲደርስ ነውአልኩት ከእዚያ በ 6 ሰዓት ምን ሰላት አለ አልኩት
- 6 ሰዓት ምንድን ነው ?
- ከለሊቱ 6 ሰዓት
- ከለሊቱ 6 ሰዓት ?
- አዎ
- እስቲ ምንድን ነው ይንገሩን እሱን ያብራሩት?
- ያው ማለት ከለሊቱ 6 ማለት አላህ ዋክበር ማለት እኮ እንግዲህ ያው ሹዋር አለ ማለት ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላህ ዋክበር ማለት ?
- አዎ ችግር አለ ማለት ነው
- ለምን ?
- ሕዝቡ እንዲወጣ ማለት እንግዲህ የተለየ ነው ለየት ያለ ነገር ነዋ
- ለምን ቀን 7 ሰዓት ቢደረግስ ቀን 6 ሰዓት 7 ሰዓት ቢደረግስ ?
- እሱ ሰዓቱ ነዋ
- እኮ እሺ ሰዓቶቹን ይንገሩና መደበኛ ሰዓት አለው እንዴ ?
- አለው አዎ
- መቼ መቼ ነው ?
- አሁን ምሳሌ ጠዋት ከጠዋት ስንጀምር
- ቆይ ቆይ መቃወሚያ አለ
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን መቃወሚያ ነው አሁን በዋና ጥያቄ ወቅት ያልተነሳ ስለሰላት 5 ጊዜ የሚለውን እኛም አልጠየቅንም ስለዚህ በመስቀለኛ ጥያቄም ሆነ በዋና ጥያቄ ያልተነሳ ስለሆነ አግባብ አይደለም ጥያቄው ሊጠየቅ አይገባም ሊመልሱም አይገባም
- ዐቃቤ ሕግ መልስ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እኔ እያንዳንዱን ጥያቄ ምስክሩን ስጠይቃቸው ጠበቆች ያሉትን የመስቀለኛ ጥያቄ የምደግመው ይደክመኛል ግን ሆነ ብዬ ነው እንዲህ መቃወሚያ እንዳይነሳ ነው ይሄንን ጥያቄ ከማቅረቤ በፊት ጠበቆችያነሱት ጥያቄ ስደግምላቸው ነበር ለምስክሩ ለሊት 6 ሰዓት ሰላት አለ ወይ ብዬ ጠይቄአለሁ ጠበቃው ሲጠይቄኝ ብሎ እራሱ ምስክሩ አሁን ተናግሯል ለምን አልክ ሲባል ለሊት 6 ሰዓት ሰላት የለም ይሄ መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ተነስቷል አሁን ድጋሚ ጥያቄ ላይ ለምን እንደዚህ አልክ መቼ መቼ ነው ታዲያ መሰገድ ያለበት 6 ሰዓት ልክ አይደለም እያሉ ከሆነ ይሄ ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ታዲያ መቼ ነው ይሄ በጣም ተያያዥነት ያለው እና በመስቀለኛ ጥያቄም የተነሳ ጥያቄ ነው እና አግባብ አይደለም ውድቅ ይደረግልን

1763

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ትዕዛዝ ሰጥቷል በዐቋቤ ሕግ የቀረበው ዳግመኛ ጥያቄ ትክክለኛው- የሰላት ሰዓት መቼ ነው የሚል ጥያቄ ነው ይሄንን ጥያቄ መሠረት ሲያደርግ በእዚህ ቀደም ብሎ በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ምስክሩ የመሰከራቸው የምስክርነት ቃሎች አሉ ከእነዚህ ውስጥ 6 ሰዓቱ የ 6 ሰዓቱ ጥሪ ከመስኪድ የመጣው ጥሪ ትክክለኛ አይደለም የአዛን ሰዓት አይደለም 6 ሰዓት የሚል ምስክርነት ስለሰጠ ተብሎ ቀርቧል ስለዚህ አሁን የቀረቨው ምንድን ነው የትኛዎቹ ሰዓቶች ናቸው ትክክለኛው ለአዛን ሰዓቱ ብሎ መጠየቅ በመስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ የተመለሰውን መልስ ለማብራራት የቀረበ ጥያቄ በመሆኑ ምክንያት ይሄም በስነ ስርዓት ሕጉ /ግልፅ ያልሆነ/ ትክክለኛው የአዛን ሰዓቶች ይጥቀስ ብሎ ጥያቄ መቅረቡ ተገቢ ነው
- እናመሰግናለን ምስክር ቀጥል ካቆምክበት ?
- ጠዋት ስንት ሰዓት ?
- 12 ሰዓት ተኩል ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ቀን ደግሞ 7 ሰዓት 6 ተኩል እና ደግሞ 10 ሰዓት ወደ 10 ሩብ ጉዳይ ወይም 12 ከሩብ ወይም 1 ተኩል 2 ሰዓት
- 2 ሰዓት አካባቢ ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላ የለም ?
- የለም
- የለም?
- ሰላት የለም
- ይሄ ታዲያ 6 ሰዓት አንተ በወቅቱ በጠቀስከው ጊዜ 6ሰዓት ተደረገ ያልከው አዛን ለምንድን ነው ?
- ያው እንግዲህ አወሊያ ላይ ያው ሰደቃ ብሎ ያው ጀምሮ ነበር ?
- እነ ማን ?
- ያው እዚያ የነበሩ ሰዎች ናቸዋ እነኚያ 4ቱ ሰዎች
- እዚህ የጠቀሷቸው 4ቱ ሰዎች ?
- አዎ እና በእዚያ በሰደቃው ምክንያት ሰደቃ ያው አታደርጉም ብሎ ያው መንግስት ከልክሏቸዋል ከእዚያ በኋላ እንግዲህ ያው ሰደቃ ማድረግ ካልቻልን ብለው

1364

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ለሕዝቡም ያው እንዲቀሰቀስ አላህ ዋክበር /ግልፅ ያልሆነ/ በየመስኪዱ ግማሱ በመስኮት ሰብሮ ግማሹ በበር ሰብሮ/ግልፅ ያለሆነ/ አዛን እንዲሉ ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ያው ተደርጓል

- የት ተሰበረ እስቲ የሚያውቁትን ይንገሩን የት ምን ተሰበረ ?
- ለምሳሌ አሁን አንዋር መስኪድ ላይ ተሰብሯል
- ተቃውሞ አለን
- መቃወሚያ
- የማጣሪያ ጥያቄ ዓላማው በመስቀለኛ ጥያቄ የተነሱትን ነገሮች ምናልባት መደናገር የተፈጠረባቸው ነገሮች ለማጥራት እና ለማስተካከል ነው እንጂ በእዚያው ጥያቄውስጥ እንደገና ጥያቄው እየቀጠለ ምስክሩ ከሰጠው መልስ ላይ በመነሳትም ቢሆን መሄድ የለበትም
- ልትጠይቁ የፈለጋችዋትን
- አሁን ለምሳሌ በአወሊያ መስኪድ ስለተሰበሩ ነገሮች መስታወቶች ዋና ጥያቄ እሳቸው አልተጠየቁም አልመለሱም እኛም አወሊያ መስኪድ እሳቸው አንዋር መስኪድን ብቻ እና ቄሮ መስኪድ ብቻ አድርገው ስለነበር የጠየቁት የመለሱት አንዋር መስኪድ እና ቄራ መስኪድን ብቻ ነው መሠረት አድርገን የጠየቅነው አሁን ከአዛኑ ጋር ተያይዞ እንደገና አወሊያ ሄደው ስለ አወሊያ እንዲያስረዱን ነው የተጠየቁ ያሉት ስለአዛኑ ተነስቶ መልሷል ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይን መሠረት ከእዚህ የሚቀጥለው ጥያቄ ግን አዲስ ጥያቄ ስለሆነ ሊቆም ይገባል ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አሁን እራሱ ከእዚህ ቀደም ስንከራከርበት የነበረው ጉዳይ ጉዳት አልደረሰም ተብሎ በመስቀለኛ ጥያቄ በተደጋጋሚ በጠበቆች እንዲረጋገጥ ተፈልጎ ምስክሩ ሲጠየቅ ነበር ምስክሩ ሲመልስ እንደነበር ያው ግልፅ ነው ሲሰማ የነበረ ነገር ነው አንድ እሱ ነው
- በተነሳው ጥያቄ /ግልፅ ያልሆነ/ የተነሳው ጥያቄ ከተባለው ውጪ ሌላ አወሊያ መስኪድ የተባለ ነገር አለ እሱ ላይ ጥያቄ እያነሱብን ስለሆነ ለልተሰማ ነው ዋና ጥያቄ በመስቀለኛ ጥያቄም /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚህ ተነስተው

1365

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኛ መስኪድን አያይዘን አልጠቀስንም አንድ መስኪድ ጠቅሰን እኛ የጠቀስነው ምን ተፈፀመ ለሊት አዛን ሕገ ወጥ አዛኖች ተደረጉ አሉ
- አወሊያን አልጠቀሱም ነው ?
- እኛ ምስክሩ ሲገልፁ ያው በገባቸው መንገድ እያንዳንዱ ሰው ሲያስረዳ በራሱ መንገድ ነው የሚያስረዳው ሊጠቅሱ ይችላሉ ይሄንን ልንገድብ ይከብደናል ግን እኛ የጠየቅነው ጥያቄ ግን ምንም ቅድም የተፈቀደልን ጥያቄ ነው የጠየቅነው እሱን ነው እያብራሩ እየቀጠሉ ያሉት ምስክሩ ጉዳት እንኳን ስለእዚያ እንኳን የመሰከሩት ከሆነ ተቃውሞ የቀረበው ስለጉዳትም አሁን ከእዚህ ጥያቄ በፊት ስንከራከር የነበረው ስለጉዳት ነው
- ስለዚህ የጠየቅነው ጉዳት ነው ነው ?
- አዎ
- አሁን የተነሳው ነገር ዐቃቤ ሕግም ያው አወሊያ ላይ አላነሳንም እያሉ ነው አሁንም አወሊያ ላይ ያለ የተነሳ ካለ እሱን ታቆሙ እና ከተጀመረው ትቀጥላላችሁ
- እሺ ምስክር ላስታውስ እና አሁን በጠቀስከው ጊዜ ከለሊቱ 6 ሰዓት ላይ አዛን ተባለ ሰው ተሰበሰበ ከእዚያስ ?
- ከእዚያ ያው እንግዲህ በነጋታው ያው ይሄንን ነገር
- አይ ሰው ተሰብስቦ ምን ተፈጠረ ?
- ምን ተፈጠረ ያው እንግዲህ ጨለማ ነው እንግዲህ ያው የተደረገው ድርጊት ያው የደረሰበት ነው የሚያውቀው ጨለማ ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ተፈጠረ የሚያውቁት ካለ ይግለፁት የሚያውቁት ካለ ይግለፁት የማያውቁት ከሆነ ደግሞ አይገደዱም የሚያውቁት ነገር ምን የተፈጠረ ነገር አለ ?
- በቃ አላህ ዋክበር ተባለ በቃ ያው አንዋር ላይ መስኪድ በቃ እንደተሰበሰቡ ተደረገ በቃ ያው
- በማግስቱስ ?
- ያው እንደዚያ ነው
- ስለዚህ ቅድም አሁን ከእዚህ ከመቃወሚያ በፊት ያሉኝ ተሰበረ ምናምን ያሉኝ ነገር ምንድን ነው ?

1766

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት ለመግባት አዛን ለማለት ነዋ
- ተቃውሞ አለኝ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጠቤት ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ከሰጠበት በኋላ እንደገና እዚያው ጋር ተመልሰው ተሰበረ ያልከው የት ነው ብለው እዚያ እንደገና ወደ አወሊያ ነው እየመለሷቸው ያሉት ስለአወሊያ እንዲያወሩ እያደረጓቸው ያሉት አሁን ምስክሩ ስለአወሊያ አይጠየቁ ተብሏል የፍ/ቤቱ ብይን መከበር አለበት
- ተያያዥ ጉዳይ አንድ ላይ ምናልባት ከፈቀደልኝ አዎ አንድ ላይ ሆኖ እሱን እንድጠይቅ እንዲፈቀድልኝ
- /ግልፅ ያልሆነ/ የቅድሙን ግልፅ እናድርገው አወሊያ ላይ ምን ተፈጠረ የሚል ጥያቄ ነው ተነስቶ የነበረው እናንተም ጋር ተነስቶ የነበረው መቃወሚያ ስለአወሊያ መጀመሪያም የተነሳ ነገር የለም ስለዚህ አሁንም አሁን እዚህ የተረዳነው ነገር ስለአወሊያ እንዳይነሳ እንትን ሰጥተናል እና የነበረው ጥያቄ ምን ተፈጠረ የሚል ስለነበር ምናልባት እሱን ነው እየመለሱ የነበሩት እስቲ ከእዚህ ተነስታችሁ ግልፅ አድርጉ
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን እያጨቃጨቀ ያለው ነገር ምናልባት የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ ምስክሩ ካለው ወጥተው ነው እየጠየቁ ያሉት ምንድን ነው ምስክሩ በለሊት በፍፁም አላሉም ወደ ኋላ ሪከርዱ ሊሰማ ይችላል በለሊት ዐቃቤ ሕጉ ነው የጨመረው ትክክለኛ ቃል ያሉት ስለአንዋር 6 ሰዓት ላይ አዛን ተባለ እያሉ ነው የተናገሩት የሚያውቁትም የአንዋርን ድርጊት ነው በአንዋርድ ድርጊት ከጠዋት 2 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ነበሩ 6 ሰዓት ላይ ተክቢራ አዛን እየተባለ ነበር ያሉት ስለቀኑ ነው 6 ሰዓት /ግልፅ ያልሆነ/ ዐቃቤ ሕግ ግን ይሄንን ገልብጠው ለሊት የምትለዋን መጀመሪያ አልያስያዙም እና ፍ/ቤቱም ይመልሳቸዋል ብዬ ነበር ዞሮ ዞሮ ግን አሁን ለተፈጠረው ችግር ይቺ ለሊት የምትል ነገር ምስክሩ ወደ ኋላ ሄዶ ሊሰማ ይችላል አልተናገሩም ያሉት ቀን 6 ሰዓት ላይ አዛን ተባለ ስለዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ ዐቃቤ ሕጉ የማያምኑ ከሆነ ወደ ኋላ ሄደው ይሰማ እና በአጠቃላይ መፍትሔ ይሰጠዋል ብዬ አስባለሁ የተከበረው ፍ/ቤት
- እስቲ አሁን የተነሳው ከጠበቃ አሁን ከተናገሩት ውጪ የመጀመሪያው ተቃውሞ ምን ነበር መጀመሪያ ምስክሩ አሁን መጨረሻ ላይ ሲጠየቁ ምስክሩ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሱ በብይን ታለፈ ቆዩ እስቲ አንዴ /ግልፅ ያልሆነ/
- የተነሳነው ክርክር ምንድን ነበር ስለአወለያ ነበረ አወለያን እንዳያነሱ ተባሉ በድጋሚ ዞር አሉ እና እሳቸው ዐቃቤ ሕጉ የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ ስለአወለያ ጉዳት ነው እየጠየቁ ያሉት ሰውዬው ስለአወለያ በደረሰ ጉዳት ለሊት እቃ ተሰበረ ምን ወደ የሚል ነገር ነው የሄዱት
- ስለአወለያ ጉዳት ነው እየተመለሰ ያለው ?
- አዎ
- እንደገና ደግሞ ለሊት የምትለዋ ነገር
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ዐቃቤ ሕግ
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ያላሉትን እንደውም እያሉ ያሉት ጠበቆቹ ናቸው ምስክሩ ስለአወለያ ገና አልጀመሩም እኮ መልሱን መመለስ አልጀመሩም ቀድሞ አቋረጡ እና አወለ.ያ የሚሉት
- ስለአወለያ ጠይቃችዋል አልጠየቃችሁም ?
- አልጠየቅንም እኛ አወለያ መስኪድም ሲጀመር አወለያ መስኪድ በለሊት ድረስ አይድረስም ይሄ ምስክር ጭብጡም አይደለም አያውቅም እና ያላለውን ነው እንትን የሚሉ እና መሀል ላይ ከምንገባ ብለን ነው ይጨርሱ ብለን ነው
- ጨርሰዋል ?
- አዎ ጨርሰናል
- ብይን ሰጥተናል ቅድም ወደ ኋላ ተመልሰው ምስክሩ ለሊት አላሉም የሚለው ነገር ምናልባት ካለመረዳት ሊሆን ይችላል እኛ መዝግበናል ለሊት 6 ሰዓት አዛን አይደረግም ነው ምስክሩ ገና ሲጀምር ሲጀምር ሲመሰክር የነበረው እና እሱ ተብሏል አዲስ ምስክሩ ያላለው ተጨመረ የሚለው አግባብ አይደለም በእዚያ መሠረት ብታራሚት እሷን ሌላው አሁን ወደተነሳው ነገር ቅድም በእዚያ ጥሪ በአዛን ጥሪ ባልተፈቀደ ሰዓት በአዛን ጥሪ መሠረት ሕዝቡ ወጣ ነው ያለው ምስክሩ ወጣ ብሎ ቆመ እና ሕዝቡ ወጥቶ ከእዚያ በኋላ ምን አለ ዐቃቤ ሕግ ከእዚያ ሲጠይቅ እና ይሄ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

በዋና ጉዳይ አልተነሳም በሚል ተቃውሞ ነበር የመጀመሪያው ይሄ ላይ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል ብይን ሲሰጥ ምናልባት ግልፅ ያልሆነ ነገር ካለ ነው እንጂ በለሊቱ 6 ሰዓት ተጠርቶ በእዚያው አዛን መሠረት ሕዝቡ ወጣ ተባለ ከእዚያስ ምን ሆነ የሚለው ነገር ምንም አዲስ ፋክት መጨመር አይደለም ነው ተያይዞ የሚሄድ ስለሆነ ይቀጥል ነው የመጀመሪያው በእዚያው ከእዚያ በጎላ ዐቃቤ ሕግ አሁን ምስክሩ ከእዚያ በኋላ ሲመሰክር ለሊት ጨለማ ነው ብሎ ቆመ ከእዚያ በኋላ ጉዳት ብለህ ነበር እና ብሎ ዐቃቤ ሕግ ወደ ኋላ እንትን ብሎ ነበር አሁን የቆመው ምስክሩ መጀመሪያ ሲናገሩ ጉዳት ብሎ ነበር ያ ተቃውሞ የተነሳው እሱ ላይ ነው ማታ በእዚህ በወጣው ሕዝብ ጉዳት ተብሎ ነው ተቃውሞ የተነሳው ስለዚህ ያ ደግሞ አዲስ ነገር አይደለም ቀጥል ተብሏል ነገር ግን አሁንም ምስክሩ የሚመሰክሩት ስለአንዋር መስኪድ ጋር በተያያዘ እና ቁራ ብለዋል እና በ2ቱ ጋር በተያያዘ ነው እና ስለአወሊያ ከሆነ ጥያቄው አልተነሳም በ2ቱ መስኪዶች ጋር በተያያዘ ከሆነ ጥያቄአችሁን ቀጥሉ በእዚሁ ?

- የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን ምስክር ስለ አወሊያ ሳይሆን አንዋር እና ቁራ በለሀል ከቅድም ጀምሮ ስታስረዳ እዚያ የደረሰ ጉዳዮች አሉ ወይ በማታ አሁን አንተ ባልከው ሕዝቡ ከወጣ በኋላ ?
- ሕዝቡ ብዛት ያው መሰብሰቡ ነዋ
- እሺ መሰብሰቡ
- ሰብስቦ እንግዲህ ያው
- አሁን ቅድም በድጋሚ ጥያቄ ስንጠይቅህ ለመግባት ወደ መስኪድ ምናምን ስትል ነበር ?
- አዎ ፍተሻው
- ምንድን ነው እሱን አዎ ስላቋረጡን ከእሱ ጀምሮ ?
- ፍተሻው አሁን ማለት መስኪድ ላይ ሰው ሰገባ ማንኛውም ሰው ቢሆን አይፈተሽም ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ሰላም ነው ያው ሰግደው ስመሠርተው ነው ግን አሁን ይሄንን ያን ቀን ይሄ ፕሮግራም ሲተላለፍ ያው እስኪሪቢቶ ይዞ እንዳይገባ ወረቀት ይዞ እንዳይገባ ያው ሁሉ ነገር እየተፈተሸ ነበር ግን

1269

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ማን ነው ይሄንን ፍተሻ የሚያደርገው ?

አይታዩም ይሄንን ተሸፋፍኗል

የሚፈትሹት አይታዩም ?

አይታዩም ተሸፋፍነዋል

እንዲፈተሽ የሚያደርግ ሰው አለ ?

ያው እንግዲህ ያው ተልኮ ይኖረዋል ማን እንደላከው እኔ እንጃ

እየተፈተሸ ወደ ውስጥ ይገባ ነበር ?

አዎ እየተፈተሸ ይገባል

ሲገባ መድረኩን የሚመራው ማን ነው ?

ያው እነ ያሲን ኑሩ ናቸው

እነ ያሲን ኑሩ ናቸው ?

አዎ

መስኪድ በለሊት ይገባል እንዴ ፎአድ ?

በለሊት አይገባም እዚያው የሚያድር ዘበኛ አለ እንጂ አይገባም

ለሊት ታዲያ አዛን ብሎ የወጣው ሰው እንዴት ገባ ወደ መስኪድ ?

ወደ መስኪድ

እንዴት አድርጎ ገባ ?

እንግዲህ ያው እንግዲህ ዘሎም ይሁን እሱ አይደለም እዚያ አካባቢ ሰው አይደለም ያው በታክሲም እንኪን ከሩቅ ቦታ በላዳ ተሳፍሮ የመጣ ሰው አለ

አዛን ሲባል ?

አዎ ተሳፍሮ መጥቶ እጁን ተደብድቦ ባለ ሱቅ ነው ተደብድቦ ምን ሆነሀል ስለው አንዋር በተዘረጋው ተክቢራ ሄጄ ያው ተደብድቤአለሁ ብሎ ነገረኝ

ዘበኞች የሉትም እንዴ መስኪድ ?

ዘበኞች እንኪን ለዘበኞቹ ያው ውጡ ብሎናል ያው

እኮ አልከለከሉም ሰው በለሊት ሲመጣ ?

እንግዲህ ያው ኃይል ያው አልቻሉም ይሆናል ኃይል ሰው የሚጫው ሰው ኃይል አልቻሉማ

1370

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልቻሉም ?
- አዎ
- እስቲ ምናልባት ዐቃቤ ሕግ አሁን ጥያቄ ሲያቀርቡ ያው ከእዚያም ሲሰጥ እንደነበረ ያልተነሳውን ብቻ
- እሺ አቶ ፎአድ ቅድም አርብ ቀን ሐምሌ 8 ምን ቀን ዋለ ሲባሉ አርብ ቀን ብለዋል በደንብ ያስታውሱታል ?
- አዎ
- እስቲ በምን እንዳስታወሱ ይንገሩን ?
- በምን እንዳስታወሱ ጁማ መሆኑን
- በጁማ ?
- አዎ
- ጁማ ቀን ነው ቅድም የነገሩን ጁማ ላይ ነው የዋለው ?
- አዎ
- ሰደቃ አሁንም አለ ወደ ፊትም የኖራል ነገር ግን እነሱ ያዚጋጃት ሰደቃ ለመቀስቀሻ ስለነበር ነው የተከለከለው ብለዋል ?
- አዎ
- ሰደቃ ለምንድን ነው በኃይማኖት የሚዘጋጀው ?
- የሚዘጋጀው
- እርሶ በሚያውቁት ?
- የሚዘጋጀው እንግዲህ ያው 1ኛ የተራበ ሰው ይበላል 2ኛ ደግሞ ያው ማለት ያው የኃይማኖት ባለቤትም ያው የሚታወስበት ጊዜ ነው ያው ማለት በየጊዜው አለ
- ለእዚህ ዓላማ ነው የሚደረገው ?
- አዎ በእዚያ ምክንያት ተደርጎ ነው ያው የሚደረገው
- ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ የምንናገረው ነገር ከእዚህ ታሪኩ ጋር ስለዚህ ሰው አትከልክሉ ግቡ ብሏል ያሉን ኑሩ ብለዋል ይሄ ብቻ ነበር የሚባል የነበረው በእዚያ ወቅት የኃይማኖት ትምህርት ብቻ ነበር የነበረው በእዚያ ወቅት ?
- የኃይማኖት ትምህርት አይደለም ቢላው አስይዘው ስጋ አለከመል

ECLN
1371
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተቃውሞ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁንም ኧዲስ ጥያቄ ነው እየጠየቁ ያለው አሁን ማን ነውያለው ብለን ጠየቅን ያለውን ሰው ተናግረዋል ማጣራት ከሆነ እዚህ ጋር ነው የሚቆመው ግን ከእዚህ ሌላ እሱ ምን ይናገር ነበረ የሚለው ከእዚህ በፊት እሱ ስለተናገረው ነገር ተጠይቀው ስላልመለሱ አሁን ያን ያለው እሱ ነው አይደለም የሚለውን እኛ መስቀለኛ ጥያቄ እንደገና የምናጣራበት ዕድል የለም ስለተጠየቀው ነገር ያሉን ነው ከተባለ በቃ ተጣርቶ የሚቆመው እዚያው ጋር ነው ሌላ ተጨማሪ ፋክት መጠየቅ የለበትም ከድጋሚ ጥያቄ ዓላማ ውጪ የሆነ ነው አሁን እኮ ዋና ጥያቄ ነው እየሆነ ያለው
- አሁን የተጠየቀው ማለት ጥያቄ አሁን ያለንበት ደረጃ የተከበረው ፍ/ቤት እንደሚረዳው ወደ ማብራራቱ አንገባም ማጠቃለያ ነው በዋና ጥያቄ በመስቀለኛ ጥያቄ ያልተብራሩ ነገሮችን የሚብራራበት በመስቀለኛ ጥያቄ ደግሞ የፈረሰብንን የምናስተካክልበት ወቅት ነው
- ቆይ ቆይ እሱ ግልፅ ነው
- ስለዚህ
- ዐቃቤ ሕግ አሁን ምንድን ነው መጨረሻ ላይ የተባለው ነገር አዲስ ፋክት ነው እያሉ ነው እሷን ብቻ እሷ ለምን እንደተነሳች እሷን ብቻ ይንገሩን /ግልፅ ያልሆነ/
- አዲስ ነገር አልተነሳም አሁን እየጠየቅን ያለነው ያሉን ኑሩ ይሄንን ብቻ ነው ወይ ያለው አሉን በቃ ይቺን አዎ ሲል አቆሙ እነሱ ስለዚህ ይሄ ብቻ ነው ወይ የተባለው እያብራራን ነው እያስተካከልን ነው በመስቀለኛ ጥያቄ እኮ በእነሱ በኩል አፍርሰዋል አዎ ከእዚህ ሌላ ከእዚህ ሰላማዊ ንግግር ውጪ ሌላ ነገር አልተነገረም እያሉን ነው ነገር ግን አይ ይሄ አይደለም ከእዚህ ውጪ አልተነገረም ዓላማውም ይሄ አልነበረም ነው የእኛ ጥያቄ
- ብይን ተሰጥቷል ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ የተነሳው ያሉን ኑሩ ይሄንን ብቻ ነው የተናገረው ወይ ተብሏል ምስክሩ ምላሽ የሰጡት ነገር አለ ዐቃቤ ሕግ እዚህ ላይ ከእዚህ ውጪ የተናገሩት ነገር አለ የሚል ማብራሪያ ጥያቄ አንስተዋል

1372

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከጠበቆች በኩል የቀረበው ይሄ አዲስ ፍሬ ነገር ነው በዋና ጥያቄ አልተነሳም ብለዋል ስለዚህ ፍ/ቤቱም አዲስ ፍሬ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ላይ ብይን ሰጥቷል ምስክሩ ሲመልሱ ያሲን ኑሩ የተናገሩትን ነገር የተናገሩ ነገር አለ ያው ሪከርድ የተደረገ ማለት ነው ከእዚያ ውጪ ሌላ የለም ወይ የሚለው ነገር ተጠይቋል ያ ማለት ኤክስክሉድ ማድረግ ሌላ ነገር አለማንሳት የሚሉ ነገሮች ሌሎች ተያያዥ ነገሮች አሉ እና ስለዚህ ከእዚህ ውጪ የተናገረ ነገር አለ ወይ የሚለው ያው በግልፅ የተነሳ ነገር አለ ስለዚህ ከእዚህ ውጪ የተናገሩ የተነገረ ነገር መኖር አለመኖሩን መጠየቅ ዋናው ነገር በመስቀለኛ ጥያቄ ከተነሳው ነገር ጋር በቀጥታ የሚያያዝ በመሆኑ ከእዚያ ወጥቷል ሊባል የሚችል አይደለም ስለዚህ ጥያቄው ከቆመበት ይቀጥል ተብሏል

- እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት ይቀጥሉ ምስክር አሁን ቅድም ላስታውሶት እና አሁን ካሉት ያሲን ኑሩ የምንናገረው የአላህ ቃል ነው ብሏል ከእዚህ ውጪ የተናገሩት አለ ወይ ይሄ ብቻ ነው የኃይማኖት ትምህርት ብቻ ነው የነበረው ያን ቀን ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ያው ስጋ ቢላውም አሸክሞናል በቢላው አስይዞናል በሬውም አሸክሞናል ያው ስለእኛ ስለእኛ መጥፎነት ያው ለሰው ያው ሊያስተላልፉ ይችላሉ ምናምን ብሎ ያው ይሄንን ሲያወራ ነበር
- ስለዚህ የኃይማኖት ትምህርት ብቻ አይደለም ?
- አይደለም
- ሲነገር የነበረው ?
- አዎ
- ሕዝቡ ለምንድን ነው መስኪድ የተሰበሰበው ተብሎ ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ዲህን ተነክቷል ተብሎ ነው ብለዋል ?
- አዎ
- ማን ነው ይሄንን ያለው ?
- ማን ያው እነኚህ ያው ከ 17 ሰዎች ውስጥ ማለት ነው
- ምን ብለው ምን ማለት ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልሀባሽ የሚባል መጥፎል ሴት ልጅ ሱሪ አድርቃ /ግልፅ ያልሆነ/ ትችላለች እና ወለድ ይቻላል ዚና ይቻላል እኛ ሶፊዎቹን ገድለን ከእዚያ በኋላ ያው ወደ ለሌላው እንገባለን መጀመሪያ ያው ሶፊዎችን ማለት መውሊድ የሚያከብሩትን መጀመሪያ እነሱን እንትን ማለት አለብን
- ምን ማለት አለብን ?
- መግደል አለብን አዎ
- ይሄንን ሲሉ ነው ሕዝቡ ሲያለቅስ የነበረው ስሜቱ ተነክቶ ?
- አዎ
- ፊታቸውን ሸፍነው ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- ለምን በምን ምክንያት ነበር ፊት መሸፈን ፊት ሸፍኖ እዚያ አካባቢ እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈለገው ለምንድን ነው ፊት መሸፈን ያስፈለገው ቦታው ምንድን ነው ?
- ማንነቱን /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ያደርጉ ስለነበር ነው ?
- ያው ፍተሻውን ያው ፍተሻውን እዚያ ቦታ ያለውን ነገር እንትን ክትትል የሚያደርጉ ሰዎች ያው የራሳቸውን እንትን ያው ቀይረው ነው ያው ሰሌዳ ቀይረው ነበር የሚንቀሳቀሱት የነበሩ ሰሌዳ እየቀየሩ ማለትም ያው ማንነታቸው ያው ፊታቸው ካልታየ አይታወቅም ያው
- እኮ ምን ተግባር እየፈፀሙ ስለነበረ ነው ማንነታቸውን የሸፈኑት ነው ?
- ያ ፍተሻ እዚያ ፍተሻ እስኪሪቢቶ ደብተር እንዳትይዝ
- ለምንድን ነው እንደዚህ የሚደረግ የነበረው ?
- መስኪድ ላይ ተደርጎ እስካሁን ተደርጎ እኔ አይቼ አላውቅም
- አያውቁም ?
- አዎ ምናልባት የመንግስት መስሪያ ቤት ከሆነ እንጂ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ከፍ/ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ የሰጡት መልስ

1374

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር ቅድም ሰው እየተፈተሸ ይገባ ነበር ነውያሉት ሁሉም ሰው ነው እየተፈተሸ የሚገባ የነበረው ?
- አዎ
- የመጣው ሁሉ ሰው ?
- ሁሉም ሰጡ
- የሚመለስ የለም ?
- የለም በ3ቱም በር ያው እየተፈተሸ ነው የሚገባው
- ሲፈተሽ የሆነ ኃይል አለ ብለዋል ?
- አዎ
- ምንድን ነው እሱ ኃይል ?
- እንግዲህ ያው ምንነቱን ያው እራሱነቱ አይታወቅም ፊቱ ሸፍኖታል አይኑ ብቻ ነው ያው
- ይሄንን ስትፈትሹ በምን ነበር የሚፈትሹት ?
- በእጃቸው
- በእጅ ነወ ?
- አዎ
- ሌላ የያዙት ነገርስ የለም ?
- ሌላ የያዙት ነገር አልነበረም
- በነገው ዕለት እንግዲህ ነገ ይሆናል ብለን እናስባለን በግልፅ ነገ አይሆንም ከተባለ ሁላችንም የምናረጋግጥ ከሆነ እንመጣለን ነገ ነው ከተባለ ዐቃቤ ሕግም ፖሊሲም ማረሚያ ቤትም አንመጣም ነገ ይሄ /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ ነገ አንመጣም ማለት ነው ስለዚህ መቼ እንገናኛለን አርብ ዕለት በእዚሁ ተመሳሳይ ሰዓት እንገናኛለን ያው እንዲህ ማሳሰቢያችሁን ሰምታችሁ አክብራችሁ አሁን ከሰዓት በኋላ ያካሄድነው ችሎት ጥሩ እንደሆነ ነው የምንወስደው በእዚሁ እንዲቀጥል።

ECLN
1375
http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የመ.ቁ 124754

17/5/05 ዓ.ም

ዳኞች:- ብስራት ተልዕቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

አሣሽ:- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድማገኝ ቴዎድሮስ ጌታቸው ዘረሰናይ ምስግና /ግልፅ ያልሆነ/

ተከሣሾች:- እነ አቡበከር 28 እራሳቸው ከማረሚያ ቤት ቀርበዋል የቀረ ተከሣሽ አለ የለም ስለዚህ ጠበቆች የተከሣሽ ጠበቆች ባህሩ መካንጋ፣ ተማም አባቡልጉ፣ መሐመድ አብደላ፣ ሞላልኝ መለሰ ፣ ሀሰን ሁሴን ፣ ተካ ዳባ ፣ አህመድ ጀማል የ 28ኛው አዲስ መሐመድ፣ ዳዊት ነጋሽ፣ ሀሊማ ሰይድ ቀርበዋል

- መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ቀሪ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ነበር ዐቃቤ ሕግ ቀርበዋል ምስክሮቹ
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- እኛ እንኳን የምንጠይቀው
- እስቲ ምናልባት ምስክሩ ጋር እንዳይያያዝ
- አይ

1

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የዐቃቤ ሕግ ምስክር እንኳን ደህና መጡ አሁን እዚህ ሲቀርቡ ስምዎን ብቻ ነው የሚገልፁት የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ነው የሚገልፁት ከእዚያ ውጪ አድራሻዎ የአባትዎ የአያት ስራዎ አይገለፅም ስለዚህ ነፃ ሆነው የሚጠየቁትን ብቻ ዐቃቤ ሕግ የሚጠየቀውን እዚያ የሚጠየቀውን ጥያቄዎን እያዳመጡ ጥያቄዎን መመለስ ነው ስለዚህ የመጀመሪያ ስምዎ ማን ነው የሚባል ?
- ሀይረዲን
- ስንተኛ ምስክር ናቸው ዐቃቤ ሕግ
- 77ኛ
- **77ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ለምንድን ነው እዚህ የመጡት?**
- ለምስክርነት
- እነ ማን በተከሰሱበት ነው ?
- እነ አቡበከር አህመድ እና ሳቢር ይርጉ
- በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- አቡበከር አህመድ ፣ ሳቢር ይርጉ
- ሳቢር ደጉ ነው ?
- ይርጉ
- አህመዲን ጀባል
- ሌላ
- በእነሱ ነው
- በእነዚህ ሰዎች ላይ ነው ?
- አዎ
- እስቲ አንዴ ተነሱ ተከሣሾች ያውቋቸዋል
- የተከበረው ፍ/ቤት ይቅርታ ከተፈቀደልኝ የምናመለከተው እዚህ ጋር ነው ይሄንን ነው ባለፈውም ተደጋጋሚ ስናመለክት ነበር ብይን እንዲሰጥበት አሁን እናመልክት እና ፍ/ቤቱ ብይን ይስጥልን ለሚቀጥሉት ምስክሮች ማለት ነው
- አሁን ምስክሩ ቁጭ ብለዋል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ አይ ምስክሩን ፍሬ ነገር ላይ የሚመለከት ሳይሆን ስነ ስርዓት ስለሆነ ብዙ እንትን አይልም ብለን ነው ወይ ምስክሩ አንዴ ውጪ እንዲቆይ መደረግ ይችላል
- የተከበረው ፍ/ቤት ባለፈው ይሄንን ነገር ደጋግመን ስናነሳ ነበር ምስክር እዚህ ሊመሰክር ከመጣ በኋላ ተከሣሾች እንዲቆሙ ተደርጎ ሄዶ የሚለይበት ምንም ዓይነት የስነ ስርዓት ድጋፍ የለም አንድ ተከሣሽ ነው ብለን ብናስብ በእዚህ መዝገብ ያለው ተከሣሹ ከማረሚያ ቤት ይመጣል እዚያ ሳጥን ውስጥ ይቆማል ምስክር መጥቶ መመስከር ይጀምራል ምናልባት ፍ/ቤቱ ጥርጣሬ ካደረበት ያንን ተከሣሽ ታውቀዋለህ ወይ ስሙ ማን ነው ብሎ ሊጠይቅ ይችላል ይሄ ነው መደበኛው ስርዓት ተከሣሾች በቁጥር ስለበዙ የተለየ ስራ ልንከተል አይገባም ስለዚህ ማንኛውም ምስክር ሊመሰክር እዚህ ችሎት ውስጥ ሲቀርብ ለምሳሌ ቅድም ምስክሩ እንዳለው ሳቢር አህመድ እያለ ሲጠራ እነዚያ ሰዎች መቆም መቻል አለባቸው ተነስተው ከሌሎቹ ሁሉም 29 ሰው ቆሞ የተከበረው ፍ/ቤት ስርዓት ያስይዝልን
- ልክ ነው አሁን እነሱ እየተናገሩ ነው ምንም ቢሆን ቢናገሩም ድምፅ ማሰማት የለም ትላንት ተነጋግረናል ቀጥሉ
- እነዚህ ስማቸው የሚጠራ ሰዎች ልክ አንድ ተከሣሽ እንዳለው መዝገብ አለባቸው ምስክሩ ከእነዚያ ውስጥ ከበደ ይሄ ነው ቴዎድሮስ ይሄ ነው እያለ መለየት መቻል አለበት ያንን ነው ሊሆን የሚችለው እንጂ ከ 29 ሰው ምንም ግንኙነት የለውም ምስክሩ 29 ሰው አያውቅም በፍፁም እና የማይሆን በሰውኛም አስተሳሰብ ሎጂካልም አይደለም ማናችንም ከእዚህ ውስጥ ተነስተን የዛሬ ፣ ዓመት የሆነ አጋጣሚ ያየነውን ሰው ከ 29 ሰው መሀል ላይ ይሄ ስነስርዓታዊም አይደለም ስለዚህ እዚህ ላይ ለቀጣዮቹ ምስክሮች አስገዳጅ የሚሆን ብይን ይስጥልን ፍ/ቤቱ አሁን ምስክሩ የሚጠራው መጥቶ የሚጠራቸው ሰዎች ቆመው ከእነዚያ ውስጥ እከሌ ይሄ ነው እከሌ ይሄ አይደለም ይሄ ደግሞ አይደለም እኔ አላውቀውም ብሎ መለየት መለየትም ካለበት በእዚያ ደረጃ መሆን አለበት 128 በሚያዘው መልኩ ማለት ነው ስነ ስርዓት ሕጉ 128 የሚያዘው ይሄንኑ ስለሆነ ተከሣሽ እንደመጣ ሳጥን ውስጥ ስለሚቆም የተጠራ ተከሣሽ ሳጥን ውስጥ ስለሚቆም ከእዚያ ድንጋጌ አንፃር ብይን እንዲሰጥልን ነው የፃናመለክተው
- እዚህ ጋር የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ብለን ስንል በእነኚህ ተከሣሾች ጋር አይደለም ማለት በእዚሁ በችሎት ባለው አሰራር አሁን ጓደኛዬ በገለፀው ተከሣሾች ይቀርባሉ ይቀመጣሉ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ስማቸው ሲጠራ ይነሳሉ ያለው አሰራር በችሎቱ ማለቴ ነው ስለዚህ ይሄ ለእነሱ ተብሎ ዛሬ የተጀመረ አይደለም አሁን በተባለው መልኩ እንዲሆንልን ነው በአክብሮት የምጠይቀው

- መልስ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ከተፈቀደልን
- ብይን ሰጥተንበታል መልስ አያስፈልገውም ብለናል አካሄድ ስለሆነ ፣ኛ 128 የሚለው ተከሣሹ ሳጥን ውስጥ ይቆማል ነው የሚል እና ማንነቱ ይረጋገጣል ነው የሚል ይሄንን አረጋግጠናል በፊት በነበረው አረጋግጠናል ከእዚህ በኋላ ምስክር መስማት ነው የሚሆነው ምስክር ቀርቦ በሚሰማበት ጊዜ 2 ነገር ነው የሚኖረው አንድ ያየውን ነው 2 የሰማውን ነው የሚናገር ስለዚህ ተከሣሹን ማለት ምስክሩን እዚህ ቁጭ አድርገን የምንጠራ ከሆነ ለምስክሩ እኛ እያሳየነው ተከሣሹን እኛ እያሳየን ስለሆነ ምስክሩ እራሱ እንዲያውቅ ነው የሚደረገው ስለዚህ ምስክሩ ሊያውቃቸው ይችላል ላያውቃቸው ይችላል ካወቃቸው ያሳያል ካላወቃቸው ግን የሰማውንም ቢሆን ሊመስክር ስለሚችል የሰማውን መስክሮ ከእዚያ በኋላ ፍ/ቤቱ /ግልፅ ያልሆ/ 28 ተከሣሽ ነው አንድ ተከሣሽ ነው መለየት ነበረበት አልነበረበትም በትክክል እንዴት ነው ያወቃቸው ምናምን የሚለውን መጨረሻ ላይ የፍ/ቤቱ ሚዛን ነው የሚሆነው ስምቼአለሁ እነ ኣከሌ እነ እከሌ የሚባሉ ሊል ይችላል እንዴት ስማን እንዴት አወክ ከእዚያ የሚዛን ጉዳይ ነው የሚሆነው አይ አውቃቸዋለሁ ካለ ደግሞ ሊያውቃቸው ይችላል አውቋቸውም ደግሞ 50/60/100 ሊኖር ይችላል በእዚህ መካከል ሁሉን የመለየት ዕድል ላይኖረው ይችላል ስለዚህ ሰው በመሆኑም የመረሳት ዕድል ሊኖረው ይችላል ስለዚህ እንዲህ እንዲህ ዓይነት ነገሮች በኋላ ሚዛን ውስጥ ገብተው የሚመዘኑ ነው እንጂ የሚሆኑት ከአሁኑ ምስክሩ ሲጠራ እኛ የምናሳየው ከሆነ ተነሽ እያልን የምናሳይ ከሆነ ከእዚያ በኋላ ምስክሩ ይለያቸዋል ችግር የለም ስለዚህ እንዲህ ዓይነት የስነ ስርዓት ሕግ ስለሌለ አልተቀበልነውም በእዚሁ እንቀጥላለን ማለት ነው
- በእዚህ በጠበቆች በኩል እየተደረገ ያለው አግባብ አይደለም ብትታረሙ ይሻላል ፣ኛ ድምፅ ታሰማላችሁ ትረብሻላችሁ እዚህ ሴነገር የፈለገውን ሊናገር ይችላል መልስ የሚያሰጥ ከሆነ ከእናንተ መልስ በኋላ ብይን ሊሰጥ ይችላል ይሄ ከየት የመጣ እንትን ነው ትክክል ሊሆን ይችላል ትክክል ላይሆን ይችላል የተናገረው እሱ ተናግሯል ተራ ሲሰጣችሁ ነው መናገር እንጂ የደቦ ስራ እየሰራችሁ ነው አግባብ አይደለም ይሄ ሌላው ደግሞ ድግግሞሽ አለ መልስ

1379

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ሲሰጥ ስትጠይቁ ጥያቄ እና እዚህ ላይ የዛሬ ሳይሆን ድግግሞሽ ብታስቀሩ ስትጠይቁ አንዱ ሲጨርስ ባትደግሙ የተጠየቀውን ነገር /ግልፅ ያልሆነ/

- ምስክር ቅድም 3 ሰዎች ጠርተውልናል ስለዚህ እነዚህን ሰዎች በስም ነው በአካል ነው የሚያውቋቸው ?
- በብዛት በስም ነው የማውቃቸው በአካል ያየዋቸው አንድ ቀን ብቻ ነው
- አንድ ቀን ብቻ ነው ?
- አዎ
- አሁን ቢያዩዋቸው ይለዩዋቸዋል ?
- ምናልባት ሊመሳሰሉብኝ ይችላሉ /ግልፅ ያልሆነ/ ከመሞከር ውጪ ያየዋቸው አንድ ቀን ነው በስም በደንብ አውቃቸዋለሁ አንድ ቀን መድረክ ላይ ነው
- መድረክ ላይ ብቻ ነው ያዩዋቸው ?
- አዎ
- እስቲ ቀና ብለው የሚችሉ ከሆነ መለየት የማይችሉ ከሆነ አይገደዱም ነኛ ተከሣሽን ለይተው አሳይተዋል እሺ አንተ ነህ ነህ አይደለህም ስንተኛ ተከሣሽ ነህ 7ኛ ተከሣሽን ለይቶ አሳይቷል ቁጭ በሉ እሺ ቢቃ ቁጭ በሉ
- ከእነዚህ አሁን ከሚጠሯቸው ሰዎች ጋር ፀብ ዝምድና አላችሁ ?
- የለኝም
- የላችሁም ?
- አዎ
- እሺ ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ
- ምስክር የሚያውቁትን ነገር በዝርዝር ያስረዱናል ረጋ ብለው ከመጀመሪያ ጀምረው የሚያውቁትን ነገር ያስረዳሉ ይጀምሩ እስቲ ?
- ያው አቡበከር ያየዋቸው መድረክ ላይ ነው
- ከጊዜው ይጀምሩ ጊዜውን ያስታውሳሉ ?
- ጊዜው ሰኔ 2004
- ሰኔ ስንት ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቀኑን አላስታውስም
- ሰኔ ወር 2004 ?
- አዎ ያው የሰደቃ ፕሮግራም ተብሎ
- የት ?
- ሀምዛ መስኪድ ካራቆሬ እዚያ በነበረው መድረክ ላይ መጀመሪያ መድረክ ይመራ ስለነበር እዚያ ቦታ ስለነበርኩ /ግልፅ ያልሆነ/ የማውቀውን ያህል ለመግለፅ
- ማን ነው እሱ ?
- አቡበከር
- እሺ ምን አለ ?
- ያው አቡበከር መጀመሪያ ሰው በተሰበሰበበት የ 10 መስኪድ ሕብረተሰብ ነው የተሰበሰበው በእዚያ ላይ መጀመሪያ ንግግራቸውን ሲያደርግ ስለ ጅሀድ ጥቅም አብራርቷል በሰፊው
- እስቲ ምን ምን አለ እስቲ ያለውን ትገር ይንገሩን ?
- እስልምና እየጠፋ ነው ሀባሽ የሚባል መጥቶ መጅሊስ እና መንግስት እየደገፉት በጣም በዳናችን ላይ ችግር እየመጣ ስለዘየነ ሳህበች በነብዩ ወቅት የነበሩ ሳህበች ለጅሀድ በታዘዙ ጊዜ ዝግጁ እንደነበሩ እና በጣም ጉጉት እንደነበራቸው ከነብሳቸውም ከምናቸውም የበለጠ በጣም የተዘጋጁ እንደነበረ በሰፊው አብራርቷል
- እኮ እና ምን እናድርግ ነው የሚለው /ግልፅ ያልሆነ/ ?
- እና ያንን ስሰፊ ካብራሩ በኋላ መታሰርን መሞትን ፀጋ ነው ነው ያሉት በአረብኛው ነይማ ነይማ ማለት ያው ፀጋ /ግልፅ ያልሆነ/ እና ስለዚህ ለኃይማኖታችሁ ለዲን መሞት ጅሀድ ነው ያው ጀነት የሚያስገኘው በሚል ሰፋ ያለ ቅስቀሳ ነው የተደረገው
- ሕዝቡ ምን ይላል ?
- ያው በመሀል በመሀል ሲናገሩ አላህ ክበር ነበር የሚለው
- አቡበከር ሲናገር በመሀል በመሀል አላህ ክበር ይላል ሕዝቡ ?
- አዎ
- ሌላስ ምን አለ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእዚህ ዓይነት የሰደቃ ፕሮግራም በሀገራችን ከሠራሪያ መስኪዶች በላይ እያካሄድን እንገኛለን አሁንም እዚህ ተገኝቼ ለእናንተ ይሄ አብራርቼ አሁን ደግሞ በተመሳሳይ እዚሁ አዲስ አበባ ሌላ መድረክ ስላለኝ አሁን ወደ እዚያ እሄዳለሁ ብሎ ምርጫችን በመስኪዳችን መሆን እንደሚችል እንደሚገባ ነው ያብራራው ማለት ነው
- ጥሩ አሁን ሲመሰክሩ ከ 80 በላይ መስኪዶች የሰደቃ ፕሮግራም እያዘጋጀን ነው ብለዋል ሲል ነበር ብለዋል እኛ እያለ ነው የሚያወራው ?
- አዎ
- እነ ማን ናቸው?
- ያው እኛ ብሏል በሰፊው አላብራራውም ያው እኛ ሲል ያው ሕዝቡ ያው እኔ እዚያ ያለው ሰው እንደተረዳሁ እኛ ሲባል ያው የተመረጡ ኮሚቴዎችም አሉ
- ምን ያህል ?
- ተመርጠናል ብለው በአወሊያ የተመረጡ 17 ኮሚቴ አሉ የሚል አለ
- ስለዚህ ኮሚቴውን ነው እኛ የሚለው ?
- ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ማለት
- እኮ ኮሚቴውን ነው እኛ የሚለው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ምንድን ነው ተቃውሞ ?
- እኛ የሚለው ኮሚቴውን ነው ወይ መሪ ጥያቄ ነው እየጠየቁ ያሉት ስለዚህ ይሄ ጥያቄ ሊታለፍ ይገባል
- የተከበረው ፍ/ቤቱ እራሱ /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ይሄ መቃወሚያ አይደለም መልስ ሳይሰጥ በእዚሁ አልፈነዋል ምክንያቱም እኛ የሚል ምስክሩ ቀደም ብለው ተናግረዋል በአወሊያ ያሉ ኮሚቴዎችን እኛ እያሉ ይገልፃሉ የሚል ነው ከእዚያ ተነስተው ነው የጠየቁ ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ ቀጥሉ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት እሺ ምስክር ይቀጥሉ እኛ የሚሉት ኮሚቴውን ነው አይደለ ?
- አዎ

1382

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ሲገልፁ 1ኛ አቡበከር አህመድ 2ኛ ሳቢር ይርጉ 3ኛ አህመዲን ጀባል ብለው ጠቅሰው ነበር የአቡበከርን ነገሩን ሳቢር ይርጉስ ?
- ሳቢር ይርጉ እሱም ሰፋ ያለ ማብራሪያ ነው የሰጠው ከተሰጠው የሰጠውን ሁሉ ይዤዋለሁ ማለት አይደለም
- እስቲ እንደአቡበከር የሚያስታውሱትን ይንገሩን ?
- የማስታውሰውን እናንተ ክርስቲያን ወንድሞቻችን ክርስቲያኑ በእዚያ መድረክ ላይ የተወሰኑ ከ 200 በላይ የሚሆን ክርስቲያኖች ተቀስቅሰው እዚያ ሰደቃ አለ ተብሎ ተጠርቶ ነው እናንተን ክርስቲያኖችን ወንድሞቻችን እዚህ የጠራናችሁ የሚዲያ ውሸትን ልናስረዳችሁ ነው የጠራናችሁ ሚዲያ በየወቅቱ ገለፃ የሚያደርገውን ውሸት ሰምታችሁ እውነት መስሏችሁ እኛን እንዳታርቁን እና አንድም ጊዜ ሚዲያ እውነት ተናግሮ አያውቅም ነው ያሉት
- ሌላስ ?
- ሌላ ያው ሀባሸ ገብቷል ኃይማኖታችን እየጠፋ ነው ያለው ጠላቶቻችን ሊለዩን እና ላከፋፍሉን ይጥራሉ
- እነ ማን ናቸው ጠላቶቻቸው ?
- ያው የኃይማኖቱ ጠላት ማለት ነው ያው ሀባሸም ሊሆን ይችላል ያው ከመጀመሪያ ከገለፀው አካያ ስንረዳው ሀባሸ እና ሀባሸን ያስገባው ክፍል ማለት ነው
- ማን ነው ?
- መጅሊስን እና መንግስት እየደገፏቸው ስለሚገኙ ኃይማኖታችንን እየጠፋ ነው ያለው ስለዚህ ይሄንን ውሸት ልናስረዳችሁ ነው የጠራናችሁ ለምሳሌ ብሎም ጠቅሷል ያው እናንተ ክርስቲያን ወንድሞቻችን እናንተም ጥያቄም ይኖራችዋል የእኛም ጥያቄ አለ በጋራ ተባብረን ጎን ለጎን ሆነን ጥያቄአችን አንድ ላይ ማሰማት አለብን የእኛንም ጥሪ ጥያቄ እናንተም እንድታስተጋቡልን ነው
- ሌላስ ምን ይል ነበር ባይሆንስ ይሄ ባይደረግስ ምን ይሁን ?
- ትግል ነው ያው ለዲን ነው እኛ ተጠንቅቀን መቆን አለብን ነው ሰውን የቀሰቀሰው የነበረው
- ትግሉ እንዴት ነው ?

1383

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው የትግሉ ዓይነት ሰፊ ባያብራራውም ለሁሉ እሱ በየሳይ ላይ በእዚህ ተመሳሳይ ሁኔታ እንደዚሁ አዘጋጅተን ነበር አለ የሰደቃ ፕሮግራም እዚያ ላይ ባዘጋጀነው ፕሮግራም እንጀራ እንዲያቀርቡልን አነስተኛ እና ጥቃቅን የተደራጁትን አነጋግረን ነበር ነው ያለው ያንን አዘጋጅተን ነበረው ላይ ማታውኑ የመንግስት ተጠሪ ለእነኚያ አንስተኛ እና ጥቃቅን ለተደራጁት ለአከራሪዎች እንጀራ ከሸጣችሁ ንግድ ፍቃዳችሁን እንሰርዝባችዋለን ብሎ አስፈራርቷቸው ቁልፍ ዘግቶብኝ ጠፍቷል ከእዚያም በማግስቱ የአካባቢው ሕብረተሰብ ቀስቅሰን 70 ሺህ እንጀራ ከየቤቱ ሰብስበን አምጥተን ፕሮግራማችን ልንፈፅም ችለናል እና ይሄንን ያህል ተፅኖ አለብን ለማለት ነው ያብራራው
- ምንድን ነው ዓላማው ይሄ ሰደቃ ፕሮግራም ?
- እኔ በበኩሌ እንደዚህ ዓይነት ሰደቃ አይቼ አላውቅም
- እንዴት ?
- በሰደቃ ስም ተጠራ እንጂ አላማው ሕብረተሰቡን ሰብስቦ ያሰቡትን ዓላማ ለመቀስቀስ መሰብሰቢያ እንጂ እንደዚህ ዓይነት ሰደቃ ግን የለም
- ምንድን ነው ያሰቡት ዓላማ ?
- ዓላማው አሰልምና ጠፍቷል መጅሊስ እና መንግስት ተባብረው እስልምናን የሚያጠፋ ሀባሽ የሚባል ነገር ቁራን የጅብሪል ነው የሚል ሰላት በቀን 2ቴ መስገድ ይቻላል የሚል ሴቷ ሱሪ ለብሳ ሰላት መስገድ ትችላለች እስከማለት የደረሰ ስለሆነ ለዲናችሁ ተነሱ ነው ያለው
- ይሄ ሁላ እውነት ነው እንዴ ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አለ ?
- በጣም የሌለ ነገር ነው
- የለም ?
- ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት በኢትዮጵያ ውስጥ የለም እና ይሄንን
- መቃወሚያ ምንድን ነው መቃወሚያ
- የተከበረው ፍ/ቤት አለ የለም እየተባለ የሚጠየቅ ጥያቄ ያው መልሱ ግልፅ ነው ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አለ እንዴ ከተባለ አንድ ምስክር መልሱ የታወቀ ነው መሪ ነው ስለዚህ ይሄ ጥያቄ እንዲታለፍ በተጨማሪ ዐቃቤ ሕግን እኛም በተደጋጋሚ እየተነሳን ፍ/ቤቱ ሂደቱን

1384

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥያቄውነ ብቻ ተውተ ሌላውነ ?
- ይሄንንም በተመሳሳይ መሪ ጥያቄዎችን እንዲተው እና ቀጥታ የሆኑ ጥያቄዎችን /ግልፅ ያልሆነ/
- ከእሱ ጋር ነው የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ የመጡት ተከሣሾቹ ምን አሉ እንጂ ከእዚያ አልፈው ይሄ ነገር አለ የለም የማለው ካመጡበትም ጋር የማገናኝ አይደለም አሁን ምስክሩ ተከሣሹ ምን አለ ነው እንጂ ምስክሩ ያለው ነገር እውነት ነው ሀሰት ነው የሚለውም አግባብ አይደለም ስለዚህ ሊቆም ይገባል
- ምላሽ ስጡበት
- 1ኛ አሁን ከመጨረሻው ብጀምር ምስክሩ የሚያስረዱትን ጭብጥ እኛ ቀድመን አስይዘናል እኛ ነው የምናውቀው ምን እንደሚያውቁ ስለዚህ እኛ ነን የምንጠይቀው ዋና ጥያቄ ላይ ስለዚህ እኛ በጠየቅነው ላይ መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ነው እንጂ የተከሣሾች ጠበቆች ድርሻ እኛ ምን በዋና ጥያቄ መጠየቅ እንዳለብን ሊነግሩን የሚችሉበት ስነ ስርዓት የለም አንድ እሱ ነው 2ኛ እኛ ይሄንን ምስክር የጠየቅነው መሪ ጥያቄ ተደጋግሞ ብይን ተሰጥቶበታል በእዚህ ፍ/ቤት መልሱን ነግሮ ነው አይደለም ብሎ መጠየቅ ነው ብሏል ፍ/ቤቱ አሁን እኛ የጠየቅነው ነባሽ የማባል ጎዶማኖት አለ ወይ ነው ይሄ ምኑ ነው መሪ ጥየቄ ካለ አለ ይላል ከሌለ አይ የለም በእዚህ ምክንያት ነው ብሎ ያስረዳ ምንድን ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ብይን ሰጥተናል እኛ የተመለከትነው እንደተባለው ሀባሽ አለ የለም የሚለው አዎ የሚል መልስ ነው የሚሆነው ወይም የለም ነው የሚሆነው ስለዚህ ጥያቄአችሁን ዋና ጥያቄ አድርጋችሁ አስተካክላችሁ ጠይቁ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር አህመዲን ጀባልስ ምን አደረገ ?
- ያው ወደ እዚያ አህመዲን ጀባል ጋር ከመሄዱ በፊት ከሳቢር ጋር ያው መጨረሻ መዝጊያው ላይ ብዙ ደቂቃዎች እና ብዙ ሰዓት ነው የተናገረው ከእዚያ መጨረሻ ላይ ክርስቲያን ወንድሞቻችን የእኛው ጥያቄ ከጎናቹኝ ሆናችሁ ልታስተጋቡ በጠራናችሁ ጊዜ አክብራችሁ እዚህ ስለመጡ ለእነሱ 3 ጊዜ አላህ ክበር በሉላቸው ብሎ ሕዝቡን አላህ ዋክባር እያስባለ ነበር
- በምን ምክንያት እሺ ጥሩ ቀጥል ?

1285

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላህ ዋከበር እያለ አሁንም ይሰማል ወይ እያለ መስኪዱ ሞልቶ ግቢው ድንኳን ተደንኩኖ ነበር የተሰበሰበው ለእዚያ ሰው አላህ ከበር እያለ መሰማት አለመሰማቱን እያረጋገጠ ውጪ ያለው ሰው ይሰማል ወይ ወይ እያለ 3 ጊዜ አላህ ከበር አስብሏል በመጨረሻም ምርጫችን በመስኪዳችን ብሎ ነው የተናገረው ለማለት ፈልጌ ነው
- ወደ አህመዲን ጀባል ይሂዱ ?
- ያው አህመዲን ጀባልም በተመሳሳይ ሀባሽ ገብቷል ነው ሀባሽ የሚባል እምነትን የሚያበላሽ ቁርአን የጅብሪል ቃል ነው የሚል እስልምናን ከፋፍሎ አደጋ ሊጥል የመጣ መንግስት ጣልቃ አትግባ ቢባል እምቢ ብሎ ጣልቃ እንደገባ አድርጎ ነው ያብራራው አንድ ሰው ሳይጠራ ነው ወይ የሚመጣው መንግስት መቼ ተጠርቶ ነው እኛ መሀል ሊገባ የፈለገው ስለዚህ ለእነ ዶ/ር ሽፈራው ሕገ መንግስቱን እወቁት ብለን እያስተማርናቸው ነው ያለው ስለዚህ ሀባሽ መንግስት እና መጅሊስ እየደገፈው ስለሆነ እኛም ተደጋግፈን ይሄ ሀባሽ የሚባለውን ነገር ከኢትዮጵያ ማጥፋት አለብን ነው ያለው
- ሀባሽ የሚባውን ነገር ከኢትዮጵያ ማጥፋት አለብን ?
- አዎ ከኢትዮጵያ ማጥፋት አለብን
- በምን መልኩ ?
- ያው ማጥፋት አለብን ከተባለ የጥፋት ሁኔታ ያው /ግልፅ ያልሆነ/ ባይብራራም ማጥፋት ማጥፋት ነው
- ምን ባይሆንስ ባይጠፋስ ምን እናድርግ ነው ?
- ሕብረተሰቡ እኮ ሀባሽ መጥቷል በሚል ሴት ወንዱ ትንሽ ትልቁ እኮ ሀሳቡ ተቢታትኖ እስካሁን ድረስ ላለንበት ብጥብጥ የተቀሰቀሰው እና ሕዝቡ የተነሳው እኮ አሁን ሙት ቢባል ለመሞት የተዘጋጀ ዓይነት ሁኔታ ነው የተፈጠረ ያለው
- አለ እንደዚህ የሚባል ኃይማኖት ?
- ሀባሽ የለም ሀባሽ ማለት በመስረቱ ሀባሻ ማለት ሀበሻ ማለት ነው አረብኛው ቃል ሀባሽ አንድ ከሆነ ሀበሽ ይባላል
- የምናመለክተው አለ የተከበረው ፍ/ቤት ከተፈቀደልን
- ተቃውሞ ነው ?

1376

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ተቃውሞ አለ ነኛው ግለሰቡ ያዩትን የሰሙትን ሳይሆን አስተያየታቸውን እየመሰከሩ ነው ያሉት 2ኛ ፍ/ቤቱ ባለፈው ትዕዛዝ ሰጥቷል ብሏል በእዚህ ላይ የኃይማኖት ጉዳይ ነው እያስመሰከሯቸው ያሉት በእዚህ መሠረት የሚሆን ከሆነ እኛም መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ብዙ የኃይማኖት ጥያቄዎችን ስናነሳ ልንከለከል አይገባም ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት ነኛው ምስክሩ የግል አስተያየታቸውን ሳይሆን የሰሙትን ያወቁትን ነው ለነሲሀበኩሩ መደረግ ያለበት ዐቃቤ ሕግ ግን እየጠየቀ ያለው ሰውዬው የሙያ ኤክስፐርት ኤቪደንስ ናቸው ሳይባል አስተያየታቸውን ነው እየጠየቀ ያለው ይሄ ነኛው ሊመዘገብብን አይገባም ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ላይም ደግሞ ሊቆም ይገባል ማለት ነው የተከበረው ፍ/ቤት ኃይማኖታዊ ጥያቄ የሆኑትን የኃይማኖት ጉዳዮችን ደግሞ ሊጠይቅ ሊፈቀድለት አይገባም ለእሱ ከተቀፈለት ቀጥሎ እኛ በምናቀርበው መስቀለኛ ጥያቄ ላይ
- ተቃውሞውን ብቻ ወደ ፊት ስላለው ነገር ?
- አመሰግናለሁ
- መልስ እንሰጥ
- መልስ ስጡበት እስቲ ?
- አሁን ጠበቃውም ያነሳው ነገር የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 137 በሚያዘው መልኩ አንድ ምስክር የሚያስረዳው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚያውቀውን መሆኑ ስነ ስርዓት ሕጉ በግልፅ አስቀምጧል በቀጥታ የሚያውቀውን ተናገረ በተዘዋዋሪ ደግሞ እንዲህ የሚባል ኃይማኖት የለም የውሸት ነው ቅስቀሳው ብሎ ነው ያስረዳው ይሄ ነው እና ምንም ባስያዝነው ጭብጥ መሠረት ስነ ስርዓት ሕጉን ተከትለን ነው እያስመሰከርን ያለነው
- ብይን ሰጥተናል ብይኑ ምንድን ነው ምናልባት ትላንት አልነበሩም ቀደም ሲል የተሰጠው ብይን ዐቃቤ ሕግ አትምራ ነው የተባለው ዋና ጥያቄ እንዲጠይቅ ነው የኃይማኖት ክርክር ተብሎ ትላንትም የሰጠነው ማሳሰቢያ ዛሬም የተባለው ምንድን ነው ምስክሩ ከሚለው ውጪ አንቀፅ ይሄንን ያህል አንቀፅ ይሄንን ያህል የት ቁጥር አለ የሚለው ነገር ነው እሱን ነገር እሱን መሠረት አድርገን አይደለም እኛ የምንወስነው ነገር ግን ምስክሩ በራሱ ያመጣውን ቃል ማብራራት ይገባዋል ስለዚህ አልሀባሽ ብሎ ጠርቷል ከአሁን በፊትም ምስክሩ እንዴት እንደተረዳው እና ምን እንደሆነ ማብራራት የግድ ነው ስለዚህ የተጠየቀውም ጥያቄ ይሄ ነው ከእዚያ ውጪ ሄዶ ነው ስለኃይማኖት ቁርአን ምን እንደሚላ ማስረዳት ትዩስ ምን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ይላል እንዲህ እንዲህ የሚሉ ነገሮች ግን መጨረሻ ላይ ሄደን ሄደን በእሱ የምንወስን ስላልሆነ መሠረታችን ይሄ ሕግ ነው የሚሆነው ስለዚህ ያንን መሠረት አድርገን ነው ትላንት ያነሳነውን ቅድምም የተሰጠው በእዚህ አግባብ ነው ስለዚህ አልሀባሽ ምን ማለት ነው የሚለውን ነገር እንዲያብብራ እዚህ ጋር ስህተት አለው ብሎ ፍ/ቤቱ አልወሰደም ይሄንን መሠረት አድርጋችሁ ጠይቁ

- ምስክር ካቆምክበት ቀጥል ይቀጥሉ ካቆሙበት ?
- ሀባሽ ማለት ሀበሻ ማለት ብዙ ሀበሻዎች ሀባሽ ይባላሉ አንድ ከሆነ ሀበሽ ነው ስለዚህ ሀበሻ የለም ማለት አይቻልም ሀበሻ ሀበሻ ነው ነገር ግን ኃይማኖት አይደለም ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት ስለሌለ ሕብረተሰቡ ሀባሽ አለ ብሎ መቀስቀሱ አግባብ ትክክል እውነት የሆነ ነገር አይደለም
- ግን ምንድን ነው የሚቀሰቅሱት እነዚህ አሁን የጠሯቸው ተከሣሾች ?
- እና ያው ሀባሽ መጥፋት አለበት ነው
- ምንድን ነው ሀባሽ ነው የሚሉት ?
- ሀባሽ የሚሉት አንድ ወቅት ለምሳሌ የእስልምናን እምነት ኮርስ ሊሰጡ ከውጪ የመጡ ሰዎች ነበሩ
- አይደለም እሱን ሳይሆን ተከሣሾቹ ምንድን ነው የሚሉት እርሶ አሁን የተረዱበትን ተናግረዋል ሀበሻ ማለት ነው ብለዋል ተከሣሾቹስ ምንድን ነው ነው የሚሉት ሀባሽ ለተሰበሰበው ሕዝብ ?
- ኃይማኖታችን እያጠፋው ነው ወለድ መብላት ይቻላል ይላል ሴት ሱሪ ለብሳ ማሰገድ ትችላለች ይላል ሰላት ጠዋት እና ማታ ብቻ ነው መሰገድ አለበት ብሏል ቅብላ እየዞረ ነው
- ምንድን ነው ቅብላ ?
- ቅብላ ማለት አቅጣጫ ይዘህ የምትሰግድበት ማለት ነው የስግደት አቅጣጫን ለምሳሌ በሰሜን የምንሰግድ የነበረው ወደ ደቡብ እንደዚህ መቀየር ማለት ነው እንደዚያ እያደረገ ነው ቁርአን የአላህ አይደለም እያለ ነው የጅብሪል ቃል ነው ብሏል ስለዚህ መጅሊስ እና መንግስት ተባብረው ያስገቡት ስለሆነ ኃይማኖታችን ሊጠፋ ነው ተነሱ ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/

1388

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ያው አህመዲን ጀባል ሲያብራራ ከአሁን በፊት ያው የነበሩትን አፄዎቹ ኃይማኖትን ሊያጠፉ በተነሱበት ጊዜ ጠፍቷል ብዙ ከ 10 በላይ የነበሩ /ግልፅ ያልሆነ/ በሕዝብ መነሳት እና የሕዝብ ተቃውሞ ሊወድቁ ችለዋል የሚልም ጭምር ነው የተጠቆመው
- ይቀጥሉ ?
- ሊወድቁ ችለዋል በእዚህ ነገር ላይ ወላ ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሆን አያገባውም አሁን አዲስ ስራ የመፅሔት በቅርቡ የወጣች መፅሔት አለች አገለባብጩ ከአንዴም ሶስቴ አንብቤአታለሁ እስልምናን በ 3 ከፍሎ ወሀብይ ስንይ ሱፊ እያሉ አንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ያብራሩት ነበር እሱን አዲስ መፅሔት ያወጣው ስህተት እንደሆነ እና ትክክል እንዳልሆነ ያየው መሆኑን ለሕብረተሰቡ መግለፁን ነው የሰማሁት በቦታው ስለነበርኩ ማለት ነው
- እና ስለዚህ ይሄንን ብሎ ካለ በኋላ ምን መደረግ አለበት አለ አሁን ስላለፉት ቀደምት መንግስታት ስለመውደቃቸው አነሳ ምን መሆን አለበት ነው የሚሉ ?
- ያለ አግባብ የጫነ
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለ የማረቅድልን ቢሆን
- ምንድን ነው ተቃውሞ
- ሰውዬው እንዲህ ብሏል አለ እንዲህ ብሏል ካለ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ ምን አሉ ከእዚያ በኋላ ምን ይሁን አለ ምን ይደረግ አለ ማለት መንገር ነው ድርጊትን አልገለፁም የተከበረው ፍ/ቤት ፋክትን ነው የገለፁት /ግልፅ ያልሆነ/
- አዎ ምስክሩ የሆነውን የተደረገውን ሰማሁ ያሉትን ማለት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ከእዚያ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ነገር አቶ ብርሃኑ እየነገራቸው ነው ያለው ምን ማለት ነው ከእዚያ በኋላ ምን ይሁን አለ ማለት አክሽን እንዳለ አስመሰለው ማለት ነው ቀጥሎ እዚያ ጋር ስለማቆሙ ወይም ስላለማቆሙ ምስክሩ ሳይመሰክር መሪ ጥያቄ የሚሆንበት ምክንያት ላስረዳ የተከበረው ፍ/ቤት ስለመቆሙ ስለማቆሙ ምንም ኢንዲኬሽን ሳይሰጥ እሳቸው ምን አሉ አሲፍ ድርገት መኖሩን ነገሩ ማለት ነው ከእዚያ በኋላ ነው ምን ይሆናል አሉ ይሄ ፐውርሊ መሪ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ሊመዘገብብን አይገባም በእዚህ ላይ ሊመሰክርም አይገባም አመሰግናለሁ
- ለእዚህ መልክ አለኝ የተከበረው ፍ/ቤት

1389

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መልስ
- ምንድን ነው መልሱ በአጭሩ ነኛ እሳቸው በዝርዝር እኚህ ምስክር አልጨረሱም አንድ 2ኛ እኔ ያነሳሁት ምንድን ነው ስለቀደምት መንግስታት 3ቱ ያሏቸው ቅድም የገለፁዋቸው /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ከገለፀ በኋላ መጨረሻ ምንድን ነው የእዚህ ማጠቃለያው ምንድን ነው ስለዚህ ይሄ መሪ ነው ምን ማለት ነው እና በሪሳ ግልፅ አይደለም ጥያቄው
- ተመልክተነዋል ስለዚህ የመጨረሻው ጥያቄ ምን ይሁን ነው የሚል ምን ይሁን ደግሞ መሪ ጥያቄ ስላልሆነ ዐቃቤ ሕግ ቀጥሉ ብለናል
- የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ እስቲ በእዚሁ ይቀጥሉ እና መጨረሻው ምን መሆን እንዳለበት ምን አለ ይሄንን ይግለፁ ? የሚያስታውሱትን ማለት ነው ?
- ያው አግባቡ ያንን ሁሉ ሕብረተሰብ የተሰበሰበው ኃይማኖት ጠፍቷል ነው ኃይማኖቱ ከጠፋ ተነስ ከተባለ ወዴት ነው የሚነሳው ጣልቃ ገብቶ ተፅኖ ያሳደረውን ክፍል መጣል ነው
- እንዴት በምን ?
- በጅሀድ ነው
- ምንድን ነው ጅሀድ ?
- ጦርነት
- ማን ላይ ?
- የተጫነን ክፍል ኃይማኖቱን ሲያጠፋ ካየ ያንን የሚጫነውን ክፍል ማጥፋት አለብን ማለት ነው በተቻለ ችሎታ ማለት ያው ጅሀድ ሲባል ያው ጦርነት ነው
- ሌላው ቅድም ያሉትን ላስታውሶት እና ሲገልፁ /ግልፅ ያልሆነ/ በሚመለከት ሲገልፁ ከክርስቲያኖች ጋር በተያያዘ ወደ 200 አካባቢ የሚሆኑ ክርስቲያኖች ነበሩ ብለዋል እና እነኚህን ከእዚህ ከአጠቃላይ ከተሰበሰቡት መሀከል 200 መሆናቸውን መገመት ይቻላል እንዴ እንዴት አወቁ ለማለት ነው ?
- የአካባቢው ሰው በደብዳቤ ነው የተጠራው የአስሩም መስኪድ ሕብረተሰብ በያለበት ወደ እዚህ ሕዝቡን አምዛ መስኪድ ጠርቶ እንዲያመጣ መልዕክት ተላልፏል በእዚያ አማካይነት

1390

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የነዐሩም መስኪድ ሕብረተሰብ ሲሰበሰብ ለክርስቲያኖቹም በተለይ እንደገና ተዞሮ በየአካባቢው ተጠርቷል እዚያ አካባቢም ያሉት ከሌላም ቦታ እና ሲጠቀስ በቁጥር ይሄንን ያህል ነው ብዬ በግልፅ መግለፅ አልችልም ግን ከ 200 በላይ ነው ተብሎ ነው የተገለፀ የነበረው

- አለቡ ሲገልፁት ነው አረቡ የሰሙት ማለት ነው አቢ ሌላው ቀድም ሲገልፁ እነኚህ ክርስቲያኖች የጠራናቸው የሚዲያውን ውሸት ለማሳየት ነው ብለው ያው ገልፀዋል የትኛው ሚዲያ ውሸት ነው ለማሳየት እንደዚያ ያለው የትኛው ሚዲያ ማለቱ ነው ወይም የሰሙት ካለ የሚያስታውሱት ?
- ያው ሚዲያው እኮ ይሄ በቴሌቭዥን የሚታየው ማለት ነው ለሕብረተሰቡ የሚገለፀበት
- ማለት ከምን አንፃር ማለት ነው ?
- የሰሙት የተገለፀ ሚዲያ ካለ የሰሙት የተገለፀ ሚዲያ አለ የእዚህ ሚዲያ የእዚህ ሚዲያ የተገለፀ ካለ እሱን ይግለፁት ?
- እሱን አላስታውስም
- አያስታውሱም ?
- አዎ
- አንድ ጥያቄ ልጠይቆት ሰደቃ ለምንድን ነው የሚዘጋጀው በእርሶ እርሶ በሚያውቁት በኃይማኖቱ ለምንድን ነው የሚዘጋጀው ?
- እኔ በማውቀው ሰደቃ ማለት የሚበሉ የሚጠጡ ያጡትን
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን የሚፈቅድልን ቢሆን ሰደቃ ለምንድን ነው
- ምንድን ነው ?
- ሰደቃ ለምንድን ነው የሚዘጋጀው ፒዩርሊ ቁርአን ሊጠቀስ ነው አዲስ ሊጠቀስ ነው እንዲህ ከሆነም ቀጥለን እኛም እንደዚያ እንዲፈቅድልን ነው የሚገባው የኃይማኖት ጉዳይ ነው ፒዩርሊ ሰደቃ ለምንድን ነው የሚዘጋጀው
- ሙስሊም ስጠቡን
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን እሳቸው ምስክሩ ሲገልፁ ክርስቲያኖች በደብዳቤ ተጠርተዋል ፕሮግራሙም ሰደቃ ነው ተብሏል ስለዚህ ሰደቃ ምንድን ነው በኃይማኖቱ ምን ለምን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ዓላማ ነው የሚዘጋጀው ክርስቲያኖች በማን በደብዳቤ እየተጠሩ እዚያ የሚገኙበት እንዲህ እንድትረዱልን ነው እየተባለ የሚነገራቸው ምንድን ነው በምን ጉዳይ ነው ሰደቃ ምንድን ነው በኃይማኖቱ ለምን ዓላማ ነው የሚዘጋጀው ነው

- እሺ ምናልባት ምስክሩ ቀደም ሲል ዐቃቤ ሕግ ያስያዙት ፋክት አለ ክሱ ላይም አለ ይሄ ነገር አንድ ፋክት ነው ይሄ ፋክት ለምንድን ነው የሚዘጋጅ የሚለው ይሄንን ቢያብራሩት ልክ ትላንትና ከእዚያ በፊት በነበረው የኃይማኖት ጥበብ ውስጥ ገብተው ያብራራሉ ብሎ መውሰድ የሚቻል አይደለም በሌላ መንገድ ምስክሩ በሚያውቁት ልክ በእዚያው ልክ እነሱ የሚያብራሩትን እዚያው ይመልሳሉ ከእዚያ ውጪ ምስክሩ ከሚያውቁት በላይ ሲሄድ ነው ክርክሩ እየጦፈ የሚሄደው ስለዚህ እሱ ነው ትክክል ያልሆነው ዐቃቤ ሕግ ትክክል ነው ቀጥሉ ብለናል
- እሺ ምስክር ይቀጥሉ ለምንድን ነው የሚዘጋጀው በኃይማኖቱ ሰደቃ ?
- በኃይማኖቱ እኔም ወደ ኃይማኖቱ ዝርዝር ውስጥ ልገባ አይደለም ሰደቃ ማለት ለተራበ ማብላት ማለት ነው የተራበ ሊበላ ሊጠጣ ያጣን ያለው ሰው ላለው ሰው መስጠቱ ሰደቃ ነው በአጭሩ ሌላ ውስጥ የኃይማኖት ዝርዝር ውስጥ ባልገባ እና በእዚያ መሠረት አሁን ግን በኢሉኑ ጠቅት እዘዩ ኢትዮጵየ ውስጥ ያለው የሰደቃ ፕሮግራም ከኃይማኖቱ ጋር የተገናኘ ሳይሆን ሙስሊሙን ሕብረተሰብ አሁን ለተባሉት ችግር አለ ለተባለው ነገር መቀስቀሻ ሽፋን ለመጠቀም ሰደቃ ተብሎ ተጠራ እንጂ እንደዚህ ዓይነት ሰደቃ የለም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት ዋና ጥያቄ
- ጨረሳችሁ ?
- አዎ
- ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- ምስክር ስምዎን ስላላስታወስኩት ምስክር ልበሎት አቶ ሀይረዲን እርሶ እነዚህ 3ቱን ተከሣሾች ያዩዋቸው የት ሆነው ነው ማለት መስኪድ ውስጥ ነበሩ ወይስ ከመስኪድ ውጪ ሆነው ነው ?
- መስኪድ ውስጥ ነበር
- መስኪድ ውስጥ ነው ሁሉንም በአንድ ቀን ነው ያዩዋቸው ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- በአንድ ቀን ?
- በአንድ ቀን
- ሁሉንም ሰኔ ወር ውስጥ ነው ?
- አዎ
- ጥሩ እስቲ እያንዳንዳቸው አለባበስ በወቅቱ ምን ይመስል ነበር እስቲ ይንገሩን ?
- አለባበሳቸውን አሁን ላስታውሰው አልችልም
- ካላስታወሱ አላስታውስም እያሉ ያልፋሉ ችግር የለም ?
- አላስታውስም
- አላስታውስም እያሉ ስለሆነ ቀጥሉ ሌላ ጥያቄ አላስታውስም ብለዋል ?
- እንዲሉም ስለፈለግን ነው እኮ የተከበረው ፍ/ቤት
- አሉ አልሰሙም ?
- እኮ አይ ልቀጥል ተመሳሳይ ጥያቄ ስላለኝ ?
- እሺ ቀጥሉ
- ሁሉም ቆመው ነበር ወይስ ቁጭ ብለው ነበር ሲናገሩ የነበረው ?
- ትዝ የሚለኝ አቡበከር በወንበር ቁጭ ብሎ መናገሩ ነው
- ወንበር ነበረ ?
- አዎ
- ወንበሩ አካባቢ እስቲ ስላለው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር ማለት መድረክ ተዘጋጅቶ ነበር ?
- አዎ ፊት ለፊት መስገጃው ቦታ ለመድረክ መሪዎች ክፍት ሆኖ ወደ ኋላ ያለው ሕዝብ ወደ ፊት ቁጭ ብሎ እነሱ ወደ ሕዝቡ ዞረው እያብራሩ ስለነበር እኔም ከእዚያው ሰው መሀል የተቀመጥኩ ስለነበር በደንብ አይቼዋለሁ
- በዕለቱ የተናገሩት እነሱ ብቻ ናቸው እንዴ ?
- ሌሎቹም ነበሩ ከእነሱ ቀጥሎ የተናገረ አለ አሁን በትክክል ላስታውሰው [illegible] ስላልቻልኩ ነው
- አዎ ማለት ከእነሱ በፊት ሌላ የተናገረ ሰው አለ ?

ECLN

http://ethiopianlawnetwork.com/

- እኔ ከገባሁ በኋላ የለም እኔ
- እርሶ ከመጀመሪያ ይቅርታ ካቋረጥኩ አልጨረሱም
- ጨርሻለሁ
- እርሶ ከመግባትዎ በፊት እርሶ በመሀል ነው የገቡት ?
- በመሀል ሳይሆን 2 ሰዓት ካለፈ በኋላ ነው የገባሁት ከእዚያ በፊት የነበረውን አላውቅም
- ፕሮግራሙ ስንት ሰዓት ላይ አለቀ ?
- ወደ 9 ሰዓት አካባቢ
- 9 ሰዓት ?
- አዎ
- የተጀመረበትን ያውቃሉ ?
- ከ 2 ሰዓት ተኩል 3 ሰዓት አካባቢ ካለው በግምት ነው በእዚያች ሰዓት ሆን ብዬ በእዚያ ሰዓት አላየሁም እዚያው አካባቢ ነው እኔም ከቤቴ ወደ መስኪድ የሄድኩት
- ተከሣሾቹ 3ቱም አንድ ላይ መድረክ ላይ ቁጭ ብለው ነበር ?
- ከሕብረተሰቡ ቁጭ ይላሉ መድረክ አስተዋዋቂ አለ አሁን በመቀጠል የሚያቀርብልን እከሌ ነው እያለ ስለሚገልፅ አሁን አቡበከር ማብራሪያ ይሰጡናል ብሎ ጋብዞት ነው እንደገና ወደ መድረኩ /ግልፅ ያልሆነ/
- ጥሩ ቅድም ክርስቲያኖችም በደብዳቤ ተጠርተዋል ብለዋል ይሄ የጠራቸው ማን ነው ?
- የሰደቃ ኮሚቴ ተብሎ በማግስቱ እንደሚደረግ ድረስ በመስኪድም ገንዘብ ይዋጣ ነበረ
- አይ የጠራቸው ?
- የጠራቸው
- ደብዳቤ ሲፃፍ እሺ ይቀጥሉ ?
- የሰደቃ ኮሚቴ ተብሎ ነው ከመስኪዱ ኮሚቴ ጋር በመሆን ነው ጥሪ የተላለፈው በዘበኛ ነበር እያዞረ የተሰጠ የነበረው
- ከመስኪዱ ኮሚቴ ጋር ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ደብዳቤው ማህተም አለው ?

1394

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱን አሁን አላስታውሰውም ልብ አላልኩትም
- የሰደቃ ኮሚቴዎችን ያውቃሉ እንዴ በስም ?
- አላውቅም
- አያውቋቸውም ?
- አዎ
- ቅድም ስለሰደቃ ትርጉም ሲሰጡ ነበር ሰደቃ ማለት ድሆችን ማብላት ብቻ ነው እንዴ በእስልምና እርሶ አሁን ቅድም ትርጉም ሲሰጡ ከእዚያ ውጪ ሌላ ትርጉም የለውም ሰደቃ ሰፊ ትርጉም የለውም እንዴ ?
- ወደ ቁርአኑ ቅድም ወደተባለው የኃይማኖት ማብራሪያ ውስጥ አትግባ ስለተባልኩ በእዚያ መግባት እችል ከሆነ ወደ ማብራሪያ መግባት
- ጥሩ አንድ ትርጉም
- ካልሆነ እኔ /ግልፅ ያልሆነ/
- አንድ ትርጉም ስለሰጡ እስቲ እኔ ትንሽ ልጨምርሎት
- አሁን ምንድን ነው የሚያደርጉት የሚያውቁትን ብቻ ነው ስለ ሰደቃ ቅድም የገለፁት ነገር አለ ሰደቃ ብለው ሰደቃ ማሉት ይሄ /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን እሳቸው እየጠየቁ ያለው ይሄ ነው ወይ እያሉ ነው እርሶ የሚያውቁትን ብቻ ነው የማያውቁትን አይገደዱም ?
- ሰደቃ የተራበ ማብላት ነው መስጠት ከእዚያ ውጪ ይሄ የነበረው ሰደቃ ግን የራበውን ሳይሆን ለዓላማ የተጠራ ነው ነው ያልኩት ቅድም ከእዚህ ካልኩት ውጪ አይደለም
- ጥሩ ለምሳሌ ምሳን ከጓደኛ ጋር መብላት ሰደቃ አይደለም እንዴ አይደለም ነው ብለው ማለት ይችላሉ ችግር የለውም ?
- እስቲ ምንድን ነው የመጨረሻ ጥያቄ
- ለምሳሌ ምሳን ከጓደኛ ጋር መብላት ሰደቃ አይባልም ወይ ?
- አሁን እኔ የማውቀው የእዚያን ቀን ተሰብስቦ የተደረገው ሰደቃ ፕሮግራም እንጂ የሰደቃን ዝርዝር ሁኔታ ከሀዲስ እና ከቁርአን ማብራራቱ አሁን የሚጠበቅብኝ ስላልመሰለኝ ነው
- ሌላ ጥያቄ

1395

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቶ ሀይረዲን ሀባሽን ያስገባው መጅሊስ እና መንግስት መሆኑን ተናገሩ ብለዋል ሀባሽን ማን እንዳስገባ ያውቃሉ እርሶ ? ወይም መጅሊስ እና መንግስት ያለማስገባታቸውን ያውቃሉ ?
- በመሰረቱ ሀባሽ የለም የለም እያልኩ ያስገባው ታውቃላችሁ ወይ ማለቱ እኔ
- ስለሀባሽ የሰጡት ትርጉም ከየትኛው የትርጉም መፅሐፍ የወሰዱት ነው ወይስ የእርሶ አስተያየት ነው ?
- የትኛውም ክታብ ላይ አረብኛ ቋንቋ ሀባሽ ማለት /ግልፅ ያልሆነ/ ሀበሻ ነው
- ቋንቋውን አይደለም የጠየኮት ሀባሽ የሚወክለው አስተሳሰብ
- ተቃውሞ አለ
- በቃ በቃ ጥያቄው ይበቃል ተመልሷል ሌላ ጥያቄ ጠይቂ
- ሀባሽ የተባለውን ነገር ላለማድረጉ እንዴት አወቁ ?
- ኧረ ጠበቃ እስቲ ወደ እዚህ መልሰውታል እኮ
- ምን ብለው መለሱ የተከበረው ፍ/ቤት
- አናውቃም አልሀባሽ የሚባል የለም አናውቅም እኔ የማውቀው ነገር የለም አሉ
- የለም አሉ ኦኬ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጡት አስተያየት በኃይማኖት ጉዳይ ላይ በ 3 ነገር አለ ብለዋል ትክክል መሆን አለመሆኑ እንዴት ነው የሚያውቁት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚ አለ
- ምንድን ነው መቃወሚያው ?
- ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጡት አስተያየት እውነት መሆን አለመሆኑን ያውቃሉ ወይ ብሎ መጠየቅ ምንድን ነው የተከበረው ፍ/ቤት ይሄን ምስክር ምስክሩ የጠቅላይ ሚኒስትሩን አስተያየት የሚተች አይደለም እና
- ይበቃል
- እስቲ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲህ ብለው ተናግረው ሕዝቡን ቀስቅሰዋል ላለው ፅ/ቤቱ ጋር አስተካክሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አይደለም ተስቀስ ያለ ?
- አይደለም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተናገሩትን ቃል 3 እስልምና አለ ብለው ሱኒ ሹፊ እና ምናምን የሚባል

1396

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወይ እሱን መፅሐፍ ያውቁታል ከሆነ
- /ግልፅ ያልሆነ/ እሱ ላይ የተባለው ፋክት
- ከመፅሐፍ ያውቁታል ከሆነ እሱን ጥያቄው በእዚህ አስተካክሉት
- እሱ የተባለው ፋክት እውነት ነው እይደለም ነው ፎር ዛት ማተር አሁን እሱን ተናገረ ብለው መስክረዋል የተከበረው ፍ/ቤት አሊጌሽን አፍ ፋክት
- ቆይ ቆይ ይኸሎት እስቲ ለማንኛውም ይጨርሱ እና
- ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመፀሐፍ ላይ ፃፉት ተብሎ አቶ አህመዲን ያቀረበው ነገር አህመዲን ያቀረበው ነገር ምን ስህተት አለበት
- እስቲ ቆይ ምላሽ ስጡበት ነበር የተባለው እናንተ አሁን ብይን ለመስጠት ነበር ማብራሪያ ነው የጠየቅናቸው እናንተን ቀጥታ ወደ ጥያቄ
- ስለዚህ ነኛው ምስክሩ መስክረዋል በዋና ጥያቄ ላይ ይሄ ጉዳይ በየትኛውም መልኩ ቢመሰከር ምስክርነት የተሰጠበት ከሆነ በየትኛውም መልኩ አንስተን ልንጠይቀው እንችላለን የተከበረው ፍ/ቤት አንድ አሁን ደንበኛችን ላይ ደንበኛዬ ላይ እየተመሰከረ ያለው ይሄንን ፋክት ብለዋል ጉዳዩ ደግሞ ከመቀስቀስ ጋር የተያያዘ እስከሆነ ድረስ ይሄ የተናገሩት ነገር እውነት አለመሆኑ ሰውዬው ሊያስረዱ ካልቻሉ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አሁን ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተናገሩት በፍፁም ስህተት ነው ስህተት መሆኑን አንስተው ተናግረዋል ሰውዬው አዎ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አዎ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተናገሩት
- ቆይ ቆይ አሁን ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተናገሩትን አይድገሙ እሱ ችግር የለውም አሁን ዋናው ጥያቄውን ብቻ ጥያቄ ያነሱት እርሶ ጠቅላይ ሚኒስትር ያሉት ነገር እውነት ነው ውሸት ነው ነው እያሉ ?
- አቪየስሊ አዎ

1097

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- /ግልፅ ያልሆነ/
- ተፅፏል 2ቱም ጥያቄ ነው ተፅፏል አልተፃፈም እውነት ነው ውሸት ነው ፎር ዛት ማተር ተብሎ ከሆነ በመፅሔት ያለ ከሆነ እሱን ነው የደገመው ማለት ነው እውነት ነው ውሸት ነው ተፅፏል አልተፃፈም ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- የግራ ቀኛችሁን መቃወሚያ ተመልክተናል እንደተመለከትነው ምስክሩ ቀደም ብለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፃፉት ፁሑፍ አለ እሱን በመፅሔት ላይ ፅፈዋል ብለው ተከሣሾቹ ይሄንን ያወሩ ነበር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተናገሩት ብለው ነካ አድርገው ያለፉት ነገር አለ ይሄንን ዘርዝረዋል ነገር ግን አሁን እዚህ ጋር የሚነሳው ነገር ምንድን ነው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉት እና የፃፉት ነገር ትክክል ነው ትክክል አይደለም የሚለው ይሄ የመመለስ ግዴታ የለባቸውም አንድ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መፅሐፍ ነበር እዚያ አካባቢ ወይ ይሄ ተገቢ ጥያቄ ነው ይሄንን ልትጠይቁ ትችላላችሁ ከእዚያ ውጪግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉት የጠቅላይ ሚኒስትሩን ኢንቴንሽን ወይም ኃሳብ ወይም ትክክል ነው ትክክል አይደለም የሚለው ምስክሩ የመመለስ ግዴታ የለባቸውም ከእዚያ ውጪ ግን እርሶ ምናልባት ቀደም ሲል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉት በፍፁም ውሸት ነው የሚሉት ይሄ የክርክር አካል አይደለም ይሄንን ያስተካክላሉ እሱን አስተካክለው ይቀጥሉ
- አቶ ሀይረዲን የተባለው ነገር በአህመዲን ጀባል የተነገረው እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሉት የተባለው ነገር የተፃፈ ነው የተፃፈ አይደለም እንዴት አወቁ ?
- አዲስ ራዕይ መፅሔት አለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንድ ወቅት ስለ ሀባሽ ስለተለያዩ ነገሮች በተጠየቀው ነገር ላይ ማብራሪያ የሰጡባት መፅሔት ናት ያቺን መፅሔት ያብራራችው ትክክል አይደለም ብሎ ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- ያቺ መፅሔት ላይ የተባለችዋ ነገር ግን ነበረች አልነበረችም እርሶ መፅሔቷን አይተዋታል አላዩዋትም ?
- አይቼአታለሁ
- ምን ትላለች ?
- ያው መፅሔቷ የምትለው ስለ እምነት መሠረታዊ እምነቱ ምን እንደነበረ ጥንት እምነት በእስልምና የሚለው ሰለፊ እና ወሀቢ ምን የሚል ዝርዝር ያለ ነው አሁን በሰፊው በቃሌ
- አያስታውሱትም ማብራሪያ የተሰጠበት ነው ?

1397

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ማብራሪያ የተሰጠበት
- በማን በኃይማኖት ኤክስፐርት ነው ?
- እንደግለሰብ እኮ አይደለም መፅሔቷ የምትወጣው
- አይ እንደግለሰብ ወጣች እልወጣችም ሳይሆን በማን ነው ማብራሪያ የተሰጠው ?
- ያው መፅሐፉን አዲስ ራእይ ብለውታል አዲስ ራእይ የሚለው መፅሐፍ /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም ስለጅሀድ /ግልፅ ያልሆነ/ ማስወገድ አለብን የለብን ስለጅሀድ ትርጉሙ ይሄ ነው የሚለውን ነገር ወይም እዚያ ጋር እርሶ ተናገሩ የሚሏቸው ሰዎች ጅሀድን የገለፁበት መልክ የእርሶ አረዳድ ነው የጅሀድ ትርጉም ነው ?
- የእኔ የግምት አረዳድ ሳይሆን ካብራሩት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው የተናገርኩት
- ጅሀድ ትርጉ አንድ ነው ብዙ ነው ?
- ብዙ መሆን አለመሆኑ ሳይሆን
- ብዙ ነው አይደለም ነው ጥያቄዬ ?
- ጅሀድ ጅሀድ ነው ያው ጦርነት ነው
- እንዴት ጦርነት ሊሆን ይችላል ጅሀድ ?
- በቃ ልክ ነው አሁን ቅድም በገለፁት አግባብ እሳቸው የሚያውቁት ይሄንን ነው
- ስለዚህ የእርሶ አረዳድ ነው ማለት ነው ?
- የእኔ አረዳድ ሳይሆን ጅሀድ ጦርነትም ነው
- እሺ /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ እነሱ ሲያብራሩ ጅሀድ ካሉ በኋላ ስለ ጅሀድ ጥቅም ከተናገረ በኋላ አንድ ሰው መታሰርም መሞትም ፀጋ ነው ካለ ምን ማለት ነው ስለዚህ ከእዚህ አኳያም የጅሀዱ ማብራሪያው መጋደል መሞት መሆኑን የሚያሳይ ስለሆነ /ግልፅ ያልሆነ/
- መታሰርም መሞት ማለት ነው የጅሀድ ትርጉም ከሆነ የዘለለ ነው ወይ ፋክት አይደለም ወይ ?
- መቃወሚያ አለ የተከበረው ፍ/ቤት

1099.

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን ተመልሷል ከእዚህ በላይ ምን ይመለሳል አሁን እሳቸውም በሚያውቁት የሰሙትን የሚያውቁትን መልሰዋል አሁን ከእዚህ በላይ ምን ያመጣሉ ስለጅህድ መልሰዋል አጠቃላይ መለሱ የሚያውቁትን መለሱ ከእዚህ በላይ ምን ያምጡ አሁን
- አይ መለሱ ማለት እኮ ሰዎች መጋደልም መሞትም ነው ያሉት ሲል የእሳቸው ትርጉም ከመሆን ይዘላል ወይ የተከበረው ፍ/ቤት
- ምንድን ነው ፍ/ቤቱ የሚመዝነው ምስክሩ የሚያውቁት ይሄንን ነው ትክክል ነው ትክክል አይደለም እንግዲህ ወይ እናንተ በኋላ የምታመጡት ሊሆን ይችላል
- እሺ እቀበላለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም እንደዚህ ዓይነት ሰደቃ እርሶ እኔ አይቼ አላውቅም ነው እንደዚህ ዓይነት ሰደቃ የለም ነው ምንድን ነው ያሉት ወይስ ከምን መነሻ ነው እንደዚያ ሊሉ የቻሉት ይሄ የእርሶ አስተያየት ነው ስለሰደቃ ያለው ማለት ነው ወይስ ፋክት ነው እውነት ነው በምንስ ነው እውነት የሚሆነው ?
- ሰደቃ ማለት ማብላት ነው
- ጥያቄዬ ገብቶታል ምስክር አሁን ቅድም ስለሰደቃ ሰደቃ እንዲህ ነው እንዲህ ዓይነት ሰደቃ አይቼ አላውቅም ማለት ይሄ ምንድን ነው የሚያመለክተው ስለ ሰደቃ ነው የሚያመለክተው ስለ እርሶ ነው የሚያመለክተው እርሶ እንዲህ ዓይነት ሰደቃ ያለማየትዎ ሰደቃውን ትክክል መሆኑን ለምን ያስቀረዋል ?
- ሰደቃ ቅድም ባልኩት አግባብ ነው በመሰረቱ የራበውን ማብላት ሆኖ እያለ ይሄንን ከ 10 በላይ በሬ አርዶ ሕብረተሰቡን ሰብስቦ አብልቶ ወደ ቤት መሄድ አንድ ነገር ነው ግን
- በቃ በቃ
- አመሰግናለሁ አቶ ሀይረዲን ቅድም በደብዳቤ ነው የተሰራው ብለዋል በደብዳቤ የጠራው የመስኪዱ ኮሚቴ ነው ወይስ እነዚህ ሰዎች አሁን አህመዲን አቡበከር እና ሳቢር ያሏቸው ማን ነው የጠራው በማን ፊርማ ነበረ ?
- እሱን ቅድምም ብዬአለሁ ወረቀቱ ማህተም መኖሩ እና ፊርማውን
- እሺ በመስኪድ ኮሚቴ ነው ወይስ በእነዚህ ሰዎች ነው የተጠራው ይቺን ብቻ ወይ የእነሱ ነው ወይ አይደለም የሚውን /ግልፅ ያልሆነ/ ?ዥ

1400

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በጋራ ነው ማለት ይቻላል ለምን መነሻዬ ነፃ ሰደቃ ለማድረግ ማታውኑ ከተለያዩ ቦታ የመጡ የሰደቃ አስተባባሪ ኮሚቴዎች በሚል በእስፒከር እስማ ስለነበር ግን ደብዳቤው ሲበተን ግን በዘበኛም አዛን በሚልም ሰው በየአቅጣጫው ነው ደብዳቤ ሲበትን የነበረው
- የመስኪድ ኮሚቴዎች ናቸው ማለት ነው እነዚያ ?
- ኮሚቴው ሲበትን አይደለም እኔ ዘበኛው መሳተፉ ያው የኮሚቴም እውቅና አለው ብዬ ኮሚቴውም አብሮ ተሳትፎበታል
- በወቅቱ ከተጠሩት መካከል የመንግስት ባለስልጣናት ነበሩ የተጠሩ ?
- አላየሁም
- ቅድም ኮርስ ሊሰጡ የመጡ ሰዎች ነበሩ ብለዋል ከየት ሀገር ነበር የመጡት ቅድም ከሀባሽ ጋር ተያይዞ ለምን ተነሳ ሲባሉ ኮርስ ሊሰጡ የመጡ ሰዎች ነበሩ ብለዋል እነ ማን ነበሩ እነዚያ ሰዎች ስንት ነበሩ ?
- አንድ 3 የማስታውሳቸው አሉ ስማቸው አላውቅም
- ከየት ሀገር ነው የመጡት ?
- ከሊባኖስ
- ከሊባኖስ ነው የመጡት ?
- አዎ
- ለማን ነበር ኮርሱን የሰጡት ?
- ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ አንዳንድ ችግር ተፈጥሯል ተብሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ከእስላም እና ከክርስቲያን እስልምና እና ክርስትና የሚያጋጩ
- /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ነው
- ለምን ያህል ሰው ነበር የተሰጠው ?
- አይ እየመለሱ ነበር እሷን ይጨርሱ እና
- ይቀጥሉ ምናልባት ጥያቄውን ለማስታወስ ፈልጌ ነው ቀጥሉ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ማለት 3 ሰዎች ያህል ከሊባኖስ መጥተው ስልጠና ሰጥተዋል ብለዋል ለምን ያህል ሰው ነበር የተሰጠው የት ነበር ስልጠናው የተሰጠው ?

1401

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆይ ቆይ አቡን ጥያቄ ሌላ ነው ቀድሞ የመለቡተ አነዚያ ሰዎች በየተ ነው የመጡተ ነው የመጡበትን ቱናግረዋል ?
- አዎ
- ምን ነበር የሚያስተምሩት /ግልፅ ያልሆነ/ ከእሱ በኋላ ሌላ
- ምንድን ነበር
- በኢትዮጵያ ውስጥ በሙስሊሙ እና በክርስቲያኑ መሀል የእምነቱን ሁኔታ ጠንቅቆ የማያውቁ ሰዎች ግጭት እየፈጠሩ ብዙ ሰዎችን ከመንግስትም የመላተም ሁኔታ እና ከሕብረተሰቡም ከክርስትና እምነት ተከታዮችም የሚያጋጭ አብሮ መሳተፍ እንደሌለ በክርስቲያኖች አብሮ በዓል ማክበር እነሱ ሰላም ማለት አግባብ አይደለም በሚል ሀገራችን ላይ ችግር የተከሰተ ነበር በእዚያ አግባብ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ትክክለኛውን እምነት ጠንቅቆ እንዲያውቅ በደንብ አድርጎ ተረድቶ እንዲሄድ አሎማዎቹ ተሰብስበው የነበረውን ቀደም ሲል የነበረውን እምነት ሊያሰለጥኑ ኮርስ እንዲሰጡ በመጅሊሱ አማካይነት
- በመጅሊስ አማካይነት መጥተው ነው የሰጡት ?
- አዎ
- ማለት ክርስቲያኖቹም ነበሩ በሬጠናው ላይ ሠይስ ሙስሊሞች ብቻ ናቸው ?
- ሙስሊም ብቻ ነው
- ሙስሊሞች ብቻ ናቸው ?
- አዎ
- ብዛታቸው ምን ያህል ነው ?
- አላውቀውም
- ለምን ያህል ጊዜ ነው የተሰጠው በቀናት በወራት በስንት ጊዜ ?
- እሱን አላስታውስም
- እርሶ ስልጠናው ላይ ነበሩ ?
- አዎ
- ማለት ስንት ጊዜ ነው ስልጠናው የተሰጠው አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ?
- አላስታውስም ብለዋል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ ቀኑን ነው መጀመሪያ ለስንች ቀን ተሰጠ ለአንድ ወር ነው ለ 15 ቀን የሚውን ነበር የጠየኳቸው ስልጠናው ላይ ከነበሩ ለስንት ጊዜ ነበር ስልጠናው የተሰጠው ?
- እኔ የተሳተፍኩበት ከ 10 ቀን በላይ ነው
- ከ 10 ቀን በላይ ነበረ ?
- አዎ
- በትክክል ስንት እንደሆነ አንድ ጊዜ ጊዜ ብቻ ነበር የተሳተፉት ?
- 2ቴ ተሳትፌአለሁ
- 2 ጊዜ መቼ እና መቼ ነበር ጊዜው ?
- እስቲ ቆይ ቅድም ምናልባት ነክተው ነው የተውት ምስክሩ ስላነሳው ነው ዝም ያልናቸው እንጂ ዐቃቤ ሕግ በዋና ጥያቄ አላነሱም
- ይበቃኛል የተከበረው ፍ/ቤት ጨርሻለሁ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር ቅድም በሰጡት ምስክርነት ላይ ከተደረገው ቀደቃ ላይ ክርስቲያኖች ነበሩ ብለዋል አይደል ትክክል ከሆንኩ አዎ ይሉኛል ካልሆነ አይደለም ይሉኛል ክርስቲያኖች ነበሩ ብለዋል ?
- ብለዋል እሱ ላይ የሚያነሱትን ጥያቄ
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት
- እሱ ላይ የሚያነሱ ጥያቄ ያንሱ ብለዋል እሳቸው
- እኮ መስቀለኛ ስለሆነ /ግልፅ ያልሆነ/ እያስደረኩ መሄድ ፈልጌ ነው
- እኮ ልክ ነው አሁን ብለዋል እሱ ላይ ልትጠይቁት ያሰባችሁት ነገር ስህተት መሆኑን ከሆነ ስህተት የሆነውን ነገር /ግልፅ ያልሆነ/
- ነበሩ አይደል ክርስቲያኖች ?
- አዎ
- እሺ አመሰግናለሁ ሰደቃ ለክርስቲያን ማድረግ ይቻላል አይደል በእስልምና ኃይማኖት ቅድም ካሉት አንፃርም ቢሆን ይቻላል አይቻልም ?
- ይቻላል
- እሺ አመሰግናለሁ ግን በእዚህ መልክ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በቃ አይ መልሰውልናል ችግር የለም ቅድም ሲመስክሩ ተከሣሾቹ ሰደቃ በተደረገበት አካባቢ ነዋሪ አይደሉም አይደል?
- አዎ እዚያ መሆናቸውን አላውቅም
- ነዋሪ አይደሉም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም ሲነግሩን የሰደቃውን ፕሮግራም ያዘጋጁት የአካባቢ ኮሚቴ እና የመስኪዱ ጥበቃ በጥሪ አማካይነት ነው ክርስቲያኖችም ሲጠሩ የነበሩት በደብዳቤ አማካይነት ዘበኞቹ ናቸው ነው አይደል ያሉት የአካባቢው ኮሚቴ ነው ሰደቃውን ያዘጋጀው ነው ያሉት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ ኮሚቴው ሳይሆን
- በቃ ይበቃል አልተመለሰም እንዴ
- በግልፅ አልተመለሰልኝም
- አላልኩም አሉ እርሶ ሌላ ጥያቄ ሊሄዱ ሲሉ ነው ይበቃል ያልኳቸው
- የተከሰሱ ሰዎች በእዚህ አካባቢ ላይ ነዋሪ ካልሆኑ በአካባቢው ሰው ተጋብዘው ነው አይደል ሰደቃው ላይ የተገኙት ?
- በአካባቢው ተጋብዘው ሳይሆን ሰደቃውን አዘጋጁቹ /ግልፅ ያልሆነ/
- እርሶ በምን አወቁ ቅድም ኮሚቴው ስለማዘጋጁቱ አላውቅም ብለዋል እነሱ ስለማዘጋጁታቸው በምን አወቁ ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- /ግልፅ ያልሆነ/ መቃወሚያ
- ምስክሩ ያላሉትን ተቃራኒ ነው ምስክሩ ያሉትን መድገም ካለብኝ ልድገምላችሁ ግን አላሉም ምስክሩ አላሉም ምስክሩ ካሉት ተቃራኒ ነው አሁን
- እኮ ምንድን ነው እሷን ቃል ብቻ
- ምስክሩ ያሉት በ80 መስኪዶች ሰደቃ እያዘጋጁን ነው ብለዋል ኮሚቴዎቹ ብለው ነው የመሰከሩት አሁን የተከሣሽ ጠበቃ ደግሞ የሚሉት ቅድም ሲመሰክሩ እኔ ይሄንን ሰደቃ ማን እንዳዘጋጀው ኮሚቴ ያዘጋጀው ማን አላውቅም ብለዋል ብለው ነው አሁን ደግሞ ጠበቃው የሚጠይቁት ስለዚህ ተቃራኒ ነው

1404

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መልስ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ቦ 80 መስክ ዴቹ ውሰጥ ፕሮግራም ተዘጋጅቷል ያሉትን አዎ ብለዋል ነገር ግን እሳቸው አሁን እኚህ ምስክር በሚመሰክሩበት መስኪድ ላይ የተደረገውን ፕሮግራም በተመለከተ አንድም ኮሚቴው ነው ያደረገው የመስኪዱ ኮሚቴ ነው ያደረገው ብለው መስክረዋል አሊያም አላውቅም ብለው ነው የመሰከሩት ይሄ ሁላችንም የሰማነው ነው ስለዚህ ይሄንኑ የማያውቁትን ነገር አላውቅም ብለዋል ብለው ኮንፈርም ማስደረጉ ምኑ ላይ ነው ችግር ያለው ጥያቄ

- ላብራራ የተከበረው ፍ/ቤት
- ብይን ሰጥተናል ቀደም ሲል ምስክሩ እዚህ ከያዝነው /ግልፅ ያልሆነ/ ሰደቃውን የጠራው ኮሚቴው ነው የሚል አስቀምጠዋል ጥያቄውም በእዚህ አግባብ የተነሳ ነው ትክክል ነው ብለናል ነገር ግን ጠበቃው ከጥያቄው የሚያስተካክሉት ነገር ምንድን ነው ትላንት የሰጠነው ማሳሰቢያ ላይ ዛሬም አልታረመም ብዙ ነገር ተናግሮ ኮንፈርም እንዲያደረግ ብቻ አይደለም ምናልባት መሪ ጥያቄ ሁል ጊዜ ምስክር በመሪ ጥያቄ ብቻ ነው በእዚያ ታጥሮ ይሄ እውነትን አያመጣም ጠበቃው ብሎ ብሎ ብሎ መጨረሻ ላይ ኮንፈርም የሚያደርግ ከሆነ ትላንት እንዳልነው ከመርካቶ ተነስቶ እስከ ሀያት ድረስ የተደረገውን ነገር የስ አር ኖ ብሎ ኮንፈርም የሚያደርግ ከሆነ አያት ያለችዋን ብቻ ነው ኮንፈርም የሚያደርገው ከእዚያ ወደ እዚያ ያለውን ይረሳዋል ስለዚህ ፍ/ቤቱ መጨረሻ ላይ ሄዶ ሄዶ የሚመዝነው ጠበቃ ያለውን ነው ማለት ነው ስለዚህ አንድ አንዷን ጥያቄ እየጠየቃችሁ መልስ ብቻ ነው ከምስክሩ መጠበቅ ያለባችሁ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር ስለዚህ በወቅቱ በእዚያ መስኪድ ውስጥ ንግግር ያደረጉ ሰዎች የአካባቢው ሰው ካልሆኑ ፕሮግራሙን ካላዘጋጁ ተጋብዘው ነው ማለት ነው አይደል ?
- አሁን የተናገርኩት አረሳሁትም ኮሚቴ ያልኩት የሰደቃ ኮሚቴ አልጠራም አላልኩም ይሄንን ጥሪ ያስተላለፉት አሁኑ መልዕክቱን የሚያስተላልፉ የነበሩ ሰዎች ይሄንንም በ 80 መስኪድ በላይ በሀገራችን ከምናደርገው አንዱ ነው ብለው የገለፁት እነሱ እኮ ነው አስተባባሪ የመስኪድ ኮሚቴ አይደለም ነው እንጂ የምለው የሰደቃ ኮሚቴ እና የመስኪድ ኮሚቴ ይለያያል የመስኪዱ ኮሚቴ ግን ዘበኛው እነሱ ለቀሰቀሱት ሰደቃው ደብዳቤ ያሰገድረቡ ላይ ዘበኛ ተሳትፎበታል እያልኩ ነው ያለሁት

1405

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አመሰግናለሁ ደብዳቤውን የፃፈው የመስኪዱ ኮሜቴ ነው ?
- እሱን ነው ቅድምም አብራርቼአለሁ ማህተሙን ማን የፃፈው መሆኑ ደብዳቤ መበተኑን ልወቅ እንጂ እሱን በደንብ አድርጌ /ግልፅ ያልሆነ/
- ቀጥሉ
- ስለዚህ እነሱ ስለመጥራታቸው አያውቁም ማለት ነው ? እነሱ የተከሰሱ ሰዎች ስለመጥራታቸውም አያውቁም ማለት ነው ደብዳቤውን ካላዩ ?
- ጠርተዋል
- እስቲ ጠበቃ ቅድም የተሰጠው ማስጠንቀቂያ አለ በግልፅ ይሄ የታለፈ ይመስለኛል እና እራስዎን ኮንኩሉድ እያደረጉ ነው መስክሯል ምስክሩ አሁን ያነሱት ጭብጥ ላይ በግልፅ የመሰከሩት ምንድን ነው ሰደቃ ኮሚቴዎች አሉ ተጠርቷል ከተከሣሾቹም የተወሰኑ ሰዎች ቅድም በስም የጠሯቸው ማለት ነው ከእዚያ ውስጥ በተለይ አንድ ሰው እዚያ ነበረ 10 መስኪዶች አዘጋጅተናል እንደዚያ ዓይነት ተመሳሳይ ስለሚሉ ብለው መስክረዋል ቅድም እና የአሁኑ ኮንኩሊዥን ከእዚያ ጋር የሚሄድ አይደለም ሌላ ጥያቄ
- አመሰግናለሁ በሰደቃ ፕሮግራሙ ላይ ክርስቲያኖች እንደነበሩ ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል አንድ ሰው ክርስቲያኖችን ሰብስቦ እስላማዊ መንግስት ላቋቁም ነው ይላል እንዴ አይልም አይደል?
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን በጠበቃው የተባለው ነገር በዋና ጥያቄ እኛም አልጠየቅንም ምስክሩም አላሉም እስላማዊ መንግስት እንመሰርታለን የሚል የተከሣሽ አለ ተባለ
- ላስተካክለው የተከበረው ፍ/ቤት
- አይ ይሄንን ጥያቄ እናንተ ምላሽ ሳትሰጡበት አልተነሳም
- አዎ ላስተካክል
- ስላልተነሳ ድካም ነው ይሄንን ጥያቄ እለፉት እና ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት በስህተት ነው ጅሀድ የሚለውን ለመናገር ብዬ ነው ጂሀድ የሚለው ደግሞ ሁላችንም ሰምተነዋል ምስክሩም ያሉት ነው ስለዚህ ጅሀድ በተመለከተ የሚያብራራበት ሁኔታ አለ የለም አይኖርም ነው እኔ እያልኩ ያለሁት ምስክሩ ደግሞ የሚሉትን ይበሉ

1406

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንዴት
- አሁን የሰደቃ ፕሮግራም ላይ 200 የሚሆኑ ክርስቲያኖች ነበሩ ብለዋል ከተከሰሱት ውስጥ ስለጅሀድ እያብራሩ ነበረ ብለዋል ስለዚህ ክርስቲያኖችን ሰብስቦ ወይም ክርስቲያኖች ባሉበት
- ባሉበት ነው ወይ ይሄንን ያወሩት ነው ?
- አዎ የሚል የለም ስለዚህ አይባልም ይባላል ነው
- አይደለም እነሱ እያሉ ነው ወይ ይሄንን ያወሩት ትክክለኛ ጥያቄ ነው ይሄ ምንም እንትን የለውም ስለ ቅድም የተነሳው ነገር ስላልተነሳ ነው ስለዚህ አሁን እነሱ ባሉበት ነው የሚል ከሆነ ጥያቄው ትክክል ነው ቀጥሉ
- እነሱ ባሉበት ነው ይሄ ነገር ሲባል የነበረው ?
- ምኑ
- ክርስቲያኖች ባሉበት ነው ስለ ጅሀድ እርሶ ያሉት ማብራሪያ የተሰጠው ?
- አዎ
- ስለዚህ ክርስቲያኖቹ ምን አሉ እነሱንም ጭምር ነው ወይስ ለሙስሊሙ ብቻ ነው ጅሀድ በተመለከተ?
- እነሱን በማብራሪያ ላይ ቅድም ባልኩት ላይ አለ ለእናንተም የራሳችሁ ጥያቄ አላችሁ ለእኛ ሙስሊሞች ጥያቄ አለን የ2ታችንም በጋራ ጥያቄአችን ጎን ለጎን ሆነን ማሰማት አለብን ከጎናችሁ ቆማችሁ አስተጋቡልን ነው እንጂ ሊበሉ አይደለም በልቶ መሄድ እና ለመብላት ተጠርቶ ለቅስቀሳ መጠራት ይለያያል
- ግልፅ ነው ይቀጥሉ
- ቅድም ሲመሰክሩ አህመዲን ጀባል ዶ/ር ሺፈራው ሕገ መንግስቱን ይወቁት ብሏል የሚል ነገር ተናግረዋል ዶ/ር ሽፈራው ሕገ መንግስቱን ይወቁት ወይም ይተግብሩት የሚል ነገር ተናግረዋል ብለዋል ይሄንን ብለዋል አይደል ?
- አዎ ይተግብሩ ሳይሆን
- ይወቁት
- ቀጥሉ ይመልሱት ችግር የለውም

1407

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሕገ መንግስቱ መንግስት ጣልቃ እየገባ ነው ሕገ መንግስቱን ለእነ ዶ/ር ሺፈራው እያስተማርናቸው ነው ሳይጠራ ነው ወይ የሚገባው ሰው አሁን ሲጠራ ነው እንጂ ና ተብሎ ሲጠራ ነው እንጂ የሚመጣው መንግስት ማን ጠርቶት ነው የሚመጣው ብሎ ነው
- ስለዚህ በሕገ መንግስት መሠረት ይሰራ እያሉ ነው ማለት ነው ?
- በሕገ መንግስት
- ቆይ እሱ ይሽውሎት አሁን ጥያቄውን ይጠይቁ
- ጣልቃ ገብቷል እያለ እኮ ነው ያልኩ
- ቆይ አሁን ይሄ ጥያቄ ስለዚህ ብለው ኮንኩሉድ ኤደረጉት እርሶ አሁን
- የተከበረው ፍ/ቤት አዎ ካሉ
- አልተደረገም ገና ነው ያዳምጡ አልተደረገም ይሄ ነው.ይሄ ማለት /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ ላይ ገልብጦ መተርጎም ነው እሱን አትተርጉሙት በቀጥታ ምስክሩን ደግማችሁ ጠይቁ ይሄ ማለት ብላችሁ የሚመራውን ነው እንጂ ሌላ /ግልፅ ያልሆነ/ አዲስ አታምጡ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት በእዚያም ተባለ በእዚህ ስለ ሕገ መንግስቱ ተነስቷል ሕገ መንግስቱ ወይ ጣልቃ አይግቡብን ብለው ቢሆንም ወይ ይከብርም ብለው ቢሆንም ወይም ይወቁትም ቢሆን ብለው የሕገ መንግስቱ ስም ተነስቷል አይደል ?
- አነሳሱ ነው
- ተነስቷል አይደል ግን የሕገ መንግስቱ ስሙ ተነስቷል እዚያ መድረክ ላይ ?
- ግልፅ ነው ጠበቃ እኮ
- ተነስቷል
- /ግልፅ ያልሆነ/ ያው አለ እዚህ ላይ የሚጠይቁትን ይቀጥሉ
- አንድ ሰው የተከበረው ፍ/ቤት እሺ አንድ ሰው በአንድ ጊዜ በአንድ መድረክ አንዴ ሕገ መንግስት ይከበር ሌላ ጊዜ ጅሀድ አውጀናል እንዴት ሊል ይችላል ምስክር ይሄንን አብራሩ?
- ልመልስ ያሉት መንግስት ጣልቃ ገብቷል ነው ስለዚህ ሕገ መንግስቱን እያስተማርነው ነው ስለዚህ ጣልቃ ከገባ መንግስት ጣልቃ ገብቷል ተነሱ ነው እኮ ዓላማው
- እኮ ተነሱ ሕገ መንግስቱ እንዲከበር ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይደለም መንግስት ጣልቃ ስለገባ ኃይማኖት እየጠፋ ስለሆነ መነሳሳት
- ቀጥል
- አመሰግናለሁ አቶ ኃይረዲን ቅድም በሰኔ ወር ነው 2004 ዓ.ም ነው ብለው ነበር ሰኔ ወር ሲጠየቁ ጊዜውን አያውቁም ነበር ጊዜውን መጀመሪያ ላይ ነው ሰኔ መጨረሻ መሀከል የትኛው ላይ ነበር ቀኑ ማለት ነው ጊዜው ሰኔ ወር ብለዋል መጀመሪያ መጨረሻ ወይስ መሀል አካባቢ ?
- የሚመስለኝ ከ 10 ቤቶች አካባቢ ከመጀመሪያው እስከ መሀል ባለው አካባቢ ይመስለኛል
- ከ 10 እስከ 15 ?
- ከ 10 እስከ 17 ባለው ጊዜ ነው የሚመስለኝ እርግጠኛ አይደለሁም
- ቀኑ እርግጠኛ አይደሉም ?
- አዎ
- ቅድም አቡበከር መድረክ አስተዋዋቂ ነበር ብለዋል ሌላ መድረክ አስተዋዋቂ ነበር ከአቡበከር ውጪ ?
- መድረክ አስተዋዋቂ ነበር አላልኩም መድረክ መሪ ነበረ ነው ያልኩት
- መድረኩን የመራው አቡበከር ነው ?
- አዎ አስተዋዋቂ እሱን ጋብዞት
- አስተዋዋቂው ማን ነው ?
- እሱን አላወኩትም በሰዓቱ
- ቅድም ሰደቃውን ያዘጋጀው ልድገመው እና የአካባቢው ሕብረተሰብ ሁሉ ገንዘብ ሲያወጣ አይተዋል መስኪድ ውስጥ እርሶ ቅድም ስለተናገሩ ልክ ነኝ ?
- ማዋጣት
- ሲያወጣ አይተዋል አይቼአለሁ ብለዋል ?
- እኔ እዚያ ውስጥ አልነበርኩም
- አላዩም ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሰደቃ መጀመሪያ የሰደቃ ቀን ነው የተገኘሁ ብዬአልሁ ከእዚያ በፊት ግን በእስፒከር ተከፍቶ ማታ ማታ ሰደቃ ልናደርግ ነው ተብሎ በጨረታ መልክ እየተደረገ ማታውን የሚቀሰቅስ ሰው እንደነበረ በእስፒከር ሰምቼአለሁ
- ማን ነው የሚቀሰቅስ የነበረው ?
- የሰደቃ ኮሚቴ /ግልፅ ያልሆነ/
- ስሙን ያውቁታል ሰውዬውን ?
- አላውቀውም በእነሱ አማካይነት የተዘጋጀ
- የሀምዛ መስኪድ አባል ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ?
- አላወኩትም
- /ግልፅ ያልሆነ/ ናቸው ?
- ያው አላወኩም ካለ ይበቃል
- አይ መገመት ይችላሉ ብዬ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ስለዚህ አያውቁትም ቅድም ሀባሽ የሚሉት ከሊባኖስ መጥቶ ስልጠና የሚሰጡትን ነው ብለው ነበር ከእዚህ በፊት
- መቃወሚያ አለ የተከበረው ፍ/ቤት
- ምንድን ነው መቃወሚያችሁ
- ያው እሳቸው ምስክሩ ደጋግመው ተናግረዋል ሀባሽ የሚባል ነገር አላውቅም ብለዋል ስልጠና ለሙስሊም ሕብረተሰቡ ከሊባኖስ መጥቶ ስልጠና ሰጥቷል ብለዋል እንጂ ሀባሽ የሚባሉ ብሎ እንደዚህ ዓይነት አሁን ጠበቃው እንደጠየቁት አይደለም እሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ግልፅ ነው
- እዚህ ጋር የተከበረው ፍ/ቤት በተጨማሪ አልጨረስንም
- ልመልስ የተከበረው ፍ/ቤት
- አልጨረሳችሁም ?
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ምንድን ነው ቅድም እንደተገለፀው በተለይ እዚህ ሀባሽ ስልጠናንን በሚመለከት እኮ እኛ የተከበረው ፍ/ቤት እንደሚያስታውሰው እኛ በዝርዝር ማለት ነው በዝርዝር ከሊባኖስ ስልጠና አሉ እና አለፉት እንጂ ቅድም ወ/ሮ አዲስ ስትጠይቅ ማለት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ነው በዝርዝር ዝም ያልነው ለነሱ ጉድጉድ በሚል ነው ነገር ግን በዋና ጥያቄ ላይ በምንም መልኩ ስለሀባሽ ስለሰልጠና በዝርዝር የገለፁት ነገር የለም አሁም ከእዚያ ተያይዞ ነው እየቀረበ ያለው እና ከእዚህ /ግልፅ ያልሆነ/

- ግልፅ ነው እስቲ ግልፅ አድርጉት ጥያቄው
- ጥያቄው የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም እሳቸው ስለሀሳሽ ሲተረጉሙ እነሱ ሀባሽ የሚሉት ከሊባኖስ መጥተው ከውጪ መጥተው የሚያሰለጥኑትን ሰዎች ናቸው አሉ ይሄ በግልፅ ሪከርድ አለ እኔም ፅፌዋለሁ እሱን መሠረት አድርጌ ነው የጠየኳቸው እና በዋና ጥያቄ የተነሳ ጥያቄ ነው የጠየኩት የተከበረው ፍ/ቤት
- ከውጪ የመጡት ናቸው አልሀባሽ ማለት ነው
- የሚሉት ብለው የራሳቸውን ትርጉም ነው እሳቸው የሰጡት
- አሁን እኮ ጥያቄው ግልፅ ይሁንልን
- ጥያቄው ምንድን ነው ሀባሽ የሚሉት ብለው ቅድም እርሶ ከውጪ የመጡትን ሰዎች ነው ብለዋል ብዬ ልቀጥል ስል ነው ጥያቄውን ሳላስከትል ነው ዐቃቤ ሕግ የተቃወመኝ ለማለት ነው ጥያቄው
- ጥያቄው /ግልፅ የልሆነ/
- አዎ አልተናገርኩም አልጠየኩም
- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ደግሞ እያልን ያለነው
- ቆይ ቆይ እናንተማ መልስ ሰጥታችዋል አሁን /ግልፅ ያልሆነ/ እኛ ከያዝነው እንትን ላይ እነዚያ ከውጪ የመጡ ሰዎች አልሀባሽ ናቸው ብሎ በማንም አልተነሱም ከውጪ የመጡ ሰዎች ከምስክሩ የያዝነው ነገር አስተማሩ በክርስቲያኖች እና በሙስሊሞች መካከል ያለውን ችግር ለመፍታት ሲባል የኃይማኖት ትምህርት እየተሰጠ ነበር እነሱ አልሀባሽ ናቸው ብለው አላስቀመጡም ይሄንን ጥያቄ አልፈው ሌላ ጥያቄ
- ቅድም ከውጪ የመጡ ሰዎች ብለው ነበር የሚያስተምሩ እነዚህ ሰዎች ወይም ከሊባኖስ መጡ ያሉትን ማለት ነው ከእዚህ ቀደም መጥተው አስተምረው ያውቃሉ ኢትዮጵያ ውስጥ እርሶ በሚያውቁት ማለት ነው ያውቃሉ ወይስ እያውቁም ?
- እስቲ ምንድን ነው ይሄ ጥያቄ
- በአጭሩ የኃይማኖት አስተማሪ ከሊባኖስ መጥቶ ያውቃል ወይ ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ በፊት ነው ከእዚያ በኋላ ?
- ከእዚያ በፊት
- የሚያውቁት አለ ከእዚያ በፊት መጥቶ በእዚህ ጉዳይ በእዚህ ጉዳይ ነው በእዚህ ጉዳይ ካልሆነ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የሚያውቁት የለም
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ ሊባኖሶች የመጡት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው በኃይማኖት ትምህርት ኢትዮጵያ ውስጥ?
- እኔ የተሳተፍኩበትን ነው እንጂ
- በቃ ይበቃል
- እነዚህ ሰዎች የመጡት
- እስቲ ምናልባት ጠበቆች እዚህ ጋር አንድ ነገር እስቲ እንትን አድርጉ ዐቃቤ ሕግ ይሄንን በዋና ጥያቄ ስለ ሰዎች ያነሳነው ነገር የለም ምስክሩ እዚያ ቦታ ለመኖሩ ላለመኖሩ ቅድም የተጠየቀው ጥያቄ በቂ ይመስለኛል ቅድም ተጠይቋል በብዛት እነዚህ ሰዎች መጥተው ስልጠና ሰጡ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚል አሁን ይሄንን የሚያረጋግጥላችሁ ምስክሩ እዚያ አካባቢ ነበር አልነበረም ነው ጭብጥ አይደለም እነዚያ ሰዎች መጥተው ያስተማሩት እንዲህ ነው እንዲህ ነበር ምናምን የሚለው ነገር
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ጭብጥ ስላልሆነ አሁን ተከሣሹ ነበር ወይ አልነበረም የሚለውን ለማስነሳት ነው እናንተ የምትጠይቁት በትክክል አውቆታል ወይ ነው እሱን ደግሞ ቅድም በዝርዝር በተለያየ ጥያቄ ተጠይቋል እሱን ፍ/ቤቱ ግምት ይወስዳል ከእዚህ በኋላ እሱ ላይ ብንደጋግመው ያው ሌላ ነገር አያመጣም ስለዚህ ሌላ ጥያቄ ቀጥሉ
- ከውጪ እንዲመጡ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነው ብለው ነበረ ማን ነው ይሄንን ጥያቄ ያቀረበላቸው ጥያቄውን ያቀረበላቸው እንዲመጡ ማን ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥያቄ ቀርቦላቸው ሳይሆን ይሄንን የሚመራ የነበረው ይሄንን ኮርስ ሊሰጡ ከውጪ መጥተው የእምነቱን ትክክለኛውን እምነት ለማስተማር መጥቶ እኛንም የበፊት የተማርነውን አስታወሱን እንጂ አዲስ ነገር በተማርኩት ላይ ምንም የተጨመረ ነገር
- የሚያውቁት ከሆነ ማን ነው የጠራው ነው ?
- መጅሊስ
- መጅሊስ ነው ቅድም ስለጅሀድ አቡበከር ማብራሪያ ሰጠ ብለው ነበር አቡበከር ለጅሀድ ስለጅሀድ ወይም አህመዲን የተናገረው ካሎት ውስጥ ለጅሀድ ከተሰጠው ትርጉም የወጡት ነገር አለ ጅሀድን በተመለከተ ሌላ ቃሉን ሳይሆን ጅሀድን በተመለከተ ተናገሩት ያሉት ነገር ወይም አብራራ ያሉት ነገር ከጅሀድ ውጪ የሆነ ነገር አለ ሌላ የተናገሩት ነገር እንዳለ ሆኖ ማለት ነው ?
- ቅድም የተናገርኩትን ብቻ ነው የሰማሁት
- አዲስ ነገር ቅድም የተናገሩት
- አይደለም የተናገሩትን አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት የተናገርኩትን ሳይሆን የጠየኩት እኔ
- ከተናገሩት ውጪ ያለ ነገር ቅድም ከገለፁት ውጪ የገለፁት ነገር አለ ወይ ነው ?
- አዎ
- አለ ቅድም እርሶ ዘርዝረዋል እንዲህ እንዲህ አደረጉ ብለው ከእዚህ ውጪ የገለፁት ነገር የሚያስታውሱት ነገር አለ ?
- የለም ያስታወስኩት ተናግሬአለሁ
- የለም አሉ
- አቡበከር ወይም አህመዲን ጀባል ጀሀድ ነው ተነሱ ጦርነት እንፍጠር ሲሉ ሰምተዋል ሰምተዋል ?
- ለኃይማኖት መታሰር መሞት ፀጋ ነው የሰማሁት ይሄንን ነው
- ቅድም ሰደቃ ፕሮግራሙ ጋር እንሂድ እና ሰደቃ ማለት ደሀን ማብላት ነው ብለው ነበረ እዚህ ሀምዛ መስኪድ በተደረገው የሰደቃ ፕሮግራም ላይ የሰደቃ ብቻ ፕሮግራም ነበር ፕሮግራሙ ማስተማር አልነበረበትም ትምህርት ዳዋ አይሰጥም ነበር ?
- ትምህርቱማ አሁን የተናገርኩት ነው ትምህርት ነው ተሸሎ የተሰጠው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይበቃል አሁን የተናገሩት ከሆነ ይበቃል
- ሰደቃ ማለት ደሀን ማብላት ነው ብለው ነበረ 10 በሬ ታረደ ሲሉ የተገኘው እዚያ ስብሰባ ላይ ሀብታም ብቻ ነበረ ደሀ አልነበረም ?
- ግልፅ አይደለም
- ሰደቃ ማለት ደሀን ማብላት ነው ብለዋል ስለዚህ እዚያ ፕሮግራም ላይ የተገኘው ሀብታም ብቻ ነው ወይ ደሀ አልነበረም ለማለት ነው ?
- ተቃውሞ አለኝ የተከበረው ፍ/ቤት
- ምንድን ነው ተቃውሞአችሁ
- ያው ምስክሩ አቅም አላቸው ይሄንን ይመልሱታል ግን ምስክሩ አቅም አላቸው ይመልሱታል ግን እዚያ ሰደቃው ላይ የተገኘውን ሕዝብ እከሌ ደሀ ነው እከሌ ሀብታም ነው ብለው ሊለዩ አይችሉም ያንን ሁሉ ሕዝብ እንዴት አድርገው ሊያውቁ ይችላሉ አሁን የጠበቃው ጥያቄ እዚያ የተገኘው ሰው ደሀ ብቻ ነው ሀብታም ነው ብሎ መጠየቅ ምን ማለት ነው ?
- እሺ ይሄንን ምላሽ አላሰጠንበትም ዐቃቤ ሕግ ያቀረቡት ተቃውሞ አይደለም ምስክሩ በቂ እውቀት አላቸው ይመልሱታል ነገር ግን የሚል ነገር ነው ስለዚህ ምስክሩ የሚችሉ ከሆነ ይመልሱ የማይችሉ ከሆነ አልችልም ይበሉ በቃ በቃ
- ጥያቄው አግባብ አይደለም ብለን ነው እኛ ያቀረብነው ጥያቄው አግባብ አይደለም
- ተሰጠ ሩል ተሰጥቷል ትላንት ተነጋግረናል ስህተትም ቢሆን እንቀበል ስለዚህ አሁን የነበረው ሰው ሀብታም ነው ደሀ ነው የሚል ጥያቄ ነው እርሶ የሚያውቁት ከሆነ ይመልሱ
- ሀብታም ብቻ ነው ወይስ ደሀ ብቻ ነው ጥያቄው ?
- ይሄንማ እንዴት እለየዋለሁ
- በቃ ይበቃል
- አያውቁትም ?
- አዎ
- ይበቃል ይበቃል እንዴ ይሄንን ክሪር የሆነ መልስ እኮ ነው በቃ ይሄንን መለየት አልችልም አላውቅም አሉ ከእዚህ በኋላ ሌላ ጥያቄ መጠቀል ያለበት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚህ መስኪድ ወይም ሀምዛ ስንት ጊዜ ሰደቃ የሰደቃ ፕሮግራም እንደተካሄደ ያውቃሉ ?
- የሚያውቁት ከሆነ ይመልሱ
- ማለት ግልፅ አይደለም
- ጥያቄው ግልፅ አድርጉ
- አምዛ መስኪድ ሰደቃ ስንት ጊዜ ተደረገ ?
- እኔ የማውቀው በሰፊ ቅስቀሳ ሊደረግ ሰደቃ ተብሎ የተጠራበት የእዚያን ቀን ሆኖ
- በቃ ሌላ ጥያቄ
- ቅድም ሕዝቡ እነ አቡበከር ሲናገሩ ለሞመት የተዘጋጁ ናቸው ብለው ነበረ ለምንድን ነው ለመሞት የተዘጋጁት ሰዎቹ ?
- አሁንም ይብራራልኝ
- ሰው በእዚህ የተነሳ ለመሞት የተዘጋጀ ሆኗል አሉ ለምን ሆነ ሰው እንዲህ ለምን ሆነ ለመሞት ለምን ተዘጋጀ ወይም ተነሳ ?
- ጥያቄው አሁን ግልፅ አይደለም ፡
- የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ምን ብለው ነበር ምስክሩ የተከበረው ፍ/ቤት ምንድን ነው ጥያቄዬ ለእዚህ ቅስቀሳ የተነሳ ሕዝቡ ለመሞት ተዘጋጅቷል እኮ አለ ለፍ/ቤቱ ቅድም ስለዚህ ለመሞት ለምን ተዘጋጀ ሕዝቡ እስቲ ተናገሩ ነው ያልኩት መሠረቱ ምንድን ነው ?
- ተቃውሞ አለኝ የተከበረው ፍ/ቤት
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን ማለት እሳቸው ጠበቃ አሁን ያቀረቡት በራሳቸው አባባል እና አገላለፅ ነው ሕዝቡ ደግሞ ተነስቷል ብለው እዚህ የምስክርነት ቃል አልሰጡም ከጅሀድ ጋር በተያያዘ ከሆነ ከጅሀድ ጋር ብምን እንዴት ብለው መጠየቅ ይችላሉ ሕዝቡ ግን ለሞት ተዘጋጅቶ ነበር ብለው እሳቸው ይሄንን በሰጡት የምስክርነት ቃል /ግልፅ ያልሆነ/ እየተከታተልነው የተመዘገበ ነው ሪከርድ እየተደረገ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከበረው ፍ/ቤት በቃ እኔ ጥያቄውን ልተው ዐቃቤ ሕግ እኮ
- ይሄ ነው ችግሩ አንዱ ችግር ይሄ ነው መቼ ተፈቀደላችሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ላብራራው
- አሁን ያለነው ነገር እኛም እንዳልተነሳ ስላወቅን ሕዝቡ ለሞት ተነሳስቷል የሚል ነገር እዚህ አልያዝነውም ምናልባት ቼክ ለማድረግ ነው እንደገና /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ቅድም የመንግስት ተወካይ ስልጠናው ላይ ነበረ ብለዋል የመንግስት ተወካይ ምን ነበር የሚያስተምረው ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት ካልሰሙት ነው እንጂ በዛሬው ዕለት የመንግስት ተወካይ ነበረ የሚል ከእሳቸው አፍ አልወጣም
- አላልኩም
- አሰልጣኝ ነበር አላሉም እንዴ ?
- ቆይ ቆይ እንደዚያ አላሉም አሁን /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ እናንተ ከምንመጣ እኛ የሰማነው የመንግስት ባለስልጣን ምን ወደ እኛ ምን ሊያደርግ ይገባል ብለው አሉ ነው እንጂ የመንግስት ባለስልጣን መጣ አላሉም ከእዚህ ተነስታችሁ ጠይቁ
- ቅድም አቡበከር ተናገረ አህመዲ ጀባልም ተናገረ ሳቢርም ተናገረ ብለው ነበረ ቅደም ተከተል አስቲ ማን ነው ቀድሞ የተናገረው 2ኛ 3ኛ ወይም ከእነዚህ ምስክር ተናጋሪዎች ሌላ
- በቃ በቃ ይሽውሎት በቃ ተራው ምን ነበር በቂ ጥያቄ እኮ ነው ቀጥሉ ማን ነው መጀመሪያ የተናገረው ቅድም 3 ሰዎች እንደተናገሩ ገልፀዋል ሌሎቹን አላስታውስም ብለዋል ከእነዚህ ሰዎች ማን ነው መጀመሪያ የተናገረው ቀጥሎ ?
- ከ3ቱ ከተናገሩት እርግጠኛ አይደለሁም
- ቀጥሉ
- አቶ ኃይረዲን ይሄ በእዚህ ሰደቃ ፕሮግራም ላይ በጣም ብዙ ሰው የነበረ መሆኑን ገልፀዋል እና ይሄ ፕሮግራም ከቀኑ 9 ሰዓት ነው የተጠናቀቀው ብለዋል ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ ሁሉም ሰው ያለምንም ረብሻ ያለምንም ብጥብጥ ነው አይደለም ወደየቤቱ የሄደው የመጣበት የሄደው ?
- ያው እኔ አሁን የእዚያን ሰዓት በነበርኩበት ቦታ ምን ይሁን ምን ያንን ሁሉ ቦታ ዞሬ ያንን ሁሉ ሕዝብ ተከታትዬ የያዝኩት ነገር

1416
ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያዩትን እርሶ ያዩትን እና የተረዱትን ?
- እኔማ የተረዳሁት ያየሁት ነገር ነው
- ምንም ብጥብጥ አልነበረም እርሶ ያዬት ?
- ለቀጣይ እንዲዘጋጅ
- አሁን የእዚያን ዕለት ነው እየጠየኮት ያለሁት የእዚያን ዕለት ምንም ብጥብጥ አልነበረም አይደል እርሶ ያዩት ምንም ብጥብጥ የለም ?
- አላየሁም
- ቅድም ስለጅሀድ ትርጉም ሰጥተውናል ግን አንድ ሰው ከራሱ ጋር በውስጡ ኃይማኖቱ ተገዝቶ ለመኖር እና ነብሱን አስገዝቶ ለመኖር የሚያደርገው ትግል ጅሀድ ነው አይደል ?
- እኔ አሁን
- ይሄንን ጥያቄ ብታልፉት የሚሻለው ማለት ቅድም የሰጡት ትርጉም አለ ፍ/ቤቱ የሚመዝነው ይሄንን አንድ መደምደሚያ ላይ ልንደርስ አንችልም ይታወቃል ወይ ትክክል አይደለም የሚል ነገር ሰውዬው ያውቃል አያውቅም በኋላ ብንመዝነው የሚሻለው
- ማለት የፈለኩት እኔ አንድ ሰው የገዛ ነብሱን ለፈጣሪ ለማስገዛት የሚያደርገው በውስጡ የሚያደርገው ትግል እና ጥረት ጅሀድ አይደለም ወይ ነው ይሄንን የሚያውቁ ከሆነ እንዲመሰክሩ ?
- እስቲ አሁን ያመጡት ያው ሰፋ ያለ የጅሀድ ትንተና ነው እሱ አልፈለግም አሁን በምስክሩ እውቀት ምስክሩ ቅድም የተናገሩት ሰዎቹ የተከሣሾቹ የተወሰኑት ውስጥ ሲሉ የነበሩትን ነው የተናገሩ እና ከእዚያ ያለፈ የውስጥ ትግል የውጪ ትግል ሌላ ብለን የምንሄድ ከሆነ ወደ መፅሐፉ ልንሄድ ነው እና ከእሱ ወጥተው ሌላ ቢጠይቁ
- ምናልባት እኔ የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ሲመሰክሩ ጅሀድ ነው ጅሀድ ብለዋል እነሱ ጅሀድ ማድረግ አለብን ብለዋል ብለው ሲመሰክሩ ጅሀድ ማለት አንድ ሰው የገዛ ነብሱን ለፈጣሪው ለማስገዛት በውስጡ ከራሱ ጋር የሚያደርገው ትግል ጅሀድ አይደለም ወይ ይሄንን አይደለም ወይ ያሉት ለማለት ነው ?
- ግልፅ ይመስለኛል እኮ የተሰጠው ነገር
- ወደ ሌላ ጥያቄ ይሂዱ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ምርጫችን በመስኪዳችን ብለዋል ብለው ነበር ምርጫው ተካሂዷል አይደል የመጅሊስ ምርጫ ማለት ነው ምርጫ ?
- አዎ
- ምርጫው በመስኪድ ውስጥ አልተደረገም አይደል ?
- አዎ
- የት ነው የተደረገው ምርጫው የት ነው የተደረገው ?
- እንደአካባቢው ሁኔታ ነው ለሕብረተሰቡ ማዕከል በሚሆን ቦታ
- እስቲ ቆይ ምርጫ ነገር ግን ተነስቷል ?
- አልተነሳም
- ቅድም አይ ምርጫችን በመስኪዳችን ብለው ይቆሰቅሱ ነበር ብለዋል እነሱ ምርጫችን በመስኪዳችን ብለው ከቀሰቀሱ ምርጫው /ግልፅ ያልሆነ/
- ቀጥሉ እሺ
- የት ነው የተደረገው ምርጫው ?
- ያ ምርጫ የተካሄደው እነሱ እንዳሉት ሳይሆን በመስኪዳችን ያሉት
- አሁን ይሽውሎት ምርጫ የት ነው የተደረገው ነው ጥያቄዬ ?
- ለሕብረተሰቡ ለሙስሊሙ በሚያመች እና ማዕከል በሆነ ቦታ
- እንትኗን ብቻ ነው መስኪድ ውስጥ ነው ውጪ ነው ?
- መስኪድ አይደለም
- ስለዚህ ከመስኪድ ውጪ ነው ?
- ከመስኪድ ውጪ
- ቀጥሉ
- ቅድም ክርስቲያኖችም በሰደቃ ፕሮግራሙ ላይ ነበር ብለዋል እና በሰደቃ ፕሮግራሙ ላይ ሳቢር ይርጉ ክርስቲያን ወንድሞቻችን በማለት ንግግር ያደርግ ነበር ብለዋል ክርስቲያኖችን ወንድሞቻችን ነበር ያላቸው ?
- ክርስቲያን ወገኖቻችንን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወገኖቻችን ወንድሞቻችንን ?
- አዎ
- በሚዲያ የሚነገረውን አትሰሙ ክርስቲያኖች ወንድሞቻችን አትራቁን ብለዋል ሲል በሚዲያ ክርስቲያኖች ወንድሞቻችሁ አይደሉም የሚል ነገር ተናግረዋል የተነገረ ነገር ነበር ?
- ግልፅ አይደለም
- በሚዲያ የሚነገረውን አትሰሙ ክርስቲያን ወንድሞቻችን ከእኛ ጋር አትራቁ ብሎ አለ ሲሉ በሚዲያ ክርስቲያኖችን ወንድሞቻችን አይደላችሁም የሚል ነገር ተነግሮ ነበር ወይ ነው ?
- የሚያውቁት ከሆነ በሚዲያ የሰሙት ነገር አለ ስለዚህ ጉዳይ ?
- የለም
- በቃ ሌላ ጥያቄ
- ከክርስቲያን ወንድሞቻችን ጋር ጥሪአችንን በአንድነት እናሰማለን ሲሉ ጥያቄአችንን ለመንግስት እና በአንድነት ሆነን ለመንግስት እናቀርባለን ማለታቸው ነው አይደል ?
- እናሰማለን ሳይሆን እናስተጋባለን ነው ያሉ ማስተጋባት እናንተም ጥያቄ አላችሁ ለእኛም ጥያቄ አለን ያልተመለሰ
- እኮ ጥያቄው ለማን ለመንግስት ነው የሚቀርበው አይደል ?
- እሱን እኔ ግልፅ አይደለም
- ለማን ይቀርባል ነው ያሉት ?
- ያው ግልፅ አይደለም ማለት እሱን አላውቅም እያሉ ነው እንግዲህ
- ቅድም ሀባሽ የሚባል ነገር የለም ብለዋል ሀባሽ የሚባል ነገር ከሌለ መንግስት ሀባሽ የሚል ነገር አመጣብን ያሉት ምንድን ነው ታዲያ የሚመጣው ?
- እነሱ ነው የሚያውቁ
- ሁሉም የሙስሊም ሕብረተሰብ ሀባሽ የሚባል እምነት የሌለ መሆኑን ያውቃል አይደል ሁሉም የሙስሊም ሕብረተሰብ ሀባሽ የሚባል እምነት አለመኖሩን በኃይማኖቱ አስተምሮት ያውቃል አይደል ?
- እሱን የሁሉን እኔ እንዴት አውቃለሁ

ECLN

1419

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እርሶም ያውቃሉ ?
- እኔ ሀባሽ እንደሌለ በደንብ ጠንቅቄ ነው የማውቀው
- ስለዚህ በእርሶ እምነት ሀባሽ የሚባል ነገር መንግስት ሊያመጣ አይችልም ?
- ከእዚህ በኋላ ያለው ጥያቄ ምክንያቱም ከእዚህ በኋላ እኛ አንመዝንም ምስክሩ መልሳቸውን መልሰዋል ከእዚያ በኋላ ያለው ኮንኩሊዥን
- ምናልባት ፍ/ቤቱ ጥያቄዬን ከፈቀደ አቀርባለሁ በእርሶ እምነት ሀባሽ የሚባል ነገር ሊመጣ አይችልም ማለት ነው ነው ያልኳቸው ይሄንን የእሳቸውን እምነት እና አረዳድ /ግልፅ ያልሆነ/ ፍ/ቤቱ ከፈቀደ ይጠየቅ ?
- አላውቅም አሉ ቅድም አሁንም ቢሆን አላውቅም ነው ያሉ ግልፅ ነው
- አዎ
- እኔ ይሄ እውቀት የለኝም አሉ ይሄ የለኝም ካሉ ከእዚህ በኋላ
- አሁን ስለሕብረተሰቡ ነበር የጠየኳቸው መጀመሪያ አሁን ግን ስለግላቸው ነው የጠየኩት እና ፍ/ቤቱ ከተቀበለኝ በግላቸው አሁን ቅድም ስለሕብረተሰቡ የጠየኳቸውን አላውቅም አሉኝ እሱን ተቀብዬለሁ በግላቸው ስለራሳቸው ነው ?
- ቆይ አይደለም ቅድም እኮ ስለእራሳቸውም ተናግረዋል አሁንም እየተናገሩ ነው 2 ነገሮች እየተናገሩ ነው 1ኛ እኔም አላውቅም ሕዝብም ስለማወቁ አላውቅም እያሉ ነው ምናልባት ከእዚህ ውጪ የሚያውቁት ካለ ቀጥሉ የሚያውቁት ነገር አለ ከእዚህ ከተገለፀው ውጪ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- በቃ
- አቶ ሀይረዲን ምናልባት ስጠቅሶት ከተሳሳትኩኝ ያርሙኛል ቅድም የተናገሩትን እኔ ለማስታወሻ ስለሆነ በዝግጅቱ 10 መስኪዶች ተሳትፈዋል ወይም ከ 10 መስኪድ ሕዝብ መጥቷል ከ2 አንዱ ብለዋል ወይም ያርሙኛል አላግባብ ብዬዎት ከሆነ
- ያሉትን በትክክል ያንሱት አሁን እሳቸው ይሄንን ሁሉ እንዲያስታውሱ ሳይሆን በትክክል ያሉትን መዘው መስቀለኛ ጥያቄ ያድርጉት ?
- አዎ ምንድን ነው እኔ መጠየቅ የፈለኩት ዝግጅቱ ቢያንስ ከአንድ መስኪድ በላይ የሆነ ሰው እንደተሳተፈበት ወይም እንደተዘጋጀ ገልፀዋል ትክክል ነኝ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ስለዚህ ትልቅ ዝግጅት ስለነበረ በሩ ላይ የተለጠፈ ነገር የለም ይሄንን ዝግጅት የሚገልፅ መስኪዱ በር ላይ አልነበረም በእዚያን ዕለት ሰደቃ የሚደረግ ለመሆኑ የተሳተፉ መስኪዶች ብዛት በጨርቅ ወይም በሌላ ነገር ?
- ይበቃል መልሱት ይሄንን
- የተለጠፈበት ምን መሆኑ ባላስታውስም
- እንዴት አወቁ 10 መስኪድ መሆኑን እንዴት አወቁ ነው ጥያቄው ?
- መድረክ አስተዋዋቂም ይናገር ነበረ የተለጠፈም ነገር የ 10 መስኪዶች የሰደቃ ፕሮግራም ተብሎ ተለጥፎ ነበር
- ቀጥሉ ሌላ ጥያቄ
- ተከሣሾቹ ሲናገሩ መቼም ይሄ ትልቅ ዝግጅት ስለነበረ የሚቀርፃቸው ሰው አልነበረም እንዴ የሚቀርፃቸው ?
- የሚቀርፅ ሰው ነበረ ?
- ነበረ
- ተከሣሾቹ በዕለቱ አሁን ቅድም የገለፁትን ብቻ ነው የተናገሩት ወይስ ሌላም ነገር ተናግረዋል ?
- እሱ ድጋሚ ነው እዚያ ተጠይቆ ምላሽ ተሰጥቷል አዳምጠውኛል ?
- አዎ
- ቅድም ሌላ የተናገሩት ነበር ወይ የሚል 3 ሰዎች ሁሉ ተጠቅሰው ጥያቄ ተጠይቋል አልተጠየቀም ተጠይቋል ተመልሷል
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ ሀይረዲን ክርስቲያኖች ለምንድን ነበር የተጠሩት እዚያ ሰደቃ ፕሮግራም ላይ ለምንድን ነው የተጠሩት ?
- ያው ቅድም የተባለው ሀባሽ መጥቷል ተብሎ የተባለው ቅስቀሳ ላይ ከሙስሊሙ ሕብረተሰብ ሆኖ ያንን እንዲያስተጋቡ እና እንዲያግዟቸው ነው የጠሯቸው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለእዚህ ነው የጠሯቸው ?
- አዎ
- ይሄንን ምናልባት የችሎት አስከባሪዎች አላችሁ አይደል እንዲህ ዓይነት እራስዎ ኖት እንዴ እርሶ መሄድ ይችላሉ
- ጨርስናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የፍ/ቤቱ ጥያቄ አልተነሳም ስለዚህ ምስክር እናመሰግናለን ጨርሰዋል ይመለሱ
- የተከበረው ፍ/ቤት ከእዚያ በፊት ጠዋትም አንድ አቤቱታ አቅርቤ ነበር በጎላስለተባለ
- ቆይ እስቲ
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ምስክር እሺ እንግዲህ እርሶ የሚገልፁት የመጀመሪያ ስምዎን ብቻ ነው ስለዚህ የመጀመሪያ ስምዎ ማን ነው ?
- አጠይብ አወል
- አጠይብ ነው ?
- አዎ
- ስንትኛ ምስክር ናቸው ?
- 69ኛ
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- የዐቃቤ ሕግ ምስክር
- በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- በአቡበከር አህመድ ፣በአህመዲን ጀባል ፣ በያሲን ኑሩ ፣ በሼህ ሱልጣን አማን ፣ በሳቢር ይርጉ ፣በበድሩ ሁሴን ፣በካሚል ሸምሱ ፣ በስይድ የአባቱ ስም አላውቀውም በመልክ አውቀዋለሁ በዩሱፍ እሱም እንዲሁ
- የአባቱ ስም አያውቁም ?
- አላውቀውም በመልክ ስለማውቀው ነው
- እነዚህን ሰዎች በአካል ነው በስም ነው የሚያውቋቸው ?
- እነዚህ የጠራዋቸው በአካልም ጭምር አውቃቸዋለሁ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአካል ያውቋቸዋል ?
- አዎ በመልክ አውቃቸዋለሁ
- እስቲ ተነሱ እዚህ ሆነው መለየት ይችላሉ ተነስተው መለየት ይችላሉ 1ኛ ተከሣሽን ለይተው አሳይተዋል እሺ ያሲን ኖት ስንተኛ ትከሣሽ ኖት 3ኛ ተከሣሽን እሺ በድሩ ሁሴን ኖት 5ኛ ተከሣሽ 4ኛ ተከሣሽ እሺ ጥቁር የለበሰው ነው ጥቁር ቲሸርት ስንተኛ ተከሣሽ ነህ 16ኛ ተከሣሽ ስምህ ትክክል ነው ሌላ የትኛው ናቸው እሳቸው ናቸው ስንተኛ ተከሣሽ ኖት 17ኛ ተከሣሽ እሺ የሱፍ ኖት እርሶ ስንተኛ ተከሣሽ ኖት 18ኛ ተከሣሽ አህመዲን ጀባል 2ኛ ተከሣሽ ሌላ አሎት ወደ ላይ መሄድ ይችላሉ
- ሳቢር ይባላሉ የቀሩት ሳቢር የሚባሉት ሳቢር ይርጉ
- ይመለሱ 7ኛ ተከሣሽ ለጊዜው ተመሳስሎብኛል አንድ ቀን ብቻ ነው ያየሁት ብለዋል ከእነዚህ ሰዎች ጋር ፀብ ዝምድና አላችሁ ?
- ምንም የለንም
- የላችሁም ?
- የለንም
- ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ
- አቶ አጠይብ
- አቤት
- አሁን የዘረዘሯቸውን ሰዎች ወይም ተከሣሾች የት ነው የሚያቋቸው ?
- በእርግጥ ግማሾቹ በሲዲም ትምህርት የሚያስወጡ የኃይማኖት እውቀትም ያላቸው ግማሾቹም በአወሊያም በእዚህ ግርግር ጊዜም የማውቃቸውም አሉ ግማሾቹም ደግሞ ያው በግል ጉዳይ መንገድ ላይ ተገናኝተን የማውቃቸው አሉ
- የሚያውቋቸው አሉ ?
- አዎ
- ለምስክርነት ነው የመጣሁት ብለዋል ?
- ትክክል ነው
- በምን ጉዳይ ነው የሚመሰክሩት ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአወሊያ ላይ ያየሁትን ነው የምመሰክረው
- ምንድን ነው ያዩት አወሊያ ከጊዜው ጀምረው እስቲ ይንገሩን ?
- በአወሊያ በሣምንቱ በጁማ ሰላት በኋላ የሚደረገውን ቅስቀሳ ነበር ያየሁት በእዚያን ሰዓት አስተዋዋቂ የነበሩ አቶ ሳቢር ይርጉ ናቸው አቶ ሳቢር ይርጉ በእዚያን ጊዜ ሕዝቡን ሲቀሰቅሱበት የነበረው እዚህ የተሰባሰብነው በጁማ የመንሰበሰበው ጥያቄኦችን እስካልተመለሰ ድረስ እዚህ ጁማ ነው የምንሰግደው ቤትም እንዳትገቡ ጥያቄኦችን ግልፅ እና ግልፅ ነው መንግስት ሀባሽ ያስወጣልን ከሀገራችን የሚሉ ቅስቀሳዎች ነበሩ እንደገና በተጨማሪም እዚህ የተሰበሰቡ 100 ሺህ ሕዝብ በ 100 ሺህ ሕዝብ የሚቆጠር ሰው መንግስት 17 ኮሚቴዎች እኛ የመረጥናቸው መሆናቸው እየታወቀ እያለ አላውቃቸውም ስላለ መንግስት እዚህ ያለን ሰዎችን በተፈለገ ሰዓት ላይ ኑ እንሂድ ብለን ስንነግራችሁ ተዘጋጅታችሁ እንድትጠብቁ መሄድ አለብን የሚለውን ቅስቀሳ ሲያደርግላቸው ነበር አላህ ዋክበር እያለ ሰዎችን ያነሳሳ ነበረ እንደዚህ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ነበሩ
- ጊዜው ያስታውሱታል ወሩን ቀኑን ዓ.ምቱን ?በ
- በእርግጥ ዓ.ም 2004 ነው ቀኑ በትክክል አላውቀውም እንጂ በሚያዝያ ወር አካባቢ ነበር እኔ በነበርኩበት ጊዜ ማለት ነው
- ሚያዝያ አካባቢ ?
- ሚያዝያ አካባቢ ነው
- አቶ ሳቢር ይሄንን ብለዋል ሌሎቹስ ይቀጥሉ እስቲ ?
- አቶ አህመዲን ጀባል ሰፊ ሰዓታት የወሰደ ነበር ሲናገሩ የነበሩት ከሚናገሩት ስለ ሕገ መንግስት ሲዘረዝሩ ነበር ሕገ መንግስት መንግስት በኃይማኖት ጣልቃ አይገባም ኃይማኖትም በመንግስት ላይ ጣልቃ አይገባም ኃይማኖት እና መንግስት የተለያዩ ናቸው ማንኛውም ኃይማኖት በማንኛውም ሰው የመሰለውን ኃይማኖት መከተል ይችላል ማንኛውም ኃይማኖት በሌላ ኃይማኖት ደግሞ ጣልቃ አይገባም እንደዚህ እንደዚህ የመሳሰሉት ዘረዘሩ እና ቀጥለው ምንድን ነው ያሉት ነገር ግን በአሁን ሰዓት ሀባሽ የሚባለውን በሀገራችን ገብተው በግደ አስተምሮቱን አንድንማር ወይም አንድንከተለው ሲያስገድዱን በእኛ ኃይማኖት ላይ ጣልቃ ገብተው ሲያስገድዱን
- እነ ማን ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነ ህባሽ ሲያስገድዱን መንግስት ግን ዝም ብሎ ማየቱን ሕገ መንግስቱን እየጣሰ ያለው መንግስት ነው የእኛ ጥያቄ ምንድን ነው ሕገ መንግስቱ ይከበር አይደለም እንዴ ብሎ ሲል አላህ ዋክበር እያሉ ይቀሰቅሷቸው ነበረ ቀጥሎም መንግስት ሀገር ሲሸራረፍ ዝም ብሎ እያየ ነው ለምሳሌ አብደላ ሀረሪ የህባሽ አስተማሪ የሆኑ ሰውዬው ሀረር የሶማሌ ናት ብሎ ያምናሉ ብሎ ይቀሰቅሳሉ ይሄንን እያወቀ መንግስትም ሲሸራረፍ ህባሽን መደገፉ መንግስት ይሄንን ነገር በጣም አስጊ ሁኔታ ላይ ነው ያለው እና እኛ ግን ሀረር የማን ናት ብሎ ይጠይቀዋል ሕዝቡን ሕዝብ ደግሞ የእኛ ናት ይላል አላህ ዋክበር የሚለውን ነገር ይቀሰቅሳቸዋል እንደገናም ሙስና ህባሾችን ሙስናን ይደግፋሉ ነገር ግን መንግስት ደግሞ ሙስና ፀረ ልማት ፀረ ዲሞክራሲ ፀረ ሰላም ፀረ እንደዚህ እንደዚህ ብሎ ይናገራል ነገር ግን ህባሽን ወግኖ መሄዱን ፀረ ሙስናነቱን ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው እንዴት እንዳየው ይሄ መንግስትን በደንብ ሊያስተውልበት የሚገባ ነው ብሎ ይላል እኛ ሙስሊሞችን ምንም ማንም የምንፈራም አይደለም በእስልምናችን በዲናችን ለመጣ ምንም አንፈራም ሞትም ቢሆን ይሄ ጅህድ ነው መሞት አለብን በኢትዮጵያ ወደ 80 ፐርሰንት የምንሆን ሙስሊሞች ነን ስለዚህ ምንም የምንፈራው ነገር አይኖርምም ዲናችንም ነው በእዚህ በጀይባ አወሊያ የተሰበሰበ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ ነው ቅስቀሳ እየተደረገ ያለው በአሁኑ ሰዓት በየቤቱ እየተደረገ ያለው ዋና አጀንዳ መነጋገሪያ የሆነው መንግስት ከእዚህ በፊት የነበረውን የአፄዎች መሪዎች የእኛ ኃይማኖት ተከተሉ የሚሉ መሪዎች ነበሩ በአሁን ሰዓት ግን የእኛ ኃይማኖት ተከተሉ የሚሉ ሳይሆን በአድ የሆነ ቅይማኖት ከሌላ ሀገር የመጣ ኃይማኖትን እንድንቀበል የምንገደድበት ነው እያለ ሕዝቡን መነጋገሪያ አጀንዳ ነው ያደረገው ስለዚህ አንድ ድምፅ ነው ያለን አንድ ቃል ነው ያለን አንድ ነን ምንም እንኳን ሶፊያ ወሀብያ ሰለፊያ እያሉ ሊሸራርፉን ቢሞክሩም አንለያይም አንሸራረፍም

- የት ነው ይሄ መቼ ነው የት ነው ?
- በጁማ ሰላት ነው
- ወሩን ?
- ቅድም በጠቀስኩት ወር ነው ሚያዝያ ጥር ነው
- ሚያዝያ ወር ነው ?
- 2004 ነበረ

1425

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቦታው የት ነው ?
- በአወሊያ ት/ቤት ላይ ነው የተነገረው
- አወሊያ ሌላ የሚያስታውሱት አለ አቶ አህመዲን የተናገሩት ?
- ሌላ ያሉትን እዚህ እኛ በተሰበሰብንበት ብዙ ጆሮ ጠቢ ሊኖር ይችላል ብዙ የመንግስት ተወካይ ሊኖር ይችላል ብዙም የደህንነት ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ ኃይማኖታችን አሰከሆነ ድረስ ግን ማንም ስለማንፈራ ጥያቄአችን ግልፅ እና ግልፅ ነው መጀመሪያው አወሊያ የሙስሊም ተቋም ነው ወደ ሙስሊም ተቋም መመለስ አለበት ይላል 2ኛ ያልመረጥነው መጅሊስ ይውረድልን ይላል 3ኛ ደግሞ ሀባሽ በግድ እንድንማር አስተምሮት እንድንማር የሚደረገው ያለው ይቁምልን ይሄ ነው ጥያቄአችን ይሄ ጥያቄ እስካልተመለሰ ድረስ ምንም ቢመጣ ስለማንመለስ ሁላችሁም ተነሱ የሚለውን አላህዋክበር በማለት ሲቀሰቅሳቸው ነበር
- ተነሱ ምን ለማድረግ ነው ?
- ጅሀድ ተነሱ ለማለት ነው
- ጅሀድ ተነሱ ምን ማለት ነው ጅሀድ ተነሱ ማለት ?
- ዲናችን ያው መብት እየተነፈግን ስለሆነ ዲናችን ለማስከበር ዲናችን እናስከብር ነው መስዋት እንክፈል ነው
- መስዋት እንክፈል እሺ አቶ ያሲንስ ?
- አቶ ያሲን የተናገሩት ወደ መጨረሻ አካባቢ ነበረ ያኔ በየሣምንቱ ጁማ ነበር የሚሰገድ የነበረው ነገር ግን ያቺ ጁማ አቶ ያሲን ኑሩ የተናገሩበት በሚቀጥለው ጁማ በአወሊያ እንደማይሰገድ እና ነገር ግን ቀጥሎ ከ4ኛው ጁማ ላይ እንዲመጡ ማሳሰቢያ ከተነገረ በእዚያን ቀን ነበረ አቶ ያሲን የተናገሩት
- መቼ ነው ይሄስ ጊዜው መቼ ነው ?
- ያው ጁማ በሚያዝያ ወር ነው ይሄም
- ይሄም ሚያዝያ ላይ ?
- ሚያዝያ ላይ ነው
- ዓ.ም ?
- 2004 ላይ ነው

1426

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነው ያሉት ?
- አቶ አቡበከር ከተናገሩ በኋላ ነበረ ምናልባት የእሳቸው ባስቀድም ምናልባት እሱን
- ይቀጥሉ እንደተመኞት ?
- አቶ አቡበከር የተናገሩት እኛ ሙስሊም ሕብረተሰብ የመረጠን ኮሚቴዎችን መፍትሔ ለማምጣት ወደ መንግስት መስሪያ ቤቶችም ጎራ ብለን ነበረ ከእዚህ በፊትም በዙም መስተንግዶ ትክክለኛ አቀባበል አልተደረገልንም ነበር እንግልት ነበረን ነገር ግን አሁን እኛ እስከመጨረሻ ድረስ እናንተ በመረጣችሁ እና በሰጣችሁን ተልኮ ለማስፈፀም ምንም ሳንፈራ ወደ ኃላም ሳንል እንቀጥላለን ምክንያቱም መንግስት ሊመራን የሚችለው በሀገር ጉዳይ እንጂ በዲናችን ጉዳይ ስላልሆነ ዲናችን የማይቀበለው ነገር ከሆነ እኛም አንቀበለውም ያልሆነ መልስ ይዘንላችሁ አንመጣም ልትፈሩ አይገባም የመንግስት መልስ ምንም ይሁን ምን ሊያስደነግጣችሁም አይገባም ነገር ግን እኛ ለሸላም ጠንቅቀን እስክንጨርሰው ድረስ ተስማምተን የመጣንበትን ነገር አለ እንድትቀበሉን ነው የምንጠይቀው ነው ያለው አሱም ከዛሬ ጁማ በኋላ 4ኛው ጁማ ላይ ነው የምንገናኘው በሚቀጥለው ጁማ አንገናኝም ይሄ ማለት ግን ወደ ኋላ ማፈግፈግ አይደለም መፍራትም አይደለም ፈርተንም ስለማናውቅ ወደ ኋላ አንልም እናንተም ቀጥሉ እኔ ብታሰርም እኔ ብሞትም ትከተሉኛላችሁ እንጂ ወደ ኋላ ማለት የለባችሁም አደራችሁን ነው ያለው ይሄንን ከተናገረ በኋላ አቶ ያሲን ኑሩ የሆነች አረብኛ ነገር ነበረች ጠቀስ ያደረጉ አስታውሳለሁ የግብፅ ሕዝብ ለመንግስት ለመጣል ሲሉት የነበሩትን መፈክር የተወሰነ ቃላትን ቀየር በማድረግ ነው
- ምንድን ነው የሚለው ?
- አሻብ ዩሪን ኢስቃጠስኩት የሚለውን ነገር ነበር የተናገሩት
- ምን ማለት ነው ?
- ይህ ማለት ደግሞ ሕዝቡን ዝምታውን ይሰበር ዝም ማለት የለብንም ዓይነት ነው ስለዚህ ይሄ ጁማ ዛሬ የሚቀጥለው ጁማ አንገናኝም ማለት ተቃውሞ ይቆማል ማለት አይደለም ተቃውሞ መቀጠል አለበት ዝምታ ለዲናችንም አይበጀንም ዝም አንልም
- ምን እናድርግ ?

1427

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተቃውሞአት'ነ ድምፃት'ነ ማሰማት አለብ'ን ብሚለው ነው አጠ'ነክረው የተናገሩተ የአ'ንድ የመንግስት ባለስልጣን ስም በመጥቀስም እና የአንድ የኃይማኖታችን መሪ የሆኑ ይማሙ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚባሉ የእሳቸው ስም በመጥቀስም ለማመሳሰል ሞክረዋል
- እንዴት ?
- ይማሙ ሻፍ የተናገሩትን የእኔ ንግግር በቁርአን እና በሀዲስን ተቀባይነት ከሌለው እና የሚጋጭ ከሆነ ከአጥር ወዲያ ወርውሩት ብለዋል እኛም በተመሳሳይ የዶ/ር ሺፈራውም ይሁን የሌላም ንግግር የማይመቸን ከሆነ በአጥር መወርወራችን አይቀርም
- ማን ነው ያለው ይሄንን ?
- አቶ ያሲን ኑሩ ነበር የተናገሩት ይሄንን ይሄንን ቅስቀሳ አደረጉ
- አቶ አቡበከር አቶ በድሩ ምን አሉ ?
- አቶ በድሩ እንደተባባሪ መሆናቸው ነው የማውቀው አስተባባሪ /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ እሳቸው ጋር
- ይግለፁልን ማለት ምንድን ነው ተባባሪ ነበሩበት ያሉት ?
- ያው የእነሱ ተባባሪነቱን ከእነሱ ጋር ወግነው እንደሚሰሩ
- በምንድን ነው የሚገልፁት ?
- በሀባሽ ገብቷል አዲስ ኃይማኖትም ገብቷል የሚለውን ነገር እንደቀስቃሽም እንደአጋዥም ሆነው ከኮሚቴዎች ጋር ከአወሊያ የነበረው ጊዜ ዋና ደጋፊ እንደነበሩ ነው የማውቃቸው
- ዋና ደጋፊ እኮ እሱን እስቲ በደንብ በግልፅ ይንገሩን የት የት ነው ያዩዋቸው ስንት ጊዜ አይተዋቸዋል እርሶ ከመቼ ጀምሮ በጊዜ ?
- እኔ ያየዋቸውም በአወሊያም ነው ለአንድ ጊዜ ነው ያየዋቸው ከእዚህ በፊትም በሰውም በወሬም እሰማለሁ ቤተሰቤቼም እህቴም ወንድሞቼንም የእሱ ደጋፊ ሆነው እሱ አብሮ እንዲያውም ከእኛ ጋር ስንከራከር አቶ በድሩ ጋር ተደውሎ ለምስክርነት ደውሎ ሀባሽ እንዳለ ማስረጃ ሆኖ እኔን ለማሸነፍ እህቴ ተከራክራኛለች አወሊያ ላይም በቃ ሽር ጉድ ይሉ እንደነበረ እንጂ መድረኩን ይዘው ሲናገሩ እንኳን አልሰማሁም
- እሳቸው አባሪ ናቸው ብለዋል እና በምን ማለት አባሪ ናቸው ሲሉ በምንድን ነው ያወቁት ይሄንን ?

1428

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሀባሸን አለመቀበላቸውን ከቤተሰቦቼም የእሱ ደጋፊዎች ሆነው ቤተሰቤ እህቴ እና ወንድሜ አሉ ከእነሱ ጋር እንደተናገሩ እና ነው የማውቀው ሌላ ግን በሚዲያ ወይም በማይክራፎን በመድረክም አልሰማሁም
- አቶ ካሚል ሸምሱስ ?
- እሳቸውም እንደዚህ ናቸው አቶ ካሚል ሸምሱ በከሊፋ ሕንፃ ላይ እዚያ አካባቢ ነው ሲናገሩ በጆሮዬ ስለሰማሁ ነው ሀባሸ የሚባው አዲስ ኃይማኖት መጥቷል ሲሉ ሲናገሩ ስለሰማሁ ነው በመልክም ስለማውቃቸው እኔም ስለማያውቁኝ ያው ሲናገሩ ስላዳመጥኳቸው የእነሱ መሆናቸውን አወኩኝ
- እሺ እኮ የተናገሩትን ይንገሩን የእነሱ ?
- አዲስ ኃይማኖት መምጣቱ በጥቅሉ አዲስ ኃይማኖት በሀገራችን ገብቷል ሀባሸ የሚባለውን መንግስትን አስታኮ መንግስትን አስታኮ የገቡ አረቦችን መንግስት የሚደግፋቸው ለምን እንደሆነ እሱ ግራ እየተጋባን ያለነው የሚለውን ነገር ነው የተናገሩት
- ይሄንን ነው የሚያስታውሱት ሌላ የሚያስታውሱት አለ ?
- ሌላ የማስታውሰው የለም
- አቶ የሱፍስ ?
- አቶ የሱፍ በግልፅ በመጅሊስ አካባቢ የመጅሊስ ስብሰባ በነበረ ጊዜ ለስብሰባ የተጠራ ሰው እንጂ ያልተጠራ ሰው መግባት በተከለከለ ጊዜ ካልገባሁ ብሎ ሲረብሽ ነበረ እኛ ከተጠራን ሰዎች አንዱ ነበርኩኝ እና ስገባም እዚያ ጋር ስለተከራከሩኝ በግልፅ የተናገሩት በእዚያን ሰዓት ዲነህ ነው መንግስት መደገፍ ሳይሆን ዲነህ ነበር መደገፍ የነበረብህ ብሎ አለኝ መንግስት እና ዲን መደገፍ የራሱ አለው ብዬ ስመልስለት ሀባሾች ነው ያለኝ ሀባሽ ብሎ ነው የሰደበኝ ሀባሽ ማለት ምናልባት አረብኛ ካወክ ትርጉሙ ከአሁን ከተናገርክ የሚሄድ ነገር አይደለም ተባብለን ተመላልሰናል እና ያ አቋሙን በእዚያን ሰዓት ነው ያወኩት
- በሌላስ ሌላ ቦታ የሚያውቋቸው አሉ በአወሊያ ረብሻ ምናምን ብለዋል ቅድም ?
- እሳቸው አቶ የሱፍን እንደድጋፍ እንደማተም ወረቀትን ማሰራጨትን ድጋፍ እንዳላቸው አውቃለሁ
- ምንድን ነው እስቲ ይንገሩን እሱን በዝርዝር ማተም ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወረቀትን መበተን ማለት ነው
- መበተን ምንድን ነው ወረቀት የሚበተነው ወረቀት ምንድን ነው ?
- የሚበተነውን ለምሳሌ እሳቸው ጋዜጠኛ ነኝ ብለው ነው የሚሉት እና የሚበትኑት ወረቀት ግን እንደዚህ መጅሊስን አይወክለንም በሚለው በስፋት እንደሚበትኑ ነበረ የማውቀው
- የት ነው የበተኑት መቼ መቼ ነው ቢጊዜ የሚያስታውሱ ከሆነ ቦታውን ?
- በጊዜው በትክክል ባላስታውሰውም ቦታው ግን በመጅሊስ አካባቢ ነበረ በአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች አካባቢ ጦርኃይሎች አካባቢ ነበረ
- ይሄንን አሁን ያሉትን ምንድን ነው ይዘቱ ?
- ይዘቱን መጅሊስን አይወክለንም የሚለው ነው ብዙም ወረቀቱን ማንበብ አልቻልኩም የተወሰነ ወረቀት ነው ያየሁት ሙሉ ለሙሉ አላነበብኩትም ርዕሱ ግን መጅሊስን አይወክለንም የሚለው ብቻ ነው ያየሁት
- መጅሊስ አይወክለንም የሚል ነው ያዩት ሼህ ሱልጣን በተመለከተስ ?
- ሼህ ሱልጣን አንድ መስኪድ አለ በመስኪዱ ላይ የፖለቲካ እንጂ የኃማኖት ያልሆነ ፖለቲካ ሲያስተምሩ ነው የነበረው
- ምንድን ነው እስቲ /ግልፅ ያልሆነ/ ትምህርቱን ንገረን ?
- ፖለቲካ የሚያስተምሩበትን
- /ግልፅ ያልሆነ/
- መስኪድ ሀምዛ የሚባለው መስኪድ ላይ ነው ከእዚህ ከአወሊያ ከሀባሽ ምናምን በሚባለው ወሬ በፊት ነው ቀደም ብሎ ነው በትክክል ጊዜውን ባላስታውሰውም በ 2003 አካባቢ ነው ሲያስተምሩበት የነበረውን ትምህርት ክርስቲያኖችን በዓሉ ቢደርስም የኃይማኖታቸው በዓል ስለሆነ ለእኛ ስለማይመለከተን እንኳን አደረሳችሁ መባባል በኃይማኖታችንም አይፈቀድም ይሄንን ይቅር እና በክርስቲያን ሀገር እንኳን በትክክል በኃይማኖታችን ከመጣን በክርስቲያን ሀገር መኖር እራሱ ክፉር ነው የሚለው ነበር
- ምን ማለት ነው ክፉር ነው ?
- ክፉር ነው ማለት ክህደት ነው ወይም ከእስልምና የወጣ ነው የሚለውን ነው
- ስለዚህ ምን እናድርግ ነው ?

1430

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ ያው ምክንያቱን ምን ማድረግ እንዳለባቸው አልዘረዘሩም ክልክል መሆኑ ነው በክርስቲያን መንግስት ያለበት ወይም እንድ መንግስት በሸሪያ ሳይሆን በራሱ ባረቀቀው ሕግ የሚያስተዳድር ከሆነ በራሱ በሰው ሰራሽ የሆነ ሕግ የሚመራ መንግስት ለምሳሌ ወለድን በሕገ መንግስቱ የሚፈቅደ ከሆነ ወንድ እና ሴት በውርሻ እኩል የሚያካፍል ከሆነ ሴቶችን ተገላልጠው ቢሄዱም መብት የሚሰጣቸው ከሆነ መጠጥ አስካሪ መጠጥ ቢጠጣ የማይከለክል ከሆነ እንደዚህ እንደዚህ ነገሮችን የሚያደርግ ሕገ መንግስት ያለውን መንግስት ከሆነ በእዚህ መንግስት መገዛት በእስልምና አይፈቀድም የሚለውን ትምህርት ያስተምር ነበረ ሌላውን ሸሪያ የሚባል ሕግ የራሳችን ሕግ አለን በዳኛ ወይም ደግሞ ፍ/ቤት ሄደህ መዳኘት በሸሪያችን አይፈቀድም እንዲያውም ፍ/ቤት ጋር ሄደህ እንድትዳኝ ፍቃደኛ ከሆንክ እንሂድ እንዳኝ ብለህ ካልህ ወይም ደግሞ ፍ/ቤት ላይ ተቀምጠህ ብይኑን ትክክል ነበር ብለህ አስተያየት ከሰጠህ ወይም ከሸሪያ ይመሳሰላል ብለህ የምትል ከሆነ የሚል የመሳሰሉት ነገሮችን ይሄ በሙሉ ክፉር ነው ወይም ክህደት ነው ምክንያቱም ለሸሪያ የሚፃረር ሰው ሰራሽ ሕግ ሆኖ እያለ እሱን መመስከርህ ክልክል ነው ሌላም በክርስትና ስም መጠራትም ተሸቡ ሆኖ ሲል ነበር
- ምን ማለት ነው ?
- ተሸቡ ማለት መመሳሰል ነው መመሳሰል ክርስቲያኖችን መምሰል ነው ሙስሊም አብደላ አብዱራህማን ተብሎ መጠራት አለበት እንጂ በቀለ ታደሰ ተብሎ ከተጠራ ተሸቡ ይሆናል ወይም መመሳሰል ተመሳስሏል ይባላል በባዓላቸው ጋር መገናኘት መመሳሰል ነው በቋንቋቸው መናገርም መመሳሰል ነው በአለባበሳቸው በባህላቸው እንደእነሱ መሆን መመሳሰል ስለሆነ አይፈቀድም በቀን አቆጣጠርም እነሱ በሚቆጥሩት አቆጣጠር መቁጠርም ተሸቡ ነው ይሄንን ይሄንን የመሳሰሉትን ያስተምሩ ነበር
- አንተ ምንድን ነው የምትሰራው የት ነው የምትሰራው
- ቆይ ቆይ ዐቃቤ ሕግ አሁን ካለፋችሁት እለፉ
- አቶ አጠይብ ቅድም ስትጀምር ከአወሊያ በአወሊያ ረብሻ ወቅት ነው የማውቃቸው ብለሀል የአወሊያ ረብሻ
- ምንድን ነው ተቃውሞ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ የአወሊያ ረብሻ የሚለው ንግግር 2 ጊዜ እየተደጎመ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም ያው ያስተካክሉታል ብለን አልፈነው ነበር አሁን 2ኛ ጊዜ ተደገመ ምስክሩ ፍፁም ረብሻ የሚል ነገር አልተናገረም ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ እየመራ እየጠየቀ ነው ረብሻ እንዳለ እያስመሰለ ጥያቄው ተስተካክሎ እንዲቀርብ እንዲታዘዝልን
- መልስ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ያው መሪ ጥያቄ ተጠይቃችዋል ተብሎ ሳይሆን እየተጠየቅን ያለነው ያልተባለ ነው ዐቃቤ ሕግ /ግልፅ ያልሆነ/ እንዲደረግለት እየጠየቀ ያለው ነው እየተባለ ያለው ስለዚህ ያው በእዚህ ችሎት አብረን እየሰማን ያለነው አልተባለም የሚባል ከሆነ እንግዲያው ፍ/ቤቱ በብይን የሚያልፈው ነው የሚሆነው መሪ ጥያቄ ነው አይደለም እየተባልን ያለነው አልተባለም ኮንፈርሜሽን እየጠየቁበት እያለው እየተባለ ያለው ፋክት አልተባለም አላሉትም ዐቃቤ ሕጉ እራሳቸው ናቸው እያሉ ያሉት ነው እየተባለ ያለው ስለዚህ ፍ/ቤቱ ይሄንን አልሰማሁም ምስክሩ አላሉም የሚል ከሆነ በእዚያው በብይን የሚያልፈው ነው የሚሆነው
- እናንተ አለን ብላችሁ ነው የምታነሱት
- ብለዋል ነው ምስክሩ ብለዋል ነው ብለዋል
- ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል የሰጠው ብይንም ምስክሩ ረብሻ አላሉም የሚል ነው እዚህ የያዝነው እና የመዘገብነው ረብሻ የሚል አላነሱም ስለአወሊያ እንስተው ግን ወጣ ገባ ይሉ ነበር እዚያ ስብሰባ እንደነበረ እና አጠቃላይ የዘረዘሯቸው ነገሮች ነው የነበሩ እና ረብሻ አነሳን ያሉት አንድ የመጅሊስ ስብሰባ ጊዜ እንግባ አንግባ የሚል ነገር ነው ያነሱት ስለዚህ እሱ ላይ ከሆነ ከእኚያ ግለሰብ ጋር እንግባ አንግባ በተባለው ረብሻ ከሆነ እሱን አንስታችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ ከእዚያ ውጪ ግን የእነሱን የመቃወሚያ ጥያቄ የነበረው ምስክሩ ከመጥራታቸው በፊት ረብሻ አለ ወይ ብለው ሲጠይቁ ይሄ ነገር ምስክሩን ማሳሰብ ነው ነው ስለዚህ በፊት ካልተነሳ እና ካልተደገመ ትክክል ነው የሚሆነው ዋና ጥያቄ አድርጋችሁ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ ከእዚያ ጋር በተያያዘ ከሆነ ግን ያንን መሠረት አድርጋችሁ ጠይቁ
- አቶ አጠይብ በምንድን ነው የሚያውቋቸው እነዚህን ተከሣሾች ?
- ማለት ሁሉም ወይስ

1432

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ በግል የሚያውቋቸውን አይደለም በግል ሕይወትዎ የሚያውቋቸውን ሳይሆን አሁን ከነገሩን ከአወሊያ ጋር በተያያዘ አወሊያ ምን ስለነበር ነው ?
- አወሊያ ላይ ሀባሽ ገብቷል መንግስትን አስታኮ መንግስትን ደግፎ በግድ ስልጠና እንዲሰጣቸው እየተደረገ አዲስ ኃይመኖት እንድንቀበል እያደረገ ነው ያለው በሚለው ነበረ ሕዝቡን ቀስቅሰውት ሴት ሱሪ ተለብሳለች ሴት ማሰገድ ትችላለች ቁርአን አላህ ቃል አይደለም አላህ ሁሉ ነገር ቻይ አይደለም የተወሰነ ነገር የማይችሉ ነገሮች አሉ ወለድ መብላት ይቻላል ምዕዋት
- በእዚህ ቅስቀሳ የተፈጠረ ነገር አለ ?
- በእዚህ ቅስቀሳ ያው ተሰባስቦ ጁማ ተሰባስቦ አላህ ክቡር እንዲሉ እና እንዲሰባሰቡ የተደረገ ነገር እንጂ ሌላ የተፈጠረ ነገር አላየንም
- ሌላ የተፈጠረ የሚያውቁት ነገር የለም አንድ ምናልባት አቶ ሰይድን በተመለከተ እስቲ ምንድን ነው እሳቸው ጋር በተመለከተ የሚያውቁት ነገር ?
- አቶ ሰይድ የቄራ መስኪድ አሰጋጅ ናቸው በቄራ የዳዋ ና ፕሮግራም ዝግጅት በነበረ ጊዜ አቶ ሳቢር መድረኩን እየመሩ ነበር እና በእዚያን ጊዜ
- መቼ ነው ይሄ ?
- ይሄ በግንቦት ወር አካባቢ 2004
- 2004 እሺ ?
- ነበረ በእዚያን ሰዓት አቶ ሳቢር ይርጉ ሲሉት የነበሩ በግልፅ በማይክራፎን በእዚያን ሰዓት እንደውም የዙር ሰላት ቆይቶ የተሰገደበት ሰዓት ነበረ እስከ 9 ሰዓት አካባቢ ነበር የተሰገደው መንግስት ጣልቃ ገብቷል በኃይማኖታችን ጣልቃ ስለገባ መንግስት እጁን ያውጣልን ግልፅ እና ግልፅ ጥያቄ ነው ብሎ አቶ ሳቢር ይሄንን ባሉበት ጊዜ ነበረ አቶ ሰይድ የእዚያም አዘጋጅም ስለነበሩ አስተባባሪ እንደነበሩ ነው የማውቀው ያስተባብሩ እንደነበረ ለፕሮግራም ዳዋ እና ፕሮግራም
- ምን ለምንድን ነው የተዘጋጀው አሁን የሚሉት ዳዋ ምን ማለት ነው ?
- ዳዋና ይሄ ሰደቃ ፕሮግራም የሚሉትን እኔ አልገባኝም ብዙም ለምን እንደፈለጉትም
- ምን ማለት ነው አልገባኝም ማለት ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዳዋ ሲባል ጥሪ ነው ጥሪ የሚደረገው ደግሞ ታይማኖታዊ ሰበካ ነው ነገር ግን በሬ ታርዶ የሚደረግም እሱ ዳዋ ብዬ ስለማላምነው ሌላ ይበጣ ኦፕሬሽን የሚለው ማመኑ ነው የለኝ እኔ
- ከየት ነው የተነሳው ይሄ ምትዎት ምን ስለተመለከቱ ነው ወይም ምን ስለሰሙ ነው ?
- በእዚያን ሰዓት መልዕክት ሲተላለፍ የነበረው ቀስቃሽ የሆነ መልዕክት ስለነበረ ሕዝቡን የሚቀበዋዙበጣ
- ምን የሚል የሚያስታውሱት ?
- መንግስት ጣልቃ ገብቷል መንግስት ከኃይማኖታችን እጁን ያንሳል የሚለውን ቅስቀሳ ሲያደርጉ ስለነበረ ይህ ለማለት ደግሞ ሕዝቡን ሰብስበህ መናገር ስለፈለጉ ለእዚህ ብሎ ይመስለኛል ሰው እንዲሰበሰብላቸው ያረጉት
- ያደረጉት ?
- አዎ
- ይሄንን ማን ነው የሚመራው ?
- በእዚያን ሰዓት በቄራ መስኪድ ያሉ አቶ ሰይድ ነበር ሲመሩት የነበሩ እሳቸው ሲያስተባብሩ ነበር
- ሲያስተባብሩ ነበር ?
- አዎ
- ጨረሳችሁ ?
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከሣሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- የሚያነጋግሯቸው ካለ ለአንድ ለ 2 ደቂቃ ያነጋግሯቸው
- መስቀለኛ ጥያቄ የለንም
- መስቀለኛ ጥያቄ የለንም ብለዋል መስቀለኛ ጥያቄ ያልተነሳ በመሆኑ ድጋሚ ጥያቄ አይኖርም ፍ/ቤቱም ማጣሪያ ጥያቄ የለም ምስክር እናመሰግናለን ጨርሰዋል ከእዚህ በኋላ ሌላ ምስክር መጨረስ አጓኾላም የመስለኛል ፣ ሰዓት ነው የምትኖረን እስከ 10 ሰዓት ስለሚሆን ያው ሰኞ በተለመደው ሰዓት እንገናኛለን::

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የመ.ቁ 124754

20/5/05 ዓ.ም

ዳኞች:- ብስራት ተልዕቀ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ክሣሽ:- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድማገኝ ቴዎድሮስ ጌታቸው ቀርበናል

ተከሣሾች:- እነ አቡበከር አህመድ የቀረ ተከሣሽ የለም አብዱራዛቅ ነው የቀረው ሌላም የቀረ አለ ሰንተኛ ተከሣሽ ናቸው

- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ያው ዛሬ የምናሰማቸው ምስክሮች እኚህን ተከሣሽ የሚመለከቱ ስላልሆኑ መቀጠል የምንችል ይመስለኛል
- ቀሪውን ተከሣሽ አይመለከትም ?
- አይመለከትም
- 29ኛ ተከሣሽ አልቀረቡም ሌሎቹ ተከሣሾች ከ28 ተከሣሾች 27ቱ ቀርበዋል ቀሪ ምስክር መዝገቡ ለዛሬ ጠበቆች
- ተማም አባቡልጉ፣ ባህሩ መካንጋ፣ ሀሰን ሁሴን ፣መሐመድ አብደላ ፣ሞላልኝ መለሰ ፣ንጋቱ ጌታሁን፣ ተካ ዳባ ፣ አህመድ ጀማል፣ ዳዊት ነጋሽ ፣ሀሊማ ሰይድ ቀርበናል
- የ28ኛ ተከሣሽ ማን ናቸው አህመድ ጀማል እሺ ቀርበዋል

1435

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ቀሪ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ነበር ዐቃቤ ሕግ ስለ ቀሪው ተከሣሽ ተጠይቀው ዛሬ የቀረቡት ምስክሮች በቀሪው ተከሣሽ ላይ የሚያስረዱት ነገር ስለሌለ በቀረቡት ላይ ብቻ ስለሆነ በእዚሁ ይቀጥልልን ብለዋል እነሱም እኛም በእዚሁ ይቀጥል ብለናል አቅርቡ ምስክር እሺ ዐቃቤ ሕግ ስንተኛ ተራ ቁጥር ናቸው
- 75
- ምስክር እንኳን ደህና መጡ
- እንኳን ደህና ቆዩን
- አሁን የሚመሰክሩት ማለት ስምዎን ብቻ ነው የሚሰጡት የመጀመሪያ ስምዎን ከእዚያ ውጪ ያለው ለምስክሮች ደህንነት ሲባል አይጠየቅም ስለዚህ ስምዎ ማን ነው ?
- አህመድ
- ለምንድን ነው እዚህ የመጡት ?
- ለምስክርነት
- እነ ማን በተከሰሱበት ?
- እነ አቡበከር አህመድ
- በማን በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- አቡበከር አህመድ ፣ አህመዲን ጀባል ፣ ካሚል ሸምሱ ፣ ሳቢር ይርጉ፣ ያሲን ኑሩ
- 5 ሰው ላይ ?
- አዎ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አውቃቸዋለሁ
- ፀብ ዝምድናስ አላችሁ ?
- የለንም
- ሊያሳዩን ይችላሉ ?
- አዎ
- እስቲ አንዴ ተነሱ 1ኛ ተከሣሽን አሳይተዋል 2ኛ ተከሣሽን አሳይተዋል 2ኛ ተከሣሽ ኖት እርሶ አይደል በእዚያ በላይ በኩልም ምስክሩ 1ኛ እና 2ኛን ተከሣሾች ከለዩ በኋላ ሌሎቹን በስም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የጠቀሷቸውን ተከሣሾች አንድ ቀን ብቻ ስላየዋቸው ማሷታወስ አልቻልኩም ብለው /ግልፅ ያልሆነ/ ካሉ በኋላ በዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥሉ

- አቶ አህመድ የመጣሁት በምስክርነት ነው ብለዋል አሁን ጠቁመው ያሳዩዋቸውን ግለሰቦች አሉ እነዚህን ግለሰቦች የት ነው የሚያውቋቸው ከጊዜው ጀምረው በዝርዝር ያስረዳሉ ይጀምሩ ?
- አሁን በአቡበከር አህመድ አህመዲን ጀባል በአወሊያ ት/ቤት የተናገሩት 2ኛ በሀምዛ መስኪድ በሰደቃ እና ዳባ 3ኛ በመስኪድ አንዋር ያደረጉት ንግግር እሱን ለመመስከር
- ጥሩ እሺ ከአወሊያ እንጀምር ?
- ከአወሊያ እንጀምር እና ወደ ሚያዝያ እና ግንቦት አካባቢ ይሆናል
- ስንት ዓ.ም ነው ?
- 2004 በእዚያን ጊዜ አቡበከር አህመድ መንግስት ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥቷል ጫና ፈጥረውናል በኃይማኖታችን መስዋት መሆን አለብን ይሄ ሀባሽ አስተምሮ አስገድዶ /ግልፅ ያልሆነ/ ከመንግስት ጋር ሆኖ አስገድዶ /ግልፅ ያልሆነ/ ለእዚህ ጅህድ መነሳት አለብን ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት ወለድ ይፈቅዳል ክርስቲያን አግባ ይላል
- ክርስቲያን ?
- ክርሲያን ሴት አግባ ይላል እንደዚህ እያለ ጫና እየፈጠረ ስለሆነ ለእዚህ ጅህድ ማድረግ አለብን ጅህድ መውጣት አሉብን ለኃማኖት መሞት አለብን ብሎ አሻአብ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚል መፈክርም ያስማ ነበር
- ምን ማለት ነው ?
- አሻአብ /ግልፅ ያልሆነ/ ማለት ሕዝቡ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይፈልጋል ማለት ነው
- ምን ማለት ነው ?
- ሕዝቡን ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይፈልጋል ማለት ነው
- እንዴት ?
- በቃ ይሄ ልክ እንደ ውጪ ሀገር ግብፆች ምናምን የሚያደርጉት ተቃውሞ ዓይነት ይመስላል
- ግብፆች ምን ማለት ?

1437

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያ ታሪር አደባባይ የሚያደርጉት የነበረ አገላለፅ እንደዚያ ነበረ /ግልፅ ያለሆነ/ ማለት ሕዝቡ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይፈልጋል የሚል እምነት ነበረ እንደዚያ ሰምቼአለሁ ከእዚያ በኋላ አመዲን ጀባል ተነሳ መንግስት ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት
- የተከበረው ፍ/ቤት የምናመለክተው አለ እየተመሰከረ ያለው ከጭብጥ ውጪ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ምንድን ነው ?
- ከጭብጥ ውጪ ነው እስካሁንም ድረስ እየተመሰከረ ያለው ከጭብጥ ውጪ ስለሆነ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክርነቱ ሊቀጥል አይገባም ጥያቄው ሊቀጥልብን አይገባም
- ምንድን ነው ከጭብጡ ውጪ እስቲ እሱን አስረዱ ?
- ጭብጡ ፍ/ቤቱ የያዘበት ጭብጥ አለ አሁን እየተባለ ያለው የሰዎቹን አመለካከት ነው እየመሰከሩ ያሉት እንጂ ድርጊት አይደለም ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት ከእዚህ በፊትም ዝም ብለን ቀጥለናል እየተደረገ ያለው የደንበኞቻችንን አመለካከት ነው ሰዎቹ እየመሰከሩ ያሉት ዐቃቤ ሕግም ጥያቄ እያቀረበ ያለው እና ካለው ድርጊት ላይ አስመስክር አዘርዋይስ የፍ/ቤቱ ጭብጥ በሽብር ሕጉ አንቀፅ 3 ስር ነው ጉዳዩ ይሂድ የተባለው እና በእዚያ መሠረት ምስክርነቱ እንዲቀጥል ይደረግልን አለበለዚያ እስካሁንም አሁንም እየሆነ ያለው ነገር ከጉዳዩ ጋር የማይያያዝ ኢረለቫንት የሆነ ነገር ነው ጥያቄው ምስክርነቱ ሊቀጥል አይገባም የተከበረው ፍ/ቤት፡
- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት እንግዲህ ጭብጣችን ቀደም ብለን አስይዘናል እኛ እናውቀዋለን ጭብጡን ፍ/ቤቱም ያውቀዋል እንግዲህ የተከሣሽ ጠበቃ ይሄንን ካላወቁ አስቸጋሪ ነው እና አሁን ምስክሩ እየመሰከሩ ያሉት ነኛ ተከሣሽ ጅሀድ መውጣት አለብን የሕይወት መስዋትነት መክፈል መሞት አለብን እና አሁን እሳቸው በአረብኛ የገለፁት ደግሞ ንግግርን ይናገር ነበር ያ ንግግር ምን ማለት ነው ብለን የጠየቅናቸው ያንን ንግግር ነው ያብራሩት ስለዚህ ምንም አላግባብ መሆኑን ምንም እኛ የታየን ነገር የለም እና ውድቅ እንዲደረግልን
- ብይን በጥተናል ብይኑ ምንድን ነው ምስክሩ እየመሰከሩ ያለ ተከሣሾች በወቅቱ የነበራቸውን ኃሳብ ነው ኃሳብ ደግሞ ያው ከድርጊት ጋር ቀነጥሶ የሚታይ አይደለም ስለዚህ ከጭብጡ የወጣ ነው ብለን አልወሰድነውም ዐቃቤ ሕግ ይቀጥል ብለናል

1487

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እናመሰግናለን የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር ካቆመበት ይቀጥሉ ?
- ከእዚያ ቀጥሎ አህመዲን ጀባል ተነሳ እሱ ያለው መንግስት ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት በኃይል ሊጭነን መጥቷል ሀባሽ የሚለው ሴት ሱሪ አድርጋ ትሂድ ወለድ ይፈቅዳል ከዲን ውጪ ይፈቅዳል ይሄንን ሁሉ ያደረገው መንግስት ሆን ብሎ ነው የሀበሽ አስተምሮ እየጫነን ነው ይሄ ደካማ መጅሊስ አምጥቶ እንደዚህ አደረገን መጅሊስ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አላህ ዋክበር /ግልፅ ያልሆነ/
- ምን ማለት ነው ?
- ሕዝብ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይፈልጋል ማለት ትርጉሙ እንደዚያ ብሏል ከእዚያ በኋላ ይሄንን አስተሳሰብ ይሄንን አስተምሮ መታገል አለብን መሞት አለብን ይሄ ጅሀድ ነው ከእዚህ በላይ ነገር የለም ስለዚህ ለጅሀድ ኃይማኖታችን መሞት አለብን ብሎ ሲናገር ሰምቼአለሁ
- እና ምን እንሁን ነው ?
- ጅሀድ በቃ ጅሀድ ማለት ጦርነት ማለት ነው
- ሌላ የሚያስታውሱት አለ አቶ አህመዲን ጀባል በወቅቱ ከተናገራቸው ነገሮች ሌላ የሚያስታውሱት አለ አቶ አህመዲን ከተናገራቸው ?
- ነገሩ ብዙ ነገር የተናገረው ግን ካስታወስኩት እነዚህ ናቸው በቃ ለኃይማኖታችን መሞት አለብን ጅሀድ ነው መንግስት አውቆ እስላማዊ መንግስት እመሰርታለሁ ይላል እስላማዊ መንግስት እንመሰርታለን ብሎ ይላል እኛ ብዙዎች ነን እስላማዊ መንግስት መመስረት እንችላለን ኃይማኖታችን ጀሀድ መነሳት አለብን ሲል እንደዚያ ብሏል
- ወደ ያሲን ኑሩ እንሂድ ?
- ያሲን ኑሩ በተመሳሳይ የተለየ ነገር አልተናገረም ሀባሽ የሚባል መጥቷል ሀባሽ መቀበል የለብንም እዚህ የተሰባሰብነው ሕዝቡ ደግፈን ነው ስለዚህ ሕዝቡ ሌሎቹ ተጨማሪ ይዘን መጥተን መተባበር አለብን ጅሀድ መነሳት አለብን ሲል ተናግሯል
- ካሚል ሸምሱስ ?
- እንደዚሁ ዓይነት ነው አላህዋክበር አላህዋክበር ጅሀድ ነው እዚህ ሕዝቡ ደግፎናል በውጪም ተቀባይነት አለን አላህ ዋክበር ጅሀድ ነው ለጅሀድ መሞት አለባችሁ በአፈራ ጀነት ትገባላችሁ ሲል ተናግሯል

1459

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄ ሁሉ አወሊያ መስኪድ ውስጥ ነው ?
- አዎ አወሊያ መስኪድ ውስጥ ነው
- ሳቢርስ ?
- ሳቢር የተናገረው በመስኪድ ሀምዛ ነበር በሰደቃ እና ዳዋ ፕሮግራም እሱ የተናገረው ምንድን ነው እናንተ ክርስቲያኖች
- መቼ ነው የሀምዛ መስኪዱ ?
- ሀምዛ መስኪድ ቀኑን በትክክል አላስታውሰውም የሰደቃ እና የዳዋ ፕሮግራም የሚል ነበር
- ወሩን አያስታውሱም ?
- ወሩ አላስታወስኩትም
- ዓ.ም ?
- 2004 ነው
- 2004 ቅድም ሲመሰክሩ አወሊያ መስኪድ ውስጥ የነበረው ሚያዝያ እና ግንቦት ይመስለኛል በግምት ብለዋል ?
- አዎ
- ከእዚያ በኋላ ነው ይሄኛው ወይስ ከእዚያ በፊት ?
- ከእዚያ በኋላ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያው ?
- ምስክሩ ግንቦት የሚል ነገር አልተናገሩም ሚያዝያ ነው ያሉት ስለዚህ ያላሉትን እንዳሉ ተብሎ መደረጉ ሊሰረዝ ይገባል ነው
- ምላሽ ስጡበት
- ያው ምስክሩ ቅድም ሲመሰክሩ ይሄንን ነው ያሉት ሚያዝያ እና ግንቦት በግምት በማላስታውሰው ብለው ይሄንን ፍ/ቤቱ ወደ ኋላ አስመልሶ /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ያው ቀደም ሲል ምስክሩ ሚያዝያ እና ግንቦት የሚል እኛም መዝግበናል ስለዚህ ዐቃቤ ሕግ ቀጥሉ

ECLN
1442
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ እኔ ያልኩትም ሚያዝያ እና ግንቦት አካባቢ ሲል ነበሩ ያ የነበርኩት ከእዚያ በኋላ ሳቢር እዚያ መስኪድ ዳዋ
- ከሚያዝያ እና ግንቦት በኋላ ነው ሀምዛ መስኪድ ?
- አዎ የዳዋ እና የሰደቃ ፕሮግራም ነበር ከእዚያ በኋላ ሳቢር ይርጉ እናንተ ክርስቲያኖች ዛሬ የጠራናችሁ መንግስት ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት ስላመጣልን ጫና ስለፈጠረልን ከእኛ ጋር ልትተባበሩ ይገባል ነገም እናንተ ተመሳሳይ ጥያቄ ስላላችሁ ነገም ለእናንተ ጫና ሊደርስባችሁ ስለሚችል ከእኛ ጋር ልትተባበሩ ይገባል
- ማንን ነው እንደዚያ የሚለው ?
- ሳቢር ይርጉ
- ለማን ነው እንደዚያ የሚለው ?
- ለክርስቲያኖች የተጋበዙ ነበሩ
- ክርስቲያኖች ነበሩ ?
- አዎ
- ማን ነው የጋበዛቸው ?
- እነዚያ የዳዋ እና የሰደቃ ፕሮግራም የሚያዘጋጁት አቡበከር እንዳለው በ80 መስኪዶች እንደዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ዳዋ ፕሮግራም አዘጋጅተናል አንዱ የመስኪድ ሀምዛ የተዘጋጀ ነው ይሄ ነው ብሎ እነ አቡበከር እንዳዘጋጁት ነው የተናገረው አቡበከር
- ምንድን ናቸው እነ አቡበከር ?
- እነ አቡበከር እኔ እንጃ እኔ እንዳየሁት ከሆነ በሰደቃ እና ዳዋ ሰበብ ለየት ያለ ቅስቀሳ ፖለቲካ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚናገሩት የነበረው
- እኛ የሚለው እነ ማንን ነው እኛ የሚለው ?
- እንግዲህ ያዘጋጁት ኮሚቴዎች መሆን አለባቸው
- መቃወሚያ አለን የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያችን 2 ነው አንደኛው የተመሰከረ ያለው አስተያየት ነው አስተያየት የሰውዬው አስተያየት ነው ፋክት አይደለም 2ኛ ክሱ ላይ ከጭብጡ ጋር የማይያያዝ ሰደቃ የሚባል በሰደቃ ምክንያት የተከሰሰ ሰው የለም ወይ አሚልቶ በእዚያ መሠረት ይደረግ እስካሁንም ዝም ብለናል የተከበረው ፍ/ቤት ያስተካክላሉ

1441

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በሚል ማለት ነው አሁን ሰደቃ ነው እያስመሰከሩ ያሉት ሰደቃ ደግሞ ኃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን በክሱ ላይ በሰደቃ ምክንያት አይደለም ወይ አጠቃላዩን ይበሉት እና ከክሱ ጋር በተያያዘ መልኩ ይቅረብ ስለዚህ የግለሰቡ አመለካከት አይደለም እኛም ለመስማት ቁጭ ያልነው ፍ/ቤቱ ለመስማት ቁጭ ያለው ስለዚህ ፋክት ይነገረን ይሄኛውን ጉዳይ ደግሞ የሚያስተባብሉ ቢሆን የተከሰረው ቁ/ቤተ 2ኛም ለነዚጠይቁ ቢፈቅድላቸው ለይጠሁም አመሰግናለሁ

- ምላሽ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ለምን በተደጋጋሚ እነዚህ ነገሮች እየቀረቡ እንዳሉ ለእኛ ግልፅ አይደለም 2ኛ ፍ/ቤቱ እራሱ ከእዚህ በፊት ብይን በሰጠባቸው ነገሮች ነው አሁን ጠበቃው ደጋግመው ይሄንን እያነሱ ያሉት እኛ ይቅርታ ይደረግልን ይሄ ለመበጥበጥ ነው የሚመስለው ሆን ተብሎ ፖይንታቸው ግልፅ አይደለም እኛ አልገባንም አንድ እሱ ነው 2ኛ ምስክሩ እየመሰከረ ያለው በአይኑ ያየውን በጆሮው የሰማውን ነገር ነው ያንን ነው እያብራራ ያለው ምንም ግልፅ አይደለም መልስ ለመስጠት እንኳን የሚያስችል መቃወሚያ አይደለም እየቀረበ ያለው
- ብይን ሰጥተናል ብይኑ አንግዲህ ቀደም ብሎ እንደተነገረው በዚያ ነገር አንዱ ፋክት ነው ውስጥ ያለው አንድ ፋክት ብቻውን ተረጋግጦ በዙሪያው ያሉ የዋናው ድርጊት በዙሪያው ያሉ ፋክቶች ናቸው በማስረጃ የሚረጋገጡት ስለዚህ ሰደቃን ምክንያት በማድረግ የሚል ክሱ ላይ አብሮ አለ ሽፋን በማድረግ የሚል በፋክት ባለፈውም እንደዚህ ዓይነት አንስተናል ስለዚህ 1ኛ እሱ ነው 2ኛ ከእዚህ ውጪ ያሉ አስተያየት አመለካከት ምናምን የሚባሉ ነገሮች ቅድም በተሰጠው አግባብ ነው ኢንቴንሽን የሚረጋገጠው 3ቱ ኢለመንቶች የሚረጋገጡት አንዱ በእዚህ ምክንያት ነው ድርጊቱ ታደርጓል አልተደረገም በኋላ ፍ/ቤቱ የሚመዝነው ነው የሚሆነው ስለዚህ በእዚህ ምክንያት ተቃውሞ አልተቀበልነውም በሌላ መንገድ ዐቃቤ ሕግ ለመበጥበጥ የሚለው ቋንቋ በራሱ ተከራካሪን የሚያሻክር ስለሆነ እንደዚህ ዓይነት ቃላቶችን ተቆጥባችሁ ብትከራከሩ ጥሩ ነው ምናልባት ምስክር አሁን የሚያውቀትን የእርሶን ኣመለካከት ሳይሆን የሚያውቀትን ሲባል የነበረውን ወይም የሰሙትን ያዩትን እሷን ብቻ እንትን እያላችሁ ትሄዳላችሁ ማለት ነው
- አዎ እኔ ያየሁት እና የሰማሁት

1442

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር ይቀጥሉ ካቆሙበት ሀምዛ መስኪድ ሳቢር ይርጉ ሰለተናገራቸው ነገሮች እየተናገሩ ነበር ?
- አዎ
- እስቲ ደግመው ይንገሩን ያስታውሱን ስለተቋረጠ ?
- ሳቢር ይርጉ ያለው እናንተ ክርስቲያኖች ዛሬ የጠራናችሁ መንግስት ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት ስላመጣልን ጫና ስለፈጠረልን ነገም እናንተ እንደኛ ሊደርሳችሁ ስለሚችል እኛን ማገዝ አለባችሁ ብሎ ተናግሯል መንግስት አውቆ እስላማዊ መንግስት እመሰርታለሁ ብሎ ከእናንተ ጋር እያጣላን ነው ስለዚህ እኛ እስላማዊ መንግስት ልንመሰርት አይደለንም ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት ስላመጣልን መንግስት ይሄንን ለመከላከል ነው ይሄ ጅሀድ ነው ከእኛ መሆን አለባቸው ሲል ተናግሯል
- ቅድም ሲመሰክሩ በአወሊያ መስኪድ አህመዲን እና አቡበከር እስላማዊ መንግስት እናቋቁማለን ሲሉ ነበር ብለዋል አሁን ደግሞ ሳቢር ይርጉ ሀምዛ መስኪድ ክርስቲያኖች ባሉበት እስላማዊ መንግስት መንግስት ያቋቁማሉ የሚለን ከእናንተ ሊያጣላን ነው ብለዋል ለምንድን ነው 2ቱ የተለያየው ?
- አይ ይሄ ያለው ክርስቲያኖች ለመሳብ ሆን ተብሎ ነው እንጂ ሳቢር ይርጉ ዓላማቸው እነዚህ ተቃውሞ ከእዚያ ስለነበረ ክርስቲያኖች ለመሳብ ያደረገው ንግግር ነው
- በጣም ጥሩ ሌላ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አይ እንደዚያ ነው ያለው መንግስት
- አሁን ያሉት አውቀው ሕዝቡን ለመሳብ ነው ብለዋል እና ይሄ የግልዎ አስተያየት ነው ወይስ ከእዚያ የሰሙትን ነው ?
- ምክንያቱም ጅሀድ እያለ ይናገር ነበር ጅሀድ ማለት ጦርነት ነው እስላማዊ መንግስት እዚያ እንመሰርታለን ተብሎ ይናገሩ ነበር እንደገና ለክርስቲያኖች እንደዚያ ሲል ቀጣይ የሚያሳየው የእነሱንም /ግልፅ ያልሆነ/ የተደረገ ነው
- ጥሩ ምስክር ሀምዛ መስኪድ ውስጥ ከሳቢር ይርጉ ሌላ ንግግር ያደረገ ሰው ነበር ?
- አዎ አቡበከር ተናግሯል ወንበር ቁጭ ብሎ ነበር ስለጅሀድ በሰፊ አውርቶዋል
- ምን ብሎ ?

1443

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጅህድ መነሳት አለብን መንግስት ሀባሽ ኃይማኖት አምጥቶልናል ይሄ ሀባሽ ኃይማኖት ዲናችንን የሚያበላሽ ነው ሱሪ አድርጋ ትሂድ ሴት ይላል እንደገና ከኃይማኖታችን ውጪ የሆነ ነገር ያዘናል ስለዚህ ለእነዚህ መፋለም አለብን መዋጋት አለብን ብሎ ብዙ ስለጅህድ ሲተነትን ነበር ካስታወስኩት ይሄ ነው እኔ ያስታወስኩት ከእዚያ ቀጥሎ አህመዲን ጀባል ነበር የተናገረው አህመዲን ጀባል ስለ ራዕይ የሚል መፅሔት ነበር የተናገረው ይሄ ጠቅላይ ሚኒስቴራችን በእኛ ኃይማኖት ጣልቃ ገብቷል ኃይማኖታችን ለ 3 ከፍሏል ራዕይ መፅሔት ደጋግሜ አንብቤዋለሁ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ፍፁም ጣልቃ ገብቷል ስለዚህ ማንኛውም ቢሆን እኛ አንፈራም ለኃይማኖታችን ጅህድ መሞት አለብን ጠቅላይ ሚኒስቴር አያገባውም ይሄ ዓይነት የአፄዎቹ እና የአፄ ዮሐንስ ዓይነት ነው ስለዚህ የአፄ ዮሐንስ ዓይነት ነው እነሱ ግፍ የሰሩት ነው ያሉ ግፍ የሰሩት አፄ ዮሐንስ ሙስሊሞች ግፍ የሰሩት የእነሱ ተቀፅላ ነው አንቀበለውም ሲል አህመዲን ጀባል ተናግረዋል
- ሌላስ ማን ንግግር ያደረገ አለ ሀምዛ መስኪድ ?
- ከእዚያ ሌላ የተናገረ አላስታውሰውም
- ሌላ ይቀጥሉ እስቲ ከእዚያ በኋላ የሚያውቁት ነገር ምንድን ነው ይሄ ሀምዛ መስኪድ ላይ ከተደረገው ቅስቀሳ በኋላ ቀጥሎ የሚያጠቃት ነገር ምንድን ነው ከሀምዛ መስኪድ በኋላ ቅድም ምስክርነት ሲጀምሩ 1ኛ አወሊያ መስኪድ 2ኛ ሀምዛ መስኪድ 3ኛ ?
- አዎ ይቅርታ አንዋር መስኪድ ሐምሌ 8 ጠዋት 4 ሰዓት አካባቢ አህመዲን ጀባል ትላንትና በአወሊያ ላይ መንግስት በጣት የሚቆጠሩ ቢገድልም 80 ከብት መጥቶ ቢወስድም ቢታሰሩም ቢገረፉም ይሄ ጅህድ የጀመርነው አይቋረጥም ይቀጥላል ሲል ነበረ ይሄ መስኪድ አንዋር ነው
- ማን ነው እንደዚያ ያለው ?
- አህመዲን ጀባል
- የምን ሞት የሞተ ሰው ነው የሚሉት ?
- አወሊያ ላይ መንግስት ሰው ገድሏል በጣት የሚቆጠር
- መቼ ?
- 80 ከብት ዘርፏል
- መቼ ነው አደረገ የሚሉ ?

1444

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሐምሌ 7 መሆኑ ነው ትላንትና ማታ ብሎ ነው የሚነገር የነበረው
- ትላንት ማታ መንግስት ሰው ገድሏል ?
- አዎ ሰው ገድሏል በጣት የሚቆጠር 80 በሬ ነድቶ ወስዷል ዘርፏል የተመቱትም አሉ ቢመቱም እንትን ቢሉም ትግላችን አይቋረጥም ጅሀድ እንቀጥላለን ሲል ሲናገር ነበር
- የሞተ ሰው ነበር እንዴ ?
- እኔ እሱ ሲናገር እንደዚህ ሰምቼአለሁ ሲሞት ግን አላየሁም
- ጥሩ ከእዚያስ ሌላ ማን ንግግር አደረገ ?
- ከእዚያ በኋላ እኔ አልቆየሁም ወደ ስራዬ ሄድኩኝ ሌላ የተናገረ አልሰማሁም
- ጥሩ ቅድም ያሉት ሀምዛ መስኪድ አንድ ቀን ብቻ ነው ያዩዋቸው ?
- አንድ ቀን ነው የዳዋ እና የሰደቃ ፕሮግራም የሚል ነ0 መስኪዶች ያዘጋጁት የሚል ነበር
- ከእዚያ ውጪ ሀምዛ መስኪድ ውስጥ ንግግር ያደረገ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሰው ነበረ ?
- አይ ከእዚያ በፊት አላየሁም ያን ቀን ነበረ ያየሁት
- የእዚያን ቀንስ እርግጠኛ ኖት እነዚያ ሰዎች ብቻ ናቸው ንግግር ያደረጉት ?
- በእርግጥ እኔ 3 ሰዓት አካባቢ ነበር የገባሁት ከእኔ በፊት ተናግሮ ይሆናል
- አይ እርሶ ከገቡ በኋላ ?
- እኔ የገባሁ በኋላ እነዚህ ናቸው የሰማሁት ከእዚያ በኋላ እነዚህ ከሰማሁ በኋላ ወጥቼ ሄጃለሁ
- ቅድም ክርስቲያኖች ተጠርተው ነበር ብለዋል
- የተከበረው ፍ/ቤት ማሳሰቢያ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ማሳሰቢያ ነው ተቃውሞ
- ተቃውሞ ተብሎ ይመዝገብልን ምስክር በሚሰማበት ሂደት ውስጥ
- ተቃውሞ ካላችሁ ?
- እሺ ተቃውሞ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር በሚሰማበት ሂደት ውስጥ ምስክሩ የአቀማመጡ እና የአይን ግንኙነቱ ከፍ/ቤቱ ጋር ነው መሆን ያለበት ግን ከእዚህ ተቃራኒ ነው እየሆነ ያለው እና ፍ/ቤቱ ይሄንን እንዲያስተካክልልን ነው

1495

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር ወደ እዚህ ነው እየተመለከቱ እንትን የሚሉት ለነገሩ እኛ እየተቆጣጠርናቸው ነበር ምናልባት አይ ኮንታክት አላየንም ግን ፊታቸውን ከዞሩ ሊያስመስሉ ስለሚችል ወደ እዚህ ዞረው ይመስክሩ ጥያቄውን በጆሮ ይስሙ በእዚህም በእዚያም በኩል በኋላ የሚጠየቀውን
- አይ እኔን ስላናገሩኝ
- ልክ ነው ወደ እዚህ ዞረው
- ምስክር ሀምዛ መስኪድ ውስጥ የስብከት ፕሮግራም ነበር አይደል እርሶ የሰሙት ቅድም የነገሩን ማለት ነው
- ይደገም
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ምንድን ነው
- ምስክሩ እስካሁን ሲመስክሩ የስብከት ፕሮግራም አለ ብለው አልመስከሩም አሁን ግን የስብከት ፕሮግራም አለ አይደል ብለው መጠየቅ ተገቢ አይደለም ቃላቱን ጥያቄ ሊጠይቁ ይችላሉ ግን የስብከት ፕሮግራም አለ አይደል ነበር አይደለም ወይ ብሎ መጠየቅ ግን በቀጥታ መምራት ስለሆነ ዐቃቤ ሕግ ጥያቄአቸውን እንዲያስተካክሉ
- ዐቃቤ ሕግ
- እኛ ያው ተርሚኖሎጂውን ነው ቅስቀሳ ነው ስብከት ነው እሱን ቅድም ምስክሩ ተራ በተራ ይናገሩ ነበር ስለጅሀድ ስለተያየ ስለኃይማኖት ሲሉ ስለነበር ስብከት ብለን ወስደነው ካልሆነ እንግዲህ እንታረማለን
- ብይን ሰጥተናል መጨረሻ ላይ ስብከት ነው ወይ የሚል መሪ ጥያቄ ነው ስለዚህ እሱን አስተካክላችሁ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ጥሩ ምስክር ቅድም የጠቀሷቸው ሰዎች በየተራ ይናገሩ ነበር እሱ ፕሮግራም ነበር ከእዚያ በኋላስ ሌላ ፕሮግራም ነበር ?
- ከእዚያ በኋላ በቃ የሰደቃ ፕሮግራም ቀጥሏል ሌሎች ይናገሩ አይናገሩ እኔ ግን ወደ 9 ሰዓት ከምናምን
- ምን ምን ዓይነት ፕሮግራም ነበር አሁን እርሶ ያሉት የንግግር ፕሮግራም ነበር ?
- አዎ
- ከንግግር ፕሮግራም ውጪስ ?

1446

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከንግግር ፕሮግራም ውጪ በቃ ይሄ የቅስቀሳ ዓይነት ንግግር ነበር ቅድም እንዳልኩት ብዙ ሰው ተናግሯል ይሄንን ነው እኔ የሰማሁት
- የመጡ ክርስቲያኖች ነበሩ ብለዋል ቅድም ?
- አዎ
- ምን ተደረገላቸው ?
- ግብዣ ተደርጎላቸው ነበር
- ሌላስ ?
- በቃ እዚያ ወንበር ተዘጋጅቶላቸው በስነ ስርዓት ተቀምጠ የግብዣ ተካፋዮች ነበሩ ምግብ ምናምን እንደነበር አይቼአለሁ
- ጥሩ አወሊያ ላይ ቅድም የጠቀሷቸው ሰዎች አሉ ካሚል ሸምሱ ፣ያሲን ኑሩ፣ አቡበከር አህመድ እና አህመዲን ጀባል ያ ንግግር ሲደረግ ቅድም እንደጠቀሱት እርሶ ክርስቲያኖች አልነበሩም በእዚያ አወሊያ ላይ በተደረገ ፕሮግራም መሀል ንግግር ያደረገ ሌላ ሰው የሚያስታውሱት አለ ?
- አይ የማስታውሰው የለኝም
- ዋና ጥያቄ አበቃን
- እሺ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ
- ምስክር አቶ አህመድ አሁን የተናገሩት ነገር በሙሉ ተናገሩ እነ አህመዲን ይሄንን አለ አቡበከር ይሄንን አለ እና ምን ሆነ እንደዚያ አለ እና ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- ምንድን ነው መቃወሚያው
- መስቀለኛ ጥያቄ ነው እና ምን ሆነ ብሎ መስቀለኛ ጥያቄ የለም ዋና ጥያቄ ነው ስለዚህ መርተው የሚፈልጉትን መጠየቅ ይችላሉ እና ምን ሆነ ምንድን ነው ያው ያለውን ነገር በሙሉ እኛ አስመስክረናል መስቀለኛ ጥያቄ ካላችሁ በመስቀለኛ ጥያቄ መልኩ እንዲያቀርቡ ነው የምናመለክተው
- መልስ የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ቀጥሉ ?

1147

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መስቀለኛ ጥያቄ መርቼም ልጠይቅ ሳልመራም መጠየቅ መብቴ ነው መብት ነው እንጂ መፎቶ መጠየቅ ቀጥታ ጥያቄ ብጠይቅስ መስቀለኛ ጥያቄ-ላይ እስከተነሳ ድረስ እሱ ላይ እስከተንተራስኩ ድረስ እሱን መሠረት አድርጌ እስከጠየኩ ድረስ የጥያቄ አቀራረቤ ሕጉ አይገድብም ዐቃቤ ሕግም ሊገድቡኝ አይገባም ሲምፕሊ ሕጉ በሰጠኝ መብት መጠቀም እችላለሁ አለመጠቀምም እችላለሁ ስለዚህ ያደረጉት ነገር ኖርማሊ ሕግን መሠረት የደረገ አይደለም ስለዚህ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ሌላ እንትን ላለማብዛት ጠበቃ የጠየቁት ጥያቄ ተገቢ ነው ቀጥሉ ብለናል
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ አህመድ ይሄ ሁሉ ሆኖ ይሄ ሁሉ ተብሎ ምን ሆነ ምን ተፈጠረ ?
- ይሄ ሁሉ ተባለ እነሱ አሉ እኛ ሰማን አላህዋክበር ሲባል ቅስቀሳ ሲደረግ ነበር ከእዚህ ውጪ
- ጥያቄዬ አልገባዎትም አቶ አህመድ
- ያው ከእዚህ ውጪ አላውቅም አሉ
- እሺ
- አቶ አህመድ ቅድም በተለይ አቡበከር አህመድእና አህመዲን ጀባል ሕዝቡ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይፈልጋል ለእዚህ መታገል አለብን ወዘተ የሚል ምስክርነት ሰጥተዋል ለእዚህ አንድ የተወሰነ ድርጊት መፈፀም አለብን የሚል አስተያየት ኃሳብ አቅርቧል አንድ የተወሰነ ድርጊት ምን አሉ ሕዝቡ ምን እናድርግ አሉ ?
- እንግዲህ ጅሀድ ነው ጦርነት እናንሳ ለኃይማኖታችን ከሚል ድርጊት በላይ
- እሱን ማለቴ አይደለም ምን ምን ዓይነት ነው በኃይል ይሄንን መንግስት እንጣል አሉ አላሉም አይደለም ?
- ነው እኔ የሚገባኝ ነው
- እንደዚያ ብለዋል ወይ ?
- አዎ እስቀጥእኒዛ ማለት እኮ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ እንፈልጋለን ማለት በኃይል ማለት
- አስተያየቱን አይደለም የምንፈልገው እነሱ የተናገሩት ነገር ምንድን ነው ተናግረዋል አልተናገሩም ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ

1448

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንድ የተወሰነ የኃይል ተግባር መፈፀም ይገባናል አሉ አቃ ወይም አይደለም
- መቃወሚያ አለ ምንድን ነው መቃወሚያ አለ ቀርቧል
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ ኦረዲ መስክረዋል አሁን የተከበሩ ጠበቃ በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቋቸው ምንድን ነው የያሉት ሲሏቸው /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ያሉትን አረብኛ ቃል ተናግረው ሕገ መንግስቱን መቃየር ነው የምንፈልገው በኃይል ብለዋል አሁን ጠበቃው ደጋግመው ነው ምስክሩን ወደ ማስገደድ እየሄዱ ያሉት እና አግባብ አይደለም
- ክቡር ፍ/ቤት እኔ የጠየኩት ድርጊቱን ነው ምን ድርጊት እንፈፅም አሉ ብለዋል ወይስ አላሉም ድርጊት አንድ የተወሰነ ድርጊት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ጥያቄው ምስክሩን ያስጨርስ አንድ 2 ጥያቄአችሁ 2 ነው ምን ለማድረግ ነው ሲባል ድርጊት አይደለም አሁን እሱ ሲመልስ ምንድን ነው እያደረጋችሁ እያደረጉ ያሉት ድርጊት እንዲመስክር ነው ግን ምን ለማድረግ ነው ድርጊቱን ምን ለማድረግ ነው እያሉ ነው የመስከሩት እሱን ደግሞ እየመለሰ ነው ምናልባት ከእዚህ ጋር አስተውሉ እና ድርጊት እና ሊደረግ የሚችል ድርጊት 2ቱ ይለያያሉ እሱን ቆይ ጥያቄው ትክክል ነው ነገር ግን የመጀመሪያው ተመልሷል ድርጊት ተፈፅሟል አላለም እሱም ግን ድርጊት ለመፈፀም ይሄንን ይሄንን ብለዋል እያሉ ነው ያሉት ምስክሩ ስለዚህ ከእዚህ የተለየ ማለት ሌላ የሚመልሱላቸው ጥያቄ ካለ ቀጥሉ ምስክሩ እንትኑንም ይጨርስ መልሱን ይጨርስ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እንፈፅም ያሉት የተለየ ድርጊት ምንድን ነው ጥያቄው ?
- ድርጊቱ በቃ መንግስትን ለመቃወም እና እስላማዊ መንግስት ለመመስረት የሚል ድርጊት ተቃውሞ /ግልፅ ያልሆነ/ ለመፈፀም
- ስለዚህ ተቃውሞ ብቻ ነው በተቃውሞ ነው ሰው መቃወም አለባችሁ /ግልፅ ያልሆነ/
- አሁን እሱ ጥያቄ ተገቢ አይደለም አሁን ምስክሩ ከመለሰ በኋላ ባለፈው ተነጋግረናል የራስህን ኃላብ መጨመር እራሱ መመስከር ስለሆነ እሱን አስተካክላችሁ ጠይቁ
- ሌላው ሀምዛ መስኪድ ላይ ክርስቲያኖቹ ለተጠሩት ክርስቲያኖች የጠራናቸው መንግስት ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት
- /ግልፅ ያልሆነ/

1449

http://ethcriminalawnetwork.com/

- መንግስት ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት ስላመጣብን ይሄንን እንድታውቁልን ነው መንግስት እስላማዊ መንግስት ለማቋቋም አስባችዋል ብሎ በሚዲያ የሚያወራው ሀሰት ነው ያሉት አውቀው ነው ክርስቲያኖችን ለማግባባት እንጂ የእውነት አይደለም ያሉት የግል አመለካከትዎ ነው?
- አይ ትክክል እንደዚያ ነው
- በምን አወቁ ?
- ሆን ብለው አውቀው
- በምን አወቁ ?
- ምክንያቱ ከመጀመሪያ የሚንቀሳቀሱት እስላማዊ መንግስት እንመሰርታለን ጅሀድ ብለው ካወሩ በኋላ ለሕፃን እንኳን እንደዚያ አይባልም እንደዚያ ብለው እያወጁ ጅሀድ ነው እያሉ እስላማዊ መንግስት እንመሰርታለን እያሉ እንግዲህ እንደዚህ ብሎ ሲል ይሄ ግልፅ ነገር ነው
- ስለዚህ የግል አስተያየት ነው ማለት ነው እርሶ የደረሱበት ?
- አይደለም ያሉት እንደዚያ ነው
- ያሉት እንደዚያ ነው እያሉ ስለሆነ እሱን /ግልፅ ያልሆነ/
- አይደለም ይሄንን አውቀው ነው /ግልፅ ያልሆነ/
- እነሱ እስላማዊ መንግስት እንመሰርታለን ብሎ አውቆ መንግስት /ግልፅ ያልሆነ/ ነው ነው ያሉት እነሱ ግን መጀመሪያ ጅሀድ ብለው አውጀዋል ጅሀድ ብለው ካወጁ እስታጥኒዛም ካሉ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ እንፈልጋለን ካሉ እስላማዊ መንግስት እናቋቁማለን ካሉ ከእዚህ በላይ ትርጉም ምን አለው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ አሁን
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አቶ አህመድ ቅድም እስቲ ከሀምዛ መስኪድ እንጀምር እና እርሶ ሀምዛ መስኪድ የት ጋር ነበሩ ?
- ውስጥ ነበርኩኝ
- ውስጥ ነበሩ ስለዚህ ተከሣሾች ይናገሩ የነበረው የት ጋር ሆነው ነበር ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፊት ለፊት ላይ ሆነው
- ፊት ለፊት ላይ ? ...
- አዎ
- እስቲ እያንዳንዱ ምን ዓይነት ሁኔታ ፊት ለፊት ምን ነበረ የሚናገሩት ቆመው ይሁን ቁጭ ብለው ይሁን አለባበሳቸው ምን ይመስል እንደነበረ መድረክ ይኑር አይኑር እነዚህን ነገሮች እስቲ ይግለፁልን እዚያው ውስጥ ስለነበሩ ይሄንን ነገር ሁሉ ያዩ ነበር አይደል ?
- ጥያቄው አንድ አንድ ይሁን
- አንዳንድ እሺ አይ ለማስታወስ ያህል ነው አንድ በአንድ እጠይቃለሁ ጥሩ መጀመሪያ የተናገረው ማን ነበር ?
- አቡበከር አህመድ
- አቡበከር አህመድ ከመናገሩ በፊት የተናገረ ሰው የለም ?
- አዎ እኔ /ግልፅ ያልሆነ/
- አላጋጠሞትም ጥሩ አቡበከር አህመድ እንዴት ነበር የተናገረው ማለት ቆሞ ነው ወይስ ቁጭ ብሎ ?
- ቁጭ ብሎ ነው የተናገረው
- ቁጭ ብሎ በማይክ ነው ወይስ ያለማይክ ?
- በማይክ ነው
- በማይክ ነው አቡበከር ቁጭ ሲል ከፊት ለፊቱ ምን ነገር ነበር ማለት ጠረቤዛ እንደዚህ መድረክ ነገር ነበረ ?
- አይ እንደዚያ አልነበረም ሰው በሙሉ ቁጭ ብሎ ነበረ
- ቁጭ ብሎ ዝም ብሎ በወንበር ቁጭ ብሎ ነበር ?
- አዎ
- ከፊት ለፊቱ ምንም አልነበረም ?
- ሰው ነበረ
- አይደለም አይ አቡበከር ሲቀመጥ ከፊት ለፊቱ ውኃ ነገር ጠረቤዛ ነገር እንደዚህ አልተደረገለትም ?

1451

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሄን እኔ አላስታውስም ቁጭ ብሎ መኖሩ ብቻ ነው የማውቀው
- አለባበሱ ምን ይመስል ነበር ማለት ጀለቢያ ነበረ ኮት እና ሱሪ ነበረ ኮፍያ ነበረ እነዚህ ነገሮች ?
- አይ ስለአለባበሱ አሁን ትዝ አይለኝም
- ትዝ አይሎትም ጥሩ ከእዚያ ቀጥሎ ማን ነው የተናገረው ?
- አህመዲን ጀባል
- አህመዲንም እንደዚህ ቁጭ ብሎ ነው የተናገረው ?
- አይ ቆሞ ነበር የተናገረው
- ቆሞ ነበር የእሱንም አለባበስ አያውቁትም ?
- ትዝ አይለኝም
- ጥሩ ቀጥሎ ማን ነው ?
- ቀጥሎ ሳቢር ነበር የተናገረው
- ኃይማኖታዊ መንግስት እንመሰርታለን አለ እንጂ አቡበከር መቼ እንደሚመሰርቱ አልተናገረም አይደል ?
- አቡበከር
- ይቺን ቃል ብቻ ?
- አቡበከር በእዚያ መስኪድ ሀምዛ አቡበከር ቁጭ ብሎ ነው የተናገረው ቁጭ ብሎ ነው ተናገረ ስለዚህ የተናገረው ደግሞ ቅድም
- ይኸውሎት ምስክር አሁን ጥያቄው የመጨረሻው መቼ እንመሰርታለን ነው ይሄ እስላማዊ መንግስት የሚባለውን መቼ እንመሰርታለን አሉ ነው ጥያቄው ?
- አይ ቀኑ አልጠቀሰም ለእዚህ ቀን አላለም /ግልፅ ያልሆነ/
- ቀጥሉ ?
- እንመሰርታለን እንጂ የት ቦታ እንመሰርታለን የሚለውንም አልገለፁም ?
- አልገለፁም ይሄንን
- እንዴት እንመሰርታለን የሚለውንም አልገለፀም ?
- እንደዚህ እስላማዊ መንግስት እንመሰርታለን እንጂ እንደዚያ አላለም

145

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አወሊያ መስኪድስ አወሊያ መሰበሰቢያ ሰርጉ ከመስኪድ ውጪ ነው ወይስ መስኪድ ውስጥ ነበሩ ?
- እኔ ከመስኪድ ውጪ ነበርኩኝ
- ከመስኪድ ውጪ ሆነው ነው የሰሚቸው ?
- አዎ
- ተናጋሪው እራሱ አሁን ተከሣሾች ስለመሆናቸው በምን አወቁ ?
- ስማቸው እየተጠቀሰ ነበረ
- ማን ነበር የሚጠቅሰው ?
- ማን እንደሆነ ስሙ ባላውቀውም ውጪ ስለነበርኩኝ ግን አቡበከር አህመድ ይናገራል መሪያቸን ነው አቡበከር አህመድ ይናገራል ይላል ከእዚያ በኋላ ደግሞ የታሪክ ሙሁር አህመዲን ጀባል ይናገራል እያሉ በየተራ ይናገሩ ስለነበር በእዚህ አወኳቸው
- ስለዚህ እራሳቸው ስማቸውን እያስተዋወቁ አልነበረም ማለት ነው ?
- አዎ
- ሌላ ሰው ነበር የሚያስተዋውቅላቸው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እሺ ይቅርታ አልጨረሱም
- ቀጥሉ ጥያቄ
- እርሶ እነ አቡበከርን ስንት ጊዜ ነው ያዩዋቸው ቅድም አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያየሁ ያሉትን እነ ማንን ነው ?
- አቡበከር አህመድ አህመዲን ጀባል እዚያ መስኪድ ሀምዛ ውስጥ አይቼአቸዋለሁ
- ስለዚህ በአካል ያያቸው ሀምዛ መስኪድ ነው ?
- አዎ
- በአካል ያዩዋቸው ?
- አዎ
- ከእዚያ በፊት አያውቋቸውም ?
- አላውቃቸውም

1453

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ አወሊያ ጥናቱ የሚሰጠው ድምፃቸው በእስጢፋኖስ አቡበከር እከሌ እከሌ ሲባል ስለሰሙ ነው አይደል ?
- አዎ
- ጥሩ እርሶ ያዩት ሀምዛ መስኪድ ከሆነ ከእዚያ በፊት የማውቋቸው ከሆነ አቡበከር ይናገር አቡበከር አህመድ ይናገራል ተብሎ አቡበካር ይናገር ወይም ሌላ ሰው ስለመናገሩ አርግጠኛ ሊሆኑ አይችሉም አይደል ?
- እርግጠኛ ነኝ ምክንያቱም አቡበከር አህመድ ብሎ ከተናገረ የአቡበከር አህመድ ንግግር ከጨረሰ በኋላ ደግሞ እሱ አህመዲን ጀባል ይናገራል ብሎ ስለጋበዘው በእዚህ እርግጠኛ ነበርኩኝ
- ስለዚህ ከእዚህ በመነሳት ነው እርሶ እርግጠኛ የሆኑት ?
- አዎ
- በዕለቱ የእነሱ ድምፅ የሚመስል ተቀርፆ ይተላለፍ ወይም ደግሞ ሌላ ጊዜ የተናገሩት ይተላለፍ ወይም በዕለቱ ገብተው ይተላለፉ እርግጠኛ መሆን አይችሉም ?
- አይ እርግጠኛ ነኝ ምክንያቱም ቆመው ሁሌ ስለሚናገሩ በየጁማው እነሱም ወጥተው እንደሚናገሩ ስለማውቅ በእዚህ እርግጠኛ ነበርኩኝ
- እርሶ እኮ የሚያውቋቸው ሀምዛ መስኪድ ነው ከእዚያ በፊት አያውቋቸውም ?
- ሀምዛ መስኪድ ነው የማውቃቸው ግን ስማቸው እየተጠቀሰ ሲናገር ያው እነሱ መሆናቸው አረጋግጬአለሁ
- ቅድም ጅሀድ የሚለውን ከተሳሳትኩ ያርሙኛል ጦርነት ማለት ነው ብለዋል ትክክል ነኝ ?
- አዎ
- ይሄ ትርጉም ጦርነት መሆኑን በምን አወቁ ?
- ይሄ ግልፅ ነው ጅሀድ ማለት በአረብኛ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ጦርነት ማለት ነው
- ከእዚህ ውጪ ሌላ ትርጉም የለውም ጅሀድ የሚለው ?
- ጅሀድ ሌላ ከእዚህ እኔ የማውቀው የለውም ጦርነት ማለት ካልሆነ በስተቀር
- ጦርነት ብቻ ነው አረብኛ ትርጉም ሲሉ የትኛው የአረብኛ ትርጉም ማለትዎ ነው ማለት ዲክሽነሪ አይተው መዝገበ ቃላት አገላብጠው ነው ወይስ ከእዚያ በፊት ያውቁታል ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ሙስሊም እንደመሆኔ መጠን ጅሀድ ሲባል ጦርነት መሆኑን ነው እኔ የማውቀው
- የሚያውቁት ሌላ ትርጉም እንዳለው አያውቁም ?
- አዎ በቅስቀሳ /ግልፅ ያልሆነ/ አንፃር ስትመለከተው ደግሞ ጅሀድ ብለው ሲጠቅሱ ያው ጦርነት መሆኑ ለአመፅ መሆኑ ግልፅ ነው
- ይበቃል ሌላ ጥያቄ
- አንዋርስ አንዋር መስኪድ ላይ እርሶ የት ጋር ሆነው ነበር ያዩት ?
- እኔ ውስጥ ነበርኩኝ
- መስኪድ ውስጥ ?
- አዎ
- ጥሩ ማለት ተከሣሾቹን ፊት ለፊት በአይን ያዩዋቸው ነበር ?
- አህመዲን ጀባል ሲናገር አይቼዋለሁ
- ሌሎች ሌላው ሲናገርስ ?
- እኔ አህመዲን ጀባል ብቻ ንግግር ሰምቼ ነው ቅድም እንደተናገርኩት የሄድኩት
- አሀ የአህመዲንን ብቻ ነው የሰሙት ?
- አዎ
- በዕለቱ አህመዲን በስንት ሰዓት እንደተናገረ ያስታውሳሉ ?
- ወደ 4 ሰዓት አካባቢ ይሆናል
- 4 ሰዓት እርሶ ስንት ሰዓት ነበር የገቡት እዚያ መስኪድ ውስጥ ስንት ሰዓት ነበር የገቡት ?
- እኔ ሰው ተሰብስቦ ሳይ ወደ 4 ሰዓት አካባቢ ነበር የገባሁት
- የገቡት ?
- አዎ
- 4 ሰዓት ሲገቡ እርሶ ቦታ አግኝተው ገቡ ማለት ነው ?
- አዎ
- ማለት አልተጨናነቀም ነበር ግቢው?
- አይ ክፍት ቦታ ነበር ገባሁ
- ምን ቁጭ ብሎ ወይስ ቆሞ ነበር የሚናገረው ?

1455

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆሞ ነበር የሚናገረው
- በማይክ ነበር የሚናገረው ?
- በማይክ ነበር የሚናገረው
- አመሰግናለሁ አቶ ሀምዛ አወሊያ የት ነው የሚገኘው ?
- አወሊያ ወደ ኮልፌ ነው ወረዳ ስንት እንደሆነ ባላስታውስም
- ቦታው ?
- ውንጌት አካባቢ አለፍ ብሎ ነው የሚገኘው
- ቦታው በቦሌ ነው በካራቆሬ ነው ?
- አይ ወደ ውንጌት ኮልፌ ቀራንዮ
- ኮልፌ ቀራንዮ እኮ መንገዱ ለምሳሌ ከፒያሳ ለማያውቀው ሰው
- እስቲ ቆይ አሁን ውንጌት አለፍ ብሎ ነው ብለዋል ከእሱ ቀጥሎ ይጠይቁ
- ሀምዛ መስኪድ የት ነው የሚገኘው ?
- ሀምዛ መስኪድ ወረዳ 3 ኮልፌ ቀራንዮ
- ቅድም ሲያስረዱ /ግልፅ ያልሆነ/ ኢስቃጠኒዛም እያሉ ይናገሩ ነበር ብለዋል ?
- አዎ
- እርሶ ትርጉምን ያውቁታል እንዴ ?
- አዎ አውቀዋለሁ
- እስቲ ለፍ/ቤት ቃል በቃል ዓረፍተ ነገሩ ሳይሆን ሻብ ማለት ምን ማለት ነው ዩሪድ ምን ማለት ነው ኢስቃጥ ምን ማለት ነው ኒዛን ምን ማለት ነው የሚለውን ያስረዱልን ሺአብ ምን ማለት ነው ሺአብ ማለት ምን ማለት ነው ?
- እሺ ክቡር ፍ/ቤት ከእዚህ በላይ ሞተንተን ይቻላል ችግር የለም ለመመለሱ አልሻብ ማለት ሕዝብ ማለት ነው ዩሪድ ይፈልጋል ማለት ነው ኢስቃጥ ማለት ለውጥ ኢስቃጥኒዛን ማለት ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይፈልጋል ማለት ነው
- ኒዛን ምን ማለት ነው ኒዛን ሕገ መንግስት ማለት ነው ?
- ሕገ መንግስታዊ ለውጥ አልሻብ ዩሪድ ሕዝቢ አልሻብ ማለት ሕዝብ ነው ዩሪድ ይፈልጋል እስቃጠኒዛ ማለቱ ሲደመር ሕገ መንግስቲ ለውጥ ይፈልጋል ማለት ነው

1456

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እና ሕገ መንግስታዊ ለውጥ መፈለግ ምን ተግባር አለው ታሜያ ፡
- ሕግ ባለበት ሀገር
- አሁን ይሄ
- ጥያቄውን ትቼዋለሁ የተከበረው ፍ/ቤት
- ጅሀድ ብለው አውጀዋል ብለዋል በማይክራፎን ነው ጅሀድ እያሉ ሲያውጁ የነበሩት ?
- ጥያቄው ይደገምልኝ

- ጅሀድ ብለው አውጀዋል ሲሉ ነበረ በማይክራፎን ነው ጅሀድ ነው እያሉ ሲያውጁ የነበሩ ?
- በአደባባይ በማይክራፎን ግልፅ ባለ ሕዝብ በተሰበሰበበት
- የሁሉም መስኪዶች ላይ ?
- አዎ
- ሀምዛ መስኪድ ክርስቲያኖች ነበሩ ብለውናል ?
- አዎ
- ክርስቲያኖች ባሉበት ነው ጅሀድ እያሉ ሲያውጁ የነበሩ?
- አዎ
- ክርስቲያኖቹ ምን አሉ አብረን እንወጣለን አሉ ወይስ ምን አሉ ?
- ተጋብዘው መጥተዋል ምናልባት እርሶ እንዳሉት አረብኛ ትርጉሙ ላይገባቸው ይችል ይሆናል
- የተደረገውን ብቻ ያሉት ነገር ካለ ያሉት ነገር አለ ክርስቲያኖች ያን ቀን ?
- ምንም ያሉ የለም
- እስከ መጨረሻው ፕሮግራሙን ሲከታተሉ ነበር ቁጭ ብለው ?
- እኔ እስከ 9 ሰዓት ተኩል አካባቢ ነበርኩኝ እስከ እዚያ ድረስ የተወሰኑ ነበሩ የሄዱም ነበሩ
- ፕሮግራሙ ስንት ሰዓት ተጀመረ ጠዋት
- እኔ የገባሁት 3 ሰዓት ነው ከእዚያ በፊት የተጀመረ ይመስለኛል
- ካእዘ የ በፊት ነው የተጀመረው ?
- አዎ
- እርሶ በገቡበት ወቅት ክርስቲያኖች አይተዋል ?

1457

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ በደንብ አርጅቶአል ወንበር የዘራኝ የነጥቦል በሰነ ስርዓት ሁኖ በፊት ነበር
- መስኪድ ውስጥ ?
- ግቢ ውስጥ መስኪድ ግቢ ውስጥ ሞልቶ መስኪዱማ ሞልቷል ግቢ ውስጥ ነበረ ድንኳን ተሰርቷል ብዙ ድንኳኖች ነበሩ
- ከአወሊያ እና ከሀምዛ መስኪድ የትኛው ላይ ነው ተከሣሾቹ ቀድመው ንግግር ያደረጉት ?
- የአወሊያ ቀድመው ተናገሩ ከእዚያ በኋላ መስኪዳ ሀምዛ ተናገሩ
- ከእዚያ በኋላ መጨረሻ ላይ ነው አንዋር የተናገሩት ?
- ከእዚያ በኋላ አንዋር መጨረሻ 3ኛ አንዋር
- ከሀምዛ እና ከአንዋር የቱ ይቀድማል ከሀምዛ መስኪድ እና ከአንዋር መስኪድ ?
- ሀምዛ ይቀድማል ከእዚያ አንዋር ተናገሩ
- እሺ አቶ አህመድ እነዚህ 3ቱ መስኪዶች አሁን ያሏቸው የጠቀሷቸው 3ቱ መስኪዶች በተለያየ ቦታ ላይ የሚገኙ መስኪዶች ናቸው አይደል ?
- አዎ
- በእነዚህ 3ቱም ቦታዎች ላይ በተለያየ ቀን እርሶ የተገኙበት ምክንያት ምንድን ነው ?
- አቤት ይደገምልኝ
- በ3ቱ መስኪዶች በእነዚህ በተለያዩ ቀናት እርሶ የተገኙት ለምንድን ነው ?
- መቃወሚያ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄ ቀደም ሲል ብይን የተሰጠበት ጉዳይ ነው ስለምስክሩ ግላዊ ሁኔታ እንዴት ሄዱ አድራሻን ቦታን ማዕከል ያደረገ ነገር ሊጠየቅ አይገባም አግባብነት የለውም ከብይኑ ጋር የሚጋጭ ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/ ?
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤ እኔ ስለምስክሩ የግል ሁኔታ ፍ/ቤቱ በብይን እንዳይገለፁ ያደረጋቸውን ነገር አይደለም የጠየኩት ምስክሩ ግን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያውቁትን ነገር ነው የሚሰረዱት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያወቁበትን ሁኔታ ነው አሁን የጠየኩት 3ቱ መስኪዶች ላይ እርሶ የተገኙት ለምንድን ነው ነው ?

1458

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መጨረሻ ላይ ምስክሩ እዚያ ቦታ ለምን ሄዱ እየተባሉ ነው የተጠየቁት ስለዚህ ይሄ ከአድራሻ ጋር የሚያያዝም ስላልሆነ እሳቸው ግላዊ ሕይወት ጋር የሚያያዝ ስላልሆነ እዚያ ቦታ ላይ ለምን ሄዱ በምን ተገኙ ምክንያቱም እዚያ ተገኝተው እየመሰከሩ ስለሆነ ለምን ሄዱ የሚለው ጥያቄ አግባብ ነው ጠበቃ ቀጥሉ ብለናል
- ለምን እንደሄድኩ ለማብራራት ነኛ አወሊያ መስኪድ ለመስገድ ሄድኩኝ ወደ 7 ሰዓት አካባቢ ነበረ መስኪድ ሀምዛ አካባቢዬ እዚያ ነው የሰደቃ እና የዳዋ ፕሮግራም ጥሪ ተደርጎልኛም ነበረ በጥሪ መሠረት ሄጃለሁ አንዋር መስኪድ ደግሞ ለስራ ስሄድ ጊዜ ያልተለመደ ሰዓት በ 4 ሰዓት በማይክራፎን ሲነገር ስሰማ ምን መጣ ብዬ ወይ ሌላ ትምህርታዊ አለ ብዬ ስገባ ሰማሁ
- በሀምዛ መስኪድ የሰደቃ ፕሮግራም ጥሪ ተደርጎልኛል ብለዋል የፕሮግራሙ መጥሪያ ምንድን ነው የሚለው የአንድነት እና የሰደቃ ፕሮግራም ነው የሚለው ወይስ ምንድን ነው የሚለው ?
- የአንድነት እና የሰደቃ ፕሮግራም ነው የሚለው
- አንድነት ማለት ምን ማለት ነው ?
- አይደለም ይቅርታ የዳዋ እና የሰደቃ ፕሮግራም ነው የሚለው የዳዋ እና የሰደቃ ፕሮግራም ነው የሚለው
- ዳዋ ማለት ምን ማለት ነው ?
- እንግዲህ ዳዋ ማለት ስለ ኃይማኖት ትምህርታዊ ምናምን የሚሰጥበት ነው
- ስለዚህ የኃይማኖት ትምህርት የሚሰጥበት ስደቃስ ማለት ምን ማለት ነው ?
- ሰደቃ ደግሞ ላጡ ሰዎች ለምስኪኖች እርዳታ የሚሰጥበት ነው
- ስለዚህ 2ቱም የሚደረግበት ፕሮግራም ተብሎ ነው የተጠራው በሀምዛ መስኪድ በተደረገው ፕሮግራም ላይ እነዚህ 2ቱም ድርጊቶች ተፈፀመ ማለት ትምህርትም ተሰጥቷል መጋበዝም ፕሮግራም ተፈፅሟል አይደል ?
- አይደለም ይሄ በዳዋ ሽፋን በኃይማኖት
- አይደለም አስተያየትዎን አይደለም ?
- አስተያየት አይደለም ጥያቄ ልመልስ
- ጥያቄዬን ተረዱኝ

1459

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆይ አሁን ምስክር የሚያደርጉት ምንድን ነው ግብጣ ተደርጓል ትምህርት ተሰጥቷል ነው ጥያቄው ተሰጥቷል አልተሰጠም ይቺን ብቻ ?
- ትምህርት አልተሰጠም ቅስቀሳ ነበር የተሰጠው
- ቀጥሉ
- ቅድም ሀባሽ የሚል አስተምሮ መንግስት አመጣብን ብለው ያስተምሩ ነበር ብለዋል ሀባሽ የሚባል ትምህርት አስተምሮ አለ እንዴ ?
- ይደገምልኝ ጥያቄው
- ሀባሽ የሚባል አለ ወይ እንዲህ ዓይነት አስተምሮ አለ ወይ ?
- ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት የለም
- እንደዚህ የሚባል አስተምሮም የለም ?
- እንደዚያ ብሎ ኃይማኖት ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት የለም እንደዚያ ብሎ አስተምሮት ግን
- ግልፅ ነው ቀጥሉ
- አስተምሮት ግን ብለው የቆሙት አስተምሮቱ አለ ወይ ነው ግን ብለው ነው ?
- አለ አስተምሮቱ ?
- የለም ሀባሽ የሚባል የለም
- አንድ ሰው ስለ ኃይማኖቱ ከራሱ ጋር ከውስጡ የሚያደርገው ትግል ማለት በኃይማኖቱ እራሱን አስገዝቶ ነብሱን በአምላክ አስገዝቶ ለመኖር የሚያደርገው ትግል ጅሀድ ነው የሚባለው አይደል ?
- አይደለም ይሄ ኢባዳ ይባላል ጅሀድ ጦርነት ነው
- ምንድን ነው የሚባለው ?
- ኢባዳ ወይም ለአላህ መገዛት ነው እንጂ ጅሀድ ሊባል አይችልም ደግሞ ጅሀድ እንኳን ቢባል በውስጥ ከአላህ ጋር የምታነጋግረው ነው እንጂ ለሰው እየሰበሰብክ መፈክር እያሰማህ አይደለም እሱ ጅሀድ አይደለም
- በሀምዛ መስኪድ በተደረገው ፕሮግራም ላይ ክርስቲያኖችም ተገኝተው ነበር ለክርስቲያኖቹ ሳቢር ንግግር ሲያደርግ ክርስቲያን ወንድሞቻችንን ከእኛ ጋር አብራችሁ ሁኑ ብለዋል ነው ያሉት አይደል ?

1460

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ክርስቲያኖችን ወንድሞቻችን ነው ያላቸው አይደል ?
- እንግዲህ ከጋበዟቸው ወንድሞቻችን
- ያሉትን ያሉትን ?
- አዎ እንደሱ ነው ያላቸው
- በሀምዛ መስኪዱ ፕሮግራም ላይ ከያሲን ኑሩ ሌላ ማን ነው ከሳቢር ይርጉ ሌላ አቡበከር ነበር ብለዋል ሌላስ ማን ነበር ?
- እኔ የሰማሁት አቡበከር አህመዲን ጀባል እና ሳቢር ይርጉ ሲናገሩ ነው
- እነዚህ 3ቱ ሳቢር ክርስቲያኖቹን ወንድሞቻችን ሲላቸው እነሱ ምንም የተቃወሙት ነገር የለም አይደል ?
- ያሉት ነገር የለም
- ራዕይ በሚለው መፅሔት ላይ መንግስት ከፋፍሎናል ብለው ተናግረዋል ብለዋል ራዕይ የሚለውን መፅሔት እርሶ አይተውታል ?
- በእርግጥ በእጁ ይዞት ነበረ
- አይ እርሶ አይተውታል ወይ ነው ?
- እኔ በእጁ መያዙን ነው እንጂ እኔ
- አይ እርሶ መፅሐፉን አይተውታል አላዩትም ?
- አላየሁትም
- አንብበውታል ወይ ማለት ነው ?
- አላነበብኩትም አላየሁትም
- ቅድም ሕዝቡ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይፈልጋል ብለዋል ነው ያሉት ትክክል ነኝ ?
- አዎ
- ሕዝቡ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይፈልጋል ነው ያለው ?
- አዎ
- አዎ እያሉ ነው ጠበቃ
- የሀምዛው መስኪድ ፕሮግራም ስንት ሰዓት ላይ ነው ያለቀው ?

1461

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይደገምልኝ
- የሀምዛ መስኪድ ፕሮግራም ሰንት ሰዓት ላይ ነው ያለቀው ?
- እኔ ወደ 9 ሰዓት ተኩል ሄድኩኝ ከእዚያ ይቆይ አይቆይ አላወኩም
- እርሶ ስንት ሰዓት ነው የሄዱት መጀመሪያ ጠዋት ?
- ወደ 3 ሰዓት አካባቢ ይሆናል
- ጠዋት 3 ሰዓት እስከ 9 ተኩል ድረስ ቆይተዋል ?
- አዎ
- እርሶ በቆዩበት ጊዜ በመስኪዱ በሚደረገው ፕሮግራም ላይ ምንም ዓይነት ብጥብጥ ነገር አልነበረም አይደል ?
- እኔ ውስጥ ነበርኩኝ ውጪ ብዙ ሰው ስለሆነ ይኑር አይኑር እርግጠኛ አይደለሁም
- እርሶ ያዩትን ያዩትን ነው የጠየኮት እርሶ ያዩት ምንም ብጥብጥ ፕሮግራም የለም አይደል ?
- ያው እርግጠኛ አይደለሁም ያሉ ስለሆነ
- አይ እሳቸው እራሳቸው ያዩትን ውስጥ በነበሩበት ቦታ ላይ ያዩትን ያዩትን ይመስክሩልኝ ምንም ባዩት እርሶ ምንም ብጥብጥ አልነበረም አይደል ?
- ይሄንን እኮ መልሰዋል ያ ማለት እኔ ያየሁት የለም ማለት እኮ ነው በሌላ አገላለፅ
- እሺ ፍ/ቤቱ በእሱ መልክ ከተረዳልን እሺ
- ተከሣሾች ንግግር ሲያደርጉ ነበር ብለዋል አቡበከር አህመዲን /ግልፅ ያልሆነ/ ሳቢር ንግግር ሲያደርጉ ነበር ብለዋል በሀምዛ መስኪድ ላይ እነሱ ያደረጉትን ንግግር የተቃወመ ሰው የለም አይደል ?
- እኔ በተቃውሞ የሰማሁት ነገር የለም ይኑር አይኑር ውጪ ውስጥም አላየሁም
- ከሀምዛው መስኪድ ፕሮግራም ሌላ በአንዋር መስኪድ በተደረገው ፕሮግራም ላይ ስማቸውን ያወኩት ብለው ቅድም ሲያስረዱ አቡበከር መሪያቸን ነው አሁን እሱ ይናገራል ብሎ ሌላ ሰው አስተዋውቆት ነው ንግግር ያደረገው ብለዋል ልክ ነኝ ?
- አይ አንዋር መስኪድ አይደለም
- የት ነው ይሄ ?
- ይሄ አወሊያ ነው ያልኩት

1462

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አወሊያ ላይ አቡበከር መሪያቸን ነው አሁን ይናገራል ብሎ ሌላ ሰው አስተዋውቆት ነው የተናገረው አይደል

ይደገምልኝ

- አቡበከር መሪያቸን ነው አሁን ይናገራል ብሎ ሌላ ሰው አስተዋውቆት ነው የተናገረው አይደል ?
- አዎ
- እሱን እኮ መልሰዋል ምን ልትጠይቁ ነው አሁን ቅድም እሳቸው ጠይቀው በግልፅ ተመልሷል
- እሺ አይ አቡበከር መሪያችን አይደለም ብሎ የተቃወመ ሰው አልነበረም አይደል ?
- እኔ እሱ አልሰማሁም
- አህመዲንስ ምን ብሎ ነው ያስተዋወቀው አህመዲን ምን ብሎ አስተዋውቆት ነው የተናገረው እሱም ተናግሯል ብለዋል ?
- አዎ የታሪክ ሙሁር አህመዲን ጀባል አሁን ይናገራል ብለዋል
- እኮ ምንድን ነው ብሎ ነው የተናገረው ?
- ማን አህመዲን ጀባል በቃ ይሄ ሀባሽ ኃይማኖት መንግስት አምጥቷል
- አይደለም ቅድም አቡበከርን መሪያችን ነው ብሎ እንዳስተዋወቀው አህመዲንንስ ምን ብሎ አስተዋወቀ ነው ?
- አህመዲን ጀባል አሁን ይናገራል የታሪክ ሙሁር አህመዲን ጀባል ይናገራል ብሎ ነው የተናገረው
- ስለዚህ ምንም ያስተዋወቀው ነገር የለም ስለ እሱ ?
- አዎ
- ስለካሚል ሸምሱስ ?
- አይ ስለእዚያ ስለእነዚያ አራሳቸው ካምል ሸምሱ ይናገራል እንደዚያ ይናገራል ያሲን ኑሩ ይናገራል ተብሎ ያው በየተራ እነሱ መሆናቸው ከተጠቀሰ በኋላ ተናገሩ
- እንጂ ሌላ ስለእነሱ የተነገረ ነገር የለም ?
- አዎ

1463

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ልቀጥል ነው
- ቀጥሉ
- አቶ አህመድ ዕለቶቹን ያስታውሳሉ መቼ መቼ እንደሆኑ አወሊያ መቼ እንደተካሄደ ሀምዛ መቼ እንደተካሄደ እና አንዋር መቼ መቼ እንደነበረ
- ቅድም የገለፅኩት ይመስለኛል ከግንቦት እስከ ሚያዝያ አካባቢ ይሆናል
- ዕለቶቹ
- ዕለቱ ዕለቱን ያውቁታል ?
- አይ አላውቀውም እለቱ ቀኑ
- አያስታውሱትም ?
- አላስታውሰውም
- ሌላ ጥያቄ
- ቀኖቹን በትክክል አያስታውሱም ?
- አዎ
- መገመት አይችሉም ከሰኞ እስከ አርብ
- አይ አልችልም
- አያውቋቸውም ?
- ያው ግልፅ እኮ ነው በቃ እንደዚህ ካሉ ይበቃቸዋል
- አህመዲን ሀምዛ መስኪድ የተናገረው ከምሳ በፊት ነው በኋላ ነው ?
- ከምሳ በኋላ
- ቅድም አንዋር መስኪድ ነበረ ብለዋል አንዋር መስኪድስ ዕለቱንም አያስታውሱትም ?
- ሐምሌ 8 ነው አህመዲን ጀባል የተናገረው
- ነው ?
- ጠዋት 4 ሰዓት አካባቢ ነው
- ሐምሌ 8 ምን ላይ እንደሚውል አያውቁም ?
- እሁድ ነበር
- እሁድ ዕለት ?

1464.

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እርሶ የት ነበሩ በእዚህ ሰዓት አንዋር አሱ ንግግር ሲያደርግ የት ነበሩ ?
- አንዋር መስኪድ-ውስጥ ገብቼ ነበር ብዬአለሁ
- ውስጥ ነበሩ ?
- ይሄ ጥያቄም ተጠይቆ ተመልሷል እኮ
- እንትን ልል ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- አሁን ይኸው ጥያቄውን ጠይቁ አሁን ቅድም ተጠይቆ የት ውስጥ ነበሩ ውጪ ነበሩ ውስጥ ነበሩ እንዴት አወቁ ተብሎ እሳቸው ተጠይቀዋል
- እሺ አህመዲን ጀባል የቱ ጋር ሆኖ ንግግር አደረገ ?
- መስኪድ ውስጥ ፊት ለፊት ሆኖ
- መስኪዱ ውስጥ ?
- አዎ
- ማለት ኢማሙ የሚያሰግዱበት ?
- ኢማም በሚያሰግድበት ፊት ለፊት ሆኖ ወደ ሕዝብ እያየ ነው የተናገረው
- ለእርሶ የሚታዮት ቦታ ነበር አህመዲን ?
- እሱም ተጠይቋል እስቲ ጠበቃ እስካሁን ያው ሲጠየቅ የነበረ ነው እየጠየቁ ያለው እስቲ አዲስ ነገር ካላችሁ የት ላይ ሆኖ ነው ይናገሩ የነበረ የሚል የት ሆነው ነበር ይናገሩ ነበር ተብሎ እኔ ውስጥ ነበርኩ ምናምን ተብሎ ተጠይቋል
- እርሶ ስንት ሰዓት ወጡ ከአንዋር?
- እኔ ከአንዋር ሶላት ሰግጄ ማን ነው ሶላት ከመስገዴ በፊት ስራ ስለነበረኝ ወጥቼ ሄድኩኝ
- ሳይሰግዱ ወጡ ?
- ሳልሰግድ ነው የወጣሁት
- ሲገቡስ ስንት ሰዓት ገቡ ?
- ወደ 4 ሰዓት
- ሲገቡ ሲወጡ እንዴት ነበር በሩ ያስገባ ነበር ሕዝብ ብዛት ነበረው ?
- እዚያ የሚፈትሹ ወጣቶች ነበሩ

1465

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምን ዓይነት ወጣቶች ?
- ወጣቶች ወጣት ወጣት እንዴት ልበል
- ያዩዋቸዋል ፊታቸውን ለይተው ፊታቸው ይታዮታል ?
- አዎ ያኔ ያየውን ፈትሸው ያገባሉ ስትወጣ ዝም ብለህ ትወጣለህ
- በየትኛው በር በኩል ነበር የሚፈተሸው ?
- እኔ በሰላም ሆቴል ፊት ለፊት ነበር የገባሁት በእዚያ ተፈትሼ ገባሁ
- ፖሊሶች አልነበሩም ?
- አላየሁም
- አላዩም?
- አልነበሩም
- ስለዚህ የሚፈትሹ ሰዎቹን ማየት ይችላሉ የተሸፋፈነ ሰው የለም ?
- አዎ የተሸፋፈኑ ነበሩ ነፃ ዝም ብሎ ወጣትም ነበሩ
- የትኞቹ ?
- ያ በቃ እዚያ ወጣት የተሸፈነ ወጣት /ግልፅ ያልሆነ/ ያደረገ ነበር ዝም ብሎ ኮፍያም ሳያደርግ ዝም ብሎ እንደኔ ዓይነቱም ነበር
- ኮፍያ እና /ግልፅ ያልሆነ/ ምን ማለት ነው
- ነበረ ያልነበራቸውም ነበሩ እንደማንኛውም ጊዜ ማለት ነው
- /ግልፅ ያልሆነ/ በሀምዛ እና በአወሊያ መስኪድ የተደረገውን ፕሮግራም ማን እንዳዘጋጀ ያውቃሉ ?
- እንግዲህ እኔ በሀምዛ መስኪድ አቡበከር እራሱ እንደጠቀሰው በመላ ሀገሪቱ በ 80 መስኪድ ያዘጋጀነው የሰደቃ እና የዳዋ ፕሮግራም አንዱ የእዚህ መስኪድ ሀምዛ ነው ሲል አቡበከር አህመድ ተናግሯል ስለዚህ እነሱ እንዳዘጋጁ እርግጠኛ ነበርኩኝ ማለት ነው
- እርግጠኛ ኖት ግምት ነው አቡበከር ከመናገሩ
- እርግጠኛ ነኝ በጣም እርግጠኛ ነኝ
- እርግጠኛ ያሉበት ምክንያት አቡበከር

1466

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይሽውሎት ቢቃ ይሄንን መለሱ ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲጠየቁ ይሄንን በማለታቸው ምክንያት እነሱ ናቸው ያዘጋጁት ብዬ ወስጀአለሁ አሉ
- እኮ ግምት ነው እኮ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- እኮ ና እሱ ግምት ነው ግምት አይደለም
- ለፍ/ቤት እንተወው እሺ
- ቅድም አወሊያ ወይም አምዛ መስኪድ የተፈጠረ ነገር የለም ብለው ነበር አንዋርስ የተፈጠረ ነገር አለ ?
- በቃ እኔ እዚያ ውስጥ ስለነበርኩኝ ውጪ ላይ የተፈጠረ አላውቅም
- ወጡ እኮ ሲወጡ የተፈጠረ ነገር አለ ?
- አላየሁም
- ግቢ ውስጥ አንዋር ውስጥ ንግግር ያደረገ አለ ከእርሶ በሚያዩበት ሰዓት ?
- አቤት
- ከኢማሙ ቦታ ውጪ ንግግር ያደረገ ሰው አይደተዋል ?
- እኔ አላየሁም
- አቶ አህመድ ጥቂት ጥያቄዎች ናቸው አንድ ሁለት በሀምዛ በአወሊያ እና በአንዋር መስኪዶች ተከሣሾች ሲናገሩ እነሱን የሚቀርፃቸው ሰው አልታዘቡም በሞባይል በቪዲዮ በመሳሰሉት ?
- አላየሁም
- ምንም አልነበረም ?
- አላየሁም
- በተለይ ሀምዛ መስኪድ ሲገቡ መስኪዱም ውስጥ ስለ ፕሮግራሙ መዘጋጀት የሚገልፅ የተለጠፈ ነገር መስኪዱ በር ላይ ተናጋሪዎች ከሚናገሩበት ቦታ ላይ አልነበረም ?
- እኔ አላየሁም ግን የዳዋና እና የሰደቃ ፕሮግራም የሚል ግን በትልቅ ፁሑፍ ተለጥፎ አይቼአለሁ
- ተለጥፎ ?
- አዎ

1467

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የት ጋር ነበር ሀምዛ መስኪድ የት ጋር ነበር የተሰጠፈ ?
- ሀምዛ መስኪድ መግቢያ ላይ ሾልቅ ውሑፍ የዳዋና የ 10 መስኪዶች የዳዋና የሰደቃ ፕሮግራም የሚል አይቼአለሁ
- የ 10 መስኪዶች ?
- አዎ
- 10 መስኪዶች ነበር ያዘጋጁት ?
- እንደዚያ ይላል ውሑፍ እንግዲህ መሆኑ ነው
- አቶ አህመድ ቅድም ሲመሰክሩ ሀምዛ መስኪድ ስብሰባ ላይ የተገኘሁት በመጥሪያ ወረቀት ደርሶኝ ነው ብለው ነበር እና መጥሪያ ወረቀቱ ላይ ያለው ማህተም የሀምዛ መስኪድ ማህተም ነው አይደል ?
- አይደለም ማህተም የለውም
- ማህተም የለውም አርማስ የለውም ?
- የለውም
- አቶ አህመድ በእነኚህ 3ቱ መስኪዶች ተከሣሾች ንግግር ያደረጉት ለተሰበሰበ ሕዝብ ነው አይደል ?
  - አዎ
  - ወይስ እርሶ ብቻ ነበሩ ?
  - አይደለም
  - ሌላ ሰውም ነበረ ስለዚህ
  - ቆይ ቆይ ተጠይቄል እሱ በግልፅ መልሰውታል አሁን እናንተ እሱ ጋር ልትጠይቁ ያሰባችሁትን ነገር መዛችሁ መጠየቅ ነው እንጂ 3ቱም ላይ በግልፅ ሕዝብ በተሰበሰበበት ብለው ግልፅ መልስ ሰጥተዋል
  - እንደመንደርደሪያ /ግልፅ ያልሆነ/ ወደ ጥያቄዎቼ ልገባ ነው
  - አሁን ማለት እሱን የምትጠይቁ ነው የመሰለዋ አይደለም ማለት እሱ እንዲመለስላችሁ የፈለጋችሁት ይሄ ነገር ማለት ነው

1468

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ሌሎች የተሰበሰቡ ፕሮግራሙ ላይ የነበሩ ሰዎችም ነበሩ አሁን እስካሁን እገሌ እንዲህ ተናገረ እገሌ ያሉትን እንዳላሉ ምን ያህል እርግጠኛ ኖት እርሶ ሌሎችም ሰዎች ስለነበሩ ማለት ነው በስፍራው
- መቃወሚያ አለኝ የተከበረው ፍ/ቤት
- ጥያቄው ግልፅ አይደለም መጀመሪያ
- አዎ
- እስቲ ቆይ ግልፅ ያድርጉ ጥያቄውን
- ተከሣሾቹ አሁን ተናገሩ ያሉትን ላለመናገራቸው ለመናገራቸው ምን ያህል እርግጠኛ ኖት ሌሎች ታዛቢዎች ሰዎችም ባሉበት ስለሆነ ማለቴ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ጉዳይ ለመጠየቅ ፈልጌ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለ
- ይሄ የሚሰጥም አይደለም አሁን ቅድም ያሉት ነገር አለ ቅድም ያሉት ነገር አለ ምን ያህል ለማለታቸው ምን ያህል እርግጠኛ ኖት የተባለው ጥያቄ እንዲህ እንዲህ በመባሉ በማለተዋወቃቸው እንዲህ በማለታቸው አይተናል አሉ ስለዚህ ከእሱ ተነስታችሁ ጥያቄ ጠይቁ ምን ያህል እርግጠኛ ኖት ማለት የቅድሙን እንዲደግሙት ከሆነ ሪዜ ማጥፋት ነው
- ይሄንን ጥያቄ አልፈዋለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ አህመድ ምን ያህል የእስልምና ኃይማኖት እውቀት አሎት ተምረዋል መደበኛ ትምህርት ?
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁንም መቃወሚያ አለን
- ይሄም ቆየማ ቅድም አሁን ባለፈው የሰጠነው ማሳሰቢያ አለ አልነበሩም አዎ ስላልነበሩ ነው ምስክሩ በሚያውቁት በሚያውቁት የሚሉትን አሁን ወደ ኋላ ሄደን የኃይማኖት ጉዳይ ስለማንመረምር ጥያቄውን ምንድን ነው የምታደርጉት ፋክት ላይ ፋክት ላይ ቤዝ ይደረግ ሰውዬው በሚያውቁት ልክ ብቻ ነው የሚመመሰክሩት ፋክቱን ነው እኛ የምናጣራው እንጂ
- እኮ አውቃለሁ ብለው ቅድም የቃላት ትርጉም ይሰጡ ስለነበረ ይሄንን ደግሞ የቃላት ትርጉም መስጠት የሚችል የእምነቱ እውቀት ያለው ሰው
- እኮ በተረዱት መጠን አሁን እኮ በተረዱት መጠን ነው የመሰለኝ እንግዲህ ከእዚያ በኋላ የሚመዘነው ከእዚያ በኋላ ነው ተነቦ እዚህ ሰዎች ያወቁ ነበር ምንድን ናቸው

1469

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ምናምን የሚለውን ነገር የሚመዘን ከእዚያ በኋላ ነው"አሁን እሳቸው ይሄንን ያውቃል ይሄንን አታውቁም ብሎ ማስገደድ

- የተከበረው ፍ/ቤት ትርጉም ለመስጠት እውቀት ይፈልጋል ብዬ እኮ ነው
- ይሄ ይታለፍ ብለናል እንግዲህ ለማንኛውም ከእዚህ በላይ መሄድ አንችልም
- ቀጥሉ
- አቶ አህመድ ቅድም ሐምሌ 8 ቀን ነበረ አንዋር ያሉት ይሄንን ቀን እርሶ በምን አስታወሱ ?
- እኔ ይሄንን ቀን በደንብ አስታውሰዋለሁ
- በምን ?
- የራሴ ጉዳይ ስለነበረኝ
- ሌላ ቀኖችንም እንዲህ ያስታውሳሉ ሌላ ቀኖችን የማስታወስ ልምድ አሎት ?
- እንግዲህ ጉዳይ ካለ የማስታወስ ጉዳይ ካለ ታስታውሰዋለህ
- ስለዚህ ብጠይቆት ያውቃሉ ለምሳሌ ያህል በዓል የመውሊድ በዓል መቼ ነበር እስቲ ቀኑን ማስታወስ ይችላሉ ?
- በ 16 ነበር
- በ 16 ?
- የአሁኑ መውሊድ በ 16 ነበር
- አረፋ መቼ እንደነበር ያስታውሳሉ ?
- የእሱን ጊዜ አላስታውስም
- የትኛው ጊዜ ይርቃል ?
- እንግዲህ የማስታውሰው አስታውሰዋለሁ የማላስታውስ ግዴታ አስታውስ ይባላል እንዴ የተከበሩ ጠበቃ
- አላልኮትም የጠየኮትን?
- አይ እንደዚያ መሰለኝ
- ይሽውሎት ካላስታወሱ አላስታውስም ነው ያው አላስታውስም ነው ዓይነቱ በእዚያ መንገድ ይሂድ
- አንዋር መስኪድ እርሶ በነበሩበት ሰዓት መብራት መጥፋት መኖሩን ያስታውሳሉ ሚሄዱ ?

1470

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ እኔ እሱ ልብ አላልኩም አላወኩም
- መብራት ንግግር ከነበረ መብራት ሲቋረጥ ይቋረጣል አይደል ?
- አዎ ጀነሬተር ስላለ ጀነሬተር ተጠቅሞ ከሆነ እኔ አላውቅም
- ስለዚህ ለአፍታም ቢሆን ንግግሩ አልተቋረጠም ?
- እኔ ልብ አላልኩም
- ክረምት ስለነበረ ዝናብ መኖር አለመኖሩን ያስታውሳሉ በወቅቱ ?
- አዎ ካፊያ ዝናብ ነበር
- ካፊያ ነበር ዝናብ ነበር ?
- አዎ
- ጨርሻለሁ
- ጨረሳችሁ ?
- አንድ ጥያቄ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ስለ 3ቱ መስኪዶች ምስክር አስረድተውናል በሀምዛ መስኪድ ውስጥ ሕዝቡ ምን ይል ነበር ተከሣሾቹ ስለጅሀድ ተናገሩ ብለዋል ስለጅሀድ ሲናገሩ ሕዝቡ ምን ይል ነበር ?
- እንግዲህ ሕዝቡ ምን ይል ነበር ያው ያዳምጥ ነበር
- ማዳመጥ ብቻ ነው ሌላ ነገር የለም ?
- እንግዲህ እንደእኔ ዓይነቱ ከሆነ ያዝናል የሚያዝን
- አይደለም ሕዝቡ ያለው ያን ቀን ያለውን ?
- ያዳምጥ ነበር ሕዝቡ ተሰብስቧል ተጠርቷል ያዳምጥ ነበር
- የሚያዝንም ካለ የሚያዝን ሰው ነበር ወይ በንግግር የሚገልፅ እነሱን እየተቀበለ የሚገልፅ ካለም እሱን ይገልፅ ነበር ምንድን ነው እሱ ነው ?
- አዎ የሚቃወማቸው ነበር ይሄ ትክክል አይደለም ኃይማኖት የማይፈቅደው ስርዓት ለዳዋ ብሎ ጠርቶ ለምን ጅሀድ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚሉ ሰዎች ብዙዎች ነበሩ
- ከየት ነው ከውጪ ነው ከውስጥ ነው ?
- ከውስጥ ነበሩ
- እርሶም ከሚቃወሙት ጋር ነበሩ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ውስጥ ነበርኩኝ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ከኋላዬ
- ከሚቃወሙት ጋር ነበሩ እርሶ ወይስ ዝም ብለው ከሚያዝኑት ጋር ነበሩ ? ከሚያዝኑት ጋር ነው ከሚቃወሙት ጋር የነበሩት ?
- ኢይ እኔ በቃ ከሚያዳምጡ ሕዝቡ ከተቀመጠ በኋላዬ ይሄ ትክክል አይደለም ጅሀድ ብሎ ነገር በመስኪድ ላይ አይፈቀድም ሲሉ ሰምቼአለሁ
- የሚያለቅሱ ሰዎች ነበሩ ?
- አይ ሲያስለቅስ አላየሁም
- በሌላ በ3ቱ መስኪዶች የሚያለቅስ ሰው አልነበረም ?
- እኔ አላጋጠመኝም
- እርሶ ግን ነበሩ በመስኪዶቹ በ3ቱ ?
- እንግዲህ ይሄንን ሁሉ ሺህ እያንዳንዱ አይን ማየት ያስቸግራል
- ጨርሻለሁ
- ጨረሳችዋል መስቀለኛ ጥያቄ አብቅቷል ድጋሚ ጥያቄ ዐቃቤ ሕግ ካላችሁ
- አለን አንድ ሁለተ ጥያቄ የተከበረው ፍ/ቤተ
- ምስክር ቅድም በተከሣሽ የተከሣሾች ጠበቆች ሲጠየቁ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ይሉ ነበር ምን ለማለት ነው ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ?
- ይሄማ እኔ እንዳየሁት ከሆነ እንደሰማሁት ተቃውሞ ነው ሕገ መንግስታዊ ለውጥ
- እንዴት ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን ቅድም የሚጠቅሱት
- ቆይ መቃወሚያ አለ እስቲ
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ሕገ መንግስታዊ ለውጥ ትርጉም እኛ በመስቀለኛ ጥያቄ አልጠየቅንም ስለዚህ ሕገ መንግስታዊ ትርጉም ምንድን ነው ብለው ባለሙያም አይደሉም እኚህ ሰውዬ የሕገ መንግስት ኤክስፐርት አይደሉም የምንም ኤክስፐርት አይደሉም የኃይማኖትም ኤክስፐርት አይደሉም ስለዚህ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ ሊመዘግብ
- ቆይ እስቲ አዳምጡ ጥያቄው እሱ አይደለም የተጠየቀው ጥያቄ እኛ ይዘነዋል የሕገ መንግስቱ ትርጉም ምን ማለት ነው
- እኛ መቼ ጠየቅን የተከበረው ፍ/ቤት

1472

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንደዚያ አይደለም ጥያቄው መጀመሪያ አዳምጡ ወይ እኛ ተሳስተን ከሆነ ሊያስተካክሉት ይችላሉ እስቲ ጥያቄአችሁ ምንድን ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት እኛ የጠየቅነው ጥያቄ በአረብኛ አቶ መሐመድ ይመሱልኛል የጠየቋቸው እያስተረጎማቸው ነበር እንደውም እያንዳንዱን ቃሉን ለማስታወስ የተከበረው ፍ/ቤት በእዚህ አጋጣሚ እኛ ማመልከት የምንፈልገው ነገር በተለይ እሳቸው ጠበቃ በጣም በተደጋጋሚ ሒደቱንም ያደፈርሰዋል አሁን እኛ እነሱ የሚከተሉትን ሂደት
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ያስቁምልኝ ይሄ የግል ጉዳይ አይደለም እኮ ይሄ የእሳቸው /ግልፅ ያልሆነ/
- ስርዓት ያደርግሉ ለምን መሰሎት ሳይሰጥዎ ምን ሳይሎ ለምንድን ነው የሚናገሩ አሁን ትክክል ይሁን አይሁን ገና እሳቸው ተናግረው ሳይጨርሱ እርሶ በመሀል እኮ በቃ ገቡ አንዱ ይሄ እኮ ነው ባለፈውም የተነጋገርነው ይሄንን ነው መሀል ላይ ማንም ሰው ሳይፈቀድለት መናገር ክልክል ነው ስህተትም ቢሆን ብለን እኮ ተነጋግረናል ስለዚህ አሁን እሳቸው ተናግረው መቼ ጨረሱ አልጨረሱም እኮ አሁን ይሄም ጥሩ አይደለም አሁን እንደዚህ በጣም ስሜት ገብቶ ተናዶ በእዚህ መንገድ እራስ መነቅነቅም ምን ማለትም ትንሽ እሱም ጥሩ አይደለም ስሜት ውስጥ እንዳይገባ ብዙ ነገር ተነጋግረናል ስለዚህ አሁን ተናግረው አልጨረሱም ወደ ጉዳዩ ግቡ ወደ ጉዳዩ ቀጥ ብላችሁ ወደ ጉዳዩ ግቡ ወደ ጥያቄው ግቡ
- ጥሩ እኛ የጠየቅነው ጥያቄ ምስክሩ አረብኛ ቋንቋን እየገለፁ ታሪህ አደባባይ ግብፅ ላይ ይባል የነበረውን ነገር ይሉ ነበር ብለው በመስክሩት መሠረት የአቶ መሐመድ የተከሣሾች ጠበቃ ይሄንን ጥያቄ ሲጠይቁ ነበር ይሄንን መሠረት አድርገን ምን ማለት ነው ምን ለማለት ፈልገው ነው ሕገ መንግስታዊ ለውጥ የሚሉት ቅድም ምን ችግር አለው ብለው መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ሲጠይቋቸው ስለነበር ምን ለማለት ፈልገው ነው ብለን ነው የጠየቅነው እኛ
- ከእዚህ ተነስታችሁ መቃወሚያችሁን አቅርቡ ጥያቄው ይሄ ስለሆነ
- አይ ጥያቄው ይሄ ነው ምናልባት ተቃውሞ ካላችሁ ነው እዚህ ጋር ?
- አዎ ልክ ነው አሁንም ዐቃቤ ሕግ በትክክል እንዳረጋጠት እነሱ ምን ለማለት ፈልገው ነው ብለው የእሳቸውን አስተያየት ነው የጠየቁት እነሱ ምን ለማለት ፈልገው ነው የሚለው ነገር ትንታኔ ነው የሚፈልገው ፋክት አይደለም ምስክሩ ደግሞ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያወቁትን ነገር ብቻ ነው እንዲመሰክሩ የመጡት እነሱ ሰማለተ የፈለጉት ነገር ከሆነ ግን የእሳቸው አስተያየት ነው የሚሆነው ስለዚህ አስተያየት ደግሞ መመስከር የለባቸውም

- ምንድን ነው ይሄንን መቃወሚያ እና መልስ ተመልክተነዋል እንግዲህ እኛ እንደተመለከትነው የቀረበው ጥያቄ ምን ፈልገው ነው የሚለው ጥያቄ በመጀመሪያ ሲጠየቅ የግል አስተያየት የሚመስል ነው ስለዚህ ጥያቄው ምን ለማድረግ ነው ተብሎ ተስተካክሎ በእዚህ መንገድ ተጠይቆ ምላሽ ተሰጥቶበታል ምስክሩ የራሳቸውን አስተያየት ሳይሆን በወቅቱ ይደረግ የነበረውን ነው የሚመልሱት የራሳቸውን አስተያየት ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቱ የሚመዝነው ነው የሚሆነው
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እናመሰግናለን ምስክር እሺ በወቅቱ ቅድም የጠየኮት ጥያቄ አለ በወቅቱ እነዚህ አሁን የጠቀሷቸውን ሰዎች ይናገሯሉ ያሏቸው ነገሮች አንዱ ሕገ መንግስታዊ ለውጥ እንፈልጋለን ወይም እርሶ በአረብኛ ያሉት ቃል ነው በምን መልኩ እናድርግ ነው የሚሉት ይሄንን ?
- እንግዲህ በአመፅ ነዋ በጅሀድ
- ይሄንን እንዴት አወቁ እርሶ ?
- ጅሃዱ የማለ ስለተናገሩ ከነሰረው ስቅቃሴ ከነበረው ስሜት ቦቃ እኔ የተገነዘብኩት ይሄ ነው
- በጣም ጥሩ ቅድም አሁንም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ እነ አቡበከር መሐመድ 80 መስኪድ ላይ ተመሳሳይ መድረኮችን አዘጋጅተናል እያሉ ይናገሩ ነበር ብለው መልሰዋል ለጠበቃው ሲጠየቁ እነ አቡበከር ምንድን ናቸው አሁን የጠቀሷቸው ግለሰቦች ምንድን ናቸው ?
- እንግዲህ የሰደቃ እና የዳዋ ፕሮግራም በየሀገሪቱ የሚያዘጋጅ ነው ማለት ነው
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ምንድን ነው ተቃውሞ
- እነ አቡበከር ምንድን ናቸው የሚለው ነገር በዋና ጥያቄ ላይ አልተነሳም አልተመሰከረም መስቀለኛ ጥያቄ ላይ እኔ ነኝ የጠየኩት እኔ የጠየኩት አቡበከር መሪያችን ነው ሲሉ የተቃወመ ሰው አለ ወይ ነው የእኔ ጥያቄ የተቃወመ ሰው የለም ነው የመለሱት እነ አቡበከር ምንድን ናቸው የሚል ነገር በፊትም አልተመሰከረም በመስቀለኛ ጥያቄ አልተጠየቀም አሁን አዲስ ፋክት ነው የመጣው እና ሊጠየቅ አይገባም
- ምላሽ ስጡበት

1434

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የተከበረው ፍ/ቤት እኛ ኦሳጁጡ የጠየቅኩት ጥያቄ ላይ መመሪያት ኦፍርገን ኦፀ ዐለመ ፁኡጠመ

ሌላ የእሳቸው ባልደረባ የሆኑ ሰው ላይ ነው ጥያቄው ምን ነበር በመስቀለኛ ጥያቄ የተነሳው ለምስክሩ ይሄንን ዳዋ እና የሰደቃ ፕሮግራም ማን እንዳዘጋጀው ያውቃሉ ወይ ተብለው ተደጋጋሚ ሲጠየቁ ነበር ምስክሩ መስቀለኛ ጥያቄ ምስክሩም ሲመልሱ ነበር አዎ በእዚህ በእዚህ ምክንያት ተረድቼአለሁ እያሉ ሲመልሱ ነበር ያንን መሠረት አድርገን ነው እነ አቡበከር እነ አቡበከር ሲሉ ስለነበር ጠበቆችም ምስክሩም እነ አቡበከር ምንድን ናቸው ብለን የጠየቅነው ይሄ አግባብነት ያለው ነው

- እኛ በያዝነውም ላይም መስቀለኛ ጥያቄ የተነሳ መሆኑን አረጋግጠናል ዐቃቤ ሕግ ቀጥሉ
- እናመሰግናለን ምስክር ይቀጥሉ እነ አቡበከር ምንድን ናቸው ?
- እነ አቡበከር እንግዲህ ጅሀድ ብለው ቅስቃሴ እያደረጉ በዳዋ ሽፋን ይሄንን ሲያደርጉ ነበር
- እስቲ ቆይ ጥያቄው ምንድን ናቸው የሚለው ትንሽ ግልፅ አይደለም ምንድን ናቸው ማለት ቀጥታ መልሱ /ግልፅ ያልሆነ/ ምንድን ነው ወይ ሌላ የምትጠይቁት ነገር
- ማን ነው ስልጣን የሰጣቸው ለእነ አቡበከር ?
- እንግዲህ ስልጣን የሰጣቸው ባላውቅም ግን እራሳቸው የፈጠሩት ይመስለኛል
- ተቃውሞ አለን
- ምንድን ነው ተቃውሞአችሁ
- የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄውን እንዲያስተካክሉ ሲያዝ አበላሽተውታል የባሰ ምክንያም ስልጣን የተባለ ነገር ምንም የተነሳ የለም ዋና ጥያቄ ላይ አልተነሳም መስቀለኛ ላይ አልተነሳም ዐቃቤ ሕግ የተከበሩ ዐቃቤ ሕግ ወደ የሚፈልጉት መልስ እየመሩ ነው ምስክሩን እና አሁንም ተስተክክሎ ይጠየቅ ነው ጥያቄው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አዎ መሪ ነው ስልጣን የሚለው ወዴት እንደሚመራ የታወቀ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄውን አሻሽለን ማቅረብ እንችላለን
- እሺ አሻሽላችሁ አቅርቡ
- ምስክር ምን ስለሆኑ ነው አሁን እርሶ 3 መስኪድ ሲሄዱ 3ቱም ቦታ እነ አቡበከርን እነ አህመዲን ጀባልን አግኝተዋል እና በስም የጠቀሷቸውን ሰዎች ለምንድን ነው እነሱ በየመስኪዱ የሚገኙት ምን ስለሆኑ ነው ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ አሁን በየመስኪዱ የሚሄዱት ይሄ ጀሀልማዎች የሽብር ፈጠራ በሰደቃ ሰበብ ለመጠራት እንጂ እንደዚህ ዓይነት
- እኮ ምን ስለሆኑ ነው በየመስኪዱ እነ አቡበከር የሚገኙት ?
- እኔ እነዚህ ሽብር ለመፍጠር እና አክራሪ ስለሆኑ ይመስለኛል
- ኖ ኖ ጥሩ ሊሆን ይችላል እርሶ የእርሶ አመለካከት ነው እርሶ የሚያውቁት ነገር አለ እነሱ ምን ስለሆኑ ነው መስኪድ መድረክ የሚመሩት
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን
- ምንድን ነው ተቃውሞአችሁ
- ምስክሩ የሚያውቁትን ነገር በተደጋጋሚ መስክረዋል ዐቃቤ ሕጉ ግን አንድ ጥያቄ ደጋግመው እያሰሙ ምስክሩ የማያውቀውን ነገር እንዲያውቅ እያስገደዱት ነው ወይ ደግሞ ምስክሩ የእነሱም ቢሆን ማስገደድ ያለባቸው አይመስለኝም ስለዚህ ይስተካከል
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አንድ ዓይነት ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ግልፅ አድርጉ እና/ግልፅ ያልሆነ/ አንድ ዓይነት ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት የተከበረው ዐቃቤ ሕግ ምስክሩ ሲመልሱ ኖ ኖ የሚለው እራሱ ይሄንን አይደለም የምፈልገው ማለት ነው ሌላ የተለየ ነገር የለም ይሄንን አይደለም ያንን መልስልኝ እንደማለት ነው እና ጥያቄ ከተጠየቀ በኋላ ምስክሩ ከመለስ
- መልስ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን ኖ ኖ ማለታችን ይሄ መብታችን ነው እኛ የምንፈልገውን ነው ምስክሩን የምናስመስክረው 1ኛ እሱ ነው 2ኛ እኔ ከምፈልገው አቅጣጫ የሚወጡብኝ ከሆነ ምስክሩን መመለሴ ነው እኔ እንጂ ሌላ መልስ ነግሬአቸው አይደለም ያንን መልሱልኝ እያልኩ አይደለም ያለሁት እና አግባብነትያለው ጥያቄ ነው መቃወሚያውም ብዙ ግልፅ አይደለም 2ኛ ለአንድ ጥያቄ አንድ ሰው 5 ዓይነት 6 ዓይነት መልስ ሊሰጥ ይችላል እነዚያን 6 ዓይነት መልሶች አግሶስት አድርጌ እስክጨርስ መጠየቅ የሚከለክለኝ ስነ ስርዓት የለም እና በእዚያ መልኩ ነው እኛ የወሰድነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይተነዋል ዐቃቤ ሕግ ምስክር ሲመሰክር ጥያቄው ካልገባቸው ጥያቄው ግልፅ አልሆነም ነው የሚባለው እንጂ ኖ ኖ ይሄንን ያቋርጡ ምናምን የሚለው ነገር እሱ ለምስክር ጥሩ አይሆንም ስለዚህ የተነሳው ነገር ተገቢ ነው ቀጥሉ ብለናል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እሺ ምስክር ይቀጥሉ እስቲ
- ጥያቄው
- አሁን እርሶ 3 መስኪድ ሲሄዱ 3ቱም ቦታ መድረክ ላይ እየወጡ ንግግር ያደርጉ የነበሩት እነ አቡበከር ናቸው እነ አህመዲን ናቸው እያሉ ስም ጠቅሰዋል አይደል ምን ስለሆኑ ነው እነሱ 3ቱም ቦታ ተገኝተው መድረክ ላይ እየወጡ የሚናገሩት ምንድን ነን ብለው ነው ?
- እነሱ ምንም ስልጣን ያላቸው አይመስለኝም ግን ሕዝብ መርጦናል ሕዝቡ ፈርሞልናል ሕዝቡ 100 ሺህ የሚያክል ሰብስቦ ፈርሞልናል ብሎ ሲናገሩ ነበር ለእዚያነው እኛም የሕዝብ ውክልና አለን ብለው ይናገሩ ነበር
- እንደዚያ ይላሉ ?
- አዎ
- በጣም ጥሩ የመጨረሻ ጥያቄ አንዋር መስኪድ ሲገቡ ቅድም መስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ የተሸፋፈኑ ሰዎች እና ያልተሸፋፈኑ ሰዎች ፍተሻ ያደርጉ ነበር ብለዋል አይደለም ?
- አዎ
- ጥሩ ሌላ ጊዜ ይደረግ ነበር እንዴ ?
- አይ አይደረግም የእዚያን ጊዜ ብቻ ነው
- ለምንድን ነው ?
- እንግዲህ ያለወቅቱ ያለ ሰዓቱ ያልተለመደ ስለሆነ የተለየ ነገር
- እነ ማን ናቸው የሚፈትሹት ?
- ወጣቶች ናቸው
- የመስኪዱ ዘበኞች ናቸው ?
- ኣኦ ኣይደለም
- ታዲያ ምንድን ናቸው ?
- እንግዲህ እነዚህ ከእነ አቡበከር የመጡ ነው መሰለኝ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ውስጥ ሲገቡ መድረኩ ላይ
- ይሽሎት ምስክር የሚመስለኝ የሚለውን ይተውት እና የሚያውቁት ከሆነ እነሱ ነው የእነሱ ናቸው የማያውቁት ከሆነ ደግሞ አይገደዱም
- በእርግጥ እኔ ሲፈትሹ ነው ያየዋቸው በምን እንመጣ አላውቀውም እርግጥ
- ጥሩ ውስጥ ሲገቡ መድረኩን ይመራ የነበረው ንግግር ያደርግ የነበረው ማን ነው ተፈትሸው ሲገቡ ?
- አህመዲን ጀባል ነበር እኔ ያየሁት መስኪድ ውስጥ
- ድጋሚ አበቃን የተከበረው ፍ/ቤት
- የፍ/ቤቱ ጥያቄ
- አሁን ሲናገሩ መስኪድ ድሮ ፍተሻ አልነበረም ፊታቸውን የሸፈኑ እና ያልሸፈኑ ፍተሻ ያደርጉ ነበረ ያልተለመደ ሰዓት ስለሆነ ነው ፍተሻው ብለዋል እና ?
- አዎ
- ምን ዓይነት ሰዓት ነው ይሄ ያልተለመደ ያሉት ቀን ነው ማታ ነው ?
- 4 ሰዓት ነበር
- ቀን ነው ማታ ?
- ቀን
- ቀን 4 ሰዓት ?
- አዎ
- ቀን 4 ሰዓት መስኪድ አይገባም ነበር በፊት ?
- የሶላት ሰዓት አይደለም አልተለመደም
- እነዚህ የሚፈትሹ ሰዎች ምን የያዙት ነገር ነበር ?
- የያዙት ነገር የለም አላየሁም
- ምንድን ነው የሚፈትሹት ?
- ሰው ሲገባ በስነ ስርዓት ፈትሸው ሞባይል ከያዝክ ይይዛሉ የጥፍር መቁረጫ ምናምን ሰብስበው በፈስታል ያስቀምጣሉ እንደዚያ ሲያደርጉ አይቼአለሁ
- የሚሉት ነገር ነበር የሚነጋገሩት ?

1478

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ የሚናገሩት ሌላ አልሰማሁም
- አልሰሙም እናመሰግናለን ጨርሰዋል
- አመሰግናለሁ
- የተከበረው ፍ/ቤት አንድ አጭር ምስክር አለ እና አንድ አጭር በጣም አጭር ነው በእኛ ከ 5 ደቂቃ በላይ የማይወስድ ነው በእኛ ዋና ጥያቄ ሐሰተኛ ምስክር በንችል
- 5 ደቂቃ
- አዎ በእኛ ዋና ጥያቄ ከእዚያ አይበልጥም
- ዛሬ ከሰዓት በኋላ ያው የሕንፃ ርክክብ ስላለ የማያስቀጥለን ነው የሚሆነው ስለዚህ ነገ በተለመደው ሰዓት 3 ሰዓት ተኩል እንገናኛለን ማለት ነው

ECLN

1479

http://ethcriminalawnetwork.com/

4ኛ ወ.ችሎት

የመ.ቁ 124754

21/5/05 ዓ.ም

ዳኞች:- ብስራት ተልዕቀ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ECLN

አሣሽ:- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድማገኝ ቀርቤአለሁ

ተከሣሾች:- እነ አቡበከር አህመድ ያልቀረበ ተከሣሽ አለ ከእናንተ መሀል ዶ/ር ከማል አልቀረቡም 29ኛ ናቸው መቀመጥ ትችላላችሁ እናንተ ጠበቆች አሰመዝግቡ አሰቲ በራሳችሁ

የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አህመድ ጀማል ቀርቤአለሁ ሰለተቀሩት ተከሣሾች ባህሩ መካንጋ ሀሊማ ሰይድ ፣አዲሰ መሐመድ እና ንጋቱ ጌታሁን ቀርበናል

- አሁን የመዝገብ ቁጥር ሲጠራ ስህተት ተፈፅሟል እየተባለ ነው ስለዚህ አሁን የጠራነው መዝገብ ቁጥር 124754 ቢታረም ጠበቆች ያው አልተሟሉም በቀረቡት መቀጠል እንችላለን ችሎቱ እንጀምራለን ከመጀመራችን በፊት ግን አንዳንድ ነገሮች ትላንት ከነበረው ክርክር የታየው ነገሮች አሉ ምናልባት ከጠበቆችም ከዐቃቤ ሕግም የሚታዩ ነገሮች አሉ ትላንት እንደቀረበ ምላሽ መስጠት ይቻል ነበር ነገር ግን ትላንት ከግራ ቀኙ እንደቀረበ በእዚያ ነው ከተሰጠ ምናልባት ታይቶ ታስቦ ቀዝቀዝ ብሎ በትኩሱ ከሚሰጥ እንደዚሁ ቢሰጥ ብለን ነው ያሳደርነው ስለዚህ በእዚህ መሠረት ዛሬ የነበሩትን እና ግድፈቶች ናቸው ብለን ያየነው

1480

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከ2ቱም ወገን ለወደፊት ይሄንን ይዘን መቀጠል የለብንም እዚሁ ጋር መታረም አለበት ያልናቸው ነጥቦች አሉ እሱን ለማንሳት ነው ፤ኛው ከዐቃቤ ሕግም ከጠበቆችም- ስሜታዊ የመሆን ነገር ይታያል እንደዚሁም ክርክሩን ከተፈለገው አሳልፎ ወደ ግለሰባዊ ይዘት ወዳለው ክርክር የማድረግ እንትን ይታያል ከ2ቱም ወገን ይሄ ስነ ስርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም መታረም አለበት ግለሰባዊ መሆኑ እና ስሜታዊ መሆኑ እዚህ ላይ መቆም አለበት ሌላው በግልፅ አቶ ተማምን የሚመለከት ነው አቶ ትማም አልቀረቡም ዛሬ ትነግራላችሁ እናንተ ከደረሱ ይድረሱ ያው ንገሩ ምንድን ነው የታየው መታረም አለበት የተባለው ፤ኛ ሳይፈቀድላቸው ማንኛውም ሰው መናገር እንደሌለበት ያው ተደጋግሞ ተገልፆዋል ነገር ግን ይሄንን ትቶ ተራቸውን ሳይጠብቁ ይናገራሉ ይሄ አንድም የፍ/ቤትን ትዕዛዝ ያለማክበር ነው ይሄም እራሱን የቻለ እንትን ነው 2ኛው ስነ ስርዓቱ በተፈለገ አካሄድ እንዳይሄድ ማድረግ ነው እና ይሄ መታረም አለበት ነው ጥያቄ ካላቸው አስፈቅደው መቀጠል ሌላው በግልፅ በብይን የታለፈውን ነገር ደጋግመው ማንሳት አለ ይሄ ምንም ከስነ ስርዓት ሕጉ የሚጠበቁ አይደለም በስነ ስርዓት ሕጉ የተቀመጠ ግልፅ አካሄድ አለ ብይኑ ስህተትም ይሁን ሮንግም ይሁን ምንም ይሁን በይግባኝ ከሚታይ በስተቀር ብይኑን የሰጠው ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን ደግሞ የማያዩበት አካሄድ የለም ይሄንን እያወቁ በድጋሚ ማንሳት ሌላ ነው ስለዚህ ከእዚህ እንዲታረሙ ነው ሌላው ወገባቸውን በመያዝ ጭንቅላታቸውን በመነቅነቅ ተገቢ ያልሆነ ፊት የማሳየት ነገር አለባቸው ይሄም ስነ ስርዓት ሕጉ የሚፈቅደው ክርክር አይደለም ከስሜታዊነት ነፃ ሆኖ ፍሬ ጉዳይ ላይ አተኩሮ ነው መከራከር የነበረባቸው ግን ከእዚህ ወጣ ያለ ነው ይሄ ሌላው በግልፅ በስነ ስርዓት ሕጉ የማይቀርቡ ወይም ደግሞ ቀርበው አስቀድመው በብይን የተሰጠ ነገር በእዚህ ፍ/ቤት ድጋሚ የማይቀርብ መሆኑን እያወቁ ድጋሚ ያነሳሉ ለምሳሌ ያህል ለማንሳት አንድ ምስክር ሲመሰክሩ ትላንት ምስክሩ የግል አስተያየታቸውን እየሰጡ ነው የግል አስተያየታቸውን መመስከር የለባቸውም ተብሎ ተቃወሙ አዎ ይሄንን ተቃውሞ ማቅረባቸው ተገቢ ነው ፍ/ቤቱ ተቃውሞውን አይቶ ብይን ሰጥቷል መልሰው ከአንድ ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ደግሞ ያንኑ ጥያቄ ያቀርባሉ ይሄ ተገቢ አይደለም ሌላው ምናልባት ከእዚህ በፊትም ብይን ተሰጥቷል አሁንም ደግሞ የሚያነሱት ችሎቱ በግልፅ መታየት ችሎቱ በዝግ ችሎት ይታይ ተብሎ ያው በግልፅ ብይን ተሰጥቷል ከእዚያ በኋላ የተከራካሪ ወገኖች መዘዶች ላልሆኑ ሰዎች ይከፈትልኝ የሚለው ነገር ምንም ስነ ስርዓቱ የተከተለ አይደለም ይሄ መቅረብ የለበትም አሁንም እየተደገመ ስለሆነ ነው

1481

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከእዚህ በፊትም ብይን ተሰጥቷል ግን ይደግሙታል እና ይሄ ስነ ስርዓቱን የተከተለ አካሄድ አይደለም እንዲታረም ነው ለምንድን ነው ይሄ እንዲታረም የተባለው ነኛው የሄ የሚቀርብበት ስነ ስርዓት የለም 2ኛው ከጠበቃ የሚጠበቀው ያው ባለጉዳዩን በአግባቡ በሕጋዊ አካሄድ መምራት ነው እሱን ማሳየት ነው ነገር ግን ሁሌም አንድ በብይን የታለፈውን እና ሌሎችን የሚያቀርቡ ነገሮችን ሲያቀርቡ ፍ/ቤቱ በብይን ውድቅ ሲያደርገው ምናልባት ከባለጉዳዮቹ ሕግ የማያውቁ ከሆነ እንደእኛ የምናቀርበው ነገር ተቀባይነት የለውም ወይ ሁሌ የሚል አደምታ ሊኖረው ይችላል ከባለጉዳዮቹ ይሄ ደግሞ ተገቢ አይደለም ጠበቃ በሕጉ መምራት ስላለበት እነኚህን እና የመሳሰሉ ነገሮች እዚህ ጋር መቆም ስላለባቸው ነው ዛሬ ይሄንን ለማስታወሻ ያቀረብነው እና አንድ በአንድ ግለፁላቸው ሲቀርቡ ከሌሎችም ጠበቆች የሚነሳው ተመሳሳይ ነገር ካለ እዚህ ጋር መቆም አለበት ነው ሳናስገነዝብ አናልፍም በሚል ነው ከተገነዘበ በኋላ ከታለፈ ምን ይሆናል እሱ በኋላ የምናየው ነው እዚህ ጋር ግልፅ መደረግ ስላለበት ነው እና ይሄንን ግንዛቤ ከዐቃቤ ሕግም በኩል የታዩ ቅድም የተነሱ ነገሮች እዚሁ ጋር መቆም ስላለባቸው ዐቃቤ ሕጎቹ ሲመጡ በግልፅ ሊነገራቸው ይገባል ካቀጠለ ምን ይሆናል እሱ ሲቀጥል የሚታየው ነው የሚሆነው እና እዚህ ላይ እንዲቆም ነው የተፈለገው ይሄ እንዲታረም ነው ይሄንን ካልን በኋላ ወደ ዛሬው ችሎት እንሄዳለን ካቆምነው ምስክር መስማት እንቀጥላለን ስንተኛ

- /ግልፅ ያልሆነ/
- ዐቃቤ ሕግ ምስክሩ ይቅረቡ 7ኛ ላይ ደርሰናል መሰለኝ አይደል
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ተከሣሾች አንዴ ትቆማላችሁ የዐቃቤ ሕግ ምስክር አሁን ከእዚህ በፊት 6 ምስክሮችን ሰምተናል 7ኛ ላይ ነው ያሉት ለምስክሩ ደህንነት ሲባል ያው የራስዎን የመጀመሪያ ስም ብቻ እንዲገልፁ ነው በፍ/ቤቱ ብይን የተሰጠው ከእዚያ በኋላ አይጠየቁም እሱን ብቻ ይገልፃሉ
- ስምዎ ማን ነው ?
- ሙራድ
- ሙራድ ስንተኛ ላይ ነው ዐቃቤ ሕግ ?
- 104ኛ ተራ ቁጥር

1482

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በ 104 ላይ የተጠቀሰ ዛሬ ለምንድን ነው የመጡት ?
- በእስጥዋስ በድሩ ሁሴን እና ለመመስከር ነበር
- ለምስክርነት ነው ?
- አዎ
- እነ ማን ላይ ?
- እስጥዋስ በድሩ ሁሴን እና ያሲን ኑሩ
- በድሩ ሁሴን እና ያሲን ?
- አዎ
- 2 ሰው ላይ ብቻ ?
- አዎ
- እነኚህ ሰዎች በአካል ያውቁታል ወይስ ?
- በአካል አዎ
- በአካል ትለየዋለህ ?
- አዎ
- እሺ መለየት ትላለህ ከቆሙት ውስጥ ተነስተህ መለየት ትችላለህ እዚያም ቆመህ መግለፅ ትችላለህ ከቻልክ ጥምጣም በእጁ የያዘ ቀይ ሰምህ ማን ነው ማንን ብለው ነው በድሩ ኖት 5ኛ ተከሣሽን አመልክቷል እሺ ሌላውስ ምን የለበሰ ቲሸርት የትኛው እሱ ነው ወረቀት የያዘ ማን ነው ስሙ በድሩ ነህ ያሲን ነህ ይቅርታ ያሲንን 3ኛ ተከሣሽን ምስክሩ አሳይቷል አሁን ከጠቀሱት 2ቱ ሰዎች ጋር ጥላቻ ወይም ዝምድና አለ ?
- በፍፁም የለኝም
- ጥላቻም ዝምድናም የለህም ?
- በፍፁም
- ዐቃቤ ሕግ ይቀጥሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን የለየሀቸው ምስክር አሁን የለየሀቸውን ተከሣሾች የት እንደምታውቃቸው ምን ሲሰሩ እንደምታውቅ እና አጠቃላይ ስለ እነሱ የምታውቀውን ጊዜውን ቦታውን በማስታወስ ለተከበረው ፍ/ቤት በዝርዝር እንድትገልፅ ነው የምትጠየቀው እና እስቲ ከያሲን ኑሩ እንጀምር የት ነው የምታውቀው ያሲንን ?

1483

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያሲን ኑሩ ዳኢ ነው ሀዲስ ብዙ ጊዜ ይናገራለ እና በእዚያ ነው የማውቀው
- እኮ ምን ሲሰራ ጊዜው ቦታው ሰዓቱ አሁን ባልካቸው ሁኔታዎች ማለት ነው ዘርዘር አድርገው እና እስቲ እሱን ግለፅ ?
- የት እንደሚሰራ ነው
- በምንድን ነው የምታውቀው እዚያ ፊትን
- ፊትህን ልክ እንደዚህ እያየህ ብቻ
- ዛሬ ከመጣህበት ምስክርነት ጋር በተያያዘ ስለእነሱ አሁን ስለጠቀስካቸው 2ቱ ሰዎች ምንድን ነው የምታውቀው ያለህን እውቀት በእነሱ ላይ ስለምትመሰክርበት ጉዳይ እሱን በማስታወስ እንድትገልፅ ነው የምጠይቅህ?
- መልካም በዕለቱ ሐምሌ 8 ላይ ነበር በአንዋር መስኪድ
- ዓ.ም መቼ ነው ?
- 2004 ላይ ነበረ ከጠዋቱ 4 ሰዓት ጀምሮ እስከ 7 ሰዓት ባሉት ሰዓታት ውስጥ ነው በርካታ ሼህ ሙስሊም ሕዝብ እዚያ ላይ ነበር እና ያሲን ኑሩ የተባለው በዕለቱ የሰማሁት ነገር ምንድን ነው
- ከስንት ሰዓት እስከ ስንት ነው ?
- ከ 4 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት
- ቀን ነው ማታ ?
- ቀን ከእዚያ ያሲን ኑሩ ምንድን ነው ያው ማንም ማንኛውም መንግስት በእኛ ኃይማኖት ላይ ጣልቃ ሊገባ አይችልም ገዢውም ፓርቲም ቢሆን በእኛ እምነታችን ላይ ጣልቃ ሊገባ አይችልም ማንም መግባት አይችልም የሚል ነገር ነበር ሲል የሰማሁት
- ይሄ እሱ አሁን እዚህ አንዋር ላይ ማለት ነው ይሄንን ብሎ ሲል ምንድን ነው ምንን መነሻ በማድረግ ነው ያ አንተ የተሳተፍክበት ወይም ደግሞ እዚህ አሁን ያልካቸው ከ 4 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ምን ነበር የሚካሄድ የነበረው ?
- አኬ በወቅቱ የነበረው ምንድን ነው እኛ በአጋጣሚ ያው መስኪድ ለመስገድ ስገባ ያው ምንድን ነው ሙስሊሞች ሲያወሩ የሰማሁት አንዋር መስኪድ የአንድነት እና የሰደቃ ፕሮግራም ስላለ እንዴ አወሊያ ነበር እኮ እዚያ እንዴት አይ እዚያ ስለተዘጋ አንዋር መስኪድ ሆኗል እና እዚያ ነው ያለው ፕሮግራሙ ምናምን ተብዬ እዚያ ሄድኩኝ በዕለቱ

1484

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያው አርፍጀም ስለነበርኩኝ ወደ 4 ሰዓት ደረስኩ ከእዚያ ከኋላ ነበርኩኝ ያው በኢጋጣሚ ይሄንን ነገር ሰማሁት

ይሄንን ሲገልፅ እያየኸው ነበር ይታይህ ነበር ይታይህ ነበር ያሲን ?

በወቅቱ ከሕዝብ መሀል ያው ቁመቴም አጭር ስለሆነ ብዙም አላየሁትም ነበረ እና ድምፁን ግን ብዙ እለየዋለሁ

መለየት ትችላለህ ?

አዎ

- ቀጥሎ ያለውስ በድሩስ ?
- በድሩ ሁሴን ደግሞ በወቅቱ የእዚያኔም እሱም ነበረ
- መቼ ነው ማለት ነው ጊዜው ?
- ሐምሌ 8 /2004 ላይ
- የት ነው ቦታው ?
- አንዋር መስኪድ ላይ
- ምን ይል ነበር
- እና በወቅቱ ሲል የነበረው ወንድሞቻችን ታስረው እኛ መተኛት የለብንም እስከ ሕይወት ፍፃሜ ድረስ መታገል አለብን የሚል ነበር ሲል የነበረው
- ይሄ አሁን አንተ እስከ ስንት ሰዓት አበቃ ይሄ ነገር ወይም እስከ ስንት ሰዓት ነበር የቀጠለው ፕሮግራሙ ይሄ ሰደቃው ፕሮግራም ማለት ነው ይሄን ይሉበት የነበረበት ከስንት ሰዓት ጀምረህ ስንት ሰዓት አበቃ ?
- በወቅቱ በቃ ከ 4 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ላይ ቆየሁኝ ከእዚያ ጥዬ ወደ በኔን መስኪድ መሄድ ጀመርኩ እዚያ ለመስገድ /ግልፅ ያልሆነ/
- ጨርሰናል
- ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- ደቂቃ ከደንበኞች ጋር ለመነጋገር
- ትችላላችሁ መቀጠል ይችላሉ
- አቶ ሙራድ ከ4 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት እንደቆዩ አንዋር መስኪድ ገልፀውልናል በእዚህን ጊዜ 2ቱ ብቻ አቶ በድሩ እና አቶ ያሲን ናቸው የተናገሩት እርሶ ባሉበት ከ 4 እስከ 6 ሰዓት

1485

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ባለው ጊዜ እስከ 7 ሰዓት ከ 4 ሰዓት እስከ 7 ሰዓት ባለው ጊዜ ንግግር ያደረጉት በድሩ እና ያሲን ኑሩ ናቸው አይደል ?

- ያው ሌሎቹም አሉ ግን እኔ ብዙም በበድሩ ሁሴን እና በያሲን ኑሩ ብቻ ላይ ነው እኔ ትኩረት እንትን ያደረኩት ምክንያቱም እኔ በወቅቱ አንድነት እና ሰደቃ የሚል ፕሮግራም ነበረ እና እኔ ሌላ ነበረ ፕሮግራም የጠበኩት በዕለቱ ይሄንን ነገር ሲሉ በጣም ተናድጄ ስለነበረ ያው ይሄንን ብቻ ነው
- መጀመሪያ ማን ነበር የተናገረው ?
- መጀመሪያ በድሩ ሁሴን
- ከእዚያ ?
- ከእዚያ ያሲን ኑሩ
- 2ቱ በተከታታይ ነው የተናገሩት እርሶ ከመስኪድ ውጪ ነው የነበሩት አይደል መስኪድ ውስጥ ነበሩ ወይስ ግቢ ውስጥ ነበሩ ?
- ግቢ ውስጥ ከኋላ
- ግቢ ውስጥ ነው ብዙ ሺህ ሕዝብ ነበረ ብለዋል እነ በድሩ መናገራቸውን በድምፃቸው ነው አይደል የሚያውቋቸው ከድምፅ በድምፅ ለይተው ነው ማለት ነው በድሩ እና ያሲን ተናግረዋል የሚሉን ?
- አዎ
- በምን በእስፒከር የሚተላለፍ ድምፅ ነው ?
- በእስፒከር
- እርሶ እዚያ ቦታው ላይ ሲደርሱ ፕሮግራሙ ተጀምሯል አይደል ?
- አዎ
- ተጀምሮ ነው የደረሱት እንጂ እርሶ እንደገቡ አይደለም የተጀመረው ?
- አይ አይደለም
- ሰው ተሰብስቦ ነው ያገኙት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ እነ በድሩ በዕለቱ ይናገሩ ወይም አይናገሩ በምን ይለያዩ በግምት ካልሆነ ?
- እነዚህ በድሩ ሁሴን እኮ ብዙ ጊዜ ካሴቱንም አዳምጣለሁ ስለዚህ ቃሉን እንዴት ይጠፋኛል

1486

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት ድምፁን ስለሚያውቁት በድሩ ነው ይሄ ድምፅ የበድሩ ነው በሚል ነው ?
- መልኩንም ድምፁንም ስለምለየው ለእዚያ ነው
- አይ ማለቴ እርሶ ድምፁን እየሰሙ ነው ይሄ የበድሩ ንግግር ነው ያሉን እና በድሩ በዕለቱ ይናገር ወይም የበድሩን ድምፅ የሚመስል ነገር ይናገር ወይም በሌላ ጊዜ የተናገረው ተቀርፆ ይተላለፍ በምን ይለያሉ ይሄንን ?
- የእዚያን ጊዜ ትክክለኛ ነው የበድሩ ሁሴን ነው ሲናገር የነበረው
- ዕለቱ ምን ነበር ዝናባማ ዳመና ፀሀይ እንዴት ነበር እርሶ ሲሄዱ ?
- በወቅቱ አላስታውሰውም በወቅቱ
- አቶ ሙራድ ለፍ/ቤቱ በማን ላይ እንደሚመሰክሩ ሲጠየቁ /ግልፅ ያልሆነ/ በድሩ ሁሴን እና /ግልፅ ያልሆነ/ ያሲን ብለው ነው የመለሱት /ግልፅ ያልሆነ/ ናቸው ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?
- ያው ሀዲስ የሚናገር ሰው ብዙ ጊዜ ክቡር የምትሰጠው ክብር ነው እንጂ
- የሚከበሩ ሰዎች ናቸው ማለት ነው እነዚህ ሰዎች ሰው የሚያከብራቸው ሰዎች ናቸው ማለትዎት ነው ?
- ማለት ሀዲስ የሚናገሩ ናቸው በወቅቱ ግን ይሄንን ነገር ሲናገሩ ትንሽ እንትን
- እኮ እስቲ እንግዲህ ቅድም አሁን መስቀለኛ ላይም እንዴት ድምፁ ይጠፋኛል በካሴትም በዲሲም አውቃቸዋለሁ ብለዋል እና እስቲ እንግዲህ እርሶ ስለ እሳቸው ከሚያውቁት በሀዲስም በሀዲስም ያሉት ነገር ምን እንደሆነ ለፍ/ቤቱ መጀመሪያ ይንገሩልን ሀዲስ ምንድን ነው ?
- እንጃ እኔ አላስታውስም
- አይ ሀዲስ ምንድን ነው ሀዲስ ?
- አንዴ ቆይ
- የተቋውሞአችን ዋናው ፍሬ ነገር ስለእነሱ ገልፀዋል ማን እንደሆነ ምን ሲል እንደነበረ ስለሀዲስ የሚጠቅሱት ወይም ስለሀዲስ ሀዲስ የሚለው ከኃይማኖት ቃል እንዲህ ይሉ ነበር እንዲህ ነበር ብሎ መግለፅ እኛ ይሄንን መሠረት አድርገን አይደለም ያስመሰከርነው እና ይሄንን ጥያቄ እንዲያነሱ በአክብሮት እንጠይቃለን
- ምላሽ ስጡበት

1487

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ያው እንደሚታወቀው መሰቀለኛ ጥያቄ በዋና ጥያቄ ላይ ተጠይቆ መልስ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ ነው ቨግልፅ ምስክሩ በችሎት የተናገሩት ላይ ነው ጥያቄ የጠየቅነው ምን ሲናገሩ ነበር የሚል እንጂ እንደከእዚህ ቀደሙ ፍ/ቤቱም እንደከለከለው የኃይማኖት ጉዳይ የትኛው መፅሐፍ የትኛው አስተምሮ የሚል አልጠየቅንም በእዚያ ተናገሩ በተባለው ነገር ላይ ምን ሲናገሩ ነበር ነው ይሄንን ነው ሰምቼአለሁ ስላሉት ጉዳይ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ ስለዚህ እንድንጠይቅ ይፈቀድልን ስለየሚመሰከርባቸው ሰዎች የተከበረው ፍ/ቤት ሙሉ መረጃ እንዲኖረው ነው ጥያቄአችን ሌላ ነገር አይደለም
- ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል አሁን የቀረበው ምስክር ያሉት /ግልፅ ያልሆነ/ የሚለው ስም የሚሰጠው ሀዲስ ለሚናገሩት ነው ብለው ነው የመሰከሩት ሀዲስ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ቀርቧል ዐቃቤ ሕግ ደግሞ ስለሀዲስ እኛ አልጠየቅንም ግንኙነት የለውም የሚል መቃወሚያ አንስተዋል ፍ/ቤቱ ይሄ ነገር ግንኙነት አለው የለውም የሚለውን አይቶታል በእርግጥ ተከሣሾች ስለሀዲስ በተናገሩት ነው የተከሰሱት የሚል ነገር ቢሆን ኖሮ የአዲስ ትንታኔ ያስፈልግ ነበር አሁን ግን ያ /ግልፅ ያልሆነ/ የሚለው ስም የተሰጠው ይሄንን ለሚናገሩት ነው ከሚል በቀር የክርክሩ ፍሬ ነገር ምስክሩ ስለተናገሩ ፍሬ ነገር አይደለም ስለሀዲስ እና ስለሀዲስ ምስክሩ እዚህ ላይ ትርጉም መሰጠቱ አስፈላጊ አይደለም ብሎ በብይን ታልፏል ስለዚህ ሌላ ጥያቄ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት እስቲ አሁን የሚመሰክሩባቸው ሰዎች ከእዚህ በፊት ስለተናገሩት ነገር የሚያውቁትን ለፍ/ቤቱ ቢያስረዱልኝ ?
- አላውቅም
- የአንዋር መስኪድ ላይ መንግስት በእኛ ኃይማኖት ጣልቃ ሊገባ አይገባም ገዢውም ፓርቲ ቢሆን የሚል ነገር ተናግረዋል ከእዚህ ውጪ የሰሙት ነገር የለም ይሄንን ብቻ ነው የሰሙት?
- አዎ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ዳኢ ናቸው ብለዋል ይሄስ ምን ማለት እንደሆነ ለፍ/ቤቱ ቢያስረዳልን ምን ማለት ነው ዳኢ ማለት ?

1487

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዳኢ ማለት ያው ሁሌም ስለቁርአን ተስፊር የሚናገሩ እና ዳዋ የሚያደርጉ ማለት ስብከት የሚሰጡ የሚል ነው በራሴ እውቀት ሲተረጎም
- ዳዋ ማለት የቁርአን አስተማሪ እና ስብከት የሚያስተምር ማለት ነው ዳኢ ማለት ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- የበርካታ ሺህ ሰዎች ነበሩ አንዋር መስኪድ ላይ ብለኸናል አንተ በነበርክበት ወቅት ከንግግሩ ንግግሩን ሰምተው ከሄደ ውጪ ሌላ ምንም ችግር አልነበረም ንግግሩን ሰምተህ ሄድክ እንጂ ሌላ ችግር አልነበረም ?
- ንግግሩን ሰምቼ አዎ በወቅቱ ተናድጄም ስለነበረ ወጣሁኝ ቶሎ
- ተናደህ ሄድክ እንጂ ሌላ የተፈጠረ ነገር የለም ?
- በወቅቱ የተፈጠረ ነገር አልነበረም
- ምንም ዓይነት ነገር ያየኸው ችግር የለም ?
- አዎ
- ስትገባ ያለምንም ችግር ነው የገባኸው ወደ መስኪዱ ?
- እስቲ በመሀል ጠቢቃ ምስክሩ የተናገሩትን መልሶ መድገም አለ እና አያስፈልግም እሷ ላይ
- ወደ መስኪድ ውስጥ ስትገባ ያለምንም ችግር አትግባ ያለህ ፖሊስ የለም ?
- አይ በሰላም ነው የገባሁት
- ምንም ችግር ሳያጋጥምህ ነው የገባኸው ?
- አዎ
- ጨርሻለሁ
- በወቅቱ ብዙ ሰው ነበር ብዙ ሺህ ሰው ነበር ብለሀል ቁጥሩ ምን ያህል ሊሆን ይችላል መገመት ትችላለህ ?
- አልገምትም
- እኔ ልገምትልህ ከ 50 እስከ 60 ሺህ ሰው ሊሆን ይችላል ?
- እኔ እንጂ
- በቃ ተመልሷል
- አይ ግምቱ እኔ ልንገረው አላውቅም ካለ እሱ
- በቃ

ECLN
1489
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወንድሞቻችን ታስረው እኛ መተኛት የለብንም ሲል ሰምቼአለሁ ብለሀል በወቅቱ የታሰሩ ሰዎች ነበሩ እንዴ ?
- እኔም ግራ የገባኝ እሱ ነበር
- አሁን ጥያቄው በወቅቱ የታሰሩ ሰዎች ነበሩ ወይ ታውቃለህ ወይ ነው የምታውቅ ከሆነ ማወቅህን ንገረን የምታውቀው አለ የታሰረ ሰው ?
- የታሰረ ሰው አላውቅም ግን ይሄንን ነገር ሲሉ ነው የሰማሁት እንጂ
- ወንድሞቻችን ታስረው እኛ መተኛት የለብንም ሲሉ ወንድሞቻችን ያሉት ምን ማለት ነው ወንድሞቻችን ማለት ?
- ወንድሞቻችን ሲሉ የነበሩት ያው እነዚህ 17ቱ የሚባሉ ኮሚቴዎች መሰለኝ እነሱ ናቸው
- ስለዚህ ኮሚቴዎቹ ታስረው ነበር ነው ያሉት ?
- እኔ እንጃ በቃ በወቅቱ የነበረው ምንድን ነው በድሩ ሁሴን ወንድሞቻችን ታስረው እኛ መተኛት የለብንም የሚል ነው እስከሕይወት ፍፃሜ ድረስ ትግል እናደርጋለን ነው ሲሉ የነበረው ይሄንን ነው ሲሉ የሰማሁት
- መጀመሪያ የአንድነት እና የሰደቃ ፕሮግራም በአወሊያ እንደሚካሄድ አውቅ ነበር ብለሀል የአንድነት እና የሰደቃ ፕሮግራም ማለት ምን ማለት ነው ?
- አላውቅም /ግልፅ ያልሆነ/
- በእስልምና ኃይማኖት የአንድነት እና የሰደቃ የሚባል ተግባር የለም ?
- እኔ አላውቅም ከእዚህ በፊት እኔ ሰደቃ ብቻ ነው የማውቀው እንጂ አንድነት አላውቅም
- ሰደቃ ማለት ምን ማለት ነው ?
- ሰደቃ ምስኪኖችን ጠርተህ /ግልፅ ያልሆነ/ 60 ምስኪኖችን ጠርተህ የምታበላበት ለእነሱ ትልቅ የሆነ ነገር የምታደርግበት ነው
- በወቅቱ ይሄ ተግባር በአወሊያ ይካሄድ እንደነበር አውቃለሁ ነው ያልከው በአወሊያ መካሄዱን አንተ ታውቅ ነበር ተሳትፈሀል ተሳትፈህ የምታውቀው ነገር አለ ?
- ዮገምልኝ
- በአወሊያ ተሳትፈህ ታውቃለህ ?
- አወሊያ ተሳትፌ አላውቅም
- ስለዚህ በአወሊያ የሰደቃ ፕሮግራም መደረጉን ታውቃለህ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አረብ አረብ አንደሚደረግ ነው እንጂ የሰዴቃ ሲደረግ ግን ሲደረግ ነበር ጥን በወቅቱ ስለተዘጋ ያው
- መስኪዱ ተዘግቷል ብለዋል አወሊያ መስኪድ መዘጋቱን እርጠኛ ነህ ታውቃለህ መዘጋቱን?
- ያው እዚያ የሄዱ ሰዎች ስለሰማሁ
- እስቲ /ግልፅ ያልሆነ/ ስሰማ አወሊያ መስኪድ ተዘግቷል ተብሎ ወደ እዚህ መጀመሪያ በዋና ጥያቄ ላይ እና ይሄ ግልፅ ነው ሌላ ጥያቄ ካሎት
- የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄዬ መዘጋቱን እሱ እራሱ ያውቃል ወይስ አያውቅም የሚለውን ነው
- ሰማው እኮ ነው ያለው /ግልፅ ያልሆነ/ አይ አይ ዋናም ጥያቄ
- አይደለም አወሊያ መዘጋቱን ስለነገሩኝ ወደ አንዋር መስኪድ ሄድኩኝ አሉ እና
- ሰምተው ነዋ
- እኮ እሱን እንዲያረጋግጥልኝ እኮ ነው መስማቱን እንጂ በራሱ መዘጋቱን የሚያውቅ ወይም የማያውቅ መሆኑን
- ሰማሁ አለ አየሁ አላለም መጀመሪያው እና ይሄንን ፍ/ቤቱ ይመዝነው
- ከሰማህ ማን ነው የዘጋው አሉ አወሊያን ?
- አላውቅም
- እስቲ ጥያቄ ባይደገም ከእዚህ በኋላ
- አንዋር ላይ የአንድነት እና ሰደቃ ፕሮግራም እንደሚካሄድ ሰዎች ነግሮዎት እርሶ ሄዱ ከእዚህ ጋር በተያያዘ ምን ተደረገ ከእነ ከ2ቱ ተናጋሪዎች ውጪ ሰደቃ ጋር በተያያዘ የተደረገ ነገር ነበረ ?
- ከእዚህ ውጪ ያየሁት ነገር የለም
- ምንም ድሆች ሲበሉ ወይም ምግብ ሲበላ አላዩም ?
- ምንም ነገር አላየሁም
- ሙራድ ያሲን ማን ነው በድሩ እና ያሲን ሲናገሩ የሚያስተዋውቅ ሰው ነበር በወቅቱ አንዋር ውስጥ ?
- ድገምልኝ
- የሚያስተዋውቅ ሰው ነበር አሁን የሚናገረው በድሩ ነው አሁን የሚናገረው ያሲን ነው ያለ ሰው ነበር አስተዋዋቂ ነበር መድረኩ ላይ ?

141

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልሰማሁም
- ስለዚህ የለም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ሐምሌ 8 ብለው ነበር እና ሐምሌ 8 ዕለቱ ያስታውሱታል ምን እንደነበረ ሰኞ ማክሰኞ ?
- እሁድ ቀን ነበረ አስታውሳለሁ
- እሁድ ቀን ነው ሐምሌ 8 ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እንዴት አስታወሱ ይሄንን ቀን ሐምሌ 8 መሆኑን ?
- በዕለቱ የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ በወቅቱ ነበር
- በአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ ነው የሚያውቁት ?
- አዎ
- የእሁኑ የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ መቼ ተጀመረ ?
- እኔ እንጃ አላውቅም
- የእሁኑን አያውቁም ?
- አላውቅም
- በዕለቱ አንዋር ውስጥ መብራት ስለመቋረጡ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- አላውቅም
- እርሶ በየትኛው በር በኩል ነበሩ አንዋር ሲወጡ ሲገቡ ?
- በታችኛው እና በታችኛው ገባሁኝ በላኛው ወጣሁ
- ሲገቡ ሲወጡ ምን ነበር ያዩት ነገር አለ የተለየ ?
- ምንም ያየሁት ነገር የለም
- ነፃ ነበር መግባት መውጣትም ይቻላል ?
- ምንም ችግር አልነበረም በሰላም ነው የገባሁት በሰላም ነው የወጣሁት
- ጨርሻለሁ
- ቅድም ሲያስረዱልን ከ 4 ሰዓት ጀምሮ እስከ 7 ሰዓት በመስኪዱ ነበርኩኝ የገባሁት ለሰላት ነው ብለዋል 4 ሰዓት የገቡት ለሰላት ነው ?

ECLN
1492
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንደዚያ አላልኩም ፕሮግራም አለ ተብዬ ገባሁ እንጂ ለሰላት በ 4 ሰዓት ማንም እንደማይሰግድ አውቃለሁ
- ስለዚህ ለሰላት አይደለም ?
- አይደለም
- ፕሮግራም አለ ተብለው ነው የገቡት ?
- አዎ
- ማን እንደጠራ የሚያውቁት ነገር አለ አያውቁም ?
- አላውቅም
- ጨርሰዋል እሺ ድጋሚ ጥያቄ ካለ ዐቃቤ ሕግ
- የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- ድጋሚ ጥያቄ የለም
- የፍ/ቤት ማጣሪያ ጥያቄ የለም ምስክሩ ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ሌላው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ከእዚህ በፊት ያው ለምስክሮች ደህንነት ተብሎ ምስክሮች የራሳቸውን ስም ብቻ ይግለፁ ሌላው አይጠየቁም ተብለዋል እና ያው ሲጠየቁ የራስዎን ስም ብቻ ይገልፃሉ
- አሁን 8ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ላይ ደርሰናል ስምዎ ማን ነው የሰራስዎ የመነሻ ስምዎ ?
- ፋሪስ እባላለሁ
- 79ኛ ተራ ቁጥር ላይ ስማቸው ይገኛል
- ዛሬ ለምስክርነት ነው የመጡት እዚህ ?
- አዎ
- እነ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት አንዴ ተነሱ እስቲ ተከሣሾች ማን ማን ነው ያሉን ?
- ሀጂ መከተ ሙሄ
- ሀጂ መከተ ሁሴን ?
- ሙሄ
- ሌላ ?

1493

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አህመዲን ጀባል፣ አቡበከር አህመድ፣ ካሚል ሸምሱ፣ ሳቢር ይርጉ ፣ በድሩ ሁሲን ፣ ያሲን ኑሩ
- ሌላ አለ የሚመሰክሩበት ከእዚህ ውጪ ሪ?
- እነዚህ ናቸው 7
- 7 ሰዎች ?
- አዎ
- እነኚህ ሰዎች በአካል ያውቁታል ?
- ምናልባት ይቀያየሩ ነበር በጊዜው አሁን አንድ ቀን ባየዋቸው ሌላ ቀን ሌላ ነገር ነው አንድ ቀን ያየዋቸው ቀን ሌላ ዓይነት መልክ ሆነው ይመጣሉ አንድ ቀን ሌላ ዓይነት መልክ ሆነው ነው የሚመጡት
- ስለዚህ መለየት ይችላሉ አይችሉም ?
- የምችላቸውን ካለ ልሞክር
- እስቲ ሞክሩ ማሳየት ከቻሉ ቆመው እዚህ ማየት ይችላሉ እና እሺ ማን ነው እሱ አቡበከር ነው 1ኛ ተከሣሽን አመልክተዋል ስማቸውን አያስታውሱትም ሌላ በድሩ ኖት 5ኛ ተከሣሽን አሳይተዋል እሺ ሌላ አለ መከተ እርሶ ኖት 6ኛ ተከሣሽን እንደዚሁ ለይተዋል ይቀመጡ ሌሎቹን መለየት አልችልም ብለዋል 2ኛ ተከሣሽን በአካል ለይተዋል በስም አለየም አሁን በስም የጠቀሱትንም ይሁን አሁን በአካል የለዩትን 2ቱ ተከሣሾች ጋር ዝምድና ጥላቻ አሎት?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ዝምድናም ጥላቻም የለም ዐቃቤ ሕግ ጠይቁ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ሼህ ፋሪስ አሁን እርሶ ያሏቸው ልትመሰክሩ የመጡበትን ጉዳይ ከመጡበት ምስክርነት ጋር በተያያዘ እያንዳንዳቸውን በሚመለከት ማለት ነው የምስክርነት ቃልዎን ያው እንዲሰጡ ነው የምንጠይቀው እና እስቲ አሁን መጀመሪያ ከአቡበከር እንጀምር እና የት ነው የሚያውቁት ምን ሲያደርግ ጊዜው ሰዓቱ ቦታውን ምን ሲደረግ እንደነበር በዝርዝር ያው እንዲገልፁ ነው የምንጠይቀው ?
- ያው በአወሊያ ላይ ማለት ነው ታህሳስ 2004 ላይ በአወሊያ ያው ጁማ መስጂድ ይጠራ ነበር ሰው በእዚያ ላይ ዳዋ ሲያደርጉ መንግስት በኃይማኖታችን ላይ ቃጭ ገብቷል ከመጅሊስ

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

ላይ ጎን በመሆን ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አሃጥተብኗል አያሉ ዳዋ ሲያደርጉ ከአሜሪካን እና ክእስራኤል 60 ሚሊየን ብር ተቀብሎ መንግስት ኃይማኖታችን ሊያጠፋብን ስለሆነ እኛ መስዋት እንሆናለን ብሎ በሕዝቡ ቅስቀሳ ሲያደርጉ እዚያ አካባቢ በመሄድ እኔ ይሄንን አይቼአለሁ

- ይሄ ማለት አሁን የገለፁት ስለአቶ አቡበከር ነው ?
- አዎ
- ከእዚህ ጋር በተያያዘ እሱ ይሄንን ገለፀ ቦታው የት ነው እሱ ይሄንን ሲገልፅ ጊዜው ሰዓቱን የሚያስታውሱ ከሆነ ?
- ጁማ ለጁማ ነበር ያው አርብ ነው በአርብ ቀን ነው በጁማ ዳዋ ሲያደርግ የነበረው
- አህመዲን ጀባል አህመዲንን ጀባልን በሚመለከት እስቲ ይቀጥሉ ?
- ያው በመድረክ እንደዚያው
- ቆዩ እስቲ አንዴ ምስክር
- ምስክሩ በእጃቸው የያዙት ነገር ወይ ለፍ/ቤቱ ይመልሱ ወይ ለችሎት አስከባሪ
- የያዙት ነገር አለ አለ እዚያ ፊት ለፊት
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ወደ ችሎቱ ማለቱ ይሄ የችሎት ስራ ነው ነገር ግን እርሶ ከእዚህ በፊትም አለ ሲናገሩ አስተውለው ይናገሩ ይሄ ነገር እጠራጠራለሁ ፍ/ቤቱ ያጣራልኝ ማለት ይችላሉ ምናልባት ከእዚያ ተነስተው እጅ ላይ ማየት ስለማይችሉ ነገር ግን በእጅ የያዙት ነገር ከሆነ እርግጠኛነት ሆነው እንደተናገሩ ነው እና ይሄ ተገቢ አይደለም ይቺን ነገር ያርሙት እርሶ ሲመስክሩ ልክ ወደ እኛ ወደ እዚያ መዞር አይፈቀድም ከእዚያም ከእዚህም በጆሮ ብቻ መስማት ነው ከእዚያ በኋላ ይቀጥሉ
- እሺ አቶ አህመዲን ጀባል አህመዲን ጀባል በሚመለከት የሚያውቁትን ደግሞ ይግለፁ ?
- ያው እነሱም እዚያው በመድረኩ ላይ ይናገሩ ነበር ይሄንኑ ነው ንግግር የሚናገሩት የነበረው መንግስት በኃይማኖታችን ላይ ጣልቃ ገብቷል ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥተውብናል ስለዚህ እኛ መስዋት እንሆናለን እናንተስ እኛ እራሳችን መስዋት እናደርጋለን እንያዛለን ብንታሰርስ እናንተ ወዴት ነው እናንተ ቤታችሁ ትገባላችሁ ወይ እያሉ ለሕዝቡ ጥያቄ ሁሉ ሲያቀርቡ ነበር ይሄንን

1495

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የት ቦታ ነው ?
- አወሊያ ላይ
- አወሊያ ጊዜውስ ወሩ ?
- ያው ታህሳስ ወር ላይ ነው
- ታህሳስ ?
- አዎ ቀኑን አላስታውስም
- ቀኑን አያስታውሱም ዓ.ም ?
- 2004
- ሳቢር ይርጉስ ?
- ያው ይሄንን ነው የሚስተላልፈው የነበረው እነሱም
- ይሄንኑ ሲሉ የሚሰጡት የምስክርነት ቃል በእያንዳንዳቸው ስለሆነ ማን ?
- መንግስት በኃይማኖታችን ላይ ጣልቃ ገብቷል ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥቶብናል ከእስራኤል 60 ሺህ ሚሊዮን ብር ተቀብሎ ከመጅሊስ ጎን በመሆን መንግስት ያው ኃይማኖታችን እንትን እያደረገ ስለሆነ ለኃይማኖታችን እንሞታለን ይሄንን ነበር የሚሉ የነበረው
- ሳቢር ይርጉ ይሄንን አለ ስለ መከተ ሙሄስ ምን ነበር የሚሉት ?
- ያው ይሄንኑ ነው ያሉት ያው መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥቶብናል
- በድሩ ሁሴንስ ?
- በድሩ ሁሴን እና ያሲን ኑሩ 2004 እንትን ላይ አንዋር መስኪድ ላይ ሕዝቡ ብዙ ሕዝብ ተጠርቶ ነበረ
- ምን 2004 ነው ?
- 2004
- ወሩ ምን ነበር ?
- ወሩ ሐምሌ ወር ላይ ነው
- ሐምሌ ቀኑን ያስታውሳሉ ?
- ቀኑ እሁድ ነበር

1496

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሁድ ?
- አዎ ስብስባው ከ 4 ሰዓት ጀምሮ እስከ 7 ሰዓት ባለ ላይ ነው እና ያው እነሱም እንደዚሁ ዳዋ እያደረጉ ነበር በደሴ ላይ ሰው ሞተላችሁ እያሉ ነው እንደውም በደሴ ላይ ሰው ሞተ ያው እንግዲህ ይሄንን ተመልከቱ እያሉ ለሕዝቡ እንደገና እያሰሙ ነበር ሕዝብ ባልሞተበት ሕዝብ ሞተ እያሉ ነበር ቅስቀሰ የሚያደርጉ የነበረው እና እኛ እንታሰራለን እዚያ ለተሰበሰበው ሕዝብ ማለት ነው እኛ እንታሰራለን እናንተ ቤታችሁ ትገባላችሁ ማለት ነው እያሉ ይጠይቁ ነበር
- ይሄ ፕሮግራም የእሁዱ አሁን ያሉት የእሁዱ የሐምሌው ፕሮግራም ምንድን ነው መልዕክቱ ምን ነበር ለምንድን ነው ከመደበኛው ለየት የሚያደርገው ምንድን ነው ?
- ለየት የሚያደርገው ያው ሕዝብ ጥሪ ነበር በጣም ብዙ ሕዝብ ነበር የመጣው የእዚያን ቀን እዚያ በጣም የተጨናነቀ ነበር ቀኑ እና ሕዝቡ ደግሞ ያው በወቅቱ በጣም ተረብሾ ነበር እውነት ነገሩ እውነት ነው ወይ ምናምን በሚል ተረብሾ ነበር
- ጥሪው በምን ተላለፈ ጥሪው ብለዋል እና ጥሪው ምንድን ነው ማን ጠራ በሚል የተጠሩት እንዴት ተሰበሰቡ ?
- ተጠርቷል የሚባል ነበረ እኔ እንደአጋጣሚ እንደክፍለ ከተማ ስለነበር ወደ እዚያ ሂዱ እንደዚህ ዓይነት ነገር ስላለ ተብለን አጣሩ ተብለን ያው ሰው እንደተጠራ ነበር የሰማሁት
- እና ሰው ምን አለ ምን ይል ነበር ምን ይታይበታል ሰው ሕዝብ የተሰበሰበው ?
- ሰው ያው እኛም እንታገላለን እያለ ነበር እዚያ ያለው ሁሉ ሰው ሳይሆን በመሀል መሀል አንዳንድ ሰዎች ናቸው ግማሹ ያልገባውም ሰው አለ በእዚያ መሀል ላይ ያለ ሰው ያልገባው ሰው አለ ምንም ነገር ያለው ነገር ግልፅ ያልሆነለትም ሰው አለ
- እስቲ እርሶ አሁን የግል አስተያየትዎን ሳይሆን ያዩትን ነገር ያዩት የሰሙት ?
- ያየሁት ያው እዚያ ሕዝብ በጣም ብዙ ነበረ
- እሱ ላይ አያተኩሩ ነው ሲናገሩ የግል አስተያየትዎ ከሆነ ሌላ ነው ያዩትን የሰሙትን ነው አተኩረው ይቀጥሉ
- ያየሁትማ የሰማሁት ያው መንግስት ደሴ ላይ መጀመሪያ የተደረገው እንትን
- በጥያቄው መሠረት ይቀጥሉ ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ ደቤ ላይ ሰው ሞተ አንደዚህ ሀገ ሲሉ ገበረ ብለዋል እና ምንድን ነው ይሄንን በእዚህ ጋር በተያያዘ ዋና ዓላማው ይሄ የዕለቱ በተለይ የሐምሌ አሁን ቅድም ያገለፁት የሐምሌው የእሁዱ ዋናው ዓላማው ምን ነበር ለማለት ነው ?
- ዓላማው እንግዲህ መበጥበጥ ነው ዓላማው ለእኔ የሚመስለኝ ዓላማው ምክንያቱም በሰላም ሀገር ላይ እንደዚህ ዓይነት ነገር መስራት ዓላማው ያው የተፈለገው ነገር ሌላ ቢሆን ነው ነው
- መበጥበጥ ይመስለኛል ?
- አዎ
- እሺ ዐቃቤ ሕግ
- ይሄንን ሲገልፁ ማለት ነው በድሩ ሁሴን ያሲን ኑሩ ምን ላይ ሆነው ነው ይሄንን ሲገልፁ የነበሩ እንዴት ነበር መልዕክቱን የሚያስተላልፉት ?
- አሁን እኔ በር አካባቢ ነበር የነበርኩት ቤቱ የተጨናነቀ ነበረ ለመስማት እየተንጠራራን ነበር እንኳን ያንን የምንሰማ የነበረው የተጨናነቀ ነበረ እናም እኛ አሁን ከእንግዲህ በኋላ እራሳችን መስዋት እናድርጋለን መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ይሽው ሰው እየሞተ ነው ቢደሴም ላይ ሰው ሞቷል ሲል ነው የሰማሁት
- አዎ ማለት የእነሱ መሆኑን መለየት የሚያስችል ሁኔታ ነበረ ማለት ሲናገሩ ማለት ነው ያሲን ኑሩ እና በድሩ ሁሴን መሆናቸውን ለመለየት የሚያስችል ነበር አገላለፃቸው ?
- አዎ ለየዋቸው እኮ አሁን እዚህም ለየዋቸው እኮ እሳቸው
- መድረክ እያዩዋቸው ነበረ ?
- አዎ በደንብ እያየዋቸው ነበረ ሲናገሩም እያየሁ ስለነበረ ነው አሁንም የለየሁት
- እያዩዋቸው ነበር ?
- አዎ
- ካሚል ሸምሱስ ?
- ካሚል ሸምሱ እዚያ አወሊያ ላይ በነበረው ነው የተናገረው እዚህ ላይ 2ቱ ነው እኔ ያየዋቸው
- አወሊያ ላይ እሱ ምን ይል ነበር ?

1498

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገቢቷል ታሪማኖት አዲስ ኃይማኖት አምጥቶብናል ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥቶብናል ከመጅሊስ ጋር ጎን በመሆን ብሎ ሲናገር ነው የሰማሁት
- ይሄንን የሚናገረው የት ቢታ ላይ ሆኖነው ?
- እዚያው አወሊያ መስኪድ ውስጥ
- አወሊያ መቼ ነበር ጊዜው ያስታውሳሉ ?
- ያው 2004 ታህሳስ ወር አካባቢ
- ታህሳስ ወር ?
- አዎ
- እና ምንድን ነው መጨረሻው ታዲያ እንዴት ሆነ የሚያስታውሱት ማለቴ ነው ዝርዝር በየጊዜው ነበር እንደዚህ ሲመጣ ሲል የነበረው ወይስ ?
- ይኸውን ነው የማውቀው እኔ ያየሁት ይሄንን ነው
- ጨርሰናል
- ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ ጥያቄ ካለ
- አመሰግናለሁ አንዋር በነበሩበት ወቅት ምን ያህል ሰው እንደነበረ መገመት ይችላሉ ?
- በጣም ብዙ ሰው ነው የነበረው ታችኛው መስኪድ ሞልቶ ነበር
- በቁጥር እንደው 100 ሺህ 50 ሺህ ?
- በቁጥር አላውቅም አልቆጠርኩም
- ደሴ ሰው አልሞተም ብለዋል ስለዚህ የሚያውቁት ነገር አለ እንዴ እርሶ ?
- ምንም የማውቀው ነገር የለኝም እዚያ ነው የሰማሁት አንዋር መስኪድ ውስጥ ነው የሰማሁት
- እኮ ሳይሞት ሞተ እያሉ ብለው ነበር ?
- አሉ እሳቸው ሲሉ ስለሰማሁ ነው እንግዲህ ሌላ ነገር የሰማሁት
- እንጂ የሚያውቁት ነገር የለም እርሶ ?
- ሌላ የሰማሁት ነገር የለኝም
- በድሩ እና ያሲንን በግድ ነበር የማያቸው ብለዋል ስለዚህ በድምፅ ነው የሰሟቸው ማለት ነው ?

1499

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- በመልክ ኣላዩዋቹውም ?
- በመልክም አይቼአቸዋለሁ አውቃቸዋለሁ 2ቱንም በደንብ ነው ያየዋቸው
- ያን ቀን ግን ለማየትም በግድ ነበር የማያቸው በመልክ አይተዋቸዋል ያን ቀን ?
- ተንጠራርተን እኮ አይተናቸዋል ተንጠራርተን እኮ እያየናቸው ነበር
- እሺ ከክፍለ ከተማ አጣሩ ተብለን ሄደን ነበር ብለዋል ማን ነበር እንዲሄዱ ያዘዞት ?
- እኔ መጅሊስ እሰራ ነበር በእዚያን ሰዓት መጅሊስ እሰራ ነበር እኔ
- ለእዚያ ነው ሊያጣሩ የሄዱት ?
- አዎ በወቅቱ እንግዲህ ያው ሄጄ ያለውን ሁኔታ ለማረጋጋት ሁል ጊዜ እንሄድ ነበር አንዋር መስኪድ በየጊዜው እንሄድ ነበረ
- አቶ ፋሪስ እርሶ በስንት ሰዓት ነው የደረሱት አንዋር ?
- በግምት ከ 4 ሰዓት በኋላ ነው የሄድኩት 4 ሰዓት አካባቢ ነው የደረስኩት
- ከ 4 ሰዓት በኋላ ?
- አዎ 4 ሰዓት አካባቢ
- ግቢውን እንዴት ገቡ ግቢውን ዝም ብለው ገቡ ?
- አዎ ገባሁኝ
- ምንም የገጠሞት ችግር የለም ?
- ያው ሰው እየተጋፋ እየተገባ ነበር እኔም ያው እየተጋፋሁ
- ሰው ከግቢ ውጪ አልነበረም ግቢው በቃው እርሶ 4 ሰዓት ሲደርሱ ግቢው በቃው ?
- እዚያ ውስጥ ነው የሞላው ውስጥ በቅቶትል እንትኑ ቤት ያኛው አዳራሹ ላይ /ግልፅ ያልሆነ/
- ሐምሌ እንደሆነ ነግረውናል ?
- አዎ
- አየሩ ምን ይመስል ነበር ዝናብ የአየሩ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር ?
- ዝናብ አልነበረም
- ፀሀይ ነበር ?

1500

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ እሱን አላስታውስም ፀሀዩን ዝናብ አልነበረም
- ካፊያም አልነበረም ?
- አልነበረም
- 4 ሰዓት ደርሰው መስኪድ ውስጥ መግባት እነሱ መስኪድ ውስጥ ነው ከመስኪድ ውጪ ነው ይናገሩ የነበሩት ?
- መስኪድ ይሄ ታችኛው መስኪድ
- ዋናው መስኪድ ሳይሆን ሌላ ?
- ታችኛው መስኪድ አዎ
- ታችኛው መስኪድ ውስጥ ነው ?
- አዎ
- እዚያ ውስጥ ነበር የሚናገሩት ?
- አዎ
- ታችኛው መስኪድ ማለት ኢማሙ የሚያሰግድበት ነው ወይስ ?
- ኧረ ትልቁ ታች ያለው
- ኢማሙ የሚያሰግድበት ተልቁ መስኪድ ነው አይደል ?
- ኢማሙ የሚያሰግድበት አይደለም
- እነሱ ትንሹ መስኪድ ነው ?
- እዚያ ታች ያለው
- ታች ያለውን ነው አነጋገራቸው በዕለቱ ማን ቀድሞ ተናገረ አንዋር ላይ በነበረው ቀድሞ ማን ተናገረ ?
- በድሩ ሲናገር ያው ከእዚያ በኋላ ያሲን ኑሩም ተናግሯል
- ተናገረ እርሶ ከ 4 ሰዓት ጀምሮ በቆዩበት እዚያ በቆዩበት ጊዜ 2ቱ ብቻ ነው የተናገሩት ?
- እኔ ያየዋቸው 2ቱን ነው
- 2ቱ ነው የተናገሩት ስንት ሰዓት ነው እርሶ የሄዱት ?
- ሰግጀ ነው የወጣሁት
- ሰግደው ስንት ሰዓት በግምት ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እዚያ ግን አልሰገድኩም እኔ እንትን ነው ተሻግሬ የሰገድኩት በኒን
- እርሶ ሰንት ሰዓት ወጡ ከእዚያ ?
- ለ 7 ያው 7 ሰዓት ነው የወጣሁት
- ከ4 ሰዓት ገቡ እስከ 7 ሰዓት ድረስ ?
- አዎ
- 2ቱ ተናገሩ አሁን ያሉትን ቃል ?
- አዎ
- በመሀል ታዲያ ምን ተደረገ በእዚህን ጊዜ ውስጥ ?
- ምንም ሌላ ያየሁት ነገር የለም
- በቃ 2ቱ ተናገሩ እና እስከ 7 ሰዓት ቁጭ ብለው ከእዚያ ሄዱ ?
- ያየዋቸው 2 ሆነው የተናገሩት ሌላውን አላየሁም ሌላ የተናገረውን አላየሁም
- እሺ ተከሣሾቹ ዳዋ ያደርጉ ነበር ብለዋል ቅድም የለዩዋቸው ተከሣሾች ዳዋ ያደርጉ ነበር ማለት ምን ማለት ነው ዳዋ ያደርጉ ነበር ማለት ምን ማለት ነው ?
- ንግግር ያደርጉ ነበር
- ዳዋ ማለት ምን ማለት ነው ?
- ያው ለሰው መልዕክት ያስተላልፉ ነበር ማለት ነው መልዕክት ያስተላልፉ
- አሁን ይኸውሎት ዳዋ ማለት ምን ማለት ነው ያልኮት ትርጉሙን የዳዋ ትርጉም እንዲነግሩኝ ነው የሚያውቁት ከሆነ ?
- አላውቅም
- አያውቁም መጅሊስ እሰራ ነበር ብለዋል ተከሣሾች ከመጅሊስ ጋር የሚያጋጫቸው ወይም ያልተግባቡበት ነገር ነበራቸው እንዴ ?
- ያው እዚህ ሀባሽ አምጥቷል በሚል ነው ሌላ ነገር የማውቀው ነገር የለኝም የተጋጨበትን ነገር አላውቅም
- እሱን አያውቁም መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል ብለዋል ብለዋል መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገባ ያሉት በምን መልክ ነው በምን ሁኔታ ነው መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገባ ያሉት ?
- ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥቶብናል በማለት ጣልቃ ገብቷል

1502

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥቶብናል በማለት ብቻ ነው መንግስት የገባው ያሉት እነሱ ?
- አዎ ሲሉ የሰማሁት ይሄንን ነው
- ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት ወይም ኣስተምሮት አለ እንዴ ?
- ኧረ ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት የለም የማውቀው የለም
- ስለዚህ የሌለ ነገር ነው መንግስት አምጥቶብናል ያሉት ?
- አዎ
- እኛ ብንታሰር እናንተ ወዴት ትሄዳላችሁ ሲል ነበር ብለዋል ወዴት ትሄዳላችሁ ብሎ ጥያቄ ብቻ ነው ያቀረበው አይደል ?
- አልገባኝም
- ቆዩ ቆዩ ግልፅ ተመልሷል
- የተከበረው ፍ/ቤት የመስቀለኛ ጥያቄ ዓላማው እኮ ያልተብራሩት ነገሮች በደንብ እንዲብራሩ ነው በእርግጥም ከተመለሰ ነገር ላይ ነው የምንነሳው በዋና ጥያቄ ላይ መመለሳቸው እኛ መስቀለኛ ጥያቄ እንዳንጠይቅ መከልከያ ምክንያት ሊሆን አይገባም የተከበረው ፍ/ቤት
- እስቲ ፍሎሶፊ እኮ ግልፅ ነው /ግልፅ ያልሆነ/ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል እና ይሄንን መስክረዋል እኮ እኛ ብንታሰር እናንተ ወደ ቤታችሁ ትገባላችሁ ወይ ነው ጥያቄው እና እዚያ ላይ ቆሞ የሚጠይቁትን መቀጠል ይችላሉ ግልፅ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄዬ እሱኑ እንዲያብራሩ ለማድረግ እና ይሄንኑ በግልፅ ሁኔታ ነገሩ ግልፅ ሆኖ እንዲቀመጥ ለማድረግ ነው ጥያቄዬ እና እሳቸው መመለሳቸው መልሰውት የነበረ መሆኑ ልትጠይቁ አይገባም መባሉ ተገቢ አይደለም የእኔ ቅሬታዬን ነው የማቀርበው አሁን ጥያቄዬ ግን ጥያቄዬ የመለሱት ነገር ላይ የተነሳሁት የመለሱትም እኛ ብንታሰር እናንተ ወዴት ትሄዳላችሁ እያለ ይናገር ነበር ብለዋል ?
- ወደ ቤታችሁ ነው ያለው እኮ በግልፅ ወዴት አላለም እኛ ብንታሰር እናንተ ወደቤታችሁ ትሄዳላችሁ ብሏል ነው ያለው ወይ ወደቤታችሁ ትሄዳላችሁ ወይ ብሏል ነው ያለው ላይ ቆሞ የሚጠይቁትን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ የተከበረው ፍ/ቤት እኛ የመዘገብነው እና የተረዳሁበት መንገድ የተለያየ ነው ማለት ነው ስለዚህ ወይ ይሄንን እንደገና አብራርቼ ልጠይቅ እኔ የተረዳሁት እኛ ብንታሰር እናንተ ወዴት ትሄዳላችሁ ብሏል ነው
- ወደ ቤታችሁ ነው ያለው ግልፅ ነው እኮ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ስለዚህ እናንተ እኛ ብንታሰር እናንተ ወደ ቤታችሁ ትሄዳላችሁ ነው ያላቸው ?
- አዎ እኛን ያው እኛ እንታሰራለን እናንተ ወደ ቤታችሁ ነው የምትሄዱት እኛ ስንታሰር ቤታችሁ ትገባላችሁ ማለት ነው ብሎ ጥያቄ ነው የጠየቁት
- ይሄንን /ግልፅ ያልሆነ/ የነበረው እሺ ከእዚህ ሌላ ግን ምንም ይሄንን አድርጉ ያንን አድርጉ አላላቸውም አይደል ?
- አልሰማሁም ሌላ
- በደሴ ሰው እየሞተ ነበር ሰው ሳይሞት ብለዋል ሰው አለመሞቱን እርሶ ያረጋግጣሉ እርግጠኛ ኖት ያውቃሉ ?
- ምንም ያወኩት ነገር የለም የተሰማም ነገር
- አሁንም ያስተካከሉ እርሶ ሲመዘግቡ በትክክል መዝግቡ ሰው ሳይሞት ሰው ሞቷል አላለም በደሴ ሰው ሞቷል አለ ስለመሞት አለመሞቱ እኔ አላውቅም ነው ምስክሩ ያለው እና በትክክል መዝግቡ እርሶ
- የተከበረው ፍ/ቤት ወደ ኋላ ተመልሰን ይሰማልን የምንለው የፍ/ቤቱን ጊዜ ለመጠበቅ ነው አሁን ግን ሀሰተኛ መሆን ስለሌለብን ይሰማልን ነው ቅድም ሲመሰክር ሰው ሳይሞት ብሎ ተናግሯል
- ቆዩ ቆዩ አሁን ምንድን ነው እሳቸው ጠይቀዋል ይሄንን ጥያቄ በቀጥታ እሳቸው በትክክል ጠይቀው ምላሽ ተሰጥቶበታል ተደግሟል ነው ምላሽ ተሰጥቶ የሞተ ሰውም እኔ አላየሁም ነው ብለው መልሰዋል ምናልባት ከእዚህ በኋላ የምትፈልጉት ነገር ካለ ነው ተደግሟል ነው ጥያቄው በትክክል ይቺን ጥያቄ እሳቸው ጠይቀዋል
- የተከበረው ፍ/ቤት ተደግሟል የሚለውን እቀበላለሁ እኔም እሳቸው ጠይቀውት እንደነበር አስታውሳለሁ ከእዚያ በተጨማሪ ጥያቄ ነበር መጠየቅ ያ[illegible] የሚለው ነገር

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ግን ብሏል ሰው ሳይሞት ብሎ ተናግሮ ስለነበር ዉይ ይሰማልን እንደሀሰተኛ መቆጠር የለብኝም የተከበረው ፍ/ቤት

- አሁን ይሄ ነው የተባለው ነገር ከእዚህ ተነስተው ሊጨምሩት የፈለጉት ነገር ካለ እሱን ጥያቄ ጠይቁ /ግልፅ ያልሆነ/
- በደሴ ሰው ይሙት አይሙት እርሶ የሚያውቁት ነገር የለም አይደል ?
- ምንም የማውቀው ነገር የለም
- እኔ ክፍለ ከተማ ነበርኩ አጣሩ ተብለን ነው የሄድነው ብለዋል የት ክፍለ ከተማ ነው የነበሩት /ግልፅ ያልሆነ/ ?
- እሱን /ግልፅ ያልሆነ/
- የተከበረው ፍ/ቤት ስለ ክፍለ ከተማ ነው የጠየኳቸው መጅሊስ እንደሚሰሩ እራሳቸው ተናግረዋል ክፍለ ከተማው የት ነው ነው ?
- ተቃውሞ አለ
- ክፍለ ከተማ ሲባል
- አይ ጥይቄውን ግልፅ ያድርጉት
- እኮ ቅድም ሲመልሱ እኔ ክፍለ ከተማ ነበርኩኝ አጣሪ ተብዬ ሄጀለሁ ብለዋል ክፍለ ከተማው የት ነው የእኔ ጥያቄ ?
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞአችን ምንድን ነው ከየት ክፍለ ከተማ ነው ይሄ አድራሻን የስራ ቦታን ሌላ ሌላ የመግለፅ ስለሆነ ያ ደግሞ ቀደም ሲል በብይን የታለፈ ስለሆነ የሚጠይቁት ካለ በሌላ ቢጠይቁ ይሻላል ይሄንን ግን ከእዚህ ጋር በተያያዘ ስለሆነ ጥያቄአቸው እንዲነሳልን በአክብሮት እጠይቃለሁ
- ብይን ተሰጥቷል በእርግጥ ከእዚህ በፊት የምስክሮች አድራሻ ማንነታቸው እንደዚሁ የስራቸው አድራሻ አይገለፅ ተብሎ በብይን ታልፏል እና አሁን የተነሳው ነገር እርሶ የተላኩት ከየትኛው ክፍለ ከተማ ነው የሚለው ከምስክሩ መኖሪያ አድራሻ ወይም ከሚሰሩበት ክፍለ ከተማ ጋር የተያያዘ ከሆነ ለመግለፅ አይገደዱም ከእዚያ ዉጪ ያለ ከሆነ ግን ይገልፃሉ
- አልገባኝም ይደገምልኝ
- /ግልፅ ያልሆነ/

1505

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነው እስቲ እስቲ ተመለሱ ያሉት እስቲ ምንድን ነው ስሙት እና ይመለስ እና እንስማው ችግር የለም
- አሁን በተባልነው መሠረት
- ግልፅ ይሁንልኝ ጥያቄው
- ይሽውሎት ስጋት አለብኝ ብለው ከአድራሻዎ ከምናምኑ እንዲህ ስጋት አለብኝ ብለው በእዚህ መንገድ የሚያስቡ ከሆነ ለመግለፅ አይገደዱም ከእዚህ ስጋት ውጪ ከሆኑ ግን ይገልፃሉ ከእዚህ ስጋት ውጪ
- እኔ አላህ በቂዬ ነው ለስጋቱ አላህ በቂዬ ነው
- ስለዚህ መመለስ እችላለሁ ነው ?
- አዎ ችግር የለብኝም
- የት ክፍለ ከተማ ነበሩ ?
- ቦሌ ነኝ
- ቦሌ ክፍለ ከተማ ምኑ ላይ ቦሌ ክፍለ ከተማ ማለት የመንግስት አስተዳደሩ ላይ ነው ወይስ የት ነው ?
- መጅሊስ ላይ ነበርኩኝ
- የቦሌ ክፍለ ከተማ መጅሊስ ?
- አዎ
- ከቦሌ ክፍለ ከተማ ነው ለአንዋር መስኪድ የተላኩት ?
- አዎ
- አንዋር መስኪድ በቦሌ ክፍለ ከተማ ስር ነው እንዴ ያለው ?
- ኣይ እዚያ እየሄዳችሁ በየክፍለ ከተማው ያው እዚያ እንትን እንዲሄድ ያለው ሁኔታ እንትን እንዲደረግ እጠየቅ ነበረ
- ይሽውሎት የጠየኮት አቶ ፋሪስ አንዋር መስኪድ በቦሌ ክፍለ ከተማ ስር ነው ወይ ነው ?
- አይደለም
- ክፍለ ከተማው ግን የሚያስተዳድረው የራሱ መጅሊስ አለው አይደለም የክፍለ ከተማው አንዋር?
- አዎ

1506

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ እዚያ ክፍለ ከተማ አጣራ ተብዬ ነው የተላኩት ብለዋል ምንድን ነው አጣራ የተባሉት?
- ያለውን ሁኔታ ያው ረብሻ ግርግርም ስላለ ለማረጋጋት ያው እኛ ትዕዛዝ ይሰጠን ነበረ ከመጅሊስ ማለት ነው
- ትዕዛዙን የሰጠት ማን ነው አጣሩ ያሉት ?
- ያው እኛ ክፍለ ከተማው አመራሮች ከመጅሊስ ጋር አብረው ነው የሚሰሩት 3ቱ አመራሮች ማለት ነው
- እነ ማን የክፍለ ከተማው አመራሮች ሲሉ የመንግስት አስተዳደር አመራሮች ማለት ነው ?
- የእንትኑ ያው የመጅሊሱ ማለት ነው
- የመጅሊሱ አመራሮች ከማን ጋር ሆነው ነው ነው የሚሰሩት ከመጅሊሱ ጋር ሆነው ነው የሚሰሩት ሲሉ ከማን ጋር ሆነው ነው የሚሰሩት ?
- መጅሊሱ ጋር የአዲስ አበባ መጅሊስ ጋር ማለት ነው
- ስለዚህ አጣሩ ያሎት የክፍለ ከተማው መጅሊስ ናቸው ?
- የአዲስ አበባ መጅሊስ
- አመራር ናቸው ?
- አዎ
- ሄደው ያጣሩት ነገር ምንድን ነው ?
- የአሁን ያየሁትን ነገር ያው የሰማሁትን
- ስለዚህ የሄዱት ወደ መስኪድ የሄዱት ለመስገድ ወይም በእዚያ/ ግልፅ ያልሆነ/ ሳይሆን ለማጣራት ነበር ?
- አዎ
- ሄደው እዚያ በሚያጣሩበት ጊዜ በቦታው ላይ ምንም ብጥብጥ ወይም ረብሻ አልተነሳም ነበር አይደል እርሶ እስከሚሄዱ ድረስ ?
- አላየሁም ያው ግርግርማ ነበረ
- ረብሻ ነው ያልኮት ረብሻ ወይም ብጥብጥ አልተነሳም አይደል ?
- በእዚያን ሰዓት አልተነሳም

1507

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቶ ፋሪስ ቅድም በአወሊያ ለኃይማኖታችን እንሞታለን ብለዋል አሉ መቼ እንደሚሞቱ አልገለፁም አይደል ?
- አልሰማሁም መቼ እንደሚሞቱ
- እንዴት እንደሚሞቱም አልገለፁም ?
- አልገለፁም አልሰማሁም እሱን
- የት እንደሚሞቱም አልገለፁም ?
- አልገለፁም እኔ ያላየሁትን ነገር
- በዕለቱ ለኃይማኖቱ የሞተ ሰው አለ ያዩት ?
- አላየሁም
- ቅድም መጅሊስ እንሰራለን ብለው ነበር አሁን እርሶ የሰሩበት የነበረው መጅሊስ ስልጣን አለ እንዴ ወይስ በሌላ ተተክቷል ?
- ተተክቷል በሌላ
- በአወሊያው ተቃዉሞ ምክንያት አይደል ?
- እሱን አላውቅም
- ይሄንን እንቃወማለን
- ተመለሰ እኮ በቃ ሳይመለስ ቢሆን አሁን ተመልሷል ቀጥሉ
- አወሊያ አርብ አርብ ሰው ይሰበሰብ ነበር ብለዋል ከመቼ ጀምሮ መሰብሰብ እንደጀመረ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- እንግዲህ ታህሳስ ላይ ነው እኔ ያልኩት ጊዜውን ይሄ ነው ብዬ የማውቀው ነገር የለም
- ታህሳስ ላይ ?
- ታህሳስ ላይ
- መቼ ምን ያህል ጊዜ ሄዱ እርሶ ለማየት ምን ያህል ጊዜ ሄደዋል በአወሊያ የተሰበሰበውን ሰው ለማየት ወይም የሚደረጉ ፕሮግራሞች ለማየት ምን ያህል ጊዜ ሄዱ ?
- አንድ ሁለቴ ሄጃለሁ
- አንድ ሁለቴ ሄደዋል ?
- አዎ
- ከእዚያ በፊት በነበሩት ፕሮግራሞች ላይ ምን ሲሉ ነበር ?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ያው ቅድም ያስቀመጥኩት ያው መንግስት በኃይማኖት ጣልቃ ገብቷል ሀባሽ የሚባል ኃይማኖት አምጥቶብናል ከመጅሊስ ጎን በመሆን ኃይማኖታችን እየተበላሸ ስለሆነ እኛ አይተን ዝም ማለት አንችልም እራሳችን መስዋት እናደርጋለን
- ጥያቄዬን በደንብ ያድምጡኝ እና እንዲመልሱልኝ ነው በየትኛው ፕሮግራም ላይ እንዳሉ በየትኛው 2 ፕሮግራም ላይ ተሳትፌአለሁ ብለዋል በየትኛው ፕሮግራም ላይ ነው ይሄንን ያሉት ?
- ያው በጁማው ላይ ነዋ
- በጁማው በ2ቱም ላይ ወይስ በየትኛው ላይ?
- በጁማው ላይ
- በመጀመሪያው ነው ወይስ በ2ኛው ?
- በ2ቱ ሰምቼአለሁ
- በ2ቱም ላይ ሰሙ ?
- አዎ
- ይሄንን እየተናገሩ ሕዝቡ በሰላም ነበር ወደ ቤቱ የሚሄደው ?
- እኔ ይሄንን ከሰማሁ በኋላ በቃ ለራሴ ወጥቼ እሄድ ነበረ የበኋላውን የሕዝቡን እኔ አላየሁም
- እርሶ ሰው ከመውጣቱ በፊት ነበር የሚወጡት ?
- አዎ
- ጨርሻለሁ
- ሌላ ጥያቄ አለ
- ድጋሚ ጥያቄ ካለ
- ሲጠየቁ አንዋር ላይ እርሶ ከወጡ በኋላ ማለት ነው እረብሻ ይፈጠር አይፈጠር ይሄንን ያውቃሉ እንዴ ?
- አይ የሰማሁት ነገር የለም ተፈጥሯል ሲባል በሌላ በወሬ እንደወሬ ነው የሰማሁት እኔ እራሴ ያየሁት ነገር የለም
- ግን በወሬ ከሌላ ሰምተዋል ?
- በወሬ ሰምቼአለሁ
- ሰምተዋል ?

1509

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ጨርሰናል
- የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ የለም ምስክሩ ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- እርሶ ያው ለምስክርነት ነው የመጡት አይደል ?
- አዎ
- ከእዚህ በፊት ለምስክሮቹ ደህንነት ሲባል ምስክሮች ሙሉ አድራሻቸውን እንዳይገልፁ ተብሏል ያው የራስዎን የግል ስም ብቻ ይገልፃሉ
- የመጀመሪያ ስምዎ ማን ነው ?
- አደም
- ስንተኛ ኖት
- የተከበረው ፍ/ቤት ታሳብ አለ የምስክሩ ቃልም መቀረፅ አለበት የ2ቱም ነው መቀረፅ ያለበት እና የ2ቱም እንዲቀረፅ ይደረግልኝ
- እኛ ታሳብ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆይ ቆይ ይሄ የስነ ስርዓት አካሄድ ስለሆነ ተቃውሞም አይደለም
- አይ እኛም ታሳብ ለመጨመር ነው
- ስለዚህ እሱን እስቲ መጀመሪያ እንነጋገርበት
- ስንተኛ ላይ የተጠቀሱት ናቸው ምስክሩ ?
- 18ኛ
- ብይን ተሰጥቷል አሁን በተመለከተ ዐቃቤ ሕግ የሰጡትን ምላሽ እንኳን በተመለከተ ይሄ አሰራር ነው ምላሽ ማሰጠት ብዙም አስፈላጊ አይደለም የችሎቱ አሰራር በመሆኑ ማለት ነው ችሎቱ ያው የቀረበውን ጥያቄ ተመልክቶ ብይን ሰጥቷል ብይኑ በአብላጫ ድምፅ ተሰጥቷል የመሀል ዳኛው እና ሌሎቹ 2ቱ ዳኞች ተለይቷል 2ቱ ዳኞች በአብላጫው የሰጡት በስነ ስርዓት ሕጉ ላይም የተቀመጠው ምስክሩ ታላፊነት አስተርጓሚው ታላፊነት ወስዶ እንደሚያስተረጉም ነው ከእዚህ የተለየ 2ቱ ይገባል የሚል በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም በአሰራርም ያለው የተለመደው የአስተርጓሚ ነው ከእዚያ በኋላ አስተርጓሚው ታላፊነቱን ካልተወጣ እሱ የሚጠየቀው ነው የሚሆነው እናም የሌላው ቃሉ የሚተረጎመው የምስክር

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ቃል ወደ መቅረፀ ድምፅ እንዲገባ አይገደድም ነገር ግን ያው አንድ ላይ ስለሚቀመጡ አልፎ በጨረፍታ የሚገባ ከሆነም ያ የሚመዘግቡት ወደ ፁሑፍ የሚቀይሩት መርጠው የሚይዙት ቃል ስለሆነ ችግር አይፈጥርም ተብሏል የመሀል ዳኛው ግን የሁሉም ምስክሮች የሚተረጎመው የአስተርጓሚ 2ቱም መግባት አለባቸው ተብሏል ስለዚህ በአብላጫው ድምፅ ውሣኔ መሠረት ይቀጥላል ማለት ነው

- አቶ አደም ዛሬ ለምስክርነት ነው የመጡት ?
- አዎ
- እነ ማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- በሀጂ አብዱራህማን ኡስማን
- እሱ ላይ ብቻ ?
- አዎ
- ሀጂ አብዱራህማን ኡስማንን ያውቁታል በአካል ?
- አዎ አውቃለሁ
- መለየት ይችላሉ አሁን ?
- አዎ አውቀዋለሁ
- አንዴ እዚያም ቆመው ከለዩ መለየት ይችላሉ መጠጋትም ይችላሉ በልብሳቸው ያሳዩ እርሶ ኖት ምስክሩ 27ኛን ተከሣሽ አሳይቷል አሁን ካሳዩን ሰው ጋር ዝምድና ወይ ጥላቻ አሎት ?
- የለኝም
- ከተባለ በኋላ ዐቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- ምስክር የምጠይቆትን እየሰሙ ይመልሳሉ አሁን ጠቁመው ያሳዩት ተከሣሽ ምን አደረጉ ተብለው እንደተከሰሱ ያውቃሉ ምን ማድረጋቸውን ነው የሚያውቁት?
- መስኪድ ያሰራል
- እስቲ በዝርዝር ይነግሩናል መቼ ነው የሚያውቋቸው ከጊዜው ይጀምሩ እና ?
- ከመቼ ጀምሮ የተባለው የመስኪዱ ነው ተከሣሽ የሚያውቁ ነው ግልፅ አድርጉት ?
- አይ ተከሣሹን የሚያውቋቸው ?
- 10 ዓመት ይሆናል
- የት ነው የሚያውቋቸው ?

1511

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሻሸመኔ አካባቢ
- ምንድን ነው የሚያውቁት ?
- መስኪድ ሲያሰራ በእዚህ ላይ ነው የማውቀው
- ምን ያህል መስኪድ አሰርተዋል
- ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ የተከሣሾችን የእያንዳንዳተው ድርጊት ምን አነደሆነ ለይተው አስቀምጠዋል ያው ጭብጥም ተደርጎ የሚያዘው የክሱ ማመልከቻው ስለሆነ ተከሣሽ 17ኛ ተከሣሽ ናቸው
- 27ኛ
- የእኔ ስህተት ነው እሺ ይቅርታ
- ስለዚህ አንስተዋል
- ምስክር ይቀጥሉ ምስክር ካቆሙበት
- ሻሸመኔ አካባቢ ነው የማውቀው ብለዋል
- ምን ሲያደርጉ ነው የሚያውቋቸው ?
- መስኪድ ሲያሰራ አውቀዋለሁ
- ከየት ገንዘብስ ?
- ከውጪ ሀገር የሚመጣ እርዳታ እያመጣ ነው የሚያሰራው
- ከየት ሀገር ሀገሩን /ግልፅ ያልሆነ/
- ከአረብ ሀገር
- ምን ያህል መስኪድ እንዳሰሩ ያውቃሉ ?
- አዎ ወደ 20 መስኪድ አውቀዋለሁ
- የት የት ነው ?
- በሻሸመኔ ወደ 10 መስኪድ አውቀዋለሁ
- ሻሸመኔ ወረዳ ?
- አዎ በሻሸመኔ ወረዳ 10 መስኪድ አውቀዋለሁ
- ሌላውስ ?
- ሻላ ወረዳ ውስጥም እንደዚሁ 10 መስኪድ አውቀዋለሁ
- መስኪድ ውስጥ መስኪዱ ብቻ ነው የሚሰራው ?

ECLN

1512

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የኢማማም ለኢማማም ተብሎ ከመስኪድ ጋር ይሰራል እሱንም ማሰራቱም አውቃለሁ
- ከእዚያ ?
- የኢማማ ማሰገጃ
- የተከበረው ፍ/ቤት ያው ምናልባት በመተባበርም በአንዳንድ የትርጉም ስህተት ካለ እያስተካከልን ቢፈቀድልን ቋንቋን የምንችል ስላለን 2ኛ ደግሞ ድምፃቸው ስለማይሰማ ከፍ ቢያደርጉት አሁን የኢማማ የሚል ብለዋል የኢማም ቤት ለማለት ነው
- አኬ ትርጉሙን ያው እኛም እንሰማለን ማስተካከል እንችላለን ድምፆን ግን ከፍ ያደርጉ የሚሰሙ ሰዎች ስላሉ ይሰሙ እርሶ ሲናገሩ ከፍ ያድርጉ ?
- የኢማም ቤትም ሲያሰራ አውቃለሁ
- የኢማም ቤት ?
- አዎ
- ከእዚያ እነዚህ መስኪዶች ከተሰሩ በኋላ ምን ይሆናሉ ?
- በእዚያ መስኪድ ኢማም ይቀጠራል
- ማን ነው የሚቀጥረው ?
- ሀጂ አብዱራህማን ነው የሚቀጥረው
- ምን ዓይነት ሰዎችን ነው የሚቀጥረው ?
- ቅጥሩ በ2 መንገድ ነው ያለው አንድ ኢማም ነው የሚቀጠረው መስኪድ ሌላው ደግሞ ዳዋ ተብሎ ዳዋ የሚያካሄዱትን ነው የሚቀጠረው
- ምንድን ነው ዳዋ ?
- ሕዝቡን የሚያስተምር ጥሪ የሚያደርጉ
- እነዚህ የሚቀጠሩ ሰዎች ደሞዝ የሚከፍላቸው ማን ነው ?
- ሀጂ አብዱራህማን
- እስቲ እነዚህ በየመስኪዱ የሚቀጠሩ ሰዎች የሚያስተምሯቸውን ነገሮች ያውቃሉ እርሶ ?
- አዎ አውቃለሁ
- ምን ምን እያሉ ያስተምራሉ ?
- ወሀብይ ተብሎ ወሀብይ ነው የሚቀጥሩት ድሮ የሚታወቁ ሼኪዎችን

1513

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማለት የትኞቹ ናቸው ድሮ የሚታወቁ ሼኪዎች ያሉት ሶፊያ ምንድን ናቸው እነሱ ሶፊያዎች?
- ሶፊያ የሚባሉት ናቸው
- ምንድን ናቸው እነሱ ?
- የድሪዎቹ ሶፊሎ ነው የሚባሉት
- የድሮ ማለት ?
- ሱናን የሚከተሉ የድሮ ሼኪዎች
- ምን ሶፊዎችን ነው የሚቀጥረው ነው የሚሉን ?
- አዎ
- ጠይቃቸው ሶሪ ሶፊዎችን ነው ወይ የሚቀጥረው ?
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ወሀብይ የሚባሉትን ነው የሚቀጥሩት
- ቆይ እስቲ አንዴ
- አይ ጥያቄው እኮ በቀጥታ ሱፊዎችን ነው ወይ የሚቀጥረው ነው ይሄ እኮ ከመምራት በላይ መመስከርም ነው አስተካክለው ይጠይቁ ጥያቄአቸውን አጠያየቁ
- መሪ ነው ነው ?
- አዎ ከመምራትም መመስከር ሱፊዎችን ነው ወይ የሚቀጥረው የሚለው ነገር ግልፅ ነው ጥያቄው
- መሪ ነው አይደለም የሚለው ላይ
- ምስክሩ እራሳቸው ሲናገሩ የነበሩት ነገር ነው እኛ ያደረግነው ምንድን ነው ከአስተርጓሚው ጋር መግባባት ስላልቻልን በእዚህ ነጥብ ላይ ምንድን ነው ያሉት እንደዚህ ነው ወይ ያሉት ብለህ ጠይቅልን ነው ያልነው እና እራሳቸው ካሉት ነው የተነሳነው ስለሱፊም ያብራሩት በፍ/ቤት ተጠይቆ ነው እና እሱን ለማረጋገጥ ነው የጠየቅነው እኛ እንጂ
- ግልፅ ሆኗል አሁን ብይን ተሰጥቷል ምስክሩ ቅድም ሲመልሱ እዚህ ኤርያ ላይ ሲደርስ የቋንቋ የትርጉም ችግር ነበረበት ምንድን ነው ያሉት ተከሣሽ ለቀጠሩት ሰዎች ደሞዝ ይከፍላሉ ብለዋል ምስክሩ ከእዚያ የተቀጠሩት ሰዎች እነ ማን ናቸው ተባለ የድሮ የወሀብይ ሼካዎችን ይቀጥራል አሉ ይሄ ደግሞ ምንድን ነው ብዬ የጠየኩት ነው ይሄ ምንድን ነው

1514

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ብዬ ስጠይቀው ሱፊዬ የሚባሉት ቡና የሚበጥሉ ፎድር ቤኪሦች ማለተ ነው ብለዋል ከእዚያ ቀጥሎ ደግሞ ዐቃቤ ሕጉ ሱፊዎችን ብቻ ነው እንዴ የሚቀጥሩት የሚል ነገር ነው እና አረዲ ተመልሷል መሪ ነው ነገር ግን ቅድሚያ ያው የተመለሰ ነገር ስለሆነ ነው ይቀጥሉ አሁን ከቆሙበት

- በመስኪድ ውስጥ የሚቀጠሩት ሱፊዎች ናቸው ?
- ወህብዮታን ነው የሚቀጥረው ነው ያልኩት
- ስለዚህ ሱፊዎች ይቀጠራሉ አይቀጠሩም ?
- አይቀጥሩም እነሱ መሆናቸው ከታወቀ አይቀጥሩም
- እነዚህ አሁን ሼህ አብዱራህማን የሚቀጥሯቸው ሰዎች ምን እያሉ ነው የሚያስተምሩት ቅድም የሚያስተምሩትን አውቃለሁ ብለዋል ምን እያሉ ነው የሚያስተምሩት ?
- እድር ሀራም ነው ክልክል ነው
- ሌላስ ?
- እድር የሚሰሩት ቃፊራዎች ናቸው
- ምንድን ነው ቃፊራ ?
- ሙስሊም አይደለም ማህበርም ሀራም ነው ይሄንን ነው የሚሉት
- ይቀጥሉ
- ለቅሶ ድንኳን መትከልም እራሱ ክልክል ነው ለለቅሶ መደራረስ እራሱ ክልክል ነው ይሄንን የሚሰሩት ቃፊራዎች ናቸው ሙስሊም አይደሉም እነዚህን የሚሰሩት ሰዎች ከሞቱ አትስገዱባቸው ነው የሚሉት መውሊድ ላይ የሚሰሩት እራሱ ሲሞቱ አትስገዱላቸው ቃፊራዎች ናቸው
- ምን ማለት ነው አትስገዱላቸው ይሄንን ግልፅ ያድርጉ እስቲ ?
- አንድ የሙስሊም ሰው ሲሞት በሰላት ነው በሸሪያ በሰላት ነው የሚሸኘው እንደዚህ ዓይነት ሰላት ደግሞ እሱ ላይ አትስገዱ ነው የሚሉት
- በሰላት አትሸኙ ማለት ነው ?
- አዎ
- እንደዚያ ነው ?
- አዎ እንደዚያ ነው ማለት ነው

1515

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይቀጥሉ ሌላስ ምን እያሉ ያስተምራሉ በዝርዝር ይንገሩን ?
- በእዚህ ዓይነት ነው ሲያስተምሩ የሚሄዱት ይህ ደግሞ 2ቱ ሙስሊሞች እንዲቃረኑ አደረገ አጣላ በእዚህ ምክንያት ነው ሰላምም አስፈሪ ሊሆን የቻለው በእዚያ ዓይነት የሚያስተምሩት አሁንም ታጥቀው ሀገር እንዲጋጭ እያደረጉ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ታጥቀው የሚል ቃል በአሮምኛ አልወጣቸውም /ግልፅ ያልሆነ/
- ቀብሳኒ ብለዋል
- ቀብሶ ማለት
- ትግል ማለት ነው
- እሺ ትክክል ነው አሁን እየታገሉ ነው ትግል ላይ ነው እንደዚያ ነው አይደል ያልከው ?
- አዎ እንደዚያ ነው
- እሺ ቀጥል
- የአካባቢው የገጠር አካባቢ ያለው ሰው በምንድን ነው የሚተዳደረው ?
- ተቃውሞ አለ
- ምንድን ነው
- የአካባቢ የገጠር ሰዎች በምን ይተዳደሩ የሚል ነገር የለሰ ምክንያትም አይደለም የለርክር ምክንያትም አይደለም ከክሱ ውስጥ ያለ ነገርም አይደለም ስለዚህ በእዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ሊጠየቅም ሊመሰክሩም አይገባም
- ከጭብጡ ጋር አይገናኝም ?
- በፍፁም አይገናኝም ከአጠቃላይ የክሱ ይዘት ጋርም አይገናኝም
- ዐቃቤ ሕግ ምላሽ
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ዋና ጥያቄ ነው እኛ ነን ምን እንደምናስመስክር የምናውቀው እንዴት ምስክሮቻችን ወደ የምንፈልገው ነገር መውሰድ እንዳለብን 2ኛ መርተን መጠየቅ አንችልም ይሄ ዋና ጥያቄ ነው የተከሣሽ ጠበቆች እንዲህ እንዲህ ነው አይደለ ብለን መጨረሻ ላይ ማረጋገጥ አንችልም ስለዚህ በእኛ አግባብ ነው ብለን በምናስበው መንገድ ዙሪያ ሄደን ሁላ ማስመስከር እንችላለን ይሄ ነፃነታችን ሊጋፋ አይገባም ለኛስ ትክክል ደጋጋሚ መቆራረጡም ጊዜ ነው እንጂ የሚፈጀው ምንም የሚጠቅም ነገር አይደለም እኛ አግባብ ያለው ነው ተቃውሞ አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት

1516

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ፍ/ቤቱ በተነሳው ጉዳይ ላይ ብይን ሰጥቷል የተባለው ጥያቄ የው ገጠር ያሉ ሰዎች እዚያ አካባቢ ያሉ በምን ይተዳደራሉ የሚል ነው የቀረበው ተቃውሞ ይሄ ከጭብጡ ጋር አይገናኝም የሚል ነው ዐቃቤ ሕግ ያው ምስክሮቻችን ወደ የምንፈልገው ለማድረስ የምንጠቀምበት ነው መምራት ስለሚችል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል ፍ/ቤቱ ከጭብጡ ጋር ይገናኛል ወይስ አይገናኝም የሚለውን አይቶታል አሁን ገጠር እዚያ አካባቢ ያሉ ሰዎች በምን ይተዳደራሉ የሚለው ከጭብጡ ጋር የሚገናኝበት መነገድ ለፍ/ቤቱ አልታየም ምናልባት እስኮፑን አጥቦ ከተከሣሹ ወይም ተከሣሹ ቀጠረ ከሚለው ሰዎች ጋር የተገናኘ ከሆነ ግን በእዚያ ኤርያ መቀጠል ይችላል ከእዚያ ውጪ የሕብረተሰቡን ብሎ የጠየቀው ነገር ነገር ከጭብጡ ጋር አይገናኝም ተብሎ ብይን ተሰጥቷል በእዚያ መሠረት አስተካክለው ይቀጥሉ
- ምስክር እነዚህ በእነዚህ አሁን በጠቀሷቸው መስኪዶች ውስጥ የሚሰብኩ ሰዎች ስለእርሻ ይሰብካሉ የሚያውቁት ነገር ስለእርሻ የሚሰብኩ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን
- እርሶ ምንድን ኖት ?
- የ28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ
- 28ኛ ነው
- አዎ የሚያያዝ ነገር ስላለው 28ኛ እና
- የሚመሰክረው በ 27ኛ ነው
- 27ኛእና 28ኛ ተከሣሽ እንደሚያያዝ ክሱ
- ቆዩ እና አሁን ይሄ የአካሄድ ጉዳይ ስለሆነ ከዐቃቤ ሕግ ከእዚህ ምላሽ መጠበቅ አስፈላጊ አይደለም እርሶ የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ ኖት የተመዘገበው በእዚህ /ግልፅ ያልሆነ/ መዝገብ ውስጥ ያለውም ይሄ ነው አሁን እየተመሰከረ ያለው 28ኛ ላይ ሳይሆን 27ኛ ላይ ነው እንዴት እንደሚገናኝ ምስክሩ የተናገሩት ነገር የለም እና ተከሣሽዋ ተጠቅሶ በተከሣሽዋ ላይ ሳይመሰከር ጥያቄ ብሎ መነሳቱ አግባብ አይደለም ከእዚህ በፊትም እንደዚሁ እኛንም ይመለከታል ብለው ያነሱት ነገር አለ እና ይሄም አግባብ አይደለም ይፅፉ ይፅሙለት ሰው ጋር ሲደርስ መጠየቅ ይችላሉ
- ስለዚህ አሁን
- አሁን አይቻልም

1517

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአጠቃላይ እኚህ ምስክር ስለ 28ኛ ተከሣሽ
- አሁን አይቻልም እንዲናገሩ አይፈቀድሎትም እኮ ነው
- እሺ አመሰግናለሁ
- አስተካክለው ያቀረቡት ጥያቄም መሪ ጥያቄ ነው ሌላ ምን ያስተምራሉ ብለው መጠየቅ ነው አሪፂ ፕሮሲጀር ስለአሪሳ ይበዛቡ ነዘር ይሄ ጠጃሚ እና የተስተካከለው ጥያቄ እራሱ ስህተት ነው
- ዐቃቤ ሕግ
- የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም የጠየቅነው ጥያቄ ፍ/ቤቱ /ግልፅ ያልሆነ/ እስፔስፊክ አድርጉት ስላለን እስፔስፊክ አድርገነዋል
- አሁን መሪ ነው የሚል ነው የተነሳው
- የጠየቅነው ደግሞ ስለእርሻ ያስተምሩ ነበር ወይ ብለን አይደለም የጠየቅነው ስለእርሻ የሚያስተምሩትን ነገር ያውቃሉ ወይ ብለን የጠየቅነው ምስክሩ ካወቁ የሚያውቁትን ያስረዳሉ መሪ እንዳይሆን በእዚያ መልኩ አድርገነዋል እስፔስፊክ እንዲሆን ደግሞ ከገጠር ሰው ወደ እርሻ አምጥተነዋል እና በእዚያ መልኩ ቢታይ
- እስቲ አስተካክለው ይጠይቁ
- ምስክር እነዚህ ብዙ ነገር ያስተምራሉ ብለው ቅድም ነግረውናል ?
- አዎ
- ከእርሻ ጋር በተያያዘስ የሚያስተምሩት ነገር አለ ?
- አለ አዎ ከእርሻ ጋር የተያያዘ
- ምን ይላሉ ?
- ማዳበሪያ አትውሰዱ
- ከማን ?
- ከመንግስት ማዳበሪያ መውሰድ እራሱ ሀራም ነው ብለው ነው የሚያስተምሩት
- ሌላስ ከእርሻ ውጪስ እንዴት ሁኑ እንዴት ሁኑ ይላሉ ?
- እንደዚሁ እረሱ ነው የሚሉት
- አይ ከእርሻ ውጪ ከእርሻ ውጪ ባሉ ነገሮች በግል ደረጃ እንደዚህ ሆኑ እንደዚህ አድርጉ እንደዚህ አታዳርጉ የሚሉት ነገር ካለ እሱን ይንገሩን ?

1517

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ትልቁ ነገር አሁን ያስተላለፍኩት ትልቁ ይሸው ነው
- ይሄ ነው ማለት አሁን የተናገሩት
- አለባበስን በተመለከተስ የሚናገሩት ነገር ነበር ?
- ሱሪ አሳጥሮ የሚለብስ ሙስሊም ነው ፂሙን የሚያሳድግ ሙስሊም ነው ስለዚህ ሱሪውን የማያሳጥር ፂሙን የማያሳድግ እስላም አይደለም በእዚህ ነው የምንለየው ነው ነው የሚሉት ሱሪውን የማያሳጥር ሰው ሙስሊም ውስጥ የለም ነው የሚሉት እንደዚህ እያሉ ያስተምራሉ
- ካፊር ምንድን ነው ?
- እስላም አይደለም ማለት ነው
- ቅድም በእነዚህ መስኪዶች የሚቀጥሯቸው ሱፊዎችን ነው ብለዋል አይቀጠሩም ብለዋል ሱፊዎቹ አይደል ይቅርታ ?
- አዎ እምቢ ነው ያሉት አይቀጥሩም
- ምን ይሁኑ ነው የሚሉት እነዚህ የሱፊ ኢማሞች ምንድን ናቸው ለምንድን ነው ምን ስላደረጉ ነው ?
- እሷን ግለፁ ምን ማለት ነው ?
- መውሊድ የነብዩን ልደት የሚያከብሩት እስላም አይደለም ብለው እምቢ አሉ ለእዚህ ነው እምቢ ያሉት
- እና ምን ይሁኑ ነው ኢማሞች የድሮ ኢማሞቹ ምን ይሁኑ ምን ይደረጉ ?
- የነብዩን ልደት ማክበር ይፈቀዳል ነው የሚሉት ለእዚህ ነው እምቢ ያሉት
- እሱ ጥሩ እሺ አሁን እሱን መሰከሩ ነገሩን አሁን የሱፊ ኢማሞች መውሊድን ያከብራሉ ይሄንን አታክብሩ ነው የሚሏቸው አሉ እነዚህ የሱፊ ይማሞችን እንደዚህ ስላደረጉ ምን እናድርጋቸው ነው የሚሉት ምን ይሁን ነው የሚሉት ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ
- ቆይ ተቃውሞአችሁ
- እነዚህ የሱፊ ይማሞች ምን ይደረጉ አሉ ብለው ነው የጠየቁት ስለዚህ ምን እናድርጋቸው አሉ እንደዚህ ተብሎ አይጠየቅም መርተው ነው የጠየቁት ይሄ ጥያቄ ሊታለፍ ይገባል የተከበረው ፍ/ቤት እንዲህ እናድርጋቸው እንዲህ ይደረጉ እንዲህ አይደረጉ ብለው እንዲመልሱ ማለት ነው አግባብ አይደለም ጥያቄው

1519

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዐቃቤ ሕግ መሪ ነው አይደለም የሚለው ላይ
- መሪ ጥያቄ አይደለም መሪ ጥያቄ ቀደም ብሎ ብይን ተሰጥቶበታል እኛ የጠየቅነው እነዚህ የድሮ ይማሞች ምን ይደረጉ ነው የሚሉት ነው ይሄ አሁን አዎ ወይም አይደለም የሚል መልስ የሚያሰጥ አይደለም ግልፅ ነው ምን ይደረጉ ነው የሚሉት የሚያውቁ ከሆነ እንዲህ ይደረጉ እንዲህ ይደረጉ ብለው ይመልሳሉ ካላወቁም አላውቀም ብለው ነው የሚያልፉት ስለዚህ መሪ ጥያቄ አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት
- የቀረበው ጥያቄ እነኚህ የሱፊ ኢማሞች ይሄንን ስላደረጉ ምን ይደረጉ ተብሏል ይሄ መሪ ነው የሚል ነው በእዚያ በኩል ግን ይሄ አዎ አይደለም የሚል መልስ የሚያሰጥ አይደለም መሪ አይደለም ብሎ መሪ ነው አይደለም የሚለውን ፍ/ቤቱ አይቶታል መሪ ነው አይደለም የሚለው ያው በእርግጥ አዎ አይደለም ብቻ የሚያሰጥ አይደለም መልሱን የሚያመላክት ነው አሁን የተያዘው ጉዳይ ግን መልሱን ያመላክታል አያመላክትም የሚለው ምን ይደረጉ የሚለው በጣም ሰፊ ስለሆነ መልሱ ያመላክታል ብሎ ፍ/ቤቱ አላመነበትም ስለዚህ ጥያቄው መሪ አይደለም ይቀጥል ብለናል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር ይቀጥሉ ምን እናድርጋቸው ምን ይደረጉ ነው የሚሉት የድሮ አ ማሞችን
- እነሱ ሲሞቱ እሱ ላይ አትስገዱ ነው የተባለው ቃሪራዎች ናቸው በእስላም ውስጥ የሉም
- አትስገዱ ማለት በሰላት አትሸኙ ማለት ነው የቅድሙ በሰላት አትሸኙ ማለት እሱ ነው ?
- አዎ
- ሌላ
- የድሮ ሱፊዎች ወይም የድሮ ኢማሞች የደረሰባቸው ችግር አለ ?
- አዎ
- ምን ?
- ለምሳሌ ሀጂ አማን ዋብ የሚባል ሞቶ እሳቸው ታዋቂ የሱፊ ሼኪ ናቸው ሞተው የካቲት 6/2003 ዓ.ም ሞተው አሁን ዳዋ የሚያደርጉት የተቀጠሩት እዚያ ሰላት እንዳይደረግላቸው ከልክለው ሰላት ያደረጉላቸውንም አራሱ እናንተም ቃሪራዎች ናቸው ተብለው ከልክለው ነበረ

1520

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ አሁን የሞቱት ነው ለኛ አሁን ስለሞቱት ሰውዬም የጠየኩት አሁን እዚያ አሁን በጠቀሱት አካባቢ መስኪዶች በሚሰሩበት አካባቢ ቅድም ኢማሞች በመስኪድ አይቀጠሩም የድሮ ኢማሞች ብለውናል ሌላ የሚደርስባቸው ችግር አለ ወይ ?
- አዎ ሱፊያዎች ተከልክለዋል
- ልክ ነው ሌላ የሚደርስባቸው ችግር አለ ወይ ?
- አዎ
- ምን ?
- ቃፊራዎች ናቸው ሰላት አታድርጉላቸው ነው የሚሉት
- ምስክር እየገባህ ነው ሲተረጉምልህ አይደል ?
- እየገባኝ ነው
- እናንተ አካባቢ ያሉት አሁን በጠቀስካቸው አካባቢ ያሉት የድሮ ኢማሞች አሁን ነገርከን ሲሞቱ ሰላት አይደረግላቸውም አትስገዱላቸው ይባላል ይሄንን ይሄንን ነገርከን ሌላ በችግር መልክ የደረሰባቸው ነገር አለ ወይ በጥቃት መልክ የደረሰባቸው ነገር አለ ወይ
- ተቃውሞ አለን
- አሱቲ ኮከሣሾች ስርዓት አድርጉ ያው ጠበቆች አሉ የሚያቀርቡት ነገር አለ ስርዓቱን ተከትለው እና ድምፃችሁ ይረብሻል እሺ
- የተከበረው ፍ/ቤት መጀመሪያ እየገባህ ነው ወይ የሚለው ጥያቄ እራሱ መጀመሪያ ተገቢ ጥያቄ አይደለም ምስክሩ የተጠየቁትን ነገር ያው ፍ/ቤቱም እየተከታተለ ነው እኛም እዚህ ጋር ቋንቋውን የሚያውቀው እየተከታተለው ነው የተጠየቁትን ነገር እየመለሱ ነው ያሉት እየገባህ ነው ወይ የሚለው ጥያቄ ሌላ አመላካች ነገር አለው እንደገና ከእዚያ አልፎ ደግሞ በተደጋጋሚ ለላመነሳት ነው የተውነው እንጂ የሚደርስ ችግር አለ ወይ የደረሰ ችግር አለ ወይ እያሉ መጠየቅ ስለችግር እንዲመሰክሩ መግፋት ነው ማመላከት ብቻ አይደለም እያስረዷቸውም ነው ያሉት ስለችግር ግለፅ በእነሱ ላይ ስለደረሰ ነገር ግለፅ እያሉ ደጋግመው እየገፉ ነው ያሉት እና ይሄ መመስከር ነው ከመምራትም በላይ እና የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንን ጥያቄ የደረሰ ችግር አለ ወይ የሚለው ነገር አዎ ብለው ስለደረሰ ችግር ትንታኔ ውስጥም የሚገባው ጥያቄው ሙሉ በሙሉ መቆም አለበት በሌላ መንገድ አስተካክለው ይጠይቁ ጥያቄአቸውን

154

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ የመጀመሪያውን ግልፅ ያልሆነ 2ኛው ግልፅ ነው እየገባ ነው ወይ የሚለው
- ተጨማሪ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆይ የመጀመሪያው ግልፅ ይደረግ እና ምላሽ እየሰጠን አይደለም ግልፅ እንዲሆንልን ነው እና የገባ ነው ወይ የሚለው ነገር ተገቢ አይደለም ሌላ አመላካች ነው የሚል ነገር አለ ተገቢ አይደለም የሚለው አንድ ነው ሌላ አመላካች ሌላ የሚለው ምንድን ነው አሉ ?
- እየገባህ ነው ወይ የሚለው ነገር
- ሌላ የምትለው ብቻ
- እኮ እየገባህ ነው ወይ የሚለው ጥያቄ እኔ የምልህን ነገር እየመለስክልኝ አይደለህም የሚለው ነገር አመላካች ነው እኔ የምልህን ነገር እየመለስክልኝ አይደለም የሚለው ነገር ማመላከት ነው መረዳት ያለብን ቅድም ዐቃቤ ሕግም አረጋግጠዋል ምስክሮቻቸውን አስጠንተው ነው የሚያመጡት ይሄ ተቃውሞ የለንም አስጠንቶ ማምጣታቸው ላይ ግን እየገባህ ነው ወይ የሚለው ነገር የሚነሳው ካስጠኗቸው ጥናት ጋር ነው ወደ እዚያ ነው የሚያመላክተው ስለዚህ ይሄ ተገቢ አይደለም እየገባህ ነው ወይ የሚለው ጥያቄ እራሱ ተገቢ ጥያቄ አልነበረም
- ሌላ አለ የተባለው
- የተከበረው ፍ/ቤት ዐቃቤ ሕግ ክርክር በሚያደርጉበት ጊዜ ሕዝብን እና መንግስት ወክለው የቆሙ እንደመሆናቸው ኤፈርነስ የሚባለው ነገር መኖር አለበት እና ተቃውሞ ብለን እየተነሳን ባለንበት ሁኔታ መልሱን የመናገር አሁን ድገመው ከተባልኩ ጥቃት ብሎ የመናገር ሁኔታ አለ እና ይሄ ባይሆን ችሎቱ በተደጋጋሚ ሲያሳስበን እንደነበረው እስሙዝሊ ችሎቱን ብናስኬደው የሚል ለማሳሰብ ነው
- እየገባህ ነው ወይ የሚለው ነገር የችሎት አካሄድ ነው እሱን ይለፈው እና 2ኛው መሪ ነው አይደለም የሚለውን
- አንለፈው የመጀመሪያውን
- እሱ የችሎት አካሄድ ነው ይለፈው እሱን 2ኛው
- እኛ እንኳን ያው በአስተርጓማ ስለሆነ ጥያቄውን ተረዳተሀል ወይ ለማለት ነው ላለ አይደለም 2ኛ የጠየቅነው ጥያቄ ቅድም አሁን ፍ/ቤቱ ከእዚህ ጥያቄ በፊት ብይን የሰጠበት ተመሳሳይ ጥያቄ ነው ያቀረብነው ተመሳሳይ ጥያቄ ነው ችግር ብሎ መጠየቅ ሌላ ቋንቋ ስላጣን ነው ጠቅላላ የሆነ ቋንቋ የደረሰ ችግር አለ ወይ ብሎ መጠየቅ ምንድን ነው

1522

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የደረሰው ችግር እርሶ ከገለፁት ችግር ሌላ የደረሰ ሌላ ችግር አለ ወይስ የለም ብሎ መጠየቅ ከእዚህ የተሻለ አማርኛ ስለሌለው ነው ከእዚያ ባለፈ ግን እኛ ምስክሮችን ሚስኮት ማድረግ ጥሩ አይደለም አስጠንተን አስጠፍቶ ማምጣት አይደለም በስነ ስርዓት ሕጉ መሠረት ምስክሮች ፖሊስ ጋር ቃል ይሰጣሉ እዚህ ችሎት ከመግባታቸው በፊት ደግሞ ቀደም ተብሎ ሪየርስ ይደረጋሉ ይሄም ከ ነ ሣምንት ከ ነዉ ቀን በፊት የተሰራ ስራ

- ይሄ የችሎት አይደለም
- አይ ሚስኮት መደረግ የለበትም ዐቃቤ ሕግ እዚህ ቆሞ ያለው የግል ጉዳይ አይደለም ይሄ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አይ እኛም /ግልፅ ያልሆነ/ ፕርሲቭ መደረግ አንፈልግም አሁን ጠበቆች በሚያቀርቡት መልኩ አይደለም እኛ ችሎቱን ሀንድል ይሄ ኬዝ ሀንድል እያደረግን ያለነው እና እነሱ ከሚሉት በላይ ስለፌርነስ እንጨነቃለን ይሄ ምስክር ሀሰተኛ ነገር ቢናገር እኛ ነን እንትን የምንለው እና
- አልጨረስንም ዐቃቤ ሕግ ነኛ እየተነጋገርን ነው እኛ ስለዚህ ጠዋት ስላልነበሩ ነው ጠዋት የተሰጠ ማሳሰቢያ ነበር እርሶ አልደረሱም ስለዚህ እዚህ እየተነጋገርን እኛ ጥያቄው ሳይገባን እናንተ ብትናገሩ ምን ዋጋ አለው ስለዚህ ይሄንን መሠረት አድርጋችሁ በቀረበው መቃወሚያ ላይ መልስ ስጡ ከተባላችሁ በቀረበው ላይ ብቻ መናገር ከእዚያ ውጪ ያለው ነገር ፍ/ቤቱ ነው የሚመዝነው ስለዚህ አሁንም አሁን በቀረበው መቃወሚያ ላይ ብቻ በጥያቄው ላይ በእሱ ላይ ምላሽ ስጡ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ብይን ተሰጥቷል ያው ቅድም አሁን የተሰጠው ማስጠንቀቂያ እንዳለ ሆነ አሁን ለተነሳው አሁን የተሰጠው ማሳሰቢያ እንዳለ ሆኖ አሁን በተነሳው ነገር ላይ ነኛ ስለምስክር /ግልፅ ያልሆነ/ የእዚህ ችሎት ጉዳይ አይደለም ይሄ ችሎት የሚያስተናግደው እዚህ የቀረበውን ነው እሱ ከእዚያ ውጪ ያለውን በእዚህ ችሎት የሚቀርበውን በስነ ስርዓት ሕጉ መሠረት የሚዳኘውን ነው እሱ እዚህ ውስጥ አይካተትም ሌላው ግልፅ ነው ወይ ምስክር የሚለው ነገር ሌላ አንድምታ አለው የሚል ነገር ተነስቷል ነገር ግን ያው አካሄዱ ነው ይሄ ላይ መልስ መስጠት አይጠበቅብህም ተብሎ ነበር ነገር ግን ያው ዐቃቤ ሕግ በሰጡት ሀሳብ ተርጓሚ ስለሆነ ቋንቋ ገብቶሀል ወይ ማለቴ ነው ሌላ አይደለም ብለዋል ፍ/ቤቱም ከእዚህ የተለየ አይረዳውም ቋንቋ ነው ማስተርጎምም ላይ ችግር ተፈጥሮ ሌላም አይገዘ ነው እና ያው ይሄ

1523

http://ethcriminalawnetwork.com/

ከትርጉም ያለፈ ሌላ አድሞታ አለው ብለሎ ፍ/ቤቱ አይወስደውም አቡ ተግር የለውም ሌላው ከእዚህ ከነገሩን ሌላ በችግር መልክ የደረሰ አለ የለም የምትለዋ አለ የለም የምትለዋ ፓርት ሌላ ችግር የሚለው ሰፊ ነው ቅድም በእዚያ መሠረት ነው ብይን የተሰጠው አለ የለም የምትለዋን ፓርት ግን አስተካክሏት

- እሺ ምስክር ቅድም ከጠቀሷቸው በድሮ ይማሞች ላይ ይደርሳሉ ካሏቸው ችግሮች ሌላ የሚያውቁት ነገር አለ ሌላ የሚደርስ ?
- አዎ
- ምን አለ ?
- ያለው ችግር አሁን ከመለስኩት መልስ ጋር ተያይዘው አትስገዱባቸው ከሚለው ጋር ተያይዞ እነሱ ቃፊራዎች ናቸው ቃፊር ስለሆኑ መግደልም ይቻላል የሚሉ ነበረ ከሞተ አትሸኙት ሰላት አታድርጉላቸው ያለው ችግር ይኸው ነው ከእዚህ ጋር የተያያዙ
- ሲናገሩ የድሮ ኢማሞችን መግደልም ይቻላል ብለው ይሰብኩ ነበር ብለዋል በምን መልኩ ነው መግደል ማለት ?
- ጅሀድ ማድረግ ይቻላል ነው ያሉት
- ዋና ጥያቄ አቦቃን
- ዋና ጥያቄ ተጠናቋል መስቀለኛ
- ምስክር ቅድም 20 መስኪዶች ከውጪ በተገኘ ከአረብ ሀገር በተገኘ እርዳታ ይሰራል ተሰርተዋል ሀጂ ኢብራሒም ሰርተዋል ብለዋል ትክክል ነኝ ሀጂ አብዱራህማን ?
- አዎ
- በምን አወቁ እርሶ ?
- አካባቢያችን ነው አዎ አካባቢያችን ነው በወረዳችንም ወደ ቀበሌያችንም ወርዶ አሰርቷል በእዚያ ነው የማውቀው
- መስኪዱን ሲያሰሩ ከእዚያ በመገመት ነው ?
- ወደ ቀበሌም ወርዶ አሰርቷል በእዚህ ነው የምናውቃቸው
- አሳቸው ፣ነዘቦን ከባንክ ሲያወጡ አይተዋል ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለ
- እሺ ተቃውሞ ምንድን ነው

1524

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በዋና ጥያቄ እንደተመሰከረው ከአረብ ሀገር ይላካል ሲባል አሰማለሁ አሉ አሁን የተከሣበ ጠበቃ እየጠየቁ ያሉት-ክባንክ ሲያወጡ አይተዋል ወይ የሚል ጥያቄ
- ጥያቄውን ለምን እንደተቃወሙ ?
- አግባብነት የለውም ምስክሩ ባልመሰከሩት ጭብጥ ላይ ነው እየተጠየቀ ያለው
- የተከበረው ፍ/ቤት ከውጪ በተገኘ ገንዘብ ነው ብለዋል ስለዚህ ገንዘቡ እንዴት ተከሣሽ ዘንድ እንደገባ የሚያውቁትን ነገር ጋር በተያያዘ ነው የሚላክባቸው የተለያዩ መንገዶች ስላሉ እነዚያን መንገዶች ሁሉ በመጠየቅ ለማረጋገጥ ነው
- ስለዚህ ተያያዥነት ያለው ነው ?
- ስለዚህ አግባብ ነው አዎ
- ብይን ሰጥተናል የተነሳው ያው ገንዘብ ከአረብ ሀገር በሚገኝ ገንዘብ መስኪድ አሰርቷል ነው አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ የተነሳው ገንዘቡን ከባንክ ሲቀበሉ አይተዋል ወይ የሚል ነው ዐቃቤ ሕግ ይሄንን ሲቃወሙ በዋና ጥያቄ ምስክሩ ከመሰከሩት ጋር አይያያዝም ብለው ነው የተቃወሙት ይያያዛል ወይስ አይያያዝም የሚለውን ፍ/ቤቱ አይቶታል አሁን ያው ገንዘብ ከአረብ ሀገር ተልኳል መስኪድ አሰርቷል ነው ፍሬ ነገሩ ከእዚህ ገንዘቡን በየት ተገኘ የሚለውን መጠየቅ መብታቸው ነው የማከለክል ነገር የለም በእዚህ ሂደት መምራትም ስለሚችሉ ከባንክም ሲያወጣ አይተዋል ማለት በስነ ስርዓት ሕጉ የማይደገፍ ጥያቄ ሆኖ አላገኘነውም ስለዚህ ጥያቄውን ይቀጥሉ ብለናል
- እኔ ባንክ ሄጄ አልተከታተልኩም
- ሰውስ አምጥቶ ሲሰጣቸው አይተዋል የተላከው ሰው አምጥቶ ብሩን ሲሰጣቸውስ ለሀጂ አብዱራህማን አይተዋል ?
- አላየሁም እኔ ከአረብ ሀገር መጥቶ በየቀበሌ እየዞሩ አብረው ሲሰሩ ነው የማውቀው እንጂ ገንዘብ ሲሰጡ አላየሁም
- ስንት ገንዘብ እንደመጣም አያውቁም አይደል ?
- አላውቀውም
- ቅድም ኢማሞች እና ዳኢዎች ተቀጥረዋል ሼህ አብዱራህማን ቀጥረዋል ብለውናል ስንት እንደተቀጠሩ ያውቃሉ ስንት ናቸው የተቀጠሩት ?

1525

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ጥቂት ነው የማውቀው ሻላ ወረዳ ውስጥም አለ ብዙ ስለሆኑ እኔ ጥቂቱን ነው የማውቃቸው
- በመልክ ያውቋቸዋል ?
- ሰዎቹን ነው
- አዎ እነዚህ ዳኢዎችን እና የሚያውቋቸው ከእዚያ በፊት ስንት ናቸው በቁጥር እርሶ የሚያውቋቸው ?
- ከእነዚያ ውስጥ 6/7 የሚሆኑትን አውቃቸዋለሁ
- ከኢማሞች እና ከአስተማሪዎች ?
- አዎ
- ቅድም ሲናገሩ በመጀመሪያ ደረጃ ሼህ አብዱራህማን እነዚህን ሰዎች ስለመቅጠራቸው በምን አወቁ እርሶ ?
- እሳቸው ባሰሩት መስኪድ ላይ ነው የሚሰሩት በእዚህ ላውቅ ችዬአለሁ ዳዋዎች በየቀበሌው ስለሚሄዱ በእዚያ ነው ሰዎቹን የምናውቃቸው
- እንጂ ሰዎቹን ሲቀጥሩ ውል ሲዋዋሉ እርሶ አልነበሩም ?
- አብሬ አልነበርኩም
- ደሞዛቸውም ስንት እንደሆነ አያውቁም ?
- ሰማን እንጂ ስንት እንደሆነ አናውቀውም ግን እነሱ ይነግሩን ነበር ተቀጣሪዎቹ ማለት ነው
- ቅድም እነዚህ ተቀጣሪዎች ያስተማሩትን ነገር ነግረውናል ይሄ ነገር ሀራም ነው ይሄ ክልክል ነው ሲሉ ይሄንን መቼ ነው ማን የሚባል መቼ ነው ያስተማረው ማን የሚባል ከሚያውቋቸው ውስጥ ቅድም አውቃለሁ
- እስቲ ጠበቃ ነኛ በአስተርጓሚ ስለሆነ አንዳንድ ይሁን የተለያየ ሲሆን አስተርጓሚው መሰብሰብ ያስቸግራል
- ቅድም 6 ያህሉን አውቃለሁ ብለዋል ከእነዚህ ውስጥ ያስተማረው ሲያስተምር የሰሙት በስም እስቲ ይግለፁልን ?
- አንዱ ሀጂ ሁሴን ሰብሮ ነው የሚባለው አንዱ ደግሞ ሼህ አሊ ሻንካ ነው የሚባለው አንዱ አንዱ ደግሞ ሸምሱ ሙስጠፋ ይባላል
- እነዚህ 3ቱም አንድ ዓይነት ትምህርት ነው ያስተማሩት አይደል ?

1526

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- በየትኛው መስኪድ ነው እስቲ የመስኪዱን ስም ይነግሩናል በየትኛው መስኪድ ነው ያስተማሩት ?
- እነሱ ኢማሞች አይደሉም ዳዋ ተብለው በየቀበሌ እየዞሩ ነው የሚያስተምሩት በየአካባቢው ሰው ይሰበሰባል በእዚያ ዓይነት እየዞሩ ያስተምራሉ ዳዋ የሚባሉት ናቸው
- ዳዋ የሚባሉት እነሱ ናቸው የሚያስተምሩት ዳዋ የሚባሉት የሚያስተምሩት ሰዎች ፍቸው ?
- አዎ
- እርሶ የሰሙት አሁን ሲያስተምሩ የሰሙበት አንድ ቦታ በየቦታው አሉን ከቦታዎቹ ውስጥ አንድ ሁለቱን መጥቀስ ይችላሉ ?
- ሌሎቹም አሉ አሁን ከጠቀስኳቸው ሰዎች ውጪ ሌሎችም አሉ ለምሳሌ
- እኔ የጠየኩት አሁን ቅድም ከጠቀሱልን ሰዎች የት የት ቦታ ላይ እንዳስተማሩ እርሶ ተገኝተው ያዳመጡበትን መርከዝ ብለዋል ከእነዚህ ውስጥ የት የት ጋር በስም መጥቀስ ይችላሉ ?
- አዎ እችላለሁ
- ይንገሩን ?
- ሀጂ ሁሴን ሰብሮ መርካሰፋጂ ወልቂጤ የሚባል አካባቢ ነው እሱ ያስተማረው እሱ የእዚያ አካባቢ ተወላጅ ነው አሊ ሻንካ የሚባለው ደግሞ እሱ ደግሞ መርከዛ 16 ቀበሌዎችን አሰባስቦ ነው ኩሬ ረጉቻ የሚባል መስኪድ ውስጥ ነው ያስተማረው
- 16 ምን ?
- 16 ቀበሌዎች አጠቃላዩ መርከዝ ነው ሚባለው
- መርከዝ ምንድን ነው የአካባቢው ስም ነው ወይስ ?
- የሚሰበሰቡበት ጣቢያ ማለት ነው
- ጣቢያ ማለት ነው መርከዝ ወይስ ግልፅ ይሁኑ መጀመሪያ እና መርከዝ ማለት የጣቢያው ስም ነው ወይስ የአካባቢው ሰፈር ስም ነው መርከዝ ?
- 16ቱን ቀበሌዎች የሚይዝ መርከዝ ነው የሚባለው
- መርከዝ ተብሎ ነው የሚጠራው በምንድን ነው ይሄ ቋንቋው ?
- አረብ

1527

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አረብኛ መርከዝ 16 ቀበሌዎችን ነው መርከዝ ማለት ይቀጥሉ
- በእነዚህ ቦታ እርሶ ተገኝተዋል አይደል ?
- መልሰዋል እኮ እኔ የተገኘሁበት ቦታ አለ ነው እንደዚያ ነው አይደል የተገኘሁበት ቦታ አለ?
- አዎ የተገኘሁበት ቦታ አለ
- ከእነዚህ ውስጥ የትኛው ላይ ነው የተገኙትን ያልተነኙትን ይግለፁልን ?
- ለምሳሌ ጣጤሳ ደዴሳ አካባቢ እዚያ ላይ ተገኝቼአለሁ ለቅሶ ክልክል ነው በለቅሶ ላይ መሰባሰብ ክልክል ነው
- ቦታዎቹን ብቻ ቦታዎች ቦታ ነው እየጠቀሱት ያለው የተገኙባቸውን ቦታዎች አንዱን ጠቅሰዋል ?
- ጣጤሳ ደሬሳ ላይ ተገኝቼአለሁ
- ወደ ማብራሪያ የገቡ መስሎኝ ነው ሌላ ቦታ እስቲ ሌላ ቦታ ነው አሁን ጥቀሱ የተባሉ ሌላ የተገኙበት ቦታ አለ ከጣጤሳ ደዴሳ ውጪ ?
- ፋጂ ወልቂጤ አካባቢያችን ነው አውቀዋለሁ ሀጂ ሁሴን ሰብሮ እዚያ ሲያስተምር አውቀዋለሁ ሀጂ አማን ዋብ የሚባል ሞቶ እዚያ ስንሄድ እዚያ ያስተምር ነበር እዘያ አስተምሮ አትስገዱበት ብሎ ሲል እዚያ አብረን ነበርን
- ማን ነው እሱ ?
- ሀጂ ሁሴን ሰብሮ
- ቅድም ሲመሰክሩ እነዚህ በሚሰጡ ትምህርቶች ምክንያት 2 እስላሞች ተጣልተዋል ብለዋል ትክክል ነኝ ?
- ጥያቄውን
- እነዚህ ዳኢዎች እና በሀጂ አብዱራህማን የተቀጠሩ ዳኢዎች እና ኢማሞች በሚያስተምሩት ትምህርት ቅድም ሀራም ነው ሀራም ነው በሚሉት ምክንያት 2 እስላሞች ተጣልተዋል ብለው ነበር ቅድም ሲመሰክሩ ትክክል ነኝ ?
- 2 ቦታ ተለይተው ግጭት እና ጥል መጣ ይሄ ነው
- እነዚህ 2 ቦታ የተከፈሉት ማን ማን ተብለው ነው የተከፈሉት ?
- አይ እስቲ ጥያቄው አሁን ጥያቄው ወደ ሌላ ማብራሪያ ሳይሆን በ 2 ተከፍሏል ብለዋል እና እነኚህ በ2 ቦታ የተከፈሉት ማን እና ማን ተብለው ነው እንደዚያ ነው ጥያቄው ?

1528

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ 2 ሙስሊሞች 2 እስላም ተጣሉ 2 እስላሞች የሚል ነው መጀመሪያ የተናገሩት እነዚህ 2 እስላሞች ያሏቸው ከምን አንፃር ነው በምን ተነስተው ነው ?
- ቆዩ እስቲ
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩን እየተከታተልን ነው እኛም እንደዚያ 2 እስላሞች እንዲህ ተጣልተው አላሉም ስለ ግለሰባዊ ሳይሆን አጠቃላይ የመሰከሩት በ2ቱ መካከል የነበረው በእነኚህ በአስተምሮቱ እና በእዚያኛው በሼኪዎቹ መካከል ባለው የማስተማሩ ሂደት ላይ ቅራኔ
- ማብራሪያ ሳይሆን
- አዎ ይሄንን
- እስቲ ቆይ እኛም የያዝነው ጥያቄ 2 የተከፈሉ የሙስሊም ግሩፕ አለ ነው እሱን ጥያቄ ነው የያዝነው ስለዚህ የጠየቁትም እሱን ነው ከእዚህ ተነስታችሁ
- አዎ
- 2 ሰዎች አላሉም አሁን እሳቸው የተረዳነው ጥያቄ 2 ሰዎች ሳይሆን 2 ግሩፕ በሚል ምናልባት 2 ስለተባለ ቃሉ ካልሆነ ይቀጥሉ
- በትምህርቱ እነዚህ አበተማሪ ዳኢዎች በሚሰጡት ትምህርት ምክንያት ሙስሊሞች 2 ቦታ ሆነዋል ብለዋል 2 ቦታ የሆኑት እነ ማን ናቸው አንደኛው ማን ነው አንደኛው ማን ነው ?
- ከሚሰጠው ትምህርት የተነሳ እና እነሱን የማይከተል ሕዝብ በእዚያ የተነሳ ለ 2 ሊከፈል ነው የቻለው ለምሳሌ ሱሪውን የማያሳጥር እነሱ ቃፊር ነው የሚሉት ለቅሶ ዱንኳን የሚተክለውን ሁሉ ቃፊር ነው የሚሉት ቃፊር ማለት ደግሞ ከእስላምነት ውጪ የሆነ ማለት ነው ይህ አባባል ደግሞ ሕዝቡን ነው ያጣላው ተለየ ያልነው ይሄንን ነው ያው ግጭት አመጣ እሱ ደግሞ ቃፊር ማለት መባል ደግሞ ግጭት አመጣ ይሄ ነው
- ስለዚህ ሕዝቡ በእነሱ ደጋፊ ና ተቃዋሚ ለ 2 ተከፈለ እንደዚህ እንረዳው ምስክር ?
- ችሎቱ በእዚህ ነው የተረዳው ምናልባት
- ነው አዎ
- እነሱን የሚደግፈው ሕዝብ ምን ያህል ይሆናል በግምት መገመት ይችላሉ ?
- አልችልም
- ብዙ ትንሽ እነዚህ ብለው ማስቀመጥ ይችላሉ ?

1529

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ጥያቄ ይሄንን ያው መልሰዋል ሌላ
- አይ አልተቀረፀም ያሉት አልተቀረፀም
- መገመት አልችልም ብለዋል እኮ
- መገመት አልችልም የሚለው አልተቀረፀም ?
- መገመት ሳይሆን የሚከተሏቸው ሰዎች ብዙ ናቸው የሚል ተናግረው ነበር
- እሱ 2ኛ ላይ የመጣ ጥያቄ ነው የመጀመሪያው ተቀርፆዋል
- እሱ ተቀርፆዋል
- ሌላ
- ቅድም ወሀብያዎች እና ሱፊያዎች ብለዋል አይደል ይሄንን ቃል አልተናገሩም ?
- አዎ
- ምን ማለት ነው ወሀብያ ምንድን ነው ?
- መሐመድ አብዱሉሀብ የሚደግፉ
- የሚደግፉ ነው የሚከተሉ ?
- የእነሱን ኃሳብ የሚደግፉ ናቸው እሱን የሚደግፉት ወሀብያ ነው የሚባሉት በእዚያ ነው ልል የቻልኩት
- እርሶ በሚኖሩበት አካባቢ አሉ አይደል እነዚህ ?
- አሉ
- በርከት ይላሉ ቁጥራቸው ?
- ብዙ ናቸው
- ሶፊያም ብለዋል ሶፊያ ምንድን ነው ?
- ነብይን መንገድ የሚከተሉ ናቸው የሚተከተሉ ተማሪዎች ናቸው የነብይን ትርጉም የሚከተሉ እና የማይጨምሩበት የማያጎድሉ ናቸው ሶፊዬ ነው የሚባሉት እነሱ
- እርሶ ካየትኛው ኖት ?
- ይቆዩ
- ይሄ አግባብነት ያለው ጥያቄ አይደለም እርሶ ከየትኛው ኖት ብሎ የምስክሩን ምን ለማለት ተፈልጎ ነው ይሄ አግባብነት ያለው ጥያቄ አይደለም የተከበረው ፍ/ቤት ከግለሰቡ ግላዊ ሁኔታ ጋር እኛ ያስመሰከርነው ነገር የለም እና በፍፁም አግባብነት ያለው ጥያቄ አይደለም

1530

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ጥያቄ የቀረበው 2 ግሩፕ ሰለሚሰፀ ምናልባት በነፃ ሆኖ ይመስከራል ወይስ ወደ አንድ ወገን አድልቶ የሚለውን ለማሳየት ያህል ከጥላቻ ከምን ከእነዚህ ከተያያዙት ጋር ይገናኛል ወይስ ነፃ ነው የሚለውን ከእዚያ ጋር ለማያያዝ እንጂ የግለሰቡን እምነት እዚህ በጭብጥነት ተይዞም አይደለም ግን ከታአማኒነት ጋር
- ብይን ሰጥተናል ከወሀብያ እና ሶፊያ ከየትኛው ወገን ኖት የሚለው ነገር የምስክሩን ግላዊ ሁኔታ የሚመለከት ነው በዋናም አልተነሳም የሚል መቃወሚያ ቀርቧል በጠበቆች በኩል በጭብጥ አልተያዘም እርግጥ ነው ነገር ግን የምስክሩን ገለልተኝነት ለማጣራት ነው የጠየቅነው የሚለው ምላሽ ሰጥቷል ስለዚህ ጥያቄው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ፍ/ቤቱ አይቶታል ያው በጭብጥ እንዳልተያዘ አከራካሪ አይደለም የምስክሩ የግል ሕይወትን የሚገልፅ ነው የሚለውም /ግልፅ ያልሆነ/ ምስክሩ ኃይማኖቱን መግለፁ ምንም የሚያመጣው ችግር የለም ከየትኛውም ኃይማኖት ሆኖ ነው የመሰከረው የሚለው በምስክሩ ምዘና ላይ ምን ዓይነት ውጤት አለው የሚለውን በኃላ ፍ/ቤቱ የሚያየው ነው አሁን ለተነሳው ግን በጠበቃው በኩል የቀረበው ክርክር ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው ጥያቄው ይቀጥል ተብሏል
- ምስክር እርሶ ቅድም ከገለፀዋቸው ከ2ቱ የትኛው ውስጥ ነው ያሉት የሚከተሉት ?
- እሱ አይደለም ሶሪ 2 የተከፈሉ ሳይሆን የተከፈሉትማ ደጋፊ ምናምን ተብለው ነው አሁን ግልፅ ነው ወሀብያ እና ሱፊያ አለ ከ2ቱ የትኛው ነው እሱ እሱን መገለፅ ይችላሉ ?
- እኛ እምነታችን ሙስሊም ነው ይሄ ደግሞ ድርጊት ነው ሕዝቡን የለየው ነው እንጂ ከሙስሊም ውጪ የሚወጣ ሰው የለም
- ስለዚህ 2ቱም ሙስሊሞች ናቸው ነው ያሉን ?
- አዎ
- እነዚህ መስኪዶች ሲሰሩ የአካባቢውን ሕብረተሰብ በገንዘብ ወይም በጉልበት እርዳታ አድርጓል አላደረገም ?
- አዎ ሕዝቡም የሚደግም ነበረ
- እኮ እርዳታ አድርጓል አላደረገም በጉልበት ወይ በገንዘብ የሚያውቁት አለ ወይ ?
- አዎ ሕዝቡ ተድቷል ለምሳሌ እንጨት በመግዛት በእዚህ በእዚህ መልክ የሚረዱ አሉ ይሄንን አውቃለሁ

1531

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መስኪዶቹ ሲሰሩ ከአካባቢው አስተዳደር አስፈቅደው ቦታ ወስደው ነው የሰሩት ያውቃሉ ይሄንን እርሶ ?
- ብዙ ዓመት ቆይቷል እና ግን ፍቃድ ይኑረው አይኑረው አናውቀውም ቆይቷል ውስጡን አናውቀውም
- መስኪዶቹ ሲሰሩ የኦሮሚያ ክልል መጅሊስ ያውቃል አያውቅም ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ
- እሺ መቃወሚያው
- ምስክሩ አሁን ቀደም ብሎ የተከበሩ ጠበቃ ሲጠይቋቸው መልሰዋል እኔ የማውቀው ነገር የለም ፍቃድ ይኑረው አይኑረው ብለው መልሰዋል እንደገና የኦሮሚያ መጅሊስስ ያውቃል ወይ ብሎ መጠየቅ ሪለደንት ነው ድግግሞሽ ነው እንጂ የተለየ ጥያቄ አይደለም ምላሽ ሰጥተውበታል ቀደም ብለው ምስክሩ
- ድግግሞሽ ነው የሚል ነው ተቃውሞ ?
- ድግግሞሽ ነው ድግግሞሽ ነው ፕሮቫይድድ እኛ ይሄንን ጭብጥም አላስመስከርንም የምናስረዳውም በቃል ሳይሆን በሰነድ ማስረጃ ነው በዋና ጥያቄም ያልተነሳ ነገር ነው
- መልስ ድግግሞሽ ነው
- አይ ድግግሞሽ አይደለም የመጀመሪያው አስተዳደሩ ነው
- የተነሳው አሁን 2 ነገር ነው ድግግሞሽ ነው በዋና ጥያቄ አልተነሳም
- አይደለም ድግግሞሽ አይደለም 2 የተለያዩ ጥያቄዎች ናቸው
- አይ እዚያ ላይ ተመስርታችሁ ያው
- እኮ ድግግሞሽ አይደሉም ነው እያልኩ ያለሁት ዐቃቤ ሕግ አሁን ድግግሞሽ ናቸው መጀመሪያው ላይ የጠየኩት አካባቢው ማለት አስተዳደሩ ቦታ ሰጥቷቸው ነው ወይስ ዝም ብለው ተነስተው ነው እየሰሩ ያሉት ነው ያልኩት እሱን አላውቅም ብለዋል መልሰዋል አሁን የጠየኩት ደግሞ የክስ ቻርጃቸው ላይ ከመጅሊስ እውቅና ውጪ ነው የሚል በግልፅ የተቀመጠ ጭብጥ አላቸው ዐቃቤ ሕግ ከእነሱ ተነስቼ ነው የኦሮሚያ መጅሊስ ይሄንን ያውቅ ነበር ሰ ሰራ መስክዱ አየውቅም የሚል አጭር እና ግልፅ ጥያቄ ነው የጠየኩት ስለዚህ ድግግሞሽም አይደለም የተያዩ ነጥቦች ናቸው /ግልፅ ያልሆነ/

ECHR
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ብይን ሰጥተናል በድጋሚሽ ነው ኦሮዲኣም የሚል ነው ነኛው ያጡ ድግግሞሽ ያሉት መጀመሪያ የአካባቢ የሚመለከተው አስተዳደር ፍቃድ ነበረው ወይ የሚለው ነው እሱ ተመልሷል አሁን ግን የመጅሊሱ ፍቃድ አለው ወይስ የለውም የሚል ነው ስለዚህ የተለያዩ ነገሮች ናቸው ድግግሞሽ አይደሉም ቁዋና ጭብጥ ላይ አልተነሳም በሰነድ ነው የምናስረዳው የሚለው እዚህ ላይ የሚነሳ ነገር አይደለም እሱ አስፈላጊ አይደለም ነገር ግን በዋናው ተነስቷል አልተነሳም የሚለውን ስናየው በዋና ጥያቄ ተነስቷል መስኪድ አስርተዋል 20 መስኪድ በሚል ነው መስኪዱ በፍቃድ ተሰራ አልተሰራ የሚለው ከእዚያ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው ጥያቄ ስለሆነ ጥያቄው ተገቢ ነው ይቀጥል ተብሏል
- ልድገምላቸው ጥያቄውን እነዚህ መስኪዶች ሲሰሩ የኦሮሚያ መጅሊስ ያውቃል አያውቅም የሚያውቁት ከሆነ ?
- እኔ አላውቀውም
- ማወቅ አለማወቁን አላውቅም ነው ?
- እኔ ስለፍቃድ አላውቀውም
- ጨርሻለሁ
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት አቶ አደም በአካባቢው ላይ ገበሬዎች ማዳበሪያ ይወስዳሉ?
- ይወስዳሉ
- እርሶም ይወስዳሉ ?
- አዎ
- ማዳበሪያውን ከወሰዳችሁ በኋላ ስትከፍሉ ወለድ አለው ?
- በግዢ ነው በግዢ ነው ምንገዛው
- በግዢ ቀጥታ ነው የሚገዙት ወይስ በብድር ?
- ብድር አይደለም እዚያ ወልዳ ይመጣል እዚያ ከእዚያ ነው የምንገዛው
- በወልዳ ምንድን ነው ?
- በማህበር እዚያ ይመጣል ከእዚያ በገንዘብ እንገዛለን
- በመስኪዶቹ ላይ ያስተምራሉ ያሏቸው ሰዎች አትውሰዱ ያሉት በወለድ የሚወሰደውን ነው ወይስ በግዢ የሚገዛውን ነው የትኛውን ነው ?

1533

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ክልክል ነው ብለው የሚሉም አሉ ግን ሌሎቹ ከሌላ ቦታ ከበረንዳም ከገበያም ይገዛሉ
- ጥያቄው ያ ክልክል ነው የተባለው ሲያስተምሩ ክልክል ነው ብለው ያስተማሩት በወለድ የሚወሰደውን ነው ወይስ የሚገዛውን ነው ይሄ ነው ጥያቄው ?
- በእዚህ አናምንም ያሉት ሌላ ከውጪ በገንዘባቸው ይገዛሉ
- ጥያቄው ግልፅ ነው ግልፅ ይሁኑ እና የተከለከለ
- ጥያቄዬን ልድገምላቸው የተከበረው ፍ/ቤት
- እስቲ
- /ግልፅ ያልሆነ/ መልስ ጋር አንድ ላይ
- ቆይ እስቲ እኛ በያዝነው ግልፅ እናድርገው እና ጥያቄው የሚለው ብድር አለ ቀጥታ ግዢ አለ ሰዎቹ ሲያስተምሩ የትኛውን ነው አትግዙ እያሉ የሚቀሰቅሱት የትኛውን ነው ጥያቄው
- የተከበረው ፍ/ቤት ግልፅ ላድርገው እና ጥያቄዬን
- ይሄ አይደለም
- አዎ የሚያስተምሩት ሰዎች በግዢ በገንዘባችሁ አትግዙ ነው ወይስ በወለድ አትውሰዱ ነው ሲል የነበረው የትኛው ነው ?
- ምን ለውጥ አለው ያው ለውጥ የለውም ተጥሉ ያው ነው ወይ በጠበቃው ወይ እዚህ በመጣው ከ2 አንዱ መመለስ ይችላሉ ብድር ብቻ ሳይሆን ያው በወለድ የሚወሰደውን ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄው አጭር እና ግልፅ ነው ወይ ፍ/ቤቱ ይድገምልን እና ይመልሱልን ወይ እኛ ደግመን እንጠይቃቸው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አልመለሱም ገንዘባቸው አውጥተው የሚገዙትን ነው ወይስ በወለድ
- በብድር በሉት በቃ በብድር በሉት እና
- በብድር አትውሰዱ ብሏል ነው
- እኮ እሱን አስተካክሉ በእዚያ መንገድ እስቲ በብድር ነው አትግዙ ያሉት በምንድን ነው ወይስ በካሽም አትግዙ ብለዋል ወይ ?
- በገንዘብም የሚገዛም አለ
- አልተመለሰም
- /ግልፅ ያልሆነ/ የመለሱት ሌላ ስለሆነ

1534

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሌላ ነው የሚመልሱት እኮ
- ትርጉሙ እኮ ትክክል ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት
- የጥያቄው ትርጉም ትክክል ነው ችግር የለውም ምላሻቸው ግን የተጠየቁትን አልመለሱም እንጂ ጥያቄው ትክክል
- መቃወሚያ አለን እኛ ግን ማለት በየጣልቃ ከምንገባ ብለን ነው ሲጀምርም ጥያቄው ችግር ስለነበረበት ነው ምስክሩ አሁን እንዲህ እየተቸገሩ ያሉት ችግሩ ምንድን ነው ምስክሩ የመሰከሩት ቀደም ብለው
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ ብለው ፍ/ቤቱ ይፍቀድላቸው እና ወይ መቃወሚያ
- ፈቅደንላቸው ነው
- ተፈቅዶልናል እኮ በገንዘብ ነው የምንገዛው ቀጥታ ሄደን ብለው መስክረዋል አሁን የተከበሩ ጠበቃ የራሳቸው 2 ቨርችዉን አመጡ በብድር እና በገንዘብ የሚል ምስክሩ ስለማያውቁ አሁን ደጋግመው በገንዘብ በገንዘብ የሚሉት ለእዚያ ነው እና ጥያቄውም አግባብነት ያለው ስላልነበረ ነው ከተመሰከረ ውጪ ስለተጠየቀ ነው
- ኣይ ኣግባብነት የለውም ያሉት ለምንድን ነው ?
- ምስክሩ ከመሰከሩት ውጪ ነው ከተመሰከረው ቃል ውጪ ነው እና ያላሉትን ስለሆነ አሁን ተመርተው እየተጠየቁ ያሉት ለእዚያ ነው መመለስም የተቸገሩት
- ምላሽ ?
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ መሰረታዊ ጥያቄ ነው ብለን እናስባለን በእኛ በኩል እንግዲህ በአስተምሮቱ አስግዙ የሚባል ዓይነት ሊኖር ይችላል ብለን ስለምናስብ የትኛው ነው የሚለውን አንጥረው እንዲለዩልን እና ለፍ/ቤቱ ግንዛቤ እንዲሰጡ ነው እና አዲስ ነገር ፈጥረን ያመጣነው ጥያቄም አይደለም ግብይት አለ በብድር ነው ወይስ በካሽ ነው አትግዙ የተባለው ወለዱን ነው የትኛውን ነው የተከለከለው የሚለውን ይሄንን ምስክሩም አልገባኝም ብለው እንትን አላሉም ሲመልሱ እያዞሩ ይመልሱታል እንጂ አልገባኝም ብለው አልተናገሩም የተከበረው ፍ/ቤት እንዲመልሱ ይደረግልኝ
- ብይን ተሰጥቷል ጥያቄው ተገቢነት አለው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነው ያየነው በዋና ጥያቄ ላይ ሲመሰክሩ ምስክሩ ማዳበሪያ አትጠቀሙ አትውሰዱ ተብሎ ሲያስተምሩ ነበር የሚል ነገር አለ ሌሎቹ እንዳለ ሆነው አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ የተነሳው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ማዳበሪያ አትውሰዱ የተባለው ወለድ ያለው ማዳበሪያ ነው ወይስ በካሽ የሚገዛውን ነው የሚል ነው ይሄ ጥያቄ ተገቢነት አለው የለውም የሚለውን ስናየው ይሄ ጥያቄ ተገቢነት የሚመዘነው ነኛ ከጭብጡ በክሱ ከተያዘው ጭብጥ ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚገናኝ መሆኑ ነው 2ኛ በመስቀለኛ የሚታይ ከሆነ ከዋናው ከተነሳው ጥያቄ ጋር ተያይዞ ነው የማ,ታየው እና በ2ቱም ስናየው ጥየቄው ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል ስለዚህ ጥያቄው መጠቀል አለበት ነገር ግን ምስክሩ እየተቸገሩ ስለሆነ ምናልባት አሁን የተነሳውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ግልፅ አድርጎላቸው ቢጠይቅ ይሻላል የሚል ላይ ደርሰናል እና ከእዚሁ ይቅረብላቸው

- እስቲ መጀመሪያ በብድር እና በቀጥታ ግዢ በደንብ ያውቃሉ እርሶ ?
- በእኛ አካባቢ በግዢ ነው
- እንጂ ይሄ በብድር የሚሰጥ አያውቁም ?
- ብድር ቀርቷል በፊት ይሰጥ ነበር አሁን በቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በግዢ ነው የምፈፅመው
- አሁን ግልፅ ነው ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ያው ምስክሩ ሲመሰክሩ ብድር ይሰጥ ነበር ቀርቷል ብለዋል ያንን ሲወስዱ የነበረውን ብድር ነው በብድር አትውሰዱ ሲሏቸው የነበረው ወይስ
- ያው ድሮ ይሰጥ ነበር አሁን ቀርቷል በእዚያ አሁን በሚመሰክሩበት ወቅት ቀርቷል ነው ይሄ ነው እኮ እንትኑ ወይ ቅሰቀሳው በተደረገበት ጊዜ ብድር ነበር አልነበረም ነው ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሰጥ ነበር አሁን ዳዋ ያደርጉ ነበር ያሏቸው ሰዎች እንግዲህ መቼ ጀምሮ እንደሆነ ሲመሰክሩ ነበር እና በመቼ ወቅት ነው ይሄ ነገር ሲሉ የነበረው ይሄንን በብድር ነው አይደለም ወይስ ግዢ አሁን ግዢ ከተጀመረበት በኋላ ነው ሲሉ የነበረው ይሄንን እንዲለዩልን ነው ?
- እሺ እስቲ ጠበቃ አሁን ነው ምስክር አሁን ያው ማዳበሪያ አትውሰዱ ብለው ሲቀሰቅሱ ነበር አሁን ግን አሁን ማዳበሪያ ብድር ቀርቷል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግዢ ብቻ ነው ብለዋል እና ቅስቀሳው ማዳበሪያ አትውሰዱ የሚለው ቅስቀሳ ያ ብድሩ ከቆመ በኋላ ነው ወይስ በብድር ማዳበሪያ መውሰዱ ባለ ጊዜ ነው ቅስቀሳው ?
- በማህበር ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ነው እና ማዳበሪያ መውሰድ ሀራም ነው ያሉት
- አመሰግናለሁ

1536

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምናልባት የተከበረው ፍ/ቤት አሁንም የተጠየው እና መልስ
- ይሄንን ጥያቄ እለፉት
- ማለት የፈለኩት ጥያቄው እኔ በትክክል መተርጎሙንም
- ግልፅ ነው እኛም እየሰማን ነው
- ከችሎቱ በቀጥታ ጥያቄው በኦሮምኛ ቢነገራቸው እና እሳቸው እንዲመልሱት ቢደረግ
- ግልፅ ነው ትርጉሙንም እየተከታተልን ነው ትርጉሙ ጋር ምንም ችግር የለውም መልሱን ሊያሰጥ የሚችል ትርጉም ነው እሱ ችግር የለውም ይሄንን ጥያቄ እለፉት እና ሌላ
- ማዳበሪያ መውሰድ ሀራም ነው ሲሉ የነበሩት ከመቼ ጀምሮ ነው ?
- 6/7 ዓመት ይሆናል ለምን ማዳበሪያ አትወስዱም ተብሎ ሲጠየቁ አይበቃም ከማህበር ነው የሚወጣ ነው የተባለው ብለው ነው ሲከለክሉ የነበረው
- ቅድም እኔም እወስዳለሁ የአካባቢው ገበሬም ይወስዳል ብለዋል ?
- አዎ
- የሱፊ አስተምሮ የሚከተሉ ገበሬዎች ይወስዳሉ ማዳበሪያ ?
- ይወስዳሉ
- የወሀብያ አስተምሮ የሚከተሉት ይወስዳሉ ማዳበሪያ ?
- እኔ ተከታትዬ አላየሁም ይወስዱ አይወስዱ ግን አስተምሯል
- ግን ማዳበሪያ ይጠቀማሉ ብለዋል ስለዚህ ይሄንን ጥያቄ ትቼዋለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም መግደል ይቻላል ብለው ሲያስተምሩ ነበር ጅሀድ ማድረግ ይቻላል ብለዋል ብለዋል በሙስሊሞች ላይ ነው ጅሀድ ይቻላል ሲሉ የነበረው ?
- አዎ በሱፊዬዎች ላይ እና በቀድሞ ሼኪዎች ላይ ጅሀድ ማድረግ ይቻላል ብለው ነው አስተማሪዎች ያስተማሩት
- ዳዋ የሚያስተምሩ ሰዎች ትምህርት የአካባቢውን ሰው እንዲቃረን አደረገ ብለዋል በኃሳብ ነው እንዲቃረን ያደረጉ በኃሳብ ነው ልዩነት የተፈጠረው በአስተምሮ በኃሳብ ማለት ነው ?
- ዳዋ የሚያስተምሩ
- አዎ ቅድም ሲመስክሩ በሀጂ አብዱራህማን የተቀጠሩ ሰዎች የሚያስተምሩት ትምህርት የአካባቢውን ሰው በ 2 ከፈለ ብለው መስክረዋል እና በኃሳብ እና በአስተምሮ ነው እንዲለያይ ያደረገው ወይ ብለው ጠይቁ ?

1537

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ ጥያቄውን ግልፅ ያድርጉ ለእናንም ግልፅ አይደለም
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት የ 2 የአካባቢውን ሰው 2 የከፈለ ዓይነት ነገር እንዳለ ምስክሩ መስክረዋል እና ከ 2 የተከፈለው በኃሳብ ነው ወይ በአስተምሮ ሱፊ እና ወሀብይ የሚል ነገር ምስክሩ ሲመሰክሩ ነበር እና በእዚህ መንገድ የተከፈለው በአስተምሮ እና በአመለካከት በአስተሳሰብ ነው ወይ የሚል ነው ጥያቄአችን በአመለካከት እና በአስተሳሰብ ነው ወይ የአካባቢው ሰው ለ 2 የተከፈለው ?
- ጥያቄው ወይ በምን ምክንያት ነው ቢባል ይሻላል እሱን እሳቸው ይለዩት እስቲ አመለካከት ምናምን የሚለውን እሳቸው አሁን በትክክል ያውቁታል ?
- የተከበረው ፍ/ቤት መሪ ጥያቄ ይቻላል መስቀለኛ
- ይቻላል መሪ ጥያቄ ሳይሆን መሪ ጥያቄ አትጠይቁ ማለት አይደለም ወይ በሚገባቸው ለምሳሌ አስተሳሰብ አመለካከት የሚሉትን እነሱ አሁን እንዴት ነው ይሄንን እኮ በጣም ትንሽ እንትን ያለ ሰው ነው
- እሺ የአካባቢው ሰው ከ 2 ተከፈለ ብለዋል ብለዋል በዳዋ ምክንያት ከ 2 የተከፈለው በአቂዳ ወይም በእምነት ነው ?
- እነሱ የሰጡማረት ትምህርት ነው ሕዝቡን የለየጡ
- እኮ በምን ሁኔታ ነው የለየው እንዴት ነው የለየው በእምነታቸው ነው ለ 2 የከፈላቸው እንዴት ነው ?
- በግልፅ ነው 2 ሊከፍል የቻለው መውሊድ የሚሰሩት ቃሬራዎች ናቸው በሚል ነው ሙስሊም አይደለም ነው ያሉት
- ይሄ ማለት በአመለካከት ተለያዩ ማለት ነው ወይ ?
- ክልክል ነው ብለው ነው የመከሩት
- ሀጂ አብዱራማን ያሰሩት መስኪድ ሲሰራ የአካባቢው ሰው በጉልበትም በገንዘብም አስተዋፆ ሲያደርግ ነበር ብለዋል የአካባቢው ሰው እዚያ መስኪድ ውስጥ ይሰግዳል ?
- ይሰግዳል
- የሱፊ እና ወሀብይ ያሏቸው ሰዎች ለእነዚህ መስኪድ ይሰግዳል ይሰግዳሉ አይሰግዱም ?
- መስገድ አይከለክሉም
- ሰላትን አይከለክልም

1538

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሉ ንደ ላይ ነው በአንድ መስኪድ በአንዱ ላይ ይሰግዳሉ
- አይከለክልም ብለው መልሰዋል ያው ቅጥር ላይ እንጂ
- ቅድም ሲመሰክሩ መግደል ይቻላል ጅሀድ ነው ሲሉ ነበር ብለዋል በአካባቢዎት ላይ የተገደለ ሰው አለ እንዴ ?
- መጀመሪያ እንደገለፅኩት የሞተ ሰው የለም
- ጨርሻለሁ
- አቶ አደም ቅድም ገንዘብ በአረብ ሀገር ይገባል ብለው ነበረ ከየትኛው የአረብ ሀገር እንደሚገባ ያውቃሉ ?
- ከየትኛው አረብ ሀገር
- አላውቅም ከአረብ ጋር መጥቶ ቀበሌ ውስጥ ሲዘዋወሩ አየን እንጂ ከየትኛው አረብ እንደመጡ አላውቅም
- ቅድም ሱሪ ማሳጠር ፂም ያላሳደገ ወለድ ሀራም ነው እያለ አስተምረዋል ብለዋል ዳኢዎቹ እነዚህ ዳኢዎች
- መቃወሚያ አለ
- ወለድ አላሉም ይስተካከል
- ወለድ ይቅር እና
- ላለመድገም አላሉም ወለድ የሚባል አላነሱም ስለዚህ ይሄንን አስተካክላችሁ ጠይቁ
- እሺ ሱሪ ማሳጠር ፂም ያሉት ነገር ከእስልምና ውጪ ነው ለቅሶ መያዝ ብለው ነበር እና እነዚህ ሰዎች እነዚህ ዳኢዎች ይሄንን ነገር ሲያስተምሩ ቁርአን እና ሀዲስ ይከለክላል ነው የሚሉት ወይስ የእኛ አመለካከት ነው እያሉ ነው የሚያስተምሩት ቁርአን እና ሀዲስ ይጠቅሳሉ ነው ይሄንን ሲያስተምሩ በእዚህ መልኩ ክልክል ነው እንዲህ አታድርጉ ብለው ቁርአን ነው ሀዲስ ነው ይላሉ ወይስ የራሳቸውን ነው የሚናገሩት ?
- ምን
- ቁርአን እና ሀዲስ ይጠቅሳሉ በእዚህ መልኩ ቁርአን ከልክሏል ሀዲስ ከልክሏል ነው የሚሉት ወይስ ?
- ክልክል ነው ሀራም ነው ብለው ነው የሚያስተምሩት ምን ከየትኛው ላይ አግኝተው እንዳሉ ለማለት እንደቻሉ አላውቅም ግን እንደዚያ ብለው አስተምረዋል

1539

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሼህ አብዱራህማን እነዚህን መስኪዶች አሰሩ ዳኢዎችንም ቀጠሩ ብለው ነበረ ለዳኢዎቹ በእዚህ መልኩ አስተምሩ ቅድም እርሶ የተናገሩትን ነገር አስተምሩ ብለው ትዕዛዝ ሲሰጡ አይተዋል ሼህ አብዱራህማን ለአስተማሪዎቹ በእዚህ መልክ አስተምሩ ብሎ ትዕዛዝ ሲሰጡ አይተዋል እርሶ በትክክል አይተዋል አላዩም ?
- እንደዚያ ብለው ትዕዛዝ ሲሰጧቸው እኔ አላየሁም
- ሺህ አብዱራህማን ያሰሩትን 20ውንም መስኪድ ያውቃሉ እርሶ ?
- አውቃለሁ
- ሺህ አብዱራህማን እነዚህን መስኪዶች ያሰሩት ለማን ነው ?
- ውስጡ እንዲሰግዱ ለሙስሊም ሕብረተሰብ
- ጨረሳችሁ የተለየ ካልሆነ ማንኛውንም ድጋሚ አናስተናግድም ከእዚህ በኋላ በጣም ረጅም ጊዜ ወስዳችዋል የተለየ ብቻ ከሆነ
- የቀድሞቹ ኢማሞች /ግልፅ ያልሆነ/ ካፊሮች ናቸው እነዚህን በተመለከተ ጅህድ ማወጅ መግደልም ይቻላል የሚሉ ምስክርነት ሰጥተዋል መግደልም ይቻላል ብለዋል ይሄንን ማን ሲል ነው የሰሙት የት ነው የሰሙት ማን ሲል ነው የሰሙት እርሶ ሰምተዋል ?
- እነ ሀጂ ሁሴን ሰብሮ የሚባሉት እንደዚያ ብለው ነው ያስተማሩት ፋጂ ወልቂጤ የሚባል አካባቢ ላይ እዚያ ያስተምሩ ነበረ
- ይሄም ተነስቷል
- ይሄ ታሳብ ሼህ አብዱራህማን ስለመሆኑ የሚያውቁት ነገር የለም አይደለም ?
- ቆዩ ቆዩ አስተካክለዋል ወይስ ይቀጥላሉ ጥያቄውን ወደ ግል አስተያየት እየመጡ ነው እሱን ጠብቀው
- በቃ አልፈዋለሁ ጥያቄዬውን
- ቅድም በእነዚህ መስኪዶች ውስጥ በሚሰጠው ትምህርት ምክንያት በእነዚህ መስኪዶች ውስጥ በሚሰጠው ትምህርት ምክንያት ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ለ2 ተከፍሏል ብለዋል በእዚህ ምክንያት ምንም ዓይነት ችግር አልደረሰም አይደል ምንም ዓይነት ግጭት አልደረሰም
- ተጠይቋል ተጠይቆ ተመልሷል ያልተደገመ ብቻ ነው የተባለው

1540

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ሀጂ አብዱራህማን ሼህ አብዱራህማንን ለ10 ዓመት አውቃቸዋለሁ ብለዋል ከመቼ ጀምሮ ነው የምታውቃቸው ?
- ከ 95 ዓ.ም ጀምሮ አውቃለሁ
- እነዚህ 20 መስኪዶች ተሸርተዋል ያልካቸው ከመቼ ጀምሮ ነው የተሰሩት ?
- በ2000 ዓ.ም የተሰራም አለ ከእዚያ ወዲህም አዲስ እየተሰራ ያለም አለ አንድ ዓመት አይደለም በየዓመቱ በየዓመቱ ነው የሚሰራው ከ 2000 ዓ.ም በፊትም የተሰራ አለ
- ለመጀመሪያ ጊዜ ሀጂ አብዱራህማን መቼ ነው ያሰሩት የመጀመሪያውን መስኪድ ያሰሩት መቼ ነው ?
- 96/97 እያስፋፉ መስራት ጀመሩ
- የመጀመሪያ የሰሩት መቼ ነው ?
- እኛ አካባቢ ግን የመጡት በ2000 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ነው
- አሁን ጥያቄዬ ሼህ አብዱራህማን የመጀመሪያውን መስኪድ ያሰሩት መቼ ነው ነው ?
- በእዚህ ዓመት ተሰሩ በእዚህ ዓመት ተሰሩ ለማለት አላውቀውም ለማለት አልችልም ግን ሻላ ውስጥ የተሰሩት መስኪዶች ናቸው የተሰሩት
- አንተ ሳታውቃቸው በፊት የተሰሩ መስኪዶች አሉ ወይ ?
- ጠበቃ ግልፅ /ግልፅ ያልሆነ/ ይለፉት እና ሌላ
- አሁን እኮ እሳቸውን የሚያውቀው ከ 95 እሳቸውን የማውቃቸው ብሎ 2000
- ግልፅ ነው ምስክሩ ከመሰከረው ፍ/ቤቱ ማየት ይችላሉ
- እሺ ሱፊ እና ወሀብይ ተብለው ይከፋፈላል ብለዋል ቅድም ወሀብይ የሚለውን አስተምሮ የሚከተሉት የአካባቢው ገበሬዎች እና ነዋሪዎች ናቸው አይደል ?
- ማንን የሚከተል ወሀብያ
- ይሄ ተጠይቋል ይለፉ ይሄንን ጥያቄ
- ቅድም ስታስተምር ጅሀድ ብለው አስተምረዋል ብለሀል ጅሀድ ብሎ ሲያስተምር የሰማኸው ማን ነው ?
- ይሄም በተመሳሳይ
- ማን ነው ጅሀድ ብሎ ያስተማረው የሚለውን አልመለሰም ጅሀድ ስለመባሉ ብቻ ነው
- ተናግሯል

1541

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አልተናገረም የተከበረው ፍ/ቤት ወይ ይሰማልን አልተናገረም
- እስቲ-እዚህ እኮ ተጠይቆ ተጠይቆ ማን ነው ያስተማረ የሚል ጥያቄ ተጠይቋል እስቲ ሩል መቀበል እኮ ግዴታ ያለብህ ይመስለኛል እና እስቲ ስርዓት አድርጉ እስቲ
- ጅሀድ ማለት ምን ማለት ነው እሺ ?
- እስላም የልሆነውን ሰው ቢገድሉትም ጥፋት የለውም ነው የማሉት
- አይደለም ጅሀድ ማለት ምን ማለት ነው ጥያቄው ?
- በአጭሩ ስንመልስ ጥል ማለት ነው
- ጥል ማለት ብቻ ነው ?
- ውጊያ ማለት ነው ጥል ማለት
- ቅድም ግደሉ ብለሀል ብሎ ሲናገር ሰምቼአለሁ ያልከው ጅሀድ ብለው ስላስተማሩ ነው ?
- ጠበቃ እስቲ ቆዩ እስቲ ይሄ አረዲ አትድገሙ የማይደገም ጥያቄ ብቻ ነው የምናስተናግደው ብለን ያልነው እየደገሙ ነው ሙሉ በሙሉ ለምን ግደሉ እንደተባለ ቅድም መስክረዋል እሱ ምንድን ነው በኋላ የሚታይ ነው እና ያልተደገመ ካለ እሱን ብቻ ምረጡ
- ምናልባት ጥያቄዬን ላስረዳ እና ፍ/ቤቱ ከተቀበለው ይቀጥል
- ግልፅ ነው ጉቡቶናል
- ጥያቄዬን አላስረዳሁም የተከበረው ፍ/ቤት ላስረዳ ዕድሉ ይሰጠኝ
- /ግልፅ ያልሆነ/
- እኔ እሳቸው ግደሉ ብለዋል የሚለውን በእኛ ጠበቆች በሁሉም ተነስቶ መጠየቁን አውቃለሁ ሁሉም አንስተው ጠይቀዋል ግደሉ የሚለውን ቃል እየተጠቀሙ ነው የጠየቁት እኔ አሁን ጅሀድ ምንድን ነው ብዬ ስጠይቃቸው አሁን የመለሱትን መልሰዋል ስለዚህ ጅሀድ የሚለው ቃል ስለተናገሩ ነው ግደሉ ብለዋል ያልከው ወይስ ግደሉ የሚለውን ቃል ቃል በቃል ሰምተህል የሚለውን ነገር ለማጣራት ነው ጥያቄው
- መልሱ
- ጅሀድ ብለው ስለተናገሩ ወይ ነው ግደሉ ብለዋል ያልከው የሚለው ?
- በቃል ነው
- በአካባቢው ሱፊ እና ወሀቢያዎች የሚባሉ አሉ ብለሀል የት አካባቢ ነው ሱፊ ወሀቢ የሚባሉት ሰዎች መኖራቸውን አንተ በትክክል የምታውቀው ስለአካባቢው ነዋሪ ነህ ?

1542

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እስቲ ቆዩ ቆዩ እስቲ ይሄ እኮ ቅድም ይለፍ ተብሏል እኮ
- አካባቢው አልተመሰከረም እስካሁን ሲመሰከር መስኪዶቹ ስለተሰሩበት አካባቢ ብቻ ነው
- ይሄ ይለፍ ተብሏል ሌላ ጥያቄ ካለ ቀጥሉ
- እርሶ በሚያውቁት አካባቢዎች ላይ የሱፊ የወሀብይም ትምህርት የሚሰጥባቸው መስኪዶች አሉ አይደል ?
- ትምህርት የሚሰጠው ወሀብዮች በሚባሉት ነው ቦታ ይዘው የሚሰጡት እነሱ ናቸው በእዚህ ነው የማውቀው
- ሱፊ የሚባሉት የሚሰግዱበት መስኪድ የላቸውም ?
- የተለየ መስኪድ የላቸውም
- ሁሉም አንድ ላይ ነው የሚሰግዱት ማለት ነው ?
- አዎ
- የወሀብዮች ትምህርት ትክክል አይደለም ብለው የሚያስተምሩ የሱፊ ዳዋዎች የሉም እንዴ አስተማሪዎች የሉም?
- የሱፊ
- ሰምተውኛል ከሰሙ ወይ ይመልሱት ?
- ተቃውሞ አለን የተከበረው ፍ/ቤት ምንድን ነው እኚህ ምስክር እስታስቲክ ዳታ አልያዙም ማን የወሀብያ የሱፊ ስንት ብዛት የት እንደሚያስተምሩ ይሄንን ሁሉ የመግለፅ ግዴታ የለባቸውም የሚያውቁትን በእውቀታቸው ቅድም እያንዳንዱን በዝርዝር ገልፀዋል መደጋገም ካልሆነ በስተቀር እስካሁን እየሰማን ያለነው ስለዚህ ይሄ ጥያቄአቸው እንዲታለፍ በትህትና እጠይቃለሁ
- ምላሽ
- የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ የሚያውቁትን የመመስከር ግዴታ አለባቸው ሕጉ ያንን ነው የሚለው ሕገ መንግስታችንም ያለው ስለዚህ የመመስከር ግዴታ አለባቸው የጠየኩት ሱፊ እና ወሀብይ የሚለውን ነገር ለችሎቱ ያስረዱት እሳቸው ናቸው ስለሱፊ እና ስለወሀብይ ነው ያስረዱት አሁ አሁን ስለወሀብይ ዳዋዎቹ እንዴት እንደሚያስተምሩ ቅድም [illegible] የሱፊ ደግሞ የሚባሉት ዳዋዎች እንዴት እንደሚያስተምሩ ነው የጠየኳቸው 2ቱም ስላሉ 2ቱም እንዴት እንደሚያስተምሩ

1543

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ገሙ 2 ገቢ ነሙ የተጠየቀሙ ያሙ ሚዛራሪያሙን በሚራ ዋጎ የቀረበሙን አንዳለ ወሲደን ማለት ነው ላለመድገም አሁን የተጠየቀው ጥያቄ ስለወሀብይ የሚያስተምር ነበረ ስለ ሱፊስ የሚያስተምር አካል ነበር ወይ በሚል ተስተካክሎ ጥያቄው በእዚህ የሚያውቁ ከሆነ ይሄንን ይመልሱ ? አይደለም ስለሱፊ ነው የሚያብራሩት ?
- አዎ ስለሱፊ ነው
- አይደለም ሱፊ የሚያስተምር ሰው ነበረ አልነበረም ነው ስለሱፊ የሚያስተምር ብቻ ልክ እንደ ወሀብይ ማለት ነው ?
- አዎ እንደወሀብይ የሚመክር አለ
- ምንድን ነውያሉት ?
- እንደ ወሀብይ የሚመክር አለ ነው ያለው
- ስለ ሱፊ ቆይ እስቲ እሷን ስለሱፊ የሚያስተምር አለ ነው ወይስ ወሀብይ አለ ነው ስለሱፊ የሚያስተምር አለ ?
- አለ
- የአካባቢው ሕብረተሰብ በ2ቱም ከሚሰጠው ትምህርት ያመነበትን ነው የሚከተለው ሊይደል ?
- እስቲ ቆይ አሁን ከኃይማኖት በጣም እየወጣችሁ ብትሄዱ ጥሩ ነው ይሄ ብቻ ሆነ ጠቅላላ በቃ አሁን እኛ ግልፅ ነው ምስክሩ ካለው አሁን ወዴት እንትን ሊል እንደሚችል ግልፅ ነው ስለዚህ በጣም ዲቴል ወደ እዚያ የምንሄድ ከሆነ ከምስክሩ አቅም በላይ ሊሆን ስለሚችል ማለት ነው
- የአካባቢው ሕብረተሰብ ያመነበትን ነው የሚከተለው አይደለም ወይ የምትለዋን ጥያቄ ካልተቀበለኝ ፍ/ቤቱ ልተወው ግን ከክሱም ጋር ተመሳሳይ ነገር ስላለው የማስገደድ ነገር መኖር አለመኖሩን ለማሳየት ነው ሰው በነፃነት ያመነበትን /ግልፅ ያልሆነ/
- ልክ ነው አሁን ቅድም እኮ ሲያስረዱ ወደ እዚያ የሚከተልም እለ ወደ እዚህም የሚከተል አለ
- ፍ/ቤቱ በእሱ ካተረዳው ጥሩ እሺ ጠርሰናል
- ዐቃቤ ሕግ ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ

1544

ECHN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከሰሰበረው ፍ/ቤት የሚፈቅድልኝ ከሆነ ታሳቤን ልግለፅ እና መጠየቅ ከፈቀደልኝ ከእዚያ በኋላ እጠይቃለሁ ታሳቤን ልግለፅ እና በቀረበው ክስ ውስጥ 27ኛ ተከሣሽ እና 28ኛ ተከሣሽ ተያይዞ የተገለፀ ነገር አለ ምስክሩ አሁን 27ኛ ተከሣሽ እርዳታ የተገኑቡ መስኪዶች መኖራቸውን ገልፀዋል ከእዚህ በፊትም በመቃወሚያ አንስተን ነበር 28ኛ ተከሣሽ የተገለፀባት ግንባታ አለ የት እንደሆነ እስፔስፊክ ቦታው ይገለፅ የሚል የታለፈ አለ ኦሮሚያ ክልል ነው የሚለው ምስክሩም የገለፁት አሁን 2 የኦሮሚያ ክልል ወረዳዎችን ገልፀዋል ከተከሣሽ ግንቦታ ጋር ይሄ የገለፁዋቸው ወረዳዎች የሚገናኝ መሆን አለመሆኑን አያይዤ ልጀምር እና ይያያዛል የሚሉ ከሆነ ፈርዘር መስቀለኛ ጥያቄዎቼን አቀርባለሁ አይያያዝም የሚሉ ከሆነ ኤክስክሉድ አድርጌ
- ጥያቄው ማለት ተከሣሽዋን አንስተዋል እንዴ ተከሣሽዋን አንስተው የመስከሩት ነገርአ ለ ?
- 27ኛ ተከሣሽን አንስተው መስክረዋል
- እኮ ስለ 27ኛ ተከሣሽ ነው እስካሁን ሲመስክሩ የቆየው
- 28ኛ ተከሣሽን ስም አልጠሩም ያ በእርግጠኝነት አልጠሩም 27ኛ ተከሣሽ በሰጡት እርዳታ የተሰሩ መስኪዶች መኖራቸውን ገልፀዋል ምስክሩ 27ኛ ተከሣሽ በሰጡት እርዳታ 28ኛ ተከሣሽ መስኪድ መገንባታቸውን የሚገልፅ የክሱ አካል አለ እሳቸው በገለፁዋቸው ወረዳዎች ውስጥ ያለ ግንባታ ይሁን አይሁን ከክሱም ማወቅ አይቻልም ከምስክሩም ማወቅ አይቻልም ልናውቅ የምንችልበት ምንም መንገድ የለንም አሁን ጠይቀን አረጋግጠን ካላለፍን በስተቀር
- እስቲ ምናልባት አሁን በእሳቸው ላይ ያለው ነገር የተመሰከረ ነገር የለም እስካሁን ድረስ
- ፍ/ቤቱ በእዚህ ከተረዳው አልፈዋለሁ
- እኛ በእዚህ ነው የምንረዳው አሁን ምንድን ነው ስለእሳቸው የሚመጣ ምስክር ካለ እዚያ ላይ ይጠይቃሉ የማይመጣ ካለ ደግሞ ተመስክሮባቸዋል ብሎ ፍ/ቤቱ ጎትቶ በእዚህ የሚያስገባበት ምንም ምክንያት የለውም
- ድጋሚ ጥያቄ ካላችሁ
- አንድ ሁለት ጥያቄ ምስክር ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ኢማሞቹን ከሼህ አብዱራህማን ጋር የቅጥር ውል ሲፈራረሙ አላየሁም ብለዋል ?
- አዎ

1545

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተቀጣሪዎቹን አግኝተው አናግረዋቸው ያውቃሉ እርሶ ?
- -አዎ
- ማን ቀጠረን ይላሉ ?
- ሀጂ አብዱራህማን ነው ያሉት
- ደሞዝ ማን ይከፍለናል ይላሉ ?
- እሳቸው ናቸው የሚከፍሉን አሉ
- ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ወሀብይ ስለወሀብይ የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ ስለሱፊ የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ ብለዋል ስለሱፊ የሚያስተምሩ ሰዎች ወሀብዮችን ግደሉ ይላሉ አይሉም ?
- ግደሉ አይልም
- ድጋሚ አበቃን
- ጥያቄ ሼህ ሀጂ አብዱራህማን ቆመው ቅድም የሚሉትን ነገር ሲያስተምሩ የያዩበት ጊዜ አለ?
- እሳቸው ሲያስተምሩ አላየሁም
- ፀ ተቡል ያነሳትዋል አንዴ ዎላ ሀልቱ ለመመለስ

ECLN

1546

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከሰዓት በኋላ ችሎቱ ከቆምንበት እንቀጥላለን ስለዚህ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ከእዚያ በፊት ምስክሩ እስኪመጣ የቀረ ሰው የተጨመረ ዐቃቤ ሕግም ጠበቃም ሊኖር ስለሚችል እና ይሄ ደግሞ ክርክሩን ለመምራት እና ለመመዝገብ የሚዝገቡ አካል እንዲሆን አስፈላጊ ስለሆነ ያው ዳኞቹ ቅድም ጠዋትም የነበሩት 3ቱም አሉ

ዳኞች፡- አሰራት ተልዕቁ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ ኦሮ

ከሣሽ፡ የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ሰማችሁን አሰመዝግቡ ብርሃኑ ወንድማኝ ቴዎድሮስ ጌታቸው ቀርበናል

ጠበቆች፡-ጠበቃ ሀሰን ሁሴን፣ መሐመድ አብደላ፣ ምላልኝ መለሰ፣ ባህሩ መካንጋ ፣ አዲስ መሐመድ፣ ሀሊማ ሰይድ እና ዳዊት ኒጋሽ እና /ግልፅ ያልሆነ/ የ 28ኛ ተከሣሽ ጠበቃ አህመድ ጀማል

- ከተከሣሾች ከጠዋቱ የቀረ ሰው አለ እንደጠዋቱ ነው 29ኛ ብቻ ነው እሺ የቀረው ዐቃቤ ሕግ ምስክር ቃለ መህላ ይፈፅሙ
- በእውነት ለመመስከር በአላህ ስም ምያለሁ
- ምስክር ያው ለምስክርነት ነው የመጡት አይደል እርሶ አይችሉም
- ይሰማኛል
- ይሰማሉ አይደል ?
- አይ ለምስክር ነው የመጣሁት
- ከእዚህ ቀደም ለሌሎች ምስክሮች እንደተባለው ምናልባት የቋንቋ ችግር ካለበት አስተርጓሚ ይመደብሎታል ችግር የለውም ?

1547

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ችግር የለውም
- ይችላሉ ቋንቋውን ?
- ቋንቋውን በደንብ እችላለሁ
- ተሪ ጋግተው ያዳምጡ እና አሁን ለሌሎችም ምስክር እንደተደረገው ለምስክሩ ደህንነት ተብሎ ምስክር እንዲገልፅ የሚጠየቀው የራሱን ስም ብቻ ነው የአባቱ ስም እና ሌሎቹን አንጠይቀውም እንዲገልፅ አይጠበቅም ስለዚህ ከእዚያው እንጀምር እና የእርሶ ስም ማን ነው እስቲ የራስዎን ?
- አብዶ
- ዐቃቤ ሕግ ስንትኛ ላይ የተጠቀሱ ናቸው ?
- በ2ኛ
- ስንተኛ ነው ያሉት ይቅርታ 72 ? አቶ አብዶ ዛሬ የለምስክርነት ነው የመጡት እና እስቲ ተከሣሾች አንዴ ተነሱ እርሶ ላይ ቁጭ በሉ እርሶ ቁጭ ብለው አሁን ካሉት እዚህ ካሉት ተከሣሾች የሚያውቁት ማን ላይ ለመመስከር እንደመጡ እሱን ይንገሩን እና ማን ላይ ነው ለመመስከር የመጡጥ ለሁ ? ይኔ ሁሉ ሰው ተነስቷል እና ማን ላይ ?
- በእውነት እኔ ተከሣሾችን በእዚያ በሐምሌ 7 የተደረገ ነው እንጂ
- ቆይ ቆይ ዝርዝሩን ሳይሆን ተከሣሾች ላይ ሊመስክሩ ነው የመጡት አይደል ?
- አዎ ተከሣሾች ለመመስከር ነው
- ማን ማን ላይ እንደሚመስክሩስ እስቲ በስም ይንገሩን መጀመሪያ ?
- እኔ የምመስክረው ሀምሌ 7 ቀን ከቀኑ 4 ሰዓት
- ቆዩ ቆዩ አሁን ወደ ዝርዝሩ ሳይሆን ሐምሌ 7 ብለዋል ያ 7 ማን ላይ ሊመስክሩ ነው የመጡት አሁን በስም ብቻ ይንገሩን እና ወደ ዝርዝሩ በኋላ እንሄዳለን ?
- /ግልፅ ያልሆነ/ አህመድ ጀባል እና አቡበከር እህመድ እና አህመድ ጀባል
- አቡበከር አህመድ እና ?
- አህመድ ጀባል
- 2 ሰው ላይ ብቻ ?
- አዎ

1548

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን ጀባል አሉ ?
- - አህመዲን ጀባል
- እነሱ ላይ ለመመስከር ነው የመጡት 2 ሰው ላይ አይደል ?
- ከእኔ ጋር ፀብ ምናምን የለም
- ቆዩ እና 2 ሰው ላይ ለመመስከር ነው አይደል የመጡት ?
- እኔ 2 ሰው
- ቆዩ ቆዩ መጀመሪያ አዳምጡ እነኚህን አሁን የጠሩትን ሰዎች አቡበከር እና አህመዲንን በአካል ያውቃሉ እርሶ ?
- በአካል ስለማላውቃቸው ያኔ ሐምሌ
- በቃ እኮ በአካል ያውቋቸዋል ወይስ በስም ነው ?
- አላውቃቸውም በአካልም በምንም አላውቃቸውም
- እሺ በምንድን ነው የሚያዉቋቸው ?
- እኔ ያን ወር መስኪድ ጥበቃ ሠራተኛ ነኝ
- ቆዩ ቆይ አሁን እነዚህ የጠሯቸው ሰዎች እዚህ አሉ የሉም ?
- አላውቃቸውም መለየትም አልችልም
- ዐቃቤ ሕግ
- አቶ አብዶ እስቲ ዛሬ ከመጡበት ምስክርነት ጋር በተያያዘ ለተከበረው ፍ/ቤት አሁን ባሏቸው ሰዎች ምንድን ነው የሚያውቁት እስቲ ስለእነሱ ምን ያውቃሉ መቼ ስለተደረገው ድርጊት ነው የሚናገሩት ይሄንን በማስታወስ እንግዲህ ከአሁን ሰዓት ጀምሮ መግለፅ ይችላሉ እና ይቀጥሉ ?
- እሺ እኔ የማውቃቸው እንግዲህ ያ እኔ የጥበቃ ሠራተኛ ስለነበርኩኝ
- የት ነው ጥበቃ ሠራተኛ የነበሩት ?
- አንዋር መስኪድ ውስጥ ሐምሌ 7 ቀን ከቀኑ 4 ሰዓት
- ዓ.ም መቼ ነው ?
- ሐምሌ 7 ዓ.ም 2004
- አንዋር መስኪድ አሉ እሺ ምን ተደረገ እስቲ ይቀጥሉ ?

1549

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሐምሌ 2004 ከቀኑ 4 በኋላ ቀኑን አላስታውሰውም በ 4 ሰዓት እና በሮቹን ስንጠብቅ በሮቹ ላይ ስንቆም በ 4 ሰዓት በሮቹን ይዘን ስንቆም ያልተለየ ወጣቶች መጡ አላህ ክበር እያሉ ያልተለዩ ወጣቶች መጡ ግቢ ሞሉ ግቢ ከሞሉ በኋላ ወደ ውስጥ ገቡ ማይክራፎን እንትን ማይክራፎን ኢማሙ የሚያስግዱበት ላይ ከፈቱ ንግግር ጀመሩ 4 ሰዓት ተኩል 5 ሰዓት አካባቢ
- ይቀጥሉ ምን ተከሰተ እንዴት አገኙ ማይክራፎኑን ከየት መጣ ?
- እኔ ጥበቃ በር ላይ ነን ውስጥ የሚደረግ ነገር ማታ ነው እንጂ አናውቅም ማታ ስንገባ ነው ቀን አንገባም ቤት ውስጥ
- ከምሽቱ 4 ሰዓት ነው ?
- ንግግር ሲጀምሩ
- ጠዋት ነው ማታ ነው 4 ሰዓት ያሉት ?
- ከቀኑ 4 ሰዓት ብዬአለሁ ንግግር ሲጀምሩ እኛ ከሰው በፊት እኛ እንሞታለን ከእናንተ በፊት እኛ እንሞታለን አብሺሩ ትላንትና የተናገርኩትን ዛሬም እናገራለሁ ከእዚያ በኋላ እሱ እየተነጋገረ እያለ ማይክራፎኑ መብራቱ ጠፋ መብራቱ ሲጠፋ ወደ ጀነሬተር ቤት ሄዱ ወጣየቹ ሞኢን ወጣየች ናቸው ግቢው ሞሉ ግቢ ከሞሉ በኋላ እኛ መለየትም የማንችል ጀነሬተር ቤት ተሰበረ ከእዚያ በጀኔሬተር አነሱ ማይክራፎኑን ማለቴ ነው ጀነሬቴር አነሱ ከእዚያ በኋላ ንግግር ጀመሩ አሁንም ትላንትና የተናገርኩትን ዛሬም እናገራለሁ
- ጀነሬተር ስበሩ ነው ምንድን ነው ?
- አዎ
- ጀነሬተሩን ነው የሰበሩት ?
- የጀነሬተር በር
- በሩን ?
- በሩን አዎ ጀነሬተር በሩን ከሰበሩ በኋላ አስነሱ
- ምኑን ነው ያስነሱት ?
- ሞተሩን
- ሞተሩን ይሄ ጀነሬተር የት ነበር ?

1550

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የመጣራት ሞተር ጀነሬተር ቤት ያለው
- ምን ውስጥ ነበር እሱ ?
- ቤት ውስጥ ነው ያለ
- የት ?
- በሩን ሰበሩ እና ገቡ በሩን ሰብረው ከገቡ በኋላ ጀነሬተር እራሱን አነሱት ቤት ውስጥ ነበረ ጀነሬተር እራሱን ሲያነሱ ጀነሬተሩ ተነሱ ንግግር ጀመሩ ንግግር ከጀመሩ በኋላ አሁንም በልበ ሙሉነት ትላንት የተናገርኩትን ዛሬም እናገራለሁ ማንንም አልፈራም አንፈራም ከእናንተ በፊት እኛ እንሞታለን ሲል በቃ ይሄንን ቃል ሰማሁ ከሰማሁ በኋላ እኛ ቤት ውስጥ ገባን በሩን ለቀቅን እና እቤት ውስጥ ገባን እቤት ውስጥ ገባን እና ቁጭ አልን በቃ ቁጭ አልን እነሱ ንግግር ጀመሩ ግቢው ሙሉ ነው ግቢው ጥቅ ነው የማናውቀው ነገር ሁሉ ሲናገሩ ነበር እኔ በጆሮዬ አልሰማሁም ያን ይሄን 3ቱን ቃል በጆሮዬ ሰምቼአለሁ
- ምን የሚለውን ?
- ጀነሬተሩን ከሰበሩ በኋላ እኔ ከእናንተ በፊት እኛ እንሞታለን ትላንት የተናገርኩት ቃል አሁንም እናገራለሁ አህመዲን ጀባል የሚባለው እና አቡበከር የሚባለው እነሱ ናቸው መድረክን የያዙት
- ማይክራፎኑን ከየት ነው ያነኙት ?
- መብራቱን ከእዚያ ከጀነሬተር ጋር ነው ያስነሱት ጀነሬተር ቤት ሰበሩ እና ቁልፉን ሰበሩ ቁልፉን ከሰበሩ በኋላ ጀነሬተሩን አነሱ ጀነሬተሩን ካነሱ በኋላ ንግግር ጀመሩ
- አዎ ጀነሬተሩ ተሰበረ በሩን ሰብረው ቁልፉን ሰብረው ገቡ አሉ ይሄንን ማይክራፎን ግን ከየት አገኙ መናገሪያውን ማን ሰጣቸው ከየት አገኙ ?
- ይሄንን የተናገረ
- ማይክራፎኑን ማን ሰጣቸው መናገሪያውን የድምፅ መናገሪያውን ?
- ከእዚያ ማን እንደሰጣቸው ማንም አልሰጣቸውም ሁላችንም ዘበኞች በር ቤት ገባን ቁጭ አልን ማንም አልሰጣቸውም እራሳቸው ገቡ በራሳቸው እንትን ፈፀሙ እኛ በ 11 በ 12 ሰዓት አካባቢ እነሱ ከወጡ ቤቱን ፍተሻ ስንገባ ኢማሙ የሚናገርበትን ተሰብሮ አየን ጀነሬተሩ ተሰብሮ አየን
- ኢማሙ የሚናገሩበት ምን ማለትዎ ነው የተሰበረው ?

ECLN
1551
http://ethiopianlawnetwork.com/

- ማይክራፎን አለ እንደዚህ ዓይነት ሚይክራፎን አለ
- ማይክራፎን ነው የተሰበረው ?
- አዎ ሳጥን አለች በሳጥን ውስጥ ነው ያለ ሳጥኑን ሰበሩ እና ያንን አወጡ ከውስጡ ከውስጡ አወጡ እና ተናገሩ
- ቅድም ያሏቸው ሰዎች ሲገቡ ያው በኃይል ብዙ ወጣቶች በርካታ ናቸው የገቡት ምናምን ብለዋል እርሶ ደግሞ እንደገለፁት የጥበቃ ሠራተኛ ኖት እንዴት ነው ማለት እንዴት ገቡ ማን ጠራቸው እንዴት እንደተጠሩ እንዴት እንደመጡ ?
- ማን እንደጠራቸው ማን እንደገቡም አላውቀውም
- አገባባቸውስ እንዴት ነው ?
- እኛ ድንገት ሆነብን እኛ ድንገት ሆነብን ሲገቡ እና እንትን ሲሉ ማንም ምንንም ሀገሩ ሰላም ብለን በራችን ከፍተን ትልቁ በር ላይ ሁላችን እየቆምን ነን ሀገሩ ሰላም ብለን ድንገት ነው የመጡብን
- ቅድም ያሏቸው ሰዎች አቡበከር እና አህመዲን ጀባል ቅድም እንዳሉት ያው እነኚህ ከእናንተ ከሌላ ቦታ ከሌላ አገር ጋር አንዲህ አንዲህ ያሏቸው ታላላቆች ሲኖሩ ሰምተሀለሁ ወይም አይተዋል አይተዋቸዋል እዚያ ምን ላይ ሆነው ነው ይሄንን ሲገልፁ የነበሩት ?
- እኔ እነሱን አላየዋቸውም ግር ብለው አብረው አብረው የገቡ ግር ብለው አብረው ሲገቡ ይሄ ይናገራል ይሄ ይናገራል ሲሉ ነው እንጂ አላየዋቸውም
- ይሄ ይናገራል ይሄ ይናገራል የሚለው ማን ነው ?
- የሚያስተዋውቀው እዚያ እዚያ የሚያስተዋውቀው አንዱ ነው ተነስቶ የሚያስተዋውቀው ስሙን አልተናገረም
- ጥሩ ሲያስተዋውቁ ግን ስማቸውን ሲናገሩ ነው አስተዋዋቂው ሲናገር ነው የሰሙት ?
- አዎ ስማቸውን አዎ
- ከእዚህ ጋር ታዲያ ማይክራፎኑ ሲሰበር ወይም እናንተ ስትደርሱ ማታ ነው ተሰብሮ ያዩት ማለት ነው ማይክራፎኑ ቅድም ከነበረበት ቦታ ተሰብሮ አይተነዋል ብለዋል እና እሱስ እንዴት እንደተሰበረ የሚያውቁት ነገር አለ ?
- እስቲ ቆይ ማይክራፎን ተሰብሯል ነው ወይስ የማይክራፎን የነበረበት ሰጥኗ ተሰብሯል ?

1552

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ማይክራፎን የነበረበት ሣጥን ምኑ ነው የተሰበረው ?
- ማይክራፎን አልተሰበረው እኮ ሣጥን አለ ኢማሙ ጋር ሣጥን አለ እንትን የሚቀመጥበት ማይክራፎን የሚቀመጥበት ሣጥኑን ቁልፉን ሰበሩት እና ሳጥኑን ከፈቱ ከከፈቱ በኋላ ያንን አወጡ እና አነጋገሩ በማይክራፎን ማለት ነው ማይክራፎን አወጡ እና አነጋገሩ እንደዚህ እንደዚህ ዓይነት ማይክራፎን አለ አነጋገሩ
- ይሄንን እያዩ ነበር እርሶ ሌሎች የጥበቃ ሠራተኞች ነበሩ ከእርሶ ጋር ?
- እኛ ጥበቃ ላይ ጥበቃ ላይ እኛ ጠዋት ስንረከብ በር ላይ እንሆናለን ውስጥ የሚሰራ ሌላ ሰው ነው እኛ ይሄንን አናውቅም ማታ ነው ማታ ሕዝብ ከወጣ በኋላ ነው ለፍተሻ ስንገባ የነለ ነገር ለአለቆቻችን እንነግራለን ይሄ ጎደለ ይሄ ጎደለ ብለን እንናገራለን
- ስለዚህ ከጎደለው መሀከል አንዱ ቅድም የገለፁት ነው የተሰበረው ማለት ነው ?
- አዎ ነው እንጂ ቀን ውስጥ የተደረገው ምንም አናውቅም በር ላይ መኪናዎች የሚገባ መኪና እና እብድ ምናምን እንመልሳለን ሌላውን ቦዶ እጃችን ነው የምንሰራ ሌላውን እንደፈለገ ፍተሻ የለ ምን የለም ኃይማኖት ተቋማት ነው
- የእዚያን ዕለት ፍተሻ አልነበረም እንዴ ?
- እኛ አንፈትሸም
- ሌላ የሚፈትሽ ነበር እንዴ ?
- አዎ እነሱ ከእኛ ተረከቡ እና ፍተሻ ጀመሩ
- እንዴት ነበር የሚፈትሹት በተርታ ቆሙ እና ፍተሻ ሲጀምሩ እኛ ምንም አላሉንም እኛ ትተን ወደ ቤት ገባን በቃ
- ፈታሾቹ እነ ማን እንደሆኑ ያውቋቸዋል ወይስ ማን መደባቸው ?
- ኧረ ወጣቶች መአት ናቸው ጉንዳን ናቸው ማን ያውቃል
- በወቅቱ እናንተ የጥበቃ ሠራተኞች ናችሁ እና ለመከላከል አልሞከራችሁም እንዴ በኃይል ሲገቡ ?
- እኛ እኛማ ጥበቃ ሠራተኞች ጠዋት ገብተን በንጋታው ጠዋት እንወጣለን በቃ
- አይ ማለቴ ምንድን ነው እርሶ እና ጓደኞችዎ ያው ጥበቃ ሰራተኞች ያላችሁት ጥበቃ ላይ የተሰማራችሁ ናችሁ እና በኃይል ሲገቡ ለመከላከል አልሞከራችሁም ወይ ነው የሚለው ?

1553

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለመከላከል ምንም ያደረግነው ነገር የለም
- ለምን ?
- የገቡት ሙስሊሞች ናቸው ኮፍያ ለብሰዋል ቀሚስ ለብሰዋል መከላከል ይሄ ይመጣብናል ይሄ ይመጣብናል አላልንም አልተከላከልንም በሩን ለቀቅን በቃ
- እንዴት በኃይል ነው ወይስ በዝግታ እንዴት ነው አገባባቸው ?
- አመጣጣቸውማ ግር ብለው ስለገቡብን ትንሽ ደነገጥን እንጂ ሁሉም ቀሚስ ለብሷል ሁሉም እስላማዊ ልብስ ስለለበሰ ሌላ ቢሆን በራችን እንዘጋ ነበረ በሩ ክፍት እንዳለ በሩን ገቡ በቃ ያንን ነው እንጂ እኔ የማውቀው ነገር የለም ውጡም አላሉንም ምንም አላሉንም አላገዱንም እኛ ነን ቤት ውስጥ የገባነው
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀኛ ጥያቄ ካለ
- አቶ አብዱ የአንዋር በር ሁሌም ክፍት ነው አይደል ?
- አንዋር በር ክፍት ነው
- ግቢው አይዘጋም ?
- ግቢው አይዘጋም
- ሰው በማንኛውም ሰዓት ገብቶ ይወጣል አይደል ?
- ገብቶ ይወጣል ማንኛውም ሰው እከሌ ገባ እከሌ ወጣ አንልም
- አይባልም ?
- አይባልም
- እርሶ በእዚያን ዕለት ከስንት ሰዓት ጀምሮ ነው እዚያ መጠበቅ የጀመሩት ?
- እኛ ከ 3 ሰዓት አካባቢ በራችን
- የተረከቡት ጥበቃ ?
- የተረከብን በ 3 ሰዓት አካባቢ ነው
- 3 ሰዓት አካባቢ ነው ?
- አዎ

1554

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሚረከቡበተ ሰዓት አነሺህ ውጣዎች አልገቡም ጥጥቶቹ አልገቡም አይደል 3 ሰዓት አካባቢ?
- 3 ሰዓት አካባቢ
- ከ 4 ሰዓት ጀምሮ ነው መግባት የጀመሩት ?
- አዎ 4 ሰዓት ጀምሮ አዎ ያን ካ 3 ሰዓት በፊት ሱቢ 8 ሰዓት ስንከፍት በሩ ለሰላት ቁራን የሚቀራ ይገባሉ ለሰላት የሚገባም አለ 8 ሰዓት ነው በሩ የሚከፈተው
- ቆይ እስቲ ምስክር 3 ሰዓት ነው የገባሁት ያሉት የጠዋት ነው የማታ ነው የጠዋት 3 ሰዓቷ?
- ሰው እኮ እዚያ ውስጥ የለም አላልኩም አሁን
- አይ አይ 3 ሰዓት ያሉት ከምሽቱ ነው ከጠዋቱ ?
- የገቡት በእኔ በኩል ነው የገቡት ወጣቶቹ አሁን 4 ሰዓት ሲገቡ በእኔ በኩል ነው የገቡት
- የለም ጥበቃ የጀመሩት ጠዋት ነው ከሰዓት ነው የተባለው የተጠየቁት አሁን ?
- እኔ ጥበቃ ከጀመርኩ ጠዋት 3 ሰዓት ተረክቤ በንጋታው 3 ሰዓት ነው የምረከበው
- ጠዋት 3 ሰዓት እሺ ጥያቄውን ይቀጥሉ
- 2ቱ ተከሣሾች በስንት ሰዓት ነው የተናገሩት ?
- ወደ 4 ሰዓት 5 ሰዓት አካባቢ ነው
- 4 ሰዓት 5 ሰዓት ?
- አካባቢ
- እርሶ እነሱ ሲናገሩ እርሶ የት ጋር ነበሩ ?
- በር ላይ በር ከውጪ በር ፖሊሶች የሚቆሙበት
- የግቢ በር ማለት ነው ?
- የግቢ በር
- በየትኛው በኩል 2 በር አለው አይደል 3 በር ?
- ከአንዋር ባንክ በታች ያለው
- ባንኩ ጋር ባለው በኩል ?
- አዎ በአንዋር ባንክ በታች ያለው እዚያ ነው

1555

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ ተከሣሾቹ ዋናው መስኪድ ውስጥ ነበሩ አይደል ?
- ተከሣሾች እኮ የእዚያን ጊዜ ሲገቡ አላየዋቸውም መአት ሕዝብ ነው የገባ
- ንግግር ያደረጉት ?
- ንግግር ያደረጉት ከ 4 ሰዓት እስከ 5 ሰዓት አካባቢ ነው
- ንግግር ያደረጉት አንዋር መስኪድ 2 መስኪድ የለውም እንዴ በውስጡ በግቢው ውስጥ ?
- ግቢው ውስጥ 2 መስኪድ አለ ፎቅ እና ዋናው በር ዋናው በር ትልቁ በር የገቡ
- አሁን የተናገሩት እነሱ ዋናው መስኪድ ውስጥ ነው ?
- ዋናው መስኪድ ትልቁ በር
- ዋናው መስኪድ ውስጥ ?
- አዎ ትልቁ በር
- ኢማሙ የሚያሰግዱበት ቦታ ?
- አዎ
- እርሶ ካሉበት ቦታ ኢማሙ እስከሚያሰግዱበት ዋናው መስኪድ ድረስ ምን ያህል ይሆናል ርቀቱ በግምት ?
- በግምት 300 ይሆናል
- 300 ሜትር ?
- 300 ሜትር በላይ ይበልጣል ካሬ ሜትር
- ጥሩ በእዚያን ሰዓት ከ 4 ሰዓት መግባት ከጀመሩ ጊዜ ጀምሮ ግቢው አልሞላም እንዴ ሰው ሰው ግቢው ሰው በሰው አልሞላም ?
- ሰው ሞላ ሰው ከ 4 ሰዓት ጀምሮ ጥቅጥቅ ብሎ ነው ተከታትሎ ተከታትሎ መንደሩ በሙሉ ሜዳ በሙሉ ሞልቷል ሰው
- ሞልቶታል ?
- ሜዳ በሙሉ
- እርሶ በእዚያ በር ላይ ከእዚያ አልተነቃነቁም ?
- አዎ

1556

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተከሣሾቹ ውስጥ ተቀላቅለው ገቡ እንጂ እርሶ በትክክል ሲገቡ ይግቡ አይገቡ የሚያውቁት ነገር የለም ?
- የማውቀው ነገር የለም
- ስለዚህ ተከሣሾች መኖሪያቸውን በምንድን ነው ያወቁት ተከሣሾቹ ገብተው ይናገሩ ነበር አሉ ?
- አዎ
- ምን ይሄንን በምን አወቁ ?
- ይሄኔ ይሄ ይናገራል ብለው አስተዋወቂ እያስተዋወቀ ነበር
- ሌላ ሰው ነበር የሚያስተዋውቀው ?
- ሌላ ሰው ነበር የሚያስተዋውቀው
- ተከሣሾቹ አሁን ይናገራሉ ?
- ይናገራሉ
- እያለ ያስተዋውቅ ነበር ?
- አዎ ያን ሰውዬ ስሙን አላውቀውም
- 2ቱ ተከሣሾች ነው ከእዚያ በኋላ 2ቱ ብቻ ነው የተናገሩት ?
- ያን ጊዜ 2ቱ ብቻ ነው የተናገሩት ሌሎቹን
- እርሶ እስከ ስንት ሰዓት ቆዩ እዚያ ?
- እኔማ እስከ 6 ሰዓት ቆይቼ ምሳ ልበላ ሄድኩ
- እስከ ቀኑ 6 ሰዓት ማለት ነው ?
- አዎ 6 ሰዓት ቆይቼ ምሳ ልበላ ሄድኩ ll ሰዓት መጣሁ ለአዳር
- ተከሣሾችን ከእዚያን ቀን በፊት አያውቋቸውም አይደል ?
- ምንም ነገር
- አያውቋቸውም ?
- አላውቃቸውም
- ስለዚህ እነሱ ይናገራሉ ብሎ አስተዋወቂው ስላስተዋወቀ ብቻ ነው አይደል አሁን እነሱ ናቸው የሚሉት ?

1557

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ምስክሩ የተናገረውን ነገር እየደገሙ ስለሆነ ይሄንን መስክረዋል ሌላ ጥያቄ ካሎት
- ሐምሌ 7 ነው ይሄ ድርጊት ተፈፀመ ያሉት አይደል ?
- ሐምሌ 7 አዎ
- ሐምሌ 7 ነው ?
- ከቀኑ 4 ሰዓት
- ሐምሌ 6 እርሶ ጥበቃ ስራ ላይ አልነበሩም አይደል ?
- ሐምሌ 6
- እርሶ ጥበቃ ስራ ላይ አልነበሩም ?
- የለሁም ቤቴ ነኝ
- ሐምሌ 7 ጠዋት ሲገቡ የመጀመሪያ 3 ሰዓት ሲገቡ ያደረጉት ነገር ምንድን ነው ?
- እኛ በሮቹ ምናምን ስንረከብ /ግልፅ ያልሆነ/ ሲረከብ ምንም የለም ያን ጊዜ
- ምን ምንድን ነው የተረከቡት ?
- ማይክራፎቹም ሁሉም ሁሉም አይተን ተረክበን ተማምነን ፈርማችን ፈርመን በር ላይ ቆምን
- በር ላይ ሆነው ነው ወይስ ዞረው አይተው ነው ?
- በር ላይ
- በር ላይ ሆነው ነው ?
- አዎ በር ላይ እኛ በር ነው የምንይዘው እንጂ ውስጥ አንገባም
- ስለዚህ ጠዋት ሲገቡ የኢማሙ ማይክራፎን የሚቀመጥበት ሣጥን መቆለፍ አለመቆለፉን አላዩም ነበር አይደል?
- አላወኩም
- የጀነሬተር ቁልፉ መቆለፍ አለመቆለፉን አላዩም አይደል ?
- አላየሁም እንዴት አያለሁ ቤት ውስጥ አሁን እዚህ የተደረገ /ግልፅ ያልሆነ/ ማን ያያል
- ስለዚህ አሁን ሰበሩት ያሉት እርሶ ዘ ሰዓት ላይ ሲገቡ ተሰብሮ ስላገኙት ነው አይደል ?
- አዎ ተሰብሮ ሁሉ ነገር

1558

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን እንደሰበረውም አላዩም ?
- ማን እንደሰበረ አላውቅም
- ፲፩ ሰዓት ላይ እርሶ ሲመጡ ግቢው ውስጥ ሰው ነበረ ?
- ሰው የለም
- ሰው አልነበረም ?
- አልነበረም ሌላ ሰው ሲጋጅ ምናምን አለ
- ከእዚህ ውጪ አሁን የጀነሬተሩ ቁልፉ እና የይማሙ ማይክራፎን የሚቀመጥበት ሳጥን ተገነጠለ ካሉት ውጪ የደረሰ ምንም ጉዳት የለም አይደል ?
- ምንም ጉዳት የለም
- ምን አሉ ?
- ሚጥኑን መስበሩ ብቻ ነው
- ከእሱ ሌላ ምንም የደረሰ ጉዳት የለም ?
- አዎ
- አቶ አብዶ ቅድም ሲመሰክሩ በዐቃቤ ሕግ ሲጠየቁ የእኔ ስራ በር ላይ ነው ብለው ነበረ በር ላይ ነው የእኔ ስራ ወደ ውስጥ አልገባም እብድ ማባረር ሌላ የሚገባ ስው የምመልሰው ብለው ነበር ልክ ነው ?
- ያን ጊዜ በስራ ስራ ላይ ነበርኩ ስራ ላይ ስለነበርኩ ማን እንደተናገረ እና ማን /ግልፅ ያልሆነ/ ለፖሊስ ቃል ሰጠን ቃላችን ለፖሊስ ሰጠን
- እስቲ ቆይ ልክ ነው የሚመልሱት
- ልክ አይደለም
- ጥያቄውን ግልፅ አድርጉ
- ቅድም በዐቃቤ ሕግ ሲጠየቁ የእኔ ስራ ውጪ ሆኜ እብድ መመለስ ሰዎች እንዳይገቡ ነው ውስጥ ያለውን ስራ ደግሞ የሚሰሩት ሌሎች ናቸው ብለው ነበረ ስለዚህ ከእዚህ አንፃር ይሄ ማይክራፎኑ ሳጥን ተሰበረ ያሉትን ከእዚያ በፊት መሰበር አለመሰበሩን ያውቃሉ ወይ ?
- እሱ ተጠይቋል እኮ
- ጥያቄው ይለያል

1559

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሱ ተጠይቋል መሰበር አለመሰበሩ ይታወቅ ነበር ወይ ተጠይቋል
- እሺ ፍተሻ ነበረ ብለዋል ?
- አዎ
- ፍተሻ ፖሊሶች ነበር የሚፈትሹት?
- ፍተሻማ በጣም ነበረ ፍተሻ
- እሱ ፖሊሶች አላሉም እስቲ
- እኔ የጠየኩትን
- አይደለም ፖሊሶች አላሉም አልተነሳም
- እነሱ እራሳቸው
- ፍተሻ የነበረው ሌላ ሰው ነው አይ አያስቅም በደንብ ነው የጠየቁት ፍተሻ ፖሊስ ሲፈትሽ ነበር አላሉም ያሉት ነገር ምንድን ነው ፍተሻ የእኛ አልነበረም ፍተሻ የነበረው መጀመሪያ ምንም ፍተሻ አልነበረም በኋላ ግን የማናውቃቸው ሰዎች ይፈትሹ ነበር እሱ ይሄንን ነው ያሉት ፖሊስ አላነሱም
- /ጣልፅ ያልሆነ / እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ስለዚህ ማን ነበር የፈተሸው ?
- የፈተሸው ወጣቶች መአት መጡ እና ወጣቶቹ ፈተሹ እንጂ ከእዚያ በፊት አንፈትሽም ምንም አንልም
- ወጣቶች መሆናቸውን በምን አወቁ ?
- እራሳቸው አዎ መጡ እና በሮቹን ያዙ በር ከያዙ በኋላ ፍተሻ ጀመሩ
- እሺ ወጣቶች ናቸው ብለዋል ወጣቶች መሆናቸውን በምን አወቁ ?
- ብዙ ናቸው መለየት አንተ እንኳን እዚያ ብትቆም መለየት አትችልም እኮ
- ፈታሾቹን ፊታቸውን ማየት ይችሉ ነበር እርሶ ?
- አዎ
- ይታያል ፊታቸው ?
- አዎ ይታያሉ ሲወጡም ሲገቡም ይፈትሻሉ በቃ
- ምን ነበር የሚፈትሹት ?
- ያን ጊዜ ምንም አልነበረም እየገቡ ነበር

1560

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይደለም ምንድን ነው የሚፈትሹት ወጣቶቹ ምንድን ነው ሲፈተሹ ያዩተ አርሶ ?
- እርስ በእርስ ዝም ብለው ከእኛ አለፉ እንጂ የሰማሁት ነገር የለም
- ያዩት ነገር ምንድን ነው አላዩም ሲፈትሹ ?
- ሲፈትሹ አይቼአለሁ
- ምን
- እስኪሪቢቶ እስኪሪቢቶ እንኳን አይገባም
- ሌላስ የማይገባ ነገር ምን ነበር ?
- ምንም አንድ ነገር አይገባም
- ለምሳሌ
- አይገባም ብሎ እስኪሪቢቶ ሁሉ ነገር እያወጡ ነው የሚገቡት
- ሌላ እስኪሪቢቶ አይገባም ስለታማ ነገር ይገባ ነበር ስለት ያለው ነገር ያስገቡ ነበር ?
- ማን ምንም ነገር ኪሳቸውን ሁሉ አውልቀው እኮ ነበር ከድሮ የተለየ
- ቅድም መብራት ተቋረጠ እና ጀነሬተር ተኩ ብለው ነበር ምን ያህል ቆየ ረጅም ሰዓት ነው?
- መብራት ሲቋረጥ ወደ 1 ሰዓት አካባቢ ነው 4 ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው የተቋረጠው
- ለምን ያህል ጊዜ ተቋረጠ ?
- ያ የመንግስቱ ነዋ መብራቱ የመንግስቱ ነው
- ጥያቄው ለምን ያህል ጊዜ ተቋረጠ ነው የተቋረጠበት ምን ያህል ጊዜ ነው ?
- መብራቱ አካባቢው ስለጠፋ ነው የጠፋው
- እኮ ጠፍቶ የቆየው
- ያኔ ጠፍቶ ነው እንትን ያሉት ጀነሬተር ቤት ሄደው ጀነሬተሩን የሰበሩ
- እኮ ምን ያህል ቆይተው ተከፈተ ነው የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት
- ተመልሷል ?
- አይ አልተመለሰም የተከበረው ፍ/ቤት እኔ ፍ/ቤቱ ምናልባት
- እስቲ ይኸውሎት ምስክር መብራት ጠፋ ብለዋል ?
- አዎ
- የኤሌትሪክ መብራት ነው የጠፋው ?

1561

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እሱ መብራት ጠፍቶ ለስንት ሰዓት ቆየ ?
- 4 ሰዓት ተኩል አካባቢ
- ቆይቷል የጠፋበት ነው 4 ሰዓት ተኩል ?
- የጠፋበት አካባቢው ስለጠፋ
- አይደለም የጠፋበት ስንት ሰዓት ነው ?
- 4 ሰዓት አካባቢ
- 4 ሰዓት አካባቢ ?
- 4 ሰዓት ተኩል አካባቢ
- ስንት ሰዓት መጣ ?
- ወደ 8 ሰዓት አካባቢ
- ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- ይሄ ሐምሌ 7 ያሉት ምን ቀን ነበር ሰኞ ነው ማክሰኞ ነው ?
- የሚያስታውሰት ከሆነ ይመልሱ ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ዕለቱን ነው የጠየኳቸው
- /ግልፅ ያልሆነ/
- ዕለቱን ነው
- ብለዋል በዋና ጥያቄ ዕለቱን አለየሁም
- የእዚህን ቀን ያሰገደ ሰው አውቀዋል እንዴ ዙር አንዋር ማን እንዳሰገደ ?
- በጀነሬተር ነው የተሰገደ
- ማን አሰገደ ነው ማን አሰገደ ?
- እነሱ እራሳቸው ነው ኢማሞቹም የሉም /ግልፅ ያልሆነ/ የሉም እነሱ እራሳቸው ናቸው ነው ያሰገዱት
- ከእዚህ ቀን ወዲህ እዚህ መስኪድ ውስጥ ሰብሰባ ነበር ከሐምሌ 7 ውጪ እርሶ የሚያውቁት ?

1562

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሐምሌ 7
- ሌላ ቀን ስብሰባ ሲደረግ ያውቃሉ እዚያ ግቢ ?
- ሌላ ቀን ሌላ ቀን ስብሰባ የሚደረግ ነገር የለም
- ሐምሌ 7 ብቻ ነው የተደረገው ?
- ሐምሌ 7 ነው
- የተደረገው ?
- አዎ ከእዚያ በፊት ምንም ነገር የለም
- ይሄ ሐምሌ ወር የክረምት ወር ነው እንደሚያውቁት አየሩ እንዴት ነው የክረምት ወር ስለነበረ ወቅት ስለነበር በእዚህ ዕለት ምን ነበር የሚያስታውሱት የአየር ሁኔታ ፀሀያማ ዝናብ የትኛው ነበር ክረምት ስለነበር ማለት ነው ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አየሩማ ፀሀያማ ነው ዝናብ የለም ዝናብ የለም
- አቶ አብዶ
- እስቲ ጥያቄ ያልተደገመ ምረጡ እና
- አቶ አብዶ ከገቡ ጀምሮ ትላንት የተናገርኩትን ዛሬም እናገራለሁ እያሉ ነበር ምን ማለትዎ ነው ?
- ስራ ላይ
- ትላንት የተናገሩትን የተናገርኩትን ዛሬም እናገራለሁ ትላንት ምን ነበር የተናገሩት ሌላ ነገር እንዲናገሩ ያስገደዶት ሰው አለ እንዴ ?
- እኔ የሰማሁት /ግልፅ ያልሆነ/ አሁን የተናገርኩት 3 ቃል ብቻ ነው
- ከእዚህ ውጪ እንዲናገሩ የጠየቆት ሰው አለ ?
- ከእዚህ ውጪ የሰማሁት ነገር የለም
- ቆዩ ምናልባት ቼክ አድርጉ እስቲ የመዘገቡትን ሰዎች የተናገሩትን ነው የተናገሩ እና የእሱ አይደለም ቃሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እርሶ ሕዝቡ ሲለያይ ወደየቤቱ ሲሄድ ነበሩ በቦታው ?
- አዎ

1569

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ነበሩ ?
- የት
- ማለት እዚያው መስኪድ ውስጥ ነበሩ መስኪዱ ግቢ ጥበቃ ስራዎትን እየሰሩ ነበር ሕዝቡ ስብሰባውን ጨርሶ ሲሄድ ?
- ሐምሌ 7 በር ላይ ነው ያለሁት መጅለስ ስራ ላይ ነው የላኒት /ግልፅ ያልሆነ/
- እኮ ነበሩ ማለት ነው ?
- አዎ ነበርኩ
- ስለዚህ ሕዝቡ ሲመለስ ምንም የተፈጠረ ችግር የለም በሰላም ነው ወደየቤቱ የሄደው ?
- አዎ ያንን የተናገሩት ቃል ነው እንጂ ምንም እስከእዚህም ረብሻም የለም ስለዚህ እምነቱ ሲናገሩ ወጣቶች አላህዋክበር ይላሉ ነው እንጂ
- ሌላ የተፈጠረ ችግር የለም ?
- ሌላ የተፈጠረ ችግር የለም
- ቅድም ተሰበረ ያሉት የጀነሬተር መዝጊያ ቁልፍ ወይም ጀነሬተር እንዲቀመጥበት
- የሚቀመጥበት መግቢያ
- [illegible] ቁልፉ ነው ?
- አዎ
- የማይክራፎኑም የሚቀመጥበት መዝጊያው ቁልፉ ነው
- ጠበቃ ተጠይቋል
- አሰጋጆቹም /ግልፅ ያልሆነ/ አልነበሩም ብለዋል ?
- አልነበሩም
- መጥተው እንዲያሰግዱ ጥሪ አልቀረበላቸው እንዴ ?
- ጥሪ የእነሱ ነዋ ጥሪ ያቀረቡት ጥሪ ያቀረበው የእነሱ ወገን ነው ጥሪ ያቀረበው
- እኮ መአጅኖቹ ወይም አሰጋጆቹ በቦታው ካሉ መጥተው እንዲያሰግዱ ወይም አዛን እንዲያደርጉ ጥሪ አልቀረበም ነበር እዘ የ ካሉት ለወጁ ?
- ጥሪ
- ኑ እና አሰገዱ ተብለው አልተጠሩም ?

1564

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አላቀረቡም
- እርሶ ለምሳ ሄጄ ነበረ ብለዋል እንዴት አወቁ አለመጠራቱን ?
- አላቀረቡም
- ቅድም ሲመሰክሩ ለምሳ ሄጄ ተመለስኩኝ ብለዋል ?
- ለዎ ለምሳ ሄጄ
- ታዲያ እንዴት በምን አወቁ ጥሪ መደረግ አለመደረጉን ?
- መአጅኖች የሉም ያን ጊዜ ይሰማል
- አይ ጥሪ አልተደረገም ያሉትን ?
- ጥሪማ አልተደረገም ጥሪ
- እርሶ በምን አወቁ ለምሳ ሄደው ነበር አይደለም ?
- አዎ
- በምን አወቁ ሰዎቹ እንዲያሰግዱ ጥሪ አድርገው ከሆነ ወይም አላደረጉ ከሆነ በምን አወቁ ለምሳ ከሄዱ ማለቴ ነው
- ተቃውሞ አለኝ
- እዚያው ጎረቤት ነው
- ቆዩ እስቲ
- እዚያ ለምሳ ወጥቼ እዚያው ነው የበላሁት እንጂ /ግልፅ ያልሆነ/
- መልሰውታል ለነገሩ
- አልፈዋለሁ የተከበረው ፍ/ቤት
- ተመልሷል
- ከሐምሌ 7 ውጪ የተደረገውን ፕሮግራም አያስታውሱም ወይም መደረጉን አያውቁም ?
- እሱም ተጠይቋል
- ሐምሌ 7ን እንዴት እንዳስታወሱ ይነግሩናል ?
- ለዛሬ ነ
- እሱም ተጠይቋል እኮ ምናልባት እሳቸው አልጠየቁም
- /ግልፅ ያልሆነ/

ECLN

1565

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሐምሌ 7 እንዴት አስታወሱ እርሶ ሐምሌ 7 ፕሮግራም የተደረገበት ቀን ወይም ሰው የተሰባሰበበት ቀን ሐምሌ 7 መሆኑን በምን አወቁ ?
- ሐምሌ 7 መሆኑ ያወኩበት እኛ ቀኑ ከተደረገ በኋላ በቀን በፊርማችን ከእዚያ ቢሮ ገብተን ስንፈርም ቀኑን እናያለን በእዚያን ጊዜ ነው የምናውቀው ቀኑን በቀኑ እንኳን አንሳሳትም
- ከመስኪዱ ውጪ ንግግር ሲያደርግ የነበረ ሰው አለ ከማይክራፎን ውጪ ?
- አዎ
- ከእዚያ ውጪ ንግግር ያደረገ ሰው የለም አይደል ?
- ከእዚያ በፊት
- ማለት አሁን ንግግር አደረጉ ያሏቸው ሰዎች በማይክራፎን ብቻ ነው የተናገሩት ?
- እነሱን በቃልም በእንትንም አላውቃቸውም
- አያውቋቸውም እነሱን ?
- አዎ እነሱን አላውቃቸውም መለየትም አልችልም አላውቃቸውም
- ከመስኪዱ ውጪ ንግግር ያደረገ ሰው የለም ?
- ምንም ነገር የለም
- ጨርሻለሁ
- እዚህ ላይ አልዋሽም
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት መስቀለኛ ጥያቄ ጨርሰናል
- ድጋሚ ጥያቄ ካለ
- ቅድም እርሶ ሲገልፁ ሐምሌ 7 የተፈጠረ ችግር አልነበረም ወይ ሲባሉ አዎ የለም ብለዋል እና ይሄንን ሌላ ቦታ ይፈጠር ይህ ችግር ይኑር አይኑር ይሄንን ማስታወስ ይችላሉ ?
- የት
- የእዚያን ዕለት ማለት ነው በዕለቱ እርሶ
- መቃወሚያ አለ
- እሺ

1566

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ዐቃቤ ሕግ እየጠየቁ ያሉት ስለ ሌላ ቦታ ችግር ነው እኛ ምስክሩን ስለሌላ ቦታ አልጠየቅንም ስለአንዋር መስኪድ ነው አንዋር ተጠይቆ ረብሻ እንደሌለ-አረጋግጠዋል አሁን ዐቃቤ ሕጉ እየጠየቁ ያሉት ሌላ ቦታ ችግር ተፈጥሮ እንደሆን እያሉ ነው ስለዚህ
- አልተነሳም ?
- [illegible]
- ግልፅ ነው ይሄ ዐቃቤ ሕግ ምላሽ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ለማለት የፈለኩት ምንድን ነው ዋናው ከአንዋር በኋላ ችግር ይፈጠር አይፈጠር ይሄንን ማወቅ ይችላሉ ወይ ነው በአጭሩ
- ከአንዋር በኋላ
- ቆዩ ምስክር
- ጥያቄውን እስቲ ግልፅ አድርጉት ምን ነበር የመጀመሪያው አሁን እኛ የያዝነው ነገር ምንድን ነው ከውጪ ከአንዋር መስኪድ ውጪ ያለ ነገር ሌላ ቦታ አድርገን ነው የወሰድነው አንዋር መስኪድ እዚያ ውስጥ ያለውን ነው ?
- በዕለቱ ሐምሌ 7 ቅድም ሲጠይቁ እሳቸው በዕለቱ እረብሻ ነበር ተባሉ አንዋር ጋር ማለት ነው አይ አላውቀም ነው ያሉተ የእኔ ደግሞ እኔ አሁን ያልኩት ምንድን ነው ቅድም እንደዚያ ብለው አሁን ደግሞ በዕለቱ ከአንዋር ከመስኪዱ ከተወጣ በኋላ ማለት ነው ለተከሰተው ወይም የሚከሰት ከመስኪዱ በኋላ ከተወጣ በኋላ ይሄንን ማወቅ ይችላሉ ወይ ስለተከሰተው ሁኔታ ማወቅ ይችላሉ ነው ያልኩት ይችሉ አይችሉም
- ብይን ሰጥተናል ከአንዋር መስኪድ በኋላ የተፈጠረው ነገር የሚያውቁት ነገር አለ ወይ የሚል ነገር ነው አልተነሳም የሚል መቃወሚያ ተነስቷል ምስክሩ በመስቀለኛ ጥያቄ 2ቱ ያ ተሰበሩ ከተባለ ውጪ የደረሰ ነገር ተብሎ አላውቅም ብለው የመለሱ ስለሆነ በመስኪዱ ዙሪያ ከእዚያ መልስ ያለውን ነገር መጠየቅ ከመስቀለኛ ጥያቄ ከተነሳው የወጣ ስላልሆነ ጥያቄው ትክክል ነው ይቀጥል ብለናል
- የተከበረው ፍ/ቤት አመሰግናለሁ
- ይሄንን ያውቃሉ ከእዚያ ዘጋላ በለመፈጠሩ ከአንዋር ውጪ ስለተከሰተው ነገር የሚያውቁት ነገር አለ ?
- አንዋር

1567

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከእዚያ በኋላ ማለት ነው ከእዚያ ውጪ ?
- ከእዚያ በኋላ የማውቀው ነገር የለም ከእዚያ በኋላ
- ጨርሰናል
- ቆይ አንዴ አቶ አብዶ ሐምሌ 6 አንዋር አካባቢ ስለተፈጠረው ነገር ያውቃሉ ?
- ሐሃሌ 6 ለሪ ሃለሁሃ
- አልነበሩም ስለዚህ ምን ይድረስ ምን ይድረስ የሚያውቁት ነገር የለም ?
- /ግልፅ ያልሆነ/
- አበቃን ድጋሚ አበቃን
- ቆዩ አንዴ
- እሺ ተቃውሞአችሁ
- እንዲሰረዝ ነው ቃሉ የተከበረው ፍ/ቤት
- ተቃውሞአችሁን አሰሙ
- ተመልሷል /ግልፅ ያልሆነ/
- ቅድም የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት ዕድሉን ከሰጠኝ
- አሁን ከእዚህ በኋላ /ግልፅ ያልሆነ/
- ትተውታል ጨረሳችሁ
- ጨርሰዋል እናመሰግናለን መሄድ ይችላሉ የዛሬውን የችሎት ውሎ በእዚሁ ጨርሰናል ነገ በተለመደው ሰዓት እንገናኛለን::

ECLN

1568

http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.....
Re.NO
ቀን.....
Date

CD መገኘቱን መስክረዋል ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይን መልስ ሰጪ መብቱን ጠብቆ ነው፣ የሰጠው ማስረጃ አልቀረበም በማለት መከላከል አያስፈልገውም በማለት በነፃ እንዲሰናበት ብይን ሰጥቷል።

በይግባኝ እንደተረምልን የምንጠይቀው ዳኝነት

መልስ ሰጪ በስር ፍ/ቤት ክስ ከቀረበባቸው የሽብር ቡድን አባላት በአዋለያ ትምህርት ቤት እና በአንዋር መስጊድ ሲያደርጉት በነበረው የአመጽ ጥሪ እና ቅስቀሳ ዋና አስተባባሪ በመሆን የተሣተፈ ነው። አመፅ በየጊዜው መቀጠል ያለበት ስለመሆኑ የሚበተን ወረቀት እንዲዘጋጅ መመሪያ በመስጠት በአመጽ ለሚሣተፉት አፋቸውን የሚለጥፉበት ፕላስተር በማዘጋጀት ሕገ-ወጥ የአመፅ ሰልፍ እንደዘጋጀ ለ4ኛ ተከሣሽ ካሚል ሸምሱ የደምፅና የፁሁፍ መልዕክት አስተላልፎአል መልስ ሰጪ ድርጊቱን አምኗል። ፍ/ቤት በመልስ ሰጪ ላይ ያቀረብነውን የቴክኒክ ማስረጃ ሣይመረምር የግባኝ ባይ በስር ፍ/ቤት መብቱን ጠብቆ ቃሉን ሰጥቷል በማለት በነፃ እንዲሰናበት የሰጠው ብይን አግባብ አይደለም ምክንያቱም የስር ተከሣሽ የአሁን መልስ ሰጪ የፈፀመው ድርጊት ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን የፈፀመው የወንጀል አድማ ስምምነት (Conspiracy) ሲሆን ማስረጃው ሊሚዘንልን የሚገባው የሽብር ቡድኑ ይዞት ከተነሳው ዓላማና ግብ መሆኑ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ተሽሮ መልስ ሰጪ እንዲከላከል ብይን እንዲደሰጥልን በትሕትና እናመለክታለን።

ብርሃኑ ወ/አገኝ
ፌ/ዐቃቤ ሕግ

ግሥ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

1569

http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.....
Re.NO
ቀን.....
Date

ፍ/ቤት ቀርበው የምስክርነት ቃል ከሰጡት በተጨማሪ የሰነድ ማስረጃ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/27/2/ መሰረት የሰጠው ተከሣሽ የእምነት ቃል፣ የተለያዩ የቅስቀሳና የአመፅ ጥሪ ሲያስተላልፉ የነበሩ የሰነድ ማስረጃ ደምፅ ከምስል VCD በሃይማኖት ሽፋን ቅስቀሳ ሲደርጉ የነበሩ እና በአካላቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው የፖሊስ አባላት የሕክምና ማስረጃ በንብረት ስለደረሰው ጉዳት የሚገልጽ ማስረጃ ከክስ ማመልከቻችን ጋር በመያይዝ አቅርበናል፡-

24ኛ ተከሣሽ ሀሰን አቢ ላይ በስር ፍ/ቤት የቀረበው ክስ የኮሚቴውን የሽብር ዓላማ እና አጀንዳ በመቀበል ይህንኑ አጀንዳ ለማስፈፀም በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ልዩ ቦታው አወሊያ መስጊድ በተሰበሰበው ሕዝብን ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው ግጥሞችን ወደ መድረክ እንዲቀርቡ በማድረግ እንዲሁም መስጊዱን በመቆጣጠር እና ሰዎችን በመፈተሽ የተሳተፈ በመሆኑ እንዲሁም ከ28/08/2004 ዓ.ም እስከ 20/10/2004 ዓ.ም ድረስ ላልታወቁ ግብረአበሮቹ አወሊያ በሚቀጥለው ሳምንት የጁምአ ትግላችን ይቃጥላል እኛ የመቱ ሙስሊሞች በደህና እንጠራ ነበር በአሁኑ ሰዓት ግን እስልምናችን እየተረገጠ ይገኛል፣ ሙስሊሞች ለመሆኑ በሕይወት እያለን ሃይማኖታችን የማንም አይሁድ እና የማንም ለሆዳቸው ባደሩ መናፍቅ ካድሬዎች ማጫወቻ መሆን የለበትም፣ ወይም እንዴት ይሆናል የመቱ ሙስሊሞች ፀጥ ብለው አክራሪ ያልሆኑ ስልጠና መከታተላቸው ትክክል አይደለም ወኔ ይጐድላቸውል በአንዋር መስጊድ ለሚደረገው ተቀውሞ አፋቸውን የሚለጥፉበት ፕላስተር፣ ማዘጋጀቱንና የሚበተን ወረቀት እንደያዘጋጀ መመሪያ በመስጠት፣ በተለይም ሚያዚያ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ለ4ኛ ተከሣሽ ለሆነው ካሚል ሸምሱ ስልክ በመደወል ለሕገ-ወጥ ሰልፍ እንደዘጋጁ የድምፅና ፁሁፍ መልዕክት በማስተላለፍ ክስ ቀርቦበታል ማስረጃ በሚመለከት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ ሕ/ቁ/27/2/ መሰረት በሰጠው የእምነት ቃል ድርጊቱን ስለመፈፀሙ አረጋግጧል ከተከሣሽ መኖሪያ ቤቱ በብርበራ ሲደረግ የነበሩ ታዛቢዎች የቅስቀሳ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

1370

http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.....
Re.NO
ቀን.....
Date

ሃይማኖታዊ አስተማሪዎችን ሊመሩት ይገባል በማለትመድረኩን በመቆጣጠር በካሴዱት ምርጫ የመስሊሙ ሕብረተሰብ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ በማለት ሰይመው፣ በሕዝቡ የተወከሉ ለማስመሰልና ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት ፊርማ በማስባሰብ፣ የተማሪዎቹን ጥያቄ ለሽብር ዓላማቸው በሚመች መንገድ በመቀልበስ ሂደቱን በመቆጣጠርና በመምራት፣ የሽብር ዓላማቸውን ለማስፈፀም ከጥር 5 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በየሣምንቱ አርብ ለፀሎት በአወሊያ መስጊድ ለሚሰባሰበው ሕዝብ የሽብር ዓላማቸውን ለማራማድ በአዲስ አበባና በክልሎች ባዘጋጁት የሰደቃ እና የአንድነት ዝግጅቶች በማለት ለሚጠሩት ሕዝብ፣ በማህበራዊ ድህረገፆች፣ ለዚህ ተግባር በተቋቋሙት የተለያዩ ሃይማኖታዊ መገናኛ ብዙሃኖች በመጽሐፍት በራሪ ጹሁፎችና ዘጋቢ ፊልሞች አማካይነት የሙስሊሙ ማህበረሰብ የእምነት ነፃነቱ ያልተከበረ ሃይማኖታዊ ነፃነቱን የተነፈገ እንደሆነ፤ መንግስት እንደቀድሞ ሥርዓቶች እስልምናን በተቀነባበረ መንገድ እየጨቆነ እንደሆነ፣ ሃይማኖቱን በግድ እንዲቀይር እያደረገውና ሆነ ተብሎ በከፍተኛ ትምህርት እንዳይማር እየተደረገ እንደሆነ በማስመሰል፣ ሕዝብ ሙስሊሙ ጀህድ በመውጣት ሃይማኖትህን ነፃ ልታወጣ ይገባል!! ገዢው መንግስት አያስተዳደረንም! ከአክራሪ አስተምሮት ውጪ የሚያስተምሩ ኢማሞችን መግደል ጀህድ ነው! ሌላው አስተምሮት ከኢትዮጵያ ተጠራርጉ እስካ ልወጣ ድረስ ትግላችን እስከ ሕይወት መሰዋእትነት ለመክፈል መዘጋጀት አለብን፣ በማለት ሕዝቡን ለሽብር ዓላማቸው በመቀስቀስና በማነሳሳት ሲሆን በተለያየ ጊዜ የዓመፅ ጥሪ በማስተላለፍ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ በኮልፌ ቀ/ክ/ከተማ በአንበሳ አውቶቢስ ላይ ጉዳት ደርሷል። ሕግን ለማስከበር በተሰማሩ የፖሊስ አባላት ላይ በአካላቸው ላይ ጉዳት አድርሰዋል፣ በባንክ ቤት በንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል። የአሁን መልስ ሰጪ የክስ ማመልከቻ ደርሶት እምነት ክህደት ተጠይቆ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለቱ ዓቃቤ ሕግ ከግብረአበሮቹ ጋር ከ101 በላይ የሰው ማስረጃ አቅርቦ አሰምቷል፤ ቀጥታ ማስረጃ፤ አካባቢና የተከሣሾች መኖሪያ ቤት ሲፈተሽ በብርበራ ወቅት የነበሩ ታዛቢ ምስክሮች እንዲሁም በእራሳቸው ፍቃዳኝነት ከኢሚይል ሲያወጣ በነበሩ ተከሣሾች ላይ ታዛቢ የነበሩ ምስክሮች

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

1571

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር.....
Re.NO
ቀን.....
Date

የተመለከተውን በመተላለፍ ሲሆን ዝርዝሩ፣ ተከሣሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን እና የወንጀል አድማ ስምምነት በማድረግ፣ በመላ ሀሰባቸውና አድራጎታቸው የወንጀል ድርጊቱን እና ወንጀሉ የሚሰጠውን ውጤት ሙሉ በሙሉ በመቀበል እና የራሣቸው በማድረግ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት ከተረጋገጠው የእምነት ነፃነት በመቃረን ከራሣቸው አክራሪ አስተሳሰብ አስተምህሮት ውጪ መኖር የለበትም በሚል ሃይማኖታዊ ዓላማ እና በሀገሪቱ ሃይማኖታዊ መንግስት ማቋቋም /መመስረት/ የሚል የፖለቲካዊ ግብ በማስቀመጥ ቀኑና ወሩ በውል ተለይቶ ካልታወቀበት ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የሃይማኖት አስተማሪዎች ቡድን በማለት በሕቡዕ ባቋቋሙት ቡድን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅድ በማውጣት እና እስትራቴጂዎችን በመንደፍ በተለይም የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማቋቋም እና በነዚህ ድርጅቶች አማካኝነት የሸብር ዓላማቸውን ለማስፈፀም አክራሪነትን በማስፋፋት ከፍተኛ መጠን ያለውን ገንዘብ ከተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ምንጮች በማሰባሰብና በማሰራጨት፣ ከመጀሊስ እውቅና ውጪ አክራሪነትን ለማስፋፋት የሚረዱ ተቋማትን በማቋቋም፣ አክራሪነት የሚሰብኩ መገናኛ ብዙሃንን በመመስረትና በመጠቀም በሃይማኖታዊ ፅንፈኝነትና በአክራሪነት ዙሪያ በውጭ ሀገር ስልጠና በመውሰድና የተጻፉ መፅሐፍቶችን ከተለያዩ ሀገራት በማሰመጣትና መፅሐፍቶች ላይ ሃይማኖታዊ መንግስት ለመመስረት ስለሚቻልበት ሁኔታ ውይይት በማድረግ፣ የዝግጅት እንቅስቃሴ ሲያደርጉ፣ ከቆዩ በኋላ በታህሣሥ ወር 2004 ዓ.ም በኮልፌ ቀ/ክ/ከተማ ክልል ውስጥ በሚገኘው አወልያ ኮሌጅ የኮሌጁ ተማሪዎች ካነሱት አስተዳዳራዊ ጥያቄ ጋር ተያይዞ የተነሳውን አለመግባባት የሸብር ዓላማቸውን ለማስፈፀም እንደመልካም አጋጣሚ በመቁጠር፣ የተማሪዎቹን ጥያቄ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ መፍትሄ የሚያፈላልግ ኮሚቴ በሚል የሸብር ቡድኑን ዓላማ የሚያስፈጽም ኮሚቴ እርስ በራስ በመመራራጥ የሸብር ቡድን አቋቁመው ወደ አወሊያ በመሄድ፣ በሕዝብ የተመረጡ ለማስመሰል አስቀደመው ባቀዱት መሰረት የተማሪውን ጥያቄ

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 የመ.ሣ.ቁ. 1870 ፖስታ ቤት አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተሰለጠ ሠራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

The Federa Democra Ministry o of Ethiopia Justice Invest igation and Prosecutio Process

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በፍትህ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of justice

ቁጥር 5/መ/ቤ/ም/ዐ/ሥ/2148/06
Re.NO
ቀን 13-05-2006
Date

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

አዲስ አበባ

ፌ/ከ/መ/ቀ.124754

የግባኝ ባይ..... የፌደራል ማዕከል ዐቃቤ ህግ

መልስ ሰጪ.....ሀሰን ዓቢ ሰኢድ

በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/189/1/ መሰረት የቀረበ የይግባኝ ቅሬታ

ይግባኙ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ታህሣሥ 3 ቀን 2006 ዓ.ም በመ/ቁ/ 124754 በሰጠው ብይን ላይ ቅር በመሰኘት ነው።

የይግባኝ ቅሬታ አቀራረቡ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/187/1/ እና /2/ ስር ያለውን የሕግ ድንጋጌ እና ጊዜ የጠበቀነው፣-

የቅሬታችን ዋና ፍሬ ጉዳይ በአሁን መልስ ሰጪ ላይ እነ አቡበክር መሀመድ 32 ሰዎች በተከሰሱበት የሽብር ወንጀል ክስ ተከሣሽ /መልስ ሰጪ/ 24ኛ ተከሣሽ በመሆን በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ 32/1/ሀ/፣ /ለ/ እና /38/ እንዲሁም በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3/1/2/፣ /4/፣ /6/ እና አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ክስ ቀርቦበት በነፃ እንዲሰናበት በሰጠው ብይን ላይ ቅር በመሰኘት ነው።

የይግባኙ ዝርዝር

የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመልስ ሰጪ እና በግብረአሮቹ ላይ የመሰረተነው ክስ፣

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ለ/፣ 38/1/ እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3/1/፣ /2/፣ /4/፣ /6/ እና አንቀጽ 4 ስር

ቴሌ ፋክስ 755061 ስልክ 764014 ፖ.ሣ.ቁ. 1370 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Fex ---------- Tel. 51 50 99 P.O. Box 1370 Addis Ababa Ethiopia
" ፍትህ በተለወጠ አመራር ፣ በተለወጠ ሥራተኛ ፣ በተለወጠ ተቋም ፣"

1573

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውሣኔ መስጠት የስራ ሂደት

የወ/ይ/መ/ቁ 97182

መጋቢት 10 ቀን 2006 ዓ/ም

ለ ሀሰን ኸሊፋ አሊሞ መሐመድ

ከኮሰን 10/7/07

በይግባኝ ባይ/ዎች፡- 1ኛ ኮሎኔል መለሰ ካሳ መሸሻ ሃ/ማ.

2ኛ _____

በመልስ ሰጭ/ዎች ፡- 1ኛ/ ሰሎሞን ልጋ

2ኛ/ _____


ችሎቱ ይግባኝ ባይ በ ግሩ 13 ቀን 2006 ዓ.ም

አዘጋጅተው ያቀረቡትን የይግባኝ ማመልከቻ እንደተመለከተው ቅሬታው ግራ ቀኙ በተገኙበት መጣራት ያለበት ሆኖ ስላገኘው መልስ ሰጭ 5 ገጽ የይግባኝ ቅሬታና ይህ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ደርሶት መ3ዚ91 ቀን 2006 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ለቃል ክርክር ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 1ኛ ወንጀል ችሎት አዟል፡፡

ዳኛ ባላቸው አንሺሶ ኬሞቤሜ
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ዳኛ

ETHIOPIAN CRIMINAL LAW NETWORK

http://ethcriminalawnetwork.com/



የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የውሳኔ መስጠት የሥራ ሂደት

03/8/06 የወ/ይ/መቁ. 97182

ቀን 01/08/2006

ለ ከፍተኛ ፓሊስ መኮንን ሃይማኖት ገብረ ሕይወት

በይግባኝ ባይ/ዮች፡- 1. ፖሊስ መኮንን ሃይማኖት መኮንን ሀገሩ

2. _____

መልስ ሰጪ/ዎች፡- 1. ሀለን አሊ አማዲ.

2. _____

ችሎቱ ይግባኝ ባይ በ 4/5/13 ቀን 2006 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡትን የይግባኝ ማመልከቻ እንደተመለከተው ቅሬታው ግራ ቀኙ ባሉበት በተገኙበት መጣራት ያለበት ሆኖ ስላገኘው መልስ ሰጪ 5 ገጽ የይግባኝ ቅሬታ ማመልከቻ ከመጥሪያ ጋር ደርቧቸው ሚያዝያ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለሆነው ቋጠሮ ለቃል ክርክር ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ፡፡ መልስ ሰጪ በቀጠሮ ቀን 2:30 ሰዓት እንዲቀርቡ መጥሪያ እንዲያደርሱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለፖሊስ ወንጀል ችሎት አዟል፡፡

በላቸው አንዳርጎ ኬምቤማ
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ዳኛ

1579

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የውሣኔ መስጠት የስራ ሂደት

የወ/ይ/መ/ቁ 97182

ማርች 01 ቀን 2006 ዓ/ም

ለ ሀጽ ከሽ ኦሊሳ 03/8/06

ጠበቃ

በይግባኝ ባይ/ዎች፡- 1ኛ ፖሊስ መሰላስ ሀይሉ

2ኛ

በመልስ ሰጭ/ዎች ፡- 1ኛ/ አቶ ኦርዲላ

2ኛ/

ችሎቱ ይግባኝ ባይ በ ጥር 13 ቀን 2006 ዓ.ም


አዘጋጅተው ያቀረቡትን የይግባኝ ማመልከቻ እንደተመለከተው ቅሬታው ግራ ቀኙ በተገኙበት መጣራት ያለበት ሆኖ ስላገኘው መልስ ሰጭ 5 ገጽ የይግባኝ ቅሬታና ይህ የፍ/ቤቱ ትእዛዝ ደርሶት ማርች 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ለቃል ክርክር ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 1ኛ ወንጀል ችሎት አዟል፡፡

በላቸው አንሺሶ ሌምቤሞ
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ዳኛ

1506

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/



የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የውሳኔ መስጠት የሥራ ሂደት

የወ/ይ/መቁ. 97182

ቁጥር

ቀን 6/10/2006

[illegible] 06 10

ቢይግባኝ ባይ [illegible]

በመልስ ሰጭ [illegible] መካከል ሰላለው

[illegible] የወንጀል ይግባኝ ክርክር ጉዳይ

ጠ/ፍ/ቤት ውሳኔ መስጠት የሥራ ሂደት ወንጀል ችሎት 29/4 ሠሚ ቀን

2006 ዓ.ም. ይግባኙን ባለመቀበል ውሳኔ ሰጥቷል።

ስለዚህ የውሳኔው ትክክል ግልባጭ 2 ገጽ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ላክን መሆኑን እገልፃለን። በዚህ ጉዳይ መዝገብ ያልተላከልን መሆኑን እናሰታውቃለን።

6/10/06

መንበረ ነጋሽ
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት
ም/ሬጅስትራር

1578

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ቀን 05/10/06

ከመረጃ ክፍሉ የሚፈልጉትን መረጃ አይነት በመፃፍ ወይም ፊት ለፊት የ ✓ ምልክት በማድረግ ይስተናገዱ::

❖ መረጃ የሚጠይቁት ችሎት፡- ሰበር ☐
ወንጀል ☑
ፍትሐብሄር ☐

- መረጃ የሚጠይቁበት መዝገብ ቁጥር 97182
- የቀልኩበት ማስረጃ ይሰጠኝ _____
- የመ/ቤቱ ስም _____
- ስለ ወደፊት ቀጠሮ ይገለፅልኝ _____
- በቀጠሮ የቀረብኩባቸው ቀናት ይሰጠኝ _____
- የውሳኔ /ትዕዛዝ/ ቅጂ ይሰጠኝ ✓
- የውሳኔ/ ትዕዛዝ/ ቅጅ በመሸኛ ይሰጠኝ _____
- ከመዝገብ ውስጥ የሚገኝ የውሳኔ /ትዕዛዝ/ እንዲሁም ልዩ ልዩ ማስረጃዎች ኮፒ እንድወስድ ይፈቀድልኝ

_____

የአመልካች ስም ~~ሀሰን ጀማል ሰዲቅ~~

ፊርማ _____

ተቀብያለሁ (ወሰድኩ)

1579

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወንጀል ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ጥር 22 ቀን 2005 ዓ.ም

ዳኞች:- ብሰራት ተህልቆ

ባህሩ ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ:- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድምአገኝ ቴዎድሮስ ጌታቸው እና ዘረሰናይ ምስግና ቀርበናል

ተከሳሾች:- እነአቡበክር አህመድ 31 ሰወች ከ1-29 ተከሳሾች ከማረሚያ ቤት በአጃቢ ሆነው ቀርበዋል 30ኛ እና 31ኛ ተከሳሾች የህግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ናቸው የተከሳሾች ጠበቆች ሃሰን ሁሴን ተካ ዳባ ባህሩ መካምጋና ሃሊማ ሰይድ /የማይሰማ/ አህመድ ጀማል

- መዝገቡ ባዳሪ ተቀጥሮ የነበረው የአቃቤ ሕግ ምስክሮች መስማት ሂደትን ለመቀጠል ተብሎ ነበረ በዚሁ መሰረት አቃቤ ሕግ ምስክሮቹን ማቅረቡ ተረጋግጧል ማን ነው የቀረበው ስንተኛ ምስክር ቃለመሃላ ፈጽሙ
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- እሺ ምስክር ከሳሽ አቃቤ ሕግ የእርስዎን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ሙሉ ስሞ እንዳይገለጽ በጠየቀው መሰረት ፍ/ቤቱ ይሄን ተቀብሎ የመጀመሪያ ስሞን ብቻ ነው የሚጠይቀው አድራሻዎም እንደዚሁ አይገለጽም ስለዚህ የመጀመሪያ ስሞን ብቻ ይነግሩናል

1586

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስሞ ማን ነው ?
- ኑረዲን
- ለምን መጡ ዛሬ?
- ለምስክርነት
- ተከሳሾቹን ያውቋቸዋል እንዴ?
- /የማይሰማ/
- ማን ማን ላይ ነው ሊመሰክሩ የመጡት?
- ሙራድ ሽኩር
- ሙራድ ሽኩርን ያውቁታል በአካል ይለዩታል ?
- በአካል እለየዋለሁ
- እስቲ አንዴ ተከሳሾች
- የትኛው ነው እሺ ምስክሩ 10ኛውን ተከሳሽ በመለየት አሳይተው እምመሰክረው በሱ ላይ ነው ብለዋል የከሳሽ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ አቶ ኑረዲን አሁን ጠቁመው ያሳዩት ተከሳሽ አደረገ የሚሉትን ድርጊት በዝርዝር ያስረዳሉ ከጊዜው ይጀምራሉ ጊዜውን ያስታውሳሉ አቶ ኑረዲን አይሰማም ጊዜውን ያስተውሳሉ ከጊዜው ጀምሮ እስቲ የሆነውን ነገር በዝርዝር ?
- በያም 15 መሃል አካባቢ
- ወሩ ምንድን ነው?
- ወሩ ነሐሴ መጀመሪያ ሐምሌ መጨረሻ አካባቢ ይመስለኛል
- ስንት ዓመተምረት?
- 2004
- እሺ?
- እና በዛ ሰዓት ሙራድ ሽኩር ያም ነበረ በአመት ዘካ የሚወጣበት ሰዓት ነው ከያሙ አብሮ ማለት ነው እኔ ነጋዴ እንደመሆኔ መጠን ባለኝ ንብረት በየአመቱ ዘካ እወጣለሁ እና ይሄ ተከሳሽ ኮሚቴዎች ተቸግረዋል ቤተሰቦቻቸው ተቸግረዋል ለነዚህ ኮሚቴዎች የሚሆን አመታዊ ዘካ ያላቸው ሰወች እንጠይቃለን ነጋዴ እንደመሆንህ መጠን አንተ ይዜንን ብር ልትሰጠኝ አንተጋ መጥቻለሁ የሚል ይጠይቀኛል
- የምን ዘካ ነው?
- አቤት
- የምን ብር ነው?
- የዘካ
- ምንድን ነው ዘካ?
- ዘካ ማለት ሰው ካፈራው ንብረት 2.5% በየዓመቱ ያው በሙስሊም ኃይማኖት መሰረት ይወጣል ያ ገንዘብ ማለት ለተቸገሩን የሚበሉት ላጡ ችግር ላለባቸው ያው በኃይማኖት መሰረት የተለዩ ጉዳዮች ችግሮች አሉ ያ ማለት ለተራበ
- ስለዚህ ሙራድ ምንድን ነው ያደረገው?
- ሙራድ ቀጥታ እነዚህ ታሳሪ ኮሚቴዎች ብዙዎቹ ደራሶች ናቸው ችግሮች ናቸው ቤተሰቦቻቸው ቀሊለኤል የሌላቸው ብዙዎቹ አሉ ብዙ ነጋዴዎችን የተወሰነ ጠይቀናል

1582

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

አንተም እንደ ነጋዴነትህ ይሄንን አመታዊ ግዴታ የሆነብህን የዘካ ብር ለሌሎች እንደምትሰጠው ሁሉ ለነዚህ አካሎችም ይገባቸዋል

- እነማን ናቸው እነዛ ኮሚቴዎቹ?
- ኮሚቴዎቹ ያው በየጊዜው ስማቸው የሚገለፀው እነአቡበክር አህመድ
- ሌላስ ?
- ሌላ ያው ያሲን ኑሩ እነዚህ እነዚህ ማለት ነው
- ይቀጥሉ ይጥሩልኝ እሚያስታውሷቸውን ይጥሩልኝ ?
- ያው እኔ ብዙ ጊዜ ሚዲያ የምሰማቸው ያሲን ኑሩ ፣አቡበክር አህመድ ፣አህመድ ሙስጠፋ ፣ ካሚል ሸምሱ፣ ጀሚል ያው ብዙ ጊዜ ሚዲያ የምንሰማቸው
- እነዚህን ሰወች በአካል ያውቋቸዋል?
- እነዚህ ሰወች ያው መድረክ ላይ ኃይማኖታዊ አስተማሪዎች ስለሆኑ መድረክ ላይ ብዙ ጊዜ አያቸዋለሁ ከዚህም ድርጊት በፊት ሁሌም ያው መድረክ ላይ አስተማሪዎች ናቸው
- ስለዚህ አሁን የጠሯቸውን የኮሚቴ አባሎች መለየት ይችላሉ እስቲ ይሞክሩ አሁን ያሉን አቡበክር አህመድ፣ አህመድ ሙስጠፋ ፣ካሚል ሸምሱ አሁን የጠቀሷቸው ሰወች አሉ አደለ እነሱን ነው የሚያስታውሱ ከሆነ የነሱና ያሳዩን ይነሱ?
- መቃወሚያ ምንድን ነው ?
- በስንተኛ ተከሳሽ ላይ ነው ለመመስከር የመጡት ሲባሉ በ10ኛ ላይ ተብሏል አቃቤ ሕግ ከዚህ ባለፈ ስለኮሚቴም ጠየቀ አቶ ሙራድ ኮሚቴም አደሉም ናቸውም እላሉም ስለዚህ ስለኮሚቴ ሞጠየቅም አይችሉም እንደገና ስለነዚህ ተከሳሾች ማን ናቸው አሳይ ካስያዘው ጭብጥ በጣም ይለያል ነው ስለዚህ ይሄን ነገር ማስረዳት መጠየቅም አይችልም በግልጽ ለፍ/ቤቱ 10ኛ ተከሳሽ ላይ ነው የሚመሰክሩት ብለዋል ከ10ኛ ተከሳሽ ውጪ የሚያስረዱት ነገር ሊፈቀድላቸው አይገባም ነው
- እሺ አቃቤ ሕግ መልስ ስጡ
- ጭብጥን የሚወስነው የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር አደለም አቃቤ ሕግ ነው ጭብጥን የሚወስነው እና የምናስረዳውን ጭብጥ ቀደም ብለን ባስያዝነው መሰረት እየቀጠልን ያለነው ምስክሩ በሱ አረዳድ ቅድም እመሰክራለሁ ያለውን ሰው በቀጥታ የሚያውቀውን ሰው መስክሯል አሁን በምስክርነት ሂደቱ እነዚህ እነዚህ ሰወች የኮሚቴ አባሎች ናቸው ብሎ እራሳቸው ምስክሩ ሲናገሩ ከነበሩት ስለገለፁ እነዚህን ሰወች በአካል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ያውቃሉ ወይ ጠቁመው ያሳዩ ማለት ምንም ችግር የለውም 2ኛ የስነስርዓት ግድፈትም የለውም ምክንያቱም የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ሕግ ቁጥር 137 አንድ ምስክር በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ የሚያውቀውን ነገር እንደሚያስረዳ ስለሚያዝ በተከበሩ ጠበቃ የተነሳው መቃወሚያ ውድቅ እንዲደረግልን ነው የምናመለክተው

- መቃወሚያው ቀርቧል መልስ
- ሰጥተውበታል ትእዛዝ ነው የሚሰጠው ስነስርዓት ሕጉም ያንን ነው የሚያዘው
- ጥያቄውን አንስታችኋል?
- አይ ለእሳቸው
- ጥያቄውን ካላነሳችሁ ተውት አሁን የጠየቅናችሁን ጥያቄ
- በመሰከሩበት ነገር ላይ መልስ ወይም ጥያቄ መጠየቅ ትችላላችሁ ስለዚህ ምስክርነቱ ቀጥሎ ጥያቄ
- እንተወው ነው ጥያቄውን አንስተናል ነው
- ጠይቁ ብቻ እንዳንባል ነው ስለኮሚቴ ስለጠየቁ አሁን ጥያቄያችንን ለማንሳት በኋላ በመስቀለኛ ጥያቄ ስለኮሚቴው እንድንጠይቅ የሚፈቀድ ከሆነ ይጠይቁ እንዳንገደብ ነው በኋላ የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄ ከሆነ ምስክሩ ያነሳውን አቃቤ ሕግ ያነሳውን ኤኒ ጥያቄ የመጠየቅ እኔ ይሄ የሚጠፋችሁም አይመስለኝም
- አይ እንዳንከለከል ነው በኋላ
- በሉ ቀጥሉ
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እሺ ምስክር አሁን የጠቀሷቸውን ሰወች እስቲ የሚያስታውሷቸውን ይነሱና ያሳዩኝ አቶ ኑረዲን አልሰሙኝም ቅድም አቋርጠኖት ነበረ ቅድም ያሳዩ እሚያስታውሷቸውን ?
- ጥያቄውን እንደገና ጠይቋቸው እና አስታውሷቸውን ጥያቄውን
- እሺ ቅድም አቡበክር አህመድ፣ አህመድ ሙስጠፋ ፣ ካሚል ሸምሱ ፣ ያሲን ኑሩ እያሉ የጠቀሷቸው ስሞች አሉ ለኮሚቴ አባሎች ገንዘብ ሰብስበዋል ብለውናል እና ከኮሚቴ አባሎች ደግሞ እነዚህን በስም በተደጋጋሚ ስለሚነሱ አውቃለሁ ብለዋል እነዚህን ሰወች በመልክ እማስታውሳቸውን ልጠቁም ስላሉ ይነሱና ይጠቁሙ እስቲ ?
- እንግዲህ ይቻልኩትን ልሞክር
- አሞ የቻሉትን አይ አይጨነሱ

1584

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተቃውሞ አለን አቃቤ ሕግ ምስክሩ ያላሉትን ነገር ነው አህመድ ሙስጠፋ ብሎ አልተናገረም እኮ 2ኛ የኮሚቴ ቤተሰቦች ነው እንጂ ያሉት ለኮሚቴ አባላት እረዳለሁ አላሉም ለኮሚቴ አባላት ቤተሰቦች ነው በግልጽ ያሉት ፍ/ቤቱም የመዘገበ ይመስለኛል እንጂ ለኮሚቴዎቹ እረዳለሁ አላሉም ስለዚህ በዚህ ጭብጥ ላይ በድጋሚ ሊጠየቁ አይገባም ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- የተከበረው ፍ/ቤት ስነስርዓታዊ ነው ወይ ይሄ ግን ብይን ተሰጥቶ የለ አሁን ከ1 ደቂቃ በፊት ነው ብይኑ የተሰጠው በዚሁ ጉዳይ ላይ ጥያቄውን ድገም ስለተባልኩኝ ነው የደገምኩት ሌላ የተለየ ነገር አደለም እና ያልነው ምስክሩ ከዛ አሁን ይሄ መቃወሚያ ከቀረበ በኋላ የመሰከሩት ነገር የለም ተነስተው እንዲጠቁሙ ነው የነገርናቸው እኛ
- /ግልጽ ያልሆነ/
- ሙስጠፋን እራሳቸው ነው ያሉት አሁን ፍ/ቤቱ መጠየቅ ይችላል ምስክሩን ኮሚቴ ምናምን ለነሱ ነው የተሰበሰበው አደለም በኋላ ምስክሩ ስለሚያስረዳ እሱን እኛም አሁንም ባይመዘገብ ችግር የለብንም በኋላ ምስክሩ ያስረዳል እሱ ሙሉ ነገር ስላላስረዳ ገና መሃል ላይ ነው ስማቸውን ሲጠቅስ ጠቁም ያልነው እና እሱ በዛ መልኩ ቢታይ አለመመዝገብ ይችላሉ እሱ
- ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ብይን ሰጥቷል በተከሳሾች ጠበቃ የተነሳው መቃወሚያን በተመለከተ የመጀመሪያው መቃሚያን ፍ/ቤቱ እንደተመለከተው አህመድ ሙስጠፋ የሚለው ስም ምስክሩ ጠቅሰዋል ተመዝግቦ ያለ በመሆኑ ፍ/ቤቱ አልጠቀሱም ተብሎ የቀረበውን መቃወሚያ አልፎታል 2ኛውን መቃወሚያ በተመለከተ ከሳሽ አቃቤ ሕግም ምስክሩ በሂደት የሚመሰክሩት ነገር ስለሆነ እሱን ማንሳት እንችላል ያለ ስለሆነ ለምስክርነት መስማት ሂደቱ ይቀጥል ተብሏል
- እሺ ምስክር ይነሱና ይጠቁሙ እስቲ የሚያስታውሷቸውን?
- ይነሱ ይጠጉ ወደዛ
- አቡበከር የሚለዩ ከሆነ ያሳዩን የትኛውን ነው እሱን ነው ያሉት 2ኛ ላይ ያሉት አቡበከር ነው እሺ ሌላ ያሲንን ይለያሉ እሺ ሌሎቹንም መለየት ተመልሰህ የአንዱን ስም ታስመዘግባለህ አሁን ያልከውን
- ያው እንግዲህ ብዙ ጊዜ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ መድረክ ላይ ስማቸው ሲጠራ ነው በመልክ ደረጃ ግን ሁለቱን በደምብ ነው የማውቃቸው ሌሎቹ ላይ ትንሽ
- ሁለቱ ማለት?

158 S

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አህመድ ሙስጠፋ ካሚል ሽምሱ ሌሎቹ ትንሽ አሁን ያው ሳያቸው ግር ብሎኛል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት 4ኛ እና 8ኛ ተከሳሾችን ጠቁሞ አሳይቷል እሺ ምስክር ቅድም ሙራድ ሸኩር መጥቶ የዘካ ገንዘብ ብሎ ጠይቆኝ ነበር አሉ ሰጡት ?
- አዎ ሙራድ ለታሳሪ ቤተቦች ችግር ላይ ናቸው ቤተሰቦቻቸው ይሄን የዘካ ብር በእስልምና ኃይማኖት መሰረት ለ8 ዓይነት ቤተሰቦች ሊሰጥ ስለሚገባ የነዚህ ቤተሰቦች ችግርተኞች ናቸው እና ይሄንን ብር ይገባል ለሌላው አካል እንደምትሰጠው ያለህን ከዚህ አካፍለህ እንደምትሰጠኝ ይሄንን ልጠይቅህ መጥቻለሁ አለኝ ይሄ በዛው መሰረት እኔ ከዘካው ብር ሃምሳ ሺ ብር አንስቼ ሰጥቼዋለሁ
- በወቅቱ የታሰረ ሰው ነበረ?
- በወቅቱ እነዚህ ኮሚቴዎች ታስረዋል
- እነማን ናቸው ?
- እነዚህ አሁን የጠቀስኳቸው
- አሁን በስም የጠቀሷቸው?
- አዎ ሌሎች ያው ዝርዝር እያንዳንዱን አላውቅም
- ምን ያህል ብር ሰጡት?
- ሃምሳ ሺ ብር ሰጥቼዋለሁ
- ከዛስ?
- ከዛ በቃ ያንን ብር ይዞ ሄዷል
- አሁን ሲገልፁ 8 ዓይነት ዘካ አለ ብለዋል ከነዚህ ውስጥ አሁን የገለፁት ምክንያት ይካተታል?
- አዎ ይሄንን እነዚህ ሰወች ብዙዎቹ ነጋዴዎች አደሉም አሁን ቤተሰባቸውን መቀለብ አይችሉም እስር ቤት ነው ያሉት ስለዚህ የእለታዊ ወጪ ቤተሰቦቻቸው ማግኘት አይችልም ሕፃናቶች ሴቶች እናቶቻው መስጠት ይሄንን ኃይማኖቱ አንዱ የሚፈቅድላቸው ስለሆነ በእስር ላይ ስለሆኑ እነሱ ይሄ ነገር ያው ይገባል አለኝ እኔም ያው በራሴ ባለኝ እውቀት ይሄን ነገር ያው እነዚህ ምክንያቶች እስካሉ ድረስ እኔም ዘካ ከሚሰጣቸው አንዱ ነው ብዬ አምኜበት ያው የዘካውን ብር አንስቼ ሰጠሁ
- ግን ታሰሩ የተባሉ ሰወች እንደተባለው ችግርተኞች ስለመሆናቸው የሚያውቁት ነገር አለ እርስዎ?

1586

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ አሞ ሙራድ ሸኩር ማለት ያው መስኪድ አካባቢ እኔን ሲያስተምር 5 ዓመት ጀምሮ አውቀዋለሁ ኃይማኖት ያስተምራል ሲያስተምር አብዛኛው ተቸገሩ ያላቸውን እውነት ይሆናል በሚል ያው እሱን ተከትዬ ኃይማኖት አስተማሪ ስለሆነ ችግረኛ ያላቸውን ሰወች ያው ችግረኞች ቢሆኑ ነው በሚል ነው እሱን አምኜ
- እንጂ አላረጋገጡም ማለት ነው ?
- አሞ እነዚህ ሰወች ቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ ሂደታቸው ያላቸው ደሃ ይሁኑ ሃብታም ዝርዝር እንትናቸውን አላውቅም ያው ምስክርነቱ በቤታቸው ችግር መኖሩን ያው እሱ በገለፀልን መሰረት ነው
- ዋና ጥያቄ አበቃን
- ዋና ጥያቄ ቀርቦ ተጠናቋል የተከሳሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቡ ከዛ በፊት ዘግይታችሁ የመጣችሁ ጠበቆች ካላችሁ ስማችሁን አስመዝግቡ
- 28ኛ ተከሳሽ በስተቀር ላሉ ጠበቃ መሃመድ
- ጥያቄ አሁን በተነሳው ጥያቄ ላይ
- ቀጥሉ
- አቶ ኑረዲን ሙራድን ከሙራድጋር ያሎት ቀረቤታ ምን ያህል ነው ትውውቃችሁ?
- እኔ ሙራድ ከ5 ዓመት ጀምሮ መስኪድ ቁጭ ብሎ ሲያስተምር በሚያስተምርበት ሰዓት እኔም ተቀምጬ አደምጬዋለሁ በዛ መሰረት ያው መስኪድ አካባቢ ላይ እንደሚያስተምር ከዛ ጀምሬ አውቀዋለሁ
- በጥቅሉ ሌላም ሰው ሲያስተምር ነው ወይስ የእርስዎ የግል አስተማሪ ነው እንዴ?
- የለም ሁሉንም ሰው ግሩፕ ሰብስቦ ሲያስተምር አውቃለሁ
- ከዛ ውጭ የቀረበ ትውውቅ የላችሁም?
- አሞ ከዛ ውጭ በአስተማሪነቱ ቁጭ ብዬ የሱን ፕሮግራም በመከታተል በዛ ነው ያወቅኩት ያው ላምነው የምችለው በዚህ መድረክ ላይ ባለው አቋም ነው
- ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ዘካ ለሌሎች እንዲሰጥ ሰጥተውት ያውቃሉ ወይስ የመጀመሪያ ጊዜ ነው?
- ከዚህ በፊት እኔ ያው ዘካ በየዓመቱ ባወጣም ከዚህ በፊት ሰጥቼው አላውቅም አሁን ግን ቀጥታ ነጋዴ ነህና ንብረቶች አሉህ ዘካ ታወጣለህ ችግርተኞች እኔ እማውቃቸው እነዚህ የኮሚቴዎች ቤተሰቦች አሉና ስጠኝ የሚል ያው ጥያቄ አቀረበልኝ በዛ ሰዓት ያው ሰጥቼዋለሁ

1987

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ ሃምሳ ሺ ብር ሰጥቼዋለሁ ብለዋል ገንዘቡን በሰጡበት እለት ሃምሳ ሺ ብር ከባንክ አውጥተዋል ወይም ከዛ በላይ ?
- እኔ ያው ካለኝ ካፒታል ከባንክ አውጥቼ ቤቴ አስቀምጬ ለተቸሩ ችግር ላለባቸው ለድሆች ምስኪን ድሆች ሰጥቻለሁ
- በእለቱ አውጥተዋል ?
- መቼ
- ለሱ ከባንክ አውጥተው ነው የሰጡት?
- በእለቱ ከባንክ አደለም አውጥቼ የሰጠሁት ከቤት ለዚሁ ተለይቶ ከተቀመጠ ብር ነው
- እሺ ለሱ ከመስጠቱ አንድ ቀን ቀደም ወይም በዋዜማ አውጥተዋል ብር ከባንክ ?
- አዎ
- በዋዜማው ?
- ከዛ በፊት ያው በባንክ እኔ እንደምንቀሳቀስ በየጊዜው ያው አወጣለሁኝ በሳምንት 3 ቀን ሁለት ቀን ወደ ባንክ እመላለሳለሁ ያው ብሮች አወጣለሁ ለዚህ ጉዳይም ያው ለይቼ ቀኑ ምናልባት ለሱ የሰጠሁበት በዋዜማው ቀኑና ሰዓቱን ባለየውም አውጥቻለሁ
- ብሩን ሲሰጡት ሌላ ሰው ነበረ እንዴ?
- ብሩን ስሰጠው ሌሎች ሰወች አልነበሩም
- ብቻችሁን ናችሁ?
- ብቻችንን ነን
- የት ነው የሰጡት ብሩን?
- ብሩን እዛው ቤተል ነው የሰጠሁት
- ቦታውን ሊጠቅሱ ይችላሉ የሰጡበትን ?
- ቤተል አካባቢ ነው
- የሰጡትን የብር አይነት ያስታውሳሉ ምን አይነት ብር ነው የሰጡት ባለ መቶ ባለ አስር ባለ ሃምሳ ባለአንድ ብር ?
- ባለ መቶ ብር የታሸጉ ሃምሳ ሺ ብር ነው በየ አስር አስር ሺ ብር
- እንዴት ግን አሁን ይሄ ሃምሳ ሺ ብር ብዙ ብር ነው እንዴት አመኑት ?
- እኔ መድረክ ውስጥ ያስተምራል ምናልባት የማውቀው ከአምስት ዓመት ይሞሮ ነው ይሄን ሰው ኃይማኖትን ሲያስተምር ያው መድረክ ላይ ባለው ሁኔታ ተነስቼ ይሄንን ሰው ይታመናል ብዬ ያው በግል እንደራሴ አቋም አምኜዋለሁ

1584

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥሩ የሰጡት ለታሰሩ ቤተሰቦች ብሎ እንደወሰደ ነው የገለፁልኝ ትክክል ነው?
- አሞ እሱ ጥያቄ ቀጥታ አቀረብልኝ የዘካ ብር አንተ እጅ ላይ ለድሆች ትሰጣለህ እና እነዚህ ታሳሪ ቤተሰቦች ተቸግረዋል ለነዚህ ቤተሰቦች ገንዘብ ማድረስ መስጠት ይጠበቅብናል ሌሎችንም ነጋዴዎች ጠይቀናል አንተም የዘካውን ብር ለታሳሪ ቤተሰቦች ቀጥታ ስጠን የሚል ጥያቄ አቀረብልኝ በዚህም ቀን ሰጥቼዋለሁ

ECLN

158 9

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ በጠየቀው መሰረት ለታሳሪ ቤተሰብ አለመስጠቱን ያውቃሉ እንዴ?
- እኔ ይሰጣል በሚል አምኚ አስቤ ሰጥቼዋለሁ እምነቱም ይሰጣል ነው ከመነሻም ከዛ በኋላ ግን መጥቶ ሰጥቼዋለሁ ብሎ ዝርዝር እሪፖርት ያደረገልኝ ነገር የለም
- የለም አሁን ጥያቄው እርስዎ ለታሳሪ ቤተሰብ ገንዘብ እንዲሰጥ ሰጥተዋል ይስጥ አይስጥ እሚያውቁት ነገር አለ?
- እኔ ለታሳሪ ቤተሰቦች ይሰጣል በሚል እምነት ሰጥቼዋለሁ ከዛ በኋላ ግን ያው ለማድረሱ ያደርሳል የሚል እምነት ይኑረኝ እንጂ ማድረሱን የማውቀው ነገር የለም
- የታሳሪ ቤተሰቦች መጥተው አልደረሰኝም ብለው እርስዎ ያመለከቱት ነገር አለ?
- ለታሳሪ ቤተሰብ ያው እኔም ሄጀ አልጠየቅኩም እነሱም ቀጥታ የላክልን አልደረሰንም የሚል ጥያቄም አልቀረበም
- አቶ ኑረዲን ቅድም እነዚህ ሰወች ኮሚቴ መሆናቸውን አውቃለሁ ብለው ነበረ ካወቁበት ምክንያት አንዱ መድረክ ላይ ሲያስተምሩ ነው ብለዋል ከዚህ ውጪ በሚዲያ የሰሙት ነገር አለ ኮሚቴ ስለመሆናቸው?
- አዎ በየጊዜው ስማቸው ይጠቀሳል
- በምን?
- በሚዲያ በተለያየ በጋዜጣ በተለያዩ ጊዜያቶች ስማቸው ይገለፃል
- ለምሳሌ በምን አይነት ጋዜጣ በግል በመንግስት?
- በመንግስት ጋዜጣ በተለያየ ያው መስኪዶችም አካባቢ ኢንፎርሜሽን ያው ብዙ ቦታ ላይ የጣራል
- እነዚህ ሰወች የኃይማኖት አስተማሪዎች እንደሆኑ አውቃለሁ መድረክም ላይ ሰምቻለሁ ብለው ነበረ እና እነዚህ ሰወች በሚያስተምሩበት ወቅት ወይም በእርስዎ በተገኙበት መድረክ እነዚህ ሰወች ጥላቻን ያስተምሩ ነበር?
- ተቃውሞ አለኝ የተከበረው ችሎት
- ተቃውሞ አስመዝግቡ
- እ እኛ በዋና ጥያቄ ቅድም ያነሳነው የኮሚቴ አባሎች ብለው ሲጠቅሱ እነማንን ያውቃሉ ኮሚቴ አባሎች ብለን ስም ነው ያስመሰከርነው ስለ ሰበኩት ነገር ጭብጥ አላስያዝንም አላስመሰከርንም የዚህ ምስክርም እውቀት ውጪ ነው አሁን የተከበሩ ጠበቃ እያቀረቡ ያሉት ጥያቄ ጭራሽ ይሰብኩ ስለነበረው ነግር ይዘት ነው ችግር ነው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

የሚያስተምሩት ወይስ ሌላ ነገር ብሎ መጠየቅ በፍፁም አግባብነት ያለው ጥያቄ በዋና ጥያቄም ያልተነሳ እኛም ያላስመሰከርነው ነው ውድቅ እንዲደረግ ነው የምናመለክተው

- አሺ መልስ ስጡበት
- የተከበረው ፍ/ቤት ይሄንኑ ፊርቼ አስቀድሜ ጠይቄያለሁ እኔ ስለኮሚቴዎቹ ከተነሳ የት ያውቋቸዋል ሲያስተምሩ አውቃቸዋለሁ ብለዋል እኔ በተለያየ ቦታ ሲያስተምሩ አይቻለሁ ስላሉ እዛ በሚያስተምሩበት ቦታ ጽንፈኝነትን አቃቤ ሕግ እንደሚለው ያስተምራል ወይ የሚል ጥያቄ ነው ይህ ደግሞ በምን አወቃችሁ ሲባል መጀመሪያ በዋና ጥያቄ የተነሳ ነገር ስለሆነ እሳቸው በተገኙበት መድረክ ያዩትን ነገር ለፍ/ቤቱ እንዲያስረዱ ነው
- የቀረበውን መቃወሚያ እንዲሁም ምላሹን መርምሮ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል የቀረበው መቃወሚያ ምስክሩ የመሰከሩት የኮሚቴ አባላት ማን ማን እንደሆነ ለኮሚቴ አባላት ስለሚዋጣው ገንዘብ ጋር ተያይዞ የተነሳ ነው ጉዳይ በመሆኑ ምክንያት ምስክሩ ምን ያስተምሩ ነበረ የሰጡት ስብከት ሌላ ነገር ተቀላቅሎበት ሲያስተምሩ ነበረ ወይ ተብሎ የቀረበው ጥያቄ ካስመሰከርነው በዋና ጥያቄ ላይ ከተነሳው ነጥብ የተለየ ነው ስለዚህ ሊመሰከር አይገባም የሚል የአቃቤ ሕጉ መቃወሚያ በተከሳሾች ጠበቆች በኩል የቀረበው ይገናኛል ብለኮሚቴ ከተነሳ ኮሚቴዎቹ ሲሰሩ ስለነበረው ነገር ሁሉ ለማስመስከር እንችላለን ስለዚህ ጥያቄ ሊፈቀድ ይገባል የሚል ነው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የተመለከተው በአብላጫ ድምጽ የቀረበው ጥያቄ ሊቀጥል ይገባል ተብሏል ስለዚህ የአብላጫው ድምጽ ሊቀጥል ይገባል ተብሎ የቀረበ በመሆኑ ምክንያት ይሄው ጥያቄ ይቀጥል
- አቶ ኑረዲን መድረክ ሲያስተምሩ አውቅ ነበር ስላሉ በሚያስተምሩበት ወቅት የሚያስተምሩት ምን እንደነበረ እስቲ ለፍ/ቤቱ ያስረዱ?
- ምናልባት እኔ ኮሚቴዎቹ አብዛኛው ነጋዴ እንደመሆኔ መጠን ሰላት ሰግዶ መውጣት ካልሆነ በስተቀር አዘውትሬ ብዙ ጊዜ አልቀመጥም ግን ብዙ ጊዜ ያሲን ኑሩ አቡበከር አህመድ ካሴቶቻቸውን አደምጣለሁኝ እና በነዚህ ካሴቶች ያው በኔ እውቀት ሰላማዊ የሆነ እስላማዊ የሆነ ትምርት ነው የሚመሩት በነዛ ካሴቶች ባደመጥኩት ማለት ነው እነዚህ ካሴቶች ማለት የዛሬ አመት የዛሬ ሁለት ዓመት የተሰሩ ካሴቶች አሉ ያው እነሱ እነሱን አድምጬ በራሴ በኩል /ግልጽ ያልሆነ/ ነገር የለኝም ሌላው ደግሞ ምናልባት ባገኘሁት አጋጣሚ ከዚህ በፊት ምናልባት ይሄ ክሱ በተነሳበት ሰሞን ሳይሆን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ከነበረው ጊዜዎች መድረክ ላይ ካሚል ሸምሱን አድምጫለሁ እኔ ምናልባት ለአመጽ የሚያነሳሳ የሚለውን ነገር እራሴ የሰማሁት ነገር የለኝም

- እሺ እነዚህ ሰወች ሲያስተምሩ ቁርአንና ሃዲስ ይጠቅሳሉ ወይስ በግላቸው ነው የሚሰብኩት?
- ማንኛውም የኃይማኖት አስተማሪ ሲያስተምር ቁርአን እና ሃዲስ ተጠቅሶ ነው የሚያስተምረው የትኛውን ቁርአን እንደጠቀሱ ዝርዝሩን እኔ አሁን /ግልጽ ያልሆነ/ እርእሱን ባላስታውስም
- እሺ ሙራድንስ በተመለከተ ከ5 አመት በፊት ጀምሮ በአስተማሪነት ያውቁታል ከዚህ የተለየ ነገር አለ የአቶ ሙራድ?
- አቶ ሙራድ እኔ ከዚህ የተለየ ነገር የለኝም
- እሺ ቅድም በተከበሩ አቃቤ ሕግ ሲጠየቁ ቤተሰባቸው ችግረኛ መሆኑን አረጋግጠዋል ተብለው ነበረ እና ይሄ የዘካ ገንዘብ በሌላ ጊዜ ሲሰጡ ወይም ሲጠየቁ የድህነት ማረጋገጫ ይጠይቃሉ እንዴ እርስዎ?
- ጥያቄው ይደገምልኝ
- ጥያቄው ቅድም በአቃቤ ሕግ ሲጠየቁ ቤተሰባቸው ችግረኛ መሆኑን አውቀዋል ወይ አረጋግጠዋል ሲባሉ አላረጋገጥኩም ብለዋል በሌላ ጊዜ ዘካ ሲሰጡ ከዚህ በፊት ወይም በዛን ወቅት ዘካ ለሚሰጡ ሰወች ሲሰጡ ይሄንን ሲያደርጉ የቤተሰብ ደሃ መሆን ማረጋገጫ ይጠይቃሉ እንዴ እርስዎ?
- እኔ ዘካ በማንኛውም በምሰጥበት ጊዜ አንድ እራሴ በትክክል ያወቅኩትን እሰጣለሁ 2ኛ መስኪድ አካባቢ ያሉ ኢማሞች እከሌ እኛ የምናውቀው ችግረኛ አለ ካሉን በተመሳሳይ ለሙራድ በዚሁ መልክ የሰጠሁት እንዲሁም ደግሞ ሌሎች መስኪድ ኢማሞች መስኪዳችን አካባቢ በተለያየ ነገር ያሉ ችግረኞች አሉ እኛ የምናውቀው ድህነታቸውን እኛ እምንመሰክርላቸው ባሉኝ ሰዓት ሌላ እኔ እነዛን ሰወች በአካል መፈለግ ሳያስፈልገኝ እነዛን ሰወች አምኜ ሰጥቻለሁ ሙራድን በተመሳሳይ እነዚህ ሰወች ችግር አለባቸው ቤታቸው ውስጥ ልጆቻቸው ባለቤቶቻቸው የቤት ኪራይ የሚከፍሉት አጥተዋል የሚበሉት አጥተዋል እና ዘካ ይገባቸዋል ስጠኝ አለኝ ኃላፊነቱ የሱ ሆኖ እኔም ደግሞ አምኜው ሰጥቼዋለሁ
- እሺ ጨርሻለሁ አመሰግናለሁ
- መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የአቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ይቀረብ

1592

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ አቶ ኑረዲን ቅድም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ በመገናኛዎች በጋዜጣ እና በሚዲያ አውቃለሁ ብለዋል በየተኛው ጋዜጣ እና ሚዲያ ነው እነዚህ ሰወች ኮሚቴ ስለመሆናቸው የሰሙት ?
- ያው እኔ አሁን አንዴ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ቅርበ የትኛው እንደሆነ ባላስታውሰውም እነ አቡበክር አህመድ ኮሚቴዎች በሚል የታሰሩበት ሰሞን በተለይ ማለት ነው የዛን ነው የሰማሁት
- እኮ ኮሚቴዎች ናቸው ይላል ወይስ ዘገባ ነው በታሰሩበት ሰሞን የሚለው ዜና ነው ወይስ እነዚህ ኮሚቴዎች ናቸው ተብሎ ነው ዝርዝሩ ይዘቱን ይንገሩን የሚያስታውሱ ከሆነ?
- ይዘቱ እኔ አንድ የፌደራል ጉዳዮች ማ/ር ጠርቶ እነዚህ ሚዲያ ላይ የታዩበት ጊዜ አንድ እንትን ያልኩት እነዚህ የህዝብ ኮሚቴዎች በሚል ዛሬ 26 በሌሎችም ቀናቶች የፌደራል ጉዳዮች ቀጠሮ አላቸው ይወያያሉ የሚለውን ነው እንዲሁም ደግሞ በመንግስት ሚዲያ በቴሌቪዥን በዛን ሰዓት ላይ በጠረጴዛ ሰጥተው መቀመጣቸውን ያንን አስታውሳለሁ
- የትኞቹን እርግጠኛ ኖት አሁን እነአቡበክር አህመድ ናቸው በቴሌቪዥን ነው ያዩዋቸው ከመንግስትጋ ይወያያሉ ተብሎ በቴሌቪዥን ሲታይ?
- እኔ ያው መልክ ብዙ ጊዜ የምለያቸው አሁን የጠቀስኳቸው ሁለቱን ሰወች ነው ሚዲያ ላይ ግን የተወሰኑ ሰወች ቁጥር አለ በዛን ሰዓት የፌደራል ጉዳዮች ሚ/ር በሚያናግሩበት ሰዓት ያው የቀረቡትን ማለት ነው
- እኮ እዚህ ውስጥ አሁን ካዩዋቸው ውስጥ አይተዋል በቴሌቪዥን?
- አዎ አህመድ ሙስጠፋ እና ካሚልን አይቻለሁ ያው መልካቸውን ስለምለያቸው ማለት ነው የሌሎቹን ግን ለመለየት አልችልም
- ስለዚህ አሁን ሚዲያ የሚሉት በማንና በማን ነው?
- ሚዲያ በቃ መሰረት ያረግኩት ሚዲያ ኮሚቴ የሚለውን የፌደራል ጉዳዮችን የቀረበውን ነው ይበልጥ ደግሞ እኔ በመልክ ለይቼ አሁን የጠቀስኳቸው ካሚል ሽምሱ እና አህመድ ሙስጠፋ
- የሚለዩዋቸው?
- አዎ

ECHR

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ ቅድም አሁን በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠየቁ ዘካን በተመለከተ አረጋግጠው ነው ወይ የሚሰጡት የቤተሰብ ችግርተኛ የሚለውን ማስረጃ እያዩ ነው ወይ የሚሰጡት ሲባሉ እኔ ከዚህ በፊት የምሰጠው በኢማሞች ችግርተኞች አሉ ተብለው ሲጠይቁ እኛም እርግጠኞት ነን ማረጋገጫ እንሆናለን ሲባል ነው የምሰጠው ብለዋል በኢማሞች ነው እንዴ የተጠየቁት አሁን በዚህኛው በኢማሞች ተጠይቋል በመስኪድ ባሉ ኢማሞች ዘካ ይስጡ ለችግርተኞች ተብሎ ተጠይቋል?
- አዎ እንትን ነው ዘካ የአገራችን ላይ ሁሉ ያለውን ንብረቱን ካሰበ በኋላ ሰውየው የወሰነውን ዘካ ካወጣ በኋላ ግዴታ በነፍስወከፍ በግሉ ነው ውሳኔው የራሱ ነው ዘካ አውጪው አካል
- ገብቶኛል የራሱ ነው ግን ለሚሰጠው አካል ግን ያው መለየት አለበት አደለም?
- አዎ ለሚሰጠው አካል ለነዚህ ምስኪኖች ነው አብዛኛው እውቀቱ ብዙ ሙስሊሞች ያውወቁታል ነጋዴዎችም ማለት ነው የሚገባቸውን ሰወች ማለት ነው እና በዛን ሰዓት እኔ ያው ኢማሞችን ሲጠይቁ የመስኪድ ኢማሞች ሆነው ብዙ ችግረኛ ያውቃሉ በጠየቁ ሰዓት ያው ሰጥቻለሁ እንዲሁም ግለሰቦችን በተመሳሳይ እከሌ የሚባል እኔ የማውቀው ችግረኛ አለኝ እና ዘካ የምሰጣቸው ሰወች አሉ አምጣ ሲል ይሰጣል ያው የሞራልም በተመሳሳይ ይሄንኑ ያው ጥይቄ ሲያቀርብ ነው እሱን አንስቼ የሰጠሁት
- እሺ ኃላፊነቱ የሱ ይሆናል ብለዋል ኃላፊነቱ የሱ ይሆናል ማለት ምን ማለት ነው?
- በኃይማኖቱ መሰረት አንድ ሰው የቻልከውን ያህል ድረስ እኔ መድረክ ላይ ሲያስተምር አየሁኝ ምናልባት ይሄንን ገንዘብ ለግል ጥቅሙ አያውለውም እነዚህ ያላቸው ችግረኞች በትክክል ችግረኛ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል እነዚህ መሰረት አርገህ አንድን ሰው በእምነቱ መሰረት ማመን አይከለክልም ከዛ በኋላ እኔ ኃይማኖታዊ ግዴታዬ ነው ያንን ብር አወጣሁት ያንን ብር ለተገቢው ጉዳይ ባያውል በኃይማኖቱ መሰረት ያው ተጠያቂነቱ የሱ ነው እኔም ደግሞ ያው ግዴታዬን ተወጥቻለሁ በኃይ
- እኔ ማመን እና መስጠት ነው የሚጠበቅብኝ የሱ አላማ ምን እንደሆነ ማወቅ አይጠበቅብኝም ነው ?
- እኔ የሱ አላማው ሌላ አላማው እንዲያውል ገንዘቡን አልፈቀድኩለትም
- አደለም እኔ መስጠት በኃይማኖት የሚጠበቅብኝን ዘካ መስጠት ነው ከዛ ውጪ የሱን አላማ እስካመንኩት እና እስከሰጠሁኝ ድረስ የሱን ዓላማ ማረጋገጥ አይጠበቅብኝም ነው?

1594

ECHN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አቃቤ ሕግ መቃወሚያችሁን አስመዝግቡ
- ምስክሩ በድጋሚ ጥያቄ እየተጠየቁ እየመለሱ ነው ያሉት አቃቤ ሕግ ግን በራሳቸው አቅጣጫ ነው እያስመሰከሩ ያሉት ስለ አላማ አልተጠየቁም በኃይማኖቱ እሱ ይጠየቅበት አሉ እንጂ የሱ ዓላማ ያስፈጽም ያሉት ነገር የለም እና አቃቤ ሕጉ የራሳቸውን ኢንተረስት ነው እያስመሰከሩ ያሉት እና የተከበረው ፍ/ቤት ይሄ ጥያቄ ሊጠየቅም አይገባም ከተጠየቁም ደግሞ መልሰዋል በዋና ጥያቄ ከተነሳው አንፃር ድጋሚ ጥያቄ ጠይቀው የመለሱ ስለሆነ ጥያቄውን ሊቀበለው አይገባም ፍ/ቤቱ
- እሺ አቃቤ ሕግ መልስ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት እሳቸውም አሁን ጠበቃውም በመስቀለኛ ጥያቄ ሲጠይቁ ከዚህ በፊት ዘካ ሲሰጡ የቤተሰብ ችግርተኛ ማስረጃ እያያችሁ ነው ወይ የምትሰጡት ብለዋል ሲመልሱም ኃላፊነቱን የሚቀበለኝ ሰው ነው እኔ በኃይማኖቱ ያለብኝ ግዴታ መስጠት ነው ማመን ነው ከዛ ውጪ ግን ኃላፊነቱ የሱ ነው ማለት አሁን እንደገለፀት ማለት ው ለግል ጥቅሙም ሊያውለው ይችላል ወይም ደግሞ ለተቸገሩት ሰወች በትክክል ሊያደርስ ይችላል ከዛም ውጪ ላለ ዓላማ ሊያደርስ ይችላል ስለዚህ ይሄን ማወቅ ይችላል ወይ ነው እሳቸው እየተናገሩ ነው ያሉት እራሳቸው የሚጠይቁት ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ማስረጃ እያያችሁ ነው ወይ ማስረጃ አይተዋል ወይ ብለው ጠይቀዋቸዋል ከዛ ተያያዥነት ያለው ነው አሁን በድጋሚ ጥያቄ የተጠየቀው ጥያቄ
- ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ትእዛዝ ሰጥቶበታል በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ የተነሳው ጥያቄ ዘካው የሚሰጠው ለማን እንደሆነ ትለያላችሁ ወይ የሚል ጥያቄ ተነስቷል ስለዚህ ያንን መሰረት አድርጎ ከሳሽ አቃቤ ሕግ አሁን ያነሳሁት ጥያቄ ለመሆኑ ፍ/ቤቱ ግንዛቤ የወሰደ ስለሆነ አሁንም ከአላማው ጋር ተያይዞ የተነሳው ጥያቄ ከጉዳዩ የማይገናኝ ነው ብሎ ለመውሰድም አይቻልም ስለዚህ ከዳግመኛ ጥያቄ አላማ አንፃር ጥያቄው ሊቀጥል ይገባል ብሏል ፍ/ቤቱ
- እሺ አቶ ኑረዲን ቅድም የጠየቅኩትን ጥያቄ ልድገምሎት አሁን ዘካ የኔ መስጠት በኃይማኖቴ መስጠት ግዴታዬ ነው አምኜ መስጠት ግዴታዬ ነው ዘካውን መስጠት እንዳለ ሆኖ ማለት ነው ስለዚህ ለምን ዓላማ እንዳዋለው ወይም ደግሞ እንደፈለገው የሚያውቁት ነገር አለ ወይ አሁን አቶ ሙራድ ሽኩር ማለት ነው ?
- እኔ ቀጥታ የዘካውን ያው ስሰጠው በፊት እንደገለጽኩት ለነዚህ ለታሰሪ ቤተሰቦች እንዲሰጥ ነው የጠየቀኝም እንዲሰጥም ነው እኔ የሰጠሁት ከዛ በኋላ ከኔም ይጠበቅ

1595

http://ethcriminalawnetwork.com/

የነበረው ወይም ያደረግኩት ይሄንን ሰው ማመንን ነው ይሄንን ብር ለነዚህ ለተባሉት ሰወች ያደርሳል ነው ብሩን ደግሞ ለዚህ መሰል ችግሮች ካልሆነ በስተቀር ለሌላም አላማም ያው መዋልም ስለማይችል ለዚህ ያደርገዋል በሚል እምነት ያው ሰጥቼዋለሁ እኔም ከዛ በኋላ ግን የነዚህ ሰወች በትክክል ያደርስላቸዋል እምነት ካልሆነ በስተቀር እኔ ክትትል አድርጌ የደረሳቸውን ሰወች ደርሷችኋል ወይ ብዬም አልጠየቅኩም አላረጋገጥኩም እሱም ከዛ በኋላ ተገናኝቼ አግኝቼው ባልከኝ በጠየቅከኝ መሰረት ብሩ ቦታው ላይ አድርሰሽዋል ወይ ብዬም ያው አልተነጋገርንም አልነገረኝም አልጠየቅኩትም እኔም ከዛ በኋላ የብረን ሂደት ያው እኔ የማውቀው ነገር የለም ይሰጣል በሚል እምነት ካልሆነ በስተቀር

- ስለዚህ አሁን እርስዎ አቶ ሙሉ ሽኩር ከኮሚቴውጋ ምን አይነት ግንኙነት እንዳለው ለምን አላማ እንደሰበሰበው የሚያውቁት ነገር የለም?
- ያው በጠቀሰልኝ ዓላማ በስተቀር
- ብቻ ነው የሚያውቁት ነገር የለም?
- አዎ
- እሺ ቅድም ሲያስተምሩ በካሴት ደረጃነው የማውቀው ብለው ሁለት አቶ ያሲን ኑሪን እና አቶ አቡበክር አህመድን ጠቅሰዋል ከዛ ውጪ እኔ ነጋዴነኝ በተለያየ ጊዜ አልገኝም ሰግጄ ነው የምወጣው ብለዋል ከዛ ውጪ እነዚህ አሁን በችሎት የቀረቡት ተከሳሾች ማለት ሌላ ዓላማ ኖሯቸው ይቀስቅሱ አይቀስቅሱ ወንጀል ይፈጽሙ አይፈጽሙ የሚያውቁት ነገር አለ እንዴ?
- ሌላ ዝርዝሩን የማውቀው ነገር የለም በኮሚቴው እንትን ያው በተለይ ሚዲያ ላይ በፌደራል ጉዳዮች በነበረው ሂደት የሕዝበ ሙስሊሙን ጥያቄ ወክሎ በመቅረብ ሂደት ላይ የነበረውን ኮሚቴነታቸውን
- እንጂ አሁን በእንትን ደረጃ አያውቋቸውም ?
- አዎ ሌላ ዝርዝሩን እኔ ብዙ የማውቀው ነገር የለም
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዳግመኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክር ምላሽ ሰጥተዋል ከፍ/ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ የሌለ በመሆኑ ምስክሩ ተሰናብተዋል 12ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም ምያለሁ

15 96

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ በአስተርጓሚ ነው ምስክርነት ቃላቸውን የሚሰጡት እና ለምስክሩ ደህንነት ሲባል ስማቸውን ብቻ እንደሚገልፁ ንገራቸው አድራሻቸውንም አይገልፁም አስተርጓሚ ንገራቸው በሶሪ ካባ አማካኝነት ነው የተተረጐመው
- እሺ የመጀመሪያ ስሞትን ብቻ ይንገሩን?
- ከድር
- አቃቤ ሕግ ስንተኛ /የማይሰማ/?
- 120ኛ
- ዛሬ እዚህ ፍ/ቤት ለምን መጡ?
- ለምስክርነት ነው
- ማን ላይ ሊመሰክሩ ነው የመጡት የሚመሰክሩበትን ሰው ያውቃሉ ወይ?
- አዎ አውቃለሁ
- ማን ይባላል የሚመሰክሩበት ሰው?
- ሼህ አብዱራህማን ኡስማን
- ሌላስ?
- ሌላ የለም
- አብዱራህማን ኡስማንን ያውቋቸዋል ወይ በአካል?
- አዎ አውቀዋለሁ
- ሊያሳዩን ይችላሉ ወይ?
- ምስክር በሼህ አብዱራህማን ኡስማን ላይ ነው የምመሰክረው ብሎ ለይቶ አሳይቷቸዋል ምስክሩ የሚመሰክረው በ27ኛ ተሳከላሽ ላይ ለመሆኑ ፍ/ቤቱ አረጋግጧል ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- ሼህ ከድር አሁን የለዩዋቸውን ሰው ተከሳሹን የት ነው የሚያውቋቸው አሁን እርስዎ የለዩዋቸው?
- ሻሸመኔ ወረዳ አውቃቸዋለሁ ሻሸመኔ ዙሪያ
- ሲጠየቁ የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለዋል ምንድን ነው የሚመሰክሩት?
- እሳቸው ያሰሩትን እና የሰሩትን በሚመለከት መናገር እፈልጋለሁ
- እስቲ ንገረን ዘርዘር አርግና ለፍ/ቤቱ አስረዳ?
- እሳቸው የሚሰሩት እኛ አካባቢ መስኪድ ይሰራሉ የእስልምና ሰበተማሪዎችን ይቀጥራሉ ይሄን ይሄን ሲሰሩ አውቃለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የእስልምና አስተማሪዎች ይቀጥራሉ ማለት ምን ማለት ነው መስኪዱ በማን ነው የሚተዳደረው?
- የሰሩት መስኪድ ውስጥ የእምነት አስተማሪዎች ናቸው ብለው ሲቀጥረ አውቃለሁ
- መስኪዱ በማን ነው የሚተዳደረው ይቀጥራሉ ስትለን ምን ማለት ነው አንድ መስኪድ ሰራተኛ ሲቀጥር እንዴት ነው እሳቸው መስኪድ አሰርተው እራሳቸው የሚቀጥሩት እንዴት ነው እሱን አስረዳ ?
- ብዙን ጊዜ መስኪድ ይሰራሉ ካሰሩ በኋላ ደግሞ ሰወችን ያስተምራሉ ብለው እዛ የሚሰሩትን ይምድባሉ እንዲመድቡ ያደርጋሉ
- መስኪዶቹን በማን ፍቃድ ነው የሚሰሩት ስንት መስኪድ አሰርተዋል አንተ የምታውቀው ?
- አቃቤ ሕግ ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ ምስክር ይቀጥሉ ቅድም ካቆሙበት አሁን ቅድም ለይተዋል ምስክሩ የት እንደሚያውቋቸውም ነግረውናል ምንድን ነው ስለ እሳቸው የሚሰክሩት እሱን ይቀጥሉ ?
- ሰወች መቅጠራቸውን አውቃለሁ ሰወቹም ደግሞ ትምህርት እና ቁርአን ያስተምራሉ ነው የሚባለው እምነት እና ቁርአን ነው የሚያስተምሩት ይሄንን መሆኑን አውቃለሁ እነዚህ ሰወች ደግሞ በአካባቢ የማውቃቸው ሰወች አደሉም
- ምን ማለት ነው ከየት ነው የመጡት?
- ከተለያየ ቦታ ነው የመጡት
- ከዚህ በፊት ከየት ነበረ እዛ አካባቢ መስኪድ ማን ነበረ የሚያስተምረው ከዛ በፊት?
- ከዛ በፊት እዛ ቦታ መስኪድ አልነበረም መስኪድ በሌለበት ቦታ ላይ ነው አዲስ የሰሩት
- በማን ፍቃድ ነው ያሰሩት ይሄንን መስኪድ ?
- ለማን አስፈቅደው እንዳሰሩ እኔ አላውቀውም
- ስንት መስኪድ ነው ያሰሩት?
- ሻሸመኔ ከተማ ውስጥ 4 መስኪድ አውቃለሁ
- ሌላ የምታውቀው አለህ?
- ሻላ ውስጥ ደግሞ ከ4-5 አውቃለሁ ይሄንን ነው መስኪድ የማውቀው
- እነዚህ መስኪዶች ላይ በተመሳሳይ አስተማሪዎች ነው የሚቀጥሩት?
- አዎ

15 08

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ማን ነው የሚያስተዳድረው መስኪዶቹን አሁን የገለጽክልንን መስኪዶች ማን ነው የሚያስተዳድራቸው?
- ሼህ አብዱራህማን በየወሩ ይመጣሉ እየመጡ ይከታተላሉ
- እሳቸው ናቸው የሚያስተዳድሩት?
- አዎ
- ቅድም ቁርአን እና ኃይማኖት የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ናቸው ከየት እንደመጡ አላውቅም
- የተከበረው ፍ/ቤት
- ተቃውሞ ነው
- አዎ ተቃውሞ ነው
- እሺ ያስመዝግቡ
- አቃቤ ሕግ ጠይቀዉ የተመለሰው መልስ /የማይሰማ/ የሚያስተዳድሩት የሚለው ጥያቄ መልሱ ምንም ጥርጥር የሌለው አዎ ወይ አይ ምስክሩም ይሄንን እንትን አላሉም
- የተመለሰው ጥያቄ ላይ ነው ?
- አዎ
- /የማይሰማ/
- ፍ/ቤቱ የተነሳውን የመቃወሚያ ሃሳብ መርምሮታል ከሳሽ አቃቤ ሕግ በዚህ ላይ መልስ እንዲሰጥ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም ምክንያቱም መቃወሚያው በቀረበው ጥያቄ ላይ ሳይሆን ጥያቄው ቀርቦ መልስ ተሰጥቶበታል ስለዚህ ስነስርዓት ሕጉን መሰረት አርጐ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በተመለከተ ጥያቄ ቀርቦ መልስ ከተሰጠ በኋላ ሊቀርብ የሚችል መቃወሚያ አይኖርም እና ጥያቄው ሲቀርብ ነው መቃወሚያ ሊቀርብ የሚገባው በተመለሰ ጥያቄ ላይ ፍ/ቤቱ ወደኋላ ተመልሶ ጥያቄ እና መልሱን የሌለ በመሆኑ ጥያቄ /ግልጽ ያልሆነ/
- እሺ ቅድም ሲገልፁልኝ እነዚህን እሳቸው በሼህ አብዱራህማን የሚቀጠሩ አስተማሪዎች የቁርአን እና የኃይማኖት ትምህርት ያስተምራሉ ብለሃል ምን ሃይማኖት ነው የሚያስተምሩት እሱን ንገረኝ እስቲ ?
- ያው የእስልምና ትምህርት ተብሎ ነው የሚያስተምሩት ግን ከመሰጥጡ አልፎ አልፎ ችግር ያለባቸው አሉ
- ምንድን ነው ችግር ያለባቸው ማለት?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለምሳሌ እንደ ችግር ውስጡ የሚያመጡት አንዳንዴ ወለድ መውሰድ አይሆንም ብድርም አይሆንም ለሞተ ሰው መቀመጥ አይሆንም የመሳሰሉት ነገሮች
- አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ ምስክር ይቀጥሉ ቅድም ካቆሙበት አሁን ቅድም ለይተዋል ምስክሩ የት እንደሚያውቋቸውም ነግረውናል ምንን ነው ስለ እሳቸው የሚመሰክሩት እሱን ይቀጥሉ ?
- ሰወች መቀጠራቸውን አውቃለሁ ሰወቹም ደግሞ ትምህርት እና ቁርአን ያስተምራሉ ነው የሚባለው እምነት እና ቁርአን ነው የሚያስተምሩት ይሄንን መሆኑን አውቃለሁ እነዚህ ሰወች ደግሞ በአካባቢ የማውቃቸው ሰወች አደሉም
- ምን ማለት ነው ከየት ነው የመጡት?
- ከተለያየ ቦታ ነው የመጡት
- ከዚህ በፊት ከየት ነበረ እዛ አካባቢ መስኪድ ማን ነበረ የሚያስተምሩው ከዛ በፊት?
- ከዛ በፊት እዛ ቦታ መስኪድ አልነበረም መስኪድ በሌለበት ቦታ ላይ ነው አዲስ የሰሩት
- በማን ፍቃድ ነው ያሰሩት ይሄንን መስኪድ?
- ለማን አስፈቅደው እንዳሰሩ እኔ አላውቅም
- ስንት መስኪድ ነው ያሰሩት?
- ሻሸመኔ ከተማ ውስጥ 4 መስኪድ አውቃለሁ
- ሌላ የምታውቀው አለ?
- ሻላ ውስጥ ደግሞ ከ4-5 አውቃለሁ ይሄንን ነው መስኪድ የማውቀው
- እነዚህ መስኪዶች ላይ በተመሳሳይ አስተማሪዎች ነው የሚቀጥሩት?
- አዎ
- ማን ነው የሚያስተዳድረው መስኪዶቹን አሁን የገለጽክልንን መስኪዶች ማን ነው የሚያስተዳድራቸው ?
- ሼህ አብዱራህማን በየወሩ ይመጣሉ ያው እየመጡ ይከታተላሉ
- እሳቸው ናቸው የሚያስተዳድሩት?
- አዎ እሳቸው ነው የሚያስተዳድሩት
- ቅድም ቁርአን እና ኃይማኖት የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ናቸው ከት እንደመጡ አናውቅም ብለዋል
- የተከበረው ፍ/ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ተቃውሞ ነው?
- አዎ ተቃውሞ ነው
- እሺ ያስመዝግቡ
- አቃቤ ሕግ ጠይቀው የተመለሰው መልስ ላይ አምልጦ ነው እንጂ ግልጽ የሆነ መረ ጥያቄ ነው እሳቸው ናቸው የሚያስተዳድሩት የሚለው ጥያቄ መልሱ ምንም ጥርጥር የሌለው አዎ ወይም አይ የሚል ነው ምስክሩም ይሄንን እንትን አላሉም
- የተመለሰ ጥያቄ ነው ?
- አዎ አምልጦ ነው እንዲሰረዝ ነው የምንጠይቀው
- ፍርድ ቤቱ የተነሳውን የመቃወሚያ ሃሳብ መርምሮታል ከላሽ አቃቤ ሕግ በዚህ ላይ መልስ እንዲሰጥ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም ምክንያቱም መቃወሚያው በቀረበው ጥያቄ ላይ ሳይሆን ጥያቄው ቀርባ መልስ ተሰጥቶበታል ስለዚህ የስነስርዓት ሕጉን መሰረት አድርጐ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደተመለከተው ጥያቄ ቀርቦ መልስ ከተሰጠ በኋላ ሊቀርብ የሚችል መቃወሚያ አይኖርም እና ጥያቄው ሲቀርብ ነው መቃወሚያ መቅረብ የሚገባው ስለዚህ በተመለሰ ጥያቄ ላይ ፍ/ቤቱ ወደኋላ ተመልሶ ጥያቄ እና መልሱን ሊሰርዝ አይችሉም ተብሏል የሌለ በመሆኑ ጥያቄ ወደሌሎች ጥያቄዎች ይቀጥሉ
- እሺ ቅድም ሲገልፁልን እነዚህን እሳቸው ሼህ አብዱራህማን የሚቀጠሩ አስተማሪዎች የቁርአን እና የኃይማኖት ትምህርት ያስተምራሉ ብለሃል ምን ኃይማኖት ነው የሚያስተምሩት እሱን ይንገሩን እስቲ?
- ያው የእስልምና ትምህርት ተብሎ ነው የሚያስተምሩት ግን በውስጡ አልፎ አልፎ ደግሞ ችግር ያለባቸው አሉ
- ምንድን ነው ችግር ያለባቸው ማለት ?
- ለምሰሌ እንደ ችግር ውስጡ የሚያመጡት አንዳንዴ ወለድ መውሰድ አይሆንም ብድርም አይሆንም ለሞተ ሰው መቀመጥ አይሆንም የመሳሰሉት ነገሮች በብዛት ይነሳሉ ይሄንን አውቃለሁ
- ሌላ የምታስታውሰው አለህ ከኃይማኖቱ ከዚጋር ተያይዞ?
- አንዳንድ ሰወች ከነዛ ውስጥ ይሄንን መንግስት አንፈልገውም የእስላም መንግስት አላህ ያምጣልን ብለው የሚሉ አሉ
- የት ነው የሚሉት?
- ሻሸመኔ ውስጥ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መቼ ነው ጊዜው የትኛው መስኪድ ?
- አራዳ መስኪድ ውስጥ
- የት የሚገኝ ነው?
- አራዳ ክ/ከተማ ውስጥ ነው የሚገኘው
- እዚህ አዲስ አበባ ነው የት ነው?
- ሻሸመኔ
- እሺ ማን ነው የሚለው ይሄንን አሁን ያልከውን?
- ሼህ ተማም ሃሰን የሚባል
- ማን ናቸው እኚህ ሼህ ተማም?
- ከእሳቸው ከእነሱጋር ሆኖ ስለእምነት የሚያስተምር ነው
- እነሱ እያልክ የምትገልፀው እነማን ናቸው እነሱ?
- ሼህ አብዱራህማን ኡስማን
- እነሱ የምትሏቸው በምን ምክንያት ነው አሁን አንተ እነሱ የምትለው በምንድን ነው እስቲ አብራራው ማለት የተለየ ግሩፕ አለ ወይም የምታውቀው አለ ስብስብ?
- ከእሳቸውጋር ብዙ ሰወች ስላሉ እነሱ ለማለት ፈልጌ ነው
- እኮ እነዚህ ሰወች ምንድን ናቸው እስቲ ንገረን ዘርዘር አርግና ንገረን ምንድን ነው የሚሰሩት?
- የሚሰሩት ስራ ይሄውን ብቻ ሲሆን ስማቸው ብዙ ነው ለምሳሌ ሼህ ሁሴን ቃሲም የሚባል ሼህ መሃመድ በዳሶ የሚባል ሼህ ሁሴን ኢብራሂም ሌሎቹም አሉ ግን እኔ እነዚህን ነው የማውቀው
- እነዚህን በምንድን ነው የምታውቃቸው?
- አሁን የገለጽኩትን ነገሮች እሰማለሁ
- አሁን ጠቅለል አርገህነው የነገርከን የአንድ ሰው ነው የነገርከን እስቲ በሰወች እየነገርክ ማለት ሲናገሩ የሰማኸው ካለ ወይም የምታውቀው ነገር ካለ በሰወች ስማቸውን እየጠቀስክ ንገረን?
- ሼህ ተማም ሃሰን የሚባለው እስላም መንግስት አላህ ያምጣልን ብሎ አራዳ መስኪድ ሲናገር ሰምቻለሁ
- ይሄ መስኪድ በማን ነው የሚተዳደረው?
- መስኪዱ ያው የህዝብ ነው በህዝብ ነው የተሰራው ሰውየው ከእነሱጋር ይሰራል እንጂ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ኦኬ ሰውየው ማለት አሁን የገለጽካቸው ሰው ?
- አዎ
- የተለያየ ስራ ነው እንዴ ያላቸው እነዚህ የኃይማኖት አሁን የጠቀስካቸው ሰወችም የኃይማኖት ሰወች ናቸው አደል?
- አዎ
- ከእነሱጋር ነው የሚሰራው እያልክ ሌላ ቡድን እንዳለ ነው የተረዳነው ካልተሳሳትን እና ምንድን ነው አለ ወይ እንደዛ አይነት እንደዛ ነው ወይ እየገለጽክ ያለኸው?
- ክቡር ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- መቃወሚያ ምንድን ነው አስመዝግቡ
- መቃሚያችን ያው ምስክር የሚሰማው የሚሉትን ነው ፍ/ቤቱ እየሰማ ነው ስለቡድን ያነሱት ነገር የለም ምስክሩ አቅቤ ሕጉ ቀጥታ ቡድን ብለው እንዲያስረዱላቸው ነው የፈለጉት እና ይሄን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ሊቀበለው አይገባም ይሄን በተመለከተ የተከበረው ፍ/ቤት ምክንያቱም እስከ አሁን ድረስ ምስክሩ ቡድኑን አስመልክቶ እስከአሁን ድረስ ምስክሩ ቡድንን አስመልክቶ ሁለት ሰው እንኳን አለው ብሎ አልተናገረም እና ሊቀበለው አይገባም ቡድን የሚባል ቃል አልወጣም ጥያቄው መሰረቱ ሊመዘገብም አይገባም እና እንዲሰረዝ ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ አቃቤ ሕግ መልስ ይስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት አሁን ከሰወቹ እንኳን ከአራት በላይ ጠቅሰዋል ከሼህ አብዱራህማን ጋር አብረው የሚሰሩ ከእነሱጋር የሚሰሩ እያሉ ገለፀ አሁን አራዳ የሚገኘው መስኪድ ላይ የእስላም መንግስት ያምጣልን አላህ ብለው ተናገሩ ሲባል ማን ናቸው ሲባል ሼህ ተማም የሚባሉ አሉ ምንድን ናቸው እኚህ ሰው ሲባሉ እዛው የሕዝብ መስኪድ የሚተዳደረው ላይ የሚሰሩት ነገር ግን ይሄን ንግግር የተናገሩት እዛ ነው ነገር ግን ከእነሱጋር እንደሚሰሩ አውቃለሁ አሉ አሁን እንደተረዳነው ከምስክሩ ከእነሱጋር የሚሏቸው ቡድን እንዳለ ያስረዳል እና ከፋፍለው ነው እየነገሩን ያለው እንደዚህ አይነት ነገር አለ ወይ በግልጽ እሱን ያብራሩልን ነው ያልተናገሩትን እኛ በፍፁም አልተናገርንም ቡድን እንዳለ ያሳያል ከእነሱጋር እንደሚሰራ አውቃለሁ እያሉ ደጋግመው ነው የሚናገሩት ስለዚህ ከእነሱጋር የሚሉት እነማንን ነው ?
- ፍ/ቤቱ የቀረበውን መቃወሚያ እና ምላሹን መርምሮ ትእዛዝ ሰጥቶበታል ከሳሽ አቃቤ ሕግ እንዳቀረቡትም ምስክሩ ከ27ኛ ተከሳሽ በመጀመር ከዛ ከእሳቸውጋር ይሰሩ የነበሩ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሰወችን በዝርዝር ጠቅሰዋል ስለዚህ እነሱን ጠቅሰው ያሉ ለመሆኑ አቃቤ ሕግ መሰረት አድርጐ አነድላይ ያሉ ለመሆኑ ለማመልከት ቡድን የሚለውን ለመጠቀሙ ፍ/ቤቱ ተረድቷል እና በዚህ መሰረት ግለሰቦቹን ወይም ተከሳሽ እና ሌሎች ሰወችን ለማመልከት የተጠቀመበት አነጋገር ስለሆነ ጥያቄው መቀጠሉ አግባብ ነው ብሏል ፍ/ቤቱ

- እሺ ሼህ ከድር አሁን ደጋግመው ሲያስረዱን እነሱ እያሉ እየገለፁልን ነው አሁን እነሱ የሚሏቸው በናንት ኃይማኖት ውስጥ ነው ያሉት አደለ እናንተ በምትሰሩበት መስኪድ ውስጥ ነው የሚንቀሳቀሱት እነ ሺህ አብዱራህማን ?
- አዎ
- አሁን የእርስዎ ሌላ ቡድን እንዳለ አይነት አርገው ነው እየገለፁ ያሉት እና አለ ወይ በምንድን ነው የተከፋፈላችሁት እነሱ የምትሏቸው ይሄ እነሱ የሚለው መጠሪያ በምንድን ነው ?
- እነዚህ ሰወች ልል የቻልኩት አንደኛ እነዚህ ሰወች በእነዚህ ነው እንትን ያሉት የተዘጋጁት
- ለምንድን ነው የተዘጋጁት?
- አስተማሪዎች ናቸው በእሳቸው ሲለቀቅ ተቀጠሩ እሳቸው ለማለት ፈልጌ ነው
- ለምንድን ነው እነዚህን አስተማሪዎች ከተለያየ ቦታ የቀጠሯቸው?
- በምን እንደተቀጠሩ አላውቀውም ግን የሚሰሩት ደግሞ አሁን የነገርኳችሁን ነው
- እነዚህ አስተማሪዎች ምንድን ነው የሚያስተምሩት በትክክል እስቲ በግልጽ ንገረን ምንድን ነው የሚያስተምሩት እናንተ አሁን ከተለያየ ቦታ የመጡ አስተማሪዎች ብለሃል እኛ የማናውቃቸው ከተለያየ ቦታ የመጡ አስተማሪዎች ሼህ አብዱራህማን በሰሩት መስኪድ ላይ ተቀጥረዋል ብለዋል ምንድን ነው የሚያስተምሩት አስተምሮቱን የምታውቀው አለህ ?
- ትምህርታቸውን አላውቀውም አንዳንድ ጊዜ ምክር እሰማለሁ ከዛ ምስክር ውስጥ ደግሞ ለሞተ ሰው ለቅሶ መቀመጥ የሚለውን ሰምቻለሁ ወለድ መውሰድ አይሆንም ሲባል ሰምቻለሁ
- የት ነው ይሄ የሚባለው ?
- እዛው መስኪድ 04 ውስጥ የሚገኘው ሼህ ሁሴን ቃሲም የሚባለው ሲናገር ሰምቻለሁ እሱ ደግሞ ከእሳቸው ተቀብሎ እዛ ያለ ነው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሼህ አብዱራህማን ምንድን ነው ስራቸው እዛ ሻሸመኔ አሁን የገለጽክልኝ ቦታ ምንድን ነው እናንተ በምንድን ነው የምታውቋቸው ?
- መስኪድ ሲያሰሩ ነው እኔ የማውቀው ሰው ሲቀጥሩ አውቃለሁ አሁን እኔ ያልኳቸው ሰወች ደግሞ አሁን ያልኩትን መስራታቸውን አውቃለሁ
- ሌላ የሚሰሩትን ነገግረ ታውቃለህ?
- ሌላ አላውቅም የሚሰሩትን
- መስኪዱ ከምንድን ነው ማለት ከየት በመጣ ገንዘብ ነው የሚሰራው?
- ከአረት ነው የሚባለው ተሰርቶ ሲያልቅ አረቦቹ ይመጣሉ ሲያስመርቁ አያለሁ
- ከየት አገር ?
- ጥያቄው ግልጽ አደለም
- ከየት አገር ማለት ከአረብ አገር ስትል ብዙ አገሮች አሉ እና ከየትኛው አገር በስም የምታውቀው ?
- ከየት እንደሚያመጡ አላውቀውም
- ከአረብ አገር ሲባል ነው የሰማኸው?
- አረብ መሆናቸውን አውቃለሁ እንጂ ከየት እንደሆነ አላውቅም
- መጥተው አይተሃቸዋል?
- አንድ ቀን አይቻለሁ አዎ
- የት ነው ያየሃቸው?
- ሻሸመኔ አጄ አካባቢ በአጄ መንገድ ላይ አጄ የሚባል ቦታ ላይ መስኪድ ተሰርቶ መልካ ቁንጡሬ የሚባል ቀበሌ ቦታ ላይ ሲመረቅ አንድ ቀን አይቻለሁ
- እሺ በአጠቃላይ ስንት መስኪድ ነው ያለው ማለት ነው በእሳቸው የተሰራ?
- እኔ የማውቀው ሻሸመኔ ከተማ ውስጥ አራት መስኪድ
- ሌላ?
- ሻላ ውስጥ ደግሞ 6 መስኪድ አውቃለሁ በጆሮ የሰማሁት ደግሞ መስኪዱ ብዙ ነው
- እነዚህን ማን እንደሚያስተዳድራቸው የምታውቀው ነገር አለ ?
- ይዜንን እኔ አላውቅም እነሱን ነው እዛ ብዙ ጊዜ የማየው
- ከየመቼ ጀምሮ ነው የተሰሩት?
- እንደግምት በ1996 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2003 ዓ.ም. እየተመላለሱ ሲሰሩ አያለሁ
- ከየት ነው የሚመላለሱት?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- በአዲስ አበባ እና በእኛ አገር መሃል
- ምስክር አሁን ሲገልፁ ሻሸመኔ ውስጥ 4 ከሻሸመኔ ውጪ ደግሞ 6 መስኪዶች እንደሰሩ አውቃለሁ ሼህ አብዱራህማን ብለዋል በጆሮዬ የሰማሁት ደግሞ ብዙ ነው ብለዋል ምን ያህል ነው በጆሮ የሰሙት?
- በጆሮዬ የሰማሁት ሲራሮን ጨምሮ ሰባ ሰማንያ ይሆናሉ
- አሁንም ቅድም ሲመልሱ ገንዘቡን ከአረብ አገር ነው የሚያመጡት ብለዋል ምምን ምን ያረጉበታል ይሄንን ገንዘብ ?
- መስኪድ ያሰሩበታል በግላቸውም ይገለገሉበታል
- ከድር አንተ ሙስሊም ነህ አደለም?
- አዎ
- ሼህ አብዱራህማን መስኪድ መስራት ከጀመሩ በኋላ ነው ሙስሊም የሆንከው ?
- ተቃውሞ አለ አስመዝግቡ
- ከዚህ በፊት ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ስንጠይቅ አቃቤ ሕግ ተነስተው አስቁመውናል ፍ/ቤቱም ተቀብሏቸዋል የግል ጥያቄ ነው የግል እምነታቸውን የተመለከተ ነው አንድ ምስክር ያየውን የተረዳውን ነገር ነው እንጂ መመስከር ያለበት የግል እምነቱን ወይም አስተያየቱን ነው ስለዚህ አቃቤ ሕግ ምስክሩ በቦታው ላይ አየሁ የሚሉትን ነገር ከመጠየቅ ውጪ የግል እምነቱን ወይም አስተያየቱን ሊጠይቁ አይገባም ጥያቄው እንደሰረዝ እንጠይቃለን
- ትላንትጠይቃችሁ ነበረ የመስቀለኛ ጥያቄ
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት ጠይቃቸው ኃይማኖት የትኛው ይመደባል የሚል ጥያቄ ጠይቃችሁ ነበር እሱ ጥያቄ በቀባይነት አግኝቶ ቀጥላችኋል እናንተ ?
- ከዛ በፊት የነበረው ማለት ነው
- አደለም ቀጥላችኋል ትላንት አቃቤ ተቃውሞ አንስቶ የትኛው ኃይማኖት ውስጥ ነው ያለኸው ተብሎ ይሄ የግል እንትኑን የሚነካ አደለም ኃይማኖቱን መናገር ችግር የለውም ተብሎ ትላንት ብይን ተሰጥቷል ለእናንተ ስለዚህ ምናልባት ከዚህ ተነስታችሁ የምታነሱት ካለ
- የተከበረው ፍ/ቤት አሁን ምስክሩ እየተጠየቁት ጥያቄ የግል እምነታቸውን በተመለከተ ነው ለምሳሌ እኔ እራሴ በዚህ ችሎት የጠየቅኩት መስኪድ ውስጥ ተኛጋሪው ሲናገሩ ሰወች አለቀሱ ያሉ ምስክር እርስዎስ አልቅሰው ነበረ ወይ ብዬ ስጠይቅ አቃቤ ሕግ

1606 26

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ተነስተው ይሄ የግል ጉዳይ ስለሆነ ሊጠየቅ አይገባም ብለው አስቁመውኝ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቶበት ቆሟል አሁን ይሄ የግል ጉዳይ ነው እያልን ነው

- እሺ ስጡበት እና
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት የግል ጉዳይ ስለሆነ ምስክሩ ያዩትን በቦታው ሲደረግ የተረዱትን እንጂ የግል እምነታቸው ሊጠየቅ አይገባም
- እሺ አንደኛው ያው አሁን በፍ/ቤቱ የተገለፀው ነው ይሄ ጉዳይ ብይን የተሰጠበት ነው ብይን የተሰጠው አሁን ጠበቃው ባሉት ባቀረቡት መልኩ ሳይሆን በተቃራኒው ነው እንዲቀጥሉ የተፈቀደው 2ኛ እኛ አሁንም ጠበቆች ፍ/ቤቱ አንደር እስታንድ ማድረግ ያለባቸው ዋና ጥያቄ ነው እየጠየቅን ያለነው መምራት አንችልም ስለዚህ እኛ አሁን የእሳቸውን ሙስሊምነት ለማወቅ አደለም የጠየቅነው እምናነሳውን ጥያቄ መራችሁ ተብለን በኋላ እንዳንቋረጥ እየዞርን ነው ያለነው ወደምንፈልገው ጥያቄ ለመውሰድ ስለዚህ እኛ የጠየቅነው ትላንት ወይም ከትላንት ወዲያ ጠበቆች ባነሱት መልኩ አደለም እኔ መስቀለኛ ጥያቄ ላይ እንዲህ አይነት ጥያቄ ቢሆን አንጠይቅም መርቼ የምፈልገው ጥያቄ ነበር አሁን ግን ዋና ጥያቄ ስለሆነ በዋና ጥያቄ መልክ ጥያቄዎቹን ለማቅረብ ነው ስለዚህ ምንም ምክንያት የለውም ጥያቄው ውድቅ የሚሆንበት የተነሳውም መቃወሚያ አለአግባብ ነው
- ፍ/ቤቱ የቀረበውን መቃወሚያ እና ምላሽ መርምሮ ትእዛዝ ሰጥቶበታል ከሳሽ አቅቤ ሕግ የቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ እንደተመለከተው የተጠየቀው ጥያቄ የግል እምነትን የሚጠይቅ እሚያመለክት አደለም እውቀቱን ስለሰውየው የሚያውቀውን ኃይማኖታቸውን መሰረት አድርጎ ስለሚያውቀው ነገር እንዲመልስላቸው የቀረበ ጥያቄ ነው በተመሳሳይ በእንደዚህ ተመሳሳይ ጥያቄዎች እንዲቀርቡ ብሎ ፍ/ቤቱ የሰጠውንም ትእዛዝ ያስታውሳል ስለዚህ በዚህ መሰረት ጥያቄው ሊቀርብ ይገባል ብሏል
- እሺ አቶ ከድር አንተ ሙስሊም የሆንከው ሼህ አብዱራህማን መስኪድ መስራት ከጀመሩ በኋላ ነው?
- አደለም እኔ ከመጀመሪያ ጀምሬ እስላም ነኝ የተወለድኩትም ከእስላም ነው
- ጥሩ ቀደም ብለው ሼህ አብዱራህማን እዛ አካባቢ ከመምጣታቸው በፊት ለእናንተ ትምህርት የሚያቀርቡ ኢማሞች ወይም ሌሎች የኃይማኖት አባቶች ነበሩ?
- አሉ አዎ
- ጥሩ እነዛን ሰወች ሼህ አብዱራህማን በመስኪዳቸው ይቀጥሯቸዋል?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይቀጥሩም
- ለምን?
- ችሎታ የላቸውም ከሚል የነሳ ነው ይምስለኛል በዚህ ምክንያት አይቀጥሩም
- እነዚህ የቀድሞ ኢማሞች ምን ይደረጋሉ የሚደርስባቸው ችግር አለ ?
- አዎ እኔ የማውቀው ከመስኪዱ የሚገኘውን እርዳታ ተጠቃሚዎች አደሉም በዚህ እኔ የማውቀው ይሄንን ነው
- እነዚህ አሁን ሼህ አብዱራህማን የሚቀጥሯቸ ኢማሞች ቅድም በስም የጠቀሷቸው እነሁሴን ሌሎች በስም የጠቀሷቸው የኃይማኖት አስተማሪዎ ስለነዚህ ስለቀደሙ ሰወች የሚሉት ነገር አለ ?
- አዎ ሳላት አናደርግም አዎ እነሱ እስላም አደሉም ከነሱጋር አንሰግድም የሚሉትን ይናገራሉ
- እና ምን ይሁኑ ነው ምን እናርጋቸው ነው ?
- ተቃውሞ አለን እያሉ ስለሆነ ተቃውሟችሁን አስመዝግቡ
- መርተው ነው የጠየቁትምን እናድርጋቸው አሉን ብለው አቃቤ ሕጉ ከዛ የቀድሞ ሼሆችን አንሰግድም አሉ ነው ያሉት ምን እናድርጋቸው አሉ እንዲህ እናድርጋቸው እንዲሏቸው ማለት ነው ስለዚህ ይሄ ጥያቄ ሊታለፍ ይገባል በግልጽ መሪ ጥያቄ ነው የጠየቁት
- እሺ አቃቤ ሕግ
- ትላንት ብይን ተሰጥቶበታል የተከበረው ፍ/ቤት ተመሳሳይ ጥያቄ ነው መሪ ጥያቄ አደለም ተፈቅዶልን ነው የቀጠልነው በዛ መልኩ ነው የአሁኑ መታየት ያለበት
- አሁን ምንድን ነው ምላሽ የምትሰጡበት ትላንት ብይን ተሰጥቶበታል ምናምን የሚለው ነገር እሱ ከግራ ቀኞችሁ ብተውት ጥሩ ነው ምክንያቱም እንደየ ሁኔታው ነው የሚታየው ይሄ ትላንት ተሰጥቶበታል ተብሎ ዛሬ እንትን የሚባል አደለም አሁን ስለተጠየቀው ጥያቄ ብቻ ነው እንጂ ስለትላንት ቅድም ያነሳነው ምናልባት እሳቸው ያልተነሳ እንደዛ መስሏቸው እሱን ለማስረዳት ነው እንጂ ትላንት ብይን የተሰጠበት ዛሬ አይነሳም ወደሚል መደምደሚያ እንዳይደርስ ነው እና ይሄንን አስተካክላችሁ አሁን የተጠየቀው ላይ መሪ ነው መሪ አይደለም የሚለውን ብቻ መልሱ
- አሁን እኛ የጠየቅነው ጥያቄ ቀደም ብሎ ምስክሩ የቂያመ ሬዲዮ ሼህ ሰላት አናረግላቸውም ሙስሊም አደሉም እንዲህ እንዲህ ይሉ ነበር እያሉ ከረዘሩ ሌላ ምን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

እናርጋቸው ይላሉ ብሎ መጠየቅ መሪ ጥያቄ አደለም መሪ ጥያቄ ቀደም ብሎ ፍ/ቤቱ ብይን በሰጠበት መልኩ ነው ትርጉሙም እና ከዛ ትርጉምጋር አብሮ የሚሄድ አደለም

- ፍ/ቤቱ መቃወሚያና ምላሹን መርምሮ ትእዛዝ ሰጥቷል ከሳሽ አቃቤ ሕግ ያነሳው ጥያቄ ከዛስ ምን እናድርጋቸው አሉ የሚል ጥያቄ ነው ያነሳው ይሄ ደግሞ ቀጥታ ምላሹን አመልክቶ መልስ ምስክሩ እንዲሰጥ ሊያደርግ የሚችል ጥያቄ አደለም ምን እናድርጋቸው አሉ የሚለው ጥያቄ ሰፊ ነው ስለዚህ የሚያውቁት ነገር ያለ እንደሆነ የሚያውቁትን ነገር እንዲመሰክሩ የሚያደርግ እንጂ የሚመራ ጥያቄ ሆኖ ስላልተገኘ መቃወሚያውን አልተቀበለውም ጥያቄ ፍ/ቤቱ ይቀጥል ተብሏል
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምስክር ስለዚህ የነዚህ የድሮ ኢማሞችን ምን እናርጋቸው ነው የሚሉት ?
- ይሄን እናደርጋለን ብለው ሲናገሩ እኔ ከሰው አፍ አልሰማሁም ይሄንን እንደ እኔ ሃሳብ ደግሞ ከእነዚህጋር አንሰግድም ሰላት አብረን አናደርግም የሚል ነው እንኔ ሃሳብ ያለው
- ጥሩ ችግር የደረሰባቸው ኢማሞች የሚያውቋቸው አሉ አርስዎ ?
- ችግር የደረሰበት ሰው እኔ የማውቀው ሰው የለም
- ምስክር እርስዎስ ላይ ችግር ደርሶቦታል?
- እኔ ላይ ደግሞ ችግር ደርሷል
- ምን ደረሰቦት?
- ይህ ደግሞ ለዚህ ጉዳይ እዚህ ከመጣሁ በኋላ ነው ማለት ነው
- ምን ተደረጉ?
- ለሊት እቤቴ መጥተው ዘርፈዋል
- እሺ ?
- ተቃውሞ አለ የተከበረው ፍ/ቤት
- ተቃውመው ምንውን ነው
- ከጭብጡ ውጪ ነው እኮ አቃቤ ሕግ እያስረዱ ያሉት እዚህ መጥተህ ከሄድክ በኋላ ከዚህ ከጉዳዩጋር የሚገናኝ ነገር አደለም ቤቱ ተዘርፏል ምናምን እያሉ ነው ግን ከጭብጡ ውጭ ነው እያስረዱ ያሉት እሳቸው ሼህ አብዱራህማን ነው አውቃለሁ ያሉት ከጉዳዩጋር የሚያያዝ ስላልሆነ ሊታለፍ ይገባል በክስ ዝርዝሩ ላይም የለም
- እሺ አቃቤ ሕግ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ያው ደጋግመን እንደገለጽነው ምስክሩ ምን እንደሚመሰክሩ ምስክሩን ያቀረበው አካል ነው የሚያውቀው እና 2ኛ ምስክሩ ቃል የሰጡት በጣም እረጅም ጊዜ ነው ለፖሊስ ቃል ከሰጡ ምስክርነት ከሰጡ ምናልባት ግማሾች ተከሳሾች ከመያዛቸው በፊት ነው እና አስቸጋሪ ነው አሁን ይሄንን ለተከበሩ ጠበቆችም ማስረዳት ስለዚህ በዛ መልኩ የሚታይ ቢሆን ችግር የደረሰባቸው ሰወች አሉ ኢማሞችም የኃይማኖት አስተማሪዎችም አሉ እያሉ ነው ምስክሩ ችግር የደረሰባቸውን ሰወች ዘርዝሩ አልናቸው ከዛ ውስጥ እርስዎስ ላይ የደረሰ ችግር አለ ወይ ብለን ጠየቅን
- በቀረበው ጥያቄ ላይ ብቻ
- አዎ እኮ እሱን እኮ መለስን የተከበረው ፍ/ቤት ምስክሩ መች ቃል እንደሰጡ ጠበቆች ሊያውቁ አይችሉም አንድ እሱ ነው 2ኛ ችግር ከደረሰባቸው ሰወች መሃል እኔ ነኝ እኔ ላይ ይህ ችግር ደርሷል ብለው እያስረዱ ነው ያሉት እና ይሄ ጥያቄ ምኑ ነው አሁን
- /የማይሰማ/
- አዎ የተከበረው ፍ/ቤት
- ይሄ ችግር ደረሰብኝ ያሉት መቼ ነው?
- በ28
- እዚህ ከመጣሁ በኋላ አሁን እዚህ ለምስክርነት ከመጡ ነው?
- ቃሌን ለፖሊስ ከሰጠሁ በኋላ ነው
- መቼ ነው እስቲ ቀኑን ንገሩኝ ?
- በ28/1/2005
- መቃወሚያውን መርምሮ ትእዛዝ ሰጥቷል ምስክሩ እየመሰከሩ ያለውን ነጥብ ከክስ ጭብጡ ሆነ ከክስ ማመልከቻውጋር አያይዞ ተመልክቶታል ስለዚህ የክስ ማመልከቻውም የሚያመለክተው በ2004 ዓ.ም. በአብዛኛው ወንጀል የተፈፀመ ስለመሆኑ እንደዚሁም 27ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ከ1991 ዓ.ም. ጀምሮ ስለፈፀሙት ተግባር በመዘርዘር በ3 ክፍል ተከፍለው የተመለከቱ የወንጀል አይነቶችን ነው የሚያመለክተው እና በነዚህ ውስጥ አሁን ምስክሩ መስከረም ወር ተፈጽሞብኛል በዚህ ዓመት መስከረም ወር ተፈጽሟል ስላሉት ነገር የሚያመለክተው ነገር የሌለ በመሆኑ ምክንያት ከጥያቄው እዚጋ አይገናኝም ፍ/ቤቱ ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ሰወችን በተመለከተ የሰሙትን ምስክሩ ከመናገራቸው ውጪም ኢማሞች ላይ የደረሰ ጉዳት

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

አላውቅም ያሉ በመሆኑ በዚሁ እንዲስተካከል ብሏል ፍ/ቤቱ ስለዚህ /ግልጽ ያልሆነ/ ጥያቄዎች ነው

- እሺ ምስክር እነዚህ ተከሳሹ በሼህ አብዱራህማን አማካኝነት የሚቀጠሩ ሰወች ስለቀደመው እስልምናስ ምን ይላሉ?
- የተከበረው ፍ/ቤት ተቃውሞ አለን
- መቃወሚያው ምንድን ነው ?
- አሁን ስለቀድሞው ስለአሁኑ ብሎ ሲጀመር አልተነሳም ማለት እኔ ክርክር ብናደርገው ጭቅጭቅ እንዳይሆን እንደው ለፍ/ቤቱ የቀድሞ የአሁን ብለው ያነሱት ጉዳይ የለም ባላነሱት ነገር ለምንድን ነው ማለት የተነሳ ነገር ጭብጡም ላይ የለም የቀድሞ ምን ተደረገ የአሁን ነው ብለው አቃቤ ሕግ አቃቤ ሕግ እያስመሰከሩ ሳይሆን ምስክርነት እየሰጡ ነው የሚመለስለው አላሉም ምስክርነትም ላይ የለም ጭብጡም ላይ የለም
- መልስ ስጡበት አቃቤ ሕግ
- ምስክሩ እራሳቸው እኔ ከቅድም ጀምሮ ስንጠይቃቸው የነበረውን ቀደም ብለን ሼህ አብዱራህማን ከመምጣታቸው በፊት ጀምሮ እኛ የእስልምና እምነት ተከታዮች ነን ሼህ አብዱራህማን ከመጡ በኋላ በተቀጣሪዎቻቸው አማካኝነት እንዲህ እንዲህ እያሉ ሲሰብኩ ነበር ብለው እስከ አሁን ሲዘረዝሩ የነበሩት ነገር አለ አሁን የጠየቅናቸው ጥያቄ ሼህ አብዱራህማን ከመምጣታቸው በፊት እርስዎ የሚከተሉት እስልምናን በተመለከተ እነዛ አሁን የተቀጠሩ ሰወች የሚናገሩት ነገር አለ ወይ ብለን ነው የጠየቅነው ምስክሩ ካሉት ተነስተን ማለት ነው እንጂ አዲስ ያመጣነው ነገር የለም ስለዚህ አሁን አግባብ ያልሆነ መቃወሚያ ነው ውድቅ እንዲደረግልን ነው የምናመለክተው
- መርምሮ ትእዛዝ ሰጥቷል የከሳሽ አቃቤ ሕግ ጥያቄ ተከሳሽ ወይም በነአብዱራህማን የተቀጠሩ ሰወች ስለቀድሞ እስልምና ምን ይላሉ የሚል አጠቃላይ ጥያቄ ነው እና ምስክሩ ከዚህ በፊት ከሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር ተያይዞ እና ከጉዳዩጋር ተያይዞ ይሄ ጥያቄ ያልተነሳና ወይም ከጉዳዩጋር ግንኙነት የሌለው ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም እና ጥያቄው ይቀጥል ተብሏል ከዚህ በተጨማሪም ጥያቄ በሚጠየቅበት ሰዓት እና መልስ በሚሰጥበት ሰዓት ድምጽ እየተነሳ ነው በተከሳሾች ስለዚህ ሂደቱን ሊያውክ ስለሚችል ድምጽ አታሰሙ ብሏል ችሎቱ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክር ይቀጥሉ እስቲ ምን ይላሉ ስለቀድሞ እስልምና የሼህ አብዱራህማን ተቀጣሪዎች ?
- በፊት እሳቸው በቀጠሩት እና በፊት ከነበሩት የሚሰራው ተቃራኒ ነው
- ምንድን ነው ይላሉ የቀደመው የድሮው እስልምና ?
- የበፊተኞቹ መውሊድ ያወጣሉ አንዳንድ ነገር በሳምንት አንዴ ዱአ ያረጋሉ አሁን በእሳቸው የተቀጠሩት ደግሞ ይዜንን ከለከሉት
- ለምን ምን ሆነ ብለው ?
- ያ አሮጌ እምነት ነው በሚል
- እንዴት አሮጌ ማለት?
- ይዜ ነው ይዜንን ያዙ ይዜ ነው ጥሩ ይዜ ነው ንፁህ ብለው ነው ያንን የከለከሉት
- እሺ እስከ አሁን ሲመሰክሩ ለቅሶ የለም የቀደሙ ሼኮች ሙስሊሞች አደሉም ሙስሊም መንግስት ይምጣልን እንዲህ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ይሰብኩ ነበር ብለዋል እነዛ ሰባኪዎች ቅድም በስም የጠራችሁ እነዚህን ሁሉ ሰባኪዎች የቀጠራቸው ማን ነው?
- ሼህ አብዱራህማን ነው
- ደሞዝ የሚከፍላችሁ ማን ነው ?
- አቃቤ ሕግ ጥያቄውን አትድገሙት
- እሺ ዋና ጥያቄ አብቅተናል
- ዋና ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የተከሳሽ ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ይቀጥሉ ተብሏል ለአንድ ደቂቃ ትታገሳላችሁ
- አቶ ከድር ቅድም ሼህ አብዱራህማን መስኪድ ያስተዳድራሉ በወር አንድ ጊዜ ነው የሚመጡት ብለዋል ትክክል ነኝ?
- አዎ
- መስኪድ ያስተዳድራሉ ሲሉ ምን ማለቶ ነው?
- እሳቸው የቀጠሯቸው ሰወች ይሰራሉ ወይስ አይሰሩም በሚል እየመጡ ጉብኝት ያደርጋሉ
- እሳቸው ሰወችን ስለመቅጠራቸው በምንድን ነው ያወቁት?
- እሳቸው የቀጠሯቸው ሰወች ነገሩኝ
- ስለዚህ እርስዎ አላዩም አደለም?
- እኔ ሲመጡ አያቸው ነበረ እነሱም ደግሞ ሲነግሩኝ ነበረ

16/12/32

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እነዛ የነገሮት ሰወች እውነት ይናገሩ አይናገሩ በምን ያውቃሉ እርስዎ?
- ይዜንን እማውቀው ነገር የለኝም እውነት ይናገሩ ውሸት ይናገሩ የማውቀው ነገር የለም
- እሳቸው በሚመጡት ምክንያት ደግሞ ነገሩ እውነት መሆኑን አውቄያለሁ ያለው ግን እሳቸው ነገሩን እውነት መሆኑን ያረጋገጥኩት እሳቸው በሚመጡበት ጊዜ አብረው ሲነጋገሩ አይቻለሁ ብለዋል አብረው ሆነው ሲነጋገሩ መስኪድጋ አይቻቸዋለሁ ሰወቹን ሰብስበው አንድላይ ሲነጋገሩ አይቻለሁ
- ሰወች የሚሏቸው እነማን ናቸው?
- አላውቃቸውም ብዙ ናቸው ግን ቅድም የተናገርኩትን ነው እኔ የማውቃቸው በስም
- ስንት ይሆናሉ በቁጥር ?
- በግምት ሃምሳ ስድሳ መቶም ሊሆኑ ይችላሉ በግምት
- እነዚህ ሁሉ ነው የነገሮት መቀጠራቸውን?
- አቤት ስለሚጠጉ እኮ ያስተጋባል
- እነዚህ ሃምሳ ስድሳ መቶ የሚሆኑት ነው እነዚህ ሁሉ መቀጠራቸውን ከአያንዳንዳቸው ነው የሰሙት እያንዳንዳቸውን ነው ያናገሩት?
- እኔ ጥቂት ሰው ነው ያነጋገርኩት እና ብዙ ሆነው ሲቀጠሩ ደግሞ ይነግሩኛል
- ሼህ አብዱራህማን እነዚህ ሰወች ሰብስበው ሲያናግሩ እርስዎ ተሰብስበዋል እንዴ አብረው?
- እኔ አልተሰበሰብኩም
- እርስዎ እንዴት ለመጠየቅ ቻሉ ?
- እኔ እዛ መስኪድ ለሰላት ሄጀነው ያየሁት እዛ ጠይቄ መልስ ተሰጥቶኛል
- ጥሩ ቅድም ሼህ አብዱራህማን መስኪዶችን እንደሰሩ ነግረውናል የሕዝቡስ ተሳትፎ ምን ነበር?
- እኔ ከሕዝቡጋር የሚገናኝ አይደለም እራሳቸውን ችለው እራሳቸው ስለሚሰሩ
- ሕዝቡ ምንም አልተሳተፈም ነው እቃ በመግዛት?
- አላየሁም እኔ እሱን አላውቅም
- ሼህ አብዱራህማን መስኪዱን እራሳቸው ነው ወይስ በሌላ ሰው ነበር የሚያሰሩት ይሰራሉ ሲሉ ምን ማለቶ ነው ?
- በሰራተኛ ነው የሚያሰሩት

1613 23

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም አረቦች በዛ አካባቢ ሲያልቅ ሲመረቅ ስላየኋቸው ገንዘቡ ከወጭ አገር ከአረቦች እንደሆነ አውቄያለሁ ብለዋል ካሳሳትኩኝ አርሙኝ እንደዛ ነው ያሉት?
- ትክክል ነው
- ከዚህ ውጭ አረቦች ገንዘብ ሲሰጡ አላዩም አደል?
- ብር ሲሰጡ አላየሁም
- እርስዎ ቅድም ሙስሊም ስወለዱ ጀምሮ ሙስሊም እንደሆኑ ተናግረዋል በሕይወቶ አረቦች በዛ አካባቢ ሲመጡ አላዩም እንዴ ?
- አላየሁም እኔ ግን ከእሳቸውጋ አብረው ሲሄዱ ነው ያየሁት እንጂ
- ጥሩ መስኩድ በእርዳታ ሲሰራስ አያውቁም ከሼህ አብዱራህማን ውጭ መስኪድ በእርዳታ ሲሰራ አያውቁም?
- አዎ ሕዝቡ ይሰራል በእርዳታ ሕዝቡ ሲሰራ አያዋለሁ
- ቅድም አስተማሪዎችን አናውቃቸውም ከተለያየ ቦታ ነው ብለዋል ከከተለያየ ቦታ መጥተው የሚያስተምሩ አስተማሪዎችን አያውቁም በመስኪድ የግድ ሁሉም ሰዎች ከአካባቢው ብቻ ነው እንዴ የሚያስተምሩት?
- በብዛት ከሩቅ የመጡ ናቸው የሚያስተምሩት እንጂ ከአካባቢ ሲያስተምሩ እኔ አላየሁም
- እነዚህ የቀድሞ ሼሆች የሚሏቸው በሕይወት ያሉ ወይ የሌሉ ናቸው ምን ማለት ነው ?
- ያለም አለ
- የሌለም አለ?
- የሌለውን እኔ የማውቀው የለም
- ለምንድን ነው የቀድሞ ሼኮች የሚሏቸው ?
- አላውቅም እኔ
- ማለት ቅድም የቀድሞ ሼሆች እያሉ ይመሰክሩ ነበረ እኮ ለምንድን ነው የቀድሞ የተባሉት?
- እኔ እንደገባኝ የመጀመሪያዎቹ መውሊድያደርጋሉ ዱአ የተለያየ ነገር ያደርጋሉ በዛ ተደግፈው ነው ሊባል የቻለው
- እኮ የመጀመሪያዎቹ ይላሉ የአሁኖቹ የመጀመሪያዎች ሲሉ አሁንም ግልጽ አላረጉትም የመጀመሪያ ማለት ወይም የቀድሞዎች ማለት አሁን ምን ስለሆኑ ነው የቀድሞ የሚባሉት?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አሁን የመጡት ተቃራኒ ስለሚሰሩ እና እነሱ ወደኋላ ስለቀሩ የበፊተኞቹ ተባሉ
- ስለዚህ ጡረታ ወጥተዋል ማለቶ ነው ስላልገባን እኮ ነው ጡረታ ወጥተዋልነው አይሰሩም ማለት ነው?
- እነሱን የቀጠረ የለም አላውቅም እኔ
- ቅድም በነሱ መስገድ አይቻልም ይላሉ ስለዚህ መጀመሪያውኑ እኮ አያሰግዱም ማለት ነው አደል?
- እነሱ ያሰግዳሉ ግን ከነሱጋር ሰላት አናደርግም ብለው ነው እምቢ ያሉት
- ቅድም እነዚህ አስተማሪዎች ያሏቸው የሚያስተምሩትንም ነገር ነግረውናል ከነዛ ውስጥ አንዱ ወለድ ይከለክላሉ አሉ ከምን አንፃር ነው ይሄ የሚከለክሉት?
- ከምን ተነስተው እንደከለከሉ አላውቅም እኔ
- በእምነቡ የእምነት አስተማሪዎች ናቸው በእምነቱ አይከለከልም እንዴ ወለድ ?
- እኔ የማውቀው ነገር የለም
- እነዚህ አስተማሪዎችን ያሏቸው በስም የጠቀሷቸው አሉ አንድ 4 አንድላይ ነበር የሚያስተምሩት ወይስ በተለያየ ጊዜ ነው?
- በተለያየ ጊዜ በተለያየ ቦታ ሲያስተምሩ ነው እንጂ አንድ ቦታ ሲያስተምሩ እኔ አላየሁም
- ጊዜውን ያስታውሱታል መቼ እንዳስተማሩ?
- ጊዜውን አላስታውስም
- ቦታውን ያስተማሩበት ቦታን?
- ሻሸመኔ 04 መስኪድ ብዬ ነበረ አራዳ የሚባል 07 ትልቅ መስኪድ ብያለሁ ስለዚህ እሳቸው በቀጠሩት መስኪዶች ሁሉ ይሰራሉ ሰወቹ
- ስለዚህ እነዚህ ሼህ አብዱራህማን በወር አንዴ ስለሆነ ሻሸመኔ የሚሄዱት እነዚህ ሰወች ሲያስተምሩ ሼህ አብዱራህማን ይኑሩ አይኑሩ የሚያውቁት ነገር የለም አደል?
- አላውቅም አዎ
- ሼህ አብዱራህማን እንደዚህ አይነት አስተምሩ ብሎ ሲያዙ በጆሮ ሰምተዋል እርስዎ?
- አልሰማሁም
- ሼህ አብዱራህማን እራሳቸው ቆመው አሁን ያሉት ትምህርት ሲያስተምሩ ሰምተዋል በጆሮ?
- አልሰማሁም

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ከጠቀሷው ከሚያስተምሩ ሰወች አንዱ ሰላማዊ መንግስት አላህ ያምጣልን ብሎ ሲናገር ሰምቻለሁ ብለዋል ትክክል ነኝ ?
- አዎ
- ይሄ ማለት ምንድን ነው ምርቃት ነው እርግማን ነው መፈክር ነው ምንድን ነው ይሄ ምኞት ነው እንዴት ተረዱት?
- ይሄ የግል አስተያየት ነው ይሄንን ብለዋል ያንን ብለዋል ያንን ስለማለታቸው አውቃለሁ /ግልጽያልሆነ/
- ይሄን ያስተማረው በመስኪድ ውስጥ ነው አደል?
- አዎ መስኪድ ውስጥ ነው የተናገረው
- ቆመው ነው ቁጭ ብለው?
- ቆመው
- ሕዝብ ነበረ?
- ነበረ አዎ
- ምን አለ ሕዝቡ ?
- ምንም አላለም
- ምስክር ሼህ አብዱራሕማን የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው በአካባቢው ላይ መኖሪያ ቤት እንዳላቸው ያውቃሉ ?
- አውቃለሁ አዎ 05 ቀበሌ ውስጥ
- እዛ ትዳር አላቸው አደል?
- አዎ በጆሮ ሰምቻለሁ እንዳላቸው
- በአካባቢው ላይ ባሉ መስኪዶች ውስጥ የአካባቢው ሰው ያለ ምንም ችግር አንድላይ ይሰግዳል አደል በመስኪድ ውስጥ ?
- ይሄን የማውቀው ነገር የለም
- እርስዎ መኪድ እየገቡ ይሰግዳሉ?
- አዎ ገብቼ ሰግጀ እወጣለሁ
- የአካባቢው ሰው ያለ ልዩነት ገብቶ ሰግዶ ይወጣል?
- አዎ እኔ በምሄድበት ጊዜ ገብተው ሰግደው የሚወጡትን አያለሁ

1616 26

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ሼህ አብዱራህማን መስኪድም ያሰራሉ በግላቸውም ከገንዘቡ ላይ ይጠቀማሉ ብለዋል ለግላቸው የሚጠቀሙት ገንዘብ ከራሳቸው ይሁን ወይስ ከሌላ ምንጭ ያገኙት ይሁን በምን አወቁ?
- ሌላ ስራ ስለሌላቸው ለንግድ ስለሌላቸው እንደራሴ ሃሳብ ልል ችያለሁ
- ሃሳቦት እንጂ ያረጋገጡት ነገር አደለም አደል ?
- ከሰወች ወሬ ነው የሰማሁት በዚሁ እየሰሩ ነው ሲባል
- እሺ ቀደም ብለው ትምህርት ያስተምሩ ነበር በአካባቢው ላይ የነበሩ አዛውንቶች ወይ ኢማልሞች ሊሆኑ ይችላሉ እውቀት የላቸውም ተብሎ በመስኪድ ካለመቀጠራቸው ውጪ ምንም የደረሰባቸው ነገር የለም አደል ?
- እኔ መልሼ ነበረ ስለነዛ ሰወች የማውቀው ነገር የለኝም
- በአካባቢው ላይ ችግር ደረሰበት የተባለ ሰው የለም ከኢማሙ ?
- እማውቀው ነገር የለም በዚህ ጉዳይ
- ጨርሰናል
- መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የከሳሽ አቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ ሼህ ከድር አሁን በመጨረሻ ከተጠየቁት ማለት ነው በመስኪድ ውስጥ ያለ ምንም ችግር ይሰገዳል ወይ ተብለው ይሰገዳል ወይም አይሰገድም ተብለው ሲጠይቁ የማውቀው ነገር የለም ብለዋል በዋና ጥያቄ ሲጠየቁ በዚህ መስኪድ ተቃራኒ ነገር ስለሚደረግ ነው ብለዋል ተቃራኒ ብለው ያሉት እና ያለ ምንም ችግር ይሰገዳል የሚሉትን እስቲ ይንገሩን ?
- ስግደት በሁሉም መስኪድ ደው ሰላት ያደርጋሉ እላቸው በሰሩት መስኪድ ውስጥ የበፊተኞቹ የሚሰሩት ስራ አይሰራም
- እሱን ለማለት ፈልገው ነው ቅድም ያብራሩትም?
- እሺ እዛ የጠቀሱት ቦታ ሻሸመኔ ከዚህ በፊት ሕዝቡ መስኪድ አሰርቶ ያውቃል ብለዋል እነዚህ በህዝብ የተሰሩ መስኪዶች ሲሰሩ እና ሲመረቁ አረቦች መጥተው አስመርቀዉ ያውቃሉ?
- መጥቶ የመረቀ የለም
- አሁን በእናንተ በሻሸመኔ ቀድሞ በተሰሩ መስኪዶች ሰወች መጥተው ሌሎች ከሌላ ቦታ መጥተው አስተምረው አያውቁም ወይ ተብለው ሲጠየቁ ይመጣሉ ብለዋል እነዚህ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

እየተጋበዙ በሌላ ምክንያት የሚመጡት እና አሁን ሼህ አብዱራህማን አመጧቸው የሚሏቸው ኢማሞች ልዩነታቸው ምንድን ነው?

- ልድገምሎት?
- አዎ
- ሼህ አብዱራህማን የሚያመጧቸው ኢማሞች ወይም ቅድም ቀጠሯቸው ያሏቸው ሰው አሉ አደለ የኃይማኖት አስተማሪዎች ?
- አዎ
- እነሱ እና በተለመደው በነባሩ ቀድመው በተሰሩ መስኪዶች እየተጋበዙ የሚመጡ የኃይማኖት አስተማሪዎች ልዩነታቸው ምንድን ነው ?
- መጀመሪያ በተሰራው ቤት በተሰራው መስኪድ ውስጥ እንደ መውሊድ ይሰራል በእሳቸው ውስጥ ደግሞ አይሰራም ልዩነቱ ይሄንን ነው የማውቀው እኔ
- አስተማሪዎቹ እዛው የሚሰሩ ናቸው ?
- አስተማሪዎቹ ደግመ በሕዝቡ ውስጥ መጥተው አይሰሩም
- የተለያየ መስኪድ
- እሳቸው በሰሩት ውስጥ ብቻ ነው የሚሰሩት
- ቅድም እነዚህን ያስተማሩት ተቀጠሩ የተባሉት አስተማሪዎች በእሳቸው ስለመቀጠራቸው በምንድን ነው ያወቅከው ስትባል ሰብስበው ሲያናግሯቸው ስላየሁ ነው ብለዋል ሁሉንም ኢማሞች ነው እንዴ የሰበሰቧቸው እዛ አካባቢ የነበሩ አጠቃላይ በተለያዩ መስኪዶች የነበሩ ሁሉንም ኢማሞች ነው ሰብስበው የነበሩት ?
- በሁለት መልክነው እነዚህ ሰወች የተቀጠሩት የአካባቢ አማኞች የሚያስተምሩ እና መስኪድ ውስጥ ደግሞ ኢማም ሆነው ቁርአን የሚያስተምሩ በዚህ መልክ ነው
- ቅድም ሲሰበስቧቸው ስላየኋቸው ነው ብለሃል ሁሉንም ኢማሞችን ነው ወይ የሰበሰቡት ሻሸመኔ አካባቢ የነበሩትን ?
- ኢማሞች እና አስተማሪዎችን አንድላይ ሰብስበው ደሞዝ ሲሰጡ ነው ያየሁት
- ቅድም እነዚህ አዲሶቹ መስኪዶች ላይ የተሰሩት መስኪዶች ላይ ሌሎች ቀድመው ኢማሞች ለምንድን ነው ያልተቀጠሩት ተብለው ሲጠየቁ እነሱ የሚሉት እውቀት ስለሌላቸወ ነው ብለዋል አንተ እንደዛ ነው ወይ እንደኃይማኖት ወይም ደግሞ እዛ እንደነዋሪነት እንደ አማኝነትህ በዛ ነው ወይ የማይቀጠሩት ወይም ደግሞ እዛ መስኪድ የማይሰሩት?

1618
34

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መቃወሚያ ምንድን ነው
- ይሄን አስመልክቶ እኛ በመስቀለኛ ጥያቄ አላነሳንም ኢማሞች እንዴት ይቀጠራሉ አይቀጠሩም ብለን አልጠየቅንም አንድ ሁለተኛ ደግሞ አሁን ምኛልባት አቃቤ ሕጉን እየጠየቅኳቸው ያሉት አስተያየት ነው ቅድም በራሳቸው ጥያቄ እንዳሉት ልክ ነው እውቀት የላቸውም ስላሉ ነው የማይቀጥሯቸው ብለው አረጋግጠዋል ያንን በተመለከተ እኛ ያነሳነው ነገር የለም ከዛ ባለፈ ግን አሁን አቃቤ ሕግ እየጠየቋቸው ያሉት አስተያየት እንዲሰጡ ነው የግል አስተያየት መፈቀድም የለበትም ከዛ ባለፈ
- የምጨምረው የተከበረው ፍ/ቤት ቅድም እኔ የግል አስተያየታቸውን ጠይቄ ተከልክያለሁ ስለዚህ አሁንም የግል አስተያየተቸው ስለሆነ ሊፈቀድ አይገባም
- አሁን አንድ ነገር አሁን ስለተነሳው ጥያቄ እናውራ ምክንያቱም ስላለፈው ነገር ስናወራ ጊዜ ነው የሚያጣብበው ምናልባት የማይታለፉ ብይኖች አሉ እነሱ የማይታለፉ ብይኖች አይታለፉም ደግሞም አይነሱም ሁላችንም የምናውቀው ነው የሚሆነው አሁን ምንድን ነው የሚሆነው ስለአሁኑ በቃ ቅድም ተውነው አሁን የግል አስተያየታቸውን እየተጠየቁ ነው በቂ ነው
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት በትናንትናው የችሎት ውሎ አልነበርኩም ነገር ግን የግል አስተያየት ምናልባት ምስክር የሚከለከለው ማጠቃለያ ሲሰጥ አሁን የተረዳውን ነው እየተጠየቀ ያለው ነገር ግን አሁን ከእሳቸው መጨረሻ ከጠየቁት ጠበቃ አስቀድሞ የጠየቁት በመስቀለኛ ጥያቄ ይሄን አላነሳነውም ብለዋል ነገር ግን አንስተውታል ከእሳቸው በፊት የጠየቁ ጠበቃ አንስተውታል እነዚህ ኢማሞች እዛች መስኪድ ውስጥ መግባት ያልቻሉት በእውቀት ማነስ ነው አደል ብለዋቸው አሉ የሚለውን አሁን በዳግመኛ ጥያቄ ያንን ለማብራራት ነው እንጂ እሳቸው ጠይቀውታል ምናልባት የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አደለም ግን የፋክት ጉዳይ ነው ይሄ አልተጠየቀም ተጠይቋል የሚባል እዚህ ችሎት ውስጥ የሚሰማ ስለሆነ ከእሳቸው ከአቶ ሃሰን በፊት የነበሩት ጠበቃ ጠይቀዋል ይሄንን በመስቀለኛ ስለዚህ ያንን ነው አሁን እያብራራን ያለነው በዚህ በዳግመኛ ጥያቄ /ግልጽ ያልሆነ/
- ፍ/ቤቱ የቀረበውን መቃወሚያ እና ምላሹን መርምሮ ትእዛዝ ሰጥቷል ለመቃወሚያው መሰረት የሆነው ጥያቄ በመስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቁ ተረጋግጧል መስቀለኛ ጥያቄ ላይ በዳግመኛ ጥያቄው ላይ ለማብራራት ተብሎ የቀረበውን ጥያቄ ተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ጠይቀው ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል ስለዚህ ጥያቄው የግል እምነትን መሰረት

39 1619

http://ethcriminalawnetwork.com/

አርጐ አይደለም የተጠየቀው ተብሎ የሚባል ከሆነ ዳግመኛ ጥያቄው ሲቀርብ የግል እምነት ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ሊወስደው አልቻለም ስለዚህ ያንን ጥያቄ መሰረት ተደርጐ ለማብራራት የሚቀጠሩትን መምህራኖች በምስክሩ አገላለጽ ወይም በጠበቃው በገለፀት አገላለጽ ኢማሞቹ የሚቀጠሩት ወይም እንዳይቀሩ የተደረጉት ምንን መሰረት አድርጐ ነው የሚለውን መርጠው ምስክሩ መልስ እንዲሰጡበት አድርገዋል ያንን ደግሞ ለማብራራት የእሳቸውን /ግልጽ ያልሆነ/ አቃቤ ሕግ ያቀረበውራ ጥያቄ ተገቢ ነው ብለናል ምክንያቱም በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ይሄ የእሳቸው ስተሳሰብ መሰረት ተደርጐ መልስ የተሰጠበት ስለሆነ ስለዚህ ጥያቄው ይቀጥል

- ሼህ ከድር አሁን ቅድም የጠየቅኮት እዛ አሁን አዲስ በተሰሩት መስኪዶች ላይ የእዛ ቀድሞ የተሰሩ መስኪዶች ላይ ይሰሩ የነበሩ ኢማሞች ለምንድን ነው ያልተቀጠሩት?
- ያልተቀጠሩበት ምክንያት በሁለት ምክንያት ነው አንደኛው እዛ የሚሰራው ስራ ውሎች እዚህ ስለማይሰሩ ነው በአዲሱ በሁለተኛ ደግሞ ችሎታ ማነስ ይመስለኛል እኔ
- አንተ የሰማኸው አለ የችሎታ ማነት ነው ተብሎ?
- ሊቀጠሩ ሄደው አንቀጥርም ብለው ስለመለሷቸው አንዳንድ ሰወች ይነግሩኝ ነበረ
- እኮ ምን ብለው ነገሯችሁ?
- ትምርትህ በቂ አደለም በሚል
- ሌላው ቅድም ሲጠየቁ ሼህ አብዱራህማን እዛው ሻሸመኔ ትዳር እና ቤተሰብ አላቸው ብለዋል በባለሃብትነት ነው የሚታወቁት ሻሸመኔ ይሄን ሁሉ መስኪድ ሲሰሩ ሕዝቡ ያውቃቸዋል በባለ ሃብትነት በራሳቸው ሃብት ነው ይሄን መስኪድ እያሰሩ ያሉት እየተባለ ይነገር ነበር እዛ ላለ የእስልምና ኃይማኖት ለምእመኑ ?
- ሕዝብ በስፋት የሚያውቀው ከአረቦች ብር ያመጣሉ መስኩድ መስራታቸው ነው የማውቀው
- ይሄን ነው የሚያውቀው እንጂ በእሳቸው ሃብት እንደሚሰራ አደለም የሚያውቀው?
- አዎ
- እሺ ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት
- ዳግመኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የከሰዓት በፊት የችሎት ውሎውን በዚህ በመጠናቀቁ ምስክሩ ተሰናብተዋል ስምንት ሰዓት ላይ መገናኘት

1620 ፈ/ሮ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የነበረው ችሎት ቀጥሏል ዳኞች አልተቀየሩም አቃቤ ሕጐችም ጠዋት የነበሩት አሉ አልተለወጡም ተከሳሾች የቀረ ሰው አለ ስንትኛ ተከሳሽ ናቸው 29ኛ ተከሳሽ እሺ ከሰዓት በኋላ 29ኛ ተከሳሽ በሕመም ምክንያት አልቀረቡም ጠበቆች የተቀየረ አለ
- 28ኛ ተከሳሽ አህመድ ጀማል አለሁ ከዛ ውጪ ያለነው መሃመድ አብደላ ሃሰን ሁሴን አቶ በሃሩ መካንጋ አዲስ መሃመድ አሊማ ሰይድ
- እሺ ቀርበዋል አቃቤ ሕግ ባልቀረቡት ተከሳሽ ላይ የምትሉት አላችሁ?
- እሺ የተከበረው ፍ/ት ያው ይሄ የወንጀል ክስ ነው ተከሳሹ በችሎት ቀርበው ጉዳያቸውን መከታተል አለባቸው ሂደቱ እየተካሄ ያለው በጠበቆች አማካኝነት እሪፐረዘንት ተደርገው እንደውም ተወክለው ነው ክርክሩን እያደረጉ ያሉት ስለዚህ ተከሳሹ በችሎት ያልተገኙት ከፍትህ ወይም ከፍርድ ሂደቱ ራሳቸውን ለማሸሽ ወይም በተለየ ምክንያት አደለም ስለዚህ ታስረው ይቅረቡ ተብሎ የተለየ ትእዛዝ እንዲወጣባቸው ወይም ደግሞ ይቅረቡ ተብሎ ሌላ ተለዋጭ ትእዛዝ የሚሰጥበት ትእዛዝ የለም
- እሱን ለማለት ሳየሆን ልክ ነው እኛም ግልጽ ነው የምናውቀው ግን አሁን ችግሩ ምስክር በእሳቸው ላይ የምታሰሙ ከሆነ ለውጥ ስለሚያመጣ ነው እሷን ለማለት ነው
- እሺ አሁን ባለው ባለን በያዝነው ምስክር እሳቸውን የሚመለከት በቀጣይ የሚመለከት ምስክር የለንም ያው ዞሮ ዞሮ አሁን እያስመሰከርን ያለነው የተከሳሹን ተሳትፎ ነው የሚመሰከረው ግን እንደአንድ ላይ እንደ ጥቅል የሚወሰደው ያም ቢሆን ግን ተከሳሾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት ተወክለው እየተከራከሩ ስለሆነ የሚቀርባቸው መብት የለም የምናስመሰክረው እንደ ጥቅል ለሁሉም በማስረጃነት የሚቀርብ ነው ነገር ግን ያው በተሳትፎ ደረጃ ግን ዛሬ የምናስመሰክርባቸው የለም እሳቸውም ተለይው ማለት ነው
- ምን ለማለት ነው ትንሽም ቢሆን ባለፈው ችሎት እንደነበረው ካንስፓይረስም ቢሆን እሱም ቢሆን ካለ ምናልባት እስካሁን ያየናቸው አንዳንዶቹ እስካሁን ያልተነሳ አለ ስማቸው እንደዛ አይነት የሚሆን ከሆነ
- አሁን የሚመጡት ምስክር ያው እንደተለመደው የእሳቸውን ስም አያነሱም ትላንትም ያሳወቅነው እኛ ኮንስፓይሬሲቭ የሆነ ቲዎሪውንም ይመለከታል በዛው ነው ክሱም የተዋቀረው ስለዚህ አይመለከታቸውም ማለት በእኛ በኩል አንችልም ክሱን ካቀረብንበት እንትን አንባር እራሱ ይሄን ፍ/ቤቱም ይመዝነው ነው ለኛ ያለን ግንዛቤ ምስክሩ
- እሺ በቃ እንቀጥላለን

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምስክሩን አቅርቡት
- በእውነት እመሰክራለሁ ብሎ በአላህ ስም ምሏል
- 13ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክር የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆናቸው ምክንያት ቃለ መሃላውን በኦሮምኛ ቋንቋ ተፈጽሟል የምስክርነት መስጠት ሂደቱም በኦሮምኛ ቋንቋ የሚሰጡ ስለሆነ በአስተርጓሚ አቶ ሶሪ ካባ አማካኝነት እንዲሰጡ ተብሏል በመጀመሪያ ለምስክሩ በአቃቤ ሕግ አመልካችነት ለደህንነቱ ሲባል የሚገልፁት የመጀመሪያ ስሙን ብቻ እንደሆነ ንገራቸው
- ስሞት ማን ይባላል?
- ሼህ መሃመድ
- በማስረጃ ዝርዝር ውስጥ
- ለምን መጡ ዛሬ ?
- ለምስክርነት
- በማን ላይ ነው የሚመሰክሩት ?
- ሼህ አብዱራህማን
- ሼህ አብዱራህማንን ያውቋቸዋል ወይ ይለዩዋቸዋል በአካል?
- አዎ አውቀዋለሁ
- እሺ ምስክሩ በሼህ አብዱራህማን ላይ ነው የምመሰክረው ብለዋል ምሰክሩን በአካል ለይተው 27ኛውን ተከሳሽ ጠቁመዋል የከሳሽ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ይቀጥል
- እሺ ሼህ መሃመድ አሁን በችሎቱ ውስጥ የለዩዋቸውን የት ነው የሚያውቋቸው ?
- ሻሸመኔ
- ለምንድን ነው የመጡት ዛሬ?
- ለምስክርነት
- በምን ጉዳይ ነው የሚመሰክሩት ?
- መስኪድ ማሰራታቸውን
- የት ነው መስኪድ የተሰራው እስቲ ይንገሩ?
- ሻሸመኔ ውስጥም ተሰርቷል ሻላ ወረዳም ተሰርቷል
- በቁጥር ሊነግሩን ይችላሉ
- የሻሸመኔን መናገር እችላለሁ
- ምን ያህል ነው?

162 42

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ የማውቀው 9 ይሆናል
- ሌላ ቦታስ?
- ሻላ እና ሲራሮ ላይ ብዙ ሰርተዋል ሰማሁ ነው እንጂ አላየሁም
- ሻሸመኔ ላይ ተሰሩ ስላሏቸው መስኪዶች በምን መልኩ ነው እንዴት ነው የተሰሩት?
- አሰሩ ሻሸመኔ ላይ
- እኮ በምንድን ነው ማለት ከዚህ በፊት እንዴት ነው ሲሰራ የነበረው ይሄ አሁን እሳቸው አሰሩት የሚሉት በምን ማለት ከየት በመጣ ገንዘብ ነው የተሰራው ?
- በአረብ አገር ብር ተሰራ ሲባል ነው የሰማሁት
- ከማን ነው የሰሙት?
- መስኪድ ሲሰራ አይቼ ማን ነው ይሄንን መስኪድ የሰራው ብዬ ስጠይቅ እሳቸው ናቸው ያሰሩት ብለው ነገሩኝ ሲሰራም አይቻለሁ
- እኮ ማን ነው የነገሮት ነው?
- እዛ መስኪዱን የሚሰሩት ሰወች ናቸው የነገሩኝ
- አሁን የጠቀሷቸውን መስኪዶች ማን ነው የሚያስተዳድረው?
- እነሱ ናቸው የሚያስተዳድሩት
- እነሱ እነማን ናቸው?
- እነ ሼህ አብዱራህማን
- ሼህ አብዱራህማን ብቻ ነው ወይስ ሌሎች ሰወች አሉ?
- እሳቸው ቀየቀጠሯቸው ሰወች
- ምንድን ናቸው ?
- ኢማማን
- ኢማም ከየት አካባቢ የመጡ ናቸው ?
- ከየት እንደመጡ አላውቅም
- እሺ እነዚህን መስኪድ ማን ነው የሚያስተዳድረው ማለት በማን ፍቃድ ነው የተሰሩት?
- መሰራቱን ነው እንጂ አላውቀውም
- አሁን ተቀጠሩ ያሏቸውን ኢማሞች ያውቋቸዋል እዛ አካባቢ ትተዋወቃላችሁ?
- አዎ ተዋውቀናል ጥቂት ሰወችን አውቃለሁ
- ከዛ በፊት ትተዋወቃላችሁ ወይ ከመምጣታቸው በፊት?
- አናውቅም

1623 43

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ምንድን ነውየሚደረገው እስቲ ይንገሩን እነዚህ አሁን መስኪዶች ተሰርተዋል በወሬም የተለያዩ ቦታዎች እንደተሰሩ ሰምቻለሁ ብለዋል ለምንድን ነው የሚሰሩት ?
- አዲስ መስኪድ አሰራላችኋለው ብለው ለህዝብ ሲያሰሩ ነው እኔ የሰማሁት
- ሌላ እስቲ የሚነግሩን ካለ ከእኚህ አሁን ከጠቀሷቸው ምስክርጋር በተያያዘ የሚነግሩን ካለ የሚያውቁት ነገር ካለ?
- አዎ አለ
- እስቲ ይንገሩን?
- በዚህ መስኪድ ሰወቹን ሲቀጥሩ በፊት የነበሩት ኢማሞች አይቀጠሩም ሶፍዬዎች
- ለምን ?
- ሶፊያ አንወድም ነው ያሉት
- በምን ምክንያት ምክንያታቸው ምንድን ነው ሲናገሩት የሰሙት ካለ ምክንያታቸውን በምን ምክንያት ነው ?
- እኔ የሰማሁት ሶፊያ ምንም አያውቁም ነው የተባለው ለዛ ነው ብለው ነው እምቢ ያሉት
- ሌላ የሚናገሩት ነገር ካለ የሰሙት?
- እነዛ የተቀጠሩት ሰወች ሶፊያ ከሞቱ ሰላት አታድርጉላቸው ሲባል ሰምቻለሁ የተቀጠሩት
- ይሄንን ማን ነው የሚለው?
- እነሱ የቀጠሯገሮው ሰወች
- ሌላስ ከዚህ ውጪ ?
- ከዚህ ውጪ ዋብያ ነው እንጂ አንፈልግም ነው ያሉት
- ምንድን ነው ዋህብያ ?
- አሉ ያሉበት ምክንያት እኔ አላውቀውም
- መቼ ነው የት ነው የተባለው ይሄ?
- ሻሸመኔ አራዳ የሚባል መስኪድ ነው የሚተላለፈው
- ጊዜው መቼ ነው ?
- ጊዜው መቼ ነው ወሩን አመተምረቱን የሚያስታውሱ ከሆነ ?
- በ1999 ዓ.ም. ጀምሮ ነው እሳቸው የቀጠሩት የሚሉት
- ይሄን የሚናገሩት ?

1624 44

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- ይሄንን ንግግር በትክክል የተናገረውን ሰው ያስታውሳሉ በስም ?
- አዎ
- ማን ነው ?
- ሼህ ኑረዲን ስሮ
- አሁን የጠቀሷቸው ሰው ከሼህ አብድራህማንጋር ምንድን ነው ግንኙነታቸው ?
- እሱ እሳቸው ናቸው የቀሩኝ ብሎ ነገረኝ
- ሌላስ ንግግር የምታስታውሰው ካለ?
- በሶፊያዎች ላይ ሀደሃድ ታውጇል
- ማን ነው ያለው ምን ማለት ነው ጀሃድ ታውጇል ማለት ?
- ጥል ነው በሱ አትተዳደሩ በሚል
- በማን ?
- በሶፊያ
- አብራርተህ ንገረን ምንድን ነው በሶፊያ ጀሃድ አውጀናል ማለት ምን ማለት ነው ከምን ተነስቶ ምንድን ማለት ሶፊያዎች ላይ ጀሃድ አውጀናል ከምን ተነስቶ ነው በምን ምክንያት ነው?
- ሶፊያ ሽርክ ነው የሰሩት ብሎ ነው ከአላህጋር ሌላ ጨምረዋል ብለው ነው የሚሰድቧቸው
- አሁን የተናገሩት ምን ማለት ነው ሽርክያ ነው ያሉት ?
- ከአላህ በታች ባህልም አይተውም ብለው ነው የሚጠሏቸው
- ይሄንን ማን ነው የሚለው?
- ሌላ እሳቸው የቀጠሩት ሌላ አለ
- ማን የሚባል?
- ሼህ ጀማል ቃሲም የሚባል
- መቼ ነው የት ነው የተናገረው ንግግር ?
- ሶል የሚባል መስኪድ ነው እሱ የተናገሩት
- ከዚህ ውጪ የምታስታውሰው ንግግር አለ አሁን በእሳቸው ተቀጠሩ ብለህ በነገርከን ሰወች የተደረጉ ንግግሮች በመስኪዶች ?
- የእስላም መንግስት አምጣልን አሉ ዱአ ይለምናሉ እንደዛ ብለው

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የት ነው የሚለምኑት እንዴት ነው እሱን አብራርተህ ንገረን የት ነው ቦታው ለማን ነው እዛ ?
- ትልቁ መስኪድ አራዳ ከተማ ሻሸመኔ ከተማ
- እነማን ናቸው የሚሉት ?
- ሼህ መሃመድ በዳሶ
- እኚህ ምንድን ናቸው ይሄን የተናገሩት ምንድን ናቸው ?
- ተቃውሞ አለን
- ያስመዝግቡ
- ምስክሩ የተናገሩት ዱአ ወይም ፀሎት ያደርጋሉ እያሉ ነው አቃቤ ሕግ ደግሞ ሲጠየቁ ይሄንን የተናገሩት ማናቸውም ንግግር እና ኃይማኖታዊ ፀሎትን የመደባለቅ ነገር አለ ይሄንን ዱአ ያደረጉት በእሳቸው ቋንቋ ወይም በእሳቸው አንደበት ይሄንን ዱአ ያደረጉት ማን ናቸው ተብሎ መጠየቅ አለበት እንጂ መንፈሱ አጠያየቁ ተቀይሮ መጠየቅ ይኖርበታል
- እሺ አቃቤ ሕግ
- አልገባኝም የተከበረው ፍ/ቤት ምናልባት ተርሚኒሎጂውን ነው እያረሙኝ ያሉት ማለት በኃይማኖት ንግግር አሁን ዱአ ተደረገ የተባለውን ንግግር ብሎ መየቀሩ ስተት ነው ብለው እያረሙኝ ከሆነ አልገባኝም በዛ መልኩ ከሆነ ተርሚኖሎጂውን እያረሙኝ ከሆነ ማለት ነው
- ክርክሩ ኃይማኖታዊ ፀሎት ወይም ዱአ አደረጉ እያሉ ነው እየተናገሩ ያሉት ሲተረጉምም ተርጓሚው ይሄንኑ ነው ያሉት እና አቃቤ ሕግ ትርጉሙን ይዘው ኃይማኖታዊ ተርሙን ካላወቁት ዱአ ብለው ነው መጠየቅ ያለባቸው እንጂ ንግግር አርገው ከጠየቁ በኋላ ላይ የሚመሰከረውንም እኛ የምንጠይቀውንም ጥያቄ አፈክት የሚያደርግ ስለሆነ በምስክሩ አንደበት ይጠየቁ ነው ጥያቄው ተርጉመው ሳይሆን በምስክሩ ቋንቋ ይጠይቁ
- እሺ ለማስተካከል እንሞክራለን የቃላት ስለሆነ ማለት ነው
- የስላማዊ መንግስት ያምጣልን ብለው ዱአ ይለምናሉ ብለዋል ቅድም እሱን ምስክር ግልጽ ያርጉልን እስቲ ዱአ ማለት ምንድን ነው?
- መጥራት ይሄንን አንፈልግም ይሄንን አምጣልን ብለው እግዚአብሔርን መለመን ነው
- እሺ አሁን ያሉት እርስዎ በገለፁት ዱአ ያሉት ለማን ነው ይሄንን ሲገልፁ የነበሩት ?

1626 2/6

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለሕዝብ
- እንዲህ አይነት ፀሎት በኃይማኖቱ ይደረጋል ወይ ዱአ አሁን ያሉት በኃይማኖት ትምህርት መሃከል እንዲህ ተብሎ ትምህርት ይደረጋል ፀሎት ይደረጋል ወይ እንደው ዱአ ይደረጋል ወይ እንዲህ ተብሎ እርስዎ በሚያውቁት ማለት ነው እስካሁን ባሎት እውቀት እስላማዊ መንግስት ያምጣልን ተብሎ ዱአ ይደረጋል ወይ በመስኪድ ደረጃ ለሕዝብ እንደዚህ በሚደረግ የኃይማኖት አስተምሮ ላይ?
- የለም
- አሁን የገለፁትን አሁን ያሉት እስላማዊ መንግስት መመስረት የሚለው በዱአ ብቻ ነው ወይስ በንግግር አለበት ከዚህ ውጪ የሰሙት ነገር አለ በንግግር በቅስቀሳ መልክ ?
- የሕዝብ መነሳሳት ነው
- የተረዱት ነው ይሄ ?
- አዎ
- አላማውን ነው የነገሩን የተረዱትን ነው እየነገሩን ያሉት ?
- ገብቶኛል
- ለምን አላማ ነው የሚደረገው ይሄ?
- ለስግደት ገብቼ ነው የሰማሁት
- እኮ ለምን አላማ ነው ይሄ እየተደረገ የነበረው?
- ሰውን ለማጋጨት
- ማለት እስቲ ይግለፁት ሰው ለማጋጨት ማለት ?
- ሶፊያ እና ዋቢያ ብሎ ለይቶ እነሱን ለማጋጨት ነው
- ይሄንን ንግግር እያደረጉ ያሉት ?
- አዎ
- ጨርሰናል የተከበረው ፍ/ቤት ዋና ጥያቄ
- የአቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የተከሳሾች ጠበቆች መስቀለኛ ጥያቄ ያቅርቡ ተብሎ ምስክሩ የሰጡት መልስ
- እሺ መሃመድ አሁን ሶፊያ እና ዋህቢያ ለማጋጨት ነው ብለዋል ምንድን ነው ሶፊያ እና የአካባቢው ምንድን ነው ሶፊያ እና ዋህቢያ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሶፊያ ማለት በመንግስት እየተገዙ የእምነት ተከታዮችን ሳይለያዩ አንድላይ የሚያስተዳድሩ ናቸው ሰውን አያበላልጡም ዋብያ ደግሞ እኛ ነን ንፁሆች ጀነትን የምናገኘው እኛ ነን ነው የሚሉት
- ጥሩ እርስዎ ቅድም ሁለቱን ለማጋጨት ብለዋል ምንድን ነው ያካባቢው ሰው ሁለቱም ነው ማለት ነው ሶፊያም ዋህብያም ነው ?
- ጥያቄው ግልጽ አደለም የአካባቢው ሰወች አደሉም ነው ወይስ ምንድን ነው?
- የአካባቢው ሰው ቅድም ለማጋጨት ነው ሁለቱን ለማጋጨት ነው የሚያስተምሩት የሚል ነገር ብለዋል ስለዚህ የአካባቢው ሰው ሶፊያ እና ዋህብያ ነው?
- አዎ
- የትኛው ይበልጣል?
- ምኑ
- ከሶፊያ እና ከዋህብያ እርስዎ በሚያውቁት ?
- እኔ ለክቼ የለየሁት ነገር የለም
- መገመት አይችሉም?
- እንዲህ አይነት ምላሽ ከሰጡ ወደሌላ ጥያቄ መሄድ ነው አላውቅም ነው ያሉት
- ሁለቱም አንድ መስኪድ ነው አደለም የሚሰግዱት ?
- አንዳንዱ ይገባል ሌሎቹ ደግሞ ስለሚፈሩ ሶፊያ መስኪድ ነው የሚሰግዱት
- ቅድም ሼህ አብዱራህማን መስኪድ በሻሸመኔ እና በሻላ ሰርተዋል ብለዋል ስለመስራታቸው በምንድን ነው የሚያውቁት እርስዎ ሼህ አብዱራህማን ስለመስራታቸው?
- የሻላና የሽራሮን ሰማሁ እሳቸው ናቸው ያሰሩት በሚል የሻሸመኔን ደግሞ ከአረቦችጋር አብረው እየሄዱ ሲመርቁ ነው ያየኋቸው
- አሃ ሲመርቁ ስላዩ ነውሰሩ የሚሉን?
- ሲሰራም ደግሞ እዛ ያሉት እሳቸው ናቸው የሰሩልን ብለው ነገሩኝ ስጠይቃቸው
- በመስኪዱ ውስጥ ያሉ ኢማሞች ሼህ አብዱራህማን ናቸው የቀጠሯቸው ብለዋል በምን አወቁ ይሄንን?
- ሰወቹ ናቸው ከእሳቸው ደሞዝ እንበላለን በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ነው ስንሰራ ያለነው አሉ
- እርስዎ ለምን ጠየቁ ሰወቹን ቤት አሉት ?

1628 2/8

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ሰወቹ ናቸው የነገሩኝ አንተም በዚህ ውስጥ ግባ ብለውኛል በእኛ ሕግ ውስጥ ግባና
- ሰወቹ እውነት ይንገሮት ሃሳት ማረጋገጥ አይችሉም አደል እነዚህ ሰወች ?
- አቤት
- ሰወችን አምነት ይዜንኑ ከመንገሮ በስተቀር እውነት ይናገሩ ወይም አይናገሩ ይዜን ማረጋገጥ አይችሉም?
- እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ
- በምን ያረጋግጣሉ ?
- አጂ ከተማ ላይ ተሰብስበው አገኝኋቸው ምንድን ነው የምትሰሩት ብዬ ስላቸው ከዚህ በፊት ስለነገርንህ እየከፈሉን ነው ያሉት ብለው ነገሩኝ
- ተሰብስበው ያዩት ኢማሞችን ነው?
- አዎ
- ጥሩ ቅድም እነዚህ ዋህብያዎች ሶፊያዎችን ይጠላሉ የሚል ነገር ተናግረዋል ሶፊያዎችን ዋህብያዎችን ይወዳሉ?
- ሶፊያ ማንንም ሰው አይጠላም ይወዳል እንጂ
- ጥሩ ተቀጣሪዎቹ ሶፊያ አለመሆናቸውን በምን አወቁ ኢማሞቹ?
- በሶፊያ ላይ አዋጅ ስላስተላለፉ ነው ጥሉዋቸው ስለተባለ
- እነዚህ ኢማሞች ከኢማሞች ስም ጠቅሰው በዚህ መስኪድ አስተማሩ ብለዋል በዛን እለት ሼህ አብዱራህማን ነበሩ እንዴ ከሕዝቡጋር ነበሩ ሼህ አብዱራህማን ያውቃሉ ይዜንን?
- የሉም እሳቸው
- ይዜን አይነት ትምህርት አስተምሩ ብለው ሼህ አብዱራህማን ለኢማሞቹ ሲነግሩ ሰምተዋል እርስዎ በጆሮዎ ?
- አልሰማሁም እሳቸው የቀጠሩት ሰው ነው የተናገረው እንጂ
- መሃመድ ቅድም ዋህብያዎች ሶፊያዎችን የማይወዷቸው ሽርክ ስለሚሰሩ ነው ብለው ነበረ ሽርክ ማለት ለፍ/ቤቱ እስቲ ምንድን ነው ያስረዱዋቸው?
- ሽርክ የተባለው ያሉበትን ምክንያት እነሱ ናቸው የሚያውቁት እኔ አላውቅም
- እሺ በሃል ይከተላሉ ብለው ነበረ በሃሉስ ምንድን ነው ሶያፊዎች የሚከተሉት ባህል ምንድን ነው?
- የኦሮሞን ባህል ሶፊያ ይወዳል

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ለምሳሌ ምን ምን ባህሎችን እርስዎ የሚያውቁትን ?
- ይሄ እሱ ያለው የኦሮሞን ባህል ነው አሁን ያለው ?
- አዎ
- እሺ ያ በአል ምንድን ነው?
- ኦሮሞ ያው በወንዝ በገዳ በወንዝ ልመና ማድረግ ለገዳ ማደር ኦሮሞ ይሄንን ነው የሚወደው
- ሌላስ አለ የሚያውቁት?
- በቃ ይኸው ነው
- እሺ እርስዎ ሼህ መሃድ ሼህ ነኝ ብለዋል በወንዝ እና ለገዳ ማደር በእስልምና ይፈቀዳል ?
- እ?
- በእስልምና በወንዝ ወይም በገዳ መተዳደር ይፈቅዳል ወይ ሸሪያ?
- አዎ ሊሆን ይችላል እርቅ ስለሚመክር ይወዳል
- ስለዚህ ይፈቀዳል ነው?
- አዎ ይፈቀዳል
- ይሄ ወሃብያ እና ሶፊያ ያሉን ሙስሊሞች ናቸው አደሉም?
- እነሱ ናቸው የለዩዋቸው እንጂ ሙስሊሞች ናቸው
- ሼህ አብዱራህማን የተለያዩ መስኪዶችን አሰርተዋል ብለው ነበረ በነዚህ መስኪዶች የሚሰግደው ማን ነው ወይም ለማን ነው መስኪዱን የሚያሰሩት?
- በመጀመሪያ ለሙስሊም ሕብረተሰብ ነው የሚሰራው ብለው ሰሩ
- ሻሸመኔ የተሰሩ የአራዳ መስኪዶችን ያውቃሉ እርስዎ?
- መስኪዱን ነው ?
- ሻሸመኔ ውስጥ ያሉትን ሃጂ አብዲራህማን አሰሩ ያሏቸውን 4 መስኪዶች ያውቃሉ በደምብ ዘጠኙንም ያውቃሉ?
- ዘጠኙንም አውቃለሁ
- የአራዳውንም ያውቃሉ ለይተው ?
- አራዳ ሰራ አላልኩም ሰው እዛ ውስጥ ነው ምክር ይሰጣሉ ያስተ[illegible]
- አራዳ መስኪድ ያለውን አላሰሩትም ?
- አላሰሩትም

163 50

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መቼ እንደተሰራ ያውቃሉ?
- አላውቅም
- እርስዎ ወሃብያ ኖት ሶፊያ ኖት የትኛውን ነው የሚከተሉት?
- እሺ መቃወሚያውን ያስመዝግቡ
- ማለት ይሄ የግል ጥያቄ ነው ፐርሰናል የሆነ ጥያቄ ነው ኦልሞስት ሃራስመንት ማለት ነው እርስዎ ወሃብያ ኖት ሶፊያ ብለው መጠየቅ ለማሸማቀቅ ነው ባያዝድ ነህ ነው ወይም ሌላ ነገር ውስጥ ለመግባት ነው ከዛ ውጪ እሳቸው እዛ አካባቢ የተረዱትን የስንስርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት ምስክርነታቸውን በዋና ጥያቄ ጠይቀዋል በዛ መሰረት ነው አሁን ሊጠየቁ የሚገባው ከዛ ውጪ ምንድን ነህ ኃይማኖትህ ምንድን ነው ተብሎ በዚህ ደረጃ ሊጠየቁ አይገባም
- እሺ መልስ
- እኛ ማሳየት የፈለግነው ምስክሩ ምን ያህል ነፃ ናቸው የሚለውን ነገር ፍ/ቤቱ መመዘን ስላለበት እሱን እሰን ማሳየት ፈልገን ነው ይሄ ደግሞ የትኛውንም ቢከተሉ ወንጀል አደለም እና መናገር ይችላሉ ከሚሰጡት ምስክርነት አንፃር ማለት ነው ከተአማኝነት ጋር በተመለከተ
- የቀረበውን መቃወሚያ እና ምላሽ መርምሮ ትእዛዝ ሰጥቷል ምስክሩ የተጠየቁት የሶፊያ ወይም የዋህብያ ከሶፊያ ወይም ከወሃብያ በየትኛው ወገን ነው ያሉት የሚል ጥያቄ ነው የቀረበው እና በዚህ ጉዳይ ላይ መልስ መስጠታቸው ምስክሩ በሚሰጡት ቃል ጋር ፍ/ቤቱ የሚመለከተው እንጂ የሚያመጣው ለውጥ አለ ብሎ ስላልገመተ ፍ/ቤቱ ጥያቄው ይቀጥል ብሏል
- ሼህ አህመድ ሶፊያ ኖት ወይስ ወሃብያ ኖት እርስዎ?
- እኔ ሶፊያ ነኝ እሱን መርጫለሁ
- ቅድም ከአራዳ መስኪድ ውጭ ያሉት ሻሸመኔ ውስጥ ስንት መስኪድ አለ?
- እሳቸው ያሰሩት ነው ወይስ?
- ሁሉም መስኪድ ?
- አጠቃላይ ቆጥሬ አላውቅም
- እሳቸው ያሰሩት ስንት ነው?
- በሻሸመኔ 9

163 S1

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በነዚህ 9 መስኪዶች ውስጥ የሕዝብ ወይም የአካባቢ ነዋሪ ተሳትፎ እንዴት ነበር እስቲ በየአካባቢው?
- ጥያቄው ምንድን ነው የተከበረው ፍ/ቤት
- ቆይ ቆይ አደለም ጥያቄው ግልጽ ነው እስፔስፊክ አርጉት አሁን ተሳትፎው ምን ነበር በምን ሁኔታ ነው የሚለውን ግልጽ አርጉት እና እሱን ይመልሱ ምክንያቱም ተሳትፎ ሲባል በጣም ሰፊ ነው
- በገንዘብም ማቴሪያል በማቅረብ በድንጋይ በእንጨት በቆርቆሮ እንዴት ነበር ሕዝብ ነበር ሙሉ በሙሉ የሚያቀርበው?
- እሳቸው ሰሩ ተብሎ የምርቃቱ ቀን አየሁት እንጂ የሕዝቡን ተሳትፎ አልተከታተልኩም
- ሕዝቡ ገንዘብ ያዋጣ እቃ ይግዛ አይግዛ አያውቁም?
- አልተከታተልኩም ካሉ ያን ነገር አያውቁም ማለት ነው ስለዚህ ይሄ መልስ ነው ግልጽ ነው ያን ነገር አላውቅም ማለት እኮ ነው ያን ነገር የማውቀው ነገር የለም ማለት ነው በዚህ አገላለጽ ሌላ የተለየ አገላለጽ ካለው
- እሺ ቅድም አራዳ መስኪድ ዱአ ሲደረግ ሰምቻለሁ ብለው ነበረ እና ዱአ የሚደረገው ለማን ነው ?
- ዱአ የሚደረገው ወይም ዱአ የሚጠየቀው ለማን ነው ነው ለአላህ ነው ወይስ ለሌላ ሰው ነው የሚጠየቀው ዱአ?
- አስተርጓሚ አንተ ነገርካቸው አደል የሚመልሱትን አንተ መናገር ነው እሳቸው የሚሰጡትን መልስ
- እኔ አምጣልን ሲባል ሰማሁ እንጂ ለምን እንደሆነ ለይተው አልነገሩንም
- እኮ ለማን አሉ ዱአ አምጣልን የተባለው ለማን ነው ለአላህ ነው ለሰወቹ ነው ነው ጥያቄው?
- ጥያቄው ግልጽ አደለም
- የተከበረው ፍ/ቤት ዱአ የሚደረገው አሁን እሳቸው የተናገሩት
- አሁን አዳንዳንድ ጊዜ ተጨባጭ ነገሩን ብናየው መንግስት የሚያስፈልገው ለማን ነው የሚለው እሱ ግልጽ ነው
- እሱን አደለም ያልኩት
- መንግስት ለማን ነው የሚያስፈልገው ብለው ያደረጉት ለአላህ ነው ወይስ ለማን ነው ነው ጥያቄው የገባኝ ምናልባት ካልሆነ ያስረዱ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተከበረው ፍ/ቤት ዱአ ተጠየቀ ተብሎ ነበረ ዱአ የሚጠየቀው ወይም ፀሎት የሚጠየቀው አንድ ነገር አድርግልኝ ተብሎ እሳቸው ቅድም በገለፁት አገላለጽ ለማን ነው ነው ወደማን ነው እንዲያደርግ የሚጠየቀው ወደማን ነው ነው ጥያቄው
- እኮ እሱ ነዋ ወደማነው እና የቅድሙ ጥያቄ ይለያያል በዚህ መንግድ ከሆነ አስተካክላችሁ ጠይቁ
- ስለዚህ ዱአ እየተጠየቀ ያለው ማን ነው አላህ ነው ወይስ ሌላን ሰው ነው የጠየቅኩት ነው በአጭሩ?
- አላህን ነው የለመኑት የሙስሊም መንግስት አምጣልን ብለው
- ቅድም ሲጠየቁ ሼህ አህመድ ኢማሞች ከሌላ አካባቢ ይመጣሉ ብለው ነበረ እና ከየት ነው የሚመጡት ኢማሞች?
- ከተዋወቅን በኋላ አንዱ ከጅማ ነው የመጣሁት አለኝ
- ሌላውስ?
- ሌሎቹን ተዋወቅን እንጂ አገራቸውን አልጠየቅኩም
- ሼህ መሃመድ ቅድም ሲመሰክሩ የሙስሊም መንግስት አምጣልን ብለው ዱአ ያደርጉ ነበር ብለዋል ዱአ ብቻ ነበረ አደለም የሚያደርጉት?
- ጥያቄው ቀርቧል ያንን እያረጉ ነበረ ብለዋል ሌሎች ያረጋሉ ያሏቸውን ምስክሩ መስክረዋል ከዛ ተነስታችሁ ሌላ ጥያቄ ጠይቁ
- በአራዳ መስኪድ ዱአ ሲያደርጉ ነበር ያሏቸው ሰው ዱአ ሲያደርጉ ሕዝቡ አሜን ነበረ የሚለው?
- አዎ አሜን ይሉ ነበር
- ከዚህ ውጪ ሌላ ነገር አልነበረም አደል ?
- የለም
- አንድ ሰው መስኪድ ውስጥ የፈለገውን ዱአ ቢያደርግ የሚከለክለው ሰው አለ እንዴ?
- የፈለገውን ሕዝቡን የሚያጋጭ ማድረግ የለበትም
- በጎይማኖቱ እንዲ አይነት ዱአ አታድርጉ ተብሎ የተቀመጠ ነገር አለ እንዴ?
- ሕዝቡን የሚያጋጭ የሚያጣላ አትፈጽሙ የሚል አለ
- ሕዝብ ስለመጋጨቱ ከእርስዎ ግምት ውጪ የተፈጠረ ነገር የለም አደል?
- እስቲ ቆይ አጠያየቁ ይስተካከል አሁን ምስክሩ ግምት አላሉም ገና እየሄዱ ነው ስለዚህ ከእርስዎ ግምት ውጭ ያምትሉዋ ነገር ተደርባ የመጣች ናት ስለዚህ እሱን አስተካክሉ

1633

http://ethcriminalawnetwork.com/

ግምት ብለው አልተነሱም ሲነሱ አሁን እዚጋ ሲመሰክሩ ግምት አላሉም ስለዚህ እርስዎ ጨመሩት ስለዚህ ጥያቄውን ብቻ ይጠይቁ ከዛ በኋላ ከመልሱ ተነስተው ግምቱን አደለም

- አካባቢው ላይ የተጋጨ ሰው አለ እንዴ በዚህ ዱአ ምክንያት የተፈጠረ ነገር አለ በዱአው ምክንያት ማለት ነው ?
- ጥል ነው መቀያየም ነው የሚታየው
- በዱአው ምክንያት የተፈጠረ ነገር አለ ወይ ነው ጥያቄው ?
- አልተጋጨም ግን ወደ መለያየት እየሄዱ ነበር
- ያው ነበር የሚለው ግምቶት ነው ወይ ?
- መቃወሚያ
- ማለት አሁን ምስክሩ መስክሯል በዚህ ሁኔታ ምን ተፈጠረ ተባለ ፊዚካል የሆነ ግጭት የለም ነገር ግን መለያየት አለ እንደ ድሮው አንድ ያለመሆን ነገር አለ ከዚህ ውጪ ግምት ሊባል አይችልም አለ ተብሎ ተረጋግጦ ተነግሯችኋል ስለዚህ ጠበቃው አሁን ወደ ግምት ግምታዊ ነው ወይ እያሉ የራሳቸውን የሚፈልጉትን ነገር እንዲመሰክሩ ነው እያረጉዋቸው ያሉት
- እሺ መልስ ስጡበት
- አመሰግናለሁ የተከበረው ፍ/ቤት ወደ መለያየት ነበር አሉ እንጂ በዚህ ዱአ ምንያት የተለያየ ሰው አለ ወይም የተጋጨ ሰው አለ ብለው አልመከሩም ስለዚህ ነበር ሊሆን ሊሆን ይችላል የሚለው ሁላችንም እንደምናየው ግምት ነው እና ይሄ የእርስዎ ግምት ነው ወይ ብሎ መጠየቁ ደግሞ ምን ችግር አለው
- ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን እና ምላሹን ሰጥቶ ትእዛዝ ሰጥቷል የቀረበው መቃወሚያ ፍ/ቤቱ እንደተመለከተው የተከሳሾች ጠበቃ ያቀረቡት ጥያቄ ግምቶ ነው ወይስ በፍሬ ነገር ደረጃ ነው ወይ በሚል ጥያቄ ቀርቦ ምላሹ ይሰጥበት ብለናል
- ሺህ መሃመድ በእርስዎ ግምት ነው አደለ ይሄ ነገር ወይስ የተፈጠረ ነገር የለም ወይስ የተፈጠረ ነገር አልነበረም በቦታው ግምቶት ነው ይሄ ነገር ?
- ተቀያይመው መኮራረፍነው እኔ ያየሁት
- በአካባቢው ላይ ሶፊያ ለብቻው ነው እንዴ የሚሰግደው ተነጥሎ ሶፊያ ነኝ ብሎ ተነጥሎ በአንድ መስኪድ ለብቻው የሚሰግድ ማህበረሰብ አለ ወይ ?
- ይሄ ጥያቄው ቀርቦ ቅድም መልስ የተሰጠበት ነው ሌላ ጥያቄ

1634 54

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በመስቀለኛ ጥያቄ ላይ ተጠይቀው ሲመልሱ እኔንም ግባ ብለውኝ ነበር ብለዋል ሁሉንም ነበር ግባ የሚሉት የነበረው?
- ልድገምላቸው እኔንም ግባ ብለውኝ ነበረ ብለዋል እና ሁሉንም ሰው ነበረ ወይ ግባ የሚሉት ?
- አንድ ሰው ነው እኔን ያለኝ
- /የማይሰማ/
- እኔ ብቻ ነኝ የተጠየቅኩት ሌሎቹን አላውቅም
- መስኪዶቹ ሲመረቁ ከአካባቢው መጅሊስ ንግግር ያደረገ ሰው ነበር እንዴ?
- የዛን ቀን አልተደረገም
- አረቦቹ ነበሩ የተከበረው ፍ/ቤት ጥያቄው ተስተካክሎ አልተነገራቸውም
- ጥያቄው ተነስቶ መልስ ተሰጥቶበታል
- አይ ጥያቄውን አቶ ሶሪ ሲተረጉሙ በትክክል አልተረጉሙም የትርጉም ስተት አለ የሚል ነገር ነው ከባልደረቦቼ የተነገረኝ
- ተመልሷልም እዚህም የሚከታተል አለ
- እኮ ያው ጥያቄዬ ከአካባቢው መጅሊስ የእስልምና ተወካይ ወይም ወኪል ተገኝቶ ንግግር ያደረገ አለ ወይ የሚል ነው ይሄንኑ ኮንፊርም ያስደርግልኝ የተከበረው ፍ/ቤት
- ሶፊያ አንወድም ይላሉ ከማለት ውጪ የተፈጠረ ነገር የለም አደለም?
- የለም
- የአራዳ መስኪድ ሼህ አብዱራህማን ያሰሩት አደለም ብለዋል ስለዚህ የመስኪዱን ኢማም እሳቸው አልቀጠሩትም አደል?
- እንደ ወረዳው እዛ አብረው ነው የሚሰሩት ቀጥረው ሳይሆን እንደ ወረዳው አብረው ይሰራሉ
- ስለዚህ ሼህ አብዲራህማን አልቀጠሩትም አደል?
- ተመልሷል እኮ
- መልሻለሁ በቃ
- ስለዚህ የአራዳ መስኪድ ኢማም በሼህ አብዱራህማን ስር ወይም ትእዛዝ የሚተዳደር ሰው አደለም አደል?
- በእሳቸው አደለም የሚተዳደረው
- አመሰግናለሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቅድም ሼህ መሃመድ በሶፊያዎች ላይ ጅሃድ ታውጀዋለህ ጀሀድ ማለት ደግሞ ጥል ነው የሚል ነገር ተናግረዋል ትክክል ነኝ ?
- በሶፊያዎች ላይ?
- እነዚህ በሶፊያዎች ላይ ጀሃድ ታውጇል ?
- ብለዋል
- ጀሃድ ማለት ጥል ማለት ነው ብለዋል አደለም?
- አዎ ልክ ነው
- ይሄ ትርጉም ጅሃድ የምንድን ነው የአማርኛ ነው የአረብኛ ቃል ነው የምን ቃል ነው?
- አረብኛ ነው
- የቃሉ ትርጉም ይሄ ብቻ ነው?
- አዎ
- ሌላ ትርጓሜ የለውም?
- እሺ ጨርሰናል የተከበረውፍ/ቤት
- መስቀለኛ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የከሳሽ አቃቤ ሕግ ዳግመኛ ጥያቄ ይቅረብ
- እሺ ሼህ መሃመድ በመስቀለኛ ቅድም ሲጠየቁ መስኪዶቹ የተሰሩት መጀመሪያ ለሙስሊሙ ተብሎ ነበር ከዛ ብለው ሲሉ ነው በቃኝ ያሉት ጠበቃው እና መጀመሪያ ለዚህ ነበረ የተሰራው ከዛ ብለው ለማለት የፈለጉት ምንድን ነው?
- መጀመሪያ እንደዛ ብለው ሰሩ እንጂ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ይሄንን መልእክት የሚያስተላልፍ ኢማም ተቀጥሮ ይህ ግጭት ተፈጠረ
- ግጭት የሚሉት ምንድን ነው?
- ከተሰራ በኋላ ነው ልዩነት የመጣው
- ምን ልዩነት ከየት የመጣ ልዩነት ?
- ያው ቅድም እንደተናገርኩት ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ሶፊያ ዋብያ ብሎ ለይቶ ነውሲያስተምር የነበረው ተቀጣሪው
- ቅድም ተደጋግሞ የተጠየቁት ጥያቄ አሁን ይሄ ዳኛ ተደረገ ብለው ያሉት እና ሶፊያዎች ይሄን ይሄን ይሄን ስለሚያደርጉ ቅድም የገለጿቸው ስለው የጠቀሱት ለምንድን ነው ምክንያቱ ምንድን ነው ስለዚህ ምን ይሻላል ነው ሼይሞች በባህል ያምሉ ብለው የገለፁት አለ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ
- እኮ የዚህ ንግግር መነሻው ምንድን ነው ለምን አላማስ ነው የተደረገው ንግግሩ?
- የሶፊያ እምነት ለስላሳ ነው በሚል እነሱ ዋብያ ደግሞ አከረሩት
- ስለዚህ ምን እናድርግ ነው ሶፊያዎችን ምን አድርጉ ነው?
- ተቃውሞ አለ
- ምንድንነው መቃወሚያው
- እርስዎ ያው ቅድም አላስመዘገቡም አሁን ቀርቤያለሁ ብለው ይቀጥሉ
- እሺ ሞላልኝ መለሰ የተከሳሽ ጠበቃ ቀርቤያለሁ አሁን ምን እናድርግ ነው የሚሉት የሚለው ነገር አዲስ ፋክትም ነው እንዲመሰክር የሚያደርገው የድጋሚ ጥያቄ አላማ ማብራራት ነው አሁን የማብራራት ጥያቄ ሳይሆን የአዲስ ፋክት እንዲመሰክር የሚያደርግ ጥያቄ ነው የጠየቁት እና ጥያቄው ሊጠየቅ አይገባም ወይ በሚያብራራ ሁኔታ አስተካክለው ይጠይቁ
- አቃቤ ሕግ መልስ ስጡበት
- እሺ የተከበረው ፍ/ቤት ይሄን ጥያቄ በተመለከተ እስከ ጥግ ድረስ ሄደው ነው የተናገሩት ሶፊያዎች በሃል ተባለ ባህል ምንድን ነው ተብሎ እስከ መጨረሻ ድረስ አብራሩት ስለዚህ ይሄ ይቅር ነው ወይ የተባለው ብለው ነው በመስቀለኛ ጥያቄ ለማስደምደም ጥረት ያደረጉት ስለዚህ ከዛ መነሻ ነው ይሄ መደምደሚያው ይሄ ብቻ ነው ወይ ሶፊያ ባህል ይከተላል የሚለው ዝም ብሎ ጥሬ የሆነ ንግግር ብቻ ነው ወይስ ሌላ አላማ አለው ከምን መነሻየተደረገ ቅስቀሳ ነው የሚል ነው
- እሺ ፍ/ቤቱ ብይን ሰጥቷል የቀረበው ጥያቄ በሁለት የተከፈለ ነገር አለ ዋብያ እና ሶፊያ ተብሎ ስለዚህ ይሄን ይሄኛው ይሄን ይከተላል ይሄ ይሄኛውን እየከተለም የሚል ክፍፍል አለ ብለው ምስክሩ መስክረዋል ከዚህ በኋላ ምን ይሁን የሚል ነው የአቃቤ ሕግ ጥያቄ የቀረበው መቃወሚያ ይሄ አዲስ ፍሬ ነገር ነው አዲስ ፍሬ ነገር መቅረብ የለብትም ብሎ መቃወሚያ አቅርቧል ፍ/ቤቱ አዲስ ፍሬ ነገር ነው አደለም የሚለውን ነው ያየው በእርግጥ በመስቀለኛ ጥያቄ ከተነሳው መስቀለኛ ጥያቄ ዋና ጥያቄ እና ድጋሚ ጥያቄ ተያይዘው የሚሄዱ ነገር ስለለሆኑ አዲስ ፍሬ ነገር መጠየቅ አይቻልም ይታወቃል ነገር ግን ይሄ ነገር አዲስ ፍሬ ነገር ነው ወይስ አደለም የሚለውን ፍ/ቤቱ አይቶታል ቅድም ያው በአፍ በሚሰጠው ትምህርት ውስጥ በሚለም ክፍፍል ተፈጽሟል ሌላው ይሄን ይፈጽማል ሌላው ይሄን አይፈጽምም የሚል ነገር ነው እና ከዚ በኋላ ምን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ሆነ የሚለውን ነገር በቀጥታም በተዘዋዋሪም ከተነሳው ነገር ጋር የሚገናኝ በመሆኑ አዲስ ፍሬ ነገር ሆኖ ፍ/ቤቱ አላገኘውም ስለዚህ ጥያቄው ይቀጥል ብለናል

- እሺ ሼህ መሃመድ ሶፊያዎች በሃልን ይከተላሉ ብለው ማለት የንግግራቸው አካል ያደረጉበት አላማ ወይም ምክንያት ምንድን ነው ሶፊያዎቹ ምን ይሁኑ ነው የሶፊያ አስተምሮ መከተሎት ምን ይሁኑ ነው ምን ይደረጉ ነው ነው?
- ምን ይሆናሉ?
- ማለት ምን ይሁኑ እንዲህ እንዲህ ስለሚከተሉ ምን እናድርግ ነው ዋህብያዎች እርስዎ ባሉት ማለት ነው ?
- ቆይ ልድገምላቸው አልገባቸውም አሁን ቅድም ሲገልፁ ሼህ ሶፊያ ባህልን ይከተላሉ ብለው ይሰብካሉ ብለዋል ስለዚህ እርስዎ በገለፁት ዋህብያዎች ሶፊያዎት ባህልን ይከተላሉ ብለው የሚሰብኩት ለምን አላማ ነው አላማው ምንድን ነው?
- ሶፊያ ከምድር ላይ እንዲጠፋ ፈልገው ነው
- መቀያየም እና መኮራረፍ አለ ከዛ ውጪ እማውቀው ግጭት የለም በምን ምክንያት ተፈጠረ ይሄ መቀያየም እና መኮራረፍ?
- አሁን ዋብያ ከሚመክረው ምክር ላይ
- ከመቼ ጀምሮ ነው በጊዜ ያስታውሳሉ?
- አላስታውስም
- በአመተምረት ከመቼ ጀምሮ እንዲህ አይነት ነገር የመጣው?
- በ1999 ዓ.ም. ጀምሮ ነው እኔ የማውቀው
- ድጋሚ ጥያቄ ጨርሰናል
- ድጋሚ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ መልስ ሰጥተዋል የፍ/ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ ቀርቦ ምስክሩ የሰጡት መልስ
- አሁን ሲመሰክሩ ይሄን የሚፈጽሙት ሶፊያዎች ከምድር ላይ እንዲጠፉ ፈልገው ነው የሚል ነገር መስክረዋል አሁን መጨረሻ ላይ እና ይሄን ነገር ከየት አገኙ የእርስዎ ግምት ነው ወይስ ያወቁበት ነገር አለ?
- ከሞቱም አትቅበሯቸው ከሞቱም አትስገዱባቸው ሲባል ከዛ ላይ ነው እኔ የተረዳሁት
- እሺ መስክረው ጨርሰዋል ተሰናብተዋል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ የዛሬው ችሎት ያው በዚሁ እናጠናቅቃለን አሁን አስር ሰዓት ነው አምስት ደቂቃ ነው ምናምን ነው የቀረው ስለዚህ ነገ በተለመደው ሰዓት አቃቤ ሕግ አታርፍዱ እንደምንም ብላችሁ ጠዋት ኑ
- እሺ ከተሰማው ምስክሮችረር ተመሳሳይ ምስክርነት ያላቸው ምስክሮች አሉ 2 ምስክሮች ስለዚህ ክሩቅ ቦታ የመጡ ስለሆነ የሚመሰክሩትም ጭብጥ ተመሳሳይ ነው ስለዚህ እነዚህን ምስክሮች ከአሁን በኋላ የማናሰማቸው ስለሆነ
- እሺ ስንተኛ ስንተኛው እንደሆኑ?
- 119ኛ እና 120 ምስክር ላይ የተገለፁት ተመሳሳይ ጭብጥ ስለሆነ ቢታለፉ ተቃውሞ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት በችሎት ቀርበው እንዲያሰናብታቸው
- እሺ ይቅረቡ
- እርስዎ የመጀመሪያ ስሞ ማን ነው የሚለባለው እሺ የእርስዎስ?
- 119ኛ ምስክርኢሴበከር
- የሚቀጥሉት?
- 120ኛ ምስክር ሃሰን
- እንግዲህ እናንተ ያው እዚህ እንድትመሰክሩ ነበር የተጠራችሁት ሆኖም ግን አቃቤ ሕግ ከዚህ በፊት ከዚህ በፊት ከመበከሩት ምስክር የተለየ ሊያስረዱ ስለማይችሉ አንፈልጋቸውም ያሉ ስለሆነ የፍ/ቤቱን ትእዛዝ አክብራችሁ በመምጣታችሁ እናመሰግናለን አሁን መመለስ ትችላላችሁ እሺ ነገር በተለመደው ሰዓት እንገናኛለን ጨርሰዋል እናንተ ተመለሱ እናመሰግናለን ወደቤታችሁ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

4ኛ ወ/ችሎት

የመዝገብ ቁጥር 124754

ጥር 23 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች :- ብስራት ተህልቁ

ባህር ዳርቻ

ቀናቴ ሆራ

ከሳሽ :- አቃቤ ሕግ ብርሃኑ ወንድምአገኝ ፣ቴዎድሮስ ጌታቸው ፣ቴዎድሮስ ባህሩ ቀርበናል

ተከሳሾች:- እነአቡበክር አህመድ የቀረ ሰው አለ ከእሳቸው ውጪ ሌላ መጥቷል 29ኛ ናቸው እሺ የተከሳሾቹ ጠበቆች አህመድ ጀማል የ28ኛ ተከሳሽ ጠበቃ፣ስለሌሎቹ አሃሰን ሁሴን ፣መሃመድ አብደላ ፣ ሞላልኝ መለሰ፣ባህሩ መካንጋ ፣ ሃሊማ ሰኢድ ፣አዲስ መሃመድ

- አቃቤ ሕግ ያው አንድ ተከሳሽ አልቀረቡት የተለየ ነገር አለ እሳቸውን በተመለከተ
- ያው እንደትላንቱ የተለመደው ነው
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም
- ምያለሁ
- እሺ እርስዎ ለምስክርነት ነው የመጡት ሙሉ ስሞ ያው ለምስክሮች ደህንነት ሲባል እንዳይገለጽ ብይን ተሰጥቷል ስለዚህ ያው የእርስዎን የመጀመሪያ ስም ብቻ የአባቶን ስም ሳይጨምሩ ይነግሩናል ከዛ በኋላ እንቀጥላለን
- እኔ ሼህ አህመድ (16)
- እሺ አቃቤ ሕግ ስንተኛ ምስክር ናቸው?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- 32ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተመዘገቡ ምስክር ናቸው
- ሼህ አህመድ ያው ዛሬ ለምስክርነት ነው የመጡት እነማን ላይነው የሚመሰክሩት?
- በያሲን ኑሩ ላይ እንደዚሁም በአቡበክር አለሙ ላይ እና በሼህ መክቱ ሙሂ ላይ
- ሦስት ሰው ላይ ነው የሚመሰክሩት?
- አዎ
- እሺ እነኚህ ሦስቱ ሰወች በአካል ነው በስም ነው የሚያውቋቸው?
- በስምም በአካልም አውቃቸዋለሁ
- ስለዚህ መለየት ይችላሉ አሁን?
- አዎ እችላለሁ
- ከቻሉ ለዩልን እስቲ ተቀምጠውም ይችላሉ ተነስተውም ማሳየት ይችላሉ በምልክት ምን እንደለበሱ ለእኛ እንዲገባ ማለት ነው ?
- 6ኛ/ ተከሳሽን ጠቁመዋል ሌሎቹን እስቲ አቡበክር የት ነው ያለው 11ኛ ተከሳሽን አቡበክር አለሙን አሳይተዋል እሺ የቀረውስ ያሲን ያሳዩን 3 ሰወች ላይ ለመመስከር ነው የመጡት ?
- አዎ
- እነዚህ ሰወችጋ ፀብ ዝምድና አሎት?
- የለኝም
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ ቀጥሉ
- እሺ ሼህ አህመድ አሁን በጠቀሷቸው ሰወች ላይ የመጣሁት ለምስክርነት ነው ብለዋል ምንድን ነው የሚመሰክሩት?
- እንግዲህ በቡድን የተሰራ ስራ እና በግል የተሰራ ስራ ለማብራራት እፈልጋለሁ
- እሺ እየለዩ መጀመሪያ በግለሰብ ?
- እሺ በመጀመሪያ ያሲን ኑሩ የተባሉት በቪዲዮ ካሴት ላይ ቪዲዮ ካሴት በማዘጋጀት አህባሽ የሚባል አዲስ ኃይማኖት መጥቷል በማለት ሙስሊሙን ማህበረሰብ የሚያደናግር እና የሚያሳስት ከዲናል ኢስላማዊ ወይም ከኃይማኖታችን ውጭ የሌለ ነገር አህባሽ አስተምረውት አንደኛ ሴት ልጅ ሱሪ ለብሳ መሄድ ትችላለች ይላል ሁለተኛ ወለድ መብላት ይበቃል ይላል ሦስተኛ ቁርአን የአላህ ፈቃድ ሳይሆን የጅብሪል ቃል ነው ይላል ስለዚህ እነዚህ ኃይማኖት ይዤ አህባሽ የሚባል ኃይማኖት አዲስ ኃይማኖት መጥቶብናል እና ዝም ብለን ማየት የለብንም የሚል ያው እንደዚህ አይነት ማደናገሪያ ካሴት ካሴቱን ከአንድ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ጓደኛዬጋ ሆኜ አይቼው እጅግ በጣም አሳዝኖኛል እንግዲህ ይሄ አንዱ ነው አቡበከር አለሙ በኩል

- ያሲን ኑሩ ላይ ትንሽ እኔ የምጠይቆትን ጥያቄ ይመልሱልኛል በአካል ያውቁታል እንዴ ከቪዲዮ በፊት?
- ከቪዲዮ በፊት በአካል አላውቃቸውም በቪዲዮ ነው የማውቃቸው
- እሺ እነዚህን ሦስት ነገሮች አህባሽ የሚባለው እምነት እንደዚህ እንደዚህ ያደርጋል በማለት ይገልፃል ከዚህ ውጪ ምንድን ነው ዝም ብለን ማየት የለብንም ምንድን ነው እያለ ያለው ?
- አዎ ዝም ብለን ማየት የለብንም ሙስሊሙ ማህበረሰብ መንቃት አለበት ኃይማኖቱን መጠበቅ አለበት መከላከል አለበት አስፈላጊ የሆኑ እንግዲህ እንደጀሃድም መነሳት አለበት የሚሉ ቅስቀሳዎች አሉ በአጠቃላይ ሙስሊሙ ማህበረሰብ በመንግስት ላይ እንዲያምጽ ሙስሊሙ ማህበረሰብ እርስ በእርስ እንዲከፋፈል የሚያደርግ ሃሰት እንደሆነ ወይም ቅስቀሳ እንደሆነ አይቼዋለሁኝ አንዱ ይሄ ነው በራሱ ሌላው ምንድን ነው ካሴቱ ሕገወጥ ነው ምክንያቱም ምንድን ነው ካሴት ሲታተም የሚመለከተው ክፍል አለ ሳንሱር ካረገ በኋላ ይታተም
- ኃይማኖታዊ ካሴት ማለቶ ነው?
- ኃይማኖታዊ ካሴቱ አዎ ይታተም ብሎ ከተፈቀደ በኋላ መታተም ሲገባው እና መሰራጨት ሲገባው በሕገወጥ መልኩ ነው የተዘጋጀው ይሄ እራሱን የቻለ ችግር ነው ማለት ነው እና ይሄ ሙስሊሙን በመከፋፈል በሙስሊሙ ላይ አመጽ የሚያስነሳ በኃይማኖታችን ላይም የኃይማኖቱን ተከታይ ቁጣ የሚያስነሳ ሆኖ ነው ያገኘሁት ማለት ነው እና ከዚህ አኳያ ነው የምመለክረው
- እሺ መቼ ነው ይሄንን ሲዲ ያዩት?
- በግምት እንግዲህ ቀኑ ትንሽ እንትን ይለኛል ወደ ሚያዝያ ወር 2004 ይመስለኛል ቀኑን ላላስታውሰው እችላለሁኝ
- እሺ ወደ ሌላው ስሙን የጠቀሱት ተከሳሽ አለ ወደሳቸው እስቲ ?
- እሺ ወደ ሌላው ተከሳሽ ወደ አቡበከር አለሙ ናቸው ወደሳቸው ነው የማመራው
- መቼ ነው የሚያውቋቸው እሳቸውን?
- አቡበከር አለሙን አምና በ2004 ነው የማውቃቸው ከዛ ወዲያ አላውቃቸውም እና አቡበከር አለሙ ምንድን ነው ዋና ተግባራቸው አህባሽ የሚባል ኃይማኖት መጥቷል ተብሎ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በተቀሰቀሰው መሰረት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ውሸጉብር ውስጥ የገባውን መማር ያለበት ማወቅ ያለበትን ለማሳወቅ ሲፈለግ አቡበከር አለሙ ምንድን ነው የሚያደርጉት በስብሰባው ላይ ታዳጊ ወጣቶችን ልጆችን ይዘው መጥተው

- የት ስብሰባው ማለት የት የተካሄደ ስብሰባ ነው?
- ለምሳሌ በኑር መስኪድ ኑር መስኪድ በአንድ ወቅት ተሰብስበው ነበረና
- ቀን ነው ማታ ላይ ነው ስብሰባው የነበረው?
- ቀን ነው
- ኑር መስኪድ የት አካባቢ የሚገኝ ነው?
- ፒያሳ አካባቢ ነው የሚገኘው እና እዛ
- መቼ ነው ይሄ ስብሰባ የተካሄደው?
- በሚያዚያ ወር ይመስለኛል አሁን 2004 በሚያዝያ ወር ነው እዛ በተካሄደው ስብሰባ ላይ ሙስሊሙን ለማስተማር ትክክለኛ ኃይማኖትን የሚያስነካ ነገር የለም አህባሽ የሚሉትም ኃይማኖት አልመጣም እኛ አናውቀውም ዲነሊ እስላም ዲነሊ እስላም ነው መመሪያችን ሃዲስ እና ቁርአን ነው ከዚህ አኳያ አንደኛ ነገር ሴት ልጅ ሱሪ ለብሳ መሄድ አትችልም ሸሪያው ይከለክላል 2ኛ ነገር ሴት ልጅ ሶላት መስገድ አትችልም ሸሪያው ይከለክላል 4ኛ ነገር ደግሞ ወለድ መብላት ይበቃል የተባለው አይበቃል
- ማን ነው ይሄንን የሚለው?
- አኛ ለማስተማር ሲፈለግ ነው ሙስሊሙን ለማስተማር ሲፈለግ በነዚህ አጀንዳዎች ላይ ስብሰባ ተጠርቶ እያለ ያን ስብሰባውን
- እርስዎ ነበሩ ስብሰባው ላይ?
- ነበርኩ አዎ
- ማን ነበረ ይሄንን ሲናገር የነበረው?
- እንግዲህ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት አሉ እንዲሁም ደግሞ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳይ የማህበራዊ ዘርፍ አሉ ይህም እንደዚሁ ቦታው ተገኝቻለሁ ማለት ነው አብሬ እከታተል ነበረ እና እነሱ ሲያስተምሩ ይሄንን አበይት ነጥብ ወደ ሙስሊሙ ለማስተማር ሲፈልጉ የእሳቸው ተግባር ምንድን ነው ታዳጊ ልጆች ይዘው መጥተው መጀመሪያ ስብሰሳውን ካዳመጡ በኋላ ስብሰባውን ለመረበሽ በመጨረሻ መልስ ጥያቄ ከቤቱ ይጠየቃል ይሄ አይነት ሁኔታ እንዴት ነው ተብሎ መልስ ሳይሰጥ ያው አላህ አክበር ብለው ይጮሃሉ ያስጮሃሉ በዛ መልሱ ስብሰባው ይበተናል ከዛህና ሙስሊሙ ማህበረሰብ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ማወቅ ያለበትን እንዲያውቅ ስበሰባውን የመበተን ስራ ሰርተዋል ማለት ነው ይሄ አንዱ ነው በሌላ በኩል እንደዚሁ ኢማም ሞሃመድ መስኪድ ሸሮ ሜዳ አካባቢ ነው የካቲት 11 ቀን 2004 ነው እዛ እኔ ላስተምር ተመድቤ ነበር ላስተምር የተመደበኩበት ዋናው ምክንያቱ ደራሲ ነኝ እኔ ደራሲ ነበርኩ የኃይማኖቱ የተሻለ የኃይማኖት ብቃት አለኝ ማለት ሳይሆን ገጣሚ ነኝ ደራሲ ነኝ ከዚህ አኳያ ግንዛቤ አለው በማለት ያው እንዳስተምር ተጠርቶ ነበረ እና እዛም አካባቢ ላይ ተገኝተው ወጣቶችን ይዘው ተገኝተው ትምህርቱን ሃዲስ እና ከቁርአን ትምርቱን ከሰጠሁኝ በኋላ ጥያቄ ተጠየቀ ጥያቄዎቹም ወለድ የሚበላ ይበቃል ይላል የአህባሽ አስተምሮት ሴት ልጅ ሱሪ ለብሳ መሄድ ትችላለች ይላል እና እንዴት ነው የሚል ነገር የመሳሰለው ነበበር የተጠየቀው ይሄንን እመልሳለሁ ስል ሳልመልስ ወዲያው አላህዋ ክበር አሉ

- እነማን ናቸው አላህዋክበር ያሉት?
- እነሱ ናቸው መሪዎቹ አቶ አቡበክር አለሙ ናቸው እና በነሱ አማካኝነት ስብሰባው ሊበተንብን ችሏል ማለት ነው
- ስንት ይሆናሉ በግምት ?
- ብዙ ናቸው እንግዲህ አይታወቅም በግምት
- እንዴት ነበረ ስብሰባውን እረበሹ ሲባል እንዴት ነበረ አላህዋክበር ሲሉ የነበረው?
- መልስ ሲሰጥ ሲል እኛ ይሄንን አንቀበልም አላህዋክበር አላህዋክበር አላህዋክበር እያሉ ስብሰባው ተበተነ በቃ ምንም መልስ መስጠት አልተቻለም ተበተነ ይሄ ነበረ እና ያ ነው ከዚህም በተጨማሪ እንደዚሁም በማደናገሪያ ሃሳቡ እዛው አቡበክር በዛው ኢማም አህመድ መስኪድ ላይ በተለይ ም/ሳ ኢድልረሳቅ ገበየሁ የተባለ ነበረ እሱ እንኳን ፖሊስ ነው በእርግጥ ሕገመንግስቱን እሱ አክብሮ ሌላውን ሊያስከብር ቃል በገባው መሰረት ለአላማ የቆመውን ሰው አሳስተው እሱም እንደዚሁ ስብሰባውን ለመበተን ከፍተኛ ጥረት አድርጉ በእኛም ላይ ዛቻ ዝቶ እገላችኋለው አጠፋችኋለው ብሎ ይሄ ፖሊስ መሆኑን አላወቅኩትም መለዮውን በፌስታል ይዞ ነው የገባው የነበረው በኋላ ላይ ነው ፖሊስ ሆኖ የተገኘው እኔ እንኳን የዛተብኝን ነገር አናንቄው ትቼ ነበረ መቻል አለብኝ ማለፍ አለብኝ በሚል ጓደኞቼ ከሰውት ያው በወንጀል ተከሶ ከስራ እንደተሰናበተ አውቃለሁኝ እንግዲህ በወንጀለኛ ፍ/ቤት ምን እንደተወሰነበት ባላውቅም ማለት ነውና ነገሩ እስከዚህ ደረጃ ድረስ የሄደ እንደሆነ አውቃለሁኝ በአጠቃላይ ግን ሲታይ የአቶ አቡበክር አለሙ ተግባር ይሄ ነበር የሼህ መክተ ሙሄ ከነዚህጋር አስተባባሪዎች ነበሩ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከነማን ጋር ነው የሚያስተባብሩት?
- ከነያሲን ኑሩጋ እና ከአቡበክር አለሙጋ ከሌሎቹ ጓደኞቹጋ እኔም አላውቃቸውም ከነሱጋ ያስተባብሩ ነበር በአላማው ላይ ያስተባብሩ ነበረ ማለት ነው ይሄን ነው የማውቀው እና ሲያስተባብሩ ምን ነበረ ወደሚለው ብገባ ደስ ይለኛል
- እሺ ይቀጥሉ
- ሲያስተባብሩ ምን ነበረ የሚለው በአወሊያ ሙስሊሙ ማህበረሰብ በተለይ ከመጋቢት ወር 2004 ጀምሮ ስብሰባ እየጠራሁ እንደአስፈላጊነቱ በዛ በስብሰባው ሙስሊሙ ማህበረሰብ ይመጣል እዛ ላይ የሚነሳው ምን ነበር አህባሽ የሚባል እምነት መጥቶልሃል ስለዚህ መነሳት አለብህ ጀሃድ አውጀናል አንፈራም መጅሊስ አህባሽ የሚሉት አስተምሮት አምጥቶብናል የአህባሽን አስተምሮት አንቀበልም የሚሉ ናቸው
- ማን ነው ይሄንን የሚለው?
- ሁሉም ናቸው እዛ አባሪ ተባባሪ ሆነው ማለት ነው እና ለሌላው ሰው
- የት ነው ቦታው?
- አወሊያ አንዋርም አንዳንድ ጊዜ
- መቼ መቼ ነው ይሄ የሚደረገው?
- በየሳምንቱ ጁምአ አለን
- በሳምንት አርብ አርብ ቀን ?
- አርብ አርብ ቀን ይደረጋል ይሄ ነገር ከአወሊያ ወደ አንዋርም መጥተው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዋርም ይሄ ሁኔታ እንዳለ አዉቃለሁኝ እና መጅሊስ አመራር ሕዝብ ያርመረጠው መውረድ አለበት የሚሉ ይገኙበታል ይባል ነበር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የመጅሊስ አመራር መውረድ አለበት ተብሎ ከተወሰነ በኋላ እንደውም ይቅርታ መጅሊስ አመራር ሕዝብ አልመረጠውም መውረድ አለበት የሚል ሲሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጅሊስ አመራር ይሄ የነበረው ወርዶ ሌላ መመረጥ አለበት ተብሎ የኢትዮጵያ ኡለማ ምክር ቤት በወሰደው ውሳኔ መሰረት ኡለማ ምክር ቤቱ የምርጫ ፕሮግራም አውጥቶ ሲንቀሳቀስ እነዚሁ ሰወች በተለያዩ ሕዝቡን አንደኛ መጅሊስ የኡለማ ምክር ቤት ሊመራ አይችለም በራሳችን ሊመራ ይገባል በሁለተኛ ደረጃ የኡለማ ምክር ቤት ስለመጅሊስ ምርጫ ያወጣው ፕሮግራም መሰረት አለበት ምርጫ በየመስኪዱ እንጂ በወረዳ መሆን የለበትም ብለው እዛ ላይም ከፍተኛ ችግር ነበረ የነበረው ይሄን አውቃለሁ ከዚጋር ተያይዞ ይህ በቃላቸው እያሉ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ወረቀቶች ፋንፍሌቶች በማዘጋጀት እዛ ፋንፍሌቶች

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

በሕፃናት ልጆች ላይ ሕፃን ብሎ ማለት ከ18 ዓመት በታች ያለ ሕፃን ነው የምንለው እኛም እንደምናውቀው ምክንያቱም ለሕግ ቀርቦ ተከሳሽ ስለማይሆን ተጠያቂ ስለማይሆን ማለት ነው በእነዛ በልጆች ወረቀቱን ያስበትናሉ ወደ ሕዝቡ እንዲገባ ያ ወረቀቱ

- የት ነው የሚያስበትኑት እነዚህ በራሪ ወረቀቶቹን?
- በጣም ጥሩ አንዋር ይበተናል በሰፊዉ ይበተናል አወልያም ይበተን ነበረ እና በተለያዩ መስኪዶች ይበተናል በምን ሰስኪድም እንደዚሁ እየተበተነ ነበረ የነበረው
- ምን ነበረ ይዘቱ ምን ይላል አንብበውት ያውቃሉ ይሄንን በራሪ ወረቀት?
- አዎ ለኔም ተሰጥቶኝ ነበረ ያው ምን ያረግልኛል ብዬ ቀድጄ ጣልኩት እንጂ ለኔም እዛው ጀምአ ስሰግድ ይሰጠኛል ምክንያቱም ምንድን ነው የሚለው ያው ቅድም ካልኳቸው ውጪ አደሉም ድምፃችን ይሰማ መንግስት በኃይማኖታችን ጣልቃ ገብቷል የአህባሽ አስተምሮት አንቀበልም አህባሽ የሚባል አዲስ ኃይማኖት መጥቶብናል የመጅሊስ አመራር በሕዝቡ ያልተመረጠ በመሆኑ መውረድ አለበት መጅሊስ ሕዝብ አልወከለውም የሚሉ የመሳሰሉት ናቸው በአብዛኛው በዝርዝር የሞሉት ማለት ነው ከሰላት ጋር ተያይዞ ጀሃድ አውጀናል አንፈራም የሚለው ይገኝበታል ማለት ነው እና እነዛ ነገሮችን አውቃለሁ እንግዲህ ማን ነገረህ ወደሚል ሊመጣ ይችል የሆነ የነገሩኝ የሚበትኑት ሕፃናት ልጆች ናቸው ወረቀቱን ስቀበላቸው ማን ሰጣችሁ ይሄንን እናንተ ልጆች ናችሁ ስንላቸው እነአቡበክር የሚሏቸው ሌሎችም እነዛ ኮሚቴ ነን ተብለው እራሳቸውን ኮሚቴ አድርገው የሚንቀሳቀሱ ልጆች ሰወች እነሱ እንድንበትን ሰጥተውን ነው የሚል ነገር ነው ያለው ይሄ ነው
- እስቲ አሁን ልጆቹን ማን ነው የሚሰጣችሁ ብዬ ስጠይቃቸው ስለኮሚቴ አለ እነዚህ የኮሚቴ ሰወች ናቸው ብለውኛል ብለዋል ምንድን ነው ኮሚቴ ነበረ እንዴ የተቋቋመ?
- ኮሚቴ አልተቋቋመም ኮሚቴ አናውቅም እኛ ኮሚቴ መቋቋሙንም አላውቅም ልጆቹ ሲነግሩኝ ግን ኮሚቴ ብለው የተቋቋሙ ልጆች ስላሉ እነሱ ናቸው
- እስቲ ስለነዚህ ሰወች እርስዎ ያውቃሉ?
- ምንም የማውቀው ነገር የለኝም እኔ
- ኮሚቴ ስለተባለው ነገር?
- ምንም ኮሚቴ መሆናቸውን አላውቅም እኔ ኮሚቴ የሚባለው በመሰረቱ ከወረዳ ጀምሮ በሕጋዊ መልኩ ሕዝብ ተሳትፎበት የተመረጠ እንጂ የተወሰነ ቡድን ተሰባስቦ የመረጠው ኮሚቴ ሊባል አይገባውም ቡጂ መምረጣቸውንም አላውቅም እኔ እና ኮሚቴነታቸውንም አላውቅም አይገባኝም

1646

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ልክ ኖት ኮሚቴ ለማቋቋም የራሱ የሆነ ስነስርዓት አለው ሕጋዊ አካሄድ አለው ነው የሚሉን የእኛ ጥያቄ ልጆቹ የሚሉት እራሱን ኮሚቴ ነኝ ብሎ የሚንቀሳቀስ አካል ነበረ ወይ እርስዎ የሰሙት?
- አዎ እንደዛ ነው እራሱን ኮሚቴ ነኝ ብሎ የአወልያ ኮሚቴ አሁን አዲስ ኮሚቴ ተቋቁሟል እሱ ኮሚቴ ነኝ ብሎ የሚለው እሱ ነው የሰጠን ለእንድንበትን ብለው ያው ምላሽ ሰጥተውኛል ማለት ነው
- እዚህ ኮሚቴ ውስጥ ማን ማን እንዳለ ያውቃሉ እርስዎ?
- አይ እኔ በትክክል አላውቅም ምሳሌ አሁን ሼህ መከተ ትሪ እንዳሉ አውቃለሁ በስምም ስለማውቃቸው ጥሩ ምግባር ነበራቸው እና አሁን እንዴት እንደገቡ አላውቅም ሌሎችም እንደዚሁ እኔ አሁን በአይን አብዛኛው አላውቃቸውም ማለት ይቻላል እኔ አላውቃቸውም ሌላው ከዚጋር ተያይዞ የምጨምረው አለኝ ሌላው ምንድን ነው በዚሁ በተነሳሳው አመጽ መሰረት በአንዋር መስኪድ ላይ ወደሚያዝያ መጨረሻው አካባቢ ይመስለኛል
- ምን ወር ላይ?
- ሚያዝያ መጨረሻው ይመስለኛል በአንዋር መስኪድ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳይ ስራ አስፈፃሚዎች አሉ በመባል በመገመት ይመስለኛል እንደዚሁም እዛ ቢሮ ላይ የመስኪድ እና ወቃፍ አስተዳደሩ ይገኝበታል ያንን ቢሮ መስኮቱ ተሰብሮ በተለያዩ ሰወች ተሰብሮ መስኮቱ አነሱን ሰወች ለመግደል ታስቦ እንገና ፖሊስ አልነበረም እና በአካባቢው ከውጭ ተፈልጐ ከአጥር ውጭ ተፈልጐ ፖሊስ መጥቶ ያን ችግሩን ትንሽ ሶሉሽን ወይም መፍትሄ ሊሰጠው ችሏል ማለት ነው ነገር ግን ፖሊሱ ያን መፍትሄ እሰጣለሁ ብሎ ያው እጁ ተመቶ ደምቶ እንደነበረ አውቃለሁኝ ከዚጋር ተያይዞ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት ሃጂ ጣሂር በሽር የሚባሉ በቦቅስ ተመተው አፍንጫቸው ሁሉ ደምቶ እንደበረ በወቅቱ አውቃለሁኝ
- መቼ ነበሩ በቦታው እርስዎ?
- ነበርኩ
- ማን ነው የመታቸው?
- መስኮቱን ሰብረው እዚህ የአህባሽ አስተምሮት የሚሰጡ ሰወች አሉ እነዚህ ሕዝብ አልወከላቸውም የመጅሊስ አመራሮችም አሉ ተብሎ በዚህ አሳቢ ነው እንግዲህ የሶላት ወቅቱ ስድስት ሰዓት ተኩል ነው እነሱ ግን የመጡት ወደ አራት ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው መጥተው እንደዚህ አይነት ድርጊት ተፈጽሟል ይሄ ከባድ ችግር እንደሆነ ነው በኔ በኩል

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

ያየሁት እና ይሄ ወንጀል ተፈጽሟል ማለት ነው በሌላ በኩል ደግሞ በነ/ር መስኪድ አካባቢ ቅድም እንደገለጽኩት አላህዋክበር በሚባልበት ጊዜ ላይ ያው ጩኸት በከፍተኛ አስተጋባ አላህዋክበር የሚል ከዛ አኪያ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳይ ምክትል ፕሬዝደንት ነበሩ ኮታቸውን ከኋላቸው እወጣለሁ ብለው ይዘዋቸው በቦቅስ እንደመቷቸው ነው ከዛ ያው ስብሰባው ተበትኗል ማለት ነው

- ምክትል ፕሬዝደንት ናቸው?
- ምክትል ፕሬዝደንት ናቸው ሃጂ ሰይድ በሸር ይባላሉ ሰይድ ግዘው ዋናው ፕሬዝደንቱ ነው ሰይድ በሸር የሚባለው ደግሞ ምክትል ፕሬዝዳንት ነው እና እሳቸው ያው በቦቅስ ተመተው ያው እንግዲህ እንዳለ አውቃለሁኝ በአጠቃላይ እነዚህ ድርጅቶች እንግዲህ ከኃይማኖታችን አኪያ ሲታይ ኃይማኖታችን የማይፈቅደው ከኃይማኖታችን ውጪ የሆነ ተግባር እንደሆነ ነው የማውቀው
- እሺ ወደሱ ይመጡልናል ሌሎችስ እንደዚህ ተመሳሳይ የሁከት ድርጊቶች ወይም ሌሎች አሁን ቅድም የጠቀሷቸው አይነት እንቅስቃሴዎች የተደረጉበት ጊዜ አለ በአንዋርም በአወሊየም?
- እንግዲህ አሁን በተጨባጭ ያየሁት እነዚህን ነው
- የሰሙትስ አለ?
- አይ የሰማሁትም እንግዲህ በእነዚህ ላይ ነው ምስክርነት መስጠት የምፈልገው ተጨባጭ የሆኑ ነገሮች ስለሆኑ በነዚህ ላይ
- አሁን በዋና ጥያቄ ሲገልፁ የቢሮ በር ተሰብሮ ሰዎችን ለመግደል ተሞክሯል ብለዋል ማንን ለመግደል ነው የተሞከረው?
- ጥሩ ያው ቅድም ግልጽ አድርጌያለሁኝ ለመግደል የተሞከረው የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች አንደኛ አመራሮች ማለት ነው 1ኛ ሕዝብ አልመረጣቸውም
- አይ የተሰበረው ቢሮ የማን ቢሮ ነው ?
- የአባስ ቢሮ ነው የአባስ ከማል ቢሮ የመስኪድ እና /ግልጽ ያልሆነ/ አስተዳደር ቢሮ ነው የተሰበረው
- ማን ናቸው ሃባስ ?
- ሃሳብ ከማል የመስኪድ እና /ግልጽ ያልሆነ/ ዘርፍ አስተዳደር ኃላፊ ናቸው
- እሳቸውን ለመግደል ቢሮ ተሰብሮ ነበር?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቢሮ ተሰብሮ መስኮቱ ተሰብሯል ቢሮው ሊሰበር ሲል የፖሊስ ጥበቃ ክልፍ እዛ አካባቢ ስላልነበረ እንደገና ከመስኪዱ ውጪ ተፈልጐ መጥቶ ያው ሂወት ሊያድን ችሏል እሱም ደግሞ ተመቶ ቆስሏል ማለት ነው ደምቶ አይቼዋለሁ እሱን ፖሊሱን እራሱ
- ጥሩ እስካሁን የገሩንን ይህ የተሰበሩ ቢሮዎች በሰወች ላይ የደረሱ ረዳቶች ማን እንደሚፈጽም ያውቃሉ ?
- እንግዲህ እማውቀው በዚሁ ሁኔታ አዲስ አህባሽ የሚባል ኃይማኖት መጥቷል ተብሎ ሕዝበ ሙስሊሙ ባልሆነ ነገር ተሰብኮ በያዘው አቅጣጫ መሰረት በነሱ በተቀጣጠለው እሳት መሰረት ነው እንጂ
- እነማን ናቸው እነሱ?
- እነዚህ እንግዲህ እነዚህ እህት ወንድሞቻችን ናቸው በተለይ ያው መስኪድ
- እነማን ናቸው እነዚህ ስለማይቀረጽ?
- እነያሲን ኑሩ እነአቡበክር አለሙ የመሳሰሉት ጓደኞቻቸው ናቸው
- ምንድን ናቸው እነዚህ የተሰባሰቡ ሰወች ?
- ያው እንግዲህ
- ምንድን ነን ነው የሚሉት?
- እነሱ እንግዲህ ኃይማኖታችንን አህባሽ የሚባል ኃይማኖት መጥቶ ኃይማኖታችን
- ምንድን ነን ነው የሚሉት እነዚህ እነ ያሲን ኑሩ እነአቡበክር አለሙ ቅድም የጠቀሷቸው ሰወች ምንድን ነን ነው የሚሉት?
- እንግዲህ እነሱ እራሳቸውን ኮሚቴ አርገናል ነው የሚሉት
- ጥሩ ስለዚህ እነሱ ያሏቸው ኮሚቴዎች ናቸው ማለት ነው?
- አዎ
- ስለዚህ እነሱ ባደረጉት ቅስቀሳ ነው እነዚህ ሁሉ ጉዳቶች የደረሱት
- አዎ
- ጥሩ ቅድም ስለ ያሲን ኑሩ ነግረውናል ስለ አቡበክር አለሙ ነግረውናል ሼህ መክተ ሙሄ ምን አረጉ?
- ሼህ መክተ ሙሄ እንግዲህ እስከ አሁን ተጨባጭ ያየሁት ሲያስተባብሩ ነው እንጂ ከአፋቸው የሆነ ነገር ሲወጣ ሰምቼ አላውቅም ግን ያስተባብራሉ ሰውየው ፈጽሞ ቀስቃሳሉ
- ምንኑን ነው የሚያስተባብሩት?
- ስልቱን ስራውን አካሄዱን ይሄ መሆን አለበት ይሄ እንዲህ መሆን አለበት የሚል ግን

1649 69

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንዴት እያረጉ እስቲ አሁን ይሄ መሆን አለበት ይሄ መሆን አለበት የሚሉትን ይግለፁት ?
- እንግዲህ ያው እነሱ እንደሚሉት አዲስ አህባሽ የመጣ አህባሽ የሚባል አዲስ ኃይማኖት መጥቶብናል ይሄንን ደግሞ ለማስቀረት ሕዝቡን መቀስቀስ አለብን ጅሃድ መታወጅ አለበት ወደሚለው ዳይሬክሽን ወደዛ አካባቢ ናቸው እንግዲህ ተጨባጭ ያው በነዚህኞቹ ላይ ያው በግልጽ ስለሰማሁ ነው እሳቸው ግን በማስተባበል ደረጃ ይሄንን ይሰራሉ የሚል
- ጥያቄ አበቃን
- ኢሺ ዋና ጥያቄ አብቅቷል መስቀለኛ
- እሺ ሼህ መሃመድ ቅድም የመጅሊስ ቢሮ አኗር ውስጥ ቢሮ ተሰብሮ የግድያ ሙከራ ተደርጐ ነበር ብለዋል ትክክል ነኝ ?
- አዎ
- እርስዎ እዛ ስብሰባ ውስጥ ነበሩ እንዴ እርስዎ?
- እኔ ምእመናን ነኝ መስኪድ ለዱአ ስራ መጥቼ ነበር
- ማለት ቢሮ ውስጥ ነበሩ?
- ቢሮ ውስጥ አደለሁም ከቢሮ ውጭ ነኝ ያለሁት ለጁምአ ሶላት መስገድ ስላለብኝ ለጁምአ ሶላት እዛው እውጭ ሆኜ እከታተል ነበር እና እዛ ነበርኩኝ መስኮቱ የተሰበረው
- ጥሩ ይሄ ሁኔታ መከሰቱን እንጂ ማን እንደፈፀመው አያውቁም አደል?
- ማን እንደፈፀመው በነዚሁ በወንድሞቻችን
- ያውቃሉ አያውቁም ለጠየቅኖት ብቻ ማን እንደፈፀመው ያውቃሉ?
- ወደዛ ልመጣ ነው
- ይሄ የሰበረው ሰው እከሌ እከሌ ሊሉ ይችላሉ?
- እከሌ እከሌ አልልም እከሌ እከሌ ማለት ሳይሆን ዝም ብሎ ያው የነዚህ ሰወች ስብስብ መሆናቸውን እናውቃለን ከዛ ደግሞ እነሱ ይሄን ችግር ሲፈጥሩያው የሚሉትን እያሉ አህባሽ የሚባል አዲስ ኃይማኖት መጅሊሱ አምጥቶብናል እያሉ ይሄን እያሰሙ ስለነበረ ከዚህ አኳያ የነሱ ናቸው የሚል ነው እንትን ያለኝ
- አሃ ከዚህ አኳያ የነሱ ይሆናል ብለው የሚል ግምት ነው ያሎት?
- አዎ ተጨባጩ
- ስለ አህባሽ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም እርስዎዋ?
- ምንም የማውቀው ነገር የለኝም

1650 70

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አህባሽ አሁን በመጅሊሱ የተነገረበት ሁኔታ እርስዎ በሚያውቁት ይሄ እንቅስቃሴ ሲጀመር አህባሽን በሚመለከት ምንም የተደረገ ነገር የለም ከተከሳሾች ውጭ አህባሽ ኢትዮጵያ ውስጥ አለ የለም በሚለው ዙሪያ ?
- ይሄ የእስልምና ኃይማኖት እስላም መኖሩን ነው እንጂ የማውቀው እስልምና ኃይማኖት የሚከፋፍል ነገር ይሄ እንዲህ ነው ይሄ እንዲህ ነው ብዬ የማውቀው ነገር የለኝም አላውቅም
- የእስልምና ጉዳይ መጽሄት ሂጅራ የሚባለውን አንብበው ያውቃሉ ?
- አላውቅም
- መጽሄት መኖሩን አያውቁም?
- መጽሄት መኖሩን ባውቅም እኔ አንብቤ አላውቅም የቁርአን ለመቅራትም ጊዜ ስለሌለኝ እንኳን መጽሃፍ ላነብ አንብቤም አላውቅም
- ያሲን ኑሩ ፊት ያወጣውን አስተምሮት አይቻለሁ ብለዋል በትክክል አዳምጠውታል ኮሴቱን ?
- አዎ በትክክል አዳምጫለሁ ያሲን ኑሩ ፎቶግራፍም ቪዲዮ ካሴቱ ላይ አብሮ ስላለ የአህባሽ እና አህባሽ አስተምሮት
- ቆይ አይተውታል ወይ ካሉት አርስቱ ምንድን ነበር የሚለው?
- ስለአርስቱ እኔ አልያዝኩትም አህባሽ እና የአህባሽ አስተምሮት በሚል ነው እንግዲህ እሱ ይመስለኛል እኔ ምስክር እሆናለሁ ብዬ አልተዘጋጀሁበትም ያንን ብቻ አየሁኝ ውስጡ ያለውን
- ሼህ አህመድ የመጠይቆትን ብቻ ይመልሱልኝ ቀላል የሚሆነው እንደሱ ሲሆን ነው የሚያውቁት ከሆነ ያውቁታል እማያውቁት ከሆነ አላውቀውም ነው የሚሉን አሁን ካሴቱን አይቼዋለሁ ብለዋል እና አርስቱን አይተውታል ወይ ?
- አርስቱን አላየሁትም
- እሺ ካሴቱ በሚያዝያ ወር 2004 ዓ.ም. ነው ያየሁት ብለዋል ካሴቱ ያኔ ነው ታትሞ የወጣው?
- እንግዲህ ያኔ ይታተም ሌላ ጊዜ ይታተም የታተመበትን ጊዜ አላውቅም ግን ካሴቱን ነው ያየሁት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ በካሴቱ ላይ ያሲን ኑሩ ያላቸውን የራሳዝውን ሃሳብ እና እምነት ነው አደለም የሚገልፁት በካሴቱ ላይ ሃሳብ እና እምነታቸውን ነው የገለፁት አደል እሳቸው ያመኑበት እና ያሰቡትን ነገር ነው የገለፁት አደል?
- አይ ቅድም ገልጫለሁ የካሴቱን መንፈሱን ጽንሰሃሳቡን ገልጫለሁ እና
- ቆይ አደለም ያ ሃሳብ የእሳቸው እምነት እና የእሳቸው አስተሳሰብ ስለሆነ ያንን እምነታቸውን እና አስተሳሰባቸውን አይደለም ወይ ከካሴቱ ላይ የገለፁት ነው የምሎት?
- አዎ ስላላቸው አስተሳሰብ ስላላቸው አመለካከት የአህባሽ ኃይማኖት መጥቷል በሚል ዳይሬክሽን ያው ገልፀዋል
- እሺ ካሴቱ ለሙስሊሙ ሕብረሰተብ ተሰራጭቷል አደል?
- አዎ ተሰራጭቷል በየሞባይላቸውም እያዩት ነው ያሉት በየእንትናቸውም ያዩታል ያ እራሱ ቅስቀሳው ነው ለዚህ ኃይማኖት የዳረገው እና ለዚህ ችግር የዳረገው ሙስሊሙ መከፋፈል ደረጃ የደረሰው ያነው
- ይኸውሎት የሚሰጡት ማብራሪያ አንደኛ በደምብ አይሰማኝም ድምፃን ትንሽ ከፍ ያርጉልኝ 2ኛ ጥያቄውንም ስለሚያሰፋው በቃ እኔ የምጠይቆትን ብቻ እያደረጉ ይመልሱልኛል እንዳላቋርጦት ነው ዝም ያልኮት በካሴቱ ላይ ሙስሊሙ ሕብረሰተስ ኃይማኖቱን መጠበቅ አለበት ይላል አደል?
- አዎ ኃይማኖቱን መጠበት አለበት አህባሽ የሚሉት አስተምሮት ስለመጣ ይሄ ያለውን ኃይማኖት መጠበቅ አለበት የሚል ነው
- አንድ ሙስሊም ኃይማኖቱን መጠበቅ አለበት የሚለው የኃይማኖቱ መሰረታዊ መርህ ነው አደለም?
- አዎ መሰረታዊ መርህ ነው ግን ሌላ አዲስ ኃይማኖት መጥቷል ቴሜ ታይሬክሽኑን መጠበቅ አለበት የተባለው ጽንሰ ሃሳቡ ይሄ ነው
- እሺ ለጥያቄ ብቻ ያርጉት ተጨማሪው ማብራሪያ እኔም ስለሚያስቸግረኝ ሙስሊሙ ሕብረሰተብ መንቃት አለበት ይላል አደል ካሴቱ?
- መንቃት አለበት እና መጠበቅ አለበት ልዩነት ያላቸው አይመስለኝም
- እኮ ይላል አደለም አይልም?
- ምናልባት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ኃይማኖቱን መጠበቅ አለበት አህባሽ የሚሉት አስተምሮት መጥቷል አዲስ ኃይማኖት የሚል ከዛ ጽንሰሃሳብ ነው ሊረዱ የምፈልገው

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ስለዚህ መ·ስሊ·መ· ሕብረሰተብ ኃይማኖቱን ነቅቶ መጠበቅ አለበት ማለት ተገቢ አስተምሮት ነው አደል?
- መጠበቅ አለበት ሲባል ተገቢ አስተምሮት ሳይሆን መጠበቅ አለበት ብሎ ማለት ነው አንድ የሆነ ነገር ተበርሂል መጥቷል እና ያንን እንዳትከለስ መጠበቅ አለብህ ያለውን ማለት ነው እንግዲህ ይሄ ነገር ባይመጣ ኖሮ ያም ባልተባለ ነበር ማለት ነው ስለዚህ አሁን መሰረተ ሃሳቡን ስናየው አህባሽ የሚባል አስተምሮት አዲስ ኃይማኖት መጥቷል በዛ ተሳታፊ እንዳትሆን መጠበቅ አለብህ ያ ደግሞ የተሳሳተ ነው የሚለው ያለ ማለት ነው ከዛ አኳያ ነው
- ይሽውሎት ሼህ አህመድ እንዳላቋርጦት ዝም ስል እንትኑን እየረበሹብኝ ነው የኔ ጥያቄ መ·ስሊ·መ· ሕብረተሰብ ኃይማኖቱን ነቅቶ መጠበቅ አለበት የሚል አስተምሮ ተገቢ የኃይማኖት አስተምሮት አደለም ወይ ነው ችግሩ አሁን እርስዎ ያሉት ችግር አለ የለም የሚለው ፍ/ቤቱ የሚመዝነው ወይም በሌላ ማስረጃ የሚታይ ነው አህባሽም ላይ ችግር አለ ወይም የለም የሚለው ነገር ግን እሱ እንዳለ ሆኖ አንድ መ·ስሊ·ም ኃይማኖትህን ነቅተህ መጠበቅ አለብህ ተብሎ ለአንድ መ·ስሊ·ም የሚሰጥ ትምህርት ተገቢ የኃይማኖት አስተምሮት አደለም ወይ ነው?
- እኮ መጠበቅ አለብህ ሲባል ከኋላ ያዘለው ነገር አለ ማለት ነው ዝም ብሎ አደለም መንቃት አለበት
- አሁን የጠየቅኩት ተገቢ አስተምሮት ነው አደለም ብቻ ነው
- አሁን የሚያደርጉት ምንድን ነው ተገቢ አስተምሮት ነው አደለም የሚል ጥያቄ ነው ተገቢ ከሆነ ተገቢ ነው ግን ይሄ አስተምሮት የነበረው አስተምሮት ይሄ አይደለም ካሉ ደግሞ እሱን ነው የሚያብራሩት?
- ተገቢ አደለም
- እኮ እንዴት?
- እንዴት ማለት ጥሩ ነው አሁን ለምሳሌ መ·ስሊ·መ· ኃይማኖቱን ጠብቆ ይዟል ድሮም ቢሆን መጠበቅ አያስፈልገውም ማለት ነው መጠበቅ አስፈላጊ ነው የተባለው ይሄ አህባሽ የሚሉት አዲስ አስተምሮት መጥቷል ስለተባለ ወደዛ እንዳይበረዝ ስለፈለጉ ነው ማለት ስለዛ ደግሞ አህባሽ የሚል አስተምሮ ደግሞ አልመጣም ስላልመጣ ዝም ብሎ መ·ስሊ·ሙን ማደናገር ነው የሚሆነው እና ከዚህ አኳያ ነው

1683

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አህባሽ የሚል አስተምሮት አልመጣም በሚል ነው ኃይማኖቱን ነቅተህ መጠበቅ አለብህ የሚል ትምህርት መሰጠት የለበትም ነው ያሉት ?
- አህባሽ የሚሉት አስተምሮ መጥቷል ስለተባለ እኮ ነው የነበረ ኃይማኖትን መጠበቅ አለብህ ተብሎ የተባለው
- አህባሽ የሚል አስተምሮ ስለሌለ ነው ወይንስ በአጠቃላይ ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ ኃይማኖትህን ነቅተህ መጠበቅ አለብህ መባል የሚል አስተምሮት መሰጠት ስለሌለበት ነው ይሄንን ነው ማብራሪያው ነው እየረበሸኝ ያለው ?
- አንዴ ስሙኝ እስቲ ምስክሩ የተረዳውን ኮንቴክስት ገልጿል ከዛ በኋላ /ግልጽ ያልሆነ/
- ምናልባት የተከበረው ፍ/ቤት የሚሰጡት ማብራሪያ ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይን መሰረት እሳቸውን ማቋረጥ ስለሌብኝ ነው እንዲጨርሱ የማደርገው ግን ማብራሪያው ጥያቄዬን እየመለሰው አደለመ ጥየቄዬን ከመመለስ ይልቅ እንደገና ሌላ ቅርንጫፍ ነው እያወጣበት ያለው
- ችግሩ የተረዱትን ገለፁበት የተረዱት መጠበቅ የሚያስፈልገው ምናምን ብለው ትንተና አስቀመጡ ከዛ በኋላ ያለው ይመዘናል እና ይሄን ፍሬ ነገር ትተው ወደሌላ
- እሺ እኔ ምናልባት ፍ/ቤቱ ጥያቄ ላስረዳና ፍ/ቤቱ አይሆንም ካለኝ ልለፍ ለፍ/ቤቱ ላስረዳ ለእሳቸው ሳይሆን የኔ ጥያቄ አህባሽ የሚል አስተምሮት ኖረም አልኖረም ሙስሊሙ ህብረተሰብ ኃይማኖቱን ነቅቶ መጠበቅ አለበት የሚል አስተምሮ ተገቢ አስተምሮት ነው ወይስ አደለም ነው ይቺን ብቻ እንዲመልሱልኝ
- ተገቢ አደለም ብያለሁ እኮ
- እሺ ቅድም ካሴቱ ሕገወጥ ነው ከመታተሙ በፊት እንዲታተም መፈቀድ ነበረበት ብለዋል ይሄን የሚል ሕግ የለም አደል ?
- ሕግ አለ
- የትኛው ነው ሕጉ ?
- በኃይማኖታችን አለ ለምሳሌ አንድ
- ምሳሌ ሳይሆን ሃጂ አህመድ በትክክል ሕጉ የትኛው እንደሆነ እና የትኛው ሕግ እንደሆነ ለይተው ሕጉን ብቻ ንገሩኝ ?
- ሕጉ ኃይማኖታዊ ሕግ ነው
- እኮ የትኛው ሕግ ነው ንገሩኝ ?

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- በሃዲሱም በቁርአኑም አለ ሰውየው ያወቀውን ነገር ማሳወቅ ማስተማር ማስተላለፍ አለበት ያ ሲባል ደግሞ የአሚኑን ትእዛዝ ወይም ደግሞ የኃላፊዉን ትእዛዝ መፈፀም አለበት
- አቤት
- የሃላፊውነ ትእዛዝ ለሃላፊው አመልክቶ ኃላፊው ሲፈቅድለት ነው መሆን ያለበት መታተም ያለበት ለምን በዛ ላይ አንድ የቁርአን አንቀጽ ብጠቅስ ከተቀደልኝ ልጠቅስ እፈልጋለሁ
- የት ቁርአን ላይ ነው ያለው ይሄ?
- አዎ
- ቁርአን ስለ ካሴት ሕትመት ያስረዳል ?
- ስለ ካሴት ሕትመት ሳይሆን ስለ ዳእዋ ስለማስተማር
- እኮ ይኸውሎት የጠየቅኮት ካሴት ታትሞ እንዲወጣ ሳይፈቀድ ካሴት መታተም የለበትም ነው ያሉት ካሴት አትም ለማውጣት የሚከለክል ሕግ አለ ወይ ነው?
- አለ
- ከየትኛው ነው ሕጉን ንገሩኝ ?
- ሕግ በኃይማኖታዊ ሕጋችን አለ ለምሳሌ
- ምሳሌ አደለም ሼህ አህመድ ሕጉ የትኛው ነው ሕጉን ንገሩን ?
- ሕጉማ ኃይማኖታዊ ሕግ ነዋ ያለው ኃይማኖታዊ ሕግ ካሴት የሚለውን ሰውየው ለማስተማርም ይሁን በተለያየ መልኩ
- ኃይማኖታዊ ሕግ እያሉ ነው በራሳቸው አለ የኃይማኖታዊ ሕግ የሚባለው ነገር ይብራራ ከተባለ እሱን ማብራራት ያለብተ
- እሺ እንግዲህ ኃይማኖታዊ ሕግ በእስልምና ቁርአን እና ሃዲስ ነው ያለው ቁርአን ላይ ነው ሃዲስ ላይ ነው ካሴት ከማሳተምህ በፊት ማስፈቀድ አለብህ የሚለው የትኛው ላይ ነው ያለው?
- እንግዲህ አላህ ሶርአን ወሳእላ በቅዱስ ቁርአን /ግልጽ ያልሆነ/ ምክንያቱ ምንድን ነው እናንተ ያመናችሁ ሰወች ሆይ አላህን ተገዙ መሃመድ የሚላችሁን ነገር ስሙ እንደዚሁም ደግሞ የስልጣን ባለቤት የሆኑት ሰወች ደግሞ ትእዛዛቸውን ማክበር አለባችሁ እነሱ ትእዛዝ አክብር ሲባል ዱአ አርግ ሲባል ስገድ ሲባል በነሱ አማካኝነት ተንተርሶ ማስረከብ አለበት ማለት ነው መስራት አለበት መስበክ አለበት ከዛ አኳያ የስልጣን አኳያ የሆኑ ሰወች አልተሻሩም አሉ በቦታው አሉ እና እዛ አመልክቶ እንደዚህ ካሴት አዘጋጅቼ ነበር ማስተማር እችላለሁ ወይ ብሎ ከዚህ አኳያ ማስፈቀድ አለበት ነው

1658

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እሺ አሁን ባሉት ትርጉም እንሂድ እና ያሲን ኑሩ ይሄን ካሴት ለማሳተም ማንን ነበር ማስፈቀድ የነበረበት ?
- የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳይ ወይም የኡለማ የአዲስ አበባ
- አሁን የሰጡት ትርጉም እኮ ስለ እስልምና ጉዳይ ምክር ቤት ምንም የሚለው ነገር የለም?
- ኃላፊ እኮ ነው የእስልምና ጉዳይ ምክር ቤት ኃላፊ እኮ ነው የሙስሊሙ ኃላፊ ነው ለጊዜው እየሰራ ነው ያለው አዲስ ይመረጥ ሌላ ጉዳይ ነው ግን ስራዉን እየሰራ እያለማ ነው ያለው እና ከዚህ አኳያ የሚሰበከውን ሰበካ የሚሰጠውን ትምህርት በዛ ዳይሬክሽን ተፈቅዶ መሄድ አለበት
- እሺ ከአዲስ አበባ እስልምና ምክር ይሄ መፍቀድ አለመፍቀድ የሚል የመፍቀድ ወይም ያለመፍቀድ ስራ ማንን የሚመለከተው በተለይ?
- ፕሬዝዳንቱን መጠየቅ አለበት ፕሬዝዳንቱ ደግሞ የሚመለከተውን ያዛሉ
- ስለዚህ ፕሬዝዳንቱ ናቸው መፍቀድ የነበረባቸው?
- አዎ ሳንሱር ይደረግና ይሄ ነገር የሚፈቀድ ከሆነ ታትሞ ይሰራጫል የማይፈቀድ ከሆነ መቆም አለበት ለምሳሌ ሙስሊሙን የሚከፋፍል ዝም ብሎ እንዲሁ ሲሰራጭ ዝም ብሎ ማየት ተገቢ አደለም ምክንያቱም እነሱ ናቸው መፍቀድ ያለባቸው
- እሺ ከፕሬዝዳንቱ ጋር የማይስማማ ሰውስ ማንን ነው ማስፈቀድ ያለበት?
- ምክትል ፕሬዝዳንቱ አለ ፕሬዝዳንቱ የማይስማማ ከሆነ ለምን አይስማማም ምን ችግር አለ የማይስማሙበት ምክንያት የለም ኃላፊ ነው ሰውየው ኃላፊነቱን ባግባቡ መወጣት መቻል አለበት ኃላፊነቱን ካልተወጣ ደግሞ ተጠያቂ ነው
- ካሴቱ የኃይማኖታዊ ትምህርት ነው አደለም ጠቅላላ ያለው ይዘት የራሳቸውን አስተሳሰብ በኃይማኖታዊ ትምህርት ነው ያቀረቡት አደል ?
- እሰን ቅድም ጠቅሰዋል ማለት በራሳቸው አስተሳሰብ ነው የገለፁት ሲባል
- የኃይማኖታዊ ትምህርት ነው የሚለውን ፍ/ቤቱ ተረድቶት ከያዘልኝ ጥያቄዬን አነሳለሁ
- ቅድም የጠቀሱት ያለው ትምርህት ይሄ ነው ብለዋል ሌላ የምትጠይቁት ካለ
- እሺ አህባሽ የሚል አስተምሮት መጣ በሚል መደናገር ተፈጥሯል ብለዋል ይሄ በጣም የአብዛኛው የሙስሊም ሕብረተሰብጋር የተፈጠረ አስተሳሰብ ነው አደለም አህባሽ የሚል አስተምሮት አለ ወይስ የለም የሚለው ነገር አነጋጋሪ ነበር አደል?
- አዎ አለ የሚል ነገር ተነግሯቸዋል ያው ሙስሊሙ ተናግቷል
- አለ ወይም የለም የሚለው ነገር በአብዛኛው ሙስሊም ህብረተሰብ ውስጥ ጥያቄ ነበ አደል?

1659 76

http://ethcriminalawnetwork.com/

- አዎ ብዥታ ውስጥ ነበር የነበረው አለ መጥቷል የሚል ነገር ነው የሚነገረው አለ የለም የሚል ነገር ብዥታ ቢኖርባቸውም ግን ያንን ለማጥራት እየተሰራ ነበረ የነበረው ለመስራት አልተቻለም
- መጅሊስ አህባሽ የሚል አስተምሮት የለም የሚለውን ነገር ለማስተማር ነበር የሚሰራው አደለም ?
- አዎ አህባሽ የሚሉት አስተምሮት የለም
- እኮ የለም የሚለውን ነገር ብዥታ ለማጥራት ነበር መጅሊስ ሲሰራ የነበረው አደለ?
- አዎ
- አህባሽ የሚሉት ሰወች አለ የሚሉበትን ምክንያት እንዲያስተምሩ መጅሊስ ፍቃድ ሰጥቷቸዋል እድሉን ሰጥቷቸዋል ?
- አዎ ፍቃድ ደብዳቤ ሰጥቷቸዋል
- እነሱ ለሕዝብ እንዲያስተምሩ እድሉ ተሰጥቷቸዋል?
- አዎ
- ሼህ አህመድ ይሄ ሴት ልጅ ሱሪ ትልበስ ቁርአን የአላህ ቃል አደለም የጅብሪል ቃል ነው የሚል እምነት እስልምና ውስጥ ይዜንን የሚያራምድ ቢነሳ አግባብ ነው?
- ጥያቄው ይደገምልኝ
- ሴት ልጅ ሱሪ ትልበስ ቁርአን የአላህ ቃል አደለም የጅብሪል ቃል ነው የሚል ሙስሊም ነኝ ወይም እስላም ነኝ ብሎ ቢነሳ ሕዝቡ መሃል ይዜንን ሃሳብ ይዞ ቢነሳ አግባብ ነው ከእስልምና አንፃር?
- አግባብ አደለም
- ይዜንን ቢነሳና አግባብ ካልሆነ ይዜ አግባብ አደለም አትቀበሉ ብሎ ማለትም ትክክል ነው አደል ቢነሳ ነው እያልኮት ያለሁት?
- አትቀበሉ ብሎ ማለት ትክክለኛ ተጨባጭ ነገር ሲሆን ነው ይዜ እራሱ እኮ ቀድሞ ከእምነቱ ውጪ ነው ይዜ እራሱ መባልም የሌለበት ነገር ነው ለምሳሌ ልጠቅስ እፈልጋለሁ
- ቅድም ተከሳሾችን እነዚህ ወንድሞቻችን ሲሉ ነበር ምን ማለቶ ነው?
- እዚህ ላይ አሁን አንድ የቁርአን አንቀጽ እገልፃለሁ አላህ በቁርአን /ግልጽ ያልሆነ/ ሲናገር
- ይተውት ይዜን ይዜ እኮ ግልጽ ነው ማለት ወንድሞቻችን ማለት ማንም ሰው የሚለው ስለሆነ

1680

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አይ ትርጉም ስላለው ነው የተከበረው ፍ/ቤት እኔ ቁርአኑን ሳይሆን የጠየቅኳቸው እንዲየው ከቋንቋ አንፃር ከምን መነሻ ተነስተው ነው እነዚህ ወንድሞቻችን የሚለው ለእኛ ትርጉም ስላለው ነው እንጂ የኃይማኖትን ትርጉም አልጠየቅኩም
- እኔም በዛ መንገድ አልነበረም እኔ የተረዳሁት ምንድን ነው ወንድሞቻችን ሲባል ማንም ሰው ወንድሞቻችን ይባላል እንጂ ከዚህ በላይ ሌላ ነገር አለ ካሉ ይቀጥሉ
- የተከበረው ፍ/ቤት ፍቃዱ ከሆነልኝ ልግለፀው ችግር የለውም
- ይግለፁት
- እና አላህ ሱብሃና ወታአላ በቁርአን ሲናገር /ግልጽ ያልሆነ/ ይላል ላኢላኢለላህ መሃመድ ኢረሱለላህ ያለው ሁሉ ወንድማማቾች ናቸው የሚለው የአላህ ቃል ነው ስለሆነ እንደዚህ ወነድሞቻችን ሙስሊሞች ናቸው አሁንም ወንድሞቻችን ሙስሊሞች ናቸው እኔም ነገ ወይ እንግዲህ ጥፋት አላህ ሱበሃና ወሳአላ የአላህ ፍርጃ ይሆንና ያጠፋና ይገባል ስላጠፉ ወንድሞቻችን አደሉም ማለት አለብኝ የአላህን ቃል መትለፍ አለብኝ ሙስሊሞች ናቸው ነገር ግን መስመር ስተዋል የሙስሊም ስራ አልሰሩም ከሚል ዳይሬክሽን ነው
- ቅደም ስለካሴት ሲያነሱ ማን እንዳዘጋጀው አያውቁም አደል ያሲን ኑሩን እዛ ከማዳመጡ በስተቀር ይሄ ካሴት በማን እንደተዘጋጀ ያውቃሉ እንዴ?
- ሰውየው ያላዘጋጀውን ያወራል እንዴ ቀርቦ ያሲን ኑሩ ፎቶ ግራፋቸው አለ ካሴቱ ላይ ማብራሪያ የሚሰጡ እሳቸው ናቸው ስለሆነም እሳቸው እንዲያዘጋጁ
- ምናልባት ጥያቄውን አንደርስታንድ ያድርጉት ማዘጋጀት ማውጣት መፃፍ የሚሉትን ወይ ለይታችሁ ይሄን ያውቃሉ ?
- እ
- አዘጋጅ እንደገና ፀሐፊ በዛ መንገድ ልትመጡ ፈልጋችሁ ነው እሱን ለይታችሁ ግልጽ አርጋችሁ
- ያሲን ኑሩ እዛ ካሴቱ ላይ ሲናገር ነው ያዩት አደል?
- አዎ
- ይሄን ካሴት ግን እንደዚህ እንዲሰራጭ ያዘጋጀው ማን እንደሆነ ያውቃሉ ?
- አይ ያሲን ኑሩ አዘጋጀሁት የተዘጋጀው ከያሲን ኑሩ ይላል ካሴቱ ላይ እርእሱ ላይ ከዚህ አኳያ የያሲን ኑሩ ዝግጅት እንደሆነ ነው የተረዳሁት
- ይበቃል ሼህ አህመድ ከአቡበከር አለሙ ጋር ኑር መስኪድ እያላችሁ በግል ፀብ አላችሁ የላችሁም?

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የለንም ጭራሽ አንተዋወቅም
- ኑር መስኪድ አንድላይ ስትሰሩ ፀብ አልነበራችሁም?
- ምንም በምንም ነገር
- ሸህ መከተ በፊት ጥሩ ነበሩ ብለዋል ምን ማለት ነው?
- አይ ጥሩ ስነምግባር ነበራቸው ለማለት ፈልጌ ነው እንግዲህ አሁን ይሄ እራሱ
- በኋላ ምን አድርገው ስነምግባራቸው ተበላሸ?
- በጣም ጥሩ በኋላ ስነምግባራቸው የተበላሸው ምንድን ነው ለምሳሌ አሁን እየተሰራ ያለው ስራ የዲን ስራ አደለም የእስላም ስራ አደለም
- በዛ የተነሳ ነው እንደዚህ ያሉት?
- አዎ አላህ ሱብሃና ወታአላ ያለው
- ይበቃል ለምጠይቆት አጭር መልስ ብቻ ነው የምፈልገው አህባሽ መጥቷል ብለው ነው ከምን መነሻ ነው አህበሽ መጥቷል ያሉት ምንም መነሻ ሳይኖራቸው ነው ምንድን ነበረ መነሻቸው?
- እኔ መነሻውን አላውቅም
- እሺ ስልጠናም አትሳተፉ ብለዋል ብለዋል የትኛውን ስልጠና ነበር እንዳትሳተፉ ያሉት?
- ስልጠና የአንድ ቀን የአህባሽ የሚለው ኃይማኖት መጥቷል የሚለውን ሕዝቡን ለማስረዳት የዛን ጊዜ መጅሊሱ እራሱ ሕዝቡ ውጅምብር ውስጥ ስለሆነ በሙስሊሙ
- የት ነበረ የጠራው ስብሰባውን ይሄንን ስልጠና ነው እንዳትሳተፉ ያሉት?
- እንዳትሳተፉ አደለም እንዳትሳተፉ ሳይሆን ስልጠናው ላይ ስብሰባው ላይ መጡ ልጆች አሉ ታዳጊ ልጆች አሉ እድሜያቸው ቢያንስ ከ15-18 የሆኑ ልጆች አሉ አዋቂዎች አሉ
- አይ አደለም
- ቆይ ጥያቄውን ግልጽ አረጉላቸው
- እሺ ጥያቄዬ ምንድን ነው አህባሽ መጥቷል ስልጠናውም ላይ እንዳትሳተፉ ያሉን ነበረ ብለዋል እና
- እሱን
- አልፈዋለሁ ትቼዋለሁ እሺ ኮሚቴዎቹ ኮሚቴ ነን ብለው ብለዋል በሕዝብ ስለመመረጣቸው ስላለመመረጣቸው አወሊያ ያውቃሉ እርስዎ አያውቁም?
- በሕዝብ እንደተመረጡ አላውቅም እራሳቸው ኮሚቶ ሆነው ነው የተሰየሙት እንጂ
- እርስዎ አወሊያ በነበረው ፕሮግራም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ይሳተፉ ነበር?

166 79

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አንዳንድ ጊዜ እሄዳለሁ ምክንያቱም መስሊም ነው የኢማኔ ጉዳይ ያሳስበኛል የኃይማኖቱ ጉዳይ ያሳስበኛል የሚተላለፈው አኳያ መስሊም እንደዚህ መሆን በመጀመሪያ ደረጃ የመስሊም ባህሪ
- እምጠይቀትን ብቻ
- እኮ እሄዳለሁ አንዳንድ ጊዜ እሄዳለሁ
- ሁል ጊዜ አይሄዱም ነበር?
- አዎ አንዳንድ ጊዜ እሄዳለሁ
- እሺ ምርጫውን በተመለከተ ኡለማ ምክር ቤት አይመለከተውም ብለዋል ኡለማ ምክር ቤት ምርጫው ይመለከተዋል እንዴ?
- አዎ ይመለከተዋል የኡለማ ምክር ቤት ስለሆነ
- በቃ ይመለከተዋል ካሉ በቂ ነው ሌላው ምክትል ፀሐፊው ሲሄዱ እርስዎ አብረው ነው የሚሄዱት
- ምክትል ፀሐፊው ምክትል ፕሬዝዳንቱ
- ሼህ ሰኢድ ቅድም ሲሄድ ነበርኩኝ ብለዋል ሁለት ጊዜ ሦስት ጊዜ አብራችሁ ነው የምትሄዱት ለስራ ነበረ የምትሄዱት እንዴት ነው?
- ሁል ጊዜ አንሄድም አንዳንድ ጊዜ ይጠሩኛል እሄዳለሁ
- ከቢሮ ነው ተነስታችሁ የምትሄዱት?
- እንግዲህ ከቢሮም ሊሆን ይልላል ቢሮም ባልሄድ ስልክ ይደውሉልኛል እንደዚህ ቅድም የማስተማር ትንሽ ደራሲ ስለሆንኩ ገጣሚ ስለሆን ብያለሁ ሂንት ስላለኝ ትምርት ቢሰጡን የሚል ውሳኔ ስላላቸው
- ጨርሻለሁ
- አመሰግናለሁ ምስክር ቅድም ሲያስረዱ በኑር መስኪድ አህባሽ ሱሪ ልበሱ የማይል መሆኑን ወለድ ብሉ የማይል መሆኑን እና ሴት ልጅ ታሰግድ የማይል መሆኑን ለማስተማር መስኪድውስጥ ገብተው እያለ አቡበክር እና ሌሎች ወጣቶች በረብሻ አላህዋክበር እያሉ ሰው እንዲረበሽ አደረጉ ነበር አደለ ያሉት?
- ልክ ነው ይኼንን ነው አደለ ያሉት?
- አልገባኝም ይደገምልኝ
- እሺ ጥያቄዬ አህባሽ ሱሪ ሴት ልጅ ሱሪ ትልበስ ወለድ መብላት ይቻላል ሴት ልጅ ታሰግድ ይላል እንዴ?

1663

http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ስለ አህባሽ አላውቅም የማውቀው ሃዲስ እና ቁርአኑን ነው የማውቀው ሃዲስ እና ቁርአኑን ብናገር ደስ ይለኛል
- በቃ እሱን ካላወቁት ሌላ
- ምን ነበረ ታዲያ ሊያስተምሩ የነበረው እርስዎ በዛ መስኪድ ሰው የሰበሰቡት ሰው ተሰብስቦ እርስዎ ምን ነበረ የሚያስተምረ የነበረው ስለ አህባሽ በተመለከተ ማለት ነውወ?
- እኔ ስለ አህባሽ በተመለከተ ስለ አህባስ ድምፁንም አላንሳም አህባሽ የሚባል ነገር የለም እኔ አይስማማኝም እኔ የማስተምረው ከሃዲስ ከቁርአኑ ነው አህባሽ የሚል አስተምሮት መጥቷል የሚሉት እነሱ ናቸው እየከፋፈሉ እነሱ ሲሉ ግን አህባሽ የሚሉት አስተምሮት ወለድ መብላት ይበቃል ቁርአን የጅብሪል ቃል ነው ይላል የሚል ነገር ነው የሚያስተምሩት እና እንደዚህ ያለ አዲስ ኃይማኖት መጥቷል ብለው
- ሌላ ጥያቄ ልጠይቆት የታላቁ አንዋር መስኪድ ኢማም ሼህ ጣሃን ያውቋቸዋል?
- አውቃቸዋለሁ
- ከዚህ በፊት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የተናገሩትን ነገር ሰምተው ያውቃሉ?
- እኔ አላውቅም
- በሬዲዮ ፋና ቀርበው አህባሽ አለ ግን ሴት ልጅ ታሰግድ አይልም ያለውን ሰምተዋል?
- አላውቅም
- ያሲን ኑሩ ያዘጋጀውን ሲዲ ከአንድ ጉደኛዬጋ አይቼ አዘንኩ ብለዋል ጓደኛዎት ማን ናቸው?
- ሃጂ መሃመድ የሱፍ ይባላሉ
- ሲዲውን በሽያጭ ነው በምን መንገድ ነው ያገኙት ?
- ጥሩ እሱ
- እርስዎ ኖት ሲዲውን ያገኙት ቀድመው እሳቸው ናቸው ያመጡት?
- ከተጠየቅኩ ልመልስ?
- ይመልሱ
- ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነገር ስለሆነ
- የተከበረው ፍ/ቤት ጠያቂው ነው እኮ ማብራሪያ የሚጠይቀው አደለ
- ጥያቄውን ጠየቁ አደል እንዴት አገኙት ነው እኮ ጥያቄው ማን አመጣው ነው አደለም ጥያቄው እንዴት አገኙት ነው ጥያቄው ይሄን ጥያቄ ደግሞ እንዴት እንዳገኙት ያብራሩ

1664 81

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እንግዲህ አሁን መሆን ያለበት ይሄ ነው ዝም ብሎ አንድ የሚያሳምን ነገር አምጥቶ ብቻ ምን ማለት ሳይሆን ይሄ ተገቢ አይመስለኝም
- ቆይ አሁን እርስዎ ዝም ብለው እንዴት አገኙት ይሄን ካሴት እንዴት ነው እርስዎ የገባው ?
- እንግዲህ ይሄን ካሴት ያገኘሁት የአራዳ ክ/ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባኤ ምክር ቤት ሰብሳቢ የሆኑት ወይም ም/ሰብሳቢ የሆኑት ካሴቱን እንዴት እንዳገኙት አላውቅም እሳቸው እዩልን ብለው የጋበዙን
- ማን ናቸው እሳቸው?
- እሬድዋን ኑሩ ስም ባልገልጽ ደስ ይለኛል
- የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ምን ኃላፊነት ያላቸው ናቸው ያሉት?
- የማህበራዊ ጉዳዮች ዘርፍ ኃላፊ ማለት ካሴቱን ከኔጋ አብረው ያዩት ማለት ነው
- ያመጡትም እሳቸው ናቸው ?
- አደለም እየተደማመጥን ቢሆን ጥሩ ነው ምንዳይቀላቀልብን
- እሺ እዩልን ያለው ማን ነው?
- እይዩልን ያለው የአራዳ ክ/ከተማ እስልምና ጉዳይ ከፍተኛ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት ወይም ምክትል ሰብሳቢ
- ለምን ጉዳይ ነው እዩልን ብሎ የመጣው ?
- ካሴቱን ምን ይዘት እንዳለው እዩልን አርሙልን አለን ማረም ስላለብን ማየት ስላለብን አየነው
- አሃ እና በግርም ወይም በስጦታም የተገኘ አደለም ይሄ የክ/ከተማው እስልምና ጉዳዮች ያመጣው ነው ማለት ነው
- ቆይ እስቲ አሁን እሳ ነው የተገኘው በቃ እሳ ከስተገኘ ያመጡበትን ከየት እንዳመጡ አላውቅም አሉ ለእኛ ግልጽ ነው እናንተ አሁን ምኑ ግልጽ እንዳልሆነ
- እርስዎ የመጅሊስ ሰራተኛ ኖት አደል?
- አዎ በፊት የመጅሊስ ሰራተኛ ነበርኩ
- ተመልሷል ግን ከዚህ በኋላ የሚቀጥል /ግልጽ ያልሆነ/ ትንታኔ ካለ መጠየቅ ይቻላል የአሁኑን
- የመጅሊስ ምርጫ መቼ እንደተደረገ ያውቃሉ ?

1665

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የመጅሊስ ምርጫ ጥቅምት 20 ይመስለኛል በአጠቃላይ በንዋር ደረጃ ከወረዳ ጀምሮ ነውና በጣም ድንጋጤ /ግልት ያልሆነ/
- ቆይ የጠየቅኩት መቼ ነው?
- ጥቅምት 20 ቀን እሁድ ቀን ይምስለኛል
- ጥቅምት 20 ከዛ በፊት የነበረው ምርጫ መቼ ነው የተካሄደው ጥቅምት 20 ቀን 2005 ከተደረገው ምርጫ በፊት የነበረው ምርጫ መቼ ነው የተካሄደው?
- እኔ አላዉቅም እሱን
- በእርስዎ ግምት ምን ያህል ጊዜ?
- በግምት መናገር አልፈልግም
- ስለዚህ ምርጫ አልተደረገም ማለት ነው እርስዎ በሚያውቁት?
- አደለም ተደርጓል ካለ ምርጫ ሳይመረጥ ሰው ኃላፊ ነኝ ብሎ አይቀመጥም መቼ እንደተመረጠ ግን አላውቅም
- ስለዚህ የማያስታውሱት ከሆነ ስለቆየ ነው ማለት ነው
- በቂ ነው በራሳቸው ትርጉም ልተረጉሙ ትችላላችሁ በኔ አመለካከት ግን
- በቃ ቆዩ
- አወልያ ላይ ሰወች ይሰባሰቡ ነበረ ብለዋል የስብሰባችሁ ወይም እንዲሰበሰቡ ያደረጋቸው የመጅሊስ ምርጫ በመዘግየቱ ለረጅም ጊዜ የመጅሊስ ምርጫ ባለመደረጉ ሊሆን ይችላል
- የተከበረው ፍ/ቤት መቃወሚያ አለን
- እሺ
- የምንታገሰው ያው ላለመቆራረጥ ነው ክርክሩን ይዤ ጥያቄ በአምስት አይነት መልኩ ነው እኚህ ምስክር እየጠየቁ ያሉት አሁንም መጨረሻ ላይ የተጠየቀው ጥያቄ ምስክሩ ደጋግመው ምላሽ ሲሰጡበት አግባብነትም ያለው ጥያቄ አደለም ሲጀመርም እኛ ስለ መጅሊስ ምርጫ በዋና ጥያቄ አላስመሰከርንም ምስክሩ ያዩትን 3 ተከሳሾች እንዲህ እንዲህ ይሉ ነበረ ሌሎቹ ደግሞ በኮሚቴ ተደራጅተው በዚህ መልኩ ይንቀሳቀሱ ነበር ብለው ነው የመሰከሩት ሲጀምሩም ተከታታይ 6 ጥያቄዎች ነው የጠየቁት አሁን የመጨረሻው ደግሞ መልስም የተሰጠበት ነው በዋና ጥያቄም ያልተነሳ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት በአንድ እርእስ ላይ 5 ጥያቄ ተነስቷል ብለው ነው ወይስ ያልተነሳ ጥያቄ ወይም ጥይቄው እየተደገመ ነው የሚለው የአቃቤ ሕግ ውሳኔ ለመስጠንም አንድ እርእስ ቢሆንም እኮ ያልተብራራ ነጥብ ካለ ከባልደረቦቼ ቢጠየቁም እኔም ባልተብራራው

1666

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

እርእስ ላይ ከመጠየቅ የሚያግደኝ ነገር የለም ስለዚህ አሁን ምስክሩን እየጠየቅናቸው ትክክለኛውን ነገር ነጥሮ እንዲወጣ ለማስቻል ነው ፍ/ቤቱ እንዲገነዘበው ነው ትክክለኛ እራሱ ጥያቄው ተጠይቆ ከሆነ እኔም ሲጀመር አልጠይቀውም ፍ/ቤቱም ያስቆመኛል አቃቤሕግም መቃወሚያ ሳያስፈልግ ማለት ነው ነገር ግን ጥያቄው እርእሱ ላይ ቢጠየቅም እኔ ነጥሮ እንዲወጣ የምጠይቀው ጥያቄ ይለያል እና እንዳልጠይቅ የሚያግደኝ ነጥብ ወይም የአቃቤ ሕግ መቃወሚያ ተገቢነት ስለሌለው እንድጠይቅ ይፈቀድልኝ

- ብይን ሰጥተናል አሁን ለመቃወሚያው መሰረት የሆነ ጥያቄ በአወሊያ የተሰበሰቡት ምርጫው ስለዘገየ ነው አደለም ወይ ተብሎ ነው ጥያቄ የተጠየቁት መቃወሚያ እዚህ ላይ ሲቀርብ አንደኛ ከርእስ ውጪ የሆነ ነገር ተጠይቋል ተደጋግሟል የሚል ነገር ተነስቷል ምላሽ ሲሰጥ ይሄ ጥያቄ እርእሱን በተመለከተ ቢነሳም ይኄን ጥያቄ የሚመለከት ነገር በግልጽ አልተነሳም ለዛ ነው ያሳሁት የሚል ነገር ምላሽ ሰጥተው ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮታል በእርግጥ ምስክሩ ስለምርጫ አንስተዋል ነገር ግን ስለምርጫ ያነሱበት አስፔክት ቆይቆ ቆይቶ ከግርግር በኋላ የኡላማ ምርጫ እንዲደረግ ተወስኗል ምርጫ ሲደረግ ሲወስኑ ቀኑን አስቀምጠዋል ነገር ግን የተከሳሾቹን ሌሎቹ ይሄንን አንደኛው ኡላማ ስለምርጫ መወሰን የለብትም ጊዜውንም ማስቀመጥ የለበትም ምርጫውም በመስኪድ መሆን አለበት ተብሎ ይሄንን ተቃውሞ ብለው ነው የመለሱት ስለዚህ አሁን ምርጫ በመዘግየቱ ነው ያ ስብሰባ የተካሄደው የሚለው የዚህ ውስጥ የሚካተት አደለም ከዚጋር በቀጥታ የሚያያዝ ስላልሆነ ይሄ ጥያቄ ይታለፍ ተብሎ ብይን ተሰጥቷል
- ቅድም ጠይቄዎት ሲመልሱልኝ እርስዎም መጅሊስ እንደሚሰሩ ነግረውናል እና መቼ እንደተመረጡ ለፍ/ቤቱ ሊያስረዱልን ይችላሉ መቼ ተመርጠው ነው ወደ መጅሊስ የገቡት ?
- ስለምርጫው በዚህ ይብቃ
- እሳቸውን በሚመለከት የተከበረው ፍ/በት
- ይሄ በቃ
- እሺ አመሰግናለሁ መጅሊስ እንዴት ገቡ እርስዎ ተቀጥረው ነው ወይስ በምን ሁኔታ ነው ወደ መጅሊስ የገቡት?
- ያው እኮ ነው
- የተከበረው ፍ/ቤት ስለምርጫ አላነሳሁም

1667

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆዩ እስቲ ይሄ በባሌም ይሁን በቦሌ ያው ነው ጥያቄው እና ብይን ማክበር አለባችሁ ይለፉት
- አቡበክር አለሙ ወጣቶችን ይዞ በኑር መስኪድ አላህዋክበር በማለት ንግግር አንዳላረግ እረበሸኝ ብለዋል መቼ ነው ይሄ የሆነው?
- በግምት በሚያዝያ ወር አካባቢ ነው የዛን ጊዜ
- ቀኑ በቃ ማብራሪያ ሳይሆን ቀኑን ነግረውናል
- ሚያዝያ ወር ምን ቀን ላይ ነው?
- እሱን አላስታውስም
- ከሰኞ እስከ አርብ በየትኛው ቀን ነው?
- አላስታውስም
- የት ነበረ አቡበክር አለሙ?
- እኔ እንጃ
- የት ሆኖ ነው ሲረብሽ ያዩት እርስዎ?
- የተጠራው ስብሰባ ላይ ገቡ
- ስብሰባው ላይ ምን ያህል ሰወች ነበሩ?
- ቁጥራቸውን አላውቅም
- መስኪድ ውወስጥ ነው ከመስኪድ ውጪ ነው?
- መስኪድ ውስጥ
- መስኪዱ ሞልቶ ነበረ?
- ዋናው መስኪድ ሳይሆን ለብቻ የሆነች ቦታ አለች እዛ ውስጥ ነውያለው
- ይቺ ቦታ ያሏት ሞልታ ነበረ?
- አዎ ሞልታ ነበረ
- ምን ያህል ሰው ትይዛለች በግምት?
- ግምቱ ግን ያስቸግረኛል
- ያ ስብሰባ የተጠራው በማን ነበር?
- ቅድም የገለጽኩት ይመስለኛል የተከበሩ ጠበቃ ድግግመሽ አይሁንብኝ
- ምክንያቱም ያን እየነሳን ስንሄድ አንደኛ እንትኑ ላይ ዱፕሊኬት እየሆነ ነው የሚሄደው የተመለሰውን ጥያቄ በትክክል ይዛችሁ እናንተ እሱ ጥያቄ ላይ ተንተርሳችሁ መስቀለኛ ጥያቄ ወይ መርታችሁ ቢሆን እሱ ላይ ማንሳት ነው እንጂ እሳቸው የመሰከሩትን በዋና

1668

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

ጥያቄ በትክክል የተመለሰውን መድገሙ ወረቀቱን ያባዛዋል ስለዚህ ጥያቄውን መርጣችሁ እሱጋ መልሱ

- እርስዎ መጅሊስ እንደሚሰሩ ነግረውናል የመጅሊስ ምክር ቤት እና አሁን ኮሚቴ ነን ይላሉ ያሉት ሰወች በፌደራል ጉዳዮች ውስጥ አብረው ስብሰባ እንዳደረጉ እና ከፌደራል ጉዳይ መልስ እንደተሰጣቸው ያውቃሉ አደል?
- እዛ እንደሚሰራ አላውቅም ሂደቱን ሰብሳቢው አመራሮች ስላሉ እነሱ ናቸው የሚያውቁት
- መልስ ተሰጥቷቸዋል አደል?
- እኔ አላውቅም
- እሺ ቅድምሲዳው ላይ ስለ ጀሃድ የተመለከተ ነገር አይቻለሁ ብለዋል ወይም ሰምቻለሁ ብለዋል እርስዎ በኡለማ ምክር ቤት ውስጥ ኃይማኖትን በተመለከተ ነው የሚሰሩት ብዬ እገምታለሁ እና እስቲ ጀሃድ ምንድን ነው ይንገሩን ፍ/ቤቱ እንዲረዳ አንድ ሰው ከነፍሱጋ ስሜቱን ለመታገል የሚያደርገው እንቅስቃሴ በእስልምና ጀሃድ ይባላል አይባልም ?
- ስሜቱን ለመቆጣጠር የሚያደርገው ጀሃድ በግልጽ እንደዚህ ብዙ አይነገርለትም
- አይነገርለትም እንጂ ጀሃድ ነው?
- ቆይ እስቲ አንዴ ቅድም ካሴቱ ላይ ጀሃድ ብለው አንስተዋል?
- አዎ
- እሺ ይቀጥሉ
- ጥያቄዬን አጭር ላድርግሎት እርስዎ አጭር መልስ ስጡኝ አንድ ሰው ስሜቱን ለመቆጣጠር የሚያደርገው ጥረት በእስልምና ኃይማኖት ጀሃድ ይባላል አይባልም?
- ጀሃድ ብሎ ማለት ሰውን በማነሳሳት የሚደረገው ጀሃድ ይባላል
- እ?
- አላህዋክበር እያሉ ሰውን ማነሳሳት ያው ለውጊያ ለጦርነት ወይም ደግሞ ሁከት ለማንሳት የሚደረግ ጀሃድ ነው
- እኮ አጭር መልስ ነው የጠየቅኮት አንድ ሰው ስሜቱን ለመቆጣጠር የሚያደርገው ትግል ማለት ነው ከራሱ ጋር ከነፍሱጋር የሚያደርገው ጀሃድ ተብሎ አይታወቅም ?
- ጀሃድ ተብሎ ይታወቃል ግን ይሄኛው
- እሺ በቃ ይሄንን ው የጠየቅኩት ሌላ ጥያቄ ልጨምርሎት
- የተከበረው ፍ/ቤት ማብራራት አደለም መስቀለኛ ጥያቄ ነው አጭር መልስ ከሰጡኝ ወደሚቀጥለው ጥያቄ ልሂድ

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይቅርታ
- የተከበረው ፍ/ቤት ማብራሪያ መስጠት እፈልጋለሁ
- ሌላ ጥያቄ ስላለኝ ነው
- ቆዩ እስቲ ምንድን ነው አሁን የተነጋገርነው ከዚህ በፊት ይካሄድ የነበረው ሁለት ሦስት ቀን ጥሩ ነገር ነው የነበረው እና ያ ነገር ወደ ቦታው እንዳይመለስ ነው ስለዚህ እሱ እንዳይመለስ ጠበቃ እየጠየቁ ያሉት ጥያቄ ጠይቀዋል ጠይቀው ሊያስረዳ የሚፈልጉት የፍ/ቤቱን ነው ሌላ አደለም ስለዚህ ለፍ/ቤቱ ሊያስረዱ ከፈለጉ የተመለሰው ምላሽ በቂ ካልሆነ ፍ/ቤቱ ቀጥል መለስ ማለት ይችላል ሰዚህ እርስዎ ይበቃኛል ብለው ፍ/ቤቱ ማስቆም አይችልም ማለት አይችሉም ተቀብለው ግልጽ ያልሆነውን ነገር ፍ/ቤቱ በመሃልምም መርቶም ሌላ ነገርም ጠይቆ እንዲብራራ ሊፈልግ ይችላል ምክንያቱም መጨረሻ ላይ የሚቸገረው ይሄ ፍ/ቤት ነው ስለዚህ መልሱ ለእርስዎ ሳይሆን ግልጽ መሆን ያለበት ለፍ/ቤቱ ነው ግልጽ መሆን ያለበት ስለዚህ አሁን ለፍ/ቤቱ ግልጽ አልሆነም ግልጽ ካልሆነ ፍ/ቤት ደግሞ ይሄንን ትእዛዝ ሲሰጥ ተቀብሎ መሄድ ነው የጠበቆችም ሆነ የአቃቤ ሕግ ጥያቄውን ማንሳት በቂ ነው መጨረሻ ላይ ለይግባኝ መሰረት የሚሆናችሁን ነገር ካነሳችሁ ፍ/ቤቱም ትእዛዝ ከሰጠ በቂ ነው መጨረሻ ላይ ለእናንተ የሚሆነው ከዛ በኋላ የምትጠይቁት ጥያቄ ነው የሚሆነው ስለዚህ በነዚህ ምክንያቶች ወደፊትም እየተጨቃጨቅን እንዳንሄድ በስርዓት እንዲመራ ትእዛዝ እያከበሩ ይሂዱ ጥያቄዉን ቅድም የጠየቁት ጥያቄ እሳቸው ይጨርሱት ፍ/ቤቱ ግልጽ ነው ካለ ያስቆማቸዋል
- እሺ እንግዲህ ስለ ጀሃድ ነው የተነሳው ጀሃድ የሚባለው ነገር አሁን ከነፍስጋ ጀሃድ አደለም የተባለው ዋና ጽንሰ ሃሳብ ከነፍስጋ የተያያዘ ሳይሆን ከጦርነት ነው አላማው ጦርነት ጀሃድ እንዋጋለን ጀሃድ እናደርጋለን እንጂ ጀሃድ ሆነ ማለት ትእግስት እናደርጋለን ነው ከነፍስያውጋ ነፍስያችን መጥፎ ነገር ላይ እንዳትሄድ መጥፎ ነገር ላይ እንዳትወድቅ ነፍስያችንጋ እንታገላለን የሚለው ጀሃድ ቢሆንም አላማው ግን የአሁኑ ጀሃድ ብሎ ማለት ጦርነት እናነሳለን ነው
- ሼህ አህመድ ጀሃድ የሚለው የአማርኛ ነው የአረብኛ ቃል ነው ?
- እንግዲህ እሱ አሁን የተነሳው ግን እኔ የተረዳሁት በዚህ በዚህ ነው ብሎ አስቀምጧል ስለ ጀሃድ ማለት ነው
- ሌላስ ትርጉም አለው ከዚህ ውጪ አሁን ከገለፁት?
- በቃ ሌላ ትርጉም የማውቀው ይሄን

ECHN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ጥሩ ቅድም አወልያ ላይ ተከሳሾች እከሌ አለ ባይሉም ጀሃድ አውጀናል ሲሉ እንደሰሙ ለፍ/ቤቱ ነግረዋል አደል ቀኑ መቼ ነበር ይሄን ያሉት?
- ቀኑ በተለያየ ጊዜ በወረቀት በፋንፍሊት ይገለፃል በቀጥታ በሰው ይገለፃል በተለያየ ቀን ነው ይሄ ቀን ብዬ ማለት አልችልም
- እርስዎ የሰሙት እራሶ በጆሮት የሰሙት ነው አሁን ያሉን ተከሳሾቹ ሲናገሩ የሰሙት ነገር እኮ ነው የጠየቅኮት መቼ ነው ያሉት ይሄንን ?
- እኮ ቀኑን አላስታውሰውም ማለት ነው
- አመተምረቱስ?
- አመተምረቱ 2004 ነው
- ቦታው አወልያ ነው ብለዋል?
- አዎ
- እርስዎ የትጋ ሆኖ ነበረ ያዳምጡ የነበረው?
- በማይክ ነው በእስፒከር ነው የማጠቀሙት የትም ቦታ ቢሆን ይሰማኛል
- እርስዎ የትጋ ነበሩ?
- እዛው መስኪዱ አካባቢ ቅጥር ግቢው ነበርኩኝ
- ስሊዚህ ከማይክ የሚተላለፈውን እየሰሙ ነው?
- አዎ
- የማንን ድምጽ ነው የሰሙት?
- እንግዲህ ያው ሁሉም አብሮ የጋራ ስራ ስለሆነ የጋራ የቅንጅት ስራ ስለሆነ ያው ተቀናጅተው ስለሆነ አንድጋ ቡድን ስለሆኑ የሁሉም ይሄ ነው ብዬ አልልም እንደ አጠቃላይ ሁላቸውም ብዬ ነው የምወስደው በድምጽ አለያቸውም
- ሼህ አህመድ
- አቤት
- ቅድም ያሲን ኑሩ ካሴት ሲያወጣ ለአዲስ አበባ መጅሊስ ማሳወቅ ነበረበት ብሎ ነው ልክ ነኝ ?
- አዎ
- ይሄንን ለምንድን ነው የሚያደርገው?
- እሱ ጥያቄ ቅድም ተጠይቆ ተመልሷል
- የተከበረው ፍ/ቤት

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኮ አሁን ይኸውሎት ምንድን ነው ያሉት ይሄ ካሴት ፈቃድ ያስፈልገዋል ወይ ሲባል ለለምን እንደሚያስፈልገው ዘርዝሯል እንደውም ቁርአን መጽሐፍ ጠቅሰው ዘርዝረዋል ስለዚህ ይሄን ከጠቀሱ እና ይሄ ከተመለሰ ከዚህ በኋላ ሌላ ጥያቄ ነው አሁን ከዚጋር ተያይዞ ምን ለማንሳት ፈልጎችሁ ነው የተለየ ነገር ካለ በቀጥታ እሱን ጥያቄ ጠይቁ
- ከእምነቱ አንፃር ነው ቅድም እሳቸው መልስ የሰጡበት ከእምነቱ አንፃር ነው ማብራሪያም የሰጡት እኔ ግን አሁን የፈለግኩት እሳቸው ከሚሰሩበት መጅሊስ ነው ከመጅሊሱ ነው ከመስሪያቤቱ ማለት ነው ቅድም ከእምነቱ አንፃር ነው ቁርአን እይቀሩ የነገሩን እና አሁን እርስዎ በሚሰሩበት መጅሊስ የመንግስት መስሪያቤት ማለት ነው እሳቸው እንደሚሉት ስለዚህ ለእዛኛው የማሳወቅ ግዴታ አለበት
- የመንግስት መስሪያቤት
- ለመጅሊስ ማለት ነው?
- ቆይ እስቲ ግልጽ አልሆነም አንደኛ እሳቸው ቅድም የጠቀሱት እስቲ እኛ የተረዳነው እንንገራችሁ እና በዛው ይቀጥሉ እኛ የተረዳነው ምንድን ነው ሲጠየቁ ማሳወቅ ነበረባቸው ለማን ለኃይማኖቱ ባለስልጣናት ለኃይማኖቱ ባለስልጣናት ደግሞ ቅድም እየጠቀሱ ለፕሬዝዳንቱ ቀጥሎ ላለው ነው እኔ ምናልባት ለመንግስት የሚል ነገር አልሰማሁም ምናልባትእስቲ ቆይ ይሄን ያንሱና አሁን እሳቸው ያሉት ይሄንን ነው ስለዚህ ማሳወቅ ነበረባቸው
- እኔ መጠየቅ የፈለግኩት በምን ሕግ ነው ለአዲስ አበባ አስተዳደር መጅሊስ እንዲያሳውቅ የሚፈልጉት ወይም የሚገደዱት
- ይኸውሎት እሱን ነው እኛም እያልን ያለነው በምን ሕግ ነው ሲባል በኃይማኖት ሕግ ነው በኃይማኖልት ሕግ እንዲህ ተብሎ በዝርዝር ነው ሲጠቀስ የነበረው እንጂ ሌላ ሕግ አልጠቀሱም
- ሌለ ሕግ የለውም መጅሊስ ይተዳደረበት ሕግ ካለ ብዬ ነበር ከሌለ በዚህ ከተረዳው እሺ
- እንደዛ ነው በኃይማኖት ሕግም ነው የተነሱት እነሱ ጠቅሰው በዝርዝር ያስረዱ
- እሺ ቅድም ሲጠየቁ አንዋር መስኪድ እንሂድ እና የአባስ የሚባለው ሰው ላይ የመግደል ሙከራ ተፈፀመበት ብለው ነበር ልክ ነኝ ?
- ልክ ኖት
- ምንድን ነው የመግደል ሙከራ ሲሉ ምን አዩ ተወጋ ተደበደበ ተተኮሰበት?
- አይ እሱ ላይ አልተደበደበም ግን

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆይ እንትን የምለው ነገር አለኝ እነሱ አላገኙትም አባስን ነገር ግን የአዲስ አበባ ሥራ አስፈፃሚዎች ካሉ ለመግደል ነበር ሃሳብ የነበረው
- በምን አወቁ ይሄን አካሄድ?
- ተሰበራ መስኮቱ ተሰበረ ገቡ እንደገና ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተመቱ ደሙ ቆሰሉ
- ስለዚህ መስኮቱ ስለተሰበረ ነው አባስ ሊገደል እንደነበረ ያወቁት?
- መስኮቱ ስለተሰበረ ብቻ ሳይሆን ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተመቱ ሲመቱ አይቻለሁ ከዚህ አኳያ ከመስኪዱ ቅጥር ግቢ ውጪ አጥር ከመስኪዱ ውጭ ፖሊስ ተፈልጐ መጥቶ ችግሩን መፍትሄ ሊሰጠው ችሏል
- በቃ ይሄን ስላየሁ ነው አሉ
- ቅድም ኑር መስኪድ ደግሞ ለማስተማር ሄደን ነበረ ብለዋል እርስዎ ከሰይድ በሽርጋር ሄደዋል በዚህ የትምህርት ሰዓት ላይ ሌሎች እንግዶች ከወጭ የተጋበዙ ሰወች አልነበሩም ?
- የለም አላውቅም አላየሁም
- አልነበሩም ነበሩ ካሉ እኮ ?
- አላየሁም እየመሰከርኩ ያለሁት ያየሁትን ነው
- ምስክር ቅድም ሲነግረን በአወልያ ስብሰባ ይደረግ ነበር
- ችግር አለ እስቲ እስቲ ሞባይላችሁን ድምጽ አለው ግን ምናልባት ሳናሳስባችሁ የቀረ ነገር በተቻለ መጠን ግን ሞባይል ጠፍቶ ነው መግባት ያለበት የጠበቆችም ምናልባት ሞባይል የያዘ ከሰራተኞችም እሺ ቀጥሉ
- ቅድም ተጠይቀው ሲመልሱ በአወልያ እና አልፎ አልፎም በአንዋር መስኪድ ስብሰባ የሚይደርጉ ወይም አላህዋክበር የሚሉ ሰወች አሉ ብለዋል ትክክል ነው በአወልያ እና በአንዋር መስኪድ ስብሰባ የሚያደርጉ ወይም በአንዋር መስኪድ ስብሰባ የሚያደርጉ ወይም አላህዋክበር የሚሉ ሰወች አሉ ብለውኛል አደል ብለው ተናግረዋል ?
- ስብሰባ ሳይሆን ከጁምአ ሶላት በኋላ የተሰበሰቡት ከዛ ከተሰበሰቡ በኋላ መልክት ይተላለፋል
- እኮ ምን ምን ይባላል?
- ቅድም ገለጽኩ አደል ጌታዬ
- አሁንም ይሄ ነገር አለ?
- እንግዲህ አሁን አወልያ የለም አንዋር አለ አልፎ አልፎ በተለይ እንደውም አሁን የዛሬ ወር አካባቢ ላይ
- አንዋር

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ቆይ ተጠይቁያለሁ ልጨርስ
- ግልጽ ነው አሁን ይሄ ለዚህ ጥያቄ ይሄ ነው
- እሺ
- ቅድም ሲያስረዱ አህባሽ አለ የሚሉ ሰወችም እድሉ ተሰጥቷቸው ነበር እንዲያስረዱ ብለዋል እንዲያስተምሩ እድል ተሰጥቷቸዋል ብለዋል በመጅሊሱ ነው የተሰጣቸው?
- አህባሽ አለ የሚል አላየሁም አህባሽ የሚባል ነገር አልመጣም አናውቅም ነው ያሉት እንግዲህ
- አይ ቅድም ስነግሩን አህባሽ የሚባል ነገር የለም ብለን እኛ ልናስተምር በኑር መስኪድ ስብሰባ አድርገን ተረበሸብን ብለዋል ባልደረባዬ ሲጠይቆት አህባሽ አለ ብለው የሚያስተምሩትስ እንዲያስተምሩ እድል ተሰጥቷቸዋል ወይ ሲባሉ አዎ ተሰጥቷቸዋል ነበር ያሉት?
- እኔ እሱ ላይ አላውቅም ስለ አህባሽ ተነሳ አህባሽ የሚባል ኃይማኖት መጣ ተብሎ ሙስሊሙ ውዥንብር ውስጥ ነው ያለው ተባለ አህባሽ የሚባል ኃይማኖት ቆዩ እስቲ
- ብለዋል አላሉም የሚለውን ከመለሱ በኋላ ወደ ማብራሪያ ሂዱ አላልኩም ነው ያሉት?
- እሺ እንደገና ይገለጽልኝ
- እሺ ጥያቄዬ ልድገምሎት?
- አዎ
- አህባሽ የለም ብለን ልናስተምር ስንል መጥተው አላህዋክበር ብለው እረበሹን ብለዋል አህባሽ ደግሞ አለ የሚሉ አሉ እርስዎም እንደመሰከሩት እና ህዝቡን ያሳስታሉ እንዳሉት እንያስተምሩ ተፈቅዶላቸው ነበረ ብለው ተናግረዋል ስለዚህ መጅሊሱን የፈቀደላቸው እንደያስተምሩ ካለ ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ መጅሊሱ ነው ፈቅዶላቸው የመጣው ?
- አህባሽ አለ የሚሉትን አልፈቀደም መጅሊሱ እያለ ያለው እንኳን ሊፈቅድ ቀርቶ አህባሽ የሚባል ኃይማኖት አልመጣም ነው ላለመምጣቱ ሕዝቡ ይረዳው ነው የተባለው እንጂ አህባሽ የሚባል እንትን አለ ተብሎ ያመለጠ ነገር የለም እኔም አላውቅም
- ቅድም ተጠይቀው ሲመልሱ በሲዲ የሚያወጣ ሰው መጅሊሱን ማስፈቀድ አለበት ብለዋል ከዚህ በፊት በሲዲ አስፈቅዶ ያወጣ ሰው ይነግሩናል ማን ነው መጅሊሱን አስፈቅዶ ያወጣ ሰው አለ ?
- እኔ በዝርዝር አላውቃቸውም አንድ አይነት ሲዲዎች እንደዚሁ ሲመጡ ያው ሳንሱር አርጉ ተብለን እንደምንሰጥ አውቃለሁኝ ግን በዝርዝር አላውቅም

1673

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እናንተ ሳንሱር አርጉ ተብሎ ይሰጣችኋል ?
- እናረጋለን ጥሩ ነው እንላለን ችግር ካለበት ይሄ ሙስሊም ለሙስሊም የማይጋጭ ነው ችግር የሚፈጥር ነው ይሄ መፈቀድ የለበትም ብለን አስተያየት እንሰጣለን ያው ከዛ ውጭ ግን እኔ እነማን እንደሆኑ ዝርዝሩን አላውቅም ሂደቱ ግን እንዳለ አውቃለሁ
- እሺ /ግልጽ ያልሆነ/ ስሞን ያስመዝግቡ
- ጠበቃ ዳዊት ነጋሽ
- ምስክር የአዲስ አበባ እስልምና ምክር ቤት የመጅሊስ ስልጣን ከምንድን ነው የሚመነጨው ?
- ስልጣን የሚመነጨው ከሕዝቡ ነው ሕዝብ ነው የሚሾማቸው የሚሽራቸው ማለት ነው
- ስለዚህ በአገሪቱ ሕግ ነው በኃይማኖት ሕግ ሳይሆን ከአገሪቱ ሕግ ነው የሚመነጨው ማለት ነው ?
- አደለም በአገሪቱ ሕግ የመንግስት መተዳደሪያ ደንብ ለብቻው ይሄ የኃይማኖልት ተቋም ስለሆነ የመንግስት አስተዳደር አይምለከተውም መንግስት ጣልቃ አይገባም ኃይማኖትም በመንግስት ጣልቃ አይገባም ስለዚህ እራሱ ኃይማኖቱ የምርጫ አፈፃፀም ስርዓት አለው ስለዚህ በአገሪቱ ሕግ ሳይሆን የራሱ ሕግ እና መመሪያ አለው የምርጫን በተመለከተ መጅሊሱ
- ስለዚህ በአገሪቱ ሕግ አይመራም ነው የሚሉት?
- በአገሪቱ ሕግ አይመራም
- የሚቋቋመውስ?
- ቆዩ ይሄ የሙያ ምስክር እየጠየቁ እኮ አደለም አንደኛ ስለመጅሊሱ በሰፊው ተጠይቋል ቅድም ሁለተኛ ደግሞ ሌላ የሕግ ትንተና ይሄ ጥያቄ ይለፉት በሕግ ይገዛል አይገዛም ይሄ የሙያ አስተያየት ነው
- እሺ የያሲን ኑሩ ሲዲ ካሴት ተገቢ ተገቢ አደለም ስተት ነው ያሉት ከየስልጣን ባለቤቶች ፍላጐት ውጪ ነው ስላሉ ነው አደለም?
- እሱም ብቻ ሳይሆን እሱ አንዱ ነው ሌላው ግን ትክክል ያልኩት ምንድን ነው ሙስሊሙን የሚከፋፍፍል ሰው ሙስሊም ለሙስሊም የሚያጋጭ በመሆኑ ነው ትክክለኛ እና የተዋጣለት ትክክለኛ ነገር የያዘ ባለመሆኑ ነው ትክክል አደለም ያልኩት ምክንያቱም ምንድን ነው ለመግለጽ ከተፈለገ ላብራራ እፈልጋለሁ ቅድምም አብራርቻለሁ
- ስለዚህ መጅሊሱን ማስፈቀድ አያስፈልገውም ነበር ማለት ነው?

1678 92

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- መስፈቀድም አለበት
- በምን ሕግ?
- በምን ሕግ ማለትማ በኃይማኖቱ ሕግ ነዋ ለምሳሌ በኃይማኖት ሰበብ ያልሆነ ነገር ቢነሳ
- በቃ
- እሺ በኃይማኖቱ ሕግ መሰረት ያላስፈቀደ ምን ይደረጋል?
- ይሄ ተጠይቋል
- ክቡር ፍ/ቤት አልተጠየቀም ይሄ
- ማስፈቀድ አለበት ተባለ ከዛ ውጪ ምን ይሆናል?
- በኃይማኖታዊ ሕግ ከሆነ ሰንክሽት ኃይማኖቱ
- ይሄ ኮንኩሉዥን ነው ምስክሩ መመለስ የሚችሉት ግን ተጠይቀው ነው ስለዚህ ከዛ ወጥተው ሌላ ጥያቄ ካሎት
- እሺ ትቻለሁ
- እሺ ሃጂ አህመድ እኔ እንዳስተምር ተልኬ
- ቆይ እስቲ ምናልባት ማን ናቸው እሳቸው ዳዊት ነው ምናልባት አሁን ስሜት ውስጥ ገብተው ጥያቄ ከጨረሱ ጨርሻለሁ ነው የሚሉት ጥያቄውን ትቻለሁ የሚለው ነገር ትንሽ እንትኑን የጠበቀ አደለም
- ሼህ አህመድ ቅድም ሲመለክሩ እዳስተምር ተልኬ አላህዋክበር በሚል ተፒራስ ጉባዔው እንዲበተን ተደርጓል ብለዋል ልክ ነኝ አደል?
- አም እንዳተምር ተልኬ ሳይሆን ካስተማርኩ በኋላ ጥያቄ ተጠይቆ ልመልስ ስል አላህዋክበር በማለት ጥያቄው /ግልጽ ያልሆነ/ ስብሰባው ተበትኗል ብያለሁ
- እሺ ያንን ጉባዔ ወይም ስብሰባ የጠራው ማን ነበር?
- የጠራው የክ/ከተማ እስልምና ጉዳይ ኃላፊዎች ናቸው የጠሩን
- የት ነበረ የተጠራው?
- በሽሮሜዳ ኢማሙ አህመድ የሚባል መስኪድ
- ብዙ ሰው ነበር እዛ ውስጥ?
- ደህና ነው የተጠራው ሰው ሞልቷል
- አላህዋክብር የሚለው ተክፒራ በተቃውሞ መልክ የቀረበ ነው?
- አም በተቃውሞ መልክ የቀረበ ነው እንግዲህ

1679 93

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የተቃወሙት እርስዎ የሚያስተምሩትን ትምህርት ነው የተቃወሙት ወይም እርስዎን ነው የተቃወሞት?
- እኔን በምን ይቃወሙኛል ስብሰባሙ ሙስሊመ ማህበረሰብ ኃይማኖቱን በትክክል እንዳይረዳው እንዳይገነዘበው እንደተወናበደ እንዲቀጥል /ግልጽ ያልሆነ/
- ይሄ ተቃውሞ የቀረበው በእርስዎ ላይ ነው ወይስ በማን ላይ ነው ተቃውሞ አላህዋክብር የሚለው ተክፒራ በተቃውሞ የቀረበ ነው ስላሉ ተቃውሞው በማን ላይነው የቀረበው?
- ስብሰባውን ለመበተን የታሰበ ነው
- ኢኽውሎት ሼህ አህመድ ተቃውሞ ነው ስላሉ ተቃውሞው በማን ላይ ነው የቀረበው?
- ተቃውሞ አለ
- ምስክሩ ይሄን ጥያቄ ሁለቴ መልሶታል እኔን ምን የሚቃወሙበት ምክንየት አለ ስብሰባውን ለመበተን የተደረገ አላማ ነው ብሏል አሁን የተከበሩ ጠበቃ ከምስክሩ የሚፈልጉት ምን እንደሆነ ግልጽ አደለም ደጋግመው ነው የሚጠይቁት /የማይሰማ/ ምስክሩ አሬዲ መልስ የሰጡበት ጉዳይ ነው ስለዚህ በዚሁ እንዲታለፍ ጥያቄው
- ማለት መልክቱ ሃራስ እየተደረጉ ነው ወደዛ እየሄደ ነው
- የኔ ጥያቄ ምናልባት አቃቤ ሕግ ተረድተውኝ ከሆነ ተቃውሞ ነው ስላሉ ነው ተቃውሞ አደለም ካለኝ አነሳዋለሁ እሳቸው ተቃውሞ ከሆነ ተቃውሞው በማን ላይ ነው ነው ተቃውሞ አደለም ብጥበጣ ነው ለመረበሽ ነው ከተባለ
- ጥያቄው ድግግሞሽ ነው ምስክራችን ሃራስ እያደረጉ ነው ማለት ያው የተነሳበት አግባብ እንደዛ ነው
- እሺ እኔ ምስክሩን ሃራስ አላረግኩም ወይም እሳቸውን ላስጨንቅ ወይም ልረብሽ ያረግኩት ነገር የለም
- አይ ሃራስ ማረግ አለማረግ የተለየ አካሄድ ነው እሱን ተውትና ፍሬ ነገሩ ላይ መልሱን ሌላ አለ የሚጨምሩት
- አይ ተቃውሞ ነው ወይስ አደለም የሚለው ነገር አልተመለሰም ተቃውሞ ነው ከተባለ በማን ላይ ነው አደለም ካሉ የተቃውሞ አደለም ስብሰባውን ለመረበሽ የተደረገ ነው ካሉ ደግሞ ተቃውሞ አደለም በሚለው ነገር አልፈዋለሁ
- በቃ እሱ ነው ተቃውሞ አደለም
- ቅድም በአወልያ መስኪድ በተደረገ ጉባዔ ላይ ጅሃድ ተብሎ ትምህርት ተሰጥቷል ብለዋል እና አወልያ መቼ ነበረ ይሄ የተደረገው እርስዎ የነበሩበት?
- ከመጋቢት 2004 ጀምሮ ሂደቱ እንዳለ ነው
- አንድ ከዚሁጋ የተያይዞ ያልተነሳ አነድ ጥያቄ ጠይቄ ብቻ ጠይቄ ለመሄድ ነው በዛን እለት ጅሃድ በተባለ ቀን አወልያ-የነበረው ጉባዔ ያለምንም ችግር በሰላም ነው.የተበተነው አደለም?

163 94

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- እኔ ያን ሰምቼ መጣሁ ከዛ ውጭ የማውቀው ነገር የለም
- እኮ እርስዎ እስኪያውቁ ድረስ ምንም ችግር አልነበረም ?
- በሰላም ይበተን አይበተን ታክሲ ይገፍ መጣሁ ሁኔታውን ተከታተልኩ
- እኮ እርስዎ እስኪወጡ ድረስ ምንም ችግር አልነበረም አደል?
- የለም ማለት ነው
- እሺ ምርጫ የመጅሊስ ምርጫ መደረግ ያለበት አደለም አደል ስለቦታው አልተነሳም አሁን የኔ ከቦታው አንፃር ነው ምርጫ በመስኪዳችን የሚለው ጥያቄ አልተመለሰም
- እሺ ወረቀት ሲበተን አይቻለሁ ብለለዋል ጁማ ልሰግድ ገብቼ ለኔ ተሰጥቶኛል ብለዋል ወረቀቱን የሰጦት ማን ነው?
- ልጆች ናቸው ቅድም ገልጨዋለሁ እኮ ሕፃናቶች ልጆች እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች እንደዚህ የዘው ያድሉ ነበር
- እሺ አቡበከር ይሄን ወረቀት ሲሰጥ አላዩም አደለም የዛን አለት?
- አቡበከር እና ሌሎቹ ልከውን ብለው ልጆቹ ጠይቄያቸው ነግረውኛል
- እርስዎ ሲሰጥ አላዩም?
- አዎ አላየሁም
- የተሰጦት ወረቀት ምን የሚል ወረቀት ነው የነበረው?
- ቅድም ግልጽ አርጌዋለሁ ተደጋጋሚ ነው
- ድምፃችን ይሰማ የሚል ወረቀት ስለመሆኑ ልጠይቃቸው ነው እና የወረቀቱን ይዘት ልጠይቃቸው ነው?
- ተዘርዝሯል አራት አምስት ይዘቶች ተዘርዝረዋል
- ወረቀቱ ላይ ትግላችን በሰላማዊ መንገድ ይቀጥላል የሚል አረፍተ ነገር አለው አደል?
- ይጋጫል በሰላማዊ መንገድ ይላል ሁለተኛ ደግሞ
- አደለም አሁን ይኸውሎት ሃጂ ሼህ አህመድ የጠየቅኮት ወረቀቱ ላይ ይሄ ይላል አይልም ነው ወረቀቱ ላይ ትግላችን በሰላማዊ መንገድ ይቀጥላል ይላል አደለም ወረቀቱ?
- ይቺን ብቻ ነጥዬ መልስ መስጠት አልችልም
- ቅድም የጠቀሱት ነገር አለ ከሱጋር ተቀላቅሎ በሰላማዊ መንገድ ትግላችንን እንቀጥላለን የሚል ቃል አለው የለውም ነው ይቺን ብቻ መልሱልኝ ?
- አልፎ አልፎ የሚበተነው ወረቀት ላይ አያለሁ ሌሎቹ በአብዛኞቹ ችግር ያለባቸው ወረቀቶች ናቸው
- እሺ ቀጥሉ

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- የኮሚቴ አባላት በሕዝብ ተመርጠናል ሲሉ ሰምቻለሁ ብለዋል መመረጥ አለመመረጣቸውን ያውቃሉ አርስዎ?
- ቅድም መልሼዋለሁ አላውቅም ብያለሁ
- እሺ ቅድም ሼህ መከተ ሙሄ መልካም ሰው ነበሩ ብለዋል ምን ማለት ነው መልካም ሰው ነበሩ?
- እሱ ተጠይቋል
- ምስክር ቅድም ሲያስረዱ አህባሽ ሳይኖር አህባሽ እንዳለ በማስመሰል ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ለማደናገር ንግግር ሲያደርጉ ነበረ ብለዋል እርስዎ ተደናገርኩ ብለው የላከ ሰው አለ እንዴ ?
- እኔ ለምን እደናገራለሁ
- አይ እርስዎን ሳይሆን እርስዎ ተደናገርኩ ብሎ የመጣ ሰው አለ እንዴ?
- አዎ የተደናገረ ብዙ አለ አውቃለሁ ብሎ
- ስንት ሰው ያውቃሉ?
- በቁጥር ይሄን ያህል ብዬ ማለት አልችልም ግን ብዙ ሰው እንተደናገረ ነው
- አሁን ድረስ አንዋር መስኪድ ሰው እየተሰበሰበ አላህዋክበር እያለ ነው ብለዋል ይሄ ሁሉ ሰው ተደናግሮ ነው ማለት ነው?
- አዎ ይሄ የተደናገረው ሰው ሳይሆን አደናጋሪዎች ናቸው አላህዋክበር የሚሉት እንጂ የተደናገረው ሰው እምነቴ የትኛው ሰው ምን ይመስላል ምንድን ነው ወለድ መብላት አይበቃም ብሏል አዲሱ ቁርአኑ ይሄ ነገር ትክክል ነው ወይ እያለ እያወቀ ግንዛቤ እያገኘ አብዛኛው በአሁኑ ሰዓት ይገኛል ነገር ግን አሁንም ቢሆን
- ያሲን ኑሩ ሰራው ባሉት ሲዲ ላይ ምስሉ ይታያል?
- አዎ
- አለባበሱ እንዴት ነበር ?
- የያሲን ኑሩ ምስላቸው ፎቶዋቸው አለ
- አሃ ፎቶው እንጂ እንቅስቃሴው አይታይም ነበር?
- ፎቶ ማለት ሲንቀሳቀስ ፎቶ ያሳያል እንትኑ
- አሁን ፎቶ ለእርስዎ ምን ማለት ነው?
- እስቲ ቆይ አሁን ግልጽ ይደረግና ፎቶ በካሴት ላይ ያለ ፎቶ ነው ወይስ በቴሌቪዥን በቪዲዮ ተከፍቶ ሲታይ በእንቅስቃሴ ምስል ያለው ?
- በቪዲዮው ላይ ያለው
- በቪዲዮ ላይ ያሲን ኑሩ እንቅስቃሴ ያደርጋል?

1682 96

ETHCRIMINALAWNETWORK.COM
http://ethcriminalawnetwork.com/

- አለ
- ምን አይነት አለባበስ ነው የለበሰው?
- እንደዚህ እንደኔ
- እንደ እርስዎ ነበር የለበሰው?
- /የማይሰማ/
- እንደርስዎ ቀይ እንትን ነበር?
- እኔ አላስታውሰውም
- እሺ ከያሲን ኑሩ የሰራውን ይሄን ሲዲ ከማየቶት በፊት ሌላ ሲዲ ይሰራ እንደነበረ ያውቃሉ?
- አላውቅም
- ያሲን ኑሩ በሕዝቡ ዳኢ ያሲን ኑሩ እየተባለ እንደሚጠራ ያውቃሉ?
- አላውቅም
- ዳኢ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃሉ?
- ዳኢ ማለት አውቃለሁ
- ምን ማለት ነው ዳኢ ማለት?
- አስተማሪ ወደ ጥሩ መስመር ሰወችን ጠሪ ማለት ነው ወይም ደግሞ አስተማሪ ማለት ነው
- እሺ ጨርሻለሁ
- ድጋሚ ጥያቄ አላችሁ አቃቤ ሕግ
- ድጋሚ ጥያቄ የለንም የተከበረው ፍ/ቤት
- እሺ ድጋሚ ጥያቄ አልተነሳም የፍ/ቤቱ ጥያቄ
- ቅድም አወልያ መስኪድ መስታወት ተሰባብሯል ግድያ ሙከራም ተደርጓል ብለው ነበር እና እነኚህን ያደረጉ ሰወች አለያቸውም ነው ያሉት?
- አዎ አወልያ መስኪድ ሳይሆን ይሄ አንዋር መስኪድ ነው
- መስተዋት የሰባበረውም እዛ ነው?
- በጣም መስተዋት ተሰባብራል ፖሊሱ ተመቷል ማን ነው የፈፀመው ነው ጥያቄው ማን ፈፀመው?
- ያው እራሳቸው አላህዋክበር የሚሉ ሰወች እና
- እርስዎ አይተዋል ያኔ እዛ ቆመው?
- አዎ እዛው ነበርኩ አዎ በአይኔ በብረቱ አ ይቻለሁ
- አሁን ተከሳሾች ውስጥ አለ?

1683

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- የለም እኔ አላውቃቸውም ግን ዝም ብሎ ትርምስ እኮ ነው ምን ይታወቃል ዝም ብሎ ጀልሞ መጣ ሰበረ እንገላለን ሲል ፖሊስ ተመስኪዱ አጥር ቅጥር ግቢ ውጪ ፖሊስ መጣ ፖሊስ ሶልሽን ሰጠ ፖሊስም ተመታ ደማ
- እሺ ጨርሰዋል እናመሰግናለን
- አዎ አለን የተከበረው ፍ/ቤት
- አቅርቡት
- በእውነት ለመመስከር
- በአላህ ስም ምያለሁ
- በምስክር ተራ ቁጥር /የማይሰማ/ ደርሰናል በምስክር ተራ ቁጥር ላይ በነኛ ላይ የተጠቀሱት
- እሺ ለምክርነት ነው የመጡት እሺ ለምስክሩ ደህንነት ተብሎ ያው ምስክሩ የራሱን ስም ብቻ ነው የባቱን ሳይጨምር ይግለጽ
- እሺ የራስህ ስምህ ማን ነው?
- ጣሂ
- እሺ ዛሬ ለምስክርነት ነው የመጡት ?
- ለአቶ ሙራድ አልቢር
- የአባታቸውን ስም አያውቁም?
- ድርጅት ነው
- እነኚህ ሁለቱ ላይ ነው ሙራድ እና ?
- አልቢር
- ሙራድ ምንድን ነው ድርጅት ነው እሱም ?
- ሙራድ ሽኩር
- ሙራድ ሽኩር እና አልቢር ላይ ለመመስከር ነው የመጡት ?
- አዎ
- ሙራድን ያውቁታል?
- አዎ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ነው
- በአካል ይለያሉ ሙራድን?
- አዎ
- እሺ ያሳዩን ?
- እሺ ምስክሩ 10ኛ ተከሳሽን አሳይቷል ይቀመጡ

1684 94

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ከሙራድጋር ፀብ ወይ ዝምድና አሎት?
- የተከበረው ፍ/ቤት ድምጽ ስለተቸገርን ጠጋ ብሎ እንዲናገር ምስክሩ
- ፀብ ዝምድና አሎት ከሙራድጋር?
- እኔ የለኝም
- እሺ አቃቤ ሕግ ዋና ጥያቄ
- እሺ አቶ ጣሃ ያው የመጣሁት በምስክርነት ነው ብለሃል እና አሁን ወጥተህ እዛ ባሳየኸው አቶ ሙራድ ላይ እና እንዲሁም በአልበር ዲቨሎፕመንት በእነኚህ ላይ የምታውቀውን የምስክርነት ቃል ለተከበረው ፍ/ቤት በዝርዝር እንድትገልጽ ነው የምጠይቀው እና እስቲ አቶ ሙራድ ምን ሲያደርግ ነው የምታውቀው ሌላው ከዚህ አሁን ከመጣህበት ምስክርነትጋ በተያያዘ መቼ ቀን ምን ሲያደርግ እንደነበረ ይሄን የምታውቀውን በዝርዝር ለተከበረው ፍ/ቤት እንድትገልጽ ነው የምጠይቀው እና መናገር ትችላለህ?
- ሚያዝያ 4 ቀን 2004 ላይ ከቀኑ አስር ሰዓት ላይ ደውሎ ወደ ተ/ኃይማኖኖት አካባቢ ና በማለት እኔም ደግሞ ወደ ተክለሃይማኖት አካባቢ ሄጄ ቆሜ ጠበቅኩት ከዛ ደውዬ መጥቻለሁ አልኩት ወደ አስራአንድ ሰዓት አካባቢ ስለው እሱ ያው በፌስታል ጥቁር ፌስታል ይዞ ይምጣል መኪና ውስጥ ማለት ነው ከዛ እኔም ደግሞ ወዴት ነህ በማለት ጠየቅኩት ስጠይቀው ወደ ቤቴ ወደ ካራ ቆሬ ውሰደኝ አለኝ እሺ ብዬ ወደ ካራ ቆሬ እየወሰድኩት እያለሁ አንድ ሰው ወደ አብነት አካባቢ እጁን ይዘረጋል ሲዘረጋ ጫነው በማለት እሱንም ጭኜ ከዛ ወደ ካራ ቆሬ እየሄድኩ አያለሁ እሱንም ጭኜ ከዛ ወደ ካራ ቆሬ እየሄድኩ እያለሁ ወይ ቴሌ ወይ ደግሞ ሃልዶስ አደባባይ የሚባል አካባቢ ስደርስ የፖሊስ ባልደረቦች ፍተሻ ነበር መኪኖች ላይ ከዛ ተራዬ ብዬ እየተጠጋሁ ሄጄ ልክ ካልዶስ አደባባይ ላይ ስደርስ ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ውረዱ ተባልን እኛም ወረድን ሦስታችንም ወረድን ከዛ ጥቁር ፌስታል መጀመሪያ ይዞ የገባው ፌስታል አጠገቡ ነበር ከዛ እሱን ይዞ ውስጡ መኪና ውስጥ ልክ ፍተሻ ሲጀመር እሱን ፌስታሉን አገኙት ከዛ እሱን ከወሰዱ በኋላ ምንድን ነው በማለት ፖሊሶቹ ሙራድ የማን ነው አለ የማን ነው ሲሉኝ የሙራድ ነው አልኩ ስላቸው ሙራድም ደግሞ የኔ ነው በማለት ለፖሊሶቹ ቃል ሰጣቸው ከዛ ፌስታሉ ሲከፈት ያው እራሳቸው ከፍተው እያዩት ነበረ
- የአንተ ስራ ድርሻ ምን ነበር?
- ሹፌር
- የማን ሹፌር?
- የነሱ የድርጅቱ
- ማን ነው የድርጅቱ ስም?
- አልቢር ዶክመንት ኮፖሬሽን አሶሼሽን

1685

ECLN

http://ethcriminalawnetwork.com/

- ይኔን ድርጅት የሚያስተዳድረው ማን ነው?
- ሙራድ እና ሃጂሱልጣን የሚባሉ ናቸው
- እሺ አንተ ስታሽከረክር የነበረው በወቅቱ ማለት ነው ይሄ መኪናው ምን አይነት መኪና ነው?
- ፒካፕ አይሱዚ ነች
- ፒካፕ አይሱዙ ነው?
- አዎ ኮዱ 353574 ነው
- እሺ ይሄንን ቅድም በዚህ በፍተሻ ወቅት ተገኘ ያልከው በዚህ በጥቁር ፌስታል ማለት ነው ምንድን ነው ያ ወረቀት ይዘቱ የምታስታውሰው እስቲ ስለሱ ንገረን?
- በሃባሽ አንመራም /ግልጽ ያልሆነ/ የሚል ወረቀት ነበር ከዛ ብዙም እኔ አላየሁትም ወደ ፖሊስ ጣቢያ መኪናውን ወደ ዳር አውጣ በማለት መኪናዬን ወደ ዳር አወጣሁ ከዛ ይዞን ወደ ወረዳ 23 ይዞን ሄደ
- ይሄ ወረቀት በግምት ምን ያህል ይሆናል?
- በግምት ብዛት አለው ሁለት መቶ አሁንም እኔ እንጃ ብቻ ሙሉ ነው ፌስታል ሙሉ ነው
- በወቅቱ ሲጠየቅ ሙራድ ያው የኔ ነው የራሱ እንደሆነ አረጋግጦልሃል እና ለምን ነበር የተያዘው ተብሎ ሲጠየቅ የሰጠው መልስ አለ?
- ያኔ እኔ መኪናውን ይዤ ወጣሁ ዳር አውጣው አሁን መንገድ ዘግተሃል ሌላ ደግሞ የሚፈተሽ መኪና አለ በማለት መኪናውን እኔ መኪናዬን ይዤ ሄድኩ እነሱ ቆመው ሲያወጡ ነበር
- መጽሃፍ እነዚህ አህባሽ አይመራንም ድምፃችን ይሰማ የሚሉ ወረቀቶች ነበሩ ብለሃል መጽሃፍ ናቸው ?
- መጽሃፎች ሳይሆኑ
- እሺ ተቃውሞ
- ድምፃችን ይሰማ የሚል ምስክሩ አልተናገሩም ይቺን ብቻ ያስተካከሉልኝ ያሉት ድምፃችንን እንስጥ ነው
- እሺ እኛ የሰማነው ምስክሩን እንጠይቀው እና ያረጋግጥ ችግር የለውም እኛ እሱን ስለሰማን ነው የጠየቅነው
- እሃ የመዘገብነው ድምፃችንን እንስጥ የሚል ነው በዛ አስተካክለው ይቀጥሉ
- እሺ ድምፃችንን እንስጥ ነው የሚለው ምስክር?
- ድምፃችንን እናሰማ
- ጥሩ መጽሃፍ ነው ምንድን ነው?
- ወረቀት ነገር ነች

1886 DD

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/

- ወረቀት ምን አይነት ?
- ልሙጥ ወረቀት
- ጥሩ ቅድም የማን ነው አልቢር ዴቨሎፕመንት በማን ነው የሚተዳደረው ስትባል አንደኛ ሙራድ ሽኩርን አሳይተሃል 2ኛ ሃጂ ሱልጣን ብለሃል ሃጂ ሱልጣን ማን ነው የአባታቸው ስም?
- ዋና ስራ አስኪያጅ ናቸው እሳቸው
- የአባታቸው ስም ማን ነው?
- የአባታቸው ስም እኔ አላውቅም
- በመልክ ታውቃቸዋለህ?
- አዎ አውቃቸዋለሁ
- አንዴ ትለይልናለህ
- እርስዎ ኖት?
- አዎ
- 17ኛ ተከሳሽን ለይተው አሳይተዋል የተከበረው ፍ/ቤት ምንድን ናቸው ሃጂ ሱልጣን አማን ለድርጅቱ?
- ዋና ስራ አስኪያጅ ናቸው
- ጥሩ አንተ ታሽከረክር የነበረው መኪና የማን ነው?
- የድርጅቱ ነው
- የማን ነው ስሙን እየጠራህ ?
- አልቢር ዴቨሎፕመንት
- ምንድን ነው አልቢር ዴቨሎፕመንት?
- ያው የእርዳታ ድርጅት ነው
- የመነግስት ነው?
- የመንግስት ነው አዎ
- ጥሩ የእርዳታ ድርጅት ነው ማለት እንዴት ማንን ነው የሚረዳው?
- የልማት ነው
- የልማት ድርጅት ነው?
- አዎ
- ይሄ የሚወሰዱ አሁን ያልካቸው ወረቀቶች ቅድም እርእሳቸውን የጠቀስካቸው በፌስታል ያሉት ወዴት ነበር የሚሄዱት?

1687 101

ECLN
http://ethcriminalawnetwork.com/